# መርሐ ሕይወት
# አንደኛ መጽሐፍ

አዘጋጅቶ ያቀረበው

ዲ/ ሥራት ገብረማርያም

1991 ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

«ሰው የሚኖረው እግዚአብሔር
በሚናገረው ቃል ሁሉ እንጂ
በእንጀራ ብቻ አይደለም።»
(ዘዳ 8፥3)



ዓሥራት ገብረ ማርያም

«የምሥራቹን ቃል ማብሠር ግዴታዬ ስለሆነ የምመካበት ነገር አይደለም፤ እንዲያውም የምሥራቹን ቃል ሳላበሥር ብቀር ወዮልኝ።» (1ኛ ቆሮ 9፥16)

## የመጽሐፉ ይዘት

ገጽ


መቅድም ........ 15
ኣንደኛ ክፍል ........ 18
ምዕራፍ 1:- ትምህርተ ሃይማኖት ........ 18
የእግዚአብሔር ፈጣሪነት ........ 18
ስለ አፈጣጠር የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች ........ 18
መፍጠር ከምንም ........ 19
የፍጥረትና የጊዜ ግንኙነት ........ 20
ሥነ ፍጥረት ........ 21
መላእክት ........ 22
መልአክ የሚለው ስም ........ 22
የመላእክት ነጻ ፈቃድ ........ 23
ሊቀ መላእክት ........ 24
ሰይጣናት ........ 26
የሰይጣን አወዳደቅ ........ 28
ጥያቄዎች ........ 30
ምዕራፍ 2:- መጽሐፍ ቅዱስ ........ 32
ብሉይ ኪዳን ........ 33
አዳምና ሔዋን ........ 33
ኖኅና የጥፋት ውሃ ........ 36
የባቢሎን ግንብ ........ 38
አብርሃም ........ 39
የአብርሃምና የሎጥ መለያየት ........ 40
አብርሃም ሎጥን ከምርኮ ነጻ ማውጣቱ ........ 40
መልከጼዴቅ አብርሃምን እንደባረከው ........ 41
... ቃል ኪዳን ........ 41


www.ethiopianorthodox.org

አጋርና እስማኤል ........
የመገረዝ ለቃል ኪዳን ምልክትነት ........
አብርሃምና ሣራ እንግዶችን ማስተናገዳቸው ........
የይስሐቅ መወለድ ........
የአጋርና የእስማኤል መ[illegible]ረር ........
እግዚአብሔር አብርሃምን መፈተኑ ........
የይስሐቅና የርብቃ ጋብቻ ........ 4
ሌሎች የአብርሃም ዘሮችና የአብርሃም ሞት ........ 4
ሐዲስ ኪዳን ........ 4
ዮሐንስ መጥምቁ ........ 4
የማትያስ መመረጥ ........ 4
የመንፈስ ቅዱስ መውረድ ........ 4
የአማኞች የኅብረት ኑሮ ........ 50
የሸባው መፈወስ ........ 50
ጴጥሮስና ዮሐንስ በአይሁድ ሸንጎ ፊት መቅረባቸው ........ 52
ከምዕራፉ የሚገኝ ትምህርት ........ 53
ጥያቄዎች ........ 56
ምዕራፍ 3:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ........ 60
የመልአኩ ብሥራት ........ 60
የጌታችን ልደት ........ 61
እረኞችና መላእክት ........ 62
ግዝረት ........ 63
የጌታችን ወደ ቤተ መቅደስ መወሰድ ........ 63
ከምሥራቅ የመጡ ጠቢባን ........ 65
ወደ ግብጽ ሽሽት ........ 66
ሄሮድስ ሕፃናትን ማስፈጀቱ ........ 66
ከግብጽ መመለስ ........ 67


ገጽ


ከግብጽ መመለስ ........ 67
ጌታችን በቤተ መቅደስ ከምሁራን ጋር ........ 67
የጌታችን ጥምቀት ........ 68
የጌታችን መፈተን ........ 70
የማስተማር ሥራውን መጀመሩ ........ 72
የጌታችን ተአምራት ........ 73
ውሃውን ወደ ወይን የመለወጥ ተአምር ........ 73
ብዙ ዓሣዎችን የማስገኘት ተአምር ........ 74
አምስት ሺህ ሰዎችን የመመገብ ተአምር ........ 75
ማዕበሉን ጸጥ የማድረግ ተአምር ........ 76
የጌታችን ምሳሌዎች ........ 76
የዘሪው ምሳሌ ........ 77
በአለት ወይም በአሸዋ ላይ የተሠሩ ቤቶች ........ 77
ጠፍቶ የተገኘው ልጅ ምሳሌ ........ 78
ጥያቄዎች ........ 80
ምዕራፍ 4:- ቤተ ክርስቲያን ........ 83
መግቢያ ........ 83
ቤተ ክርስቲያን ማለት ምን ማለት ነው ........ 85
ምእመናን ........ 85
የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ........ 85
የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ........ 86
ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ........ 86
ማማተብና ትርጉሙ ........ 87
የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን ........ 89
ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ........ 89
ሐዋርያው ቅዱስ እንድርያስ ........ 92
ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ የእልፍዮስ ልጅ ........ 94


www.ethiopianorthodox.org

ገጽ
ሐዋርያው ቅዱስ ታዴዎስ .......... 94
ቅዱስ ቂርቆስና እናቱ ኢየሉጣ .......... 94
የቤተ ክርስቲያን ዜማ .......... 95
ከምዕራፉ የሚገኝ ትምህርት .......... 96
ጥያቄዎች .......... 97
ምዕራፍ 5:- መንፈሳዊነትና ግብረገብነት .......... 100
መንፈሳዊነት .......... 100
ግብረ ገብነት .......... 100
ሁለቱ የሚመሳሰሉበት ሁናቴ .......... 100
ሁለቱ የሚለያዩበት ሁናቴ .......... 101
ጸሎት .......... 102
እግዚአብሔር የማይለወጥና ጸሎት ተቀባይ ነው .......... 102
ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ ስለሆነ ጸሎት ያስፈልገዋል .......... 104
መልስ የሚያገኝና የማያገኝ ጸሎት .......... 105
አባታችን ሆይ .......... 106
አባትንና እናትን ማክበር .......... 108
ለወላጆችቸው ታዛገች የነበሩ ልጆች .......... 108
ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብና አንደበትን መጠበቅ .......... 109
ጥያቄዎች .......... 111
ሁለተኛ ክፍል .......... 113
ምዕራፍ 1– ትምህርተ ሃይማኖት .......... 113
የእግዚአብሔር መንግሥት .......... 113
የእግዚአብሔር ብቸኛ አገዛዝ .......... 113
እግዚአብሔር በፍጥረቱ ላይ ያለው ጌትነት .......... 114
የእስራኤል ሕዝብና የሚኖሩባት ምድር .......... 114
ለወደፊት የሚወረስ የሰማያዊ ርስት ተስፋ .......... 115
እግዚአብሔር በሾማቸው ሰዎች የሚካሄድ መንግሥት .......... 116

.......... ገጽ

የመረብ ምሳሌ .......... 117
የእንክርዳድ ምሳሌ .......... 117
የሰናፍጭ ዘር ምሳሌ .......... 117
የእርሾ ምሳሌ .......... 118
የሰው ልጆች ነጻ ፈቃድ .......... 118
የእግዚአብሔር ፈቃድ ሁሉም እንዲድን ነው .......... 118
የእግዚአብሔር ውሳኔ አለመለወጥና ነጻ ፈቃድ .......... 120
ጊዜ የማይወስነው የእግዚአብሔር ዕውቀትና ነጻ ፈቃድ .......... 121
የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች .......... 122
ጾም .......... 123
የአጽዋማት ሥነ ሥርዓት .......... 124
ቤተ ክርስቲያን የወሰነቻቸው አጽዋማት .......... 124
የጌታችን ጾም .......... 124
የልደት ጾም .......... 125
የሐዋርያት ጾም .......... 125
የፍልሰታ ጾም .......... 126
ጾመ ነነዌ .......... 126
የረቡዕና የዓርብ ቀኖች ጾም .......... 126
የገሃድ ጾም .......... 127
የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች .......... 128
የተከራካሪዎች ተቃውሞና የተሰጡ መልሶች .......... 129
ጥያቄዎች .......... 134
ምዕራፍ ሁለት:- መጽሐፍ ቅዱስ .......... 137
ብሉይ ኪዳን .......... 138
ይስሐቅና ርብቃ .......... 138

www.ethiopianorthodox.org

ገጽ

ዔሳውና ያዕቆብ ........ 138
የያዕቆብ ወደ ካራን ጉዞ ........ 140
ነቢዩ ኤልያስ ........ 140
ሐዲስ ኪዳን ........ 145
ሐናንያና ሰጲራ ........ 145
ወደ ሮሜ ሰዎች የተላከ መልእክት ........ 146
ወደ ገለትያ ሰዎች የተላከ መልእክት ........ 149
ወደ ቲቶ የተላከ መልእክት ........ 150
ወደ ፊልሞና የተላከ መልእክት ........ 150
ከምዕራፉ የሚገኝ ትምህርት ........ 150
ጥያቄዎች ........ 152
ምዕራፍ 3:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ........ 155
የጌታችን ትምህርቶች ........ 155
ጌታችንና ኒቆዲሞስ ........ 155
የሰማርያይቱ ሴት ........ 157
ጌታችን ከአብርሃም በፊት የነበረ መሆኑ ........ 159
የአይሁድ አለማመን ........ 159
የጌታችን ተአምራት ........ 160
የመቶ አለቃው አገልጋይ መፈወስ ........ 160
የስምዖን አማትና የሌሎች መፈወስ ........ 161
በአጋንንት የተያዙ የሁለት ሰዎች መፈወስ ........ 161
የጌታችን ምሳሌዎች ........ 162
የተሸሸገ ሀብት ምሳሌ ........ 162
የዕንቁ ምሳሌ ........ 162
ራሱን እንደ ሕይወት እንጀራ ........ 162
ከምዕራፉ የሚገኝ ትምህርት ........ 163

........ ገጽ

ጥያቄዎች ........ 166
ምዕራፍ 4:- ቤተ ክርስቲያን ........ 168
ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ........ 168
የሕንጻው አሠራር ........ 169
የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ........ 170
ንዋየ ቅድሳት ........ 171
ጻሕል ........ 171
ጽዋዕ ........ 171
ዕርፈ መስቀል ........ 172
መሶበ ወርቅ ........ 172
ማኅፈድ ........ 173
አልባሳት ........ 173
ጥና (ጽና) ........ 173
የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን ጸሎቶች ........ 173
የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን ........ 177
ሐዋርያው ቅዱስ በርተሎሜዎስ ........ 177
ሐዋርያው ቅዱስ ፊልጶስ ........ 178
ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ........ 178
የቤተ ክርስቲያን ዜማ ........ 180
ከምዕራፉ የሚገኝ ትምህርት ........ 182
ጥያቄዎች ........ 184
ምዕራፍ 5:- መንፈሳዊነትና ግብረገብነት ........ 186
ስሕተትን አምኖ ይቅርታ መጠየቅ ........ 186

www.ethiopianorthodox.org

ገጽ

እግዚአብሔርን ማመስገን ........................................ 189
በተቻለ መጠን የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸም ........................ 192
ሌላውን ሰው እንጂ ራስን አለማመስገን ................................ 193
ጥያቄዎች ........................................................ 197
ሦስተኛ ክፍል ..................................................... 198
ምዕራፍ 1:- ትምህርተ ሃይማኖት ...................................... 198
የእግዚአብሔር ፍቅር ................................................ 198
ምሥጢረ ሥጋዌ .................................................... 200
የወልድ ሥጋ መልበስ ................................................ 200
የሥጋ መልበስና የመስቀል ምክንያት (በሰው በኩል) ........................ 201
የሥጋ መልበስና የመስቀል ምክንያት (በእግዚአብሔር በኩል) ....................203
በምሥጢረ ሥጋዌ ላይ የተነሡ መናፍቃን .................................. 205
አቡሊናርዮስ ...................................................... 205
ቢላግዮስ ......................................................... 206
ጥያቄዎች ........................................................ 208
ምዕራፍ 2:- መጽሐፍ ቅዱስ ............................................ 210
ብሉይ ኪዳን ....................................................... 210
የዲና ወንድሞች የበቀል እርምጃ ......................................... 210
ዮሴፍና ወንድሞቹ .................................................. 211
ዮሴፍና የጶጢፋር ሚስት ............................................. 212
የፈርዖን አገልጋዮች ................................................. 212
የፈርዖን ሕልም ..................................................... 213
የዮሴፍ ወንድሞች ወደ ግብጽ መሄድ ...................................... 214
ሶስና ........................................................... 215
ሩት ............................................................ 217

ገጽ

ሐዲስ ኪዳን ....................................................... 219
ስለ ሰባት ዲያቆናት መመረጥ ............................................ 219
እስጢፋኖስ ........................................................ 220
ፊልጶስ .......................................................... 221
ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች የተላከ መልእክት ...................................... 223
የይሁዳ መልእክት .................................................... 227
ከምዕራፉ የሚገኝ ትምህርት ............................................. 228
ጥያቄዎች ........................................................ 230
ምዕራፍ 3:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ2 .................................. 234
የጌታችን ትምህርቶች ................................................. 234
የተራራው ላይ ስብከት ................................................ 234
ማቴዎስን መጥራቱ .................................................... 238
በናዝሬት ተቃውሞ ተነሣበት ............................................. 238
ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ................................................. 239
የጌታችን ተአምራት .................................................. 239
የጌታችንን ልብስ የነካች·ሴት መፈወስ ...................................... 239
የኢያኢሮስ ልጅ ከሞት መነሣት ............................................ 240
የጌታችን ምሳሌዎች .................................................. 241
የደጉና የክፉው አገልጋይ ምሳሌ ........................................... 241
ክፉ አገልጋይ ...................................................... 242
ከምዕራፉ የሚገኝ ትምህርት ............................................. 242
ጥያቄዎች ........................................................ 246
ምዕራፍ 4:- ቤተ ክርስቲያን ............................................ 250
የቤተ ክርስቲያን መሥራች ............................................... 250
ስዕሎችና አይቆኖች .................................................. 252
የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን ............................................... 255

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ገጽ


ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ ........................................ 255
ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ........................................ 256
የቤተ ክርስቲያን ዜማ........................................ 258
ጥያቄዎች ........................................ 260
ምዕራፍ 5:- መንፈሳዊነትና ግብረገብነት2 ........................................ 263
ይቅርታ ማድረግ እንጂ ቂም አለመያዝ........................................ 263
ደግነት ........................................ 265
በጎአድራጊዎችንና አገልጋዮችን ማመስገን ........................................ 267
ለትክክለኛ ኑሮ ምሳሌ መሆን........................................ 268
ጥያቄዎች ........................................ 269
አራተኛ ክፍል........................................ 271
ምዕራፍ 1:- ትምህርተ ሃይማኖት........................................ 271
የእግዚአብሔር አዳኝነት ........................................ 271
ብሉይ ኪዳን........................................ 271
ሐዲስ ኪዳን........................................ 271
አማላጅነት........................................ 278
የአማላጅነት ትርጉም ........................................ 278
ስለ ቅዱሳን አማላጅነት ........................................ 278
የጌታችንና የቅዱሳን አማላጅነት ልዩነት........................................ 278
የቅዱሳን ክብርና ዕውቀት........................................ 280
ቅዱሳን ከሞቱ በኋላ ያላቸው ዕውቀት ........................................ 281
የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች ........................................ 283
ማጠቃለያ ........................................ 285
ጥያቄዎች........................................ 286
ምዕራፍ 2:- መጽሐፍ ቅዱስ........................................ 288
ብሉይ ኪዳን........................................ 288
የሙሴ መወለድና ዕድገት........................................ 288


ገጽ


የሙሴ ሽሽት ........................................ 290
በቍጥቋጦው መካከል የእሳት ነበልባል ........................................ 292
ጦቢት........................................ 292
ነቢዩ ዮናስ........................................ 294
ሐዲስ ኪዳን........................................ 295
የሳውል በክርስቶስ ማመን ........................................ 295
ሐዋርያው ጴጥሮስ በልዳና በኢዮጴ........................................ 296
ሳውል...... ........................................ 297
ሁለተኛው የቆሮንቶስ መልእክት ........................................ 298
ከምዕራፉ የሚገኝ ትምህርት ........................................ 302
ጥያቄዎች........................................ 303
ምዕራፍ 3:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ........................................ 307
የጌታችን ትምህርቶች ........................................ 307
በጸሐፍትና በፈሪሳውያን ላይ የቀረበ ወቀሳ........................................ 307
ስለ ጋብቻ ማስተማሩ ........................................ 309
ስታመነዝር ስለ ተያዘች ሴት ........................................ 309
የሀብታሙ ወጣት ጥያቄ ........................................ 309
የጌታችን ተአምራት ........................................ 310
የከነዓናዊትዋ ሴት ልጅ መፈወስ........................................ 310
በአጋንንት የተያዙ ሁለት ሰዎች መፈወስ........................................ 312
በባሕር ላይ መራመዱ ........................................ 312
የጌታችን ምሳሌዎች........................................ 313
የሠራተኞች አቀጣጠር ምሳሌ ........................................ 313
የሁለት ልጆች ምሳሌ ........................................ 314
የአገልጋዮች ትጋት........................................ 314
ከምዕራፉ የሚገኝ ትምህርት ........................................ 315


www.ethiopianorthodox.org

ጥያቄዎች ........................................ 319
ምዕራፍ 4:- ቤተ ክርስቲያን ........................................ 322
ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ........................................ 322
ምሥጢረ ጥምቀት ........................................ 322
ምሥጢረ ሜሮን ........................................ 323
ምሥጢረ ቍርባን ........................................ 324
ምሥጢረ ክህነት ........................................ 324
ምሥጢረ ንስሐ ........................................ 325
ምሥጢረ ተክሊል ........................................ 326
ምሥጢረ ቀንዲል ........................................ 326
የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን ........................................ 326
ሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ ........................................ 328
ሐዋርያው ቅዱስ ማትያስ ........................................ 329
ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ ........................................ 324
የቤተ ክርስቲያን ዜማ ........................................ 336
ከምዕራፉ የሚገኝ ትምህርት ........................................ 338
ጥያቄዎች ........................................ 342
ምዕራፍ 5:- መንፈሳዊነትና ግብረገብነት ........................................ 342
ንስሓ መግባት ........................................ 342
በእውነት መጽናት ........................................ 345
አክብሮትና ትሕትና ........................................ 347
የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች ........................................ 348
ጥያቄዎች ........................................ 349

## መቅድም

ምእመናን የሃይማኖትን ትምህርት ለማወቅ የሚችሉት አንድም በስብከት መልክ በቃል የሚሰጣቸውን ትምህርት በመስማት ወይም በጽሑፍ የሚቀርብላቸውን የሃይማኖት መጽሐፍ በማንበብና አስፈላጊውንም ጉዳይ የሃይማኖት መምህር ሲያብራራላቸው ነው። በጽሑፍ የሚቀርበው ትምህርት በቃል ብቻ ከሚቀርበው የበለጠ ጥቅም አለው። ይህም የሚሆንበት ምክንያት በአንድ በኩል በቃል በሚቀርበው ትምህርት ውስጥ ብዙ ማብራሪያዎች ላይታወሱ ሊታለፉ የሚችሉ በመሆናቸው በጽሑፍ እንደሚቀርበው ትምህርት የተሟላ ስለማይሆን ነው። በሌላ በኩል በጽሑፍ የሚቀርብ የሃይማኖት ትምህርት የተለያዩ ትምህርቶችን በተለያዩ ወቅቶች እንዲቀርቡ በማመቻቸት ምእመኑ ወይም ተማሪው አስፈላጊዎቹን ትምህርቶች ሁሉ ሳያውቃቸው እንዳይቀር ያደርጋል። ከዚያም በላይ በማስተማሪያ መጽሐፍ የሚያስተምር የሃይማኖት አስተማሪ ደግሞ በቀረበለት ዝግጅት መሠረት ስለሚያስተምርና የመጽሐፉን አቀራረብ ስለሚከተል አስፈላጊ የሆኑትን ትምህርቶች አይረሳቸውም።

ይህ መጽሐፍ በማንኛውም ዕድሜ ክልል ውስጥ ለሚገኙ ምእመናን እንደሚጠቅም ታምኖበት የተዘጋጀ ነው። ከአንደኛ እስከ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል ተከፍሎ ይቅረብ እንጂ በየክፍሉ የተዘጋጀው የትምህርት ደረጃ ምንም ያኽል አይበላለጥም። የአከፋፈሉ ዋና ዓላማ አስፈላጊ ናቸው ተብለው የታመነባቸው ትምህርቶች ሁሉ በተቻለ መጠን ሳይቀርቡ እንዳይቀሩና በአንድ ላይ ሳይሆን ተከፋፍለው እንዲቀርቡ ለማድረግ ነው። በዚህም መሠረት ይህ መጽሐፍ በበለጠ የሚጠቅመው ለሃይማኖት አስተማሪ ነው። አስተማሪው ትምህርቱን በሚያቀርብበት ጊዜ እንደየክፍሉ ቅደም ተከተል ገለጻውን ቀለል አድርጎ በመጀመር ከፍ እያለ ሊቀጥል ይችላል። ዋናው ነገር ትምህርቶቹ በመጽሐፍ ተዘጋጅተው መቅረባቸው ነው።

የመጽሐፉ ዋና ዓላማ፥ ምእመናን ሃይማኖታቸውን ካለማወቃቸው የተነሣ በሃይኖቱ ኅብረት ውስጥ ጸንተው የማይቆሙ ከመሆናቸውም በላይ በቀላሉ የመታለልና የመኰብለል ዕድለቢስነት እንዳያጋጥማቸው፥ ያም ባይሆን ሃይማኖቱንና ሥርዓቱን ከሚያጥላሉና ከሚነቅፉ ሰዎች ጋር ከመተባበር እንዲገቱ ለማድረግ ነው። በዚህም መሠረት ሃይማኖታችን ምን ያኽል በቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች የተደገፈ መሆኑን በዝርዝር በማመልከት ይህንኑ ሁኔታ

www.ethiopianorthodox.org

ምእመናን ተረድተውት ለቤተ ክርስቲያናቸው ኅላፊነት እንዲሰማቸው ለማድረግ ተሞክሮአል።

የቀረቡት ዝርዝር ትምህርቶች የተለያዩ ይሁኑ እንጂ የዐሥራ ሁለቱም መጻሕፍት አከፋፈል አንድ ዐይነት ነው። ሁሉም አምስት አምስት ምዕራፎች አሉአቸው። የየአንዳንዱም አከፋፈል እንደሚከተለው ነው።

ምዕራፍ አንድ:- ትምህርት ሃይማኖት፥

ምዕራፍ ሁለት:- መጽሐፍ ቅዱስ፥

ምዕራፍ ሦስት:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥

ምዕራፍ አራት:- ቤተ ክርስቲያን

ምዕራፍ አምስት:- መንፈሳዊነትና ግብረ ገብነት

በእነዚህ በአምስቱ ምዕራፎች አማካይነት በተቻለ መጠን የሃይማኖት ትምህርቶችን ለማቅረብ ተሞክሮአል። የሃይማኖቱ ትምህርት በእነዚህ በዐሥራ ሁለቱ ክፍሎች በሙሉ ቀርቦአል ለማለት ባይሆን የሃይማኖታችንን አቋምና ከሌሎች ጋር ያለውን ግንኙትና ልዩነት ለማወቅ እንደሚረዳ ሆኖ የተዘጋጀ ነው።

እነዚህ ዐሥራ ሁለት መጻሕፍት በሦስት መጻሕፍት ተጠቃልለው ወጥተዋል። እነርሱም:-

1. ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍል የመጀመሪያው መጽሐፍ
2. ከአምስተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል ሁለተኛ መጽሐፍ፥
3. ከዘጠነኛ እስከ ዐሥራ ሁለተኛ ክፍል ሦስተኛው መጽሐፍ ናቸው።

ማስረጃዎች በሚቀርቡበት ጊዜ አንድም በቀጥታ ቃል በቃል እየተጠቀሱ ወይም አጠቃላይ ሐሳቡ ብቻ ቀርቦአል

በእነዚህ መጻሕፍት ውስጥ ከመቃብያን መጽሐፍ የተጠቀሰው ጥቅስ አንደኛና ሁለተኛ የመቃብያን መጻሕፍት ብቻ ካሉት መጽሐፍ ቅዱስ



የተወሰደ ስለሆነ አሁን ካለው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ጋር ተመሳሳይ አይደለም።

በየምዕራፍ አራቱ በአጭር በአጭሩ የቀረበው የቅዱሳን ታሪክ ቤተ ክርስቲያን የምታከብራቸውን ቅዱሳን ሁሉ ያቀረበ አይደለም። ሁሉም ቢቀርቡ ኖሮ በጣም በበዛ ነበር: ሁሉንም ከመተው ባይሆን ጥቂቶቹን እንኳ ለዐይነት ያኽል ማቅረብ እንደሚሻል ስለታመነበት የቀረበ ስለሆነ ሌሎቹ ሁሉ ባለመቅረባቸው አንባቢዎች ይቅርታ እንዲያደርጉ ይለመናሉ።

እንደሚታወቀው የቅዳሴውንና ሌሎቹን ጸሎቶች የተሟሉ የሚያደርጋቸው ካህኑ፥ ዲያቆኑና ሕዝቡ የየእራሳቸውን ድርሻ በሥነ ሥርዓት ሲወጡት ነው። ብዙዎቹ ምእመናን ግን የራሳቸውን ድርሻ ስለማያውቁት አድማጮች እንጂ ተሳታፊዎች አይደሉም። ይህንኑ ጉዳይ ከግምት ውስጥ በማስገባት የቅዳሴው ተሰጥዎ በየክፍሉ ተከፋፍሎ እንዲዘጋጅ ተደርጓል። የቤተ ክርስቲያናችን ዜማ የተዘጋጀው በግዕዝ ስለሆነና ሕዝቡም የሚጸልየውን ጸሎት ትርጉም እንዲያውቀው አስፈላጊ በመሆኑ ከግዕዙ ቀጥሎ የአማርኛው ትርጉም ተተርጉሞ ይገኛል።

ሕዝብ ሊያውቃቸውና ሊያከብራቸው የሚገባው ልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች ቤተ ክርስቲያን በሚሉት ምዕራፎች ውስጥ ተዘርዝረው ቀርበዋል።

በተረፈ እነዚህን ሦስት መጻሕፍት የተመለከቱ አንባቢዎች በእነዚህ መጻሕፍት ውስጥ መገለጥ የነበረባቸውና የተረሱ ጉዳዮች ቢኖሩ ከአንባብያን በሚቀርበው አስተያየት መሠረት በሚቀጥለው እትም አርሞ ለማውጣት ይቻላል። ይህንንም በሚያደርጉበት ጊዜ የቤተ ክርስቲያኒቱ ምእመናን ማወቅ የሚገባቸውን ትምህርት እንዲሟላ ማድረጋቸው ስለሆነ ለቤተ ክርስቲያናቸው ደኅንነት አስተዋፅኦ እንዳደረጉ ይወቁ።

ዓሥራት ገብረማርያም

www.ethiopianorthodox.org

# አንደኛ ክፍል

## ምዕራፍ 1

## ትምህርተ ሃይማኖት

### የእግዚአብሔር ፈጣሪነት

የሚታየውንና የማይታየውን ፍጥረት ከምንም የፈጠረ እግዚአብሔር ነው። ቁሳውያን ነገሮችም ቀድሞ ያልነበሩና እግዚአብሔር ከምንም ያስገኛቸው ናቸው። ያልነበሩትን ነገሮች እግዚአብሔር ወደ መኖር ጠራቸው፤ ይህም የሆነው እግዚአብሔር በሁሉም ነገር ላይ ሁሉን ቻይ በመሆኑ ነው።

በእግዚአብሔር ዘንድ ምንም ለውጥ የሌለ ሲሆን መፍጠሩ ግን በአንድ በተወሰነ ጊዜ ተከናውኗል። እግዚአብሔር ሁሉን ነገር የፈጠረው በፈቃዱ ነው። በውስጥም ሆነ በውጪ አስገዳጅ ሁኔቴ ኖሮት አይደለም። ፍጥረቱ የግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነትና የጥበቡን ሙላት የሚያመለክት ሲሆን በዚህም እግዚአብሔር ይከበራል፤ ይመሰገናል።

<u>ስለ አፈጣጠር የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች</u>:- ሰማይና ምድር በራሳቸው የተገኙ አይደሉም። የመገኘታቸው ምክንያት እግዚአብሔር ነው። ይህን አባባል የሚያረጋግጡት የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች የሚከተሉት ናቸው።

«በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን ፈጠረ» (ዘፍ. ም.1 ቊ1)።

«እርሱ በተናገረ ጊዜ ዓለም ተፈጠረ፤ በትእዛዙም ሁሉ ነገር ጸንቶ ቆመ» (መዝ.33 ቊ:9)።

«ምድርን በኀይሉ የፈጠረ፥ ዓለሙን በጥበቡ የፈጠረ፥ ሰማያትንም በማስተዋሉ የዘረጋ እርሱ ነው» (ኤርም. 10 ቊ12)።

«...እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ሁሉን የፈጠርሁ፥ ሰማያትን ለብቻዬ የዘረጋሁ፥ ምድርንም ያጸናሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ» (ኢሳ.ም 44 ቊ :24)።



«ቀና ብላችሁ ወደ ሰማይ ተመልከቱ፤ የምታዩአቸውን ከዋክብት የፈጠረ ማነው? እርሱ እንደ ጦር ሠራዊት ይመራቸዋል፤ ስንት እንደሆኑም ቊጥራቸውን ያውቃል፤ እያንዳንዱንም በስሙ ይጠራዋል፤ በኀይሉና በችሎታው ትልቅነት ከእነርሱ አንዱ እንኳ አይጠፋም፤ ... ከቶ አታውቅምን? ከቶስ አልሰማህምን? እግዚአብሔር የዘለዓለም አምላክ ነው፤ ዓለምን ሁሉ የፈጠረ እርሱ ነው» (ኢሳ.ም 40 ቊ 26 እና 28)።

«እግዚአብሔር ሰማይን በቃሉ፥ በሰማይ የሚገኙትን ፍጥረቶች በትእዛዙ ፈጠረ» (መዝ 33 ቊ6)።

<u>አፈጣጠር ከምንም</u>:- ፍጥረት የሚለው ቃል መሠረታዊ ትርጉም:- እግዚአብሔር ምንም መነሻ ከሌለው ሁኔቴ ተነሥቶ ዓለምን መፍጠሩን የሚያመለክት ነው። ዓለምም ውሱን በመሆኑ ውሱንነት ከሌለበት ከእግዚአብሔር ባሕርይ ይለያል። በሌላ አነጋገር ፈጣሪው እግዚአብሔር ዓለምን ፈጠረ። ይህም ቀደም ብሎ ከነበረ ቁሳዊ ነገር ተነሥቶ ሳይሆን ዘለዓለማዊው አምላክ ፍጥረቱን ሁሉ የፈጠረው ምንም ነገር ካልነበረበት ሁኔቴ ተነሥቶ ነው። ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ብሎ ይጀምራል። ይህም አባባል ቁሳዊ ነገሮች ዘለዓለማዊ እንደሆኑ አድርገው የሚናገሩትን ሰዎች አባባል ይቃረናል።

ፈጠረ በሚለው ግሥ ላይ በመጀመሪያ የሚለው ተውሳከ ግሥ ያስፈለገው ለአፈጣጠሩ ሌላ ምንም ቁሳዊ መነሻ የሌለው መሆኑን ያመለክተናል። ከዚያም በላይ ምድር ምንም ያልነበረባት ባዶ ነበረች መባሉ ያፈጣጠሩን ሁኔቴ ያብራራዋል። እግዚአብሔር ሰማይን፥ ምድርን፥ ነፋስን፥ እሳትንና ውሃን የፈጠረው ያለምንም መነሻ ነው። ከእነዚህ ከፈጠራቸው ነገሮች በመነሣት ግን ሌሎችን ነገሮች ፈጥሮአል። ለምሳሌም ያኽል ከመሬት የሚበቅሉ ነሮችን፥ ከምድርና ከውሃ የሚገኙ እንስሳትን ማስተዋል ይቻላል። በዚህም መሠረት ፈጠረ የሚለው ቃል ያለምንም ቅድመ ቁስ ማስገኘትን እንጂ ከቁስ አካል መነሣትን አያመለክትም።

ከምንም ተነሥቶ ስለመፍጠር ሲናገር እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማይንና ምድርን ፈጠረ፥ ምድርም አንዳች ነገር ያልነበረባት ባዶ ነበረች ይላል። (ዘፍ:ም:1ቊ:1–2)፤ ከተፈጠረው ፍጥረት በመነሣት መፍጠርን በተመለከተ ደግሞ ምድር አዝርዕትና አትክልትን ታብቅል፤ ውሃ ነፍስ ያላቸውን ተንቀሳቃሾች ታስገኝ፤ እንደየወገኑ ታላላቅ አንበሪዎችንም ታስገኝ፤ ምድርም

www.ethiopianorthodox.org

ሕያዋን ፍጥረታትን እንደየወገኑ፥ ማለትም እንስሳትንና አራዊትን ታስገኝ ብሏል (ዘፍ:ም1 ቍ: 11፥12፥20፥21፥24)።

በሁለተኛው መቃብያን ም 7ቍ 28 ላይ እንዲህ ይላል:- «ልጄ ሆይ ሰማይንና ምድርን እንዲሁም በእነርሱ ያለውን ሁሉ ተመልከት፤ እግዚአብሔር እነርሱን ያለምንም መነሻ ማለት ከምንም የፈጠራቸው መሆኑን አስተውል የሰው ዘርም በዚሁ ሁኔታ የተፈጠረ ነው።» እንዲሁም በጥበበ ሰሎሞንም 11 ቍ: 18 ላይ «ዓለምን ከምንም ለፈጠረ ለሥልጣንህ ምንም የሚሳነው ነገር የለም» ይላል።

እንግዲህ ዓለምን ከምንም በመፍጠርም ቢሆን ወይም በተፈጠሩት ቁሳዊ ፍጥረትም አማካይነት ቢሆን የእግዚአብሔር ፍጥረት ከምንም እንጂ አንዳንድ ፈላስፎች እንደሚሉት ቀድሞ ከነበረ ቁሳዊ ነገር አለመሆኑን እንረዳለን። ይህንንም የምንልበት ምክንያት እግዚአብሔር ፍጥረትን ከመፍጠሩ በፊት ምንም ቁሳዊ ነገር ያልነበረ በመሆኑ ነው።

በሐዲስ ኪዳን፥ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌሉን መጻፍ ሲጀምር ከሆነው ነገር ማለት ከተፈጠረው ነገር ሁሉ ያለ እርሱ የሆነ ማለት እርሱ ሳይፈጥረው የተገኘ ምንም ነገር የለም ብሏል። ይህም የቁስ አካል ነገሮችን መገኘት ያጠቃልላል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም «የሞቱትን በሚያስነሣውና የሌለውን እንዲኖር በሚያደርገው በአብርሃም አምላክ ስለአመነ ነበር» ብሏል (ሮሜ. ም. 4 ቍ. 17)።

<u>የፍጥረትና የጊዜ ግንኙነት</u> :- ዓለምና ዘመን አይለያዩም። ዘመን ወይም ጊዜ የተጀመረው ከዓለም ጋር ነው። ይህም ማለት ዓለም የጀመረው ዘመን በጀመረበት ጊዜ ነው። ዘመን ከዓለም በፊት ጀመረ ብለን ለማሰብ ያስቸግረናል። ዘለዓለማዊነትና ዘመን ይለያያሉ። ቅዱስ አጎስጢኖስ እንዳለው እንቅስቃሴና ለውጥ ሳይኖር ዘመን ሊኖር አይችልም። ዘለዓለማዊነት ግን ምንም ለውጥ አይገኝበትም። በዚህም መሠረት ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ጊዜ ወይም ዘመን ሊኖር አይችልም። የዘመን መጀመር ከዓለም መጀመር ጋር የተያያዘ በመሆኑ ዘመን የተለየ ከዊን የለውም ማለት ነው።



መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ የሚለውን አምብሩስዮስ ሲተረጕመው እዚህ ላይ በመጀመሪያ የተባለው የዘመን ወይም የጊዜ መጀመሪያ ነው ብሏል።

(ዶክተር ሙሪስ ቴዎድሮስ፥ ትምህርተ መለኮት 3ኛ መጽሐፍ አ.አ.አ 1993 ዓ.ም ገጽ 10–16)

<u>ሥነ ፍጥረት:-</u> እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር እንዴት እንደፈጠረ የሚና ገረው ትምህርት ሥነ ፍጥረት ይባላል። የአፈጣጠሩ ቅደም ተከተል እንደ ሚከተለው ነው:-

1. እግዚአብሔር በመጀመሪያ ቀን ሰማይንና ምድርን ፈጠረ። እንዲሁም በዚሁ ቀን ብርሃንን ፈጠረ። እነዚህ የመጀመሪያው ቀን ፍጥረቶች ናቸው።

2. እግዚአብሔር በሁለተኛው ቀን ጠፈርን ፈጠረ።

3. በሦስተኛው ቀን ባሕርንና የብስን ለየ፤ ምድር አትክልትን፥ እህልንና ፍራፍሬዎችን እንድታበቅል አዘዛትና አበቀለች።

4. በአራተኛው ቀን ፀሐይን፥ ጨረቃንና ከዋክብትን ፈጠረ።

5. በአምስተኛው ቀን ወፎችን፥ ዓሣዎችንና የባሕር ውስጥ አውሬዎችን ፈጠረ።

6. በስድስተኛው ቀን ምድር እንስሳትን፡ በደረታቸው የሚንቀሳቀሱ ፍጥረቶችን፥ አራዊትን ታስገኝ ብሎ አዘዘ፤ እንዲሁም ሆነ። በዚሁ በስድ ስተኛው ቀን ሰውን ፈጠረ።

እግዚአብሔር ሰዎችን ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው። እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው ከዐፈር ነው። በአፍንጫው ሕይወትን የሚሰጥ እስትንፋስ እፍ አለበት። እግዚአብሔር ሰውን በምድር በፈጠረው ፍጥረት ሁሉ ላይ የበላይ አድርጎ ሾመው።

እግዚአብሔር ከሁሉም በላይ ስለሆነ በሰማይ ይኖራል እንላለን። እርሱ ግን በሁሉም ቦታ አለ እንጂ በሰማይ ብቻ የሚኖር አይደለም።

www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር ሊታይ አይቻልም። እግዚአብሔርን የምናውቀው በመጽሐፍ ቅዱስ ነው። ይህም ማለት ስለ እግዚአብሔር የሚነግረን መጽሐፍ ቅዱስ ነው ማለት ነው።

## መላእክት

መልአክ የሚለው ቃል የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈጸም ረገድ የተሰጣቸውን የሥራ ድርሻ ጠባይ የሚያመለክት ነው። መልአክም የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነው። መላእክት በዓይን የማይታዩ መንፈሳውያን የእግዚአ ብሔር ፍጥረቶች ናቸው። መላእክት የተፈጠሩት ሰው ከመፈጠሩ በፊት፥ ይህ ዓለም ከመፈጠሩ በፊትና ከከዋክብት በፊት ነው። ይህም ለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስና ከቀድሞ ጀምሮ በቤተ ክርስቲያን ሲሠራበት የኖረው ትውፊት ማስረጃዎች ናቸው። መላእክት እንደ ሰው ልጆች በመዋለድ የሚበዙ አይደሉም። ከሰዎች የበለጠ ዐዋቂነት አላቸው። ነጻ ፈቃድ አላቸው። በነጻ ፈቃዳቸውም ከተፈጠሩ ጀምረው ያላቸውን ቅድስና ሊያቆዩት ወይም ሊያጡት ይችላሉ። ቅድስናውንም ያገኙት ባረፈባቸው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ አማካይነት ነው። ሆኖም እንቅስቃሴአቸው ውሱን ነው። ለምሳሌ ጌታችን የሰውን ሥጋ ከመልበሱ በፊት የእግዚአብሔርን የማዳን ዕቅድ አያውቁም ነበር።

የመላእክት ቍጥር በጣም ብዙ ነው። መላእክትም በነገድ ይከፋፈላሉ። በነገዱ ብዛት ረገድ በሁሉም ዘንድ አጠቃላይ ስምምነት ያለ አይደለም። የነገዱ አከፋፈል በከፍተኛና በዝቅተኛ ደረጃ የሚመደብ ነው። የመላእክት ዋናው ሥራቸው እግዚአብሔርን ማመስገን ነው። የእግዚአብሔርን ዕቅድ በሥራ ላይ ለማዋል ወደ ሰው ልጆች መላክ ደግሞ ሌላው ሥራቸው ነው። እያንዳንዱ ሰው የራሱ መልአክ ማለት ጠባቂ መልአክ አለው (ማቴ. 18፥10 የሐዋ. ሥራ.12፥14–15)።

እንዲሁም ሕዝብን፥ አብያተ ክርስቲያንን፥ ከተሞችን ይጠብቃሉ።

## መልአክ የሚለው ስም

መልአክ ማለት አንዳች መልእክትን የሚላክ ማለት ነው። እነዚህም ሰማያዊ ኀይሎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለሰዎች ለመግለጥ ወይም ለሰው የመዳንን መንገድ ለማመቻቸት ከእግዚአብሔር ወደ ሰው ልጆች ይላካሉ። በዚህም መሠረት ስማቸው ጠባያቸውንና ማንነታቸውን የሚያመለክት ብቻ



ሳይሆን ለሰዎች የሚያከናውኑትን ተግባር ጭምር የሚያመለክት ነው። እነርሱም ፈቃዱን ለማስታወቅ ከእግዚአብሔር የተወከሉ ናቸው።

ከእግዚአብሔር የተላኩ እንደመሆናቸው ይህ መልእክተኛ የሚለው ስም ለነቢያትም መሰጠቱ የሚያስገርመን አይሆንም። ጳጳሳትና ካህናት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስለሚገልጹ እነርሱም ይጠሩበታል። ዮሐንስ መጥምቁም በዚህ ስም ተጠርቶበታል (ሚል 2፥7፥3፥1፥ማቴ. 11፥10፥ማር 1፥2)።

ነገር ግን ይህ ስም በተለይ የሚጠሩበት በሰማያዊው ዓለም የሚኖሩትና የማይታዩት መንፈሳውያን ፍጥረቶች ናቸው። ይኸውም ጉዳይ ከመጽሐፍ ቅዱስ ከመጀመሪያዎቹ ገጾች ጀምሮ በብዛት የተመሰከረለት ነው። ለምሳሌ በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ላይ በገነት በስተምሥራቅ በኩል የሕይወት ዛፍን እንዲጠብቁ እግዚአብሔር ኪሩቤልን ማስቀመጡ ተነግሮአል፤ የጌታ መልአክ አጋርን እንዳነጋገራት ተገልጦአል፤ የእግዚአብሔር መልእክ ሎጥን አድኖታል፤ አብርሃም በልጁ በይስሐቅ ላይ እጁን እንዳይዘረጋ ጠርቶታል፤ ያዕቆብ በሕልሙ የእግዚአብሔር መላእክት ከምድር ወደ ሰማይ በተዘረጋ መሰላል ሲወጡና ሲወርዱ አይቶአል፤ ከዚህም ሌላ መላእክት በየጊዜው ለሰዎች ተገልጠዋል (ዘፍ ም. 3ቍ24፤ ም. 16፥ ቍ7፥11፥ም. 19 ቍ 1.ም. 28ቍ: 12፥ ዘካ ም 1ቍ8፥ም.6ቍ:4)።

አንዳንድ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ መላእክትን በየስማቸው የጠቀሰበት ጊዜ አለ።

ለምሳሌ <u>ሩፋኤል</u> (ጦቢ. ም: 12ቍ.15 )፥ <u>ሚካኤል</u> (ዳን: ም10ቍ. 13፥21፥ም: 12ቍ :1፥ይሁ:ቍ:9፥ ራእ:ም:12ቍ7)፥ <u>ገብርኤል</u> (ዳን: ም: 8 ቍ:16፥ም : 9ቍ: 21፥ ሉቃ:ም: 1ቍ:19፥26) ይመለከቷል።

<u>መላእክት የመምረጥ ነጻነት አላቸው</u>:- መላእክት መንፈሳውያን ፍጥረቶች ሲሆኑ የመምረጥም ነጻነት አላቸው። ስለዚህም በቅድስናቸው ሊቀጥሉ ይችላሉ፥ ወይም ወደ ክፉ መንገድ ማምራት፥ መለወጥ ይችላሉ። መላእክትም በቅድስናቸው የሚቀጥሉት ነጻነታቸውን በበጎ ተግባር ሲያውሉትና ቅድስናቸውን ሲያዳብሩት ነው። መላእክት ቅድስናቸውን ሊያዳብሩት ወይም ወደክፉ ሊያመሩ የሚችሉ ለመሆናቸው የሚቀርበው ማስረጃ የተወሰኑ የመላእክት ነገድ በኃጢአት የወደቁ መሆናቸው ነው። ሌሎቹ ነገዶች ግን አልወደቁም። እነዚህ ያልወደቁት ወገኖች ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በፍጹም

www.ethiopianorthodox.org

ለኃጢአት የማይሸነፉ ሆነዋል። ይህም የሆነው ለቅድስናና ለበጎነት ፍጹም የሆነ ዕውቀት ስላላቸው፣ በወደቁት መላእክት ላይ የደረሰውን መከራ በማየት በቂ ልምድ ያገኙ በመሆናቸው ነው። (ሚካኤል ሚና:- ትምህርተ መለኮት ሁለተኛ መጽሐፍ ገጽ 104 – 105 እንዲሁም መቅድመ ወንጌል)

<u>ሊቀ መላእክት</u>:- ከመጽሐፍ ቅዱስና ከቤተ ክርስቲያን ትውፊት በተረ ከብነው ትምህርት መሠረት ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት ማለት የመላእክት አለቃ ነው ብለን እናምናለን። ይሁን እንጂ አንዳንድ ወገኖች ሚካኤል የተባለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ አድርገው ድፍረት የተሞላበት አስተሳሰብ ያቀርባሉ።

እንደ እነርሱ አባባል ሚካኤል የሚለው ቃል ትርጉም «እግዚአብሔርን መሳይ» ወይም «እንደ እግዚአብሔር ያለ» ማለት በመሆኑ የእግዚአብሔርን ክብር የሚጠብቅና የእግዚአብሔርን ጠላቶች የሚያጠፋው ሚካኤል ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ይላሉ። በዚህም መሠረት በዮሐንስ ወንጌል ም.14 ቍ 30 ላይ የዚህ ዓለም ገዢ ብሎ ከሰየመው ከሰይጣን ጋር ተዋግቶ ድል የሚያደርገው ሚካኤል የተባለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ይላሉ።

እነርሱ እንደሚሉት ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር ሰውን በፈጠረ ጊዜ በአምሳያው ስለፈጠረው ሰውም እግዚአብሔር ነው በተባለ ነበር፥ ወይም ከፈጣሪው ከኢየሱስ ክርስቶስ አያንስም በተባለ ነበር። ይህ ግን አይደለም። ሰውም ሰው ነው፤ መልአክም መልአክ ነው፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የሁሉ ፈጣሪ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ በማንኛውም ቦታ ሚካኤል እንደ መልአክ እንጂ እንደ የእግዚአብሔር ልጅ ወይም የእግዚአብሔር ቃል ሆኖ አልቀረበም። ሰይጣንም ቢሆን የዚህ ዓለም ገዢ የተባለው የዚህን ዓለም ሕዝብ አሳስቶ ከእግዚአብሔር መንገድ ለማስወጣት ስለተሰማራ ነው እንጂ በአም ላካቸው ፈቃድ የኖሩ ብዙዎች የዚህ ዓለም ሰዎች ሰይጣንን ይዞ ከሚያሰቃ ያቸው ሰዎች ላይ በእግዚአብሔር ኀይል ሲያላቅቁት እናያለን።

ቅዱስ ሚካኤል ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ብለው የሚያቀርቡት ሌላው ጥቅስ ደግሞ በራእይ ዮሐንስ ም.12 ከቍጥር 7 እስከ 12 እና በምዕራፍ 12 ከቍጥር 11 እስከ 16 ያሉትን አባባሎች በማጣመር ነው። በመጀመሪያው ጥቅስ የተገለጠው ቅዱስ ሚካኤል ከመላእክቱ ጋር ሆኖ ከዘንዶውና ከመላእክቱ ጋር ተዋግቶ ማሸነፉ ነው። በሁለተኛው ጥቅስ ላይ ደግሞ ሐዋርያው ዮሐንስ ሰማይ ተከፍቶ በነጭ ፈረስ ላይ ተቀምጦ ያየው ታማኝ እውነተኛ የተባለው ትርኢት



ነው። እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ይባላል፤ በልብሱና በጭኑም ላይ የነገ ሥታት ንጉሥ፥ የጌቶች ጌታ የሚል ጽሑፍ ያለበት ከመሆኑም በላይ የሰማይ ሠራዊት ተከትለውታል ተብሎአል።

አሁን እንግዲህ በእነዚህ በሁለቱ ቦታዎች የተጠቀሱትን ጥቅሶች የተመ ለከትን እንደሆነ ምንም ግንኙት እንደሌላቸው ልንረዳ እንችላለን። ቅዱስ ሚካኤልም መቼም ቢሆን የእግዚአብሔር ቃልና የነገሥታት ንጉሥ ተብሎ አያውቅም። ሚካኤል መልአክ ነው፤ ሰይጣንም በኃጢአት ከመውደቁ በቀር መልአክ ነው። ስለዚህም ነው ቅዱሳንና ርኩሳን መናፍስት ተብለው የሚ ጠሩት። ሁለቱም የእግዚአብሔር ፍጥረቶች በመሆናቸው ጦርነት ገጠሙ ተባለ። የእግዚአብሔር ቃል ግን ፈጣሪ አምላክ በመሆኑ ፍጡሩን እርሱ በፈ ቀደው መንገድ ይቀጣዋል እንጂ ከፍጡር ጋር በእኩያነት ደረጃ ጦርነት አይ ገጥምም።

ስለዚህ ሚካኤል የመላእክት አለቃ ስም ነው እንጂ የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ ስም አይደለም።

ሌላው እነዚያ ወገኖች የሚያቀርቡት አባባል ደግሞ በአንደኛ ተሰሎንቄ ም.4 ቍ:6 ላይ «የትእዛዝ ድምፅ፥ የመላእክት አለቃ ድምፅ፥ የእግዚአብሔር መለከትም ይሰማል፤ ጌታ ራሱም ከሰማይ ይወርዳል «የሚለውን ጥቅስ በመልእክተ ይሁዳ ቍጥር 9 ላይ «የመላእክት አለቃ ሚካኤል» ከሚለው ጋር አያይዘው ይህ የመላእክት አለቃ የተባለው ሚካኤል ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ይላሉ። ይህ አባባል ግን አንድም መጻሕፍትን በትክክል ካለመረዳት የመነጨ ነው፤ ወይም አባባሉ ለእነርሱ በሚያመቻቸው መንገድ ለመተርጐም ስለተ ፈለገ ነው።

በማቴዎስ ወንጌል ም.24ቍ 30–31 የተመለከትን እንደሆነ ጌታችን በታላቅ ክብር በደመና ላይ ሆኖ ሲመጣ በጌታችን ተልከው የመለከቱን ድምፅ የሚያሰሙት መላእክት ናቸው እንጂ ጌታችን ራሱ አለመሆኑን እንረዳለን። አብዛኛውን ጊዜ አድራጊና አስደራጊ በአንድ ዐይነት ግሥ ይነገራሉ። ለምሳሌ ጌታችን ኢየሱስ ያጠምቅ ነበር ሲባል ደቀ መዛሙርቱ እንጂ እርሱ አላጠ መቀም፤ ንጉሥ ሰሎሞን ቤተ መቅደስን ሠራ ሲባል በሠራተኞች አሠራው እንጂ የሠራው እርሱ ራሱ አይለም። በዚሁም ዐይነት የእግዚአብሔር መለከት ሲባል በጌታችን ትእዛዝ መላእክት የሚያሰሙት መለከት ለማለት ነው።

www.ethiopianorthodox.org

መጽሐፍ ቅዱስም በየጊዜው የቅዱስ ሚካኤልን ስም ባነሣበት ጊዜ ሁሉ እንደ መልአክነቱ ወይም እንደ ሊቀ መላእክትነቱ ነው እንጂ እንደ የእግዚአብሔር ልጅ ወይም እንደ የእግዚአብሔር ቃል አይደለም።

ለዚህም የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመልከት:-

«በፋርስ አገር ብቻኛ መሆኔን አይቶ ከመላእክት አለቆች አንዱ የሆነው ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ» (ዳን:ም:10 ቍ:13)።

«ሕዝብህን የሚጠብቀው ታላቁ መልአክ ሚካኤል በዚያን ጊዜ ይገለጣል» (ዳን 12÷1)።

«የመላእክት አለቃ ሚካኤል እንኳ ስለሙሴ አስከሬን ከዲያብሎስ ጋር በብርቱ በተከራከረ ጊዜ ‹እግዚአብሔር ይገሥጽህ› አለው እንጂ የስድብ ቃል አልተናገረም» (ይሁ 9)።

«በሰማይ ጦርነት ተነሣ፤ ሚካኤልና የእርሱ መላእክት ከዘንዶውና ከመላእክቱ ጋር ተዋጉ» (ራእ 12÷7)።

## ሰይጣናት

ከቅዱሳን መላእክት ሌላ ርኩሳን መናፍስትም አሉ። ይህን አባባል መጽሐፍ ቅዱስ ከመጀመሪያዎቹ ገጾቹ ጀምሮ ይመሰክርለታል። የቤተ ክርስቲያን ትውፊትም ይህንኑ ያረጋግጣል። በኦሪት ዘፍጥረት በሰው አወዳደቅ ታሪክ ውስጥ ሔዋን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንድታፈርስ እባብ ያግባባት መሆኑ ተገልጦአል። ያም እባብ ሰይጣን መሆኑ በሐዲስ ኪዳን ተነግሮአል። በራእየ ዮሐንስ ምዕራፍ 12 ቍ. 9 ላይ «ታላቁም ዘንዶ ወደ ታች ተጣለ፤ እርሱ ሰዎችን ሁሉ የሚያስተው ዲያብሎስ ወይም ሰይጣን ተብሎ የሚጠራው የቀድሞው እባብ ነው» ተብሎአል። እንዲሁም በብሉይ ኪዳን ስለ ዲያብሎስ በግልጽ ተገልጾ ይገኛል። በተለየም በመጽሐፈ ኢዮብ ዲያብሎስ እንዴት አድርጎ ጠንካራውን ሰው ለችግር እንደዳረገው እናነባለን። እግዚአብሔር ይመስገንና ኢዮብ ቀድሞ ወደነበረበት ሁናቴ በእግዚአብሔር ፈቃድ ተመለሰ እንጂ የሰይጣንስ አያያዝ በዚያው ለማስቀረት ነበር። የመጽሐፈ ኢዮብም አስደሳቹ ጉዳይ እዚህ ላይ ነው። መጽሐፍ ቅዱስም ሆነ ቅዱሳን የቤተ ክርስቲያን አባቶች ስለ ሰይጣን ክፉ ተግባር ዘርዝረው አስረድተዋል።



የሰይጣንን አፈጣጠር በተመለከተ የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት መሠረት በማድረግ ርኩሳን መናፍስት የተፈጠሩት እንደ ቅዱሳን መላእክት መሆኑን በማመን የቤተ ክርስቲያን አባቶች ሁሉ ይስማሙበታል። ይሁን እንጂ ሰይጣናት የወደቁት ራሳቸውን ከእግዚአብሔር ዙፋን በላይ ለማድረግ ስለሞከሩ ነው። ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር በመልኩ በፈጠረው ሰው ላይ በመቅናት በኃጢአት እንዲወድቅ አድርገውታል። ሰይጣን ሰውን አሳስቶ በኃጢአት እንዲወድቅ ባደረገው ጊዜ እርሱ ራሱ አስቀድሞ ወድቆ ነበር። እንደ ርኩስ መንፈስነቱም ሰውን ወደ ኃጢአት ለመጣል ተነሣሣ። ነገር ግን መላእክት በሥጋዊ ፍትወት ወደቁ የሚለው አስተሳሰብ ልክ አይደለም። የዚህም አስተሳሰብ መነሻ በኦሪት ዘፍጥረት ም.6ቍ 2 ላይ:- በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር ልጆች እነዚህን የሰውን ሴቶች ልጆች ውበት ተመለከቱ፤ ከመካከላቸውም የሚወድዱአቸውን እየመረጡ ወሰዱ» የሚለው ጥቅስ ነው። እዚህ ላይ የእግዚአብሔር ልጆች የተባሉት የአዳም ሦስተኛ ልጅ የሴት ልጆች ሲሆኑ የሰው ልጆች የተባሉት ደግሞ በነፍሰ ገዳይነቱ የተወገዘው የቃየል ልጆች መሆናቸውን ብዙዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ይሰማሙበታል። በሌላ በኩል ደግሞ ቅዱሳን መላእክትም የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉ። (ማቴ:ም: 22 ቍ: 29 - 30)።

ቅዱሳን መላእክት እንጂ ርኩሳን መናፍስት ወይም ሰይጣናት የእግዚአብሔር ልጆች እንደማይባሉ ለማረጋገጥ መጽሐፈ ኢዮብ ምዕራፍ 1 ቁጥር 7 እንመልከት:- «አንድ ቀን የአምላክ ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም መጡ፤ ሰይጣንም ደግሞ በመካከላቸው መጣ» (ኢዮ.ም.1ቍ.6)።

የሰይጣናት ወይም የርኩሳን መናፍስት የተፈጥሮ ጠባይ ግን በመጀመሪያ ከተፈጠሩበት ጠባይ ጋር ይስማማል። እነርሱም እንደ ቅዱሳን መላእክት ሁሉ የሚዳሰስ አካል ያላቸው አይደሉም። ለሞት የሚዳረጉ አይደሉም። የተሰጣቸውን የፈቃድ ነጻነትም በተገቢው መንገድ አልተጠቀሙበትም። ቅድስናቸውን አጡ። የክፋትም ምንጭ ሆኑ። የእግዚአብሔርን ፍጥረት ሁሉ በተለየም እግዚአብሔር በመልኩና በምሳሌነቱ የፈጠረውን ሰውን ጠሉ። የእግዚአብሔርን ሥራ ሁሉ፥ በተለየም የሰውን ልጆች የማዳን ዕቅዱን ይቃወማሉ። እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ደኅንነት ፈተናን የሚያመጣባቸው ሲሆን ነገር ግን ከአቅማቸው በላይ ፈተና እንዲመጣባቸው አይፈቅድም። የእግዚብሔር ጥበብ የሰይጣንን እንቅስቃሴ በተወሰነ ድንበር ላይ ይገታዋል።

www.ethiopianorthodox.org

በእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነትና ጸጋ ሰዎች የሰይጣንን ፈተና ድል ነሥተው ለዘለዓለማዊው አክሊል ይበቃሉ።

## <u>የሰይጣን አወዳደቅ</u>

ያለጥርጥር ሰይጣናት የተፈጠሩት በክፉ ጠባይ አልነበረም። ክፉትም የባሕርያቸው አልነበረም። ሰይጣናት ከቅዱሳን መላእክት ጋር የተፈጠሩ ደጎች ነበሩ። ነገር ግን ባላቸው የመምረጥና የፈቃድ ነጻነት የክፋትን መንገድ በመምረጥ ደግነትን ትተው በክፉው መንገድ ጸኑ። እንዲሁም እግዚአብሔርን መፍራትንና ለእግዚአብሔር መገዛትን እምቢ አሉ። ከሰማይም ወደቁ። ሰይጣናትም አሁን ባሉበት ሁናቴ የተፈጠሩ ሳይሆን ራሳቸውን ሰይጣናት አደረጉ። እግዚአብሔር ክፉ ነገርን አይፈጥርም።

አንዳንድ አባቶች ሰይጣን የወደቀው በትዕቢት ምክንያት መሆኑን ያረጋገጡት በሚከተሉት የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች መሠረት ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለደቀ መዝሙሩ ለጢሞቴዎስ በጻፈለት መልእክት «በትዕቢት ተነፍቶ ዲያብሎስ እንደተፈረደበት እንዳይፈረድበት አዲስ ክርስቲያን ኤጲስ ቆጶስ አይሁን» ብሏል (1ኛ:ጢሞ.ም.3ቍ.6)።

ዲያብሎስ አዳምንና ሔዋንን ለማሳሳት የተጠቀመበት ዘዴ በእነርሱ ዘንድ ትዕቢትና ጥርጣሬ እንዲኖር በማድረግ ነው)። ይህንንም ያደረገው:- «በፍጹም አትሞቱም፤ እግዚአብሔር ግን ይህን ያዘዛችሁ ከዚያ ዛፍ ፍሬ በበላችሁ ጊዜ ክፉና ደግን በማወቅ እንደ እግዚአብሔር እንደምትሆኑ ስለሚያውቅ ነው» በማለት ነው።

በትንቢት ኢሳይያስ ምን እንደተባለ እንመልከት:-

«አንተ የንጋት አጥቢያ ኮከብ ሆይ፥ እንዴት ከሰማይ ወደቅህ? ሕዝቦችን ታዋርድ የነበርህ አንተ ወደ መሬት ተጥለሃል፤ አንተ እንዲህ ብለህ አስበህ ነበር:- ‹ወደ ሰማይ ወጥቼ ከታላላቅ፥ ከዋክብት በላይ ዙፋኔን እዘረጋለሁ፤ በስተሰሜን ዳርቻ አማልክት በሚሰበሰቡበት ቦታ በተራራ ላይ እቀመጣለሁ፤ ከዳመናዎችም በላይ ወጥቼ በልዑል አምላክ እመሰላለሁ› ብለህ አስበህ ነበር» (ኢሳ:ም: 14ቍ:12–14)።



በትንቢተ ሕዝቅኤል ስለ ጢሮስ ንጉሥ የተነገረውና በዋናነት ስለ ሰይጣን አወዳደቅ የሚያመለክተው እንደሚከተለው ነው:-

«እግዚአብሔር እንዲህ ሲል እንደገና ተናገረኝ:- «የሰው ልጅ ሆይ፥ የጢሮስ ንጉሥ ስለሚገጥመው መጥፎ ዕድል ሙሾ አውጣ፤ እኔ ጌታ እግዚአብሔር የምለውንም እንዲህ ብለህ ንገረው:- ‹በጥበብ የተሞላህና እጅግ መልከ ቀና በመሆንህ የፍጹምነት ምሳሌ ነበርህ። የእግዚአብሔር የአትክልት ቦታ በሆነችው በዔደን ውስጥ ትኖር ነበር፤ ሰርድዮን፥ ዐልማዝ፥ ቢረሌ፥ መረግድ፥ ኢያስጲድ፥ሰንፔርና፥ በሉር ተብለው በሚጠሩ የከበሩ ድንጋዮች ያጌጠ የወርቅ ልብስ ትለብስ ነበር፤ ከተፈጠርህበት ጊዜ አንሥቶ ይህ ሁሉ ነበረህ። አንተን እንደ ጠባቂ ኪሩብ አድርጌ በመሾም በዚያ መደብሁህ፤ በተቀደሰው ተራራዬ ላይ ትኖር ነበር፤ እጅግ በሚያብረቀርቁ የከበሩ ድንጋዮች መካከል ትመላለስ ነበር። ከተፈጠርህበት ጊዜ አንሥቶ ክፋት ማደ እስከጀመርህበት ጊዜ ድረስ አካሄድህ ፍጹም ነበር፤ በመግዛትና በመሸጥ ተግባር ትጣደፍ ነበር፤ ይህም ሁሉ ወደ ግፍ ሥራና ወደ ኃጢአት መራህ፤ በዚህም ምክንያት የተቀደሰውን ተራራዬን ለቅቀህ እንድትወጣ አስገደድሁህ፤ ከነዚያ ከሚያብረቀርቁ የከበሩ ድንጋዮች መካከል እያባረርሁ አስወጣሁህ፤ መልከቀና በመሆንህ እጅግ ታብየህ ነበር፤ ክብር በመፈለግህም ጥበብህን አቃለልህ፥ ከዚህም የተነሣ አምዘግዝጌ ወደ መሬት ጣልሁህ፤ ለሌሎች ነገሥታትም የመቀጣጫ ምልክት አደረግሁህ፤ በመግዛትና በመሸጥ ከፈጸምከው በደል የተነሣ የአምልኮ ስፍራዎችህ ሁሉ ረከሱ፤ ስለዚህ በከተማይቱ የሰደድ እሳት እንዲነሣ አድርጌ በሙሉ አቃጠልኋት፤ አሁን ወደ አንተ የሚመለከቱ ሁሉ ዐመድ ብቻ መሆንህን ያያሉ፤ እነሆ ጠፋህ፤ ለዘለዓለምም አትገኝም፤ ያውቁህ የነበሩ አገሮች ሁሉ ተሸብረዋል፤ በአንተ ላይ የደረሰው መጥፎ ዕድል እንዳይገጥማቸውም ፈርተዋል» (ሕዝ:ም:28ቍ: 11–19)።

ይህን ንዑስ ክፍል ለመጠቃለል:-

ሀ. ሰይጣን ከነተከታዮቹ እግዚአብሔርን አክብሮ በማምለክና በማመስገን ፈንታ ራሱ ከአምላክ እኩል ለመሆን ስለታበየ፥

ለ. እግዚአብሔር ሰውን ስለወደደውና በመልኩና በምሳሌው ስለፈጠረው ሰይጣን ተመቅኝቶ ሰውን ኃጢአት በማሠራትና ሞት እንዲፈረድት በማድረግ ተጨማሪ ኃጢአትን በመሥራቱ፥

www.ethiopianorthodox.org

ሐ. ስለዚህ ሰይጣን ተዋርዶ የዘለዓለም ሰቃይ ተፈርዶበታል። ንስሐ ገብቶ ወደ ቀድሞ ሁናቴው የመመለስ ምንም ዕድል የለውም።



ሊቀ መላእክት ሚካኤልና የሰይጣን አወዳደቅ (ኢሳ:ም :14 ቍ 12–14)

## ጥያቄዎች

1. የሚታየውንና የማይታየውን ዓለም እግዚአብሔር የፈጠረው ከም ንድነው?
2. እግዚአብሔር ሁሉን ነገር የፈጠረው እንዴት አድርጎ ነው?
3. የሰማይና የምድር መገኘት ምክንያት ምንድነው?
4. ፍጥረት የሚለው ቃል መሠረታዊ ትርጒም ምንድነው?



5. እግዚአብሔር ራሱ ከፈጠራቸው ነገሮች በመነሣት የፈጠራቸውን ፍጥረቶች ዘርዝር
6. ጊዜ ወይም ዘመን መቼ ተጀመረ?
7. መልአክ ማለት ምን ማለት ነው?
8. መላእክት ከእግዚአብሔር ወደ ሰዎች የሚላኩት ምን ለማድረግ ነው?
9. መልአክ በሚለው ቃል ሌሎች የሚጠሩበት አሉን?
10. ሦስት የመላእክት ስሞችን አስታውስ?
11. መላእክት ነጻ ፈቃድና ነጻ ፍላጎት ስላላቸው ምን ሊሆኑ ይችላሉ?
12. መላእክት ቅድስናቸውን ሊያዳብሩ እንደሚችሉ የምንረዳው በምንድ ነው?
13. ቅዱስ ሚካኤል ሊቀ መላእክት መሆኑን የምንረዳው በምንድነው?
14. አንዳንድ ወገኖች ሚካኤልን ከማን ጋር ያገናኙታል?
15.. ሚካኤል ማለት ምን ማለት ነው?
16. በዚህ ረገድ ከስሙ ትርጒም ጋር ያያያዙት አባባል ትክክል ያይደለው ለምንድነው?
17. በራእየ ዮሐንስ ም.12ቍ 7–12 እና ም:19ቍ 1–16 የተጣመረበት አባባል ስሕተቱ ምንድነው?
18. 1ኛ ተሰሎንቄ ም:4ቍ:16 እና መልእክተ ይሁዳ ቍጥር 9 የተጣመሩበት ምክንያት ስሕተቱ ምንድነው?
19. መጽሐፍ ቅዱስ የመልአኩ ሚካኤልን ስም ባነሣበት ጊዜ ሁሉ ከመልአክነቱ ወይም ከሊቀ መላእክትነቱ የተለየ ስም የሰጠበት ጊዜ አለን?
20. ርኩሳን መናፍስት ማለት እነማን ናቸው?
21. አዳምንና ሔዋንን ያሳታቸው እባብ ሰይጣን መሆኑን በምን እናው ቃለን?
22. በመጽሐፈ ኢዮብ አስደሳቹ ጉዳይ ምንድነው?
23. ሰይጣናት የወደቁት በምን ምክንያት ነው?
24. መላእክት በሥጋዊ ፍትወት ወደቁ የሚለው አስተሳሰብ ትክክል ያይደለው እንዴት ነው?
25. የእግዚአብሔር ልጆችና የሰው ልጆች የተባሉት እነማን ናቸው?

www.ethiopianorthodox.org



www.ethiopianorthodox.org

26. የእግዚአብሔር ልጆች የተባሉት ማንና ማን ናቸው?

27. የሰው ልጆች ፈተና የሚመጣባቸው ለምንድነው?

28. በሰዎች ላይ የሚመጣው ፈተና ምን ያኽል ነው?

29. እግዚአብሔር በሰማይ ይኖራል የምንለው ለምንድነው?

30. እግዚአብሔር የሚገኘው በሰማይ ብቻ ነውን?

31. እግዚአብሔርን ማየት እንችላለንን?

32. እግዚአብሔርን የምናውቀው እንዴት ነው?

33. የአፈጣጠርን ሁናቴ የሚነግረን ትምህርት ምን ይባላል?

34. እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው መቼ ነው?

35. እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን የፈጠረው በስንተኛው ቀን ነው?

36. በሁለተኛው ቀን ምንን ፈጠረ?

37. ወፎችና ዓሣዎች የተፈጠሩት በስንተኛው ቀን ነው?

38. እግዚአብሔር በአራተኛው ቀን ምንን ፈጠረ?

39. እግዚአብሔር ምድር አትክልትንና ፍሬን እንድታበቅል ያዘዘው በስንተኛው ቀን ነው?

# ምዕራፍ 2

## መጽሐፍ ቅዱስ

መጽሐፍ ቅዱስ ስንል በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት እንደተጻፉ ቤተ ክርስቲያን የምታምንባቸውን መጻሕፍት ስብስብ ማለታችን ነው። በውስጡም ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን የተባሉ ሁለት አጠቃላይ ክፍሎች አሉት። ብሉይ ኪዳን በዕብራይስጥ ሐዲስ ኪዳን ደግሞ በግሪክ ቋንቋዎች የተጻፉ ናቸው። በአሁኑ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ከሁለት ሺህ በሚበልጡ የዓለም ቋንቋዎች ተተርጉሟል።

መጽሐፍ ቅዱስ ከሌሎች መጽሐፎች የተለየ መጽሐፍ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር እንማራለን።



የእግዚአብሔር ሕጎችንና ትእዛዞችን የምንማረው በመጽሐፍ ቅዱስ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ምክር እናገኛለን። ደጉንና ክፉውን ነገር ለይተን የምናውቀው በመጽሐፍ ቅዱስ ነው።

ብሉይ ኪዳን:- ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በፊት የነበረው የሃይማኖት መጽሐፍ ብሉይ ኪዳን ይባላል። በዚህም መጽሐፍ ውስጥ ስለሃይማኖት ሕጎች የሚናገር ክፍል አለ።

ስለ ሃይማኖት ታሪኮች የሚናገር ክፍል አለ።

የጥበብና የምክር አነጋገር የሚናገር ክፍል አለ።

የትንቢት አነጋገር የሚናገር ክፍል አለ።

ሕጎችም ሲባሉ ይህን አድርግ ወይም ይህን አታደድርግ የሚሉ ትእዛዞች ናቸው። አድርግ ወይም አታድርግ የሚሉት ትእዛዞች ካልተከበሩ ያስቀጣሉ። እነዚህም ሕጎች የተጀመሩት በአዳምና በሔዋን ላይ ነው።

አዳምና ሔዋን:- እግዚአብሔር በመጀመሪያ የፈጠራቸው ሰዎች አዳምና ሔዋን ይባላሉ። ለእነርሱም ከሌላው ፍጥረት ሁሉ የተለየ ክብር ሰጣቸው። እነርሱም የተፈጠሩት፥ ሁሉ ነገር ተፈጥሮ ከተዘጋጀላቸው በኋላ በስድስተኛው ቀን ነው።

እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን ውብ የሆነ የአትክልት ቦታ አዘጋጅቶ እንዲኖሩበት ሰጣቸው። የቦታውም ስም ገነት ይባላል። በአትክልቱም ቦታ ውስጥ ብዙ ዐይነት ፍራፍሬዎች ነበሩ። ከእነርሱም መካከል የሕይወት ዛፍ፥ እንዲሁም ክፉንና ደግን የምታስታውቅ ዛፍ ነበሩበት።

እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ወደ አትክልቱ ቦታ ባስገባቸው ጊዜ ከአንድዋ በቀር ከዛፎቹ ሁሉ ፍሬ እንዲበሉ ፈቀደላቸው። መልካምንና ክፉን ከምታስታውቀዋ ዛፍ ፍሬ አትብሉ አላቸው። ከእርስዋ ከበላችሁ ሞትን ትሞታላችሁ ብሎ አስጠነቀቃቸው።

አዳምንና ሔዋንን ተንኰለኛዋ እባብ ስላሳሳተቻቸው የተከለከለውን ፍሬ በሉ። እናንተ ዐዋቂዎች ትሆናላችሁ እንጂ አትሞቱም ስላለቻቸው ተሳስተው ትእዛዙን አፈረሱ።

www.ethiopianorthodox.org

የእግዚአብሔር ቃል አይለወጥም። በዚህም መሠረት የሞት ቅጣት ጸናባቸው። ያን ፍሬ ባይበሉ ኖሮ የማይሙቱ ነበሩ። እግዚአብሔርም የሞቱን ፍርድ በአዳም ላይ ሲያጸናበት ከዐፈር ስለተፈጠርህ ወደ ዐፈር ትመለሳለህ ብሎታል (ዘፍ: ም:2 እና: 3)።

በአዳም ላይ የተላለፈው ፍርድ በዚያው ብቻ ተወስኖ አልቀረም። ሰው ሁሉ የአዳም ዘር በመሆኑ በሰው ሁሉ ላይ ተላልፎአል። የዓለም ሕዝብ ሁሉ ከአዳም ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ነው። ይህም ማለት ሁላችንም የአዳም ልጆች ነን ማለት ነው። በአንድ በኩል ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ ነው እንጂ አንድም ንጹሕ ሰው የለም። በተጨማሪ ደግሞ ሁላችንም የአዳምን ኃጢአት ወርሰናል። በዚህም ምክንያት ሁላችንም ሟቾች ሆነናል (ሮሜ: ም:5 ቍ:12 እና 18)።

ሞትም ሁለት ዐይነት ነው። የመጀመሪያው ሞት የሥጋችን በድን ሆኖ መቀበር ነው። ይህም የነፍስ ከሥጋ መለየት ይባላል። ሁለተኛው ሞት ደግሞ የማይሞተው ነፍሳችን ከሥጋ ጋር ኅብረት ካደረገ በኋላ በወዲያኛው ዓለም መሰቃየት ነው። ከአዳም የወረስነውም ሁለቱንም ዐይነት ሞት ነው።

አዳምና ሔዋን ትእዛዝ የማፍረስ ኃጢአት በሠሩ ጊዜ ከገነት እንዲባረሩ ተደረጉ። የሞት ፍርድም ስለተፈረደባቸው ከሕይወት ዛፍ ፍሬ እንዳይበሉ ተወሰነባቸው።





አዳምና ሔዋን ከገነት ሲወጡ (ዘፍ:ም3ቍ:23)

ከአዳምና ከሔዋን ታሪክ ምን እንማራለን?

አዳምና ሔዋን የተከለከለውን ፍሬ በበሉ ጊዜ ሰውነታቸው ተራቈተ። በዚያን ጊዜ ዐፈሩና ከእግዚአብሔር ሊደበቁ ሞከሩ። እግዚአብሔር ግን ሥራቸውን ዐውቆ አጋለጣቸው። ይህም የሚያመለክተው አንደኛ እግዚአብሔር በሁሉም ቦታ የሚገኝ መሆኑን ነው። ሁለተኛ ደግሞ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር የሚያውቅ መሆኑን ነው። ይህም በመሆኑ ከእግዚአብሔር ተደብቀን የምናደርገው ምንም ነገር አይኖርም ማለት ነው። ስለዚህ የምናደርገውን ነገር ሁሉ ከሰው ተደብቀን ልናደርግ እንችላለን። እግዚአብሔር ግን ሁሉን ነገር ያውቃል።

ከአዳምና ከሔዋን ታሪክ የምናገኘው ሌላው ትምህርት ደግሞ የእግዚአብሔርን አለመለወጥና ዳኝነት ነው። እግዚአብሔር ሰውን እንደሚወድድና ልዩ ክብር እንደሰጠው ቀደም ብለን ተመልክተናል። ሆኖም ሲያጠፉ ይቀ

www.ethiopianorthodox.org

ጣዋል እንጂ በማዳላት እንደሰው ውሳኔውን አይለውጥም። በዚህም መሠረት ፍሬውን ብትበሉ ትሞታላችሁ ያለው ውሳኔ አልተለወጠም።

<u>ኖኅና የጥፋት ውሃ</u>:- ከአዳምና ከሔዋን የተወለዱት ልጆቻቸው ዐድገው ሚስት አግብተው ሌሎች ልጆችን ወለዱ። የተወለዱትም እንደዚሁ ሌሎች ልጆችን ወለዱ። በዚህ ሀይነት የሰው ዘር መብዛት ጀመረ። የሰው ልጆች መብዛት በጀመሩ ጊዜ ኃጢትም እየበዛ ሄደ። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የሚያፈርሱት ሰዎችም በዙ። ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኞች ሆኑ። በዚያን ዘመን የእግዚአብሔርን ሕግ የሚጠብቅና ትእዛዙን የሚያከብር አንድ ሰው ብቻ ተገኘ። እርሱም ኖኅ ይባል ነበር። ኖኅም በእግዚአብሔር ዘንድ ተወዳጅነትን አገኘ።

የሰዎች ዐመፅም እየበዛ በሄደ ጊዜ እግዚአብሔር የሰው ልጆችን በጥፋት ውሃ ለማጥፋት ወሰነ። ይሁን እንጂ ኖኅንና ቤተሰቡን ከጥፋት ለማዳን ፈቅዶ መርከብ እንዲሠራ ኖኅን አዘዘው። ኖኅም በታዘዘው ዐይነት መርከቡን ሠርቶ ጨረሰ። ኖኅና ሚስቱ፥ ሦስቱ ልጆቹና የልጆቹ ሚስቶች ስምንት ሆነው ወደ መርከቡ ውስጥ ገቡ። ከእንስሳትና ከአዕዋፍ እንዲሁም ከተንቀሳቃሽ ፍጥረቶች ሁሉ አንድ ወንድና አንድ ሴት ወደ መርከቡ እንዲያስገባ ታዘዘ። እርሱም ትእዛዙን አክብሮ እንደ ታዘዘው አደረገ። ሁሉም ከገቡ በኋላ እግዚአብሔር የመርከቡን በር ከኖኅ በስተኋላ ዘጋ። ዝናብም ለአርባ ቀንና አርባ ሌሊት ባለማቋረጥ በምድር ላይ ዘነበ። እግዚአብሔር በምድር ላይ ሕይወት ያላቸውን ፍጥረቶች ሁሉ አጠፋ። ከመቶ ኀምሳ ቀኖች በኋላ ውሃው ጨርሶ ደረቀ። ቁራን አንድ ጊዜ፥ ርግብን ደግሞ ሦስት ጊዜ በመላክ ሙከራ ካደረገ በኋላ በመጨረሻ ውሃው መድረቁን ዐውቆ ከመርከቡ ወጣ። ከእርሱ ጋር አብረውት የነበሩት ሰዎችና ነፍስ ያላቸው ፍጥረቶች ሁሉ አብረው ወጡ። የኖኅ ልጆች ሴም፥ ካም፥ ያፌት ናቸው። የሰው ዘር ሁሉ የመጣው ከእነዚህ ከሦስት አባቶች ነው (ዘፍ: ም 6)።





የጥፋት ውሃ (ዘፍ: 7፥17)

ከኖኅና ከጥፋት ውሃ ታሪክ ምን እንማራለን?

ለሰው ልጆች ሃይማኖታዊ የመተዳደሪያ ደንብ በጽሑፍ የቀረበው በሙሴ ጊዜ ብቻ ነው። ሙሴም የነበረው ከኖኅ በኋላ ብዙ ዘመናት ዐልፈው ነው። ታዲያ፥ ሕግ ሳይኖር በኖኅ ዘመን በነበሩ ሰዎች ላይ እንዴት ቅጣት ተፈረደባቸው? ከሙሴ በፊት በነበሩት ዘመናት ሰዎች ሁለት የሕግ መሠረቶች ነበሩአቸው። አንዱ የኅሊና ሕግ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ትውፊት ነው። ሰው ሕግ ባያውቅም ኅሊናው ሕጋዊ የሆነና ሕጋዊ ያልሆነ ነገርን ለይቶ ያመለክተዋል።

ሕግ በጽሑፍ ከመቅረቡ በፊት ዋነኛው ሃይመኖታዊ የመተዳደሪያ ደንብ ትውፊት ነበር። ትውፊት ማለት በጽሑፍ ሳይሆን በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ሕግና ታሪክ ነው። እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን ያቺን ፍሬ እንዳይበሉ የከለከላቸው በቃል ትእዛዝ ነበር። ምናልባትም ሌሎችም

www.ethiopianorthodox.org

ትእዛዞችን ለአዳም በቃል ነግሮት ለልጆቹ አስተላልፎ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ቃየልና አቤል የተባሉት የአዳም ልጆች መሥዋዕት አቀረቡ ተብሏል። የመሥዋዕት ማቅረብ ሕግ በጽሑፍ የቀረበው በሙሴ ጊዜ ነው። ይህም የሚያመለክተው እግዚአብሔር የመሥዋዕትን ማቅረብ ሕግ ለአዳም ወይም ለቃየልና ለአቤል በቃል ነግሮአቸዋል ማለት ነው። እንዲሁም ከአዳም ሰባተኛ ትውልድ የሆነው ሔኖክ የእግዚአብሔርን መንገድ ስለተከተለ አልሞተም፤ እግዚአብሔር ወሰደው ተብሎአል። ታዲያ ሔኖክ በትውፊት አማካይነት ካልሆነ የእግዚአብሔርን መንገድ እንዴት ሊያውቅ ቻለ? ሌሎችም ምሳሌዎች ካስፈለጉ አብርሃምን፥ ይስሐቅን፥ ያዕቆብንና ዮሴፍን መጥቀስ ይቻላል። እንዲሁም እግዚአብሔር ለኖኅና ለአብርሃም የተለያዩ ቃል ኪዳኖችን የገባ ላቸው ከሙሴ ዘመን በፊት ነው።

ሌላው ከኖኅና ከጥፋት ውሃ ታሪክ የምናገኘው ትምህርት የእግዚአብሔርን ዳኝነት ነው። እግዚአብሔር ጥፋተኞችን ቢቀጣም የጥፋትን መንገድ የማ ይከተሉትን ደጋግ ሰዎችን በጥበቡ እንደሚያድናቸው በኖኅና በመርከቡ ምሳሌነት ልንረዳ እንችላለን።

<u>የባቢሎን ግንብ</u>:- በቀድሞ ጊዜ ሰዎች ሁሉ የሚነጋገሩት በአንድ ቋንቋ ነበር። እነዚያም ሰዎች ወደ ምሥራቅ ሲሄዱ በሰናዖር ምድር አንድ ሜዳ አገኙና እዚያ ሰፈሩ። እርስ በርሳቸውም ኑ ጡብ እንሥራ ተባባሉ። ከዚያም ጡቡን እንዲጠነክር በእሳት ተኰሱት። የሚያጣብቁበትም ቅጥራን አገኙ። ከዚያም ለስማችን ማስጠሪያ የሚሆን አንድ ከተማ እንመሥርት ተባባሉ። ስማችንንም ለማስጠራት እስከ ሰማይ የሚደርስ ግንብ እንገንባ ተባባሉና መሥራት ጀመሩ። እግዚአብሔርም ይህን የሚያደርጉት አንድ ቋንቋ ስለሚ ናገሩ አይደለምን? ኑ ቋንቋቸውን እንደባልቀው አለ። ከዚያም ቋንቋቸውን ደባለቀው። በአንድ ቋንቋ መናገራቸው ቀርቶ በቋንቋ በተለያዩ ጊዜ አብረው ሊሠሩ አልቻሉም። በዚህም ምክንያት ሥራውን አቆሙ (ዘፍ:ም: 11ቊ: 1–9)።

ለምንድነው እግዚአብሔር ሰዎቹ ያቀዱትን ሥራ ያልፈቀደላቸው?

የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ለዚህ ጥያቄ መልስ ሁለት ምክንያቶችን ያቀርባሉ:- የመጀመሪያው ምክንያት ዕቅዳቸው በትዕቢት ዓላማ ላይ የተመ ሠረተ በመሆኑና በእግዚአብሔር ላይ ዐመፅን የሚጋብዝ ስለ ነበረ ነው። ይህም ማለት ዓላማቸው ከእግዚአብሔር እርዳታ ነጻ ለመውጣት ስለነበረ ነው።



ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ የእግዚአብሔርን ዕቅድ የሚቃረን ስለነበረ ነው። እግዚአብሔር የሰውን ልጆች ብዙ፤ ተባዙ፤ ምድርንም ሙሉአት ብሎአቸው ነበር። እነርሱ ግን በአንድ አካባቢ ብቻ ሲሰበሰቡ ምድርን ሙሏት ያለውን የእግዚአብሔርን ዕቅድ ተቃወሙ ማለት ነው (ዘፍ:11፥1–9)።



የባቢሎን ግንብ (ዘፍ:11፥1–9)

<u>አብርሃም</u>:- ቀደም ብሎ የነበረው የአብርሃም ስም አብራም ነበረ። በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር ለአብራም ተገልጦለት ከዘመዶቹና ከአባቱ ቤት ተለይቶ እርሱ ማለት እግዚአብሔር ወደሚያሳየው አገር እንዲሄድ ነገረው። እግዚ አብሔርም ዘሩን እንደሚያበዛ፥ ታላቅ ሕዝብ እንደሚያደርገው፥ ለሌሎች በረከት እንደሚሆንና ሕዝቦችም በእርሱ እንደሚባረኩ ቃል ኪዳን ገባለት። አብራምም ከካራን ወጥቶ ያለውን ሀብት ሁሉ በመያዝ ከሚስቱ ከሣራይና ከወንድሙ ልጅ ከሎጥ ጋር ወደ ከነዓን ምድር ሄደ። ወደ ከነዓን ምድር በደረሰ

www.ethiopianorthodox.org

ጊዜ እግዚአብሔር ተገልጦለት ይህቺን ምድር ለዘርህ እሰጣለሁ ብሎ ሌላ ቃል ኪዳን ገባለት።

<u>የአብርሃምና የሎጥ መለያየት</u>:- አብራም ከሚስቱ ከሣራይና ከወንድሙ ልጅ ከሎጥ ጋር ሆኖ ወደ ኔጌብ ሄደ። አብራምና ሎጥ ሁለቱም እያንዳንዳቸው ብዙ ከብቶች ነበሩአቸው። ስለዚህ አብረው ለመኖር ቦታ የማይበቃቸው ሆኑ። በዚህ ጊዜ አብርሃም ሎጥን:- ሁለታችንም ብዙ ከብቶች ስላሉን አብረን ለመኖር ያስቸግረናል። ስለዚህ ተለያይተን ብንኖር የተሻለ ነው። አንተ ወደመረጥኸው አቅጣጫ ሂድ፤ አንተ ወደ ቀኝ ብትሄድ እኔ ወደ ግራ እሄዳለሁ፤ አንተ ወደ ግራ ብትሄድ እኔ ወደ ቀኝ እሄዳለሁ አለው። ሎጥም ምርጫውን እንደ አባቱ ለሚሆነው ለአጐቱ ለአብርሃም ቅድሚያ በመስጠት ፈንታ እርሱ ተሽሎ ያገኘውን አቅጣጫ መረጠ። ስለዚህ አብራም በከነዓን አገር ሲኖር ሎጥ ግን ወደ ሰዶም አካባቢ ድንኳኑን ተከለ (ዘፍ:ም:13 ቍ:1–13)።

ሎጥ ከሄደ በኋላ እግዚአብሔር አብራምን ካለህበት ቦታ ወደ ሁሉ አቅጣጫ ተመልከት፤ ይህን የምታየውን ሁሉ ለዘርህ እሰጣለሁ፤ ዘርህንም እንደ ምድር አሸዋ አበዛዋለሁ አለው። አብራምም ድንኳኑን ነቅሎ በኬብሮን የመምሬ የተቀደሱ ወርካ ዛፎች ወደ አሉበት ስፍራ ለመኖር ሄደ። እዚያም ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሠራ።

<u>አብራም ሎጥን ከምርኮ ነጻ ማውጣቱ</u>:- በዚያን ጊዜ የባቢሎን፥ የኤላ፥ የዔላምና የጎይም ነገሥታት የሰዶምን፥ የገሞራን፥ የአዳማን፥ የጸቦይምንና የቤላዕን ነገሥታት ለመውጋት ሄዱ። እነዚያ አራቱ ነገሥታት አምስቱን ነገሥታት ድል ነሡአቸው። የሰዶምና የገሞራ ነገሥታት ከጦርነቱ ሸሽተው ለማምለጥ ሲሞክሩ በቅጥራን ጕድጓዶች ውስጥ ወደቁ። የቀሩት ሦስቱ ነገሥታት ግን ወደ ተራራዎቹ ሸሹ። አራቱ ነገሥታት በሰዶምና በገሞራ ያገኙትን ነገር ሁሉ ምግብ እንኳ ሳይቀር ማርከው ሄዱ። ሎጥም ከነሀብቱ ተማርኮ ነበር።

አብራም የወንድሙ ልጅ እንደተማረከ በሰማ ጊዜ በቤቱ ተወልደው የጦር ልምምድ ያላቸውን 318 ሰዎች በትጥቅ አደራጅቶ አራቱን ነገሥታት በመከታተል እስከ ዳን ድረስ ሄደ። እዚያም ገጠማቸውና ድል በማድረግ



አሳደዳቸው። የተወሰደውንም ምርኮ ሁሉ መልሶ አመጣ፤ እንዲሁም የወንድሙን ልጅ ሎጥን ከነሀብቱ መልሶ አመጣ (ዘፍ:ም:14ቍ:1–16)።

<u>መልከ ጼዴቅ አብርሃምን መባረኩ</u>:- አብራም አራቱን ነገሥታት ድል አድርጎ በተመለሰ ጊዜ የሰዶም ንጉሥ ሊቀበለው ወጣ። የልዑል እግዚአብሔር ካህን የነበረው የሳሌም ንጉሥ መልከ ጼዴቅም ለአብራም እንጀራና የወይን ጠጅ አምጥቶለት እንዲህ ብሎ ባረከው:- «ሰማይንና ምድርን የፈጠረ ልዑል እግዚአብሔር አብራምን ይባርክ፤ በጠላቶችህ ላይ ድልን ያቀዳጀህ ልዑል እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን።»

የሰዶምም ንጉሥ አብራምን በምርኮ ያገኘኸውን ሀብት ሁሉ ለራስህ ውሰድ፤ ሰዎቹን ግን መልስልኝ አለው። አብራም ግን አንተ አብራምን አበለጸግሁት እንዳትል እኔ ከአንተ ምንም አልወሰድም አለ (ዘፍ:ም: 14ቍ 17–25)። (ይህን ታሪክ በሁለተኛው መጽሐፍ ይመለከቷል)።

<u>እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር የገባው ቃል ኪዳን</u>:- ከዚህ በኋላ አብራም ራእይ አየ፤ እግዚአብሔርም:- «አብራም፥ አትፍራ፤ እንደ ጋሻ ሆኜ ከአደጋ ሁሉ እጠብቅሃለሁ፤ ታላቅ በረከትም እሰጥሃለሁ» ሲል ሰማው። አብራምም «ምንም ልጅ ስለሌለኝና የሚወርሰኝም የቤቴ አገልጋይ ስለሆነ የምትሰጠኝ በረከት ምን ይጠቅመኛል?» አለ። እግዚአብሔርም መልሶ «የሚወርስህ ከአንተ የሚወለደው ልጅ ነው እንጂ የቤት አገልጋይህ አይደለም» አለው። አብራም ከባድ እንቅልፍ ይዞት ሳለ እግዚአብሔር እንዲህ አለው፤ ዘሮችህ በባዕድ አገር ስደተኞች ይሆናሉ፤ እዚያም በባርነትና በጭቈና ለአራት መቶ ዓመት ይኖራሉ፤ በባርነት የሚገዛቸውን ሕዝብ እቀጣለሁ፤ ከዚያም በኋላ ብዙ ሀብት ይዘው ከዚያ አገር ይወጣሉ። አንተ ግን ብዙ ዘመን ኖረህ በሰላም ሞተህ ትቀበራለህ። ዘሮችህ ወደዚህ ተመልሰው የሚመጡት ከአራት መቶ ዓመት በኋላ ነው።

<u>አጋርና እስማኤል</u>:- የአብራም ሚስት ሣራይ ገና ልጅ አልወለደችለትም ነበር። ሣራይም አብራምን:- «እግዚአብሔር ልጅ አልሰጠኝም፤ ስለዚህ ምናልባት ከአጋር ልጅ ይሰጠኝ እንደሆነ ወደ አጋር ግባ» ብላ አጋርን ለአብርሃም በሚስትነት ሰጠችው። አብራምም አጋርን ባወቃት ጊዜ ፀነሰች። አጋር መፀነስዋን ባየች ጊዜ በሣራይ ላይ ኮራችና ናቀቻት። በዚህ ጊዜ ሣራይ አብራምን «አጋርን የሰጠሁህ እኔ አይደለሁምን? እርስዋ ግን መፀነስዋን፥

www.ethiopianorthodox.org

ባየች ጊዜ ናቀችኝ፤ ስለዚህ እግዚአብሔር ከእኔና ከአንተ ጥፋተኛው ማን እንደሆነ ይፍረድ» አለችው። አብራምም እርስዋ የአንቺ አገልጋይ ነች፤ አንቺ የፈለግሺውን አድርጊ አላት። ከዚህ በኋላ ሣራይ አጋርን እጅግ ስላሰቃየቻት አጋር ከቤት ወጥታ ኮበለለች። የእግዚአብሔር መልአክም በበረሓ አግኝቷት ወደ እመቤትዋ እንድትመለስ ነገራት። «ዘርሽን አበዛዋለሁ፤ ወንድ ልጅ ትወልጂአለሽ፤ እግዚአብሔር የሐዘን ለቅሶሽን ስለሰማልሽ ስሙን እስማ ኤል» ትዪዋለሽ አላት። አጋርም ለአብራም ወንድ ልጅ ወለደችለት፤ ስሙንም እስማኤል ብሎ ጠራው።

<u>መገረዝ የቃል ኪዳን ምልክት ስለመሆኑ</u>:- እግዚአብሔር አብራምን እንዲህ አለው:- «አንተና ከአንተም በኋላ የሚመጣው ዘርህ ከእኔ ጋር የገባኸውን ቃል ኪዳን ከትውልድ እስከ ትውልድ ጠብቁ፤ አንተና ከአንተ በኋላ የሚመጣው ዘርህ የምትጠብቁት ቃል ኪዳን ይህ ነው፤ በመካከላችሁ ያሉት ወንዶች ሁሉ መገረዝ አለባቸው፤ ሸለፈታችሁን ትገረዛላችሁ፤ ይህም በእኔና በእናንተ መካከል ላለው ቃል ኪዳን ምልክት ይሆናል፤ በመጪው ዘመን የሚወለድ ወንድ ልጅ ሁሉ በተወለደ በስምንተኛው ቀን ይገረዝ፤ እንዲሁም በቤትህ የተወለዱና በቤትህ ሳይወለዱ ከውጭ በገንዘብ ተገዝተው የመጡ ባሪያዎች ሳይቀሩ በዚሁ ዐይነት ይገረዙ። እኔም የብዙ ሕዝቦች አባት ስለማደርግህ ከእንግዲህ ወዲህ ስምህ አብራም መሆኑ ቀርቶ አብርሃም ይሆ ናል። ከእንግዲህ ወዲህ ሚስትህን ሣራይ ብለህ አትጥራት፤ ከዛሬ ጀምሮ የእርስዋ ስም ሣራ ነው። ከእርስዋም ወንድ ልጅ እሰጥሃለሁ፤ እባርካታለሁ፤ የብዙ ሕዝቦችም እናት ትሆናለች፤ ከዘርዋም መካከል ነገሥታት የሚሆኑ ይገ ኛሉ።

እግዚአብሔር ባዘዘውም መሠረት በዚያኑ ቀን አብርሃምና ልጁ እስማ ኤል፥ እንዲሁም በቤቱ ያሉ ወንዶች ሁሉ ተገረዙ።

<u>የአብርሃምና የሣራ እንግዶችን ማስተናገድ</u>:- ከዕለታት:- አንድ ቀን አብርሃም በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ ሦስት ሰዎች በእርሱ በኩል ሲሄዱ አይቶ ብድግ ብሎ በአክብሮት ተቀበላቸውና በለጋሥነት አስተናገዳቸው። ሚስትህ ሣራ ወዴት ናት ብለው ጠየቁት፤ እርሱም በድንኳኑ ውስጥ መሆንዋን ገለጠላቸው። ከሦስቱ እንግዶች አንዱ የዛሬ ዓመት ልክ በዚህ ጊዜ ተመልሼ እመጣለሁ፤ ሚስትህ ሣራ ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች አለው። ይህን በሚናገርበት ጊዜ ሣራ በድንኳኑ በስተጀርባ ሆና ታዳምጠው ስለነበረ በእው



ነት በዚህ በእርጅና ዕድሜአችን ልጅ መውለድ እንችላለንን ብላ በማሰብ ሳቀች። እግዚአብሔርም አብርሃምን በዚህ ዕድሜዬ እንዴት ለመውለድ እችላለሁ ብላ ሣራ ለምን ሳቀች ብሎ ጠየቀው። ሣራ ግን ስለፈራች አልሳ ቅሁም ብላ ካደች።

ከዚህ በኋላ እንግዶቹ ለመሄድ ሲነሡ አብርሃም ሊሸኛቸው አብሮአቸው ሄደ። ከእንግዶቹ ሁለቱ ወደ ሰዶም ሄዱ። አብርሃም ግን በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ ነበር። እግዚአብሔር ሰዶምንና ገሞራን የሚያጠፋ መሆኑን በመገንዘቡ አብርሃም እግዚአብሔርን «በደል የሌለባቸውን ደጋግ ሰዎች ከኃጢአተኞች ጋር ታጠፋለህን? በከተማይቱ ውስጥ ኀምሳ ደጋግ ሰዎች ቢገኙ ከተማይቱን በሙሉ ትደመስሳለህን? ብሎ ጠየቀው። እርሱም ለኀምሳዎቹ ስል ያቺን አገር አላጠፋም ሲል መልስ ሰጠው። ከዚያ በኋላ አርባ አምስት፥ አርባ፥ ሠላሳ፥ ሃያ፥ ዐሥር እያለ የደጋግ ሰዎች መገኘትና የእግዚአብሔርን ይቅርታ ሲለምን እስከ ዐሥር ደጋግ ሰዎች እንኳ በዚያች ከተማ ውስጥ ቢኖሩ ለዐሥሩ ደጋግ ሰዎች ሲል ያቺን ከተማ እንደማያጠፋት እግዚአብሔር ለአብርሃም ቃል ገባለት። ነገር ግን በዚያች ከተማ ዐሥር እንኳ ደጋግ ሰዎች ባለመገኘታቸው ያቺ ከተማና ሕዝቧ እንዲደመሰሱ ፍርድ ተበየነባቸውና ተደመሰሱ። እግዚአ ብሔር ግን ለአብርሃም ሲል ሎጥንና ቤተሰቡን ከጥፋት አዳናቸው።

<u>የይስሐቅ መወለድ</u>:- እግዚአብሔር በሰጠው ተስፋ መሠረትና በወሰነው ጊዜ የአብርሃም ሚስት ሣራ ወንድ ልጅ ወለደችለት። አብርሃምም የልጁን ስም ይስሐቅ ብሎ ጠራው። ይስሐቅ በተወለደ ጊዜ አብርሃም የመቶ ዓመት ሰው ነበር። በዚህ ዕድሜዬ እንድስቅ አደረገኝ ስትል ሣራ እግዚአብሔርን አመሰገነች። ልጁም እያደገ ሄዶ ጡት መጥባት ባቆመበት ጊዜ አብርሃም ታላቅ ግብዣ አደረገ።

<u>የአጋርና የእስማኤል መባረር</u>:- ከዕለታት አንድ ቀን ሣራ እስማኤልን ከይስሐቅ ጋር ሲጫወት አየችውና አብርሃምን እንዲህ አለችው:- «ይህችን አገልጋይ ከነልጅዋ አባርርልኝ፤ የዚህች አገልጋይ ልጅ ከልጄ ከይስሐቅ ጋር መውረስ አይገባውም።» ይህ ጉዳይ አብርሃምን በጣም አስጨነቀው። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ስለልጁና ስለ አጋር አትጨነቅ፤ ዘር የሚወጣልህ በይስ ሐቅ ስለሆነ ሣራ የምትልህን ሁሉ አድርግ፤ የአገልጋይቱም ልጅ የአንተ ልጅ ስለሆነ ታላቅ ሕዝብ እስኪሆን ድረስ ዘሩን አበዛዋለሁ አለው።

www.ethiopianorthodox.org

ከዚያም በማግስቱ ጥቂት ስንቅ ሰጥቶ አብርሃም አጋርን ከነልጅዋ አባረራት።

<u>እግዚአብሔር አብርሃምን መፈተኑ</u>:- እግዚአብሔር አብርሃምን ልጅህን ይስሐቅን መሥዋዕት አድርገህ አቅርብልኝ አለው። አብርሃምም በምንም ዐይነት የእግዚአብሔርን ቃል ሳይቃወም ልጁን ይስሐቅን እግዚአብሔር ባመለከተው ቦታ ለመሠዋት ተነሥቶ ሄደ። ይስሐቅም አባቱን እነሆ፥ እሳትና እንጨት ይዘናል፤ ታዲያ፥ ለመሥዋዕት የሚሆነው በግ የት አለ ብሎ ጠየቀው። አብርሃምም ለመሥዋዕት የሚሆነውን በግ እግዚአብሔር ለራሱ ያዘጋጃል ብሎ መለሰለት። እግዚአብሔር ወደ አመለከተው ቦታም ሲደርሱ መሠዊያ ሠርቶ እንጨቱን በላዩ ረበረበው። ይስሐቅንም አስሮ ከእንጨቱ በላይ አጋደመውና ሊያርደው ቢላዋ ባነሣ ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ አብርሃም፥ አብርሃም ብሎ ጠራው። አብርሃምም አቤት አለ። መልአኩም አንድ ልጅህን እንኳ እስከትሰጥ ድረስ እግዚአብሔርን የምትፈራ መሆንህን ተረድቼአለሁና በልጁ ላይ አንዳች ጉዳት እንዳታደርስበት አለው። አብርሃምም ዙሪያውን በተመለከተ ጊዜ ቀንዶቹ በቍጥቋጦ የተያዙ አንድ በግ አየ። በጉንም አመጣና በልጁ ምትክ መሥዋዕት አድርጎ አቀረበው። ያንንም ቦታ እግዚአብሔር ያዘጋጃል ብሎ ሰየመው።





የአብርሃም ለእግዚአብሔር ቃል ታዛዥነት (ዘፍ፡ 22፡ቁ፡12)

<u>የይስሐቅና የርብቃ ጋብቻ</u>:- የአብርሃም ሚስት ሣራ በመቶ ሃያ ሰባት ዐመትዋ በሞተች ጊዜ አብርሃም በጣም አርጅቶ ነበር። በዚህ ጊዜ አብርሃም የንብረቱ ሁሉ ኀላፊ ሆኖ ለረዥም ዘመን የኖረውን አገልጋዩን ጠርቶ ወደ ትውልድ አገሩ ሄዶ ለልጁ ለይስሐቅ ከወገኖቹ መካከል ሚስት እንዲመርጥለት አስማለው። አገልጋዩም ልጅትዋ ወደዚህ አገር አልመጣም ካለችኝ ምን ላድርግ ብሎ ጠየቀው። አብርሃምም የማመልከው አምላክ መንገድህን እንደሚያቃናልህ አምናለሁ። ፈቃደኛ ካልሆነች ግን ከመሐላው ነጻ ነህ አለው። ይህም የአብርሃም አገልጋይ በእምነት ተነሥቶ በመሄድ ጸሎቱን ለእግዚአብሔር ካቀረበ በኋላ ጸሎቱ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን ስላገኘ የአብርሃም ወንድም የናኮር የልጅ ልጅ የነበረችውን ርብቃን ለይስሐቅ ሚስት እንድትሆነው ይዞአት ለመምጣት ችሎአል። ከዚያም በኋላ ይስሐቅ እናቱ ሣራ ትኖርበት ወደ ነበረው ድንኳን ርብቃን ይዞአት ገባ፤ ሚስትም ሆነችው፤ ይስሐቅ ርብቃን ወደዳት፤ በእናቱ ሞት ምክንያት ከደረሰበትም ሐዘን በዚህ ሁኔታ ተጽናና።



www.ethiopianorthodox.org

<u>ሌሎች የአብርሃም ልጆችና የአብርሃም ሞት</u>:- አብርሃም ቀጡራ የምትባል ሌላ ሚስት አገባ፤ እርስዋም ዚምራንን፥ ዮቅሻንን፥ መዳንን፥ ምድያምን፥ ዮሽባቅንና ሹሐን ወለደችለት። አብርሃም ያለውን ሀብት ሁሉ ለይስሐቅ አወረሰው። ከሌሎች ሴቶች ለተወለዱትም ልጆች ገና በሕይወት ሳለ ስጦታ ሰጣቸው። ከዚህ በኋላ እነዚህ ሌሎች ልጆች ከይስሐቅ ርቀው ወደ ምሥራቅ አገር እንዲሄዱ አደረጋቸው።

የአብርሃም ዕድሜ በአጠቃላይ መቶ ሰባ አምስት ዓመት ነበር፤ በዚህም ዐይነት አብረሃም በቂ ዕድሜ አግኝቶ ካረጀ በኋላ ሞተ ፤ ልጆቹ ይስሐቅና እስማኤል ማክፌላ በተባለ ዋሻ ቀበሩት፤ ይህም ዋሻ ከመምሬ በስተምሥራቅ በሒታዊው በጸሐር ልጅ በዔፍሮን እርሻ ውስጥ የሚገኘው ነው። እርሱም አብርሃም ከሒታውያን ላይ የገዛው የመቃብር ቦታ ነው፤ በዚህ ዐይነት ሚስቱ ሣራ በተቀበረችበት ዋሻ ተቀበረ። አብርሃም ከሞተ በኋላ እግዚአብሔር ልጁን ይስሐቅን ባረከው።

## <u>ሐዲስ ኪዳን</u>

ከመጽሐፍ ቅዱስ ሁለተኛው ክፍል ሐዲስ ኪዳን ይባላል። በውስጡም የሚገኙት መጻሕፍት ከጌታችን ልደት፥ ስቅለት፥ ሞት፥ ትንሣኤና ዕርገት በኋላ የተጻፉ ናቸው።

<u>ዮሐንስ መጥምቁ</u>:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሊወለድ በተቃረበበት ዘመን ዘካርያስ የተባለ ካህን ነበር። ሚስቱም ኤልሣቤጥ ትባል ነበር። ሁለታቸውም በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ። ኤልሣቤጥ መኻን ስለነበረች ልጅ አልነበራቸውም። ሁለቱም በጣም አርጅተው ነበር። ዘካርያስም ለቤተ መቅደስ አገልግሎት ተራው ደረሰ። በዚያን ጊዜ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ ዕጣን ሲያጥን ምእመናኑ በውጪ ቆመው ይጸልዩ ነበር። ዕጣን በሚጤስበት መሠዊያ በስተቀኝ በኩል የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ለዘካርያስ ታየው። ዘካርያስም ፈርቶ ደነገጠ። መልአኩም:- «ዘካርያስ ሆይ፥ አይዞህ አትፍራ፤ ጸሎትህ ተሰምቶልሃል፤ ሚስትህ ኤልሣቤጥ ልጅ ትወልድልሃለች፤ ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ አለው። ዘካርያስ ግን እውነት መሆኑን እንዴት ላውቅ እችላለሁ በማለት ጥርጣሬውን ገለጠ። መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ዘካርያስን «ከእግዚአብሔር ተልኬ የመጣሁትን የእኔን ቃል ስላላመንክ ጉዳዩ ስኪፈጸም ድረስ ድዳ ትሆናለህ» አለው። በዚያኑ ጊዜ መናገር የማይችል ድዳ ሆነ። ውጪ ቆመው የሚጸልዩት ምእመናን ዘካርያስ ከውስጥ ሳይወጣ ሲዘገይባቸው ተገረሙ። ዘካርያስ ከቤተ መቅደሱ በወጣ ጊዜ ከሰዎቹ ጋር መነጋገር አልቻለም። በእጁ እየጠቀሰ ብቻ ያስረዳቸው ነበር። ስዚህ በቤተ መቅደሱ ውስጥ አንድ ነገር እንደታየው ዐወቁ። በዚህም ሁኔታ ድዳ ሆኖ ቆየ። ኤልሣቤጥም ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፀነሰች።

ኤልሣቤጥ የመውለጃዋ ጊዜ ሲደርስ ወንድ ልጅ ወለደች። በስምንተኛው ቀን በግዝረት ሥነ ሥርዓት ላይ ጐረቤቶችና ዘመዶች ተሰባስበው ነበር። ሰዎቹም ሕፃኑን በአባቱ ስም ዘካርያስ ተብሎ እንዲጠራ ፈልገው ነበር። እናቱ ግን አይሆንም ስሙ ዮሐንስ ነው አለች። ከዚያ በኋላ ዘካርያስን ልጅህ ማን ተብሎ እንዲጠራ ትፈልጋለህ ብለው በምልክት ጠየቁት። ዘካርያስም መጻፊያ እንዲሰጡት ጠይቆ ስሙ ዮሐንስ ነው ብሎ ጻፈ። በዚያኑ ጊዜ አንደበቱ ተፈታና መናገር ጀመረ።

ዘካርያስ አንደበቱ ከተፈታለት በኋላ ስለ ዮሐንስ አገልግሎትና ስለ አዳኙ መምጣት ትንቢት በመናገር እግዚአብሔርን አመሰገነ። ሕፃኑ ዮሐንስም ዐደገ፤ በመንፈስም ጠነከረ፤ ለእስራኤል ሕዝብ እስከታየበትም ጊዜ ድረስ በበረሓ ኖረ። ከዚያም ወደ ሕዝቡ መጥቶ ማስተማሩን ጀመረ።

እርሱም የራሱን ማንነት ሲገልጽ ሕዝቡን ለእግዚአብሔር መንግሥት የሚያዘጋጅ መሆኑን አስታወቀ። የእግዚአብሔር መንግሥት መጥታለችና ንስሓ ግቡ እያለ የንስሓ ጥምቀት ያጠምቅ ነበር። ይሁን እንጂ ከእርሱ በኋላ የሚመጣው ከእርሱ እንደሚበልጥና በመንፈስ ቅዱስ እንደሚያጠምቅ ተና ገረ። ጌታችን ኢየሱስንም ባየ ጊዜ እነሆ፥ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ብሎ መሰከረ። ከዚያም ጌታችን ኢየሱስን በዮርዳኖስ ወንዝ አጠመቀው።

ዮሐንስ እውነትን ከመናገር የማይፈራ ሰው ስለነበረ የሄሮድስ ሚስት አስገደለችው። ከዮሐንስ መጥምቁ የምናገኘው ትምህርት ምንድነው?

ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ መከራ በመቀበል ዓለምን ማዳኑ በነቢያት መጻሕፍት የተነገረ ነው። ከዚሁም ጋር ሁናቴውን አስቀድሞ መጥቶ እንደሚያመቻች ስለዮሐንስ መጠምቁ ትንቢት ተነግሮ ነበር።

በመጀመሪያ:- «በምድረ በዳ የእግዚአብሔርን መንገድ አዘጋጁ፤ በበረ ሓም ለአምላካችን ጥርጊያ ጐዳና አብጁ» ተብሏል (ኢሳ:40፥3)።



www.ethiopianorthodox.org

ሁለተኛ:- «መንገዴን ያዘጋጅ ዘንድ መልእክተኛዬን አሰቀድሜ እልካለሁ፤ ከዚህ በኋላ ‹ይመጣልናል› ብላችሁ የምትጠብቁት ጌታ ወደ ቤተ መቅደሱ በድንገት ይመጣል፤ ለማየት የምትናፍቁትም መልእክተኛዬ መጥቶ ቃል ኪዳኔን ያውጃል» ተብሎአል (ሚል:3፥1)።

ሦስተኛ:- «የእግዚአብሔር ቀን ከመምጣቱ በፊት ነቢዩን ኤልያስን ወደ እናንተ እልክላችኋላሁ። እርሱም... አባቶችንና ልጆችን ልብ ለልብ እንዲቀራረቡ ያደርጋቸዋል» (ሚል:4፥5–6)። እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ትንቢቶች ተፈጻሚ የሆኑት በዮሐንስ መጥምቁ ነው።

ከዮሐንስ መጥምቁ የምንማረው ትልቁ ትምህርት ኀጢአትን በስሙ ጠርተን ማውገዝን እንዳንፈራ ነው። ምንም ሄሮድስ በትልቅ የዓለማዊ ሹመት ደረጃ ላይ ቢሆን የወንድምህን ሚስት ማግባት አይገባህም ብሎ ገሥጸው እንጂ አልፈራውም። ስለዚህ እኛም ሰውን በመፍራት እውነትን ከመናገር እንዳን ቈጠብ ያስተምረናል።

አወላለዱም በዕድሜ ከገፉ ሰዎች መሆኑ ለእግዚአብሔር ምንም የሚሳነው ነገር እንደሌለ ያስተምረናል።

<u>የማትያስ መመረጥ</u>:- ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት ከተነሣ በኋላ አርባ ቀኖች ሙሉ ለደቀ መዛሙርቱ እየተገለጠላቸው ስለ እግዚአብሔር መንግሥት አስተማራቸው። ዮሐንስ በውሃ አጠመቀ፤ እናንተ ግን ከጥቂት ቀኖች በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ አላቸው። ይህን ተስፋ እንዲጠብቁ ከዚያ ከተስፋው መፈጸም በፊት ከኢየሩሳሌም እንዳይወጡ ነገራቸው። ይህንንም ከነገራቸው በኋላ እነርሱ እያዩት ወደ ሰማይ ዐረገ።

በእነዚህ ቀኖች ውስጥ ጌታችንን ዐሳልፎ በመስጠት ከእነርሱ በተለየው በይሁዳ አስቆሮታዊው ምትክ ሌላ ሰው ለመምረጥ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ባሳሰበው መሠረት ምርጫ አካሄደዋል። እግዚአብሔር የፈቀደውን እንዲመርጥ ከጸለዩ በኋላ በዮሴፍና በማትያስ ላይ ዕጣ ሲያወጡ ዕጣው ለማትያስ ስለወጣለት ከዐሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ጋር ዐሥራ ሁለተኛ ሆኖ ተቈጥሮአል (የሐ:ሥ:ም:1ቍ:12–26)።

<u>የመንፈስ ቅዱስ በደቀ መዛሙርቱ ላይ መውረድ</u>:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ባረገ በዐሥረኛው ቀን፥ የአይሁድ የፋሲካ በዐል በዋለ በኀምሳኛው ቀን ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ በአንድነት ተሰብሰው ሳለ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው ተስፋ ተፈጸመ።

በድንገት ብርቱ ዐውሎ ነፋስ የመሰለ ድምፅ ከሰማይ መጣ፤ የነበሩበትንም ቤት ሞላው። የእሳት ነበልባሎች የሚመስሉ ምላሶች ታዩአቸው፤ ተከፋፍለውም በእያንዳንዳቸው ላይ ዐረፉባቸው። ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፤ መንፈስ ቅዱስ እንዲናገሩ በሰጣቸው ችሎታ መጠን በሌሎች ቋንቋዎች መናገር ጀመሩ። ከተለያዩ አገሮች የመጡ የአይሁድ ሃማኖት ተከታዮች በኢየሩሳሌም ይኖሩ ነበር። እነዚህ የገሊላ ሰዎች እንዴት በየቋንቋችን ሲናገሩ እንሰማለን ይህ ነገር ምን ይሆን ብለው ተገረሙ።

አንዳንዶቹ ግን አዲስ የወይን ጠጅ ጠጥተው ሰክረዋል ብለው አፌዙባቸው።

በዚያን ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስ ከዐሥራ አንዱ ጋር ቆመና ድምፁን ከፍ አድርጎ ተናገረ። እርሱም እናንተ የይሁዳ ሰዎችና የኢየሩሳሌም ነዋሪዎች የሆናችሁ ሁሉ፥ እናንተ እንዳሰባችሁት እነዚህ ሰዎች በዚህ በጧት በሦስት ሰዓት የሰከሩ አይደሉም። ይህ ግን የምታዩት ሁናቴ እግዚአብሔር በነቢዩ ኢዩኤል አማካይነት በመጨረሻው ቀን መንፈሴን በሰው ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ» ብሎ የተናገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ነው። ይህንንም ካለ በኋላ ከነቢያት መጻሕፍት እየጠቀሰ ጌታችን ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ መሆኑን ዘርዝሮ አስረዳ። ከዚያም ይህ የሰሙት ቃል በእርሱ አማካይነት የፈሰሰ መሆኑን ባስረዳ ጊዜ ሰሚዎቹ ምን እናድርግ አሉአቸው። ቅዱስ ጴጥሮስም ንስሓ እንዲገቡ፥ በጌታችን በኢየሱስ እንዲያምኑ፥ እንዲጠመቁም ነገራቸው።

ከሰሚዎቹ በዙዎቹ ቃሉን ተቀብለው ተጠመቁ። በዚያን ቀን ሦስት ሺህ የሚያኽሉ አማኞች ተጨመሩ (የሐ:ሥ:ም:2ቍ:1–13)።

www.ethiopianorthodox.org



የመንፈስ ቅዱስ በደቀ መዛሙርቱ ላይ መውረድ የሐ:ሥ:2፥1 –12

<u>የአማኞች የወንድማማችነትና የኅብረት ኑሮ</u>:- በዚያን ጊዜ በሐዋርያት እጅ ብዙ ተአምራትና ድንቅ ነገሮች ይደረጉ ስለነበር በሁሉም ላይ ፍርሃት አደረባቸው። አማኞች ሁሉ በአንድነት አብረው ይኖሩ ነበር፤ ያላቸውም ነገር ሁሉ የጋራ ነበር። መሬታቸውንና ንብረታቸውን እየሸጡ ገንዘቡን ለእያንዳንዱ እንደሚያስፈልገው ያከፋፍሉ ነበር። በየቀኑ በቤተ መቅደስ በአንድነት ይሰበሰቡ ነበር፤ በቤታቸውም እንጀራ እየቈረሱ በደስታና በጥሩ ልብ ይመገቡ ነበር፤ እግዚአብሔርንም ያመሰግኑ ነበር፤ ሰውም ሁሉ ያከብራቸው ነበር፤ እግዚአብሔርም የሚድኑትን ሰዎች በየቀኑ ወደ ማኅበራቸው ይጨምር ነበር (የሐ:ሥ:ም:2ቍ:43–47)።

<u>የሽባው መፈወስ</u>:- አንድ ቀን ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስና ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ በጸሎት ሰዓት ወደ ቤተ መቅደስ ይሄዱ ነበር፤ ጊዜውም ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ሆኖ ሲወለድ ጀምሮ ሽባ የሆነ አንድ ሰው አዩ፤ እርሱንም ሰዎች በየቀኑ እያመጡ ኣዚያ የሚያስቀምጡት ወደ ቤተ መቅደስ ከሚገቡ ሰዎች ምጽዋት እንዲለምን ነበር። ይህ ሰው ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ዮሐንስ ወደ



ሲገቡ አይቶ ምጽዋት ለመናቸው፤ እነርሱም ሰውዬውን ትኩር ብለው አዩትና ጴጥሮስ «ወደ እኛ ተመልከት አለው። እርሱም ምጽዋት የሚሰጡት መስሎት ትኩር ብሎ አያቸው። ቅድስ ጴጥሮስ ግን ብርና ወርቅ የለኝም፤ ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ፤ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሥና ተራመድ» አለው። ቀኝ እጁንም ይዞ አስነሣው፤ ወዲያውኑ እግሩና ቍርጭምጭሚቱ በረታ። ብድግ ብሎም ቆመ፤ እየተራመደም ከእነርሱ ጋር ወደ ቤተ መቅደስ ገባ፤ እየተራመደና እየዘለለም እግዚአብሔርን ያመሰግን ነበር።



«ጴጥሮስም ብርና ወርቅ የለኝም፤ ይህን ያለኝን ግን እሰጥሃለሁ፤ በናዝሬቱ በኢየሱስ ስም ተነሥና ተመላለስ አለው» ( የሐ:ሥ:

የዳነው ሰው ከጴጥሮስና ከዮሐንስ አልለይም ብሎ ከእነርሱ ጋር ሆኖ ሳለ ሕዝቡ ትኩር ብለው ይመለከቷቸው ነበር። በዚህ ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስ «እናንተ የእስራኤል ሰዎች ሆይ፥ ስለምን በዚህ ነገር ትደነቃላችሁ? እኛ ይህን ያደረ ግነው በራሳችን ኀይል ወይም በራሳችን በጎ ተግባር ይመስላችኋልን? አይደ ለም፤ ይህ የምታዩትና የምታውቁት ሰው ድኖ የበረታው በጌታችን ኢየሱስ ስም በተገኘው እምነት ነው» አላቸው።

www.ethiopianorthodox.org

«አሁንም ወንድሞቼ ሆይ፣ በጌታችን ኢየሱስ ላይ ያደረጋችሁት ነገር እናንተም እንዳለቆቻችሁ ባለማወቅ እንዳደረጋችሁት ዐውቃለሁ። የጌታችን ሕማማትና መሞት ትንቢቱ ይፈጸም ዘንድ ነው። እንግዲህ ኃጢአታችሁ እንዲደመሰስላቸው ንስሓ ገብታችሁ ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ። ነቢያት ሁሉ ስለዚህ ዘመን ትንቢት ተናግረዋል። ጌታችን ኢየሱስም ከሞት ለመነሣቱ እኛ ምስክሮች ነን» ብሎ ለሕዝቡ ተናገረ (የሐ:ሥ:ም:3ቍ:1–10)።

<u>ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ዮሐንስ በአይሁድ ሸንጎ ፊት መቅረባቸው</u>:- ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ዮሐንስ በቤተ መቅደስ ለሕዝቡ ሲናገሩ ሳሉ ካህናትና የቤተ መቅደሱ የዘበኞች አለቃ እንዲሁም ሰዱቃውያውን ወደ እነርሱ መጡ፤ ሁለቱ ሐዋርያት የጌታችን ኢየሱስን ከሞት መነሣት በማስተማራቸውና በዚህም የሙታን ትንሣኤ መኖሩን በማስረዳታቸው ተቈጡ። ስለዚህ ያዙአቸውና ጊዜው መሽቶ ስለነበረ እስከ ማግስቱ ድረስ በወህኒ ቤት እንዲቆዩ አደረጓቸው። ነገር ግን ቃላቸውን ከሰሙት ሰዎች ብዙዎቹ አመኑ፤ የአመኑትም ሰዎች ቍጥር ወደ አምስት ሺህ ከፍ አለ። በማግስቱ የአይሁድ አለቆችና ሽማግሌዎች የኦሪት ሕግ መምህራንም በኢየሩሳሌም ተሰበሰቡ። እነርሱም ሁለቱን ሐዋርያት በመካከላቸው አቁመው ይህን ያደረጋችሁት በምን ኀይልና በማን ስም ነው» ብለው ጠየቁአቸው። ቅዱስ ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ «ይህ ሰው ድኖ በፊታችሁ የቆመው እናንተ በሰቀላችሁትና በመለኮታዊ ኀይሉ ከሞት በተነሣው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንደሆነ ለእስራኤል ሕዝብ ሁሉ የታወቀ ይሁን። ስለዚህ ድኅነት የሚገኘው በእርሱ አማካይነት ብቻ ነው» አለ። ከሸንጎው ወዲያ ገለል አደረጓቸውና እንዲህ ሲሉ ተማከሩ፤ «እንግዲህ በእነዚህ ሰዎች ላይ ምን እናድርግ? ይህ ታላቅ ተአምር በእነርሱ መደረጉ በኢየሩሳሌም ነዋሪዎች ሁሉ ዘንድ ታውቋል፤ ስለዚህ ልንክደው አንችልም። ነገር ግን በሕዝቡ ዘንድ እየተስፋፋ እንዳይሄድ ከእንግዲህ ወዲያ የኢየሱስን ስም በመጥራት ለማንም እንዳይናገሩ በብርቱ እናስጠንቅቃቸው» አሉ።

ከዚህ በኋላ ጠሩአቸውና የኢየሱስን ስም በመጥራት በፍጹም እንዳይናገሩ ወይም እንዳያስተምሩ በጥብቅ አዘዙአቸው። ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ዮሐንስ ግን «ለእግዚአብሔር ከመታዘዝ ይልቅ ለእናንተ መታዘዝ በእግዚአብሔር ፊት ተገቢ ነውን? እስቲ እናንተ ራሳችሁ ፍረዱ። እኛስ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር አንቈጠብም» አሉአቸው። የሕዝብ አለቆችና የሸንጎው አባሎች ቅዱስ ጴጥሮስንና ቅዱስ ዮሐንስን የሚያስቀጣ ምንም ምክንያት ባለማግኘ ታቸውና ሕዝቡንም ስለፈሩ እንደገና አስጠንቅቀው ለቀቁአቸው (የሐ:ሥ: ም 4 ቍ: 1–22)።

## ከዚህ ምዕራፍ የምናገኘው ትምህርት

እግዚአብሔር በአዳምና በሔዋን ኃጢአት ምክንያት ምድርንና ሰውን ከረገመና የሞት ፍርድ ካሳለፈ በኋላ፣ እንዲሁም በሰዎች ኃጢአት ምክንያት በጥፋት ውሃ ምድርንና ነዋሪዎችዋን ካጠፋ በኋላ እንደገና በአብርሃም አማካ ይነት ሕዝቦች እንደሚባረኩ ለአብርሃም ቃል ኪዳን ገባለት።

አዳም አትብላ ተብሎ የታዘዘውን ፍሬ በልቶ ትእዛዝ አፍራሽ በሆነበት አንጻር አብርሃም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ጠባቂ በመሆን ወይም ታዛዥ በመሆን የሚወደውን የሽምግልና ልጁን ለመሠዋት እንኳ ዝግጁ ነበር። በዚህም መሠረት ነው በአዳም ኃጢአት ምክንያት የሰው ዘር ሁሉ የወረሰውን የእርግማንና የሞት ፍርድ በሞቱ ለመሻር ክርስቶስ በለበሰው ሥጋ ከአብ ርሃም ዘር ተወልዶ ወደዚህ ዓለም የመጣው።

አብርሃም የሚሄደው ወዴት መሆኑን ሳያውቅ እግዚአብሔር ያዘዘውን ትእዛዝ በእምነት በማክበር ከትውልድ አገሩ ከዘመዶቹ ተለይቶ ሄደ። አብርሃም በይስሐቅ ዘር ይባልልሃል ተብሎ ቢነገረውም ይስሐቅን ሠዋልኝ ብሎ እግዚአብሔር ባዘዘው ጊዜ እሺ ብሎ ለመሠዋት ተነሣ። በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነት የምንረዳው ለመሥዋዕት የሚሆነው በግ ወዴት አለ? ብሎ ልጁ ይስሐቅ ለጠየቀው ጥያቄ «ልጄ ሆይ፣ ለመሥዋዕት የሚሆነውን በግ እግዚአብሔር ለራሱ ያዘጋጃል ብሎ በሰጠው መልስ ነው።

የአብርሃም የሽምግልና ተወዳጅ ልጅ ይስሐቅ በሚወደው አባቱ ለመሥ ዋዕት መቅረብ እግዚአብሔር አብ የሚወደውን ልጁን እግዚአብሔር ወልድን ለዓለም ቤዛነት ከመስጠቱ ጋር ምሳሌነት አለው። ሌላው በይስሐቅ ምትክ የቀረበው በግ የዓለምን ኃጢአት ለማስወገድ የክርስቶስ ምሳሌ ነው። አብር ሃምም ክርስቶስን በበግ ምሳሌነት አይቶታል።

እግዚአብሔር ለራሱ ሕዝብ መለያ ሲሰጠው ግዝረትን አዘዞታል። ይህም ግዝረት እነዚያ የታዘዙት ሰዎች የቃል ኪዳኑ ወገኖች ለመሆናቸው መለያ ነበር። የሐዲስ ኪዳኑ ሰዎች ለሆንነው ለእኛ ደግሞ ምልክታችን ጥምቀት ነው። በዚህም መሠረት ጥምቀት በግዝረት ፋንታ ተተክቶአል ማለት ነው።


www.ethiopianorthodox.org

አብርሃም ከእግዚአብሔር ጋር ሲነጋገር እግዚአብሔር እኔ የማደርገውን ነገር ከአብርሃም አልሰውርም ማለቱ እግዚአብሔር ምሥጢሩን ለወዳጆቹ ሳይደብቅ የሚገልጥላቸው መሆኑን ያመለክተናል።

አብርሃም ከእግዚአብሔር ጋር ባደረጋቸው ጥያቄዎችና መልሶች በሰዶም ከተማ ውስጥ ዐሥር ደጋግ ሰዎች እንኳ ቢገኙ ለእነዚያ ለዐሥር ሰዎች ሲል ከተማዋን እንደማያጠፋ እግዚአብሔር ለአብርሃም ቃል ገባለት። ይሁን እንጂ በከተማዋ ዐሥር እንኳ ደጋጎች ሰዎች ስላልተገኙ ለመጥፋት በቅታለች። ይህም የሚያመለክተው እግዚአብሔር ለወዳጆቹ ማለት ለደጋግ ሰዎች ምን ያኽል ግምት የሚሰጣቸው መሆኑን ነው። በዚያ ከተማ ግን ጻድቅ ሆኖ የተገኘው ሎጥ ብቻ ስለነበረ እርሱ ከነቤተሰቡ ከከተማው ጥፋት ሊድኑ ችለዋል። ከተማዋ ብትጠፋም እግዚአብሔር ጻድቁን ሰው በማስታወስ አድኖታል። ያ ሀብታም ከመሆኑ የተነሣ ከአብርሃም ጋር አብሮ ሊኖር ያልቻለው ሎጥ በአንድ ቀን ያን ሁሉ ሀብት አጣ። ብልጠት መስሎት የመረጠው አገር ለዚያ ድኽነቱ ምክንያት ሆነበት።

እግዚአብሔር ለአብርሃም በነገረው በዚያ ጊዜ ይስሐቅ መወለዱ የእግዚአብሔር ቃል የጸናና የማይለወጥ መሆኑን ያመለክታል።

ሚስቱ ሣራ ከሞተች በኋላ አብርሃም በጣም አርጅቶ ስለነበረ የልጁን የይስሐቅን ጋብቻ ማየት ፈለገ። ይህም ሲሆን ጣዖት አምላኪዎች ከነበሩት ከከነዓናውያን ጋር ሊያጋባው ባለመፈለጉ ወደ ትውልድ አገሩና ወደዘመዶቹ ሄዶ ለልጁ ለይስሐቅ ሚስት እንዲፈልግለት ታማኝ አሽከሩን አስማለው። አገልጋዩም የማገኛት ልጅ ወደዚህ አገር አልመጣም ያለችኝ እንደሆነሳ ብሎ ለጠየቀው ጥያቄ የማመልከው አምላክ መልአኩን ልኮ መንገድህን ያቃናልሃል ብሎ ጠንካራ እምነቱን አጠናክሮለታል። ጉዳዩም በእምነት ተጀምሮ በእምነት ያለቀ ነው።

የአብርሃም አገልጋይ የአብርሃም ዘመዶች ወደሚገኙበት ወደ ካራን ሄደ። እዚያም በአንድ የውሃ ጉድጓድ አጠገብ ተቀምጦ አምላክ ተልእኮውን ያሳካለት ዘንድ ጸለየ። በጸሎቱም «ውሃ ልትቀዳ የምትመጣ አንዲት ልጃገረድ ውሃ አጠጪኝ ስላት አንተ ጠጣ ለግመሎችህም እቀዳለሁ የምትለኝ እርስዋ ለጌታዬ ሚስትነት የመረጥሃት ትሁን» አለ። ይህን ጸሎት እንደጸለየ ወዲያው ርብቃ መጣች። እርስዋም የአብርሃም ወንድም የናኮር የልጅ ልጅ ነበረች። አገልጋዩም ልክ በጸሎቱ ከእግዚአብሔር ጋር እንደተነጋገረው ውሃ አጠጪኝ



አላት። እርስዋም ውሃ ቀድታ ሰጠችውና ለግመሎችህም ቀድቼ ላጠጣልህ አለችው። በዚህም ምልክት እግዚአብሔር መንገዱን እንዳቃናለት ዐውቆ የማን ልጅ ነሽ ብሎ ጠየቃት። እርስዋም የማን ልጅ እንደሆነች በነገረችው ጊዜ ሁሉን ነገር ላቃናት ለእግዚአብሔር ሰገደ።

አሁን እንግዲህ ከላይ እንደተገለጠው አብርሃም አስቀድሞ በጠንካራው እምነቱ ከአባቱ ቤትና ከትውልድ አገሬ አስወጥቶ ወደዚህ ያመጣኝ፣ የማመልከው አምላክ መንገድህን ያቃናልሃል ሲል ለአገልጋዩ አረጋግጦለታል። አገልጋዩም ቢሆን እምነት በተሞላ ጸሎቱ የእግዚአብሔርን ፈቃድ አምኖአል፤ የእነርሱ የሁለቱ እምነት ጉዳዩን የተቃና አደረገው። ሎጥ ምርጫን ለራሱ ስላደረገ ነው ያልተጠበቀ ችግር የደረሰበት። አብርሃም ግን በሁሉም ነገር የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስለተከተለ ጉዳዮቹ ሁሉ ተቃንተውለት እግዚአብሔር ጠበቀው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ አጽናኙ ሳይመጣላችሁ ከኢየሩሳሌም እንዳትወጡ ብሎአቸው ካረገ በኋላ በዐሥረኛው ቀን የተስፋውን እውነተኛነት አረጋገጠላቸው። በመንፈስ ቅዱስም ተሞሉ። በዚህም የዮሐንስ መጥምቁ «እኔ በውሃ አጠምቃችኋለሁ እርሱ ግን በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል» ያለው ትንቢት ተፈጻሚነትን አገኘ፡ (ማቴ፡ም፡3ቍ፡11)። በመንፈስ ቅዱስም በተሞሉ ጊዜ ከተለያዩ አገሮች መጥተው የነበሩ የአይሁድ እምነት ተከታዮች በየቋንቋዎቻቸው እንዲሰሙ ለማድረግ በተለያዩ ቋንቋዎች የመናገር ስጦታ ተሰጣቸውና ተናገሩ። እነዚህን ቋንቋዎች የተናገሩት ያለምክንያት አልነበረም። ለሐዋርያት አዳዲስ ቋንቋዎች ተገልጠውላቸዋልና እኛም እንናገር ብለን አስፈላጊ ባልሆነበት ጊዜና ቦታ መቀባጠር በሰይጣን ተገፋፍተን የምናከናውነው የግብዝነት ሥራ ከመሆኑ በቀር ምንም መንፈሳዊ ጠቀሜታ እንደሌለው መገንዘብ አለብን። በዕለቱ የሦስት ሺህ ሰዎች ወደ ክርስትናው እምነት መቀላቀል ዋነኛው ምክንያት የሐዋርያቱ በተለያዩ ቋንቋዎች ከተናገሩ በኋላ የሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ገለጻ ማድረግ ነው። ስለዚህ ሐዋርያት በተለያዩ ቋንቋዎች የተናገሩት ያለምክንያት እንዳልነበረ መገንዘብ አለብን።

በአስቆሮታዊው ይሁዳ ምትክ ሰው ለመምረጥ በተነሡ ጊዜ ጸሎት ካደረጉ በኋላ ዕጣ መጣላቸው ምርጫን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ለመተው ብለው ነው። ይህም በዘመነ ኦሪት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመጠየቅ በኡሪምና በቱሚም ይጠቀሙ እንደነበረው ነው (ዘጸ:28፥29–30)።

www.ethiopianorthodox.org

ሐዋርያቱ ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ዮሐንስ በቤተ መቅደሱ አካባቢ ሲወለድ ጀምሮ ሽባ የነበረውን ሰው ከፈወሱ በኋላ በአይሁድ ሸንጎ ፊት በቀረቡ ጊዜ ሐዋርያው ጴጥሮስ ባደረገው ንግግር ያሳየው ድፍረት ሁለት የጌታችን ትንቢቶችን ተፈጻሚነት ያመለክታል።

የመጀመሪያው/ በማርቆስ ወንጌል ም:13ቍ:11 ላይ:- «ሰዎች ይዘው ወደ ፍርድ ሲያቀርቡአችሁ .... የሚናገረው መንፈስ ቅዱስ ነው እንጂ እናንተ አይደላችሁም» የሚለው ነው።

ሁለተኛ/ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያውን ቅዱስ ጴጥሮስን ትወድደኛለህን ብሎ ሦስት ጊዜ ከጠየቀው በኋላ «እውነት እውነት እልሃለሁ፤ አንተ ጕልማሳ ሳለህ ቀበቶህን በገዛ እጅህ ታጥቀህ ወደ ፈለግህበት ትሄድ ነበር፤ በሸመገልህ ጊዜ ግን አንተ እጆችህን ትዘረጋና ሌላ ሰው ያስታጥቅሃል፤ ወደማትፈልግበትም ይወስድሃል» ብሎታል (ዮሐ:ም:21ቍ:18)።

በዚህም መሠረት ሐዋርያቱ ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ዮሐንስ የአይሁድ ሸንጎ ማስጠንቀቂያ በሰጣቸው ጊዜ «እኛስ ከእናንተ ይልቅ ለእግዚአብሔር እንታዘዛለን፤ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር አንቈጠብም» በማለት በድፍረት መልስ ሰጥተዋል። ይህም የሚያመለክተው መንፈስ ቅዱስ ድፍረትንና ዕውቀትን ይሰጣቸው የነበረ መሆኑን ነው።

## ጥያቄዎች

1. መጽሐፍ ቅዱስ ምን ዐይነት መጽሐፍ ነው?
2. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምን እናገኛለን?
3. መጽሐፍ ቅዱስ ስንል ምን ማለታችን ነው?
4. መጽሐፍ ቅዱስ በምንና በምን ይከፈላል?
5. መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ስንት ቋንቋዎች ተተርጉሞአል?
6. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለምንና ምን የሚናገሩ ክፍሎች አሉ?
7. የሃይማኖት ሕጎች ወይም ትእዛዞች በምን ጊዜ ተጀመሩ?
8. ሕጎቹ ባይከበሩ ምንን ያስከትላሉ?
9. አዳምና ሔዋን ማለት እነማን ናቸው?
10. እግዚአብሔር ለእነርሱ ምንን ሰጣቸው?
11. አዳምና ሔዋን በመጀመሪያ ይኖሩበት የነበረው ቦታ ምን ይባላል?
12. ይኖሩበት በነበረው ቦታ ምንና ምን ነበር?
13. እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን ምን ፈቀደላቸው? ምንስ ከለከላቸው?
14. የከለከላቸው ለምንድነው?
15. ትእዛዙን ባለማክበራቸው ምን ደረሰባቸው?
16. ትእዛዙን እንዳይጠብቁ ያደረጋቸው ማነው?
17. በአዳምና በሔዋን ላይ የተላለፈው ፍርድ በእነርሱ ላይ ብቻ ቀረን?
18. ሰው ሁሉ ከአዳምና ከሔዋን የወረሰው ምንድነው?
19. ስንት ዐይነት ሞት አለ? እነርሱስ ምንና ምን ናቸው?
20. በሰው ውስጥ ምን የማይሞት ነገር አለ?
21. አዳምና ሔዋን ከመኖሪያቸው የተባረሩት ለምንድነው?
22. አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር የተደበቁት ለምንድነው?
23. ከአዳምና ሔዋን ታሪክ ምን እንማራለን?
24. ኖኅ ወደ መርከቡ ውስጥ ያስገባው ማንንና ምንን ነው?
25. የጥፋት ውሃ የዘነበው በምን ምክንያት ነው?
26. ከኖኅና ከጥፋት ውሃ ታሪክ ምን መማር ይቻላል?
27. ሰዎች የባቢሎንን ግንብ ለመሥራት ለምን ፈለጉ?
28. እግዚአብሔርስ ለምን ከለከላቸው?
29. ቀደም ብሎ የነበረው የአብርሃም ስም ማን ነበር?
30. እግዚአብሔር ለአብርሃም በመጀመሪያ የገባለት ቃል ኪዳን ምን ብሎ ነው?
31. አብርሃምና ሎጥ ለመለያየት የተስማሙት በምን ምክንያት ነው?
32. ሎጥ በምን ነገር ተሳሳተ?


www.ethiopianorthodox.org

33. አብርሃም ሁሉ ነገር የተቃናለትና እግዚአብሔርም የጠበቀው በም[ን] ምክንያት ነው?

34. ሎጥ የተማረከው እነማን ከእነማን ጋር በተዋጉበት ጦርነት ነው? አሸናፊዎቹስ እነማን ነበሩ?

35. አብርሃም ሎጥን እንደምን አድርጎ ከምርኮ ነጻ አወጣው?

36. አብርሃም ድል አድርጎ በተመለሰ ጊዜ ማንና ማን ተገናኙት?

37. የተገናኙትስ ሰዎች ለምንና ለምን ምክንያት ተገናኙት?

38. እግዚአብሔር ለአብርሃም በራእይ ምን ገለጠለት?

39. አጋርና እስማኤል ለምን ተባረሩ?

40. ሣራ በአጋር ላይ ለምን ጭቄና አበዛችባት?

41. መገረዝ የምን ምልክት ነው?

42. አዲስ የተወለደ ልጅ በተወለደ በስንተኛው ቀን መገረዝ ነበረበት?

43. አብርሃም ያስተናገዳቸው እንግዶች ስንት ነበሩ?

44. ወደ ሰዶም የሄዱት ስንቶቹ ናቸው?

45. ሣራ የሳቀችው ለምንድነው?

46. መሳቅዋን ለምን ካደች?

47. እግዚአብሔር ለአብርሃም ምን ምሥጢር ነገረው?

48. በዚህ ጊዜ አብርሃም እግዚአብሔርን ምን ጉዳይ መላልሶ ጠየቀው?

49. እግዚአብሔር አብርሃምን በምን ፈተነው?

50. ይስሐቅ አብርሃምን ምን ብሎ ጠየቀው?

51. አብርሃም ለይስሐቅ ጥያቄ ምን ብሎ መለሰ?

52. መልአክ አብርሃምን ጠርቶ ምን አለው?

53. አገልጋዩ ተልእኮው እንደሚሳካለት አብርሃም በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነት የገለጠው ምን በማለት ነው?

54. አብርሃም ታማኝ አገልጋዩን ምን ብሎ አስማለው?

55. አገልጋዩስ ጉዳዩ ተሳካለትን?



56. ለይስሐቅ ሚስት የሆነችው ለአብርሃም የነበራት ዝምድና እንዴት ነበር?

57. አብርሃም በስንት ዓመቱ ሞተ?

58. አብርሃም የተቀበረው ማን በተቀረበት ቦታ ነው?

59. አብርሃምን የቀበሩት ማንና ማን ናቸው?

60. የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት የተጻፉት መቼ ነው?

61. እግዚአብሔር ለዘካርያስና ለኤልሣቤጥ ምን አደረገላቸው?

62. ዘካርያስና ኤልሣቤጥ ምን ዐይነት ሰዎች ነበሩ?

63. ዘካርያስ የመልአኩን ብሥራት በመጠራጠሩ ምን ደረሰበት?

64. ይህስ ችግር መቼ ተወገደለት?

65. ዮሐንስ ስለራሱ ምን አለ? ስለ ክርስቶስስ ምን ተናገረ?

66. ከዮሐንስ መጥምቁ ታሪክ ምን እንማራለን?

67. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት ከተነሣ በኋላ ለአርባ ቀኖች ሙሉ ደቀ መዛሙርቱን ምን አስተማራቸው?

68. በይሁዳ ምትክ ማን ተመረጠ?

69. ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉት ጌታ ባረገ በስንተኛው ቀን ነው?

70. ሐዋርያት በአዲስ ቋንቋ በተናገሩ ጊዜ ሰዎች ምን አሉ?

71. ቅዱስ ጴጥሮስ ምን ብሎ ያንዳንድ ሰዎችን ሐሳብ ተቃወመ?

72. በዚያን ቀን ቃሉን ሰምተው የተጠመቁ ስንት ናቸው?

73. ሸባው እንዴት ተፈወሰ?

74. ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ዮሐንስ ምን ስለተናገሩ ነው የሸንጎው አባሎች የተቈጡት?

75. ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ዮሐንስ ለሸንጎው ማስጠንቀቂያ ምን መልስ ሰጡ?

76. ቅዱስ ጴጥሮስንና ቅዱስ ዮሐንስን ለምን ለቀቁአቸው?

77. አዳምና አብርሃም እንደምን ይነጻጸራሉ?

www.ethiopianorthodox.org

78. የአብርሃም ይስሐቅን ለመሠዋት መነሣት ከክርስቶስ ሁናቴ ጋር በምን ይመሳሰላል?

79. የአብርሃም አገልጋይ ለይስሐቅ ሚስት ለመፈለግ ወዴት አገር ሄደ?

80. እዚያ በደረሰ ጊዜ ምን ብሎ ጸለየ?

81. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ከኢየሩሳሌም እንዳይወጡ ያዘዛቸው እስከመቼ ነው?

82. ሐዋርያት አዲስ ቋንቋ የተገለጠላቸው በምን ምክንያት ነው?

83. የማትያስ አመራረጥ ከብሉይ ኪዳን ሁናቴ ጋር በምን ይመሳሰላል?

# ምዕራፍ 3

## ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ

የመልአኩ ብሥራት:- ወደ ዘካርያስ በሄደ በስድስተኛው ወሩ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ተልኮ ወደ ቅድስት ድንግል ማርያም ሄደ። እርሱም «ጸጋን የተሞላሽ ሆይ፥ ደስ ይበልሽ» ብሎ የአክብሮት ሰላምታ አቀረበላት። እግዚአብሔር ከእርስዋ ጋር መሆኑንና ከሴቶች ሁሉ ይበልጥ የተባረከች መሆንዋን ነገራት። «ወንድ ልጅ ትወልጂአለሽ፤ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ» አላት። እርስዋ ግን «እኔ ድንግል ነኝ፤ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል» ብላ ጠየቀችው። መልአኩም በእግዚአብሔር ኀይል በድንግልና እንደምትወልድ ነገራት። «እኔ የእግዚአብሔር ባሪያ ነኝ፤ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ» ብላ እምነትዋን በእግዚአብሔር ላይ አሳረፈች። በዚህም መሠረት በድንግልና እንዳለች ፀነሰች (ሉቃ: ም: 1 ቍ: 26-38)።





የመልአኩ ብሥራት (ሉቃ:1፥ 26–38)

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መወለድ:- ዮሴፍ የድንግል ማርያም እጮኛ ነበር። ድንግል ማርያም ልጅ የመውለጃዋ ጊዜ ሲቃረብ ከሮማ ንጉሥ ነገሥት ትእዛዝ ተላለፈ። በሮማ አገዛዝ ሥር ያሉ ሰዎች ሁሉ ወደ ተወለዱበት አገር ሄደው እንዲመዘገቡ ታዘዙ። በዚያን ጊዜ የእስራኤል ሕዝብ በሮማ አገዛዝ ሥር ነበር። በትእዛዙ መሠረት ለመመዝገብ ድንግል ማርያምና ዮሴፍ ወደ ቤተልሔም ሄዱ። ቤተልሔም ዮሴፍ የተወለደበት አገር ነበር። በቤተልሔም የእንግዳ ማረፊያ ቤት ስላላገኙ በከብቶች ማደሪያ በረት ዐደሩ።

እዚያም በበረት እንዳሉ ድንግል ማርያም የመውለጃዋ ጊዜ በመድረሱ ልጅዋን ወለደች (ሉቃ:ም:2ቍ:1–7)።

www.ethiopianorthodox.org



የጌታችን ልደት (ሉቃ:2፡2–7)

<u>እረኞችና መላእክት</u>:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደበት አከባቢ ከከተማ ውጪ የበግ እረኞች ነበሩ። እነርሱም መንጋቸውን እየጠበቁ ነበሩ። ብርሃን አበራና የእግዚአብሔር መልአክ ታያቸው። ያንን በማየታቸው በጣም ፈሩ። መልአኩ ግን አይዞአችሁ አትፍሩ» አላቸው። እንደገናም «ክርስቶስ ጌታ ዛሬ በዳዊት ከተማ ተወልዶአል» አላቸው። «እዚያ ከሄዳችሁ በጨርቅ የተጠቀለለ ሕፃን በበረት ተኝቶ ታገኛላችሁ» አላቸው። በድንገት ሌሎችንም ብዙ መላእክት አዩ። መላእክቱም እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ነበር። ከዚያ በኋላ መላእክቱ ወደ ሰማይ ወጡ።በዚህ ጊዜ እረኞቹ የተነገረንን ነገር ለማየት እንሂድ ተባባሉና ሄዱ። ሄደውም ድንግል ማርያምንና ዮሴፍን አገኙ። ሕፃኑንም በበረት ተኝቶ አዩት። መልአኩ ስለ ሕፃኑ የነገራቸውን ነገር ሁሉ አወሩ። ወሬውን የሰሙ ሁሉ ተገረሙ። እናቱ ድንግል ማርያም ግን ይህን ሁሉ ነገር በልብዋ ይዛ ታሰላስለው ነበር። እረኞቹም ከመልአኩ የሰሙትና

www.ethiopianorthodox.org



በዐይናቸው ያዩት አንድ ሆኖ ስላገኙት እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ወደ ስፍራቸው ተመለሱ (ሉቃ: ም: 2 ቁ: 8–20)።



እረኞችና መላእክት (ሉቃ:2 ፡8–14)።

<u>ግዝረት</u>:- ከስምንት ቀን በኋላ ሕፃኑ የሚገረዝበት ጊዜ ነበር። በግዝረቱ ሥነ ሥርዓት ስሙን ኢየሱስ አሉት። ይህም አስቀድሞ መልአኩ ያወጣለት ስም ነው። መልአኩ ገብርኤል «ወንድ ልጅ ትወልጂአለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ» ብሎ ለድንግል ማርያም ነግሮአት ነበር (ሉቃ:ም:2ቁ:21)።

<u>ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ቤተ መቅደስ መወሰዱ</u> :- በኦሪት ሕግ መሠረት የመንጻት ሥርዓት የሚፈጸምበት ጊዜ ደረሰ። ሕፃኑን ለእግዚአብሔር ለማቅረብ ወደ ቤተ መቅደስ ይዘውት ሄዱ። በሕጉ መሠረት ወንድ የሆነ በኩር

ሁሉ ለእግዚአብሔር ተሰጥቶ የተቀደሰ መሆን ነበረበት። ጌታችን ኢየሱስም በኩር ስለነበረ ወደ ቤተ መቅደስ ተወሰደ።

ሕይወቱን ለእግዚአብሔር የሰጠ ስምዖን የተባለ አንድ ጻድቅ ሰው ነበር። ይህም ሰው የጌታችን ኢየሱስን መወለድ ሳያይ እንደማይሞት መንፈስ ቅዱስ ገልጦለት ነበር። ሕፃን ጌታችን ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅደስ በተወሰደበት ቀን መንፈስ ቅዱስ አነሣሣውና ወደ ቤተ መቅደስ ሄደ።: ስምዖንም ሕፃኑን ታቅፎ እንዲህ አለ።

«ጌታ ሆይ፥ የሰጠኸኝ ተስፋ አሁን ተፈጽሞአል።

ማዳንህን በዐይኔ አይቼአለሁ።

ከእንግዲህስ በሰላም አሰናብተኝ» (ሉቃ:ም:2ቍ: 29–32)።

ይህንንም ከተናገረ በኋላ ለድንግል ማርያም ትንቢት ነግሮአታል። «ሕፃኑ ለብዙዎች የመጥፋት፥ ለብዙዎች ደግሞ የመዳን ምልክት ይሆናል» ብሎአታል። ወደፊት በጣም የምታዝንበት ጊዜ እንደሚመጣም ነገራት።

በዚያም ሐና የተባለች ሌላ ነቢያት መጥታ ስለሕፃኑ እግዚአብሔርን አመሰገነች (ሉቃ:ም:2 ቍ:22–38)።





የጌታችን ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅደስ መወሰድ (ሉቃ:2፣22–38)።

<u>ከምሥራቅ የመጡ ጠቢባን (የከዋክብት ተመራማሪዎች)</u>:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደው በይሁዳ ንጉሥ በሄሮድስ ዘመን ነው። በዚያን ጊዜ የምሥራቅ አገር ጠቢባን ወደ ኢየሩሳሌም መጡ። የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ የት ነው ብለው ጠየቁ። እነርሱም ኮከቡን አይተን ልንሰግድለት መጥተናል አሉ። ንጉሥ ሄሮድስ ይህን ነገር በሰማ ጊዜ ደነገጠ። ስለዚህ ሄሮድስ ክርስቶስ የት እንደሚወለድ የሃይማኖት ሰዎችን ጠየቀ። እነርሱም በትንቢቱ መሠረት ክርስቶስ የሚወለደው በቤተልሔም ነው አሉት። በዚህ ጊዜ ጠቢባኑን አስጠርቶ ኮከቡን መቼ እንዳዩ ጠየቃቸውና ተረዳ። ከዚያም ወደ ቤተልሔም ላካቸው። ሕፃኑን ካገኛችሁት ወደ እኔ ተመልሳችሁ ንገሩኝ አላቸው።

የከዋክብት ተመራማሪዎቹ ከሄሮድስ ዘንድ እንደወጡ ያ ቀድሞ ያዩት ኮከብ እንደገና ታያቸው። ኮከቡም ሕፃኑ ወዳለበተ ቤት እስኪደርሱ ድረስ መራቸው። ወደ ቤት ገብተው ተንበርክከው ሰገዱለት። ሳጥናቸውንም ከፍ

www.ethiopianorthodox.org

ተው የወርቅ፥ የዕጣንና የከርቤ ስጦታ አቀረቡለት። እግዚአብሔርም በሕ
ወደ ሄሮድስ እንዳይመለሱ ስላስጠነቀቃቸው በሌላ መንገድ ወደ አገራ
ተመለሱ (ማቴ:ም2ቊ11–12)።



ከምሥራቅ የመጡ ጠቢባን (ማቴ:2፡1–15)።

ወደ ግብጽ ሽሽት:- የከዋክብት ተመራማሪቹ ከሄዱ በኋላ እግዚአብ
ለዮሴፍ በሕልም ተገለጠለት። ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው ስለሚፈልግ ሕ
ንና እናቱን ይዘህ ወደ ግብጽ ሽሽ፤ እስክነግርህም ድረስ እዚያ ቆይ አለ
ዮሴፍም ሕፃኑንና እናቱን ይዞ ወደ ግብጽ ሄደ (ማቴ:ም: 2ቊ: 13–15)

ሄሮድስ ሕፃናትን ማስፈጀቱ:- ሄሮድስ የከዋክብት ተመራማሪዎቹ
እርሱ እንዳልተመለሱ ባየ ጊዜ በጣም ተቈጣ: ኮከቡ የታየበትን ጊዜ ከከዋክ

www.ethiopianorthodox.org



ተመራማሪዎቹ ጠይቆ ተረድቶት ነበር። በዚህም መሠረት ወታደሮቹን ወደ
ቤተልሔምና በዙሪያዋም ወደ አሉት መንደሮች ላከ። ዕድሜአቸው ሁለት
ዓመትና ከዚያ በታች የሆኑትን ወንዶች ሕፃናት አስገደለ። ስለዚህም ጉዳይ
እግዚአብሔር ነቢያት አስቀድመው ትንቢት ተናግረው ነበር። በሄሮድስም
ድርጊት ትንቢቱ ተፈጽሞአል (ማቴ:ም: 2ቊ:16–18)።

ከግብጽ መመለስ:- ሄሮድስ ከሞተ በኋላ የእግዚአብሔር መልአክ ለዮሴፍ
ግብጽ በሕልም ተገለጠለት። ሕፃኑን ለመግደል የሚፈልጉት ሰዎች ሞተ
ዋል፤ ስለዚህ ሕፃኑን ከእናቱ ጋር ይዘህ ወደ እስራኤል አገር ተመለስ አለው።
ዮሴፍም ሕፃኑን ከእናቱ ጋር ይዞ ወደ እስራኤል አገር ተመለሰ።: መኖሪያውም
ገሊላ ክፍል በምትገኘው በናዝሬት ከተማ ሆነ (ማቴ:ም:2ቊ19–23)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተ መቅደስ:- ዮሴፍና ድንግል ማርያም
የዓመቱ የፋሲካን በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም ይሄዱ ነበር። በአንድ
ፋሲካ በዓል ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ የዐሥራ ሁለት ዓመት ልጅ ነበር። በዚያን
ጊዜ እንደልማዳቸው ዮሴፍና ድንግል ማርያም ወደ ኢየሩሳሌም ሄዱ።
ጌታችን ኢየሱስም አብሮአቸው ነበር። በዓሉ ከተፈጸመ በኋላ ወደ ቤታቸው
ሲመለሱ ከእነርሱ ጋር አልነበረም። እነርሱ ከሌሎች ሰዎች ጋር አብሮ የሚሄድ
መሰላቸው። የአንድ ቀን መንገድ ከሄዱ በኋላ ቢፈልጉ አጡት። በዚህም ምክን
ት ወደ ኢየሩሳሌም ተመልሰው ይፈልጉት ጀመር። ከሦስት ቀን ፍለጋ በኋላ
ቤተ መቅደስ አገኙት። እዚያም በሊቃውንት መካከል ተቀምጦ ሲያዳምጥና
ያቄ ሲጠይቃቸው ነበር። የሰሙትም ሁሉ በማስተዋሉ ተገረሙ። ድንግል
ርያምም «ምነው ልጄ እንዲህ አደረግኸን? አባትህና እኔ ተጨንቀን ስንፈ
ግህ ነበር» አላቸው። እርሱም «ለምን ፈለጋችሁኝ? እኔ በአባቴ ቤት መሆን
ንደሚገባኝ አታውቁም ኖሮአልን?» አላቸው። እነርሱ ግን እርሱ ያለውን
ስተዋሉም። ከዚያ በኋላ ከእነርሱ ጋር አብሮ ተመለሰ። እናቱም ይህን ሁሉ
ልብዋ ትይዘው ነበር (ሉ:ቃ:ም: 2ቊ: 41–52)።



ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተ መቅደስ

## የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ እጅ ለመጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ሄደ። ዮሐንስ ግን እኔ በአንተ እጅ እጠመቃለሁ እንጂ እንዴት አንተ በእኔ እጅ ለመጠመቅ ወደ እኔ ትመጣለህ ብሎ ከለከለው። ጌታችን ግን የጽድቅን ነገር ሁሉ እንዲህ መፈጸም ስለሚገባን አሁንስ ተው አለው። ዮሐንስም በጉዳዩ ተስማምቶ ጌታችንን አጠመቀው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተጠምቆ ከውሃው እንደወጣ ወዲያውኑ ሰማይ ተከፈተ፤ የእግዚአብሔርም መንፈስ በርግብ አምሳል ወርዶ በጌታችን ላይ ሲያርፍበት አየ። በዚያኑ ጊዜ ደግሞ «በእርሱ ደስ የሚለኝ፥ የምወደው ልጄ ይህ ነው» የሚል ድምፅ ከሰማይ መጣ።





የጌታችን ጥምቀት (ሉቃ.ም.3 ፥ 21–22)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ወንዝ መጠመቁ እስራኤላውያን የዮርዳኖስን ወንዝ ከመሻገራቸው ጋር ምሳሌነት አለው። እስራኤላውያን ዮርዳኖስን ተሻግረው የከነዓንን ምድር እንደወረሱ ጌታችን በቀደሰልን በጥምቀት አማካይነትም ድኅነትና ሰማያዊ ሀብት ለመገኘቱ ምሳሌ ነው።

በጌታችን ጥምቀት ጊዜ ምሥጢረ ሥላሴ ማለት የእግዚአብሔር ሦስትነት ምሥጢር ተገልጦአል። አብ በሰማይ ሆኖ «የምወደው ልጄ ይህ ነው» የሚል ድምፅ አሰምቶአል። ወልድ በዮርዳኖስ ተጠምቆ ሲወጣ ታይቶአል። መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በርግብ አምሳል ሆኖ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ሲያርፍ ታይቶአል።

ጥምቀት ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምንም የሚያስፈልገው አልነበረም። እርሱ የወረሰው ወይም ራሱ ፈጽሞት የሚናዘዘው ኃጢአት ስለሌለበት ጥምቀት ለእርሱ ምንም ጠቀሜታ አልነበረውም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ

www.ethiopianorthodox.org

የተጠመቀው ግን (አንድ) ለጥምቀት ሥርዓት ክብር (ኀይል) ለመስጠት፥ (ሁለት) ለእኛ አርአያ ለመሆን ነው (ማቴ:ም:3ቍ:13–16)።

<u>የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መፈተን</u>

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተጠመቀ በኋላ በዲያብሎስ ለመፈተን ወደ በረሓ ሄደ። እዚያም አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከጾመ በኋላ ራበው። በዚህ ጊዜ ፈታኙ ዲያብሎስ ወደ እርሱ መጥቶ «አንተ በእውነተ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ ይህን ድንጋይ ዳቦ እንዲሆን እዘዝ» አለው። ጌታችን ግን መልሶ «ሰው በእግዚአብሔር ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል» አለው።

ከዚህ በኋላ ዲያብሎስ ጌታችንን ወደ ኢየሩሳሌም ወሰደው። በቤተ መቅደስ ጫፍ ላይ አቁሞ «በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ ራስህን ወደታች ጣል፤ አንተን እንዲጠብቁ እግዚአብሔር መላእክቱን ያዝዝልሃል፤ እግርህም በድንጋይ እንዳይሰናከል በእጃቸው ይዘው ይደግፉሃል ተብሎ ተጽፎአል» አለው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ «እግዚአብሔር አምላክህን አትፈታተነው ተብሎ ተጽፎአል» አለው።

ቀጥሎም ዲያብሎስ ጌታችንን ከፍ ወዳለ ተራራ አወጣው። እዚያም የዓለምን መንግሥታት ከነክብራቸው አሳየው። «ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ ለአንተ እሰጥሃለሁ፤ ይህ ሁሉ ለእኔ የተሰጠኝ ስለሆነ እኔ ለፈለግሁት ሰው እሰጠዋለሁ» አለው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ግን «ሂድ አንተ ሰይጣን ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ብቻ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአል» አለው (ማቴ:ም:4ቍ1–11)።

ዲያብሎስም ጌታችንን በብዙ መንገድ ከፈተነው በኋላ ለጊዜው ትቶት ሄደ።

መንፈስ ወደ በረሓ ወሰደው ሲል ምን ማለት ነው? የእግዚአብሔር መንፈስ፥ የራሱ መንፈስ ወይም ፈቃድ፥ ማለት ራሱ ፈቅዶ ሄደ ማለት ነው። ይኸውም አንዳንድ ጊዜ ስለሰዎች ስንናገር ስሜቱ አነሣሣው እንደምንለው አባባል ያለ ነው።

በይፋ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት አርባ ቀንና አርባ ሌሊት መጾሙ ሥራችንን በተለየም መንፈሳዊ ተግባር ለመፈጸም በምንነሣበት ጊዜ ጾምንና ጸሎትን እንድናስቀድም ለያስተምረን ፈቅዶ ነው። በሌላም በኩል አርባ ቀኖችን መጾሙ ሙሴ ሕገ ኦሪትን ሲቀበል አርባ ቀኖችን እንደጾመ ጌታችንም ሕገ ወንጌልን መመሥረት ሲጀምር አርባ ቀኖችን ከመጾሙ ጋር ምሳሌነት አለው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ መሆኑ እየታወቀ እንዴት መፈተን አስፈለገው? ሰይጣንስ ቢሆን እንዴት ጌታችንን ለመፈተን ደፈረ? ለዚህስ ጉዳይ ወደ በረሓ መሄድ ለምን አስፈለገው?

ወደ በረሓ መሄዱ በረሓ ምንም ዓለማዊ ነገር የሌለበትና የማይታይበት ስለሆነ እኛም የሰይጣንን ፈተና ድል ለመንሣት የምንችለው ከዚህ ዓለም ብልጭልጭና ከአታላይነትዋ ርቀን መሆን እንዳለበት ሲያመለክተን ነው። አርባ ቀኖች ጾሞ ቢራብም ጌታችን በረሀብ ምክንያት በፈተና የማይሸነፍ መሆኑን ለማሳየትና ለእኛም አርአያ ለመሆን ነው እንጂ መጾሙም ሆነ መፈተኑ ለጌታችን ምንም የሚፈይድለት ነገር ኖሮት አይደለም። ሰይጣን ጌታችንን ሊፈትነው የደፈረው አንድም ጌታችን በተዋሕዶ የመለኮት ባሕርይ ያለው መሆኑን ስላላወቀ ወይም ስለተጠራጠረ ነው፤ ወይም ደግሞ ምንም እንኳ ተዋሕዶው የማይለያይ ነው ተብሎ ቢታመን ጌታችን በመለኮት ተውጦ ያል ጠፋና ያልተቀላቀለ የትስብእት ባሕርይ ያለው በመሆኑ በትስብእት ባሕርዩ አሸንፈ ዋለሁ ብሎ ተስፋ በማድረግ ነው። ስለዚህም ነው ከአርባ ቀንና አርባ ሌሊት ጾም በኋላ በተራበበት ጊዜ ደካማ ጐን ያገኘ መስሎት ድንጋዩን እንጀራ እንዲሆን እዘዝ ያለው።

ሰይጣንም ጌታችንን የተፈታተነው በሦት ትላልቅ የኃጢአት መሠረቶች ነው። እነርሱም:- ሦስት፥ ትዕቢትና ገንዘብ ወዳድነት ናቸው።

ጌታችን አርባ ቀንና ሌሊት ከጾመ በኋላ ሰይጣን ድንጋዩን ዳቦ እንዲሆን እዘዝ ያለው አዳምን በምግብ ፈተና እንደጣለው ጌታችንንም በዚያው መንገድ አሸንፈዋለሁ ብሎ በማሰብ ነው። ዋናው ዓላማው ግን ለእርሱ እንደመሰለው ጌታችንን ከመጣበት ከአዳኝነት ዕቅድ በማዘናጋት በተአምራት አድራጊነት፥ ብቻ በሕዝብ ዘንድ ታውቂ ወይም ዝነኛ አድርጎ ለማስቀረት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ እርሱ ያቀረበለትን የድርጊት ሐሳብ ቢፈጽም የሰይጣን ታዛዥ ሆነ ለማለት፥ ባይፈጽም ደግሞ ለማድረግ የማይችል ደካማ ነው ለማሰኘት አለበለ ዚያም ሌላ ወጥመድ ሊፈልግለት ብሎ ነው።


www.ethiopianorthodox.org

ይህ የመጀመሪያው ፈተና በሥጋዊ ፍላጎት ወይም በስስት ላይ የተመሠረተ ነው። ጌታችን ግን ሰይጣንን ድል የነሣው «አርባ ቀን በመጾሜና በመራበ የግድ ምግብ አስፈልጎኝ ድንጋዩን ዳቦ የማደርግ አይምሰልህ፤ ሰው የሚኖረው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃልም ሁሉ ነው እንጂ በምግብ ብቻ አለመሆኑ በቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፎ ይገኛል» በማለት ነው።

ሁለተኛው ፈተና ደግሞ በቤተ መቅደስ ጫፍ ላይ አቁሞ «አንተን እን ዲጠብቁ እግዚአብሔር መላእክቱን እንደሚልክና እግርህም በድንጋይ እን ዳይሰናከል በእጃቸው ይዘው እንደሚደግፉህ የተጻፈ ስለሆነ የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንክ ራስህን ወደ ታች ወርውር» አለው። ጌታችን ግን «እግዚ አብሔር አምላክህን አትፈታተነው ተብሎ ተጽፎአል» ብሎ መለሰለት። የሰይ ጣን ዓላማ ከላይ በመጀመሪያው ፈተና ላይ እንደተገለጠው ሆኖ ይህ ደግሞ በትዕቢት ኃጢአት ላይ የተመሠረተ ፈተና ነው።

ሦስተኛው ፈተና ከፍ ባለ ተራራ ጫፍ ላይ አውጥቶ የዓለምን መንግሥ ታትና ክብራቸውን ካሳየው በኋላ «ተደፍተህ ብትሰግድልኝ እኔ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ፤ እነዚህ ሁሉ ለእኔ የተሰጡኝ ስለሆነ እኔም ለፈለግሁት ለመስጠት መብት አለኝ» አለው። ጌታችን በመለኮታዊ ባሕርዩ ለመለኮታዊ ክብሩ ቀናተኛ በመሆኑ «አንተ ሰይጣን ከአጠገቤ ሂድ» ብሎ ከገሠጸው በኋላ «ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ስገድ፤ እርሱንም ብቻ አምልክ» ተብሎ ተጽ ፎአል በማለት አባረረው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መጻሕፍትን በመጥቀስ መልስ መስጠቱ ሰይጣን ለፈተናው የሚያመች መስሎ በታየው መንገድ ከመጻሕፍት ቀንጠብ አድርጎ በመጥቀስ አቅርቦ ስለነበረ ነው። የጌታም አባባል አንተ በጥራዝ ነጠቅነት ጥቅስ ያቀረብከው ስላልገባህ ነው እንጂ እንደዚህ የሚል ጥቅስም አለ ለማለት ነው። ይህም እሾኽን ማውጣት በእሾኽ ነው እንደተባለው ነው (ማቴ: ም: 4ቍ: 1–17)።

<u>ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የማስተማር ሥራውን መጀመሩ</u>:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዲያብሎስ ተፈትኖ ከተመለሰ በኋላ የማስተማር ሥራውን ጀመረ። ማስተማርም የጀመረው የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ በማለት ነው። በአይሁድ ጸሎት ቤቶች (ምኵራቦች) እየገባ ያስተምር ነበር። ዝናውም በአገሩ ሁሉ ተሰማ። ሁሉም በትምህርቱ ያደንቁት ነበር። ማስተማሩን በጀመረበት ጊዜ ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ነበር (ሉቃ:3፥23)።



**አንድ ቀን ጌታችን** ኢየሱስ ክርስቶስ በጌንሴሬጥ ባሕር አጠገብ ሲያልፍ **ሁለት ወንድማማቾችን አየ።** እነርሱም ጴጥሮስና እንድርያስ የሚባሉ ዓሣ **አጥማጆች ነበሩ።** እርሱም ባያቸው ጊዜ ተከተሉኝ አላቸው። እነርሱም ሁሉን **ነገር ትተው ተከተሉት ።**

**ከዚያም እልፍ ብሎ ሌሎች** ሁለት ወንድማማቾችን **አየ።** እነርሱም **ያዕቆብና ዮሐንስ ይባሉ ነበር።** ከአባታቸው ከዘብዴዎስ ጋር መረባቸውን እያ **በጁ ሳሉ ጌታችን ተከተሉኝ አላቸው።** እነርሱም አባታቸውንና ጀልባዋን **ትተው ተከተሉት** (ማቴ:ም:4:ቍ:12 –22)።

## የጌታችን ተአምራት

<u>ውሃውን ወደ ወይንነት የመለወጥ ተአምር</u>:- የገሊላ ክፍል በሆነች ቃና **በምትባል መንደር የሠርግ ግብዣ ነበር።** በዚህ ግብዣ ጌታችንና እናቱ ድንግል **ማርያም እንዲሁም ደቀ** መዛሙርቱ ተጠርተው ነበር። ጋባዦቹ የወይን ጠጁ **እንዳለቀባቸው ድንግል** ማርያም አይታ የወይን ጠጁ ያለቀባቸው መሆኑን **ለጌታችን ነገረችው።** ከዚያም ለአገልጋዮቹ እርሱ የሚላቸውን እንዲያደርጉ **ነገረቻቸው። ጌታም አገልጋዮቹን** እዚያ በነበሩት ስድስት ጋኖች ውስጥ ውሃ **እንዲሞሉባቸው ነገራቸው። አገልጋዮቹም** ውሃውን ከሞሉ በኋላ ያየተሞላ **ውሃ ወደ ወይንነት ተለወጠ።** ጌታም ቀድተው ለግብቻው ሮላይ እንዲሰና **ነገራቸው። የግብቻው ሮላይም** ወይን ጠጁ ቀድሞ ከነበረውና ካለቀው የተሻለ ሆኖ በመገኘቱና ከወዴት እንደመጣም ባለማወቁ ተገረመ (ዮሐ:ም: 2ቍ: 1–12)።

www.ethiopianorthodox.org



www.ethiopianorthodox.org



ጌታችን ውሃውን ወደ ወይንነት የለወጠበት ተአምር (ዮሐ:ም:2ቍ:1–11)

<u>የብዙ ዓሣዎች መገኘት ተአምር:-</u> አንድ ቀን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጌንሴሬጥ ባሕር ዳር ቆሞ ነበር። ብዙ ሰዎችም የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ይጋፉ ነበር። በባሕሩ አጠገብ ሁለት ጀልባዎች ቆመዋል። ዓሣ አጥማጆቹ በጀልባው ላይ ወርደው መረባቸውን በማጠብ ላይ ናቸው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የስምዖን ወደሆነችው ወደ አንዲቱ ጀልባ ገባ። ከዚያም በጀልባዋ ላይ ሆኖ ሕዝቡን አስተማረ። ማስተማሩንም ከጨረሰ በኋላ ስምዖን ንና ጓደኞቹን መረባቸውን ጥለው ዓሣ እንዲያጠምዱ አዘዛቸው። ስምዖን ግን ሌሊቱን ሙሉ ሲለፉ አድረው ምንም ዓሣ አለመያዛቸውን ነገረው። ይሁን እንጂ የጌታችን የኢየሱስን ትእዛዝ ለማክበር መረባቸውን እንደሚጥሉ ታዛዥነቱን ከገለጠ በኋላ መረባቸውን ጣሉ። መረቡንም በጣሉ ጊዜ መረቡ ለመቀደድ እስኪደርስ ድረስ ብዙ ዓሣዎችን ያዙ። ስለዚህም መጐተት አቅቶአቸው በሌላው ጀልባ የነበሩት ጓደኞቻቸው መጥተው ረዱአቸው (ሉቃ: ም: 5 ቍ 1–3)።



<u>አምስት ሺህ ሰዎችን የመመገብ ተአምር:-</u> ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ አንድ ገለልተኛ ቦታ መሄዱን ሰዎች በሰሙ ጊዜ ከየከተሞቹ ወጥተው በእግር ተከተሉት። ከጀልባም በወረደ ጊዜ ብዙዎች ሰዎችን አይቶ ራራላቸው። በሽተኞቻቸውንም ፈወሰ። በመሸም ጊዜ የጌታችን ደቀ መዛሙርት ቀርበው ሕዝቡን እንዲያሰናብት ነገሩት። ጌታችን ግን እናንት የሚበሉትን ስጡአቸው አላቸው። ደቀ መዛሙርቱም ከአምስት እንጀራና ከሁለት ዓሣ በቀር ሌላ ምንም እንደሌላቸው ነገሩት። እርሱም እነዚያን አምስት እንጀራና ሁለት ዓሣ ወደ እኔ አምጡልኝ አላቸው። ከዚያ በኋላ ሕዝቡን በመስኩ ላይ እንዲያ ስቀምጡ አዘዘ። አምስቱን እንጀራና ሁለቱን ዓሣ አንሥቶ ወደ ሰማይ አሸቅቦ እየና የምስጋና ጸሎት አደረገ። ከዚያም ቍርሶ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጣቸው። ደቀ መዛሙርቱም ለሰዎች ሁሉ ዐደሉ። ሁሉም በልተው ከጠገቡ በኋላ የተረፉ ቸውን ዐሥራ ሁለት መሶብ ሞልተው አነሡ። ሴቶችና ሕፃናት ሳይቈጠሩ የበሉት ሰዎች (ወንዶች) ብዛት አምስት ሺህ የሚያኽሉ ነበሩ (ማቴ: ም:14 ቍ:13–21)።



ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አምስት ሺህ ሰዎችን የመመገቡ ተአምር (ማቴ:14፥13–21)



www.ethiopianorthodox.org

<u>ማዕበሉን ጸጥ የማድረግ ተአምር</u>:- አንድ ቀን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በጀልባ ተሳፍሮ ይሄድ ነበር። እየሄዱም ሳለ ትል ዐውሎ ነፋስ ተነሣ። በዚህ ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተኝቶ ነበር ማዕበሉም ጀልባውን ስለሸፈነው ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ ሄደው እርዳ ጠየቁ። ጌታችን ኢየሱስም ተነሥቶ እምነት የጐዳላቸው በመሆናቸው ወቀ ቸው። ከዚያ በኋላ ባሕሩንና ነፋሱን ገሥጾ ጸጥ አሰኛቸው። ሰዎቹም እጅ ተደንቀው ይህ ባሕርና ነፋስ እንኳ የሚታዘዙለት ምን ዐይነት ሰው ነው ተባባሉ (ማቴ:8፥23–27)።

የተአምራቱ ታሪካዊ አጠያያቂነት መንፈሳዊ ዋጋውን የሚያሳጣው አይ ለም። ተአምራትን ደግሞ ከጌታችን የሕይወት ታሪክ ልንለየው አንችልም በተአምራት ሥራ ላይ ከተፈጥሮ ሕግ ውጪ የሆኑ ድርጊቶች እንዴት ሊ ጸሙ ይችላሉ የሚል ጥያቄና ክርክር ቢነሣ ይህ እንዲህ ዐይነቱ ተቃው የሚነሣው እምነተ ደካሞች ከሆኑ ሰዎች ነው እንጂ ከሌላ አይደለም። የተፈጥ ሕግ የምንለው፥ ሁናቴዎች የሚፈጸሙት በዚህ ዐይነት ነው ብለን በየጊዜ ያስተዋልናቸውን ጉዳዮች በማሰባሰብ ነው እንጂ በእግዚአብሔር ዘንድ እነዚ ጉዳዮች በፍጹም የማይለወጡ ቀኖናዎች ሆነው አይደለም። ከሁሉ አስቀድ ተአምራትን የሚያደርግ እግዚአብሔር ራሱ ወይም ለዚያ ተግባር እግ አብሔር የመረጣቸው ሰዎች መሆናቸውን መገንዘብ አለብን። የተፈጥ ሕግንና ሌሎችንም ነገሮች ሁሉ የፈጠረ እግዚአብሔር መሆኑን እናስታው እነዚህን ሕጎች የፈጠረ እግዚአብሔር እርሱ በፈቀደ ጊዜ አካሄዱን ለው የፈቀደውን ሊያደርግ ስለሚችል በተአምራት መገረም አይኖርብንም። እም ታችን በእርሱ ላይ ጠንካራ ከሆነ ደግሞ በተአምራታዊ ድርጊት አንገረምም

## <u>የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌዎች</u>:-

<u>የዘሪው ምሳሌ</u>:- ብዙ ሰዎች ከከተማው በተሰባሰቡ ጊዜ ጌታችን ኢየሱ ክርስቶስ የሚከተለውን ምሳሌ ነገራቸው፤

አንድ ገበሬ ዘሩን ሊዘራ ወጣ። ሲዘራም ሳለ አንዳንዱ ዘር በመንገድ ላ ወደቀና ወፎች መጥተው በሉት። ሌላው ዘር በጭንጫማ መሬት ላይ ወደቀ በበቀለ ጊዜ መሬቱ ጥልቀት ስላልነበረው ቡቃያው ደረቀ። ሌላው ዘር በእሾ መካከል ወደቀና እሾኹ ዐንቆ አስቀረው። ሌላው ዘር ግን በመልካም መሬ ላይ ወድቆ በቀለና ብዙ ፍሬ አፈራ። አንዱ መቶ፥ አንዱ ሥልሳ፥ አንዱ ሠላሳ ፍሬ ሰጠ። ሰሚ ጆሮ ያለው ይሰማ አለ።



ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዝርዝር እንዳስረዳው በመንገድ ዳር የወደቀው ዘር የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ቃለ ሰምቶ የማያስተውለውን ሰው ነው። በጭንጫማ መሬት ላይ የተዘራው የሚያመለክተው ቃሉን ሰምቶ ወዲያው በደስታ የሚቀበለውንና ሥር ስለሌለው ወዲያውኑ የሚሰናከለውን ሰው ነው። በእሾኻማ ቍጥቋጦ መካከል የተዘራው ደግሞ የሚያመለክተው ቃሉን ለጊዜው የሚሰማውን ሰው ነው። ነገር ግን የዚህ ዓለም አሳብና የሀብት ፍቅር ቃሉን ስለሚያንቀው ያለ ፍሬ ይቀራል። በመልካም መሬት ላይ የተዘራው ግን ቃሉን ሰምቶ በማስተዋል የሚቀበለውን ሰው ነው (ማቴ: ም:13 ቍ:1–9፥18–23)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳብራራው ዘር የተባለው የእግዘአብሔር ቃል ነው።

<u>በአለት ወይም በአሸዋ ላይ የተሠሩ ቤቶች ምሳሌ</u>:- አንድ ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር ቀጥሎ ያለውን ምሳሌ ተናግሮአል።

ቃሌን ሰምቶ በሥራ ላይ የሚያውለው ቤቱን በአለት ላይ የሠራውን ብልኅ ሰው ይመስላል። ዝናብ ዘነበ፤ ጐርፍ ጐረፈ ነፋስም ነፈሰ፤ ያንንም ቤት ገፋው ግን ያን ቤት ሊያንቀሳቅሰው አልቻለም። ይህም የሆነው በአለት ላይ ስለተሠራ ነው።

ቃሌን ሰምቶ በሥራ ላይ የማያውለው ግን ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራውን ሞኝ ሰው ይመስላል። ዘናብ ዘነበ፤ ጐርፍም ጐረፈ፤ ነፋስም ነፈሰ፤ ያን ቤት ገፋው፤ ቤቱ ወዲያው ወደቀ፤ አወዳደቁም አጅግ የከፋ ሆነ።

ይህም አባባሉ የሚያመለክተው የመጀመሪያው ምሳሌ በውሳኔው ማለት በእምነቱ ለመጽናት ጥንካሬ ያለውን ብርቱ ሰውን ነው። እንደ ኢዮብ ያለ እምቢ ብሎ ሰይጣንን የማሸነፍ ጥንካሬ ማለት ነው። ወይም እንደ አብርሃም ያለ ሁሉን ነገር ትቶ ለእግዚአብሔር መታዘዝ ማለት ነው። ሌሎችንም መንፈስ ጠንካሮች የሆኑ ባሕታውያንን፥ ሰማዕታትንና ቅዱሳንን መጥቀስ ይቻላል። ብዙዎቹ ሰማዕታት በእምነታቸው ስለጸኑ ነው ውድ ሕይወታቸውን ከመሠዋት ወደ ኋላ ያላሉት። ጌታችን በአለት ላይ የተመሠረተ ቤት ያለው እንደ እነዚህ ያሉትን ሰዎች የእምነት ጥንካሬ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

በአንጻሩ ደግሞ በአሸዋ ላይ የተመሠረተ ቤት ያለው አንዳች ፈተና ወይም ችግር በሚደርስባቸው ጊዜ በቀላሉ ተሸንፈው አምላካቸውን ከማምለክ ሸርተት የሚሉትን መንፈስ ደካሞችን ነው (ማቴ:ም:7ቍ:24-29)።

<u>ጠፍቶ የተገኘው ልጅ ምሳሌ</u>:- አንድ ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት። ታናሹ ልጁ ወደ አባቱ ሄዶ አባባ ከሀብትህ የሚደርሰኝን አሁኑኑ ስጠኝ አለው። ስለዚህ አባትየው ሀብቱን ለሁለቱ ልጆቹ አካፈለ ከጥቂት ቀን በኋላ ታናሽየው ድርሻውን ሸጠና ገንዘቡን ይዞ ወደ ሩቅ አገረ ሄደ። በሄደበትም አገር ገንዘቡን በከንቱ አባከነ። ገንዘቡንም ከጨረሰ በኋላ በዚያ አገር ረሀብ ስለገባ በችግር ላይ ወደቀ። ከችግሩም የተነሣ የሰሣማ እረኛ ሆኖ ተቀጠረ። ረሀቡም ስለጠ ናበት ከዐሣማዎቹ ምግብ እንኳ ሆዱን ሊሞላ ተመኘ።

ያንንም ቢሆን የሚሰጠው አላገኘም። በዚህ ጊዜ ልጁ እንዲህ ብሎ አሰበ፤ በአባቴ ቤት ተቀጥረው የሚሠሩ አገልጋዮች እንጀራ ጠግበው በልተው ይተር ፉቸዋል፤ እኔ ግን እዚህ በረሀብ መሞቴ ነው፤ ወደ አባቴ ልሂድና ይቅርታ ልጠይቀው ብሎ ተነሣና ወደ አባቱ ሄደ። አባቱም ገና በሩቁ ሲያየው ራራለትና ወደ እርሱ ሮጦ ዕቅፍ አድርጎ ሳመው። ልጁም አባባ በእግዚአብሔርና በአንተ ፊት በድዮአለሁ፤ ከእንግዲህ ልጅህ ልባል አይገባኝም አለ። አባቱ ግን ልብሱ እንዲለወጥለት፥ ለጣቱ ቀለበትና ለእግሩ ጫማ እንዲደረግለት አገልጋዮቹን አዘዘ። የሰባ ሰንጋ ተመርጦ እንዲታረድለት አድርጎ መደሰት ጀመሩ። ልጄ ጠፍቶ ነበር አሁን በሕይወት አለ። ስለዚህ እንደሰት አለ።

በዚህ ጊዜ ታላቁ ልጁ ከእርሻ ሲመለስ የዘፈንና የሙዚቃ ድምፅ ሰማ፡ ምክንያቱን ቢጠይቅ ወንድሙ ስለተመለሰ አባቱ ተደስቶ ያደረገለትን ነገሩት፡ በዚህ ጊዜ በጣም ተቈጥቶ ወደ ቤት አልገባም አለ። አባትየው ወጥቶ እንዲገ ለመነው። እርሱም ይህን ያኽል ዘመን አገልግዬህ ከጓደኞቼ ጋር የምደሰትበት አንዲት ጠቦት እንኳን ሰጥተኸኝ አታውቅም። ይህ ልጅህ ንብረትህን በከንቱ አባክኖ ሲመለስ የሰባውን ሰንጋ አረድህለት አለው። አባትየው ግን ልጄ ሆይ አንተ ሁልጊዜ ከእኔ ጋር ነህ። የእኔ የሆነ ሁሉ የአንተ ነው። ይህ ወንድምህ ግን ሞቶ ነበር፤ አሁን በሕይወት አለ፤ ጠፍቶ ነበር አሁን ተገኘ፤ ስለዚህ እንደሰት አለው (ሉቃ: 15፥11-32)።





ጠፍቶ የተገኘው ልጅ ምሳሌ (ሉቃ: 15፥11-32)

አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ይህን ምሳሌ ሲተረጕሙ እንዲህ ብለዋል:- ሁለት ልጆች አሉት የተባለው ሰው በጌታችን ይመሰላል። ታላቁ ልጁ የተባሉት ጻሓፍትና ፈሪሳውያን ሲሆኑ ታናሹ ልጁ የተባሉት ደግሞ በኃጢአተኞች ይመሰላል። ዮብቱ ቃል እግዚአብሔር ነው። ቃለ እግዚአብሔር ለሁሉም የተላለፈ ሆኖ ጻሓፍትና ፈሪሳውያን ለታይታም ቢሆን ሲጠብቁት ኃጢአተኞች ግን ሕጉን በመጠበቅ ፈንታ ወደ ተለያዩ የኃጢአት ሥራዎች መግባታቸውን ያመለክታል። ታናሹ ልጁ በሄደበት አገር ተቸግሮ ወደ አንድ ሰው ሄዶ የዐሣማ እረኛ ሆኖ በመቀጠር በረደብ ተሠቃየ። ይህ ሁናቴ የሚያመለክተው ደግሞ እርሱ የሄደበት መንገድ ጣዖት አምልኮና ሌሎች ኃጢአቶች እንጂ ቃለ እግዚአ ብሔር የማይገኝበት ሆኖ ያገኘው መሆኑን ነው። ረሀብም የተባለው ቃለ እግዚአብሔርን የሚያስተምር አለማግኘቱ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

በዚህ ጊዜ ያ ልጅ ወደ ኅሊናው ተመልሶ የአባቱ አገልጋዮች እንኳ ምግብ ጠግበው ወደሚኖሩበት ወደ አባቱ ቤት ልመለስ ማለቱ በንስሓ ቃለ እግዚአ ብሔር ወደምመገብበት ወደ ሃይማኖቱ ጉራ ወደ ፈጣሪዬ ልመለስ ማለቱ ነው። በዚህ ጊዜ አባትየው በደስታ እጁን ዘርግቶ ዐቅፎ መቀበሉ እግዚአ ብሔር ኃጢአተኞችን በንስሓ ሲመለሱ እንዲሚቀበላቸው ለማመልከት ነው። የሙዚቃና የዘፈን ድምፅ መሰማቱ «ንስሓ በሚገባ አንድ ኃጢአተኛ ምክንያት በመንግሥተ ሰማይ ደስታ ይሆናል» ብሎ ጌታችን ከሰጠው መግለጫ ጋር ተመሳሳይነት አለው (ሉቃ:15:7)።

ስለዚህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ተቀብለው ወደ ንስሓ የተመለሱት ኃጢአተኞች ናቸው እንጂ ጸሓፍትና ፈሪሳውያንማ ጻድቃን ነን ብለው በዚ ያው ቀርተዋል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመለኮታዊ ባሕርዩ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ የማያንስ ነው። ይሁን እንጂ እኛን ጉስቋላዎቹን ፍጥረቶች ለማዳን ሲል እንደ እኛው ሰው ሆኖ መወለድና ማደግ ነበረበት። በለበሰው ሥጋም ሕማማትን ተቀብሎ በእኛ ቦታ ሆኖ ሞቷል። እኛ ልንፈጽማቸው የማንችላቸውን ሕግጋት ፈጽሞአል። ወደ ግብጽ ስደት ማድረጉ እኛም ተመሳሳይ ችግር ሲያጋጥመን ከመጋፈጥ ይልቅ ዞር እንድንል እኛን ለማስተማር ብሎ ነው።

## ጥያቄዎች

1. መልአክ ማለት ምን ማለት ነው?

2. ወደ ድንግል ማርያም የተላከው መልአክ ማን ይባላል? የተላከውስ ለምንድነው?

3. ድንግል ማርያም አስቸጋሪ ሆኖ የተሰማትና መልአኩን የጠየቀችው ጥያቄ ምንድነው?

4. መልአኩስ ምን መልስ ሰጣት?

5. እርስዋስ ለመልአኩ ምን መልሰ ሰጠችው?

6. ድንግል ማርያም ልጅ የመውለጃዋ ጊዜ ሲደርስ ወዴት ሄዳ ነበር?

7.ልጅዋንስ የወለደችው የት ሆና ነው?

8. የጌታችን ኢየሱስን የመወለድ ዜና የሰሙ እነማን ናቸው? ለእነርሱስ የነገራቸው ማነው?



www.ethiopianorthodox.org

9. ወሬውን ከሰሙ በኋላ ምን አደረጉ?

10. ለጌታችን ኢየሱስ ስም የወጣለት መቼ ነው?

11. ጌታችን ኢየሱስ ለምን ወደ ቤተ መቅደስ ተወሰደ?

12. በቤተ መቅደስ ተገኝተው ስለ ጌታችን ኢየሱስ ትንቢት የተናገሩ እነማን ናቸው?

13. ከሁለቱ አንዳቸውስ ከእግዚአብሔር ምንን ለመነ?

14. በጌታችን ልደት ጊዜ ከውጪ አገር የመጡት ሰዎች ምኖች ይባላሉ?

15. የመጡትስ ለምንድነው?

16. ሄሮድስ ለምን ደነገጠ?

17. ከዚያስ ማንን ምን ጥያቄ ጠየቀ?

18. ተጠያቂዎቹስ ምን መልስ ሰጡት?

19. ዮሴፍ ከሕፃኑና ከእናቱ ጋር ለምን ወደ ግብጽ ሸሸ?

20. ከግብጽስ የተመለሱት መቼ ነው?

21. ጌታችን ኢየሱስ በ12 ዓመቱ ወዴት ሄደ?

22. እዚያስ ምን አደረገ?

23. ጌታችን ኢየሱስ አባቴ ብሎ የሚጠራው ማንን ነው?

24. ሄሮድስ ለምን ሕፃናትን አስገደለ?

25. ያስገደላቸው ሕፃናት በየት መንደር ነበሩ?

26. ዮሐንስ ጌታችንን ለማጥመቅ ያልፈለገው በምን ምክንያት ነው?

27. ጌታችን ዮሐንስን ምን ስላለው ነው ዮሐንስ ተስማምቶ ያጠመቀው?

28. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀበት ወንዝ ምን ይባላል?

29. ጌታችን ተጠምቆ ሲወጣ ዮሐንስ ያየውና የሰማው ምንና ምንን ነው?

30. ለጌታችን ኢየሱስ ጥምቀት ምሳሌ የሆነውን ሁናቴ ግለጽ።

31. በጌታችን ጥምቀት ጊዜ ምን ተገለጠ?

32. ጌታችን የተጠመቀው ለምንድነው?

33. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በበረሓ የጾመው ለስንት ጊዜ ነው?

34. ፈታኙ ዲያብሎስ ወደ ጌታችን የመጣው መቼ ነው?

35. ዲያብሎስ ያቀረበው የመጀመሪያው ፈተና ምን ብሎ ነው?

36. ጌታችንስ ለመጀመሪያው ፈተና ምን መልስ ሰጠው?

37. ሁለተኛው የዲያብሎስ ፈተና ምን የሚል ነበር?

38. ጌታችን የሰጠው ሁለተኛው መልስ ምን ብሎ ነበር?

39. ሦስተኛው የዲያብሎስ ፈተና እንዴት ነበር?

40. ጌታችንስ ለሦስተኛው ፈተና ምን መልስ ሰጠ?

41. መንፈስ ወደ በረሓ ወሰደው ሲል ምን ማለት ነው?

42. ጌታችን አርባ ቀን መጾሙ ምሳሌነቱ ከምን ጋር ነው?

43. ጌታችን ለፈተናው ወደ በረሓ መሄዱ ለምንድነው?

44. ሰይጣን ጌታችንን ለመፈተን እንዴት ደፈረ?

45. በፈተናው ላይ ዋናው የሰይጣን ዓላማ ምን ነበር?

46. ሦስቱ የፈተናው መሠረቶች ምንና ምን ነበሩ?

47. ጌታችን ኢየሱስ ለዲያብሎስ ፈተናዎች መጻሕፍትን እየጠቀሰ መልስ የሰጠው በምን ምክንያት ነው?

48. ጌታችን ኢየሱስ የማስተማር ሥራውን የጀመረው ምን እያለ ነው?

49. ጌታችን ኢየሱስ ማስተማር በጀመረ ጊዜ ዕድሜው ስንት ነበረ?

50. ጌታችን ኢየሱስ በጌንሴሬጥ ባሕር አጠገብ ሲያልፍ ምን አየ? ምንስ አደረገ?

51. ያዕቆብና ዮሐንስ ምን እያደረጉ ነበር?

52. ቃና በምትባል መንደር ምን ነበር?

53. ከጌታችን ጋር ወደዚያ አብረው የሄዱት እነማን ናቸው?

54. ድንግል ማርያም ለጌታችን ምን ነገረችው?

55. ከዚያስ በኋላ ጌታችን ምን አደረገ?

56. የጋብቻው ኀላፊ የተገረመው በምን ምክንያት ነው?



www.ethiopianorthodox.org

57. ጌታችን ኢየሱስ በጌንሴሬጥ ባሕር ያደረገውን ተአምር ዘርዝረህ አስረዳ።

58. ጌታችን ኢየሱስ ለአምስት ሺህ ሰዎች ምን አደረገላቸው?

59. ደቀ መዛሙርቱ ስለ ሕዝቡ ምን ብለው ነበር?

60. ደቀ መዛሙርቱ በእጃቸው ምን ነበር?

61. የነበሩት ሰዎች አምስት ሺህ ብቻ ነበሩን?

62. ማዕበሉ ሲነሣ ጌታችን ኢየሱስ ወዴት ነበር?

63. ጌታችን ደቀ መዛሙርቱን ምን አላቸው?

64. ጌታችን ኢየሱስ ማዕበሉን እንዴት ጸጥ አሰኘው?

65. ሰዎች ተገርመው ምን አሉ?

66. የተፈጥሮ ሕጎችን ለመለወጥ የሚችል ማነው?

67. ይህስ የሆነበት ምክንያት ምንድነው?

68. የዘሪውን ምሳሌ ዘርዝር

69. የዘሪው ምሳሌ ምኖችን ያመለክታል?

70. በአለትና በአሸዋ ላይ የተሠሩ ቤቶችን ምሳሌ ዘርዝረህ ተናገር።

71. ምሳሌውስ ምንን ያመለክታል?

72. ጠፍቶ የተገኘውን ልጅ ምሳሌ ተናገር?

73. ይህን ምሳሌ አንዳንድ አባቶች እንዴት ተረጒሙት?

# ምዕራፍ 4

## ቤተ ክርስቲያን

### መግቢያ

ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤት ነው ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በአክብሮት ጸጥ ብለን እንቈያለን እንጂ አንቅበጠበጥም።

ቤተ ክርስቲያን የሚያስደስት ቦታ ነው

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተሰብስበን እንጸልያለን።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንጠመቃለን።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንቈርባለን።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ደስ የሚያሰኙ ነገሮችን እናያለን።

ካህኑ የጸሎት ልብስ ለብሰው ዕጣን ያጥናሉ።

የዕጣኑ ጢስ ሽታ ደስ ይላል።

ዕጣን የሚያጥኑበት ዕቃ ጥና ይባላል። ካህኑ ጥናውን ሲያወዛውዙት ያስደስታል።

ዲያቆኑ በአንድ እጁ ትልቅ መስቀል በአንድ እጁ የበራ ጧፍ ይዞ ከቄሱ (ከካህኑ) ፊት ቀድሞ ሄዳል።

ቄሱና ዲያቆኑ በአገልግሎት ጊዜ የሚለብሱት ልብሰ ልብሰ ተክህኖ ይባላል።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥና በበሩ አካባቢ የምጽዋት ሣጥን አለ።

እኛም የዐሥራት ግዴታችንንና ሌሎች ምጽዋቶቻችንን በሣጥኑ ውስጥ እንከትታለን።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ደስ የሚያሰኙ ስዕሎች አሉ።

መብራቶቹ የሚያስደስቱ ናቸው።

ሻማዎቹ በመቅረዞቻቸው ላይ ሆነው ይበራሉ።

ከበሮና ጸናጽል የማመስገኛ ዕቃዎች ናቸው።

ሰዎች ሲቆሙ እንዳይደክማቸው በመቋሚያ ይደገፋሉ።

ቅዳሴ ሲጀመር ፣ፃኡ ሲባል፣ እግዚኦ ሲባልና ድርገት ሲወረድ ቃጭል ይቃጨላል፣ ደወል ይደወላል።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለ እግዚብሔር እንማራለን።

ቤተ ክርስቲያንን የመሠረተ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

የቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ይነበባል፤ ጸሎት ይጸለያል፣ የብዙ ደጋግ ሰዎች ታሪክ ይነገራል።

የሚጸለየውም በዜማ ወይም ያለዜማ ነው።

ጸሎቱም ልመና ወይም ምስጋና ነው።

የግልና የማኅበር ጸሎት አለ።

## ቤተ ክርስቲያን ማለት ምን ማለት ነው?

ቤተ ክርስቲያን ሲባል የተለያዩ ትርጉሞች አሉት። በዚህም መሠረት ቤተ ክርስቲያን ሲባል ክርስቲያን ምእመናን፣ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ማለት ሊሆን ይችላል። የእነ ዚህንም አባባሎች ዝርዝር ሁኔታዎች በሚቀጥሉት መግለጫዎች እንመ ልከት።

ምእመናን:- በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም የተጠመቁና በጌታች ን በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት ያመኑ የክርስቲያን ሃይማኖት ምእመናን ቤተ ክርስቲያን ይባላሉ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች በላከው መልእክቱ ምዕራፍ 16ቍጥር 4–5 ላይ ለጵርስቅላና ለአቂላ ሰላምታ አቅርቡልኝ ካለ በኋላ እነርሱን የአሕዛብም አብያተ ክርስቲያን ሁሉ የሚያመሰግኑአቸው ናቸው እንጂ እኔ ብቻ አይደለሁም ብሏል። እንዲሁም በቤታቸው ላለች ቤተ ክርስ ቲያን ሰላምታ አቅርቡልኝ ብሏል። እዚህ ላይ የአሕዛብ አብያተ ክርስቲያን የተባሉትና በቤታቸው ያለችው ቤተ ክርስቲያን የተባሉት ምእመናን ናቸው እንጂ ሌላ አይደለም። በተመሳሳይ አባባል ለቆሮንቶስ ሰዎች በላከው የመጀ መሪያ መልእክቱ ምዕራፍ 16 ቍጥር 19 ላይ የእስያ አብያተ ክርስቲያንና በአቂላና በጵርስቅላ ቤት ያለች ቤተ ክርስቲያን ሰላምታ እንደሚያቀርቡ ገልጾ አል። እንዲሁም በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 20ቍ:28 ላይ ለኤፌሶን ካህናት ባደረገው የመሰናበቻ ንግግር «እግዚአብሔር በገዛ ደሙ የዋጃትን ቤተ ክር ስቲያን ጠብቁ ብሏቸዋል። እዚህም ላይ እንዳለፉት አባባሎች ሁሉ ቤተ ክር ስቲያን የተባለው ምእመናን ለማለት ነው።

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች:- ቤተ ክርስቲያን ሲባል ምእመናን ማለት እንደመሆኑ ሁሉ በሌላ ጊዜ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ማለት ነው።

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ጊዜ ለበደለኛ ሰው ምን ማድረግ እንደሚገባ ሲናገር እንዲህ ብሎአል:- «ወንድምህ ቢበድልህ አንተና

www.ethiopianorthodox.org

እርሱ ብቻችሁን ሆናችሁ በደሉን ንገረው፤ ቢሰማህ እንደገና ወንድምህ እንዲሆን ታደርገዋለህ፤ ባይሰማህ ግን የሁለት ወይም የሦስት ሰዎች ምስክ ርነት ስለሚጸና ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች ይዘህ ወደ እርሱ ሂድ። እነርሱንም አልሰማም ቢል ለቤተ ክርስቲያን ንገር፤ ቤተ ክርስቲያንንም የማይሰማ ከሆ እንደ አረመኔና ተጸጽቶ እንደማይመለስ ኃጢአተኛ ቊጠረው» (ማቴ 18:15–17)። እዚህ ላይ እንደተመለከተው ቤተ ክርስቲያን የተባለው በቤተ ክርስቲያን ስም ከፍተኛ አክብሮት ተሰጥቶት የበደለኛንና የተበዳይን ጉዳይ የሚያዳምጥ የቤተ ክርስቲያን መሪ መሆኑ ነው። ይህም የቤተ ክርስቲያን ወይም የሃይማኖቱ ተወካይ ሆኖ እንደዚህ ያለ ክብር የሚሰጠው የቤተ ክርስቲያን መሪ በተናጠል ወይም መሪዎች በጋራ እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም። ስለዚህ እንደ እነዚህ ተመሳሳይ አባባሎች በሚያጋጥሙበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ሲባል የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መሆናቸውን እንገነዘባለን።

<u>የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር</u>:- በሌላ ጊዜ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን ስን የአንድ አገር የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ማለታችን ነው።

ለምሳሌ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ አቡ ባስልዮስ ነበሩ። አቡነ ባስልዮስ ፓትርያርክ ሆነው ከመሠየማቸው በፊት በኢትዮጵያና በግብጽ አብያተ ክርስቲያን መካከል ብዙ ውይይቶች ተካ ደዋል። በመጨረሻም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከግብጽ ቤተ ክርስቲያ ሥር መሆንዋ ቀርቶ የራስዋ ፓትርያርክ እንዲኖራት ስምምነት ተደረሰ።

ከዚህ በላይ የተገለጸው አባባል የሚያመለክተው ውይይት ተደርጎ ወ ስምምነት የተደረሰው በኢትዮጵያና በግብጽ አብያተ ክርስቲያን አስተዳደሮች መካከል ነው። የቤተ ክርስቲያንም አስተዳደር አብዛኛውን ጊዜ የሚመራው በጳጳሳት ሲኖዶስ ነው። ስለዚህ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፥ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን፥ የአርመን ቤተ ክርስቲያን፥ የሶርያ ቤተ ክርስቲያን፥ የሕንድ ቤተ ክርስቲያን ተብሎ በሚገለጽበት ጊዜ የየሀገሩን የቤተ ክርስቲያን አስተዳደ ወይም አመራር ለማመልከት ነው።

<u>ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን</u>:- በመጽሐፈ ዲድስቅልያ አንቀጽ ዐሥርና አንቀጽ ሠላሳ አምስት በሕንጻ ቤተ ክርስቲያን አሥራር ሥርዓቶች ላይ ለሕንጻው ቤተ ክርስቲያን የሚል ስም ተሰጥቶት እናገኛለን። ቤተ ክርስቲያንም መባሉ ክርስቲያኖች ለጸሎት የሚሰበሰቡበትና የምሥጢራት ቤተ ክርስቲያን ሥር ቶች የሚያከናውኑበት ቦታ ስለሆነ ነው። በብዙዎቻችን ዘንድ ቤተ ክርስቲያ



በሚባልበት ጊዜ ይኸው የምሥጢራት ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት የሚከናወ በትና ለጸሎትም የምንሰበሰብበት ቦታ እንጂ ሌላው አይደለም።

ስለዚህ እንደየንግግሩ አመጣጥ በመለየት ቤተ ክርስቲያን ሲባል ምእመ ናን፥ ወይም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፥ ወይም የቤተ ክርስቲያን አስተ ዳደር፥ ወይም ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ማለት ሊሆን ይችላል።

(የትምህርተ መለኮትን መጽሐፍ ይመለከቷል።)

## <u>ማማተብና ትርጉሙ</u>

ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንገባ ምን እናደርጋለን? ወደ ቤተ ክርስቲያን ስንገባ እናማትብና እንሰግዳለን። የምናማትበውም በአመልካች ጣታችንና በመኻል ጣታችን መስቀለኛ በመሥራት፥ ወይም አውራ ጣታችንን ከአመልካችና ከመ ኻል ጣታችን ጋር በማጣመር ነው። ማማተብም ሲባል መስቀለኛ በሆኑት ሁለት ጣቶች ወይም በተጣመሩት ሦስት ጣቶች መጀመሪያ ወደ ላይ ወደ ግን ባራችን ማውጣት፥

ሁለተኛ ወደ ታች ወደ ደረታችን ማውረድ፥

ሦስተኛ ከግራ ወደ ቀኝ ትከሻችን መውሰድ ነው።

ወደ ላይ ስናወጣ በአብ ስም፥

ወደ ደረታችን ስናወርድ በወልድ ስም፥

ከግራ ወደ ቀኝ ትከሻችን ስንወስድ ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ስም አንድ አምላክ አሜን እንላለን። ማማተብም ራስን መባረክ ነው።

በግዕዝ ልንለው የፈለግን እንደሆን «በስመ አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ »

አአትብ ገጽየ ወኵለንታየ በትእምርተ መስቀል ፊቴንና ሁለንተናየን በመስቀል ምልክት አማትባለሁ።

ቤተ ክርስቲያን ከጥንት አባቶች በተረከበችው ትውፊት መሠረት ምእመ ናን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ፥ ጸሎት ሲጀምሩና ሲጨርሱ፥ ምግብ ሲበሉ፥



www.ethiopianorthodox.org

ሲተኙ፥ ከእንቅልፍ ሲነቁ፤ ከቤት ሲወጡና ወደ ቤት ሲገቡ ያማትባሉ። ይህንንም የሚያደርጉት በሚከተሉት ምክንያቶች ነው።

አንደኛ/ መስቀል የጌታችን ምልክት ነው። በማቴዎስ ወንጌል ም:24 ቍ:30 ላይ «ከዚህም በኋላ የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ላይ ይታያል» የሚ ለው ጥቅስ በብዙዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ዘንድ የመስቀል ምልክት መሆኑ ታምኖበታል። በዚህም መሠረት ለእኛ ራሳችንን ላስገዛንለት ወገኖች መስቀሉ የክብር መዳሊያችን ነው። ይህን በማድረጋችንም በመስቀል ላይ የተሰቀለው የክርስቶስ ተከታዮችና በደሙ የዳንን መሆናችንን እናሳያለን።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው «የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት፥ ለእኛ ለምንድነው ግን የእግዚአብሔር ኀይል ነው» (1ኛ:ቆሮ: ም: 1ቍ: 18)። እንዲሁም በገላትያ መልእክቱ ም 6ቍ: 14 ላይ «ከክርስቶስ መስቀል በቀር በሌላ መመካት ከእኔ ይራቅ» ብሏል።

ሁለተኛ/ማማተብ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ከሞትና ከጥፋት ለማዳን ብሎ በመስቀል ላይ የተቀበለውን ሕማማት ያስታውሰናል። በሁለተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረው ተርቱልያኖስ:- «እውነተኛ ክርስቲያን ከቤቱ ሲወጣና ወደ ቤቱ ሲገባ፥ ሲተኛና ከእንቅልፉ ሲነቃ፥ ልብሱን ሲለ ብስ፥ ምግቡን ለመመገብ ሲቀመጥ፥ እንዲሁም በሥራው ሁሉ ያማትባል» ብሏል። አባባሉንም በመቀጠል:- «የማማተብ መሠረቱ ከየት ነው ብሎ ሰው ቢጠይቃችሁ መሠረቱ ትውፊት ነው፤ ልማድ አጸናው፤ እምነት ደግሞ አረጋ ገጠው በሉት» ብሏል።

የኢየሩሳሌሙ ቅዱስ ቄርሎስ:- « በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ያለህን እምነት ማሳወቅ አትፈርበት፤ በሁሉም ነገር፥ በምግብና በመጠጥ፥ ከቤት ስትወጣና ወደ ቤት ስትገባ በድፍረት አማትብ» ብሎአል።

እንዲሁም የደማስቆው ቅዱስ ዮሐንስ:- «ግዝረት የእስራኤል ልጆች መታወቂያ እንደነበረ በፊታችን መስቀለኛ ማማተብ የተሰጠን እኛ ምእመናን ከሌሎች ተለይተን የምንታወቅበት ምልክት እንዲሆነን ነው» ብሏል።

ማማተብ ራስን በራስ መባረክ ሲሆን አፈጻጸሙም እንደሚከተለው ነው።



በመኻል ጣታችንና በአመልካች ጣታችን መስቀለኛ ሠርተን ወይም የመኻል ጣታችንን፥ አመልካች ጣታችንንና አውራ ጣታችንን በማጣመር ማለት በሦስቱ ጣቶቻችን ወደ ላይ ወደ ግንባራችን አውጥተን በስመ አብ ወይም በአብ ስም፥ ወደ ታች ወደ ደረታችን አውርደን ወወልድ ወይም በወልድ ስም፥ ከግራ ትከሻችን ተነሥተን ወደ ቀኝ ትከከሻችን በመውሰድ ወመንፈስ ቅዱስ ወይም በመንፈስ ቅዱስ ስም አሐዱ አምላክ አሜን ወይም አንድ አምላክ አሜን እንላለን።

ከላይ ወደ ታች መውረድ የሚያመለክተው እግዚአብሔር ወልድ ከእግዚ አብሔር አብ ዘንድ ከወደ ላይ ወደዚህ ዓለም መምጣቱን ነው።

ከግራ ወደ ቀኝ ትከሻችን ማዛወሩ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ አንጽቶና ቀድሶ ከክፉ ተግባር ወደ በጎ ተግባር ለመዛወር እንደሚያበቃን ምሳሌነት አለው።

ከላይ ወደ ታችና ከግራ ወደ ቀኝ መስቀለኛ ማዘዋወሩ ደግሞ የክርስቶስን መስቀል አዳኝነት ያመለክታል።

ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ ዲያብሎስን ድል ስለነሣው እኛም በክርስቶስ መስቀል ኀይል ዲያብሎስን ድል ለመንሣት እናማትባለን። አስደንጋጭ የሆነ ወይም ሰይጣናዊ ትርኢት ስናይና ክፉ ነገር ስንሰማ እናማትባለን። ይህንንም ማድረጋችን የክፉ ነገር ሁሉ ምንጭ የሆነውን ዲያብሎስን ለማባረር ብለን ነው።

በሁለት ጣቶች መስቀለኛ መሥራት ለመስቀሉ ምሳሌነት ሲኖረው የሦስቱ ጣቶቻችን ጥምር ደግሞ የሦስትነትን ምሥጢር ያመለክታል።

ይሁን እንጂ ብዙዎች ሰዎች ትርጉም በሌለው ወይም ቅጥ በሌለው ሁናቴ እጃቸውን በፊታቸው ላይ ሲያወዛውዙ ይታያሉ። የሰዎች መሳቂያ እንዳንሆን የማማተብን ሥርዓት ለምእመናን ማስተማር ይኖርብናል።

## የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ:- ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ የተወለደው ከክርስቶስ ልደት በፊት በ13 ዓመት በጥብርያዶስ ባሕር አጠገብ በምትገኘው በቤተ ሳይዳ ነው። እርሱም ዓሣ አጥማጅ ነበር።



www.ethiopianorthodox.org

በሐዲስ ኪዳን ውስጥ ስለቅዱስ ጴጥሮስ ብዙ ነገሮች ተነግረዋል። እነዚያ
ነገሮች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማንበብ የሚቻል ስለሆነ እነርሱን ትተ
ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ ያለውን ታሪክ በአጭሩ ለመመልከት እንሞክር።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ስለ ክርስቶስ አዳኝነት አስተምሯል።

አንጾኪያ በነበረ ጊዜ እርሱና ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በአንድነት ሆነ
አፎድዮስ የተባለውን ሰው ለአሕዛብ ተመላሾች አግናጥዮስ የተባለውን ደግ
ለአይሁድ ተመላሾች ኤጲስ ቆጶሳት እንዲሆኑ ሾሙላቸው።

ከሊቃውንት አንዱ አሪት ዘፍጥረትን በተረጐመበት መጽሐፉ ሐዋርያ
ጴጥሮስ ወደ ሮማ የሄደው በሕይወቱ መጨረሻ አካባቢ ነው ብሏል። እርሱ
ወደ ሮማ የሄደበት ዋነኛው ምክንያት ሲሞን የተባለውን ጠንቋይ ለመቋቋ
ብሎ ነው። ይህ ሲሞን የተባለ ጠንቋይ አንድ ጊዜ በሰማርያ ከተማ የመን
ቅዱስን ስጦታ ከሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በገንዘብ ሊገዛ በመፈለጉ ሐዋርያ
ቅዱስ ጴጥሮስ የገሠጸው ሰው ነው (የሐ:ሥ:ም: 8ቍ:9–24)።

ሲሞን በሮማ ከተማ ያሳየው ከነበረው የጥንቈላ ትርኢት መካከ
በአጋንንት እርዳታ ከምድር ተነሥቶ በአየር ላይ መንጠልጠል ነበር። ሐዋ
ያው ቅዱስ ጴጥሮስ በሕዝቡ መካል በጉልበቱ ተንበርክኮ እግዚአብሔ
አጋንንትን ያሳፍራቸው ዘንድ ጸለየ። በዚህ ጊዜ ሲሞን ከአየሩ ላይ ወደ
ተሰበረ። ከዚያም በኋላ ከሰው ተደብቆ ከፎቅ ላይ ራሱን በመጣል ሞተ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ወደ ሮማ ከመምጣቱ በፊት ሐዋርያው ቅዱ
ጳውሎስ ቀድሞት መጥቶ ነበር። በሁለቱ ሐዋርያት አማካይነት ክርስትና በሮ
ከተማ ውስጥ ተስፋፋ። ይህ ሁናቴ ንጉሡን ኔሮንን በጣም አስደነገጠው
ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስና ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ተይዘው እንዲታሰ
ትእዛዝ አስተላለፈ። በከተማው ውስጥ የነበሩ ክርስቲያኖች ሐዋርያው ቅዱ
ጴጥሮስን እንዲሸሽ መከሩት። እርሱም ምክራቸውን ሰምቶ ከሮማ ከተ
ሊወጣ ሲል ጌታችን ኢየሱስን ወደ ከተማው ሲገባ ተገናኘው። ቅዱ
ጴጥሮስም «ጌታ ሆይ ወዴት ነው የምትሄደው?» ብሎ ጠየቀው። ጌታችን
«እንደገና ለመሰቀል ወደ ሮማ እሄዳለሁ» አለው። ይህም የጌታችን መል
ቀደም ብሎ ጌታችን ለጴጥሮስ ነግሮት የነበረውን አባባል እንዲያስታው
አደረገው። ይህም አባባል:- «አንተ ጐልማሳ ሳለህ ቀበቶህን በገዛ እጅ



ታጥቀህ ወደፈለግህበት ትሄድ ነበር፤ በሸመገልህ ጊዜ ግን አንተ እጆችህን ትዘረጋና ሌላ ሰው ያስታጥቅሃል» የሚለው ነው። (ዮሐ:2–:18–19)

ጌታችንም «ተከተለኝ» አለው። ቅዱስ ጴጥሮስ ከሽሽቱ ተመልሶ እስከሞ ተበት ቀን ድረስ ወደ ሮሜ እስር ቤት ገባ። እንዲሰቀልም ትእዛዝ በተላለፈ ጊዜ ራሱን ወደ ታች እግሩን ወደ ላይ አድርገው እንዲሰቅሉት አደረገ።



ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ

በሐዋርያው በቅዱስ ጴጥሮስ እጅም እግዚአብሔር ብዙ ተአምራትን አድርጓል። እንዲሁም ከሐዲስ ኪዳን ክፍል በስሙ የተመዘገቡ ሁለት መልእክቶችን ጽፏል።

(የሐምሌ: 5 ቀን ስንክሳርና አጭር የክርስትና ታሪክ ይመለከቷል)



www.ethiopianorthodox.org

<u>ሐዋርያው ቅዱስ እንድርያስ</u>:- ሐዋርያው ቅዱስ እንድርያስ የቅዱስ ጴጥሮስ ወንድም ነው (ማቴ:4:18–20)። የዮሐንስ መጥምቁም ደቀ መዝ ሙር ነበር።

ስለጌታችን ኢየሱስ በሰማ ጊዜ አንድ ቀን ሙሉ ከእርሱ ገር ውሎአል። ስለ ጌታችን ኢየሱስም ለወንድሙ ለጴጥሮስ ነገረው (ዮሐ:ም:ቍ:35–41)።

ጌታችን ኢየሱስ ለአምስቱ ሺህ ሰዎች ምግብ እንዲያቀርቡላቸው ባዘዘ ጊዜ አምስት እንጀራና ሁለት ዓሣ መኖሩን የተናገረው እርሱ ነው (ዮሐ:ም: 6ቍ:8)።

የግሪክ አገር ሰዎች ጌታችን ኢየሱስን ለማየት በፈለጉ ጊዜ ከሐዋርያው ፊልጶስ ጋር ሆኖ ጉዳዩን ወደ ጌታችን ያቀረበ እርሱ ነው (ዮሐ: ም:12 ቍ:22)።

ስለቤተ መቅደስ መፍረስ ጉዳይ ጌታችን ኢየሱስን ከጠየቁት ሐዋርያት አንዱ እርሱ ነበር (ማር: ም 13 ቍ:3)።

መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ ከወረደ በኋላ ቅዱስ እንድርያስ ወደ ትንሽዋ እስያ ሄደ። ያስተማረውም በኩርዶች አገርና በልዳ ከተማ ነበር። ወደ ልዳ ከተማ በገባ ጊዜ አብዛኛዎቹ የከተማው ኑዋሪዎች በቅዱስ ጴጥሮስ አስተማሪነት አምነው አገኛቸው።

ከሐዋርያው ቅዱስ እንድርያስም ጋር ደቀ መዝሙሩ ፊልሞን ነበር።

የጣዖት ካህናት የሐዋርያው እንድርያስን መምጣት በሰሙ ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን በቍጣ መጥተው በሰተውጪ በመቆም አማልክቶቻቸውን ይሳደብ እንደሆነ ለመስማት ማዳመጥ ጀመሩ። የዳዊትን መዝሙር ሲያነብ ሰሙት። እርሱም እንዲህ የሚለው ክፍል ነው:- «እነርሱ የሚያመልኩአቸው ጣዖቶች ግን በሰው እጅ ከብርና ከወርቅ የተሠሩ ናቸው፤ አፍ አላቸው አይናገሩም፤ ዐይን አላቸው አያዩም፤ ጆሮ አላቸው አይሰሙም፤ አፍንጫ አላቸው አያሸ ትቱም፤ እጅ አላቸው አይዳስሱም፤ እግር አላቸው አይሄዱም፤ ድምፅም መስ ማት አይችሉም፤ የሠሩአቸውና የሚታመኑባቸው እንደእነዚህ ጣዖቶች ይሁ ኑ» (መዝ :115፥4–8)።



አስደሳች በሆነ ድምፁ ልባቸው ተደሰተ፤ ኀሊናቸው ወቀሳቸው፤ ወደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ገብተውም በሐዋርያው ቅዱስ እንድርያስ እግር ሥር ሰገዱ። እርሱም አስተምሮአቸው በጌታችን አመኑ። ከዚያም አጠመቃቸውና ጣዖት ማምለክን አቆሙ።

ቅዱስ እንድርያስ ከዚያ ወጥቶ ወደ ኩርዶች አገር:- አክሲስ፥ አርጂናስና አሲፎስ ወደተባሉት ከተሞች ሄደ። ከዚያ ቀደም ብሎ ከሐዋርያው ቅዱስ በርተሎሜዎስ ጋር አዝሪኖስ በተባለች ከተማ በኩል አልፎ ነበር። የዚያች ከተማ ሰዎች እግዚአብሔርን የማያውቁ ክፉዎች ነበሩ። ሆኖም ማስተማሩን በመቀጠል እግዚአብሔር በእርሱ አማካይነት ከሚያደርጋቸው ተአምራት ብዛት የተነሣ ከእነርሱ ብዙዎቹን እግዚአብሔርን እንዲያውቁ አድርጓቸዋል።

ያላመኑት ወገኖች ግን በእርሱ ላይ አደሙበት። ሲመጣ ሊገድሉት በመስማማት ወደ እነርሱ እንዲመጣ መልእክተኞች ላኩበት። መልእክተኞ ቹም ወደ እርሱ ደርሰው አሳማኝ የሆነ ትምህርቱን በሰሙና በብርሃን ያንጸባረቀ ፊቱን በተመለከቱ ጊዜ በጌታችን ኢየሱስ አመኑና ወደላኩአቸው ሰዎች ሳይመለሱ ቀሩ። በዚህ ጊዜ እነዚያ ያላመኑት ወገኖች ወደ እርሱ ሄደው ሊያቃጥሉት ወሰኑ። ውሳኔአቸውን በተግባር ላይ ለማዋል በከበቡት ጊዜ ሐዋርያው ወደ እግዚአብሔር ስለጸለየ ከሰማይ እሳት ሲወርድባቸው አዩ። ይህንንም ሁኔታ በማየታቸው ፈርተው አመኑ። የሐዋርያው ዝና በዚያች አገር ሁሉ ተሰምቶ ብዙዎች በእግዚአብሔር አመኑ። ይህም ሁሉ ሆኖ አላማንያኑ ሐዋርያውን ለማጥፋት ከመፈለግ አላረፉም። በዚህም መሠረት ወደ እርሱ ሄደው አሰሩትና በጣም ደበደቡት። በከተማውም ራቁቱን ካዞሩት በኋላ በማ ግስቱ እስኪሰቅሉት ድረስ ወደ እስር ቤት አስገቡት።

የዚያ አገር ሰዎች አንድን ሰው በመስቀል በሚገድሉበት ጊዜ መውገርም ልማዳቸው ነበር።

ሐዋርያውም ሌሊቱን ሲጸልይ ዐደረ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተገል ጦለት አይዞህ አትጨነቅ፤ ደግሞም አትበሳጭ፤ ከዚህ ዓለም መሰናበቻህ ጊዜ ደርሶአል በማለት ተሰናብቶት ተሰወረበት። ሐዋርያውም ጌታችንን ባየ ጊዜ ነፍሱ ተደሰተች።

በማግስቱ ወስደው በእንጨት ላይ ሰቀሉትና እስኪሞት ድረስ በድንጋይ ወገሩት።



www.ethiopianorthodox.org

ከዚያም አማንያን መጥተው የተቀደሰ ሰውነቱን ወስደው በተለየ ቦታ በክብር ቀበሩት። እግዚአብሔርም በእርሱ አማካይነት ብዙ ተአምራትን አድርጎአል። (የታኅሣሥ 4 ቀን ስንክሳር)

<u>ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ፥ የእልፍዮስ ልጅ</u>:- ቅዱስ ያዕቆብ ከዐሥራ ሁለቱ የጌታችን ደቀ መዛሙርት አንዱ ነበር።

በተለያዩ አገሮች ወንጌልን ካስተማረ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ።

በኢየሩሳሌምም ወደ አይሁድ ቤተ መቅደስ ገብቶ በድፍረት ወንጌልን አስተማረ።

የሰጠውም ትምህርት በጌታችን ኢየሱስ ስለማመንና ስለ ትንሣኤ ሙታን እውነተኛነት ነበር። አይሁድ ይዘው የሮማው ንጉሥ ወኪል ወደ ነበረው ወደ አቅሎድዮስ በማምጣት ይህ ሰው ከቄሳር ሌላ ንጉሥ አለ ብሎ ይሰብካል ብለው ከሰሱት።

የሮማው ንጉሥ ወኪልም ቅዱስ ያዕቆብን በድንጋይ እንዲወግሩት አዘዘ።

በትእዛዙ መሠረት እስኪሞት ድረስ በድንጋይ ወገሩት።

ምእመናንም አንሥተው በቤተ መቅደሱ አጠገብ ቀበሩት። (የየካቲት 10 ቀን ስንክሳር)

<u>ሐዋርያው ቅዱስ ታዴዎስ</u>:- ሐዋርያት መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ቅዱስ ታዴዎስ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች እየዞረ ወንጌልን አስተምሮአል። ብዙዎች አይሁዶችንና አሕዛብን በማጥመቅ ወደ ክርስትና እምነት መል ሶአል። እንዲሁም በሶርያ ብዙዎችን አስተምሮ አሳምኖአል።

በአይሁድና በአረማውያን እጅ ብዙ ችግሮች ከደረሱበት በኋላ በሰላም ዐርፎአል። (የሐምሌ 15 ቀን ስንክሳር)

<u>ቅዱስ ቂርቆስና እናቱ ቅድስት ኢየሉጣ</u>:- የቂርቆስ ዕድሜ ሦስት ዓመት በነበረ ጊዜ እናቱ ኢየሉጣ አገርዋን ኢቆንያን ትታ ከልጅዋ ጋር ወደ ጠርሴስ ሄደች። ይህንንም ያደረገችው ክርስቲያኖችን ያሠቃይ የነበረውን ገገር ለመሸሽ ብላ ነበር። ነገር ግን የሸሸችውን ሰው ወደ ጠርሴስ መጥቶ አገኘችው። ወደ እርሱም አስጠርቶ ጣዖታትን እንድታመልክ ሐሳብ አቀረበላት። እርስዋም



ይህን አበባልህን የሦስት ዓመት ሕፃን እንዴ ለይቀበለውም አለችው። ልጅሽን እንጠይቀውን? አላት። ሕፃኑ እግዚአብሔር አናግሮት እንዲህ ብሎ መለሰ፡ «አንተ የምታመልካቸው የእጅ ሥራዎች ድንጋዮችና እንጨቶች ናቸው። ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ሌላ አምላክ የለም። በዚያ የነበሩት ሰዎች ሁሉ ተገረሙ፤ አገረ ገዥው ተዋረደ። በዚህም ምክንያት ከዕድሜው ጋር የማይመጣጠን ሥቃይ አደረሰበት። እናቱን ኢየሉጣንም የተለያዩ የሥቃይ ዐይነቶችን አደረሰባት። እግዚአብሔር ግን ኃይልና ጽናቱን ሰጣቸው። ብዙዎች ሰዎች ይህን ሁናቴ ባዩ ጊዜ በጌታችን በኢየሱስ አምነው የሰማዕትነትን አክሊል ተቀዳጁ። አገረ ገገርውም በመጨረሻ የቂርቆስና የእናቱ የኢየሉጣ ራሶች እንዲቈረጡ አዘዘና የሕይወት አክሊል አገኙ። (የሐምሌ 15 ቀን ስንክሳር)

## <u>የቤተ ክርስቲያን ዜማዎች</u>

ዲያቆኑ:- ተንሥኡ ለጸሎት – ለጸሎት ተነሡ ሲል

ሕዝቡ :- እግዚኦ ተሠሃለነ – አቤቱ ይቅር በለን ይበል።

ካህኑ :- ሰላም ለኵልክሙ – ሰላም ለሁላችሁም ይሁን ሲል

ሕዝቡ :- ምስለ መንፈስከ – ከመንፈስህ ጋር ይበል።

**ቅዳሴ በሚገባበት ጊዜ** በኅብረት የሚዜም የዘወትር ተስጥዎ

እምነ በሐ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሥርጉት ዐረፋቲሃ ወስዕልት በዕንቍ ጳዝዮን፤ እምነ በሐ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን

እናታችን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሰላም እንልሻለን። ግድግዳዎችዋ የተሸለሙና በጳዝዮን ዕንቍ ያጌጠች ናት።

<u>የቀዳሚት</u>

መስቀል አብርሃ በከዋክብት አሠርገወ ሰማየ። እምኵሉሰ ፀሐየ አርአየ። መስቀል አብርሃ በከዋክብት አሠርገወ ሰማየ

መስቀል አበራ፤ ሰማይን በከዋክብት ሸለመ (አስጌጠ) ከሁሉም ይልቅ ፀሐይን አሳየ።



www.ethiopianorthodox.org

የእሁድ

ኵሉ ዘገብረ ለጽድቅ ጻድቅ ውእቱ ወዘያከብር ሰንበተ ኢይበል ፈላሲ
ዘገብአ ኀበ እግዚአብሔር ይፈልጠኒኑ እምሕዝቡ፤

ኵሉ ዘገብረ ለጽድቅ ጻድቅ ውእቱ ወዘያከብር ሰንበተ።

እውነትን የሚአደርግ ሁሉ ሰንበትንም የሚያከብር ጻድቅ ነው።

ወደ እግዚአብሔር የተመለሰ መጻተኛ ከሕዝቡ ይለየኛ ይሆንን አይበል፤

<u>የዘመነ ፋሲካ</u>

ሃሌ ሉያ ዮሴፍ ወኒቆዲሞስ ገነዝዎ ለኢየሱስ በሰንዱናት ለዘተንሥ
እሙታን በመንክር ኪን።

ሃሌ ሉያ በሚያስደንቅ ምሥጢር ከሙታን ተለይቶ የተነሣውን ኢየሱስ
ዮሴፍና ኒቆዲሞስ በድርብ በፍታ ገነዙት።

## ከዚህ ምዕራፍ የምናገኘው ትምህርት

ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤት በመሆንዋ ልናከብራት የሚገባ
መሆኑን ተምረናል።

ማማተብ ደግሞ የራሱ የሆነ ሥርዓት አለው እንጂ ዝም ብለን እጃችን
ወደፈለግነው አቅጣጫ ማወዛወዝ አለመሆኑን ተምረናል።

የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን ደግሞ በዓለም ላይ ስለሚደርስባቸው ችግ
ሳይፈሩ ሃይማኖታቸውን መጠበቃቸውን ተመልክተናል። እነርሱም ለዚህ
ኀላፊ ለሆነችው አጭር ዘመን አለመጨነቃቸው ምን ያኽል ለዘለዓለማ
ሕይወት ያስቡ የነበሩ መሆናቸውን ያመለክታል። ይህም አድራጎታቸው ለእ
ታላቅ ትምህርት ሊሰጠን ይገባል።

የቅዱስ ቂርቆስንና የእናቱን የቅድስት ኢየሉጣን ሁናቴ ስንመለከት ደግ
እግዚአብሔር ክብሩን የሚገልጠው ዕድሜ፥ ጾታና ወገን ሳይለይ መሆኑ
እንረዳለን። በዚህም መሠረት መንፈሳዊ ቅናት ሊያድርብን ይገባል።



## ጥያቄዎች

1. ቤተ ክርስቲያን ምንድነው?
2. ቤተ ክርስቲያን የምታደስደስተው ለምንድነው?
3. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን እናደርጋለን?
4. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምን ምን ነገሮች አሉ?
5. ዲያቆኑ ከቄሱ ፊት የሚሄደው ምንና ምንን ይዞ ነው?
6. ቄሱና ዲያቆኑ የሚለብሱት የመንፈሳዊ አገልግሎት ልብስ ምን ይባላል?
7. ሻማ የሚበራው በምን ላይ ሆኖ ነው?
8. ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲቆሙ እንዳይደክማቸው ምን ያደርጋሉ?
9. ቃጭል የሚቃጨለው በምን ጊዜ ነው?
10. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምንን እንማራለን?
11. ቤተ ክርስቲያንን የመሠረተ ማነው?
12. የቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂ ማነው?
13. የጸሎት ዐይነቶች ምንና ምን ናቸው?
14. ማማተብ ማለት ምን ማለት ነው?
15. የምናማትበው መቼ ነው?
16. የምናማትበው በምንድነው?
17. የምናማትበውስ እንዴት አድርገን ነው?
18. የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ ምን ነበር?
19. በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ስለምን ጉዳይ አስተማረ?
20. አይሁድ ምን አደረጉት?
21. የሮማው ንጉሥ ተወካይ ምንን አዘዘ?
22. ቅዱስ ያዕቆብን እንደምን አድርገው ገደሉት?
23. በድኑን ማን ቀበረው?



www.ethiopianorthodox.org

24. የቅድስት ኢየሉጣ አገር ምን ይባላል?

25. ሸሽታ የሄደችበት አገር ምን ይባላል?

26. ለምን ሸሸች?

27. በሸሸችበት አገር ማንን አገኘች?

28. አገረ ገዥው ምን ሐሳብ አቀረበላት?

29. እርስዋስ ምን መልስ ሰጠችው?

30. ቅዱስ ቂርቆስ ስንት ዓመቱ ነበር?

31. ቅድስት ኢየሉጣ ለሰጠችው መልስ አገረ ገዥው ምን አላት?

32. ቅዱስ ቂርቆስ ለአገረ ገዥው ምን አለው?

33. አገረ ገዥው በቅዱስ ቂርቆስና በእናቱ በቅድስት ኢየሉጣ ላይ ምን አደረገ?

34. ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ስንት ትርጉሞች አሉት? እነርሱስ ምንና ምኖች ናቸው?

35. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የእስያ አብያተ ክርስቲያን እንዲሁም በአቂላና በጵርስቅላ ቤት ያለችው ቤተ ክርስቲያን ሲል ቤተ ክርስቲያን ማለቱ ምን ለማለት ነው?

36. እግዚአብሔር በደሙ የዋጃትን ቤተ ክርስቲያን ጠብቁ ሲል ቤተ ክርስቲያን ያለው ቃል በምን ይተረጎማል?

37. እነርሱን አልሰማ ቢል ለቤተ ክርስቲያን ንገር ሲል ቤተ ክርስቲያን ማለት ምን ማለት ነው?

38. የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፥ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን ሲል ቤተ ክርስቲያን የተባለው ምን ለማለት ነው?

39. በዲድስቅልያ አንቀጽ ዐሥርና አንቀጽ ሠላሳ አምስት የተገለጠው ቤተ ክርስቲያን ምንን ያመለክታል?

40. የምናማትበው በምን ምክንያቶች ነው?

41. የምናማትብባቸው ጊዜዎች የትኞቹ ናቸው?

42. ስለማማተብ የተናገሩ ምሁራንና ቅዱሳን አባቶች እነማን ናቸው?



44. ማማተብ ማለት ምን ማለት ነው?

45. ስናማትብ ምን እያልን እናማትባለን?

46. ሁሉም ሰው በትክክል ያማትባል'ን?

47. ካልሆነስ ምን ማድረግ አለብን?

48. ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ወደ ሮም የሄደበት ዋናው ምክንያት ምን ነበር?

49. የሄደበት ጉዳይስ ተሳካለትን?

50. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ጴጥሮስን የት ተገናኘው?

51. ጌታችን ቅዱስ ጴጥሮስን ምን ብሎ ጠየቀው እርሱስ ምን መልስ ሰጠው?

52. በዚህ ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስ ምንን አስታወሰ?

53. ከሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስና ከሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ማናቸው ነው ቀድሞ ወደ ሮም የመጣ?

54. የቅዱስ ጴጥሮስ አሟሟት እንዴት ነበር?

55. ቅዱስ ጴጥሮስ ስንት መጻሕፍት ጽፏል? ስማቸውስ ምን ምን ይባላል?

56. ከሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስና ከወንድሙ ከሐዋርያው ቅዱስ እንድርያስ ቀድሞ ጌታችንን ያገኘው ማነው?

57. ተቈጥተው ወደ ቤተ ክርስቲያን የመጡት የጣዖት ካህናት ምን አደረጉ?

58. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያው ቅዱስ እንድርያስ ተገልጦለት ምን አለው?

59. ኢአማንያኑ ሐዋርያውን እንደምን አድርገው ገደሉት?



www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ 5

## መንፈሳዊነትና ግብረገብነት

መንፈሳዊነትና ግብረገብነት ብዙ ተመሳሳይነት አላቸው።

መንፈሳዊነት:-

መንፈሳዊነት ስንል በሃይማኖታዊ ዝንባሌ መመራት ስለሆነ ሃይማኖታዊ ሰው መንፈሳዊ ነው ይባላል።

ሃይማኖታዊነቱም የቃላትና የወሬ ብቻ ሳይሆን ሃማኖታዊ ሕጎችንና ትእዛዞችን የሚጠብቅ መሆን አለበት።

ከዚያም በላይ በሃይማኖታዊ ስሜት ልቡ የተሰበረ ሆኖ ማንንም የማያስ ቀይም መሆን አለበት።

እንደዚህ ያለውም ሰው ትሑትና ከአንደበቱ ምንም ክፉ ነገር የማይወጣ ከመሆኑም በላይ ሰውን ቅር የሚያሰኝ ተግባር ስለማይፈጽም ግብረገባዊም ነው።

ግብረገብነት:- ግብረገብነት ሲባል ደግሞ ኅብረተሰቡ ትክክለኛ ነው ብሎ ያመነበትን የተግባር መመዘኛ አክብሮ መኖር ነው።

አብዛኛውን ጊዜ ኅብረተሰቡ የግብረገብነት መመዘኛ የሚያደርገው ሃይማ ኖተኛነትን ነው።

ሃይማኖት አትግደል– አትስረቅ፥ አትዋሽ የሚሉትንና ሌሎችንም ተመ ሳሳይ ሕጎችን ያዝዛል። እነዚህን ሕጎች የሚጠብቁ መንፈሳዊነት ያላቸው ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ግብረገብነት ያላቸው ሰዎችም ናቸው።

መንፈሳዊነትና ግብረገብነት የሚመሳሰሉባቸው ሁኔታዎች

መንፈሳዊ ሰውም ግብረገብነት ያለው ሰውም ጎሕትና አላቸው።

መንፈሳዊ ሰው በንግግሩ ሌላውን ሰው ቅር እንደማያሰኝ ግብረገብነት ያለው ሰውም ሌላውን ሰው በንግግሩ ቅር አያሰኝም።



መንፈሳዊነት ያለው ሰው በግሉ በተቈጣ ወይም በተጨነቀ ጊዜ ችግሩን ራሱ ይችለዋል እንጂ የሌሎችን ሰዎች መብት አይጐዳም። ግብረገብነት ያለውም ሰው እንደዚሁ ያደርጋል።

ቍጣን መቈጣጠር መንፈሳዊነትም ግብረ ገብነትም ነው።

ልጆች ወላጆችን ማክበራቸው መንፈሳዊነትም ግብረገብነትም ነው።

ችግረኞችን መርዳት መንፈሳዊነትም ግብረገብነትም ነው።

የመንፈሳዊነትና የግብረገብነት ልዩነቶች:- መንፈሳዊነት የሚያተኵረው ከሥጋዊው ኑሮ ተቃራኒ በሆነው በሃይማኖታዊ ጉዳይ ነው። ዓላማውም የእ ግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸም ነው። ግብረገብነት ግን ቀደም ተብሎ እንደ ተገለጠው ዋና ትኵረቱ የኅብረተሰቡን ፍላጎት ማርካት ነው።

መንፈሳዊነት:- ሰውን ሁሉ ከልብ ማፍቀር መንፈሳዊነት ነው።

ያለውን ነገር ሁሉ ሌሎችም ሰዎች እንዲጠቀሙበት ማድረግ የመንፈ ሳዊነት ጠባይ ነው።

በስሜት ጸሎትን ማዘውተር መንፈሳዊነት ነው።

ከምግብ በፊት፥ ከመኝታ በፊት፥ ሥራ ከመጀመር በፊትና እንዲሁም በጧት መጸለይ መንፈሳዊነት ነው።

ከሚያዝን ሰው ጋር ማዘንና ከሚደሰትም ሰው ጋር የደስታው ተካፋይ መሆን መንፈሳዊነት ነው።

ግብረገብነት:- ግብረገባዊ የሆነ ሰው ለመናገር ተራውን ይጠብቃል።

ግብረገብነት ያለው ሰው በሰው ንግግር ውስጥ ጣልቃ አይገባም።

ግብረገብነት ያለው ሰው የሌላውን ሰው መብት ያከብራል።

ግብረገብነት ያለው ሰው ከቤተሰብ ጋር በሥራ ይተበበራል።

ግብረገብነት ያለው ሰው ተስፋ ሳይቈርጥ ድክመቱን ይቀበላል።



www.ethiopianorthodox.org

ግብገረገባዊ የሆነ ሰው እባክህ፥ እባክሽ፥ እባክዎ የሚባሉትን አነጋገሮች ይጠቀምባቸዋል።

ግብረገባዊ የሆነ ሰው ለተደረገለት ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ይስጥልኝ ብሎ ያመሰግናል።

## ጸሎት

ቀደም ተብሎ እንደተገለጠው የመንፈሳዊነትንና የግብረገብነትን ትምህርት ከመለያየት ይልቅ በአንድ ላይ እንደ አንድ ትምህርት አድርጎ ማቅረቡ የተመረጠ መሆኑ ተመልክቶአል። በዚህም መሠረት ምንም እንኳ ጸሎት የመንፈሳዊነት ትምህርት ቢሆን በአጠቃላይ ለማቅረብ ስለታቀደ በአንድነት ቀርቦአል።

ጸሎት ሲባል የግል ወይም የሌላ ሰው ችግር ይወገድ ዘንድ በመለመን፥ በንስሓ፥ በስእለት፥ በምስጋና ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ወይም ኅብረት ማድረግ ማለት ነው። አንድ ሰው ማንኛውንም ሥራውን በሚጀምርበት ጊዜ በጸሎት ከጀመረ በእግዚአብሔር እርዳታ ሥራው ይቃናለታል፤ ችግር ቢደርስበት ችግሩ ይወገድለት ዘንድ ሲጸልይ ተሰሚነትን ያገኛል፤ ለእግዚአብሔር ስእለት ከተሳለ ፍላጎቱ ይፈጸምለታል፤ በደሉን በመናዘዝ ንስሓ ከገባና ከጸለየ እግዚአብሔር ይቅርታ ያደርግለታል። እግዚአብሔር የጸሎተኛውን ልመና በመስማቱና በመፈጸሙ ከጸሎተኛው የምስጋና ጸሎት ይጠበቅበታል።

ጸሎትን በተመለከተ በየጊዜው የሚነሡ ጥያቄዎች አሉ። እነርሱም የሚከተሉት ናቸው:-

1ኛ. እግዚአብሔር በውሳኔው የሚጸናና የማይለወጥ እስከሆነ ድረስ ጸሎት ምን ይጠቅማል?

2ኛ. አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ሕግጋት የሚፈጽም ከሆነና ለ… የሚፈልገው ነገር ከሌለው ለምን መጸለይ ያስፈልገዋል?

3ኛ. ጸሎት ሁልጊዜ መልስ ያገኛልን?

<u>እግዚአብሔር የማይለወጥና ጸሎት ተቀባይ ነው</u>:- እግዚአብሔር በውሳኔው የጸና እንደ ሰው ልጆች የማይለዋወጥ መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት ያረጋግጣሉ። (ዘኁ: ም 23ቍ:19፥ 1ኛ: ሳሙ:ም:15ቍ:29፥ ሚል:ም:3 ቍ:6፥ ማቴ:ም:24ቍ:35፥ ሮሜ:ም:11ቍ:29)

ሰው ንስሓ ገብቶ በሚጸልይበት ጊዜ ከክፉት ወደ በጎነት የተለወጠው ሰው ነው እንጂ እግዚአብሔር አይደለም። የእግዚአብሔር ቃል አይለወጥም ሲባል:- ሰው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ቢፈጽም እንደሚድንና ባይፈጽም ግን እንደሚቀጣ ነው። ይኸውም ሁናቴ በአዳምና በሔዋን ላይ የታየ ነው። እግዚአብሔርም ለሰው ልጆች ጠቃሚና ጐጂ ሁኔታዎችን ካመለከታቸው በኋላ በፈለጉት መንገድ እንዲሄዱ ነጻ ፈቃድን በማቸው እንጂ ያልፈለጉትን ድርጊት እንዲያደርጉ አላስገደዳቸውም።

እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ስለሰጠው የፈቃድና የፍላጎት ነጻነት ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች ያሉ ቢሆን ከእነዚህ አንዱ የሚከተለው ነው:-

«እነሆ እኔ በሕይወትና በሞት መካከል በበረከትና መርገም መካከል ምርጫ እሰጣችኋለሁ፤ በምታደርጉትም ምርጫ ሰማይንና ምድርን በእናንተ ላይ ምስክር አድርጌ እጠራለሁ፤ ስለዚህም እናንተና ዘሮቻችሁ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጡ» (ዘዳ:ም:30ቍ:19)።

ስለዚህ እግዚአብሔር ለሰው እንደዚህ ያለውን ምርጫ ሰጠው እንጂ ልማቱን ወይም ጥፋቱን አስቀድሞ የወሰነለት ወይም የወሰነበት አይደለም። በዚህም መሠረት አንድ ሰው ጥፋተኛ መሆኑን አምኖ በመጸጸት የእግዚአብሔርን ይቅርታ በሚለምንበት ጊዜ እግዚአብሔር ይቅርታ አድርጎ ይምረዋል። ደግ የነበረውም ሰው ደግነቱን ትቶ ወደክፋት ቢያመራ እግዚአብሔር ይቀጣዋል እንጂ አይምረውም። ይህንንም በሚከተለው ማስረጃ እንመልከት:-

«ክፉ ሰው ኃጢአት መሥራትን ትቶ ሕጌን ቢጠብቅ፥ ትክክልና መልካም የሆነውን ነገር ቢያደርግ በሕይወት ይኖራል እንጂ አይሞትም፤ ትክክል የሆነውን ነገር ስላደረገም የሠራው ኃጢአት ሁሉ ይቅር ተብሎለት በሕይወት ይኖራል። ነገር ግን ደግ ሰው መልካም ማድረጉን ትቶ ክፉ ሰዎች የሚያደርጉአቸውን ክፉና አስጸያፊ ነገሮችን ማድረግ ቢጀምር በሕይወት መኖር የሚችል ይመስላችኋልን? አይደለም፤ እንዲያውም ያደረገው የደግነት ሥራ ሁሉ አይታሰብለትም፤ ባለመታመኑና ኃጢአተኛም በመሆኑ ምክንያት ይሞታል» (ሕዝ:ም:18ቍ:21፥22፥24)።



www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህ የእግዚአብሔር የማይለወጠው ጠባይ ለደገ ሰው ሕይወትን መስጠት፥ ክፉውን ሰው መቅጣትና፥ በንስሓ ለሚመለሰው ሰው ደግሞ እንደ መሐሪነቱ ይቅርታ ማድረግ ነው።

<u>ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ ስለሆነ ጸሎት ያስፈልገዋል</u>:- ሁለተኛውን ጥያቄ በምንመለከትበት ጊዜ ፍጹም ጻድቃን የሆኑና ኃጢአት የሌለባቸው ሰዎች ያሉ ያስመስላል። በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ማንም ፍጹም ጻድቅ የሆነ ሰው እንደሌለ ብዙ ማስረጃዎች የሚገኙ ሲሆን ከእነዚህም ሁለቱን ቀጥለን እንመል ከት:-

«ነገር ግን ሁሉም ባዝነዋል፤ ሁሉም በአንድነት በድለዋል፤ አንድም መልካም ነገርን የሚያደርግ የለም» (መዝ: 14 ቍ:3)።

«የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአታችን ሁሉ ያነጻናል። ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናታልላለን፤ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም» (1ኛ: ዮሐ:ም:1ቍ:7–8)።

ማንም ሰው ሕግጋትን ሙሉ በሙሉ ሊፈጽማቸው ያልቻለ መሆኑን ሲገልጥ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ:- «ከሰው ባሕርይ ደካማነት የተነሣ ሕግ ሊያደርገው ያልቻለውን እግዚአብሔር አድርጎታል፤ የገዛ ልጁን በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌነት ላከ፤ የኃጢአት መሥዋዕት ባደረገው በዚሁ በልጁ ሥጋ ኃጢአትን በፍርድ አስወገደ» ብሏል (ሮሜ:ም:8ቍ:3)።

ስለዚህም በተለያዩ መንገዶች ሕግን ስለምንተላለፍና ፍጹማን ስላልሆንን የእግዚአብሔርን ምሕረት በጸሎት ሆነን መለመን አለብን እንጂ ጸሎት እንደማያስፈልገን ማሰብ የለብንም።

እንዲያውም የእግዚአብሔር ምርጥ ዕቃ የተባለው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሥጋዊና በመንፈሳዊ ሰውነቱ መካከል ምን ያኽል ትግል የሚካሄድ መሆኑን በመዘርዘር ካስረዳ በኋላ «እኔ ምንኛ ጐስቋላ ሰው ነኝ! ከዚህ ሟች ሰውነትስ ማን ያድነኛል?» ብሏል (ሮሜ:ም:7ቍ:14–24)።

ከጸላኤ ሠናይ ጋር በምናደርገው ግብ ግብ እግዚአብሔር ኀይሉንና ብርታቱን ይሰጠን ዘንድ መጸለይ አለብን እንጂ ጸሎት እንደማያስፈልገን መገመት የለብንም። የጸሎት ዋናው ገጽታ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድ ረግ እንደመሆኑ ከዚያ ታላቅ በረከት መራቅ የለብንም።

<u>መልስ የሚያገኝና የማያገኝ ጸሎት</u>:- ሦስተኛው ጥያቄ ጸሎታችን ሁሉ መልስ ያገኛል ወይ የሚል ነው። አብዛኛው ጸሎታችን ከእግዚአብሔር ዘንድ መልስ እናገኝበታለን። ለዚህም አባባል የሚከተሉት ማስረጃዎች ይገኛሉ:-

«እኔ አንድን ሕዝብ ወይም መንግሥት እነቅላለሁ፤ ወይም ሰባብሬ አጠፋለሁ ብዬ በተናገርሁ ጊዜ ያ ሕዝብ ተጸጽቶ ከክፋቱ የሚመለስ ከሆነ አመጣበታለሁ ብዬ ያቀድሁትን ክፉ ነገር አላደርግበትም» (ኤር:ም 18ቍ: 7–8)።

«እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- እንግዲህ አሁን በፍጹም ልባችሁ ወደ እኔ ተመለሱ፤ ጹሙ፤ አልቅሱ፤ እዘኑ፤... ወደ አምላካችሁ ወደ እግዚአ ብሔር ተመለሱ፤ እርሱ ቸር፥ ምሕረቱም የበዛ ነው፤ ፍቅሩም ዘለዓለማዊና ለቍጣ የዘገየ ነው፤ ከመቅጣት ይልቅ ይቅርታ ለማድረግ ዘወትር የተዘጋጀ ነው» (ኢዩ:ም:2ቍ:12–13)።

«ለምኑ ይሰጠችኋል፤ ፈልጉ ታገኛላችሁ፤ በር አንኳኩ ይከፈትላች ኋል» (ማቴ:ም:7ቍ:7)።

«ኃጢአታችንን ለእግዚአብሔር ብንናዘዝ እርሱ ታማኝና ጻድቅ ስለሆነ ኃጢአታችንን ሁሉ ይቅር ይልልናል፤ ከበደላችንም ሁሉ ያነጻናል» (1ኛ: ዮሐ:ም:1ቍ:9)።

በእነዚህና በሌሎችም ተመሳሳይ ማስረጃዎች መሠረት እግዚአብሔር አምላካችን ጸሎት ተቀባይ መሆኑን እንረዳለን። ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር አምላክ ጸሎትን የማይቀበልባቸው ሁኔቴዎች አሉ። ለምሳሌ ሙሴና አሮን በመሪባ ውሃ ጉዳይ እግዚአብሔርን ስላላከበሩ ወደ ተስፋ ምድር ከመግባት መከልከላቸው በኦሪት ዘኍልቍ ም:20ቍ:12 ላይ ተገልጦአል። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ይቅርታ አድርጎለት ያን የተስፋ ምድር ለማየት እንዲችል ሙሴ ወደ እግዚአብሔር ቢጸልይ ጸሎቱ ተቀባይነትን ያላገኘ መሆኑ በኦሪት ዘዳግም ም.3ቍ:23–26 ተገልጾአል።


www.ethiopianorthodox.org

በተመሳሳይ ሁኔታ ንጉሥ ሳኦል ከአማሌቃውያን ጋር ባደረገው ጦርነት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ አፈረሰ። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ፊቱን መለሰበት። በዚህም ምክንያት ምንም ቢጸጸትና ቢጸልይ እግዚአብሔር ጸሎቱን የማይ ሰማው ሆነ። በመጨረሻም በጠላቶቹ እጅ ወደቀ።

እግዚአብሔር የሙሴንና የሳኦልን ጸሎት ያልተቀበለበት ምክንያት በእግዚአብሔር ብዙ ከተሰጣቸው ከእነርሱ ብዙ ይጠበቅ ስለነበረ ነው (ሉቃ:12፥483) ።

ተቀባይነት ስለማያገኙ ጸሎቶች የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመልከት:-

«እጆቻችሁ በደም የተበከሉ ስለሆኑ፥ የቱንም ያኽል ሊመና ብታበዙ አልሰማችሁም» (ኢሳ:ም:1ቍ:15)።

‹በሰው ልጅ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ሁሉ በደሉ ይቅር ይባልለታል፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል የሚናገር ሁሉ ግን በዚህ ዓለምም ሆ በሚመጣው ዓለም በደሉ ይቅር አይባልለትም» (ማቴ:ም:12ቍ:32)።

«የጸሎታችሁን መልስ የማታገኙት፥ የለመናችሁትን ነገር በሥጋዊ ደስ ላይ ለማዋል በክፉ አሳብ ስለምትጸልዩ ነው» (ያዕ:ም:4ቍ:3) ።

በነዚህም ማስረጃዎች መሠረት ምንም እንኳ እግዚአብሔር አምላካች ጸሎትን ተቀብሎ የሚፈጽም መሆኑ ቢረጋገጥ አንዳንድ ጸሎቶች ግን በተለያ ምክንያቶች ተቀባይነት የማያገኙበት ጊዜ አለ።

<u>አባታችን ሆይ</u>:- ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደ መዛሙርቱ ያስተማራቸው የጸሎት ትምህርት የሚከተለው ሲሆን ይህ ትም ርት ለደቀ መዛሙርቱ ብቻ ሳይሆን ለያንዳንዱ ክርስቲያን ሁሉ የተሰጠ ነው ይኸውም እንደምን መጸለይ እንደሚገባን የጸሎት ናሙና ነው። ምንም እን አጭር ቢሆን ይህ ጸሎት ግን ለሰው ልጆች አስፈላጊ የሆኑ ጥያቄዎች ያሙአላል። ይህም ጸሎት በስድስት ክፍል ተከፍሎ ሦስቱ ለእግዚአብሔ ክብርና ምስጋና፥ ሦስቱ ደግሞ የሰውን ሥጋዊና መንፈሳዊ ፍላጎት በተመለከ ይቀርባል።



<u>አባታችን ሆይ</u> :- ጸሎቱ የሚቀርብለት እግዚአብሔር ርኅሩኅና ሰማያዊ አባታችን ነው። እግዚአብሔርን አባታችን ብለን መጥራታችን በጥምቀት እን ደገና ተወልደን የእግዚአብሔር ልጆች በመሆናችን ነው።

<u>በሰማያት የምትኖር</u>:- እግዚአብሔር በሰማይ የሚኖር ነው ሲባል እርሱ የሚኖረው ባሰማይ ብቻ ነው ማለት አይደለም። ሰማይ ለዐይናችን ከምድር ከፍ ያለ በመሆኑና እግዚአብሔርም በንጽሕናቱና በፈጣሪነቱ የሚኖርበት ቦታ ከፍ ያለ መሆን አለበት ለማለት ነው (2ኛ:ቆር:ም:5ቍ:1)።

<u>ስምህ ይቀደስ</u>:- ለእግዚአብሔር ሀልውናና ጠባይ ክብር መስጠት ይገባል።

<u>መንግሥትህ ትምጣ</u>:- የእግዚአብሔር መንግሥት የምትመጣው የሰው ልጅ ጠላት ዲያብሎስ ተደምስሶ በጌታችን ዳግም ምጽአት ጊዜ ነው። ስለዚህ፡ አባባሉ ሰይጣን ይደምሰስ ማለትም ሊሆን ይችላል።

<u>ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን</u>:- ይህ ሊሆን የሚችለው የቀድሞዎቹ ዐልፈው አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ሲተኩ ነው። ያን ጊዜ ኃጢአት አይኖርም (2ኛ:ጴጥ:ም:3ቍ:13)።

እነዚህ ከላይ የቀረቡት ሦስት ጸሎቶች እግዚአብሔርን የምናከብርባቸው ጸሎቶች ናቸው።

መንፈሳዊና ሥጋዊ ፍላጎታችን እንዲሟሉልን የምንጸልያቸው ሦስቱ ጸሎቶች ደግሞ የሚከተሉት ናቸው።

<u>የዕለት እንጀራችንን ስጠን ዛሬ</u>:- ይህን ዐይነቱን ጸሎት ቀደም ብሎ ያዕቆብና በኋላም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ጸልየውታል። ሌላው አስተሳሰብ ደግሞ ለሚመጣው ዓለም የሚሆነውን በረከት ዛሬውኑ ዋስትና ስጠን፤ ወይም ሰማያዊ ዕድል ፈንታችን በየዕለቱ እያደገ ይሂድ ለማለት ነው (ዘፍ:ም: 28ቍ:20፥ 1ኛ:ጢሞ:ም:6ቍ:8)።

<u>በደላችንን ይቅር በለን እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል</u>:- እኛ ይቅር እንል ዘንድ ሳይሆን እኛ ይቅር እንደንምለው ዐይነት ማለት ነው።

<u>ወደ ፈተና አታግባን፤ ከክፉ አድነን እንጂ</u>:- የእግዚአብሔርን ርዳታ ካላገኘ በቀር ሥጋ ለባሽ ሰው ደካማ ስለሆነና በቀላሉ ፈተና ሊጥለው



www.ethiopianorthodox.org

ስለሚችል እግዚአብሔር ከፈተና ያድነው ዘንድ ወይም ፈተናን ድል ለመ
ሣት ኀይል ይሰጠው ዘንድ እግዚአብሔርን መለመን ይገባል።

እነዚህ ከላይ የተገለጡት ልመናዎች የሰውን ልጅ መንፈሳዊና ሥጋ
ፍላጎቶች የሚመለከቱ ናቸው።

መንግሥት ያንተ ናትና ለዘለዓለሙ አሜን:- ይህ በእግዚአብሔር ላ
እምነትን የማጠናከሪያ ማረጋገጫ ነው።

## አባትንና እናትን ማክበር

እግዚአብሔር በሙሴ አማካይነት ከሰጠው ዐሥሩ ትእዛዛት አንዱ እንዲ
የሚል ነው:- «አባትህንና እናትህን አክብር፤ ይህን ብታደርግ እኔ በምሰጥ
ምድር የረኝ̈ርም ዘመን ዕድሜ ይኖርሃል» (ዘጸ:ም:20ቍ12)።

ይህን ርእስ በተመለከተ ሌሎችንም ጥቅሶች እንመልከት:-

«የወለደህ እርሱ ስለሆነ የአባትህን ምክር ስማ፤

እናትህም ባረጀች ጊዜ ውለታዋን ክፈል እንጂ አትናቃት» (ምሳ:ም:2
ቍ:22)።

«ልጆች ሆይ፥ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ፤ ይህ የሚገባ ነውና። መልካ
እንዲሆንልህ፥ ዕድሜህም በምድር ላይ እንዲረዝም አባትህንና እናትህን አ
ብር፤ እርስዋም የተስፋ ቃል ያላት ፊተኛይቱ ትእዛዝ ናት» (ኤፌ: ም:
ቍ:1–3)።

### ለወላጆቻቸው ታዛዦች የነበሩ ሰዎች

ይስሐቅ:- እግዚአብሔር አብርሃምን ለመፈተን ልጅህን ይስሐቅን መ
ዋዕት አድርገህ አቅርብልኝ ብሎት ነበር። አብርሃምም ለእግዚአብሔር ቃ
በመታዘዝ ወደ አንድ ተራራ ላይ ልጁን ይስሐቅን ወስዶ ለማረድ ቢላ
እስኪያነሣ ድረስ ለአባቱ ታዛዥ ሆነ እንጂ ምንም ዐይነት ተቃውሞ ማድረ
አልተነገረም። በዚያን ጊዜ ይስሐቅ ገና ወጣት ሲሆን አብርሃም ግን ዕድሜ
ከመቶ ዓመት በላይ ነበር። ይስሐቅ ለአባቱ ታዛዥ ስለነበረ ነው እንጂ ለ



እንኳ ቢቀር ሮጦ ከእጁ ማምለጥ ባላቃተውም ነበር። በዚህም መሠረት ይስሐቅ ለወላጆች ታዛዥነት ምሳሌ ነው (ዘፍ:22፥1–10)።

ዮሴፍ:- ወንድሞቹ ለእስማኤላውያን ነጋዴዎች ሸጠውት ወደ ግብጽ ከመወሰዱ በፊት ዮሴፍ ለአባቱ ታዛዥ የሆነ ልጅ ነበር። በኋላም በእግዚ አብሔር ፈቃድ ዮሴፍ የግብጽ ገገር በሆነ ጊዜ አባቱን በአክብሮት ወደ ግብጽ እንዲመጣ ያደረገው ከመላ ቤተሰቡ ጋር ነበር። ከዚያም ያዕቆብ ቃል ባስገባው መሠረት አባቱ በሞተ ጊዜ የአባቱን አስከሬን ወደ ምድረ ከነዓን ወስዶ በታላቅ ክብር ሥርዓተ ቀብሩን አስፈጽሞለታል (ዘፍ: 37፥42–50)።

የዮፍታሔ ሴት ልጅ:- ዮፍታሔ ከዐሞናውያን ጋር ጦርነት ለመግጠም በሄደ ጊዜ ስእለት ተስሎ ስለነበረ ጦርነቱን አሸንፎ ሲመለስ አስደንጋጭ ነገር አጋጠመው። ይኸውም ካለችው አንዲት ሴት ልጁ መለየት ነበር። በዚህ ጊዜ ልጁ ለድንግልናዋ እንድታለቅስ ሁለት ወር ብቻ እንዲፈቅድላት ከመጠየቅዋ በቀር የአባትዋን ፈቃድ ለመፈጸም መልስ የሰጠችው እንዲህ ብላ ነው። «አባቴ ሆይ፥ ለእግዚአብሔር ቃል ገብተህ ከሆነስ እግዚአብሔር ጠላቶችህን ዐሞናውያንን ስለተበቀለልህ በእኔ ላይ ልታደርግ ያቀድከውን ፈጽም።» በዚህም የቱን ያኽል ለአባትዋ ታዛዥ እንደነበረች እንገነዘባለን (መሳ: 11፥ 34–40)።

ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በለበሰው ሥጋ ከኃጢአት በቀር በሁሉም ነገር እንደ ሰው ሆኖአል። በዚህም መሠረት በሉቃስ ወንጌል ም. 2 ቍ 51 ላይ:- «ከዚያም በኋላ ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር ወደ ናዝሬት ሄደ፤ ይታ ዘዛቸውም ነበር» ተብሎአል።

## ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብና እንደበትን መጠበቅ:-

ለመንፈሳዊ ሕይወታችን መመሪያ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብ በጣም አስፈላጊ ነው። ጠላታችን ሰይጣን ሁልጊዜ በመንፈሳዊ መንገዳችን ላይ እየተጋረጠ ወደ ክፉ አስተሳሰብና ወደ ክፉ ሥራ ይመራናል። የእርሱን ወጥ መድ ለማምለጥና ቈራጥ ውሳኔ ለማድረግ ሁልጊዜ የቃለ እግዚአብሔር አስ ታዋሽነት ያስፈልገናል። ቃለ እግዚአብሔርም ማንነታችንን እንድናስታውስ የሚያደርገን ቅዱሳት መጻሕፍትን መላልሰን ስናነብ ነው።

www.ethiopianorthodox.org

ለምሳሌ በመጽሐፈ ነህምያ ም: 8 ቊ: 9 ላይ በነመለከት ካህኑ ዕዝራ ሕዝቡ ምን ማድረግ እንደሚገባው በማስረዳት ቅዱሳት መጻሕፍትን ለእስራ ኤላውያን ባነበበላቸው ጊዜ ልባቸው ተነክቶ ማልቀሳቸው ተነግሮአል። ቅዱ ሳት መጻሕፍትን በምናነብበት አብዛኛውን ጊዜ ልባችን ይሰበራል። ንስሓም ለመግባት እንወስናለን።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ቆላስይስ ሰዎች በላከው መልእክቱ መጨረሻ ላይ:- «ይህችን መልእክት እናንተ ካነበባችሁ በኋላ በሎዶቅያ ሰዎች ዘንድ ባለችው ቤተ ክርስቲያን እንድትነበብ አድርጉ፤ እናንተም ከሎዶቅያ የሚላክላችሁን መልእክት አንብቡ» ማለቱ ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብ የሚገኘውን ጥቅም ስለሚያውቅ ነው (ቆላ:ም:4ቊ:16)። እንዲያውም ለተሰ ሎንቄ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ መጨረሻ ላይ:- «ይህ መልእክት ለአማኞች ሁሉ እንዲነበብ በጌታ ስም ዐደራ እላችኋለሁ» ብሏል (1ኛ: ተሰ: ም: 5ቊ: 27)።

አንደበትን ከክፉ አነጋገር መጠበቅ እንደሚገባ ሲያስረዳ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሏል:- «ለሚሰሙት ጸጋን ይሰጥ ዘንድ እንዲያገለግል በጎ ቃል ካልሆነ በቀር ክፉ ቃል ከቶ ከአፋችሁ አይውጣ» (ኤፌ:ም: 4ቊ:29)።

ሐዋርያው ያዕቆብ ስለ አንደበታችን አደገኛነት በበለጠ ሲያብራራ እንዲህ ብሏል:- «ምላስ እንደ እሳት ናት፤ እርስዋም በአካል ክፍሎቻችን መካከል የምትገኝ ክፉ ዓለም ናት፤ ሥጋችንን ሁሉ ታረክሳለች፤ እንደ ገሀነም እሳት ኑሮአችንን ሁሉ ታቃጥላለች። የምድር አውሬዎችና ወፎች፥ በመሬት የሚ ሳቡና በባሕር የሚንቀሳቀሱ ፍጥረቶች ሁሉ በሰው ሊገሩ ይችላሉ፤ ደግሞም ተገርተዋል። ነገር ግን ምላስን ሊገራ የሚችል ማንም የለም፤ የሚገድል መርዝ የሞላባትና ዕረፍት የሌላት ክፉ ነገር ናት። በእርስዋ አባታችንን እግዚአብሔርን እናመሰግናለን፤ እንዲሁም በእርስዋ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩትን ሰዎች እንረግማለን። ከአንድ አፍ ምስጋናና እርግማን ይወጣሉ፤ ወንድሞቼ ሆይ፥ ይህ ሊሆን አይገባም» (ያዕ:ም:3ቊ:6–10)።

ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስም የክፉ አነጋገርን ጉጂነት ሲገልጽ:- «በእውነት እላችኋለሁ፤ ሰዎች በግዴለሽነት በሚናገሩት በያንዳንዱ ቃል በፍርድ ቀን ይጠየቁበታል፤ ከቃልህ የተነሣ ይፈረድልሃል፤ ከቃልህም የተነሣ ይፈረድብሃል» (ማቴ:ም:12 ቊ:36–37)።



የሚከተሉትን ተጨማሪ ማስረጃዎች እንመልከት:-

«ወንበዴዎች ክፉ ነገርን ያቅዳሉ፤ ንግግራቸውም እንደ እሳት የሚያ ቃጥል ነው» (ምሳ:ም:16ቊ:27)።

«ሰውን የሚያረክሰው ከአፍ የሚወጣው ነው እንጂ ወደ አፍ የሚገባው አይደለም» (ማቴ:ም:15ቊ:11)።

## ጥያቄዎች

1. መንፈሳዊነት ስንል ምን ማለታችን ነው?
2. ግብረገብነት ስንልስ ምን ማለታችን ነው?
3. መንፈሳዊነትና ግብረገብነት በምን ይመሳሰላሉ?
4. መንፈሳዊነትና ግበረገብነት በምን ይለያያሉ?
5. የመንፈሳዊነት ዋና ትኩረት ምንድነው?
6. የግብረገብነትስ ዋና ትኩረት ምንድነው?
7. ጸሎት ማለት ምን ማለት ነው?
8. አንድ ሰው ሥራውን ሲጀምር በጸሎት ከጀመረ ምን ይጠቀማል?
9. ችግር የደረሰበት ሰው ሲጸልይ ምን ያገኛል?
10. ኃጢአት የሠራ ሰው የእግዚአብሔርን ይቅርታ ሲለምን ምን ያገኛል?
11. ስለ ጸሎት የሚነሡ ጥያቄዎች ምንና ምን ናቸው?
12. ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ እግዚአብሔር የሚያረጋግጡት ነገር ምንድነው?
13. የእግዚአብሔር የማይለወጠው ቃሉ የትኛው ነው?
14. እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ምንን ሰጣቸው?
15. እግዚአብሔር ለሰዎች ምንን እንዲመርጡ ነገራቸው?
16. ፍጹም ጻድቅ የሆነ ሰው አለመኖሩን ከሚገልጹት የማስረጃ ጥቅሶች አንዱን አቅርብ።
17. ሰዎች የእግዚአብሔርን ሕግጋት ሙሉ በሙሉ መፈጸም ይችላሉን?

www.ethiopianorthodox.org

18. የጸሎት ዋና ገጽታ ምንድነው?

19. መልስ የማያስገኙ ጸሎቶች እነማን ናቸው?

20. ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ አባታችን ሆይ፥ የሚለውን ጸሎት ያስተማረው እነማንን ነው?

21. በምንጸልይበት ጊዜ «አባታችን» ማለታችን እንዴት ነው?

22. እግዚአብሔር የሚኖረው በሰማይ ብቻ ነውን?

23. መንግሥትህ ትምጣ ማለት ምን ማለት ነው?

24. «አባታችን ሆይ፥» የሚለው ጸሎት በስንት ይከፈላል?

25. ስለ ዕለት እንጀራ የጸለዩ እነማን ናቸው?

26. ለዕለት እንጀራ ሌላው ትርጒም ምንድነው?

27. ወላጆችን ስለማክበር የታዘዘ በየትኛው ክፍል ነው?

28. ለወላጆቻቸው ታዛዦች በመሆን በምሳሌነት የቀረቡት እነማን ናቸው?

29. ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብ ለምን ይጠቅመናል?

30. አንደበትን ስለመጠበቅ ከተሰጡት ማስረጃዎች አንዱን አቅርብ።

www.ethiopianorthodox.org

# ሁለተኛ ክፍል

## ምዕራፍ 1

## ትምህርተ ሃይማኖት

### የእግዚአብሔር መንግሥት

የቅዱሳት መጻሕፍትን ገጾች በማገላበጥ በተለያዩ ቦታዎች የእግዚአብሔር መንግሥት የሚለውን ሐረግ በምንመለከትበት ጊዜ ቃሉ ማለት ሐረጉ የተለያዩ ትርጒሞች ያሉት ሆኖ እናገኘዋለን። ከእነዚህም ትርጒሞች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል።

1. ይህ አሁን ያለንበት ዓለም ዐልፎ የፍጡር ሳይሆን የፈጣሪ አገዛዝ ብቻ የሚኖርበት ሁናቴ፤

2. እግዚአብሔር በፍጥረት ላይ ያለው ጌትነት፤

3. የእስራኤል ሕዝብና የሚኖሩባት ምድር፤

4. ለሕገ እግዚአብሔር በመታዘዝ ለወደፊት የሚወረስ ሰማያዊ ርስት፤

5. በእግዚአብሔር የተመረጡ የሃይማኖትና የአስተዳደር መሪዎች የሚገዙት አገዛዝ፥

6. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱው ራሱ ወይም እራሱ የመሠረተው መንግሥት

<u>የእግዚአብሔር አምላክ ብቸኛ አገዛዝ</u>:- የእግዚአብሔር መንግሥት ስንል እግዚአብሔር የበላይ ሆኖ የማይቈጣጠረው ፍጥረት አለ ለማለት አይደለም። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ራሳቸውን የማስተዳደር መብት ስለሰጣቸው አንዳንድ ከዚያ የተለዩ ሁኔታዎችን ለማመልከት የእግዚአብሔር መንግሥት እንላለን። ለምሳሌ ይህ አሁን ያለንበት ዓለም ዐልፎ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር በሚተካበት ጊዜ መንግሥቱ የእግዚአብሔር ብቻ እንጂ የማንም ፍጡር ሊሆን አይችልም።

ይህ አሁን ያለንበት ምድር ዐልፎ እግዚአብሔር አዲስ ሰማይንና አዲ ምድርን እንደሚፈጥር ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በሁለተኛው መልእክ ምዕራፍ 3 ከቍጥር 10 ጀምሮ ዘርዝሮ ገልጦታል። በዚያ በምንጠብቀ በወዲያኛው ዓለም ደግሞ አገዛዝና ፍርድ ያለ መሆኑን ለማመልከት ጌታች ኢየሱስ ክርስቶስ «በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሰድብ ቃል የሚናገር በዚህ ዓለምም ሆነ በሚመጣው ዓለም አይሰረይለትም» ብሏል (ማቴ: ም: 12 ቍ:32)። እንዲሁም ለወንጌልና ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ሲል ብዙ ነገሮችን የተ በወዲያኛው ዓለም መቶ እጥፍ ያገኛል ብሎአል (ማር: ም:10:ቍ:30)።

<u>እግዚአብሔር በፍጥረቱ ላይ ያለው ጌትነት</u>:- ፈጣሪ አምላካችን በፍ ረቱ ላይ ስላለው ጌትነት ለመናገር የእግዚአብሔር መንግሥት ይባላል ለዚህም የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመልከት።

«የእግዚአብሔር ዙፋን በሰማይ ነው፤ የእርሱም ገገርነት በሁሉም ላ ነው» (መዝ:103ቍ:19)።

«መንግሥትህ የዘለዓለም መንግሥት ናት፤ ግዛትህም ለልጅ ልጅ ነው (መዝ:145፥13)።

«እግዚአብሔር በምድር ሁሉ ላይ ይነግሣል» (ዘካ:ም:14ቍ:9)።

ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ «አባታችን ሆይ የሚባለውን ጸሎት ባስተማራቸው ጊዜ «ከክፉ አድነን እንጂ ወደፈተ አታግባን» ካለ በኋላ «መንግሥት ኃይል፥ ክብር የአንተ ነው» በማለት የእግ አብሔርን መንግሥትና ጌትነት አመልክቶአል (ማቴ: ም:6ቍ:13)።

<u>የእስራኤል ሕዝብና የሚኖሩባት ምድር</u>:- በብሉይ ኪዳን በተለያዩ ቦታዎ እንደተገለጠው እስራኤላውያንና የሚኖሩባት ምድር የእግዚአብሔር መን ሥት መባሉ የተለመደ ነው። ለዚህም የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመልከት፡

«ነገዶቻቸውና መሪዎቻቸው በተሰበሰቡ ጊዜ እግዚአብሔር በሕዝ በእስራኤል ላይ ነገሠ» (ዘዳ:ም:33ቍ:5)።

«የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርም በጽዮን ተራራና በኢየሩሳሌም ላ ይነግሣል» (ኢሳ:ም:24ቍ:23)።



«ቅዱሳችሁ የእስራኤል ፈጣሪ ንጉሣችሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ» (ኢሳ: ም:43ቍ:15)።

«እኔም እላችኋለሁ:- ብዙዎች ከምሥራቅና ከምዕራብ ይመጣሉ፤

ከአብርሃምና ከይስሐቅ፥ ከያዕቆብም ጋር በመንግሥተ ሰማያት ይቀመ ጣሉ፤ የመንግሥቱ ልጆች ግን በውጭ ወዳለው ጨለማ ይጣላሉ» (ማቴ ም:8 ቍ:11–12)።

«ስለዚህ እላችኋለሁ:- የእግዚአብሔር መንግሥት ከእናንተ ተወስዳ ፍሬ ለሚያፈሩ ሕዝብ ትሰጣለች» (ማቴ:ም:21ቍ:43) ።

በእነዚህም ማስረጃዎች መሠረት ብዙ ጊዜ በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር መንግሥት የሚለው ሐረግ እግዚአብሔር በእስራኤል ሕዝብ ላይ ያለው ልዩ ገገርነት ማለት መሆኑን እንረዳለን።

<u>ለወደፊት የሚወረስ የሰማያዊ ርስት ተስፋ</u>:- መንግሥት ሰማይ የሚለው ሐረግ ለሕገ እግዚአብሔር በመታዘዝ ለወደፊት እንደሚወረስ ተስፋ ሆኖም ቀርቦአል።

ለዚህም የሚከተሉትን ጥቅሶች እንመልከት:-

«በቀኝ በኩል ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል:-

እናንተ የአባቴ ቡሩካን ፡ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ» (ማቴ:ም:25ቍ:34)።

«የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም፥ በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ነው እንጂ መብልና መጠጥ አይደለም» (ሮሜ:ም:14ቍ:17)።

«ዐመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደማይወርሱ አታውቁም ን?» (1ኛ: ቆሮ:ም:6ቍ:9) ።

«ምቀኝነት፥ ስካር፥ ቅጥ ያጣ ፈንጠዝያ የመሳሰሉ ናቸው፤ ከዚህ በፊት እንደነገርኋችሁ፥ እንደዚህ ያሉትን ነገሮች የሚያደርጉ ሰዎች የእግዚአ ብሔርን መንግሥት አይወርሱም» (ገላ:ም:5ቍ:21)። «ስለዚህ ወንድሞች



www.ethiopianorthodox.org

ሆይ፥ መጠራታችሁንና መመረጣችሁን ለማረጋገጥ በይበልጥ ትጉ፤ ይ
ብታደርጉ ከቶ አትሰናከሉም። በዚህ ዐይነት ዘለዓለማዊት ወደሆነችው
ጌታችንና አዳኛችን ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት ለመግባት ሙሉ መብ
ይሰጣችኋል» (2ኛ:ጴጥ:ም:1ቍ:10–11)።

ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ባስተማረበ
የጸሎት ትምህርት ውስጥ «መንግሥትህ ትምጣ» ካለ በኋላ «ፈቃድህ በሰማ
እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን ብሏል። ይህም የሚያመለክተው
እግዚአብሔርና የእግዚአብሔር ትእዛዞች በሰማይ እንደሚከበሩ ሁሉ በም
ርም ይከበሩ ለማለት መንግሥትህ ትምጣ ተባለ።

<u>እግዚአብሔር በሾማቸው ሰዎች የሚካሄድ መንግሥት</u>:- ሌላው የ
ዚአብሔር መንግሥት የሚባለው ደግሞ በሕዝብ ሳይሆን በእግዚአብሔ
ተመርጠው የሚሾሙ ሰዎች የሚያስተዳድሩት መንግሥት ነው።

ለዚህም የሚከተሉትን ማስረጃዎች እንመልከት:-

«እግዚአብሔርም ሳሙኤልን እንዲህ አለው:- በእነርሱ ላይ እንዳልነ
እኔን እንጂ አንተን አልናቁምና በሚሉህ ነገር ሁሉ የሕዝቡን ቃል ስማ» (1
ሳሙ:ም:8ቍ:7)።

«እግዚአብሔር ብዙ ልጆች ሰጥቶኛል፤ ከልጆቼ ሁሉ በእግዚአብሔ
መንግሥት ዙፋን ላይ ተቀምጦ በእስራኤል ላይ ይነግሥ ዘንድ ል
ሰሎሞንን መርጦታል:» (1ኛ: ዜ:መ:ም:28ቍ:5)።

«ምሕረቴን ከልጅህ በማራቅ አልተወውም፤ በሕዝቤና በመንግሥቴ
ለዘለዓለም እሾመዋለሁ» (1ኛ:ዜ:መ:ም:17ቍ:13–14)።

ከእነዚህ ከላይ ከተገለጡት ሌላ ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስ
ስለመንግሥተ እግዚአብሔር የተለያዩ ገለጻዎችን አድርጓል። ለምሳሌ በታ
ተራራ ላይ ለሦስት ደቀ መዛሙርቱ መለኮታዊ ክብሩን የሚገልጥ መሆ
አስቀድሞ ሲናገር እንዲህ ብሏል:- «እውነት እላችኋለሁ፤ የሰው ልጅ በመ
ሥቱ ሲመጣ እስኪያዩ ድረስ እዚህ ከቆሙት መካከል ሞትን የማይቀም
አሉ» (ማቴ:ም:16ቍ:28)።



እንዲሁም በሌላ ጊዜ ፈሪሳውያን የእግዚአብሔር መንግሥት መቼ እንደ ምትመጣ ሲጠይቁት የሰጣቸው መልስ እንደሚከተለው ነው:- «የእግዚአ ብሔር መንግሥት በመጠባበቅ አትመጣም፡ ደግሞም እነኋት በእዚህ ወይም እነኋት በእዚያ አይሉአትም። እነሆ፥ የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ ናት» በማለት የእርሱ በዚያ መገኘት የእግዚአብሔር መንግሥት መገኘት መሆኑን አመልክቶአል (ሉቃ 3፡17 ቍ: 20–21)።

ከዚያም በላይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለእግዚአብሔር መንግሥት የተለያዩ ምሳሌዎችን ተናግሮአል። የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።

<u>የመረብ ምሳሌ</u>:- መንግሥተ ሰማይ ወደ ባሕር የተጣለች መረብን ትመስላለች። እርስዋም በየዐይነቱ ዓሣ ስትሰበስብ ዓሣ አጥማጆቹ ወደ ባሕሩ ዳር ጐትተው በማውጣት ደኅና ደኅናውን መርጠው አስቀምጠው መጥፎ መጥፎውን ግን ወዲያ ይጥሉታል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳለው በዓለም መጨረሻም እንዲህ ይሆናል፤ መላእክት መጥተው ኃጢአተኞችን ከጻድቃን ይለዩአቸዋል። ወደ እቶን እሳትም ይጥሉአቸዋል፤ በዚያ ለቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።

<u>የእንክርዳድ ምሳሌ</u>:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምሳሌ ሲናገር እንዲህ ብሏል:- መንግሥተ ሰማይ በእርሻው ውስጥ መልካም ዘር የዘራውን ሰው ትመስላለች። ያ ዘሪ መልካም ዘር ዘርቶ ከተኛ በኋላ ጠላት መጥቶ በእርሻው ውስጥ እንክርዳድ ዘራበት። አገልጋዮቹ እንክርዳዱን ለመንቀል ብለው ስንዴውንም እንዳይነቅሉ እስከ መከር ጊዜ ድረስ ስንዴውም እንክርዳዱም አብረው እንዲያድጉ ነገራቸው። በመከር ጊዜ ግን እንክርዳዱን እንዲያቃጥሉና ስንዴውን ግን በጐተራ እንዲከትቱት አዘዛቸው። ስንዴው የመንግሥተ ሰማያትን እንክርዳዱ ደግሞ የገሀነም እሳትን ሰዎች የሚያመለክት ነው።

<u>የሰናፍጭ ዘር ምሳሌ</u>:- መንግሥተ ሰማይ አንድ ሰው ወስዶ በእርሻው ውስጥ የዘራትን የሰናፍጭ ዘር ትመስላለች። ከዘር ሁሉ የምታንስ ሲሆን ባደገች ጊዜ ግን ከአትክልቶች ሁሉ ትበልጣለች፤ ዛፍም የምታኽል ስለሆነ ወፎች መጥተው ያርፉባታል፤ ጎጆም ይሠሩባታል። ይህም የሚያመለክተው የእግዚ.አብሔር መንግሥት ወንጌል በጥቂቶች ሰዎች ጀምሮ ወደ ብዙዎች ሰዎች የምትስፋፋ መሆንዋን ነው።

www.ethiopianorthodox.org

__የእርሾ ምሳሌ__፡- መንግሥተ ሰማይ አንዲት ሴት ወስዳ ከሦስት መስፈሪያ ዱቄት ጋር የለወሰችውን እርሾ ትመስላለች። እርሾውም ሊጡን ሁሉ እንዲቦካ አደረገው። ይህም የሚያመለክተው በጥቂቱ የሚጀመረው የወንጌል ትምህርት በብዛት የሚስፋፋ መሆኑን ነው።

እነዚህ ምሳሌዎች የሚገኙ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 13 ላይ ነው።

## የሰው ልጆች ነጻ ፈቃድ

የሰው ልጆች ነጻ ፈቃድ ማለት ምን ማለት ነው? ነጻ ፈቃድ ወይም የፍላጎት ነጻነት ማለት አንድን ነገር ለመውሰድ ወይም ለመተው፥ ለማድረግ ወይም ላለማድረግ የግል ምርጫ ማለት ነው። እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰውን በፈጠረው ጊዜ ሙሉ የፈቃድና የፍላጎት ነጻነትን ሰጠው እንጂ ካላንቀሳቀሱት እንደማይንቀሳቀስ የፋብሪካ መሣሪያ አላደረገውም። ነጻነትንም ከመስጠት ጋር የትኛው ድርጊት ጠቃሚና የትኛው ድርጊት ጐጂ መሆኑን አስተማረው። ትምህርት ቤቱም የዔደን ገነት ነበር። የመጀመሪያውን ትምህርት ሲሰጠው እንዲህ ብሎት ነበር፡- «ከገነት ዛፎች ሁሉ ፍሬ ብትበላ ምንም ችግር አይደርስብህም፤ ነገር ግን ክፉንና ደግን ከምታስታውቀዋ ዛፍ ብትበላ ሞትን ትሞታለህ።» አዳምም በተሰጠው የፈቃድ፥ የፍላጎትና የምርጫ ነጻነት መሠረት ያን ፍሬ ሳይበላ ከመኖር ይልቅ በልቶ መሞትን ስለመረጠ በማይለወጠው የእግዚአብሔር ቃል መሠረት የሞቱ ፍርድ በሥራ ላይ እንዲውል ተደረገ። ስለዚህም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «በአንድ በአዳም ኃጢአት ምክንያት ፍርድ በሰው ሁሉ ላይ እንደመጣ በአንዱ በክርስቶስ ጽድቅ ለሰዎች ሁሉ መጥቶአል» ብሎአል (ሮሜ:ም:5ቍ:12እና:18)።

ምስጋና፥ ግዴታ፥ የሥራ ዋጋ (ሽልማት) ወይም ቅጣትና ወቀሳ ከነጻ ፈቃድ ወይም ከነጻ ድርጊት ጋር የተያያዙ ናቸው።

የሰው ልጅ ነጻ ፈቃድና ነጻ ፍላጎት ባይኖረው ኖሮ ደንቦችና ሕግጋት መኖር ባላስፈለጋቸውም ነበር። አንድ ሰው ከሌሎች ሰዎች ምክር የሚጠይቀው የተሻለ መስሎ የታየውን ሐሳብ ለመቀበልና ያልመሰለውን ደግሞ ለመተው የመምረጥ ነጻነት ስላለው ነው።

__የእግዚአብሔር ፈቃድ ሁሉም እንዲድን ነው__፡- ምንጊዜም ቢሆን እግዚአብሔር ሰው ሁሉ ይድን ዘንድ እንጂ ይኰነን ዘንድ ፍላጎቱ አይደለም። ይህም



www.ethiopianorthodox.org

ባለመሆኑ ነው እግዚአብሔር አዳምን ያን ፍሬ በልቶ እንዳይሞት ያስጠነቀቀው። እንዲሁም ቃየል በወንድሙ በአቤል ላይ ቅናት አድሮበት ፊቱ በተኰሳተረ ጊዜ እግዚአብሔር እንዲህ ብሎታል፡- «የተቈጣኸው ለምን? ፊትህም በቊጣ የተከሳተረው ለምንድን ነው? መልካም ነገር አድርገህ ቢሆን ኖሮ ፊትህ በፈገግታ ባበራ ነበር፤ አሁን ግን ያደረግኸው ክፉ ነገር በመሆኑ ኃጢአት በበርህ ላይ አድብቷል፤ በቊጥጥሩ ሥር ሊያደርግህም ይፈልጋል፤ ሆኖም አንተ ልታሸንፈው ይገባል።» እግዚአብሔር በዚህ ዓይነት ቢያስጠነቅቀውም እርሱም እንደ አዳምና እንደ ሔዋን አለመታዘዝን ስለመረጠ ወንድሙን አቤልን በመግደል ነፍሰ ገዳይ ሆነ። እግዚአብሔር ያን ማስጠንቀቂያ የሰጠው ሰው ሁሉ እንዲድን እንጂ ማንም እንዲጠፋ ስለማይፈልግ ነው።

ሰው ሁሉ እንዲድን እንጂ ማንም ሰው እንዳይጠፋ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ከሚገልጹት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል።

«ኃጢአተኛው ከመንገዱ ተመልሶ በሕይወት ይኖር ዘንድ እንጂ ኃጢአተኛው ይሞት ዘንድ አልፈቅድም ይላል ጌታ እግዚአብሔር» (ሕዝ: ም: 33ቍ:11)።

«የእግዚአብሔር ፈቃድ ሰዎች ሁሉ እንዲድኑና እውነትን እንዲያውቁ ነው»(1ኛ:ጢ.ሞ:ም:2ቍ:4)።

«አንዳንድ ሰዎች እንደሚመስላቸው ጌታ የተናገረውን ቃል ለመፈጸም አይዘገይም፤ ግን ሰው ሁሉ ለንስሐ እንዲበቃ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ፈልጎ ስለ እናንተ ይታገሣል» (2ኛ:ጴ:ም:3ቍ:9)።

በእነዚህም ማስረጃዎች መሠረት እግዚአብሔር ሁሉም ሰው እንዲድን እንጂ ማንም እንዲጠፋ የማይፈልግ መሆኑን እንረዳለን። ይሁን እንጂ የጥፋትን መንገድ የሚመርጠውን ሰው አስቀድሞ በሰጠው የፈቃድና የፍላጎት ነጻነት መሠረት ይተወዋል እንጂ የማይፈልገውን ድርጊት እንዲያደርግ ወይም ሊያደርግ የሚፈልገውን ድርጊት እንዳያደርግ አያስገድደውም። ሆኖም የድርጊቱ ወይም ያለማድረጉ ውጤት ምን እንደሚሆን እንዲያውቅ በተለያዩ መንገዶች ይገልጥለታል።

<u>የእግዚአብሔር ውሳኔ አለመለወጥና ነጻ ፈቃድ</u>:- እግዚአብሔር በደግነቱ ላይ ወይም ከደግነቱ፥ በመሐሪነቱ ላይ ወይም ከመሐሪነቱ፥ በፍርዱ ላይ ወይም ከፍርዱ፥ በቅድስናው ላይ ወይም ከቅድስናው፥ በዐዋቂነቱ ላይ ወይም ከዐዋቂነቱ፥ በጥበበኛነቱ ላይ ወይም ከጥበበኛነቱ በኀያልነቱ ላይ ወይም ከኀያልነቱ ምንም የሚጨምረው ወይም የሚቀንሰው ነገር ስለሌለ አይለ ወጥም። ፍርዶቹና ድርጊቶቹ በፍጹም የማይሳሳቱ ስለሆኑ ተመልሶ የሚያር ማቸው አይደሉም። ፍርዶቹም ከዘመናትና ከሁናቴዎች ጋር የሚለወጡ አይደሉም። በዓለም ላይ ምን እንደሚደረግና ወደፊትም ሊደረግ ያለውን ነገር በዘለዓለማዊ ዕውቀቱ የሚያውቀው ስለሆነ ሐሳቡን መለወጥ፥ ውሳኔውን ማስተከከልና መለኮታዊ ፍርዱን ማሻሻል የሚያስፈልገው አይደለም።

እግዚአብሔር የማይለወጥ መሆኑን ከሚገልጹት ማስረጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል:-

«ሐሰትን ይናገር ዘንድ እግዚአብሔር ሰው አይደለም፤ ይጸጸትም ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም፤ እርሱ ያለውን አያደርገውምን? የተናገረውንስ አይፈጸመውን?» (ዘኁ:ም:23ቁ:19)።

«የእስራኤል ኀይል እንደ ሰው የሚጸጸት አይደለም፤ አይዋሽም፤ አይጸጸትም» (1ኛ: ሳሙ:ም:15ቁ:29)።

«እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም» (ሚል:ም:3ቁ:6)።

«ሰማይና ምድር ያልፋሉ፤ ቃሌ ግን አያልፍም» (ማቴ:ም:24 ቁ35)።
«እግዚአብሔር ከመረጠና ጸጋውን ከሰጠ በኋላ ባደረገው ነገር አይጸጸትም» (ሮሜ:ም:11ቁ:29)።

«መልካም ስጦታና ፍጹም በረከት ሁሉ ... የሚመጣው እንደ ጥላ መዘዋወር ወይም መለዋወጥ ከሌለበት ከእግዚአብሔር ነው» (ያዕ: ም: 1ቁ:17)።

እግዚአብሔር ሰውን ምን ቢያደርግ እንደሚጸድቅና ምን ቢያደርግ እንደሚኰነን አስቀድሞ አስጠንቅቆታል። የሚያስኰንን ተግባር ቢፈጽም እንደሚኰነን የማይለወጠው የእግዚአብሔር ቃል ያረጋግጣል። ይሁን እንጂ ምንም እንኳ ይህ ማስጠቀቂያ ቢሰጠን የሚያስፈርድብንን ሥራ የምንፈጽም ሰዎች ጥቂቶች አይደለንም። ታዲያ የእግዚአብሔር ቃል የማይለወጥ ከሆነ እንዴት ኃጢአተኞች በንስሐና በጸሎት የእግዚአብሔርን ውሳኔ ሊያስለውጡ ይችላሉ ተብሎ ይጠየቅ ይሆናል።

የእግዚአብሔር ውሳኔ ተለውጦ አያውቅም፤ ማንም ያስለወጠው የለም፤ ሊያስለውጠውም የሚችል የለም። አንድ ሰው ኃጢአት ከሠራ በኋላ በንስሐና በጸሎት የእግዚአብሔርን ይቅርታ በመለመኑ ኃጢአቱ የተሰረየለት እንደሆነ የእግዚአብሔር ውሳኔ ተለወጠ ማለት አይደለም።

በእግዚአብሔር ፈቃድ የጸኑ ወይም ከኃጢአታቸው በንስሓ የተመለሱ ሰዎች እንደሚድኑና ያለንስሓ በኃጢአታቸው የሚቀጥሉ ሰዎች ደግሞ እንደሚቀጡ የማይለወጠው የእግዚአብሔር ውሳኔ ነው (ሕዝ: 33፥ 11፤ ዘዳ:30፥19. ሲራ:15፥11–17)። ይህ የእግዚአብሔር ውሳኔ ሲሆን ኃጢያ አተኛው በንስሓና በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ቢመለስ ለውጥ የመጣው በእርሱ በኩል ነው እንጂ በእግዚአብሔር በኩል አይደለም።

ንስሓ የሚገባ ሰው ይቅርታ እንደሚደረግለት በእግዚአብሔር ዘንድ የተላለፈው ውሳኔ ቀደም ብሎ ነው እንጂ እያንዳንዱ ሰው ንስሓ ከገባ በኋላ የሚተላለፍ ውሳኔ አይደለም። በዚህም መሠረት የእግዚአብሔር ውሳኔ የማይ ለወጥ መሆኑን እንገነዘባለን።

ስለዚህም የሰው ልጅ ነጻ ፈቃድ ከማይለወጠው ከእግዚአብሔር ጸሎት ተቀባይነት ጋር ምንም የሚቃረነው ነገር የለም።

<u>ጊዜ የማይወስነው የእግዚአብሔር ዕውቀትና የሰዎች ነጻ ፈቃድ</u>:- እግዚ አብሔር በሁሉም ቦታ የሚገኝ እንደመሆኑ በሰማይና በምድር ሙሉ ነው። በመለኮቱም ውሱንነትና መለወጥ የለበትም። ዐዋቂነቱም ፍጹም ነው እንጂ ውሱን አይደለም። የእግዚአብሔር ዐዋቂነት መለኮታዊ ጠባዩ ነው እንጂ በትምህርት የተገኘ አይደለም። እንዲሁም የእግዚአብሔርን ዐዋቂነት ጊዜና ቦታ አይወስነውም። ያለፈው አይረሳም፤ አሁን ያለው ሁናቴ በመላ ይታ ወቃል እንጂ ጊዜና ቦታ አይወስነውም፤ ወደፊትም የሚሆነው ማንኛውም ሁናቴ በአሁኑ ጊዜ እንዳለ ሆኖ በእግዚአብሔር ዘንድ በግልጥ ይታወቃል።


www.ethiopianorthodox.org

ታዲያ፥ እግዚአብሔር ወደፊት ሊደርሱ የሚችሉትን ነገሮች የሚያውቅ ሆኖ ለምን እንዲደርሱ ይፈቅዳል? ለምንስ እንዳይደርሱ አያደርግም? ተብሎ ይጠየቅ ይሆናል።

ቀደም ተብሎ እንደተገለጠው እግዚአብሔር ሲፈጥረው ጀምሮ ለሰው ልጅ የፈቃድና የፍላጎት ነጻነትን ሰጥቶታል። በዚህም ምክንያት ለያንዳንዱ እንደየተግባሩ ጽድቅን ወይም ኵነኔን ከማዘጋጀቱ በቀር ሰው ያልፈለገውን እንዲያደርግ፥ ወይም የፈለገውን እንዳያደርግ አያስገድደውም። ስለዚህ የእግዚአብሔር የቅድሚያ ዕውቀት የሰውን ነጻ ፈቃድ ያለመገደብ መለኮታዊ ጠባዩን አይለውጠውም።

ይህንንም በሚከተለው ጥቅስ እንመልከት።

«ሕዝቤ ግን ቃሌን አልሰሙኝም፤ እስራኤልም አላዳመጠኝም። እንደልባቸው ሥራ ተውኋቸው፤ በልባቸውም ሐሳብ ሄዱ።» (መዝ: 81 ቁ: 11–12)

<u>የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች</u>:- ስለሰው ልጆች ነጻ ፈቃድ ብዙ የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች ያሉ ሲሆን ከእነርሱም መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል።

> «ለማይወደው ነገር መቼም ምክንያት ስለማይሆን በኃጢ
> አት ለመውደቁ ምክንያት የሆነብኝ እግዚአብሔር ነው
> አትበል፤ ኃጢአተኛን ስለማይፈልገው እንድሳሳት ያደረ
> ገኝ እርሱ ነው አትበል።
>
> እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁሉ ይጠላል፤ እግዚአብሔ
> ርንም የሚፈሩ ኃጢአትን አይወዱም።
>
> እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰውን ፈጥሮ የፈለገውን እንዲ
> ወስን ነጻነትን ሰጠው። አንተም ከፈለግህ ትእዛዛትን ልትጠ
> ብቅ ትችላለህ፤ ለትእዛዛቱ ታማኝ የመሆን ችሎታም
> አለህ።
>
> እግዚአብሔር እሳትንና ውሃን በፊትህ አኑሮልሃል፤ አንተ
> ወደመረጥኸው እጅህን ክተት። ሰው በፊቱ ሕይወትና ሞት
> አሉለት፤ ለእርሱም የመረጠው ይሰጠዋል» ሢራክ: ም:
> 15ቍ:11–17)።



«ሕይወትንና ሞትን፥ በረከትንና መርገምን በፊታችሁ እንዳስቀመጥሁ እኔ ዛሬ ሰማይንና ምድርን በአንተ ላይ አስመሰክራለሁ፤ እንግዲህ አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጥ» (ዘዳ:ም:30ቍ:19)።

«እግዚአብሔርን ማምለክ ክፉ መስሎ ቢታያችሁ አባቶቻችሁ በወንዝ ማዶ ሳሉ ያመለኳቸውን አማልክት ወይም በምድራቸው ያላችሁባቸውን የአሞራውያንን አማልክት ታመልኩ እንደሆነ የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ። እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን» (ኢያ:ም:24ቍ:15)።

«ማንም ሰው ሲፈተን እግዚአብሔር ፈተነኝ አይበል፤ እግዚአብሔር በክፉ አይፈትንም፤ እርሱ ራሱ ማንንም አይፈትንም፤ ነገር ግን እያንዳንዱ ሰው በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል። ከዚህ በኋላ ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች፤ ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች» (ያዕ:ም:1ቍ:13–15)።

## <u>ጾም</u>

ጾም ማለት ከቀኑ እስኪተወሰነ ሰዓት ድረስ ምንም አለመብላት ነው። ለምሳሌ እንደ ቅዱስ ጴጥሮስና እንደ ቆርኔሌዎስ ማለት ነው (የሐ: ሥ: ም: 10ቍ:3–9)። ለተወሰነው ሰዓትም ከተቈየ በኋላ ጾሞሚው የሚበላው ዳንኤል በጾመ ጊዜ እንዳደረገው ከቅባት ነጻ የሆነ ምግብ ነው።

«በዚያን ወራት እኔ ዳንኤል ሦስት ሳምንት ሙሉ ሳዝን ነበርሁ። ማለፊያ እንጀራም አልበላሁም፤ ሥጋና ጠጅም በአፌ አልገባም፤ ሦስቱም ሳምንት እስኪፈጸም ድረስ ዘይት አልተቀባሁም» (ዳን: ም:10ቍ:2–3)።

ዳንኤልም ይህን ሲያደርግ እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን ባዘዘው መሠረት መፈጸሙ ነው።

እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን ያለው እንዲህ ነው:-

«አሁንም ጥቂት ስንዴና ገብስ፥ ባቄላና ምስር፥ ማሽላና አጃ ውሰድ፥ ሁሉንም በአንድነት ቀላቅለህ እንጀራ ጋግር፥ ይህም በግራ ጐንህ በምትተኛባቸው በ390 ቀኖች ውስጥ የምትመገበው ነው» (ሕዝ:ም:4ቍ:9)።



www.ethiopianorthodox.org

በጾምም አማካይነት ራሳችንን በማዋረድና ሰውነታችንን በማድከም ዓመፀኛውን ሥጋችንን መቈጣጠር እንለማመዳለን።

የሚከተሉትን የባለመዝሙሩን አባባሎች እንመልከት:-

«እኔስ እነርሱ በታመሙ ጊዜ ማቅ ለበስሁ፤ ነፍሴንም በጾም አደከ ምኋት» (መዝ:35ቍ:13)።

«ጕልበቶቼ በጾም ደከሙ፤ ሥጋዬም ቅቤ በማጣት ከሳ» (መዝ 109 ቍ:24)።

<u>የአጽዋማት ሥነ ሥርዓት</u>

አጽዋማት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥርዓት እንዲኖራቸው መደረግ የጀመሩት ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ነው።

«እነርሱም እግዚአብሔርን ሲያመልኩና ሲጾሙ ሳለ መንፈስ ቅዱስ እኔ ለመረጥኋቸው ሥራ በርናባስንና ሳውልን ለዩልኝ አለ» (የሐ: ሥ: ም: 13ቍ:2)።

ይህም የሆነው ቀደም ብሎ ጌታችን የተናገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ነው:-

«ሙሽራው ከእነርሱ ጋር እያለ ሚዜዎች ማዘን ይገባቸዋልን? ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ የሚለይበት ጊዜ ይመጣል፤ በዚያን ጊዜ ይጾማሉ» (ማቴ:ም:9ቍ:15)።

<u>ቤተ ክርስቲያን የወሰነቻቸው አጽዋማት</u>:- ቤተ ክርስቲያን ከጌታችን በተቀበለችው ሥልጣን መሠረት ለአምልኮተ እግዚአብሔር ልዩ ልዩ ሥርዓ ቶችን አዘጋጅታለች። በዚህም መሠረት የደነገገቻቸው የአጽዋማት ዝርዝር የሚከተሉት ናቸው:-

<u>የጌታችን ጾም:-</u> ይህ ጾም በሀገራችን ዐቢይ ጾም ወይም የሁዳ ጾም ይባላል። የጌታችን ጾም የተባለበት ምክንያት ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ የጾመው የአርባ ቀኖች ጾም የጾሙ መነሻ በመሆኑ ነው። የቀኖቹም ብዛት



ኀምሳ አምስት ቀኖች ናቸው። አርባው ቀኖች ጌታችን የጾማቸው ሲሆኑ ዐሥራ አምስቱ ቀኖች የተጨመሩት በቤተ ክርስቲያን ውሳኔ ነው። የመጀመሪያው አንድ ሳምንት የዝግጅት ጊዜ ሲሆን የመጨረሻው አንድ ሳምንት ግን የጌታ ችን ሕማማት መታሰቢያ ነው። ጽዋሚው የመጨረሻውን ሳምንት ማለት የሕማማቱን ሳምንት በሚጾምበት ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ለማዳን ብሎ በእኛ ምትክ ሆኖ የተቀበለውን ሕማም ያስታውሳል።

<u>የልደት ጾም</u>:- የዚህ ጾም መጀመሪያ ሁልጊዜ ኅዳር 16 ቀን ሆኖ መፈሰኪያው በሦስት ተከታታይ ዓመቶች ታኅሣሥ 29 ቀን ነው። በአ ራተኛው ዓመት ማለት በዘመነ ዮሐንስ ግን የልደት በዓል የሚውለው ታኅሣሥ 28 ቀን ስለሆነ የሚፈሰከው በታኅሣሥ 28 ቀን ነው። ይህም የሆነበት ምክን ያት የሚከተለው ነው።

ጌታችን የተፀነሰው መጋቢት 29 ቀን መሆኑን የቤተ ክርስቲያን ትውፊት ያረጋግጥልናል። ከመጋቢት 29 ቀን እስከ ታኅሣሥ 29 ቀን ድረስ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ሊሆን የሚችለው በነሐሴና በመስከረም መካከል የምትመጣዋ ጳጒሜ አምስት ቀን ብቻ የሆነች እንደሆነ ነው። ጳጒሜ ግን ስድስት ቀን ሆና በምትውልበት ጊዜ ከመጋቢት 29 ቀን ተነሥቶ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን የሚሆነው በታኅሣሥ 28 ቀን ነው። እንደሚታወቀው አንዲት ሴት ፀንሳ የምትወልደው በዘጠኝ ወር ከአምስት ቀንዋ ነው። እመቤታችንም ጌታችንን የወለደችው በዚሁ የጊዜ ርዝመት እንጂ ከዚያ የተለየ ሊሆን አይችልም። በዚህም መሠረት የዘመነ ዮሐንስ መግቢያ ጳጒሜ 6 ቀን ስለሚሆን ሁልጊዜ በዘመነ ዮሐንስ የልደት በዓል ታኅሣሥ 28 ቀን ይውላል፤ የገና ጾምም የሚፈሰከው በዚያኑ ዕለት ነው። ይህም የቤተ ክርስቲያን ደንብና ሥርዓት ስለሆነ በራሳችን ስሜት ተነሣሥተን የልደትን ጾም መነሻ ወይም መድረሻ ልንለውጥ አንችልም።

ቤተ ክርስቲያን ይህን ጾም የደነገገችበት ምክንያት አምላካችን የሰውን ልጆች ከኃጢአትና ከሰይጣን ተገዢነት ስለተቤዠ ምስጋና ለማቅረብ ነው። እንዲሁም ነቢዩ ሙሴ የእግዚአብሔርን ቃል በጾም እንደተቀበለ እኛም የእግዚአብሔርን ቃል ማለት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ልደት አስቀድመን በመጾም እንቀበለዋለን።

<u>የሐዋርያት ጾም</u>:- ክርስቲያኖች የትንሣኤ በዓላቸውን ከአይሁድ የፋሲካ በዓል በፊት ወይም ከአይሁድ የፋሲካ በዓል ጋር አብረው እንዳያከብሩ በዓለም



www.ethiopianorthodox.org

ዐቀፍ ሲኖዶሶች ተወስንዋል። የትንሣኤ በዓልም መከበር ያለበት የአይሁድ የፋሲካ በዓል ከተከበረ በኋላ በሚቀጥለው እሑድ ነው። የሐዋርያት ጾም ደግሞ የተያያዘው ከትንሣኤ በዓል ጋር በመሆኑና ጾሙም የሚፈስከው ሁልጊዜ በሐምሌ 5 ቀን በመሆኑ የጾሙ ቀኖች ብዛት በ15 እና በ49 ቀኖች መካከል ከፍና ዝቅ ይላል።

የዚህም ጾም ምክንያት በሐዋርያቱ ላይ ስለወረደው የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ለእግዚአብሔር ምስጋና ለማቅረብ ነው።

<u>የእመቤታችን የድንግል ማርያም ጾም (ጾም ፍልሰታ)</u>:- የዚህን ጾም የእመቤታችን የድንግል ምክንያት በተመለከተ ሁለት የተለያዩ ሐሳቦች አሉ። የጾሙን ስም የድንግል ማርያም ጾም የሚሉት ወገኖች ይህን ጾም የምንጾመው በመጀመሪያ የጾመችው እመቤታችን ስለሆነች ነው ይላሉ። እነዚህ ወገኖች የእመቤታችን የተቀደሰ ሰውነት ወደ ሰማይ የተወሰደ መሆኑን ቢያምኑም የጾሙን ምክንያት ግን ከዚያ ጋር አያያይዙትም።

ሁለተኛዎቹ ወገኖች ግን የእመቤታችን ሰውነት እነርሱ ሳያውቁ ወደሰማይ ስለተወሰደ ይህ ምሥጢር እንዲገለጥላቸው ሐዋርያት የጾሙት ጾም ነው ይላሉ። የጾሙም ርዝመት ዐሥራ አምስት ቀኖች ሲሆን ጾሙ በነሐሴ አንድ ቀን ተጀምሮ በነሐሴ ዐሥራ ስድስት ቀን ይፈስካል።

<u>ጾመ ነነዌ</u>:- ይህ ጾም የነነዌ ከተማ ሰዎች የእግዚአብሔርን ምሕረት በማግኘት ከእግዚአብሔር ቍጣ የዳኑበት ጾም መታሰቢያ ነው። የሚጾመውም ለሦስት ቀኖች ሲሆን ሰኞ ይጀምርና ረቡዕ የመጨረሻው ቀን ይሆናል፤ ሐሙስ ግን ይፈስካል።

ይህ ጾም በመጀመሪያ በሥራ ላይ የዋለው በሶርያዊው ፓትርያርክ አብ ሃም አማካይነት ነው።

<u>የረቡዕና የዓርብ ቀኖች ጾም</u>:- ከጌታችን ትንሣኤ በኋላ በኀምሳዎቹ ቀኖች ምናልባት በዓለ ልደትና፥ በዓለ ጥምቀት በረቡዕ ወይም በዓርብ ቀን ካልዋሉ በቀር ረቡዕና ዓርብ ዓመቱን በሙላ የጾም ቀኖች ናቸው።

ረቡዕ ጌታችንን ለመግደል የተዶለበት ቀንና ዓርብ ደግሞ የስቅለቱ መታ ቢያዎች ናቸው።





ጌታችንን ለመግደል የተዶለተ ሤራ (ማቴ:22:15-22)

ቤተ ክርስቲያንም እነዚህን ሁለት ቀኖች የጾም ቀኖች አድርጋ በመወሰንዋ አበጀች፤ እሑድን ለጌታችን ትንሣኤ በዓል መታሰቢያ አድርገን እንደም ናከብር ሁሉ ረቡዕና ዓርብንም ለጌታችን ሕማማት መታሰቢያ አድርገን መጾም ይገባናል።

የሁለቱ ቀኖች ጾምና ጾመ አርብአ ቀደም ተብለው በዘመነ ሐዋርያት የተደነገጉ ለመሆናቸው በመጽሐፈ ዲድስቅልያ አንቀጽ ሠላሳ አንድና አንቀጽ ሠላሳ ስምንት ይመለከቷል።

<u>የገሃድ ጾም</u>:- የገሃድ ጾም በልደትና በጥምቀት ዋዜማዎች የሚጾሙ ጾሞች ናቸው። የቀኖቹ ብዛት በአንድና በሦስት ቀኖች መካከል ነው። በዓሉ በእሑድ ቀን ቢውል የገሃድ ቀን ሁለት ቀን ይሆናል፤ በዓሉ በሰኞ ቀን ቢውል የገሃድ ጾም ሦስት ቀን ይሆናል። ከእዚህ በተለዩት ቀኖች ቢውል ግን የገሃድ ጾም አንድ ቀን ብቻ ይሆናል።



www.ethiopianorthodox.org

ለገሃድ ጾም ሁለት ምክንያቶች ይሰጣሉ:- አንደኛው ምክንያት ሥጋን
አንጽቶ ነፍስን ቀድሶና ልብን ሰብሮ በዓላቱን መቀበል ስለሚያስፈ.ግ ከበዓላቱ
በፊት በዚህ ዓይነት ለመዘጋጀት የገሃድን ጾም እንጾማለን።

ሁለተኛው ምክንያት የጥምቀት ወይም የልደት በዓል በረቡዕ ወይም
በዓርብ ቀን ቢውል ስለማይጾምበት ለዚያ ማካካሻ እንዲሆን የገሃድን ጾም
እንጾማለን።

## ስለጾም አስፈላጊነት የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች:

ጾምን በተመለከተ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ብዙ ማስረጃዎች ያሉ
ሲሆን ከእነርሱም ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጾም ለእርሱ ምንም የማያስፈልገው ሲሆን ለእኛ
አርአያ ለመሆን አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ጾሞአል(ማቴ:ም:4ቍ:2)።

የሰውን ልጅ ጠላት ሰይጣንን ለማሸነፍ የሚቻለው በጾምና በጸሎት
መሆኑን ለደቀ መዛሙርቱ ሲያስረዳ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ:- «እንዲ
ዐይነቱ ግን በጾምና በጸሎት ካልሆነ በቀር አይወጣም» ብሏቸዋል (ማቴ
ም:17ቍ:21) ።

ሙሴ ሁለት ጊዜ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ጾሟል (ዘጸ:ም:34ቍ:28)።

ኤልያስ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ጾሞአል (1ኛ: ነገ:ም:19ቍ:8)።

አስቴርና ወገኖችዋ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ጾመዋል (አስ: ም:
ቍ:16)።

ዳንኤል ሦስት ሳመንት ጾሟል። በነዚያም ሦስት ሳምንቶች ውስጥ ሥ
አልበላም፤ ወይንም አልጠጣም (ዳን:ም:10ቍ:2–3)።

የነነዌ ሰዎች ከትልቁ ጀምሮ እስከ ትንሹ ድረስ ማቅ ለብሰው ስለጾ
የእግዚአብሔርን ይቅርታ አገኙ (ዮና:ም:3ቍ:5–10)።

የፋኑኤል ልጅ ሐና ዕድሜዋ ሰማንያ አራት ዓመት እስኪሆን ድረስ በጾ
በጸሎት ሆና የመበለትነት ዘመንዋን አሳልፋለች (ሉቃ:ም: 2ቍ: 36–37)



www.ethiopianorthodox.org

## የተከራካሪዎች ተቃውሞና ለተቃውሞውም የተሰጡ መልሶች

የጾምን ጠቃሚነት በሚመለከት ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ራእየ ዮሐንስ ድረስ በሚገኙት ልዩ ልዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ብዙ ማስረጃዎችን መጥቀስ ይቻላል። እነዚህንም ማስረጃዎች መሠረት በማድረግ ጥንታውያን የቤተ ክርስቲያን አባቶች ያስረከቡንን የአጽዋማት ቀኖና የምናከብር መሆናችን ግልጽ ነው። ይሁን እንጂ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጓሜ እነርሱ በፈለጉት መንገድ ከመምራታቸው የተነሣ አንዳንድ ተከራካሪዎች በጾም ጠቃሚነት ላይ ከሚያቀርቡአቸው ተቃውሞዎች መካከል ቀጥለው የተዘረዘሩት ይገኙባቸዋል።

<u>የመጀመሪያው ተቃውሞ</u>:- የዮሐንስ ደቀ መዛሙርትና ፈሪሳውያን ይጾሙ እንደነበረና የጌታችን ደቀ መዛሙርት ግን የማይጾሙ መሆናቸው በማቴዎስ ወንጌል ም.9 ቍ.14 ላይ በመገለጹ ይህ ሊሆን የቻለው የጾምን ጠቃሚነት ጌታችን ስላላመነበት ነው የሚል ሐሳብ የሚያቀርቡ ወገኖች አሉ። ይህ አባባል ግን የጥቅሱ አመጣጥና አካሄድ ሳይመረመር የተሰነዘረ በመሆኑ ትክክል አይደለም። ጌታችን አርባ ቀኖችን በመጾም ለእኛ ምሳሌ ከመሆኑም በላይ የጾምንና የጸሎትን ኀይል ያረጋገጠ መሆኑን በማቴዎስ ወንጌል ም. 17 ቍ 27 መመልከት ይቻላል።

የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ወደጌታችን ቀርበው እኛና ፈሪሳውያን የምንጾም ስንሆን የአንተ ደቀ መዛሙርት ግን የማይጾሙት ለምንድነው ብለው በጠየቁት ጊዜ የሰጣቸው መልስ ጾም አስፈላጊ አለመሆኑን ሳይሆን ሙሽራው ከእነርሱ ጋር እያለ ሠርገኞች የማይጾሙ መሆናቸውንና ሙሽራው ከእነርሱ ሲወሰድ ግን የሚጾሙ መሆናቸውን ነው። ሙሽራ የተባለው ጌታችን ነው። ሠርገኞች የተባሉት ደግሞ የጌታችን ተከታዮች ናቸው። እንዲሁም መወሰድ የተባለው ዕርገቱ ነው። በዚህም መሠረት ከዕርገቱ በኋላ የጌታችን ተከታዮች መጾም የጀመሩ መሆናቸውን ለመረዳት የሚከተለውን ጥቅስ እንመልከት።

«እነርሱም ጌታን ሲያመልኩና ሲጾሙ ሳሉ መንፈስ ቅዱስ እኔ ለመረጥኋቸው ሥራ በርናባስንና ሳውልን ለዩልኝ አለ» (የሐ. ሥ. ም13 ቍ.2)።

ጌታችንም ለዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ጥያቄ መልስ መስጠቱን በመቀጠል በአረጀ ልብስ ላይ አዲስ መጣፊያ የሚጥፍና በአረጀ አቁማዳ ደግሞ አዲስ የወይን ጠጅ የሚያኖር አለመኖሩን የሚገልጽ ምሳሌ የተናገረው የኦሪቱ የጾም

ሥነ ሥርዐት ከሐዲሱ የጾም ሥነ ሥርዐት የተለየ መሆኑን ሊያስረዳቸው ስለፈለገ ነው።

አንዳንድ ጊዜ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚቀርበው ጥያቄ ወይም ትችት ሰው ባስፈለገው ጊዜ ብቻ ይጾማል እንጂ በዓመት ወይም በሳምንት የተወሰኑ ሰዓቶችንና ቀኖችን ወስኖ መጾም አስፈላጊ አይደለም የሚል ነው።

ማንኛውም ኅብረተሰብ የግድ የመተዳደሪያ ደንብ ያስፈልገዋል። ያለ መተዳደሪያ ደንብ የሚካሄድ ማኅበራዊ ኑሮ ከቶ ሊኖር አይችልም። የሚኖርም ከሆነ ከእንስሳት ኑሮ ያልተሻለና የተበላሸ እንጂ ያማረ አይሆንም።

አንድ መንግሥት አጠቃላይ የሆነ ሕግ ማለት ሕገ መንግሥት ይኖረውና ያንን መሠረት በማድረግ የፍትሐ ብሔር ሕግ፥ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ፥ የንግድ ሕግና ሌሎችም እነዚህን የመሳሰሉ ሕጎች ይኖሩታል እንጂ በሕገ መንግሥቱ ብቻ ተወስኖ እንደማይኖር የታወቀ ነው።

ማንኛውም ሥርዐትን ያልተከተለና ማዕከላዊነት የሌለው አሠራር ውጤቱ የማያምር ከመሆኑም በላይ በእግዚአብሔር ዘንድም የተወደደ አሠራር አይደለም። እግዚአብሔርም ሥርዐተ ቢስ ከሆነው አሠራር ይልቅ በሥነ ሥርዐት የሚካሄደውን አሠራር የሚመርጥ መሆኑን ለመረዳት የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት።

ነቢዩ ሙሴ በምድረ በዳ የእስራኤልን ሕዝብ ሥነ ሥርዐት በሌለው ሁናቴ ይመራ በነበረ ጊዜ በሥነ ሥርዓት እንዲሠራ አማቱ ዮቶር የሰጠውን ምክር ተቀብሎ በመሥራቱ ሥራው የተቃናለት ከመሆኑም በላይ በእግዚአብሔርም ዘንድ የድጋፍ እንጂ ምንም የተቃውሞ ምልክት አልታየም (ዘጸ. ም. 18 ቍ.13–26)።

በሌላ በኩል ደግሞ ቆሬና አብረውት የነበሩት ሁሉ ሥነ ሥርዐትን በማፍረስ ለአምልኮተ እግዚአብሔር የራሳቸውን መንገድ ስለ ተከተሉ እግዚ አብሔር ተቈጥቶባቸው መሬት ተከፍቶ እንዲውጣቸው አድርጓል (ዘኁ :ም:16)።

መጽሐፍ ቅዱስን ለሃይማኖታችን እንደ ሕገ መንግሥት ብንወስደው ሌሎቹን የአምልኮተ እግዚአብሔር ሥነ ሥርዐቶች እንደ ልዩ ልዩ የመንግሥት ሕጎች ልንቈጥራቸው እንችላለን። ምንም እንኳ መሠረታዊውን የመጽሐፍ



ቅዱስ ድንጋጌ የማይቃረን ሆኖ ቢዘጋጅ በቤተ ክርስቲያን የሚከናወነው አምልኮተ እግዚአብሔር የራሱ የሆነ ከጥንት ጀምሮ የተሠራ ደንብና ሥነ ሥርዐት አለው።

<u>ሁለተኛው ተቃውሞ</u>:- ወደ ጢሞቴዎስ መጀመሪያ በተላከው በሐዋርያው በቅዱስ በጳውሎስ መልእክት ም.4ቍ.1–3 «በኋለኛው ዘመን አንዳንድ ሰዎች ጋብቻን ይከለክላሉ፤ የሚያምኑና እውነትን የሚያውቁ ሰዎች እግዚ አብሔርን እያመሰገኑ እንዳይበሉ እግዚአብሔር የፈጠረውን ምግብ አትብሉ እያሉ ይከለክላሉ» ስለሚል በድንግልና መኖርንና መጾምን ማስተማር ስሕተት ነው በማለት በጥንታዊቱ ቤተ ክርስቲያን ላይ የነቀፌታ ትችት የሚሰነዝሩ ወገኖች አሉ።

ተከራካሪዎቹ ከሁሉ በፊት ሊገነዘቡት የሚገባ ጉዳይ በጾም የምታምነዋና ለምእመናንም የጾምን ጠቃሚነት የምታስተምረዋ ቤተ ክርስቲያን የጥንት የመሠረትዋ እንጂ በኋላ ዘመን የተነሣች አለመሆንዋንና የጾም መሠረት የተጣለው ደግሞ ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ እንጂ በኋላ ዘመን አለመሆኑን ነው።

በተከራካሪዎቹ የተጠቀሰው ጥቅስ ግን በሦስተኛው መቶ ዓመት ተነሥተው ስለነበሩት ማኒ፥ መርቅያኖስና ሲሞን ይባሉ ስለነበሩት መናፍቃን እንጂ ስለጥንታዊትዋ ቤተ ክርስቲያን የሚያወሳ አይደለም። ማኒና ጓደኞቹ የሥጋ ምግብ፥ መጠጥና ሴት የተፈጠሩት በክፉት አምላክ ስለሆነ ክልክል ናቸው ብለው ያስተምሩ ነበር።

ጥንታዊቱ ቤተ ክርስቲያን ግን በዓመት ውስጥ በተወሰኑ ወቅቶችና በሳምንት ሁለት ቀኖች የጾምን ቀኖና ከመደንገግዋ በቀር ሥጋ መብላት ኀጢአት ነው ብላ አላስተማረችም። እንዲሁም የጋብቻን ውሕደት ከሰባቱ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን አንዱ መሆኑን አምና ታስተምራለች። መጾምም ሆነ በድንግልና መኖር የተመሰገኑና የሚመሰገኑ እንጂ የተወገዙ ወይም የሚወገዙ ድርጊቶች አይደሉም።

ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ ያለዘሙት ምክንያት ማንም ሰው ሚስቱን መፍታት እንደማይገባው በገለጸላቸው ጊዜ እንደዚህስ ከሆነ አለማግባት ይሻላል ቢሉት የሰጣቸው መልስ «ልዩ ችሎታ ለተሰጣቸው ነው እንጂ ይህ ነገር ለሁሉም አይሆንም» ብሎ ነው (ማቴ.ም 19 ቍ.9–11)። ይህንኑ



www.ethiopianorthodox.org

የድንግልናን ኑሮ በሚመለከት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በላከው በመጀመሪያ መልእክቱም ም.7ቍ.1–2 እና ቍ.7–9 እንዲህ ብሏል:- «ስለጻፋችሁልኝ ጥያቄ ሰው ከሴት ጋር ባይገናኝ መልካም ነው። ነገር ግን በዝሙት ኃጢአት ላለመውደቅ እያንዳንዱ ወንድ የራሱ ሚስት ትኑረው እያንዳንድዋም ሴት የራስዋ ባል ይኑራት። ሰው ሁሉ እንደ እኔ ሚስት ሳያገባ ቢኖር በወደድሁ ነበር። ነገር ግን ለያንዳንዱ እግዚአብሔር የተለየ ስጦታ ሰጥቶታል። አንዱ አንድ ዐይነት ስጦታ፥ ሌላው ሌላ ዐይነት ስጦታ አለው። ላላገቡ፥ እንዲሁም ባሎቻቸው ለሞቱባቸው ሴቶች የምለው እንዲህ ነው። ሳያገቡ እንደኔ ቢኖሩ መልካም ነው። ነገር ግን ራሳቸውን መቈጣጠር ቢያቅታቸው ያግቡ፤ ምክንያቱም በሥጋ ምኞት ከመቃጠል ይልቅ ማግባት የተሻለ ነውና።»

ከምግብና ከጋብቻ ራስን መግታት ደግሞ ለጽድቅ ሲባል የተፈጥሮ ፍላጎትን መካድ ማለት ነው። ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ «እኔን መከተል የሚፈልግ ራሱን ይካድ» አላቸው እንጂ ራሱን የካደ ኀጢአተኛ ነው አላላቸውም (ማቴ.ም.16ቍ.24)።

ሦስተኛው ተቃውሞ:- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም.14ቍ.17 ላይ «የእግዚአብሔር መንግሥት በመንፈስ ቅዱስ የሚገኝ ጽድቅ ሰላምና ደስታ እንጂ የመብልና የመጠጥ ጉዳይ አይደለም» ባለው መሠረት በጾምና በጸሎት የምታምነዋ ቤተ ክርስቲያን በጾም አማካይነት የእግዚአብሔር ይቅርታ እንደሚገኝ ማስተማርዋ ስሕተት ነው በማለት የሚከራከሩ ሰዎች አሉ።

ተከራካሪዎቹ ትክ ብለው አልተመለከቱትም እንጂ ይህ ጥቅስ የሚያመለክተው የጾምን ቀኖና አይደለም። የጥቅሱን አመጣጥ ለመረዳት በዚሁ ምዕራፍ ቍ. 14 ብንመለከት አንዱን ዐይነት ምግብ ርኩስ እንደሆነ ለሚገምት ሰው በልቡ ጥርጣሬ ስላለና ያ ምግብ ለእርሱ ርኩስ ስለሚሆንበት ያን ምግብ በመብላቱም ሆነ ባለመብላቱ አትፍረዱበት ብሎ የሚያስተምረን መሆኑን እንገነዘባለን።

አራተኛው ተቃውሞ:- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ቆላስይስ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም.2 ቍ.16 ላይ «እንግዲህ በመብል ወይም በመጠጥ፥ በዓላትን፥ ወይም የወር መባቻን፥ ወይም ሰንበትን በማክበር ምክንያት ማንም አይፍረድባችሁ› የሚለው ምግብን ላለመብላት በራሳቸው ላይ የሚፈርዱን



ሰዎች የሚመለከት ነው በማለት የሚተቹ ወገኖች አሉ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እዚህ ላይ ሊተችበት የፈለገው ለክርስቲያን ሃይማኖት አስፈላጊ ያልሆኑትን የአይሁድን ሕግጋት ነው እንጂ የቤተ ክርስቲያንን የጾም ቀኖና አለመሆኑን ተከራካሪዎቹ የነገሩን ቅደም ተከተል በትክክል ያልተመለከቱት ይመስላል። ከአይሁድ ሃይማኖት ወደ ክርስትና የገቡት ወገኖች የአይሁድን ሕግጋት መፈጸም ግዴታ እንደሆነ ያምኑ ስለነበረና ይህንንም እምነትና አድራጎት የማይፈጽመውን ሰው ይፈርዱበት ስለነበረ ይህንኑ ለመቃወም የተጠቀሰ ነው እንጂ የቤተ ክርስቲያንን የጾም ቀኖና የሚመለከት አይደለም።

አምስተኛው ተቃውሞ:- በማቴዎስ ወንጌል ም. 15 ቍ.11 ላይ ጌታ «ሰውን የሚያረክሰው ከአፍ የሚወጣው ነው እንጂ ወደአፍ የሚገባው አይደለም» በማለቱ በጾም ጊዜ የፍስክ ምግብ መብላት አያረክሰንም ብለው ከጥቅሱ ጋር ግንኙት የሌለው ክርክር የሚያቀርቡ ሰዎች አሉ። ጌታችን ግን ይህን የተናገረው ፈሪሳውያንና የኦሪት ሕግ መምህራን ደቀ መዛሙርትህ እጃቸውን ሳይታጠቡ በመብላት ለምን የሽማግሌዎችን ወግ ያፈርሳሉ ብለው ለጠየቁት ጥያቄ መልስ ለመስጠት ፈልጎ ነው እንጂ የጾምንና የፍስክን ምግብ በሚመለከት አይደለም። ጾም ግን ለሰውነታችን ብርታትንና ጥንካሬን ሰጥቶ ወደ ክፉ ዝንባሌና ወደ ትዕቢት ከሚመራን ከባድ ምግብና ከሚያሰክር መጠጥ መከልከል፥ የሥጋን ፍላጎት ገትቶ ለፈጣሪ አምላክ መንበርከክና ራስን ማዋረድ ነው እንጂ አንዱ ምግብ ንጹሕ ነው፤ ሌላው ምግብ ደግሞ ርኩስ ነው ለማለት አይደለም።

ነቢዩ ዳንኤል እንዴት እንደጾመ ሲያስረዳ እንዲህ ብሏል። «በዚያም ወራት እኔ ዳንኤል ሦስት ሳምንት ሙሉ ሳዝን ነበርሁ፤ ማለፊያ እንጀራም አልበላሁም፤ ሥጋና ጠጅም በአፌ አልገባም፤ ሦስቱም ሳምንት እስኪፈጸም ድረስ ዘይት አልተቀባሁም» (ዳን. ም.10 ቍ. 2–3)።

ጌታችን በማቴዎስ ወንጌል ም. 6 ቍ.16 ላይ «በምትጾሙበት ጊዜ ግብዞች እንደሚያደርጉት የሐዘን መልክ አታሳዩ» ሲል መጾም የሚገባን መሆኑ ሊገልጽልን ፈልጎ ነው እንጂ አለበለዚያ ግን የጾማችሁ እንደሆነ ወይም ለመጾም የፈለጋችሁ እንደሆነ ባለ ነበር።

ስድስተኛው ተቃውሞ:- ከዐቢይ ጾም በቀር ሌሎቹ አጽዋማት ሁሉ ሰው ሠራሽ በመሆናቸው ልንጾማቸው አስፈላጊ አይደሉም ብለው የሚከራከሩ አሉ።



www.ethiopianorthodox.org

መጻሕፍቱን በሚጽፉበት ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ ጥበቃ ያልተለያቸው መሆኑን እናምናለን እንጂ ቅዱሳት መጻሕፍትንና የቤተ ክርስቲያን ቀኖናዎችን ያዘጋጁት ሰዎች መሆናቸውን አንክድም።

ለምሳሌ ለአይሁድ ሕዝብና ለነነዌ ከተማ ሕዝብ ጾም አውጀው ሕዝቡም በአዋጁ መሠረት ጾሞ የእግዚአብሔርን ይቅርታ እንዲያገኝ ያስደረጉት አስቴር፥ መርዶክዮስና የነነዌው ንጉሥ ሰዎች እንጂ መላእክት አልነበሩም።

ስለዚህ ቅዱሳን የቤተ ክርስቲያን አባቶች ያዘጋጁልንን የአጽዋማት ቀኖና አክብረን መቀበልና መታዘዝ እንደሚገባን እናምናለን።

( ይህ ክፍል ከትምህርተ መለኮት መጽሐፍ የተወሰደ ነው።)

## ጥያቄዎች

1. በትምህርቱ ውስጥ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የተሰጡት ትርጓሜዎች ስንት ናቸው?

2. እግዚአብሔር ወደፊት ይህን ዓለም አሳልፎ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደሚፈጥር የተነበየ ማነው?

3. እግዚአብሔር በፍጥረቱ ላይ ስላለው ጌትነት አንድ የማስረጃ ጥቅስ አቅርብ።

4. በአባታችን ሆይ ጸሎት ውስጥ ስለ እግዚአብሔር ጌትነት የሚገልጸው አባባል የትኛው ነው?

5. እግዚአብሔር በእስራኤል ላይ ስላለው ልዩ ገዢነት አንድ የማስረጃ ጥቅስ አቅርብ?

6. ወደፊት ስለሚወረሰው መንግሥተ ሰማይ አንድ የማስረጃ ጥቅስ አቅርብ።

7. እግዚአብሔር በሾማቸው ሰዎች የሚካሄደው አገዛዝ የእግዚአብሔር መንግሥት ለመባሉ የማስረጃ ጥቅስ አቅርብ።

8. ጌታችን በማስተማር ላይ በነበረ ጊዜ የእግዚአብሔር መንግሥት በሕዝቡ መካከል መሆኑን የገለጠው እንዴት ብሎ ነው?

9. በታቦር ተራራ ላይ ምን ድንቅ ነገር ተከሠተ?



10. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመረብ ምሳሌ ምንን አስተማረ?

11. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እንክርዳድ ባስተማረው ምሳሌ ስንዴውን በምንና እንክርዳዱን ደግሞ በምን ምሳሌነት አቀረበው?

12. ስለ ሰናፍጭ ዘር ያስተማረው ምሳሌ ትርጉሙ ምንድነው?

13. ስለ እርሾው ምሳሌ ተናገር።

14. የሰው ልጆች ነጻ ፈቃድ ማለት ምን ማለት ነው?

15. እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የመብትና የግዴታ ትምህርትን ያስተማረበት የመጀመሪያው ትምህርት ቤት የትኛው ነው?

16. ደንቦችና ሕግጋት መኖር ያስፈለጋቸው ለምንድነው?

17. ምክር በመጠየቅና በነጻ ፈቃድ መካከል ያለው ግንኙት እንዴት ነው?

18. እግዚአብሔር ሰውን የሚያስጠነቅቀው ለምንድነው?

19. እግዚአብሔር ቃየልን ምን ብሎ አስጠነቀቀው?

20. ሰው ሁሉ እንዲድን የእግዚአብሔር ፍላጎት መሆኑን ከሚገልጡት የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች መካከል አንዱን አቅርብ።

21. እግዚአብሔር ሰውን የማያስገድደው ነገር ምንድነው?

22. እግዚአብሔር የማይለወጥበት ምክንያት ምንድነው?

23. እግዚአብሔር የማይለወጥ መሆኑን ከሚገልጹ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች መካከል አንዱን አቅርብ።

24. ጸሎትና ንስሓ የእግዚአብሔርን ውሳኔ ያስለውጣሉን?

25. የእግዚአብሔር ጸሎት ተቀባይነትንና የማይለወጠውን ውሳኔውን እንዴት ማስታረቅ ይቻላል?

26. እግዚአብሔር ወደፊት የሚመጡ ሁኔታዎችን አስቀድሞ የሚያውቅ ሲሆን ለምን ክፉ ሁኔታዎችን እንዲደርሱ ይፈቅዳል?

27. ስለሰው ልጆች ነጻ ፈቃድ ከቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች አንድ አቅርብ።

28. ጾም ማለት ምን ማለት ነው?

www.ethiopianorthodox.org

29. አንድ ጹዋሚ በጾም ጊዜ የሚመገበው ምን ዐይነት ምግብ ነው?

30. ነቢዩ ዳንኤል የማንን አርአያነት ተከትሎ ጾመ?

31. የምንጾመው ምን ለማድረግ ነው?

32. አጽዋማት በክርስትና ሃይማኖት ሕግንና ሥርዓትን መያዝ የጀመሩት መቼ ነው?

33. የጌታችን ጾም ርዝመት ስንት ነው? ምክንያቶቹስ ምን ምን ናቸው?

34. የልደት ጾም ርዝመት ምን ያኽል ነው? የጾሙስ ምክንያት ምንድን ነው?

35. የልደት ጾም ለምን በዘመነ ዮሐንስ በአንድ ቀን ቀነሰ?

36. የሐዋርያት ጾም በተለያዩ ዘመናት የተለያየ ርዝመት ያለው ለምንድነው?

37. ርዝመቱስ ከፍና ዝቅ የሚለው በስንትና በስንት ቀጥሮች መካከል ነው?

38. የሐዋርያት ጾም ምክንያት ምንድነው?

39. የፍልሰታ ጾም መቼ ጀምሮ መቼ ያልቃል?

40. ለፍልሰታ ጾም የሚሰጡት ምክንያቶች ምንና ምን ናቸው?

41. የጾመ ነነዌን ምክንያትና የቀኖቹ ብዛት ስንት እንደሆነ ግለጥ።

42. ረቡዕና ዓርብን የምንጾመው ለምንድነው?

43. የገሃድን ጾም ርዝመትና ምክንያት በዝርዝር አስረዳ።:

44. ከአጽዋማቱ መካከል በመጽሐፈ ዲድ ስቅልያ የተነገሩት የትኞቹ ናቸው?

45. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያለ ጾምና ያለ ጸሎት ምን ማድረግ እን... ማይቻል ተናገረ?

46. ሙሴ የጾመው ለስንት ጊዜ ነው?

47. አስቴር ያወጀችው ጾም ለስንት ጊዜ ነበር?

48. ዳንኤል ለስንት ጊዜ ጾመ?

49. የነነዌ ስዎች በመጾማቸው ምን አገኙ?



50. የፋኑኤል ልጅ ሐና በጾምና በጸሎት ያሳለፈችው የመበለትነት ዘመን ስንት ነው?

51. በማቴዎስ ወንጌል ም:9:ቍ14፥ በአንደኛ ጢሞቴዎስ ም:4 ቍ:1–3፥ በሮሜ መልእክት ም:14ቍ:14–17፥ በቆላስይስ መልእክት ም:2 ቍ:16፥ በማቴዎስ ወንጌል ም:15ቍ:11 ላይ ለቀረቡት የጾም ተቃውሞዎች መልስ ስጥ።

# ምዕራፍ ሁለት

## መጽሐፍ ቅዱስ

ከመጽሐፍ ቅዱስ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች መካከል ብሉይ ኪዳንን አይሁድና ክርስቲያኖች በቅዱስነቱ አምነው ይቀበሉታል፤ ሐዲስ ኪዳንን ግን አምነው የሚቀበሉት ክርስቲያኖች ብቻ ናቸው።

መጽሐፍ ቅዱስም ምንም እንኳ ተጽፎ አሁን ባለበት ሁኔታ የተዘጋጀው በተለያዩ ሰዎች መሆኑን ብናውቅ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ግን አንክድም። ይህን እምነታችንን የሚያጠናክሩልን የተለያዩ ምክንያቶች አሉ።

ለምሳሌ የመጀመሪያዎቹን አምስት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ያዘጋጀው ሙሴ መሆኑ የታመነ ነው። ታዲያ፥ እርሱ እነዚያን መጻሕፍት የሚያዘጋጀው በምን ዐይነት ነበር? ሐሳቡን ወይም ዕውቀቱን ከወዴት ያገኘው ነበር? አምስቱን መጻሕፍት በተለየም ኦሪት ዘጸአትን፥ ኦሪት ዘሌዋውያንንና ኦሪት ዘኍልቍን ብንመለከት በእግዚአብሔርና በሙሴ መካከል የንግግር መለዋወጥን እናነብባለን። በአርባ ዓመቱ የበረሓ ጉዞ ሁሉ ሙሴ የእስራኤልን ልጆች ይመራና ያስተዳድር የነበረው በቀጥታ ከእግዚአብሔር በሚቀበለው መመሪያ ነበር። ይህን አባባል የምናረጋግጠው በመጻሕፍቱ ውስጥ ተደጋግመው የቀረቡትን ገለጻዎች በመመልከት ነው። እነዚህም አባባሎች «እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው:- ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው» የሚሉ ነበሩ። ስለዚህ ሙሴ መጻሕፍቱን በሚጽፍበት ጊዜ በዚህ ዐይነት በልዑል እግዚአብሔር እየተመራ ነበር (ዘጸ: ም:19 ፥20፥ ዘሌ. ም: 4፥ ዘኍ:ም6)።



www.ethiopianorthodox.org

እንደገና በነቢያት የተጻፉት መጻሕፍትም ተመሳሳይ አባባሎችን ያ
ርባሉ። እግዚአብሔር በነቢዩ አንደበት እንዲህ ብሏል፤ ወይም ደግሞ ነቢያ
ራሳቸው እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ እያሉ ተናግረዋል (ኢ.ሳ:ም. 30
ቍ:15፥ም:56 ቍ:1ም:65 ቍ:8፥ኤር. ም: 2፥ ም:11፥ ሕዝ: ም: 6፥7)።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የተጻፉት በእ
ዚአብሔር መንፈስ መሪነት መሆኑን ተናግሮአል (2ኛ:ጢ.ሞ: ም:3ቍ:16)።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ደግሞ ትንቢቶችን ሁሉ በእግዚአብሔር የ
መረጡ ሰዎች ብቻ እንደሚናገሩአቸው ገልጦአል (2ኛ:ጴጥ:ም: 1ቍ: 21)።

በእነዚህ ከላይ በቀረቡት ማስረጃዎች መሠረት መጽሐፍ ቅዱስ የእ
ዚአብሔር ቃል መሆኑን እናረጋግጣለን።

## ብሉይ ኪዳን

ይስሐቅና ርብቃ:– በምድር ላይ ረሀብ መጣ። በዚህ ጊዜ ይስሐቅ ተነሥ
የፍልስጥኤማውያን ንጉሥ አቢሜሌክ ወደ አለበት ገራር ወደ ተባለ አገር ሄደ
እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባለትን ቃል ኪዳን ለይስሐቅም ገባለት። እ
ሚባርከውና ዘሩን እንደሚያበዛለትም ነገረው። የዚያ አገር ሰዎች በእርሰ
ምክንያት እንዳይገድሉት ስለፈራ ሚስቱን ርብቃን እኅቴ ናት ብሎ ተናገ
ይህን አባባል አባቱ አብርሃምም ሁለት ጊዜ ተጠቅሞበታል። ንጉሡ አ
ሜሌክ ግን በመስኮት ወደ ውጪ ሲመለከት ይስሐቅ ከሚስቱ ከርብቃ ጋ
በመዳራት ሲጫወቱ ስለአያቸው ምነው ለምን እኅቴ ናት ብለህ ተናገር
ብሎ ጠየቀው። ይስሐቅም በእርስዋ ምክንያት ሰዎች እንዳይገድሉኝ ፈር
ነው አለው። ከዚያ በኋላ ንጉሡ በይስሐቅ ላይ አንዳች ችግር የሚያደርስ ሰ
እንደሚቀጣ ማስጠንቀቂያ ስላስተላለፈ ይስሐቅ በሰላም ሊኖር ችሏል።

ዔሳውና ያዕቆብ:- የይስሐቅ ሚስት ርብቃ መኻን ስለነበረች ለኻያ ዓመ
ሙሉ ልጅ አልወለደችም። ይስሐቅም ስለ ርብቃ ጸለየ። እግዚአብሔር
ጸሎቱን ሰምቶ ርብቃ ፀነሰች። በማሕፀንዋም መንትያዎች እርስ በርሳቸ
እየተጋፉ ስላስቸገሯት ወደ እግዚአብሔር ጸለየች። እግዚአብሔርም አይ
በማሕፀንሽ ውስጥ ያሉት ሁለት ሕዝቦች ናቸው፤ እርስ በርሳቸው የ
ስማሙ ሁለት ወገኖችን ትወልጂአለሽ፤ ታናሹ ከታላቁ የበረታ ይሆና
አላት። የመውለጃዋም ወቅት ሲደርስ ሁለት ወንዶች ልጆችን ወለደች



የመጀመሪያው ልጅ መልኩ ቀይና ጠጕራም ነበረ። ስሙም ዔሳው ተባለ፤ ሁለተኛው ልጅ ሲወለድ የወንድሙን ተረከዝ ይዞ ወጣ። ስሙም ያዕቆብ ተባለ።

ሁለቱ የይስሐቅ ልጆች አደጉና የተለያየ የአኗኗር ዘዴ ተከተሉ። ዔሳው ወደ ዱር እየሄደ ሲያድን ይውል ነበር፤ ያዕቆብ ግን በቤት ውስጥ መዋል የሚወድድ ሰው ነበር። ዔሳው እያደነ ሥጋ አምጥቶ ያበላው ስለነበረ ይስሐቅ ዔሳውን ከያዕቆብ አስበልጦ ይወድደው ነበር። ርብቃ ግን ያዕቆብን አስበልጣ ትወድድ ነበር።

ከዕለታት አንድ ቀን ዔሳው ዐደን ሄዶ ሲመለስ ያዕቆብ ቀይ የምስር ወጥ እየሠራ ነበር። ዔሳው እርቦት ስለነበር ከወጥህ ስጠኝ አለው። ከዚህ ወጥ እንድሰጥህ ብኵርናህን ሽጥልኝ አለው። እርሱም በጣም እርቦት ስለነበረ እሺ ብሎ ሸጠለት፤ መሸጡንም በመሐላ አረጋገጠለትና በእንጀራ አድርጎ ከወጡ ሰጥቶት በላ።

ይስሐቅ አርጅቶ ዐይኖቹ በታወሩ ጊዜ ታላቁን ልጁን ዔሳውን ጠርቶት እንዲህ አለው:- ልጄ ሆይ፥ እነሆ፥ እኔ ያረጀሁ ስለሆነ የምሞትበትን ጊዜ አላ ውቅም፤ ወደ ዱር ሄደህ ዐድንና ሥጋ አምጣልኝ፤ እኔ በምወደው ዐይነት አዘጋጅተህ አምጣልኝና ከበላሁ በኋላ ከመሞቴ በፊት ልመርቅህ አለው። ይህን በሚልበት ጊዜ ርብቃ ትሰማ ነበር። ከዚያም ያዕቆብን ጠርታ አንድ የፍየል ጠቦት አምጣልኝና ለአባትህ በሚወድደው ዐይነት ካዘጋጀሁለት በኋላ ይዘ ህለት ትገባለህ፤ ምግቡንም ከበላ በኋላ ለዔሳው የታሰበውን ምርቃት ከአባትህ ተቀብለህ ትወጣለህ አለችው። ያዕቆብ ግን አባቴ ያወቀብኝ እንደሆነ ከምር ቃት ይልቅ እርግማንን አመጣለሁ ብሎ ስጋቱን ገለጠላት። እናቱ በጣም ስላበረታታችው በዕቅዱ ገፋበትና የተሠራውን ምግብ ይዞ ወደ አባቱ ገባ። አባቱም ምንም እንኳ በድምፁ ቢጠራጠረው እኔ ዔሳው ነኝ ስላለውና ማንነቱን አይቶ ሊለይ ባለመቻሉ ምግቡን ከበላ በኋላ ምርቃቱን ሁሉ አሚጦ ለእርሱ ሰጠው። ምርቃቱን ተቀብሎ ከወጣ በኋላ ወንድሙ ዔሳው ከዐደን ያገኘውን ሥጋ ይዞ ወደ አባቱ ገባ። አባቱም መታለሉን ባወቀ ጊዜ ደነገጠ። ከዚያ በኋላ ለዔሳው ምንም ሊያደርግለት አልቻለም።

ያዕቆብ ቀደም ብሎ ብኵርናውን በመውሰድ አሁን ደግሞ ምርቃቱን በመውሰድ ስላታለለው ዔሳው ወንድሙን ያዕቆብን በጣም ጠላው። አባቴ



www.ethiopianorthodox.org

<u>የያዕቆብ ወደ ካራን ጉዞና ያጋጠሙት ሁኔታዎች</u>:- የይስሐቅ ልጅ ዔሳው ሁለት የሒታውያን ሴቶችን በማግባቱ አባቱንና እናቱን በጣም አሳዝኖአቸው ነበር። ርብቃ ይህን ጉዳይ አንሥታ ከይስሐቅ ጋር ከተወያየች በኋላ ይስሐቅ ያዕቆብን ጠርቶ ከሒታውያን ሴቶች ሚስት እንደያገባ፥ ይልቅስ ወደ እናቱ ወንድም ወደ ላባ ሄዶ ከአጎቱ ሴቶች ልጆች አንድዋን እንዲያገባ ነገረው። ከዚያም መርቆ አሰናበተው። ወደ ካራንም ሲጓዝ መሽቶበት በአንድ ቦታ ዐደረ። እዚያም ድንጋይ ተንተርሶ ተኝቶ ሳለ በሕልሙ ከምድር እስከ ሰማይ የሚደርስ መሰላል አየ። መላእክትም በመሰላሉ ላይ ሲወጡበትና ሲወርዱበት ነበር። እግዚአብሔርም በአጠገቡ ቆሞ ለአብርሃምና ለይስሐቅ የገባውን ቃል ኪዳን ለእርሱም ገባለት። በማግስቱ ጥዋት ተንተርሶት የነበረውን ድንጋይ ለመታሰቢያነት ከተከለው በኋላ እግዚአብሔር ጉዞውን ቢያቃናለት ለእግ ዚአብሔር ተገዥ እንደሚሆንና ወደፊትም ዐሥራት እንደሚከፍል ቃል ገባ።

ያዕቆብም ጉዞውን ቀጥሎ አጐቱ ላባ ወደ አለበት ወደ ካራን ደረሰ። እዚያም ስለ ላባ ሁለተናዋ ሴት ልጅ ስለ ራሔል ሰባት ዓመት ላባን ሊያገለግል ተስማማ። የተስማማበት ጊዜ ሲደርስ ግን እርሱ ሳያውቅ በጨለማ በራሔል ፈንታ ታላቂቱ የላባ ልጅ ልያ ተሰጠችው። ከዚያ በማግስቱ ላባን ቢጠይቀው በሀገራችን ባህል ታላቒቱ እያለች ታናሽቱ አትዳርም አለው። ከዚያም እንደገና ሰባት ዓመት እንዲያገለግለው ቃል በማስገባት ከአንድ ሳምንት በኋላ ራሔ ልንም ሰጠው። አባታቸው ለልያና ለራሔል አንዳንድ የሴት አገልጋዮች ሰጥቶአቸው ነበር። ከሁለቱ አገልጋዮች ሁለት ሁለት ልጆች፥ ከልያ ስድስት ወንዶችና አንዲት ሴት ልጅ፥ ከራሔል ሁለት ወንዶች ልጆች በጠቅላላው ዐሥራ ሁለት ወንዶች ልጆችና አንዲት ሴት ልጅ ተወለዱለት። በብዙ ሀብትም ከበለጸገ በኋላ ወደ ሀገሩ ተመለሰ። ወደ ሀገሩም ሲመለስ በዐደረበት ቦታ ከአንድ ሰው ጋር ሲታገል ዐደረ። ያም ሰው ያዕቆብን ማሸነፍ ሲያቅተው የጭኑን ሹልዳ መታውና ጭኑ ከመገጣጠሚያው ላይ ተለያየ። ከዚያ በኋላ ሰውየው ሌሊቱ ሊነጋ ስለሆነ ልቀቀኝ አለው። ያዕቆብ ግን ካልባረክኸኝ አልለቅህም አለው። ሰውዬውም ስምህ ማነው? አለው። ስሜ ያዕቆብ ነው አለው። ሰውዬውም ከእግዚአብሔርና ከሰው ጋር ታግለህ ስለአሸነፍህ ከእን ግዲህ ወዲያ ስምህ እስራኤል ነው እንጂ ያዕቆብ አይባልም አለው። ስለዚህ እስራኤል የሚለው ስም ያዕቆብ የተባረከበት ስም ነው።

<u>ነቢዩ ኤልያስ</u>:- ከእርሱ በፊት ከነበሩት ነገሥታት ሁሉ ይበልጥ በእግ ዚአብሔር ፊት ክፉ በሠራው በዖምሪ ልጅ በአክዓብ ዘመን ከገለዓድ ቴስቢ



የሆነ ኤልያስ የሚባል ነቢይ ነበር። እርሱም አክዓብን እንዲህ አለው:- «በፊቱ የምቆም የእስራኤል አምላክ ሕያው ነው፤ በእኔ ቃል ካልሆነ በቀር ለዓመታት ዝናብ አይዘንብም።» እግዚአብሔርም ኤልያስን ከዚህ ተነሥተህ ከዮርዳኖስ ትይዩ በሆነው በኮራት ወንዝ አጠገብ ተሸሸግ። እዚያ ውሃ ታገኛለህ፤ እኔም ቍራዎች ምግብ ያመጡልህ ዘንድ አዝዤአለሁ» አለው። ኤልያስም እንደ ታዘዘው አደረገ። ዝናብ ስላልዘነበ ግን በዚያ የነበረው ውሃ ደረቀ። ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር ኤልያስን በሲዶን ወደምትገኘው ወደ ስራጵታ ሂድ አለው። እዚያም እግዚአብሔር ኤልያስን የምትቀልበው አንዲት መበለት አዘጋጀለት። የመበለቲቱም ዱቄት ከማድጋው፥ ዘይቱም ከማሰሮው ሳይጐ ድል ዝናብ እስከሚዘንብበት ጊዜ ድረስ ቈየ።



እግዚአብሔር በቁራ አማካይነት ለኤልያስ ምግብ ሲልክለት (1ነገ 17፥1-7)። በዚያን ዘመን የመበለቲቱ ልጅ ከሞተ በኋላ ኤልያስ ለእግዚአብሔር ጸልዮ ከሞት አስነሥቶታል።



www.ethiopianorthodox.org

ከሦስት ዓመትም በኋላ እግዚአብሔር ኤልያስን ሂድና ለአክዓብ ተገልጠህ በምድር ላይ ዝናብ አመጣለሁ ብለህ ተናገር አለው። አክዓብም ኤልያስን ባገኘው ጊዜ «እስራኤልን የምትገለባብጥ አንተ ነህን?» አለው። ኤልያስ ግን መልሶ «እግዚአብሔርን ትታችሁ ጣዖትን ያመለካችሁት አንተና የአባትህ ቤት ናችሁ እንጂ እስራኤልን የምገለባብጥ እኔ አይደለሁም አለው። ከዚያም ኤልያስ አክዓብን አራት መቶ ኀምሳ የሚሆኑትን የጣዖት ነቢያት ወደ ቀርሜሎስ ተራራ እንዲሰበሰብለት ነገረው። ሐሰተኞች ነቢያቱ ከተሰበሰቡ በኋላ ሁለት ወይፈኖች አስመጥቶ የበዓሊም ነቢያት ሲጮኹ ቢውሉ መሥዋዕታቸው ተቀባይነት አጣ። ኤልያስም አምላካችሁ ተኝቶ እንደሆነ፥ ወደ ሌላ ቦታ ሄዶ እንደሆነ፥ ወይም ሌላ ጉዳይ አጋጥሞት እንደሆነ እስቲ እንዲሰማ ጮክ ብላችሁ ጥሩት እያለ ያላግጥባቸው ጀመር። ከዚያ በኋላ ራሱ ኤልያስ ያቀረበው መሥዋዕት በእግዚአብሔር ዘንድ ወዲያው ተቀባይነት አገኘ። ከዚያም አራት መቶዎች ሐሰተኞች ነቢያት ተይዘው እንዲገደሉ አደረገ። ከዚያም ዝናቡ ዘነበ። የአክዓብ ሚስት ኤልዛቤል ኤልያስ የጣዖት ነቢያትን ማስገደሉን በሰማች ጊዜ አስገድልሃለሁ ብላ ስለዛተችበት ወደ ሩቅ ቦታ ሸሽቶ ተደበቀ። እግዚአብሔርም እዚህ ምን ታደርጋለህ ብሎ ቢጠይቀው እስራኤላውያን ቃል ኪዳንህን ትተዋል፤ መሠዊያህን አፍርሰዋል፤ ነቢያትህንም ፈጅተው እኔ ብቻ ተርፌአለሁ፤ እኔንም ሊገድሉኝ ይፈልጋሉ ባለው ጊዜ አንተ እንደምትለው አይምሰልህ፤ እኔ ለበዓሊም ያልተንበረከኩ ሰባት ሺህ ሰዎች አሉኝ አለው።





ኤልያስ የጣዖት ካህናትን እንዳስገደለ (1ኛ:ነገ: ም:18)

በሌላ ጊዜ ደግሞ አክአብ በሚስቱ በኤልዛቤል ምክር በቤተ መንግሥቱ አጠገብ የነበረውን የናቡቴን የወይን ያትክልት ቦታ ለመውረስ ናቡቴን በማስገደሉ ኤልያስ ከእግዚአብሔር ተልኮ ሄዶ ገሥጾታል።

ንጉሥ አካዝያስ በታመመ ጊዜ ከዚህ ሕመም እድን እንደሆነ የአቃሮንን አምላክ ብዔልዜቡልን ጠይቁልኝ ብሎ መልእክተኞች ላከ። ኤልያስም የእግዚአብሔር መልአክ በላከው መሠረት እነዚያን መልእክተኞች ተገናኛቸውና እንዲህ አላቸው:- ለመሆኑ በእስራኤል ዘንድ አምላክ የሌለ ሆኖ ነው ወደ ብዔል ዜቡል ለመጠየቅ የምትሄዱት? ስለዚህ ወደ ንጉሡ ተመለሱና ትሞታለህ እንጂ ከወጣህበት አልጋ አትወርድም በሉት አላቸው። እነርሱም ተመልሰው ለንጉሡ ነገሩት።

ከዚያም ንጉሡ አንድ የኀምሳ አለቃ ከኀምሳ ሰዎች ጋር ላከና ኤልያስን እንዲያመጡት ነገራቸው። ነቢዩ በተራራው ጫፍ ላይ ተቀምጦ ነበር። የተላከው የኀምሳ አለቃ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፥ ንጉሥ ውረድ ይልሃል አለው። ኤልያስም መልሶ እኔስ የእግዚአብሔር ሰው ከሆንሁ ከሰማይ እሳት



www.ethiopianorthodox.org

ወርዶ አንተንና ኀምሳ ሰዎችህን ይብላ አለው። እንዳለውም እሳት ከሰማይ ወርዶ በላቸው። እንደገናም አንድ ኀምሳ አለቃና ኀምሳ ሰዎች ተላኩና እንደ መጀመሪያዎቹ እሳት በላቸው። እንደገናም ለሦስተኛ ጊዜ ሌሎች ተላኩ። አሁን ግን የኀምሳ አለቃው በትሕትናና በልመና መልክ ስላነጋገረው እግዚ አብሔር ኤልያስን ከእርሱ ጋር ውረድ አትፍራ አለው። ኤልያስም ወደ ንጉሡ ሄዶ:- «እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- መሆኑን በእስራኤል ዘንድ አምላክ የሌለ ሆኖ ነው ወደ ብዔልዜቡል ለማስጠየቅ የላክኸው? ስለዚህ ትሞታለህ እንጂ ከወጣህበት አልጋ አትወርድም» አለው። ኤልያስ እንዳለውም በእግዚ አብሔር ቃል መሠረት ንጉሡ ሞተ።

እግዚአብሔር ኤልያስን በዐውሎ ነፋስ ወደ ሰማይ ሊያወጣው በፈቀደ ጊዜ ኤልያስ ከኤልሣዕ ጋር ከጌልጌላ አብሮት ተነሣ። ኤልያስ ኤልሣዕን እግዚአብሔር ወደ ቤቴል የላከኝ ስለሆነ እዚህ ጠብቀኝ ቢለው በፍጹም ከአንተ አልለይም አለው። እንደገናም እግዚአብሔር ወደ ኢያሪኮ የላከኝ ስለሆነ እዚህ ጠብቀኝ ቢለው አልለይም አለ። አሁንም ጥቂት ከሄዱ በኋላ እግዚአብሔር ወደ ዮርዳኖስ ልኮኛልና እዚህ ጠብቀኝ አለው። ኤልሣዕ ግን ከአንተ አልለይም አለው። ከዚያም ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ሲደርሱ ኤልያስ ውሃውን በመጐናጸፊያው መታውና ለሁለት ስለተከፈለለት ሁለቱም በደረቅ መሬት ላይ እየተራመዱ ተሻገሩ። ከተሻገሩ በኋላ ኤልያስ ኤልሣዕን ከአንተ ከመወሰዴ በፊት ምን ላደርግልህ እንደምትፈልግ ለምን አለው። ኤልሣዕም መንፈስህ በእኔ ላይ ሁለት እጥፍ እንዲሆን እፈልጋለሁ አለው። ኤልያስ:- «አስቸጋሪ ነገር ጠይቀሃል፤ ነገር ግን ከአንተ በምወሰድበት ጊዜ ካየህ ይሆን ልሃል፤ አለበለዚያ ግን አይሆንልህም» አለው። አብረውም እየተነጋገሩ ሲሄዱ የእሳት ሠረገላና የእሳት ፈረሶች በመካከላቸው ገብተው ለሁለት ከፈሉአቸው። ኤልያስም በዐውሎ ነፋስ ወደ ላይ ወጣ።

ኤልሣዕም አይቶ አባቴ፣ አባቴ ሆይ፣ የእስራኤል ሠረገላና ፈረሰኞች ብሎ ጮኸ። ከዚያም ወዲያ አላየውም። ልብሱንም ይዞ ለሁለት ተረተረው። ከኤልያስ የወደቀውንም መጐናጸፊያ አነሣ።

ኤልያስ በሐዲስ ኪዳን በታቦር ተራራ ላይ ከጌታችን ጋር ተገልጦአል፤ እንዲሁም ለመጥምቁ ዮሐንስ ምሳሌ ሆኖአል።



## ሐዲስ ኪዳን

ነቢዩ ኤርምያስ ስለ ሐዲስ ኪዳን ትንቢት ሲናገር:- «እነሆ ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል፤ ይላል እግዚአብሔር» ብሏል (ኤር:ም:31ቍ:31)።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን በሁለት ሲከ ፍለው ብሉይና ሐዲስ ኪዳን ብሎ በግልጽ አብራርቶታል (2ኛ: ቆሮ: ም: 3ቍ:6 እና 14)።


<u>ሐናንያና ሰጲራ</u>:- ሐናንያ የሚባል ሰው ሰጲራ የምትባል ሚስት ነበረ ችው። መሬት ሸጠና ከገንዘቡ ከፊሉን አስቀርቶለት በማምጣት ለሐዋርያት አስረከበ። ከገንዘቡም ከፊሉን ማስቀረቱን ሚስቱ ታውቅ ነበር።

ገንዘቡን ለሐዋርያት ካስረከበ በኋላ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ እንዲህ አለው:- መሬቱን በመሸጥ ካገኘኸው ገንዘብ ከፊሉን ለማስቀረት ለምን ሰይጣን አነሣሣህ? መሬቱን ሳትሸጠው ያንተው ነበር፤ ከሸጥኸውም በኋላ ገንዘቡ ያንተው ነበር። ይህ ከሆነ ታዲያ ለምን ዋሸህ? የዋሸኸውም በእግዚአብሔር ላይ ነው እንጂ በሰው ላይ አይደለም። ሐናንያ ይህን የሐዋርያውን የቅዱስ ጴጥሮስን ንግግር በሰማ ጊዜ ወደቀና ሞተ። ይህን ሁናቴ የሰሙ ሰዎች እጅግ ፈሩ። ጐልማሶችም ወስደው አስከሬኑን ከገነዙት በኋላ ቀበሩት።

ይህ ከሆነ ከሦስት ሰዓት በኋላ የሐናንያ ሚስት ሰጲራ በባልዋ ላይ የደረ ሰውን ሁናቴ ሳታውቅ መጣች። ከዚያም ቅዱስ ጴጥሮስ እንዲህ ብሎ ጠየ ቃት:- መሬታችሁን የሸጣችሁት ለዚህን ያኽል ገንዘብ ነውን? እርስዋም አዎ ለዚህን ያኽል ገንዘብ ነው ብላ መለሰች። በዚህ ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስ መንፈስ ቅዱስን ለመፈታተን እንዴት ተስማማችሁ? ባልሽን ቀብረው የተመለሱ ሰዎች እነሆ በበር ናቸው፤ አንቺንም ወስደው ይቀብሩሻል አላት። ወዲያው በድንገት እርስዋም ወድቃ ሞተች። ሰዎችም ወስደው በባልዋ አጠገብ ቀበርዋት።



www.ethiopianorthodox.org



በሐናንያና በሰጲራ ላይ የደረሰው ሁናቴ (የሐ:ሥ:ም:5፥1–1)።

<u>ወደ ሮሜ ሰዎች የተላከው የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት:-</u> ይህን
መልእክት በ56 እና በ60 ዓ.ም መካከል የጻፈው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ
ነው። በ57 ወይም በ58 ዓ.ም የሚሉ ምሁራን አሉ። ሐዋርያው ቅዱስ
ጳውሎስ ከጻፋቸው መልእክቶች መካከል ረዘም ያለና ብዙ ሐሰቦችን የያዘ
የሮሜ መልእክት ነው። ይህንንም ጽሑፍ ያዘጋጀው በቆሮንቶስ እንደሆ
ይታመናል። እንደ ሊቃውንቱ እምነት ይህን መሰል የተዋጣለት ጽሑፍ
ለማቀናበር የግድ በአንድ ቦታ ረዘም ላለ ጊዜ መቈየት ያስፈልጋል። በሐዋር
ያት ሥራ ም:20 ቍ:3 ላይ እንደተገለጠው ቅዱስ ጳውሎስ በግሪክ አገር
ለሦስት ወር መቈየቱ ተነግሮአል: ቆሮንቶስ ደግሞ ከግሪክ ከተሞች አንዷ
ነች። በዚህ መልእክቱ መጨረሻ ላይ ካስተላለፋቸው ሰላምታዎች መካከል
በምዕራፍ 16ቍ: 23 ላይ «የእኔና የቤተ ክርስቲያን ሁሉ አስተናጋጅ ጋይዮስ
ሰላምታ ያቀርብላችኋል የሚለው ነው። ይህም ጋይዮስ ሐዋርያው ቅዱስ
ጳውሎስ ካጠመቃቸው የቆሮንቶስ ሰዎች አንዱ መሆኑን ለቆሮንቶስ ሰዎች
በላከው መጀመሪያ መልእክቱ ምዕራፍ 1ቍ:14 ላይ ተገልጾአል። ሰላም



www.ethiopianorthodox.org

ታውን ያስተላለፈውም መልእክቱን ከጻፈበት ቦታ እንጂ ከሌላ ስለማይሆን በዚህ ምክንያት መልእክቱ የተጻፈው በቆሮንቶስ ከተማ እንደሆነ ይታመናል።

ይህ መልእክት ዐሥራ ስድስት ምዕራፎች ያሉት ሲሆን በአጠቃላይ ሲታይ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈለ ነው። ከምዕራፍ አንድ እስከ ምዕራፍ ዐሥራ አንድ ያለው ክፍል በሮማ ያሉ ክርስቲያኖች ከሁለት ወገኖች ማለት ከአይሁድና ከአረማውን ወደ ክርስትና የገቡ መሆናቸውን ያመለክታል። እነዚህም ሁለት ወገኖች ከክርስትናው በፊት የነበሩበትን ባህል ያንጸባርቁ እንደ ነበረ ለማስተዋል ይቻላል። አይሁድ በቀድሞ አባቶቻቸው ዝነኛነትና በሙሴ አማካይነት በተሰጠው ሕግ ይመኩ ነበር። ይህም ብቻ ሳይሆን አረማውያን ለክርስትናው እምነት ብቃት እንደሌላቸው አድርገው ይንቁአቸው ነበር። አረማውያኑ ደግሞ በዓለማዊው የፍልስፍና ዕውቀት ከአይሁድ ይበልጡ ስለ ነበረ አይሁድን እንዳልተማሩ ሰዎች ከመቍጠራቸውና ከመናቃቸውም በላይ የአይሁድ የቀድሞ አባቶች አምላካቸውን ትተው ወደ ጣዖት አምልኮ ያዘነብሉ ስለነበረና እነርሱም ክርስቶስን ስለገደሉ ይነቅፉአቸው ነበር።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ሁለቱን ወገኖች ለማስታረቅ የተጠቀመበት ዘዴ የሁለቱንም ትምክሕት ዋጋ ማሳጣት ነበር። እኛ እንደ አይሁድ ያለ እግዚአብሔርን የማወቅ ዕድል ተሰጥቶን ቢሆን ኖሮ ጣዖትን በማምለክ ከእግ ዚአብሔር አንርቅም ነበር ለሚሉት አረማውያን የሚከተለውን መልስ ሰጥቶ አቸዋል።

«የሙሴ ሕግ የሌላቸው አረማውያን በተፈጥሮአቸው ሕግ የሚያዝዘውን ነገር ይፈጽማሉ፤ በዚህም ምክንያት የሙሴ ሕግ ባይኖራቸውም የራሳቸው የተፈጥሮ ሕግ ስላላቸው ማድረግ የሚገባቸውን ያውቃሉ» (ሮሜ: ም:2 ቍ:14)።

**«ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ለሰዎች የማይታወየው የእግዚአብሔር ባሕርይ ይኸውም ዘለዓለማዊው ኀይሉና አምላክነቱ እርሱ በፈጠራቸው ነገሮች ግልጥ ሆኖ ታይቶአል፤ ስለዚህ እንደእነዚህ ያሉት ያዋቂ አጥፊዎች የሚያመካኙት የላቸውም»** (ሮሜ:ም:1ቍ:20)።

በሌላ በኩል ደግሞ አይሁድን ሲወቅሳቸው እንዲህ ብሏል።

«እነሆ፥ አኔ አይሁዳዊ ነኝ ትላለህ፤ ... የኦሪትን ሕግ ስለተማርህ መልካም ማድረግን ታውቃለህ፤ ... ሌሎችን የምታስተምር ስትሆን ራስህን ለምን አታስተምርም? አትስረቁ ትላለህ፤ አንተ ግን ትሰርቃለህ፤ አታመንዝሩ ትላለህ፤ አንተ ግን ታመነዝራለህ፤ ... አንተ በእግዚአብሔር ሕግ ትመካለህ፤ ነገር ግን ሕጉን በማፍረስ እግዚአብሔርን ትንቃለህ» (ሮሜ ፡ም፡ 2 ቍ፡ 17–23 )።

«በእግዚአብሔር ፊት ሕግን የሚያደርጉት ይጸድቃሉ እንጂ፤ ሕግን የሚሰሙት ጻድቃን አይደሉም» (ሮሜ፡ም፡2ቍ፡13)።

እንደዚህ ሁለቱንም ወገኖች ከወቀሰ በኋላ በሁለቱ መካከል ልዩነት የሌላ መሆኑን ሲያመለክት እንዲህ ብሏል:-

«ሕግ ሳይኖራቸው ኃጢአት የሚሠሩ ሁሉ ሕጉ ባይኖራቸውም ይጠ ፋሉ፤ ሕግ እያላቸው የሚያጠፉ ደግሞ በሕግ ይፈረድባቸዋል (ሮሜ፡ 2፥ 12)።

«ሰዎች ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋል፤ የእግዚአብሔርንም ክብር አጥተ ዋል» (ሮሜ፡ም፡3ቍ፡23)።

እስራኤላውያን ሕጉን መፈጸም ስለተሳናቸውና አረማውያንም በኃጢአት ስለኖሩ ሁለቱም ወገኖች በክርስቶስ አምነው ለእርሱ ታዛዥ በመሆን ብቻ ለመዳን ይችላሉ እንጂ ማንኛውም በሌላ አይመስ።

የመጽሐፉ ሁለተኛ ክፍል ደግሞ ከምዕራፍ ዐሥራ ሁለት እስከ ምዕራፍ ዐሥራ ስድስት ነው። በውስጡም ለመላው ሕዝበ ክርስቲያን አስፈላጊ የሆነ ምክሮች፥ መመሪያዎችና ትእዛዞች አሉበት። እነርሱም የክርስቶስን አንዲት ቤተ ክርስቲያንና ምሥጢራዊ አካልዋን እንደ አንድ ሕዝብና እንደ አንድ መንጋ ለአንድ እረኛ (ጠባቂ) እንዲያሰባስቡ ነው።

ከዚያም ቀጥሎ የገለጠላቸው እስከዚያን ጊዜ ድረስ በምሥራቅ አገሮች ለሚገኙ አረማውያን ወንጌል ማስተማሩን ስላጠናቀቀ ከዚያ በኋላ ለማስተማር ፊቱን ወደ ምዕራቡ ዓለም እንደሚመልስ ነው። በምሥራቅ አገሮች ብዙዎችን ወደ ክርስትና እንደመለሰ በምዕራብ አገሮችም ብዙዎችን ለመመለስ እን ሚችል ተስፋውን ገልጦአል።

መልእክቱንም ያጠናቀቀው ሰላምታዎችን በማቅረብ ነው።

<u>ወደ ገላትያ ሰዎች የተላከው የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት:-</u>

በሐዋርያት ሥራ ም፡13ቍ፡14 እና 51 ላይ እንዲሁም በም፡14 ቍ፡6 ላይ የተጠቀሱት ኢቆንዮን፥ ልስጥራ እና ደርቤን የተባሉት ከተሞች የሚገኙት ገላትያ በምትባለው አውራጃ ውስጥ ነው። እነዚህም ከተሞች ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወንጌልን ያስተማረባቸው ከተሞች ናቸው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳው ሎስ በእነዚህ ከተሞች ንጹሑን የክርስትና ትምህርት ዘር ዘርቶና ብዙዎችንም ምእመናን አፍርቶ ነበር። ነገር ግን እርሱ ከዚያ አገር ከሄደ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሐሰተኞች ሐዋርያት ከኢየሩሳሌም ወጥተው የሚከተለውን ትምህርት ማሠራ ጨት ጀመሩ:-

አንደኛ/ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በቅርብ ጊዜ ከአይሁድነት ወደ ክርስትና የተዛወረ እንጂ ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ አይደለም፤ እንዲያውም ጌታችን ኢየሱስንም ያላየው በመሆኑ ማንም እርሱን ሐዋርያ አድርጎ የሾመው የለም አሉ።

ሁለተኛ/ ማንም ሰው ወደ ክርስትና ሃይማኖት ከመግባቱ በፊት በአይሁድ ሃይማኖትና በኦሪት ሕግ ጸንቶ መኖር አለበት አሉ።

በዚህም ትምህርታቸው ብዙዎችን አሳስተው አደናቀፉአቸው።

በዚህም ምክንያት ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የገላትያ መልእክቱን ለእነዚህ ለሁለት ጉዳዮች መልስ በመስጠት ላይ ያተኰረው።

የገላትያው መለእክት ስድስት ምዕራፎች አሉት።

ከምዕራፍ አንድ እስከ ምዕራፍ ሦስት ድረስ የወንጌል አገልግሎቱን ሥራ የተረከበው ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እጅ እንጂ ከሐዋርያቱ አለመሆኑና በዚህም ምክንያት ከሐዋርያት እንደማያንስ ይገልጣል። ትምህርቱም ከክር ስቶስ ስለሆነ እውነት እንጂ ሐሰት የሌለው መሆኑን ያረጋግጣል።

ከምዕራፍ አራት እስከ ምዕራፍ ስድስት ደግሞ እነዚህ ሐሰተኞች ሐዋርያት እንደሚሉት ሳይሆን መዳን የሚገኘው በጌታችን ኢየሱስ አዳኝነት በማመን ነው እንጂ የኦሪትን ሕግጋት በመፈጸም አለመሆኑን ያብራራል።



www.ethiopianorthodox.org

ይህ መልእክት በብዙ ነገር ወደ ሮሜ ሰዎች የላከው መልእክቱን ይመ ስላል።

ወደ ቲቶ የተላከ የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት:- ቲቶ አረማዊ የነበረና በሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እጅ ክርስትናን የተቀበለ ሰው ነበር። በኢየሩሳሌም ለነበሩ ድኾች ምእመናን ከተለያዩ አብያተ ክርስቲያን የሚሰ በሰበውን ችሮታ ለማሰባሰብ ከሐዋርያው ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር አብሮ ተጉዞ አል። እንዲሁም ለዚሁ ሥራ ተወክሎም የተላከበት ጊዜ አለ። በመጨረሻም ቅዱስ ጳውሎስ ቲቶን የቀርጤስ ኤጲስ ቆጶስ አድርጎ ሾሞታል። የቤተ ክርስ ቲያን ሽማግሌዎችንም በየከተማው እንዲሾም አዝዞታል። የክርስቲያንም ሥነ ምግባርና የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ግዴታ ምን መሆን እንደሚገባቸው ዘርዝሮ ጽፎለታል። መልእክቱ ሦስት ምዕራፎች ያሉት ሲሆን የተጻፈውም የመጀመሪያው የጢሞቴዎስ መልእክት በተጻፈበት ጊዜ እንደሆነ ይገመታል። የዚህም ግምት ምክንያት ሁለቱ መልእክቶች በብዙ ነገር ተመሳሳይ በመሆና ቸው ነው። ስለዚህም ሁለቱ መልእክቶች በአንድ ጊዜ ቢነበቡ ይመረጣል።

ለፊልሞና የተላከው የሐዋያው የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት:- ፊልሞና በቆላስይስ ዝነኛ ክርስቲያንና የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስ ደቀ መዝሙር ነበር። ቤተ ክርስቲያንንም በዲቁና አገልግሎአል። ይህን መልእክት የጻፈለት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሮማው እስር ቤት ውስጥ በነበረበት ወደ መጨ ረሻው ዘመን ነው። ደብዳቤውን በተለየ የጻፈው ስለ አናሲሞስ ነው። ይህ አናሲሞስ የፊልሞና ባሪያ የነበረና ከጌታው ጠፍቶ ወደ ሮማ የኰበለለ ነው፡ ምናልባትም አንዳች ነገር ከጌታው ሰርቆ ሳይሄድ የቀረ አይመስልም። ወደ ሮማ በመጣ ጊዜ ከሐዋርያው ከቅዱስ ጳውሎስ እጅ ክርስትናን ተቀበለ፡ ስለዚህ አሁን ክርስቲያን እንደመሆኑ ከቀድሞው ጌታው ጋር በወንድምነት መልክ እንዲታረቀው ዐደራ በማለት ይህን መልእክት ጽፎ በአናሲሞስ እጅ ላከው።

ከዚህ ምዕራፍ የምናገኘው ትምህርት

ርብቃ ለኻያ ዓመት መኻን ሆና ከኖረች በኋላ ይስሐቅ ስለጸለየላት ፀን መንታዎችን ለመውለድ መቻልዋ የእግዚአብሔርን ጸሎት ተቀባይነት ያመ ክታል።

ምንም እንኳ በትንቢቱ መሠረት ያዕቆብ ከወንድሙ ከዔሳው የተሻ ዕድል እንደሚጠብቀው የታወቀ ቢሆን ያዕቆብ ያን ዕድል ከእግዚአብሔ

እጅ በመጠበቅ ፈንታ ችኵልና ራስ ወዳድ ሆነ። በመጀመሪያ የወንድሙን ብኵርና በማታለል በምስር ወጥ ገዛው። ሁለተኛ ምርቃቱንም በማታለል ወሰደበት። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ሲቀጣው የአጐቱ አታላይ አገል ሎት ለኻያ ዓመት እንዲያገለግል አደረገው። ይህም የሚያመለክተው እግዚአ ብሔር ለያንዳንዳችን እንደየተግባራችን ተገቢ ዋጋችንን ወይም ቅጣታችንን ሳይሰጠን የማይቀር መሆኑን ነው (ዘፍ:ም:31 ቍ: 36–42፤ ኤር: 9:4)።

የነቢዩን የኤልያስን ታሪክ ብንመለከት ደግሞ የእግዚአብሔርን ተአም ራታዊ ድርጊቶች እናስተውላለን። እግዚአብሔርም ከተአምራታዊ ድርጊቶቹ ሌላ እርሱ ሲፈቅድ ለወዳጆቹ ምን ያኽል ጥበቃ የሚያደርግላቸው መሆኑን ለመገንዘብ እንችላለን። በመጀመሪያ በኮራት ወንዝ አጠገብ ተሸሽጎ ሳለ በቁ ራዎች አማካይነት በየዕለቱ ምግብ የሚመጣለት መሆኑን እናስተውላለን። ከዚ ያም የወንዙ ውሃ በዝናብ መቆም ምክንያት ሲደርቅ ወደ ስራጵታ ሄዶ አንዲት መበለት ከማሰሮዋ ከማያልቀው ዘይትና ከማድጋዋ ከማያልቀው ዱቄት እየተ መገበ እንዲኖር ተደረገ።

ከንጉሡ ከአክዓብ ጋር ተገናኝቶ በድፍረት ሲገሥጸው ንጉሡ ምንም ጉዳት ሳያደርስበት መቅረቱ የእግዚአብሔር ጥበቃ መሆኑን እንረዳለን። ከዚያም በኋላ ንጉሡና ንግሥቲቱ የሚያመልኩባቸውን የጣዖታቱን ነቢያት በሚያስፈጅበት ጊዜ ምንም ንግሥቲቱ እገድልሃለሁ ወይም አስገድልሃለሁ ብላ ብታስፈራራው የእግዚአብሔር ጥበቃ ስላልተለየው ግን ምንም ልታ ደርስበት አልቻለችም። ይህም ሁሉ ሆኖ ምንም እንኳ እግዚአብሔር ሁልጊዜ ከእርሱ ጋር መሆኑን ቢመለከት እምነቱን በእግዚአብሔር ላይ አሳርፎ ከመጠባበቅ ይልቅ ከሰው ልጅ ደካማነት የተነሣ ከንግሥቲቱ ሸሽቶ ተደበቀ። እግዚአብሔርም እዚህ ምን ታደርጋለህ ተመልሰህ ሂድ ቢለው እግዚአብሔርን የሚያመልክ አንድም የለም፤ ከነቢያትም እኔ ብቻ ተረፍኩ ባለው ጊዜ አንተ የማታውቃቸው ለጣዖት ያልተንበረከኩና እኔን ብቻ የሚያመልኩ ሰባት ሺህ ሰዎች በሕዝቡ መካከል አሉኝ አለው። በዚህም መሠረት በእኛና በእግዚ አብሔር መካከልም ምን ያህል ያስተሳሰብ ልዩነት መኖሩን ልንገነዘብ እንች ላለን።

በሐናንያና በሰጲራ ታሪክ የተከሠተው ሁናቴ በመጽሐፈ ኢያሱ ም:7 በዓካን ላይ ከደረሰው ሁናቴ ጋር ተመሳሳይነት ዓለው። ዓካን ዐይኑ ሳስቶበት የተከለከለውን ነገር በድብቅ በመውሰዱ በሞት ተቀጣ። እንዲሁም ሐናንያና



www.ethiopianorthodox.org

ሰጲራ ከሸጡበት ዋጋ ላይ በድብቅ ከፊሉን ቀንሰው ስላስቀሩ በሞት ተቀጡ። ከሰው መደበቅ ይቻል ይሆናል። ከእግዚአብሔር መደበቅ ግን አይቻልም። እንዲያውም ይህን ማድረግ የእግዚአብሔርን ዐዋቂነት አለማመን ወይም መጠራጠር ነው። ይህም ምሕረት የሌለው ኃጢአት ነው። እነርሱ የሞቱት በኃጢአታቸው ቢሆንም ለሌሎች ግን ማስጠንቀቂያ ትምህርት ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ በእግዚአብሔር ዘንድ የዘር ልዩነት አለመኖሩን ይገልጻል። እንዲሁም ክርስቲያን ለመሆን ዋናው ነገር በክርስቶስ አዳኝነት ማመን ነው እንጂ አስቀድሞም ሆነ በኋላ በአይሁድ ሥርዓት ውስጥ ማለፍ አይደለም። በዚህም መሠረት አይሁድም ሆኑ አረ ማውያን በክርስቶስ እስከአመኑ ድረስ እኩል ናቸው እንጂ ማናቸውም ከሌላው አይበልጥም ይላል።

እንዲሁም በገላትያ መልእክቱ ለመዳን የሚያስፈልገው የኦሪት ሕግ ሳይሆን በክርስቶስ ማመን መሆኑን ያረጋግጣል።

ለቲቶ በላከው መልእክቱ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችንና የምእ መናንን ክርስቲያናዊ ግዴታ ዘርዝሮ ያስረዳል።

ለፊልሞና በጻፈው መልእክቱ ደግሞ በክርስቲያን ሃይማኖት ውስጥ ባሪያና ጌታ ሳይሆን ወንድማማችነት ብቻ መኖሩን ያረጋግጣል።

## ጥያቄዎች

1. በብሉይ ኪዳን ቅዱስ መጽሐፍነት የሚያምኑ እነማን ናቸው?
2. በሐዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ቃልነት የሚያምኑ እነማን ናቸው?
3. የመጽሐፍ ቅዱስን የእግዚአብሔር ቃል መሆን የምንረዳው በም ንድነው?
4. የገራር ሰዎች እንዳይገድሉት ይስሐቅ ምን አለ?
5. የፍልስጥኤማውያኑ ንጉሥ አቢሜሌክ ይስሐቅን ምን ብሎ ወቀሰው?
6. ይስሐቅ ለንጉሡ ወቀሳ ምን መልስ ሰጠ? ንጉሡስ ምን አደረገ?
7. በዔሳውና በያዕቆብ መካከል በኵር ማነው?
8. ይስሐቅ የጸለየው ስለምንድነው?

www.ethiopianorthodox.org



9. ርብቃ የጸለየችው ስለምንድነው?
10. እግዚአብሔር ርብቃን ምን ብሎ አበረታታት?
11. የዔሳውና የያዕቆብ አኗኗር የሚለያየው በምን ዐይነት ነበር?
12. ያዕቆብ ዔሳውን ያታለለባቸው ሁለት ነገሮች ምንና ምን ናቸው?
13. ርብቃ ያዕቆብን ምን ብላ መከረችው?
14. ያዕቆብስ ለምክሩ ምን መልስ ሰጠ?
15. ዔሳው ምን ክፉ ነገር አሰበ?
16. ይስሐቅንና ርብቃን ያሳዘናቸው ምን ነበር?
17. ወላጆቹ ያዕቆብን ምን ብለው መከሩት?
18. ያዕቆብ በሕልሙ ምንን አየ?
19. ጠዋት ሲነጋ ምን አደረገ?
20. አጐቱ ላባ ያዕቆብን በምን አታለለው?
21. ያዕቆብ ስለ ሁለቱ ሚስቶቹ ስንት ዓመት አገለገለ?
22. ያዕቆብ ስንት ልጆች ተወለዱለት?
23. የተወለዱትስ ከማንና ከማን ነው?
24. ያዕቆብ ወደ ተወለደበት አገር ሲመለስ ምን ሕልም አየ?
25. ያዕቆብ ምን ተብሎ ተባረከ?
26. ነቢዩ ኤልያስ የነበረው በማን ዘመን ነው?
27. እግዚአብሔር ነቢዩን ኤልያስን በኮራት ወንዝ አጠገብ እንዲሸሸግ የነገረው ለምንድነው?
28. በኮራት ወንዝ አጠገብ በተሸሸገ ጊዜ ምግብ የሚያገኘው እንዴት ነበር?
29. ነቢዩ ኤልያስ ወደ ኮራት ወንዝ አጠገብ ከመሄዱ በፊት አክዓብን ምን አለው?
30. በኮራት የነበረው ውሃ በደረቀ ጊዜ እግዚአብሔር ነቢዩን ኤልያስን ምን አለው?

31. ነቢዩ ኤልያስ በስራጵታ ያደረጋቸው ሁለት ተአምራት ምንና ምን ናቸው?

32. ከሦስት ዓመት በኋላ እግዚአብሔር ነቢዩን ኤልያስን ወደ ንጉሥ አክዓብ ምን ብሎ ላከው?

33. ንጉሡ ነቢዩን ኤልያስን ሲገናኘው ምን አለው?

34. ነቢዩስ ምን መልስ ሰጠው?

35. ነቢዩ ኤልያስ ከባዓል ነቢያት ጋር ምን ተደራደረ?

36. የድርድሩስ ውጤት ምን ሆነ?

37. ነቢዩ ኤልያስ በባዓል ነቢያት ላይ ምን አስደረገ?

38. የንጉሡ ሚስት ኤልዛቤል በነቢዩ በኤልያስ ላይ ምን አደረገችበት?

39. በዚህስ ምክንያት ነቢዩ ምን አደረገ?

40. በዚህ ጊዜ በእግዚአብሔርና በኤልያስ መካከል የተካሄደው ጥያቄና መልስ ምን የሚል ነበር?

41. አክዓብ በሚስቱ በኤልዛቤል ምክር ምን ክፉ ድርጊት አደረገ?

42. በዚህስ በንጉሡ ክፉ ድርጊት ምክንያት ነቢዩ ኤልያስ ምን አደረገ?

43. ንጉሥ አካዝያስ በታመመ ጊዜ ምን አደረገ?

44. በዚህስ ጉዳይ ነቢዩ ኤልያስ ምን አደረገ?

45. ንጉሡ በላካቸው ሰዎች ላይ ነቢዩ ኤልያስ ምን አደረገ?

46. ለሦስተኛ ጊዜ ንጉሡ የላካቸው ሰዎች ሁናቴ ቀደም ብለው ከተላኩት የተለየው በምንድነው?

47. ነቢዩ ኤልያስ ወደ ንጉሥ አካዝያስ ሄዶ ምን አለው?

48. ነቢዩ ኤልያስ በመጨረሻ ምን ሆነ?

49. ነቢዩ ኤልያስ ኤልሣዕን ምን ጠይቆት ምን መልስ ሰጠው?

50. ስለ ነቢዩ ኤልያስ በሐዲስ ኪዳን ውስጥ የተነገረው መቼና እንደምን ነው?

51. ነቢዩ ኤርምያስ ስለ ሐዲስ ኪዳን ትንቢት የተናገረው ምን ብሎ ነው?



52. የሐናንያንና የሰጲራን ታሪክ ተናገር።

53. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች የላከው መልእክት ከሌሎቹ መልእክቶቹ በምን ይለያል?

54. መልእክቱን የጻፈው የት ሆኖ ነው?

55. መጽሐፉ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል ስንል በምንና በምን ማለታችን ነው?

56. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ ለማስታረቅ የፈለገው ማንንና ማንን ነው?

57. ለማስታረቅስ ምን ዘዴ ተጠቀመ?

58. ያገላትያ መልእክቱስ በምን ዐይነት ሁለት ታላላቅ ጉዳዮች ላይ ያተኰረ ነበር?

59. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ቲቶን ምን አዘዘው?

60. ለፊልሞና የተላከው መልእክት ዋና ዓላማ ምን ነበር? ከዚያስ ምን እንማራለን ?

# ምዕራፍ 3

## ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ

### የጌታችን ትምህርቶች

<u>ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና ኒቆዲሞስ</u> :- በአይሁድ ሕዝብ ዘንድ ታላቅ ግምት የሚሰጠው የተከበረ ሰው ነበር። እርሱም በጣም የተማረ ፈሪሳዊ ሰው ነበር። እንዲሁም የአይሁድን ሕዝብ የሚያስተዳድረው የጉባኤ አባል ነበር።

ይህ ኒቆዲሞስ ጌታችን ኢየሱስን አግኝቶ ለማነጋገር ቢፈልግም በእርሱ ደረጃ ላለ የአይሁድ አለቃ ይህን ማድረግ ቀላል አልነበረም። በአንድ በኩል እርሱ ከአይሁድ ሊቃውንት አንዱ በመሆኑ ከጌታችን ኢየሱስ አንዳንድ ነገሮችን ጠይቆ ለመረዳት እንደ ኀፍረት የቈጠረው ይመስላል። በሌላ በኩል ደግሞ የአይሁድ አለቆች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስንና ትምህርቱን በጥላቻ



www.ethiopianorthodox.org

መልክ ያዩ ስለነበረ እነርሱንም የፈራ ይመስላል። በእነዚህም የምናልባት ምክንያቶች በቀን ሳይሆን በሌሊት ለመገናኘት ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሄደ።

ኒቆዲሞስ ጌታችን ኢየሱስን በተገናኘ ጊዜ «መምህር ሆይ አንተ ከእግዚአብሔር የተላከህ መምህር መሆንህን እናውቃለን፤ ምክንያቱም እነዚህን አንተ የምታደርጋቸውን ድንቅ ነገሮች እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ካልሆነ በቀር ማንም ሰው ሊያደርጋቸው አይችልም አለው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማንም ሰው እንደገና ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም ሲል መልስ ሰጠው። ኒቆዲመስም ሰው ተወልዶ ካደገ በኋላ እንዴት እንደገና ሊወለድ ይችላል? ብሎ ጠየቀው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም አባባሉን በማብራራት ሰው ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ካለተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም፤ ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፤ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው። ከመንፈስ መወለድ አለባችሁ ስላልኩህ አትደነቅ፤ ነፋስ ወደ ፈለገው አቅጣጫ ይነፍሳል፤ ድምፁንም ትሰማለህ፤ ከወዴት እንደመጣና ወዴት እንደሚሄድ አታውቅም፤ ከመንፈስም የተወለደ እንደዚሁ ነው አለው። ኒቆዲሞስ ግን የጌታችን አባባል ስላልገባው ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ሲል ጠየቀ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም አንተ የእስራኤል መምህር ስትሆን ይህን አታውቅምን? እኛ የሰማነውን እንናገራለን፤ ያየነውንም እንመሰክራለን፤ ምስክርነታችንንም አትቀበሉም፤ የምድሩን ነገር ስንነግራችሁ ካላመናችሁ የሰማዩን ነገር ስንነግራችሁማ እንዴት ታምናላችሁ? ከሰማይ ከወረደው ከሰው ልጅ በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም። እርሱም በሰማይ የሚኖር ነው። ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደሰቀለ የሰው ልጅም የሚያምኑበትን ለማዳን መሰቀል አለበት አለው። ንግግሩንም በመቀጠል በእግዚአብሔር ልጅ የሚያምን ሁሉ አይፈረድበትም፤ በእርሱ የማያምን ግን አስቀድሞ ተፈርዶበታል። ብርሃን ወደዚህ ዓለም መጣ፤ ሰዎች ግን ሥራቸው ክፉ ስለነበረ ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ወደዱ። ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ክፋቱ እንዳይገለጥበት ብርሃንን ይጠላል ብሎ ዘርዝሮ አስረድቶታል (ዮሐ:ም:3)።





ጌታችንና ኒቆዲሞስ (ዮሐ:ም:3)።

<u>የሰማርያይቱ ሴት (ዮሐ:ም:4)</u>:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከይሁዳ ወደ ገሊላ በሚሄድበት ጊዜ በሰማርያ በኩል ማለፍ ነበረበት። ሲካር ወደምትባል ከተማ ሲደርሱ ደቀ መዛሙርቱ ምግብ ለመግዛት ወደ ገበያ ሄዱ። ጌታችን በጉዞው ደክሞት ስለነበረ በያዕቆብ የውሃ ጉድጓድ አጠገብ ተቀመጠ። በዚያም ተቀምጦ ሳለ አንዲት የሰማርያ ሴት ከጉድጓድ ውሃ ልትቀዳ መጣች። ጌታችንም ሴትዮዋን ውሃ አጠጪኝ አላት። ሴትዮዋ ግን እንዴት አንተ አይሁዳዊ ስትሆን ከእኔ ከሰማርያይቱ ሴት ውሃ ትጠይቃለህ አለችው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ስጦታና ውሃ አጠጪኝ የሚልሽ ማን እንደሆነ ብታውቂ አንቺ በለመንሽውና እርሱም የሕይወት ውሃ በሰጠሽ ነበር አላት። ሴትዮዋም ጌታ ሆይ፥ ጉድጓዱ ጥልቅ ሲሆን አንተ መቅጃ የለህም፤ ታዲያ የሕይወት ውሃ ከየት ታመጣለህ? አንተ ይህን ውሃ ከሰጠን ከአባታችን ከያዕቆብ ትበልጣለህን? ብላ ጠየቀችው። እኔ የምሰጠው ውሃ ለሚጠጣው ሰው ለዘለዓለም ሕይወት የሚፈልቅ ምንጭ ስለሚሆን እኔ ከምሰጠው ውሃ የሚጠጣ ለዘለዓለም ከቶ አይጠማም፤ ከዚህ ውሃ የሚጠጣ ሰው ሁሉ እንደገና ይጠማል አላት። ሴትዮዋም ጌታ ሆይ እንግዲያውስ እንደገና ጠምቶኝ ውሃ ለመቅዳት እንዳል



www.ethiopianorthodox.org

መጣ እንዲህ ሀይነቱን ውሃ ስጠኝ አለችው። በዚህ ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባልሽን ጠርተሽ ተመለሺ አላት። እርስዋ ግን ባል የለኝም አለችው። ጌታችንም ባል የለኝም ማለትሽ ትክክል ነው፤ አምስት ባሎች ነበሩሽ፤ አሁን ካንቺ ጋር ያለው ባልሽ አይደለም አላት። ሴትዮዋም ጌታ ሆይ፥ አንተ ነቢይ መሆንህን አሁን ዐወቅሁ፤ አባቶቻችን በዚህ ተራራ ላይ ሰገዱ፤ እናንተ ግን መስገድ ያለበት በኢየሩሳሌም ብቻ ነው ትላላችሁ አለችው። እርሱም መልሶ በኢየሩሳሌም ወይም በዚህ ተራራ ላይ ለአብ የማትሰግዱበት ጊዜ ይመጣል፤ እናንተ ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ፤ እኛ ግን ድኅነት ከአይሁድ ስለሆነ ለምናውቀው እንሰግዳለን። ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በእውነትና በመንፈስ የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል እርሱም አሁን ነው አላት። ሴቲቱም መሲሕ እንደሚመጣ ዐውቃለሁ፤ እርሱ ሲመጣ ሁሉንም ነገር ይነግረናል አለችው። እርሱም የማነጋግርሽ እኔ እርሱ ነኝ አላት። ከዚህ በኋላ ሴቲቱ እንስራዋን እዚያው ትታ ወደ ከተማ ሄደችና ያደረግሁትን ነገር ሁሉ የነገረኝን ሰው ኑና እዩ፤ ምናልባት እርሱ መሲሕ ይሆናል ብላ ለሰዎች ተናገረች። ሰዎቹም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ለማየት ሄዱ። ብዙ ሰዎች በእርሱ አመኑ። ከእነርሱ ጋር እንዲቈይ ስለለመኑት ሁለት ቀን ከእነርሱ ጋር ቆየ።



ጌታችን የሰማርያይቱ ሴት (ሉ.ቃ:7፡1–10 )



<u>ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብርሃም በፊት የነበረ መሆኑ</u>

አይሁድ ጌታችንን አንተ ጋኔን አለብህ አሉት። እኔ አባቴን አከብራለሁ እንጂ ጋኔን የለብኝም፤ እናንተ ግን ታዋርዱኛላችሁ፤ እኔ የራሴን ክብር አልፈልግም፤ የእኔን ክብር የሚፈልግና የሚፈርድ ሌላ አለ። በእውነት እላችኋለሁ፤ ቃሌን የሚጠብቅ ከቶ አይሞትም አላቸው።

አይሁድም ጋኔን እንዳለብህ አሁን ዐወቅን፤ አብረሃም እንኳ ሞቶአል፤ ነቢያትም ሞተዋል፤ አንተ ግን ቃሌን የሚጠብቅ ከቶ አይሞትም ትላለህ፤ ለመሆኑ አንተ ከሞተው አባታችን ከአብርሃም ትበልጣለህን? ነቢያት ሞተ ዋል፤ ታዲያ አንተ ራስህን ማን ትላለህ? አሉት።

ጌታችንም እኔ የራሴን ክብር ብፈልግ ክብሬ ዋጋ የለውም፤ እኔን የሚያከብረኝ አባቴ ነው፤ እርሱም አምላካችን የምትሉት ነው፤ እናንተ ግን እርሱን አላወቃችሁትም፤ እኔ ዐውቀዋለሁ፤ እኔ አላውቀውም ብል እንደ እናንተ ሐሰተኛ በሆንሁ ነበር፤ እኔ ግን ዐውቀዋለሁ፤ የአባታችሁ የአብርሃም ምኞት የእኔን ቀን አይቶ ለመደሰት ነበር፤ አይቶም ተደሰተ አላቸው።

በዚህ ጊዜ አይሁድ አንተ ገና ኀምሳ ዓመት አልሆነህም እንዴት አብርሃምን አየሁ ትላለህ አሉት።

ጌታችንም አብርሃም ሳይወለድ እኔ የነበርሁ መሆኔን አረጋግጥላችኋለሁ አላቸው (ዮሐ:8፥58)።

ስለዚህ አይሁድ ሊወግሩት ድንጋይ አነሡ፤ እርሱ ግን ተሰወረባቸውና ከቤተ መቅደስ ወጥቶ ሄደ።

<u>የአይሁድ አለማመን፡</u>- ምንም እንኳ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአይሁድ ፊት ብዙ ተአምራት ቢያደርግ እነርሱ ግን በእርሱ አላመኑም። ይህም የሆነው ነቢዩ ኢሳይያስ:- «ጌታ ሆይ ምስክርነታችንን ማን አመነ? የእግዚአብሔርስ ክንድ ለማን ተገለጠ?» ያለው ይፈጸም ዘንድ ነው። ስለዚህ ማመን አልቻ ሉም። ያልቻሉበትንም ምክንያት ነቢዩ ኢሳይያስ:- «በዐይናቸው አይተውና በልባቸው አስተውለው እንዳይመለሱና እንዳይፈውሳቸው እግዚአብሔር ዐይናቸውን አሳውሮአቸዋል፤ ልባቸውንም አደንድኖአል» በማለት ገልጾ ታል።

www.ethiopianorthodox.org

ነቢዩ ኢሳይያስ ይህን ያለው የመሲሕን ክብር ስላየ ነው፤ ስለዚህ ይህ
የተናገረው ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

ከምኵራብ እንዳያስወጡአቸው ፈሪሳውያንን በመፍራት በግልጥ አል
ሰከሩም እንጂ ከአይሁድ አለቆች እንኳ ብዙዎቹ በጌታችን አምነዋል። በዚህም
አድራጎታቸው ከሰው የሚገኘውን ክብር ከእግዚአብሔር ከሚገኘው ክብ
የበለጠ ግምት የሰጡት መሆናቸውን ያሳያሉ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ:- «በእኔ የሚያምን ሁሉ በጨለማ እንዳይኖ
እኔ ብርሃን ሆኜ ወደ ዓለም መጥቼአለሁ። ቃሌን ሰምቶ በሥራ ላይ የማ
ውለውን የምፈርድበት እኔ አይደለሁም። እኔ የመጣሁት ዓለምን ለማዳን ነው
እንጂ በዓለም ላይ ለመፍረድ አይደለም። እኔን የማይፈልግና ቃሌን የማ
ቀበለውን ሰው የሚፈርድበት አለ፤ እኔ የተናገርሁት ቃል በመጨረሻ ይፈ
ድበታል» ሲል ተናገረ።

## የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ተአምራት

የመቶ አለቃው አገልጋይ መፈወስ:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወ
ቅፍርናሆም ከተማ በገባ ጊዜ አንድ ሮማዊ የመቶ አለቃ ወደ እርሱ ቀር
አገልጋዩ ሽባ ሆኖ በመሠቃየት ላይ መሆኑን በመግለጥ እንዲፈውስለት ለ
ነው። ጌታችንም እኔ መጥቼ እፈውሰዋለሁ አለው። የመቶ አለቃው ግን ጌ
ሆይ አንተ ወደ እኔ ቤት እንድትገባ እኔ የበቃሁ ስላልሆንኩ አንዲት ቃ
ብቻ ብትናገር አገልጋዩ ይድናል፤ እኔ ራሴ እንኳ ለባለሥልጣኖች ተገ
ስሆን ከእኔ በታች የማዝዛቸው ወታደሮች አሉኝ። ከእነርሱ አንዱን ና ስለ
ይመጣል፤ ሂድ ስለውም ይሄዳል፤ አገልጋዬም ይህን አድርግ ስለው ያደርጋ
አለው።

ከዚህ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመቶ አለቃውን «ሂድ እን
እምነትህ ይሁንልህ አለው። አገልጋዩም በዚያኑ ጊዜ ተፈወሰ።





ጌታችን የመቶ አለቃውን አገልጋይ መፈወሱ (ሉቃ:7፡1–10)

የስምዖን ዐማትና የሌሎችም ሕመምተኞች መፈወስ:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከምኵራብ ተነሥቶ ወደ ስምዖን ጴጥሮስ ቤት ሄደ። እዚያም የስምዖን ዐማት በጣም አተኵሶአት ታማ ተኝታ ነበር። ስለዚህ ከሕመምዋ እንዲአድናት ጌታችንን ለመኑት። ጌታችንም ወደ እርስዋ ቀርቦ አጠገብዋ ቆመና ትኵሳቱ እንዲለቅቃት አዘዘ፤ ትኵሳቱም ለቀቃት። ወዲያው ተነሥታም ታስተናግዳቸው ጀምር። ወደ ምሽቱ ሰዎች በልዩ ልዩ ደዌ የተያዙባቸውን ሕመምተኞች ሁሉ ወደ ጌታችን አመጡ። እርሱም በያንዳንዳቸው ላይ እጁን በመጫን ፈወሳቸው። አጋንንትም አንተ የእግዚአበሔር ልጅ ነህ እያሉ በመጮኽ ብዙ ሰዎችን እየለቀቁ ይወጡ ነበር። ጌታችን ግን ስለ እርሱ እንዳይናገሩ በመገሠጽ ይከለክላቸው ነበር። (ሉቃ:ም:4ቍ:38–41)

በአጋንንት የተያዙ የሁለት ሰዎች መፈወስ:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የገሊላን ባሕር ተሻግሮ ወደ ጌርጌሴኖን አገር መጣ። በዚያም አጋንንት የያዛቸው ሁለት ሰዎች ከመቃብር ቦታ ወጥተው ተገናኙት፤ እነርሱ በጣም አደገኞች ስለነበሩ ማንም ሰው በዚያ መንገድ ማለፍ አይችልም ነበር። እነር



www.ethiopianorthodox.org

ሱም በድንገት እንዲህ እያሉ መጮኽ ጀመሩ:- «አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ሆይ፥ እኛ ከአንተ ጋር ምን አለን? ጊዜው ሳይደርስ ልታሠቃየን መጣህን?» ከእነርሱ ራቅ ባለ ስፍራ የብዙ ዐሣማዎች መንጋ ተሠማርቶ ነበር። አጋንንቱም የምታስወጣን ከሆነ ወደዚያ ዐሣማዎቹ መንጋ ስደደን ሲሉ ለመኑት። ጌታችንም ሂዱ አላቸው። ስለዚህም ከሰዎቹ ወጥተው ወደ ዐሣማዎቹ ሄዱና ገቡባቸው። ዐሣማዎቹም በሙሉ ከገደሉ አፋፍ ላይ እየተንደረደሩ ወርደው በባሕር ውስጥ ሰጠሙ። የዐሣማዎቹም እረኞች ሸሽተው ወደ ከተማ ገቡና ሁሉን ነገር አወሩ፤ አጋንንት በያዙአቸው ሰዎች የሆነውንም ነገር ተናገሩ። ከዚህ በኋላ የከተማው ሰዎች ሁሉ ጌታችንን ለማየት ወጡ፤ ባዩትም ጊዜ ከአገራቸው ወጥቶ እንዲሄድላቸው ለመኑት (ማቴ: 8፥28–34)።

## የጌታችን ምሳሌዎች

የተሸሸገ ሀብት ምሳሌ:- ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመንግሥተ ሰማይን ምሳሌነት ሲናገር እንዲህ ብሏል:- መንግሥተ ሰማይ በእርሻ ውስጥ የተሸሸገውን ሀብት ትመስላለች። አንድ ሰው ይህን ሀብት ባገኘው ጊዜ መልሶ ደበቀው። ከደስታውም ብዛት የተነሣ ሄደና ያለውን ሁሉ ሸጦ ያንን እርሻ ገዛ።

የዕንቍ ምሳሌ:- ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሌላ የመንግሥተ ሰማይን ምሳሌ ሲናገር እንዲህ ብሏል:- መንግሥተ ሰማይ ጥሩ ዕንቍ ለመግዛት የሚፈልግ ነጋዴን ትመስላለች። ነጋዴውም እጅግ ክቡር የሆነ ዕንቍ ባገኘ ጊዜ ሄዶ ያለውን ሁሉ ሸጠና ያን ዕንቍ ገዛ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ሕይወት እንጀራ:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚያስተምርበት ጊዜ ራሱን በሕይወት እንጀራ መስሎ ተናግሮ አል። ይህንኑም በሚከተለው ለአይሁድ ባደረገው ንግግሩ እንመልከት።

የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ። ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም። በእኔ የሚያምን ከቶ አይጠማም። እናንተ ግን አይታችሁኝ በእኔ አላመናችሁም። አብ የሚሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል። ወደ እኔ የሚመጣውንም ወደ ውጪ አላባርረውም። እኔ ከሰማይ የወረድሁት የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ እንጂ የራሴን ፈቃድ ለማድረግ አይደለም። የላከኝ የአብ ፈቃድ ከሰጠኝ አንድ እንኳ ሳላጠፋ በመጨረሻው ቀን እንዳስነሣ ነው። የአባቴ ፈቃድ ወልድን የሚያይና በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲያገኝ ነው። እኔም በመጨ



ረሻው ቀን አስነሣዋለሁ። ጌታችን ከሰማይ የወረደ እንጀራ እኔ ነኝ በማለቱ አይሁድ በእሱ ላይ አጕረመረሙና እንዲህ አሉ:- ይህ የዮሴፍ ልጅ ኢየሱስ አይደለምን? አባቱንና እናቱንስ እናውቃቸው የለምን? ታዲያ፥ አሁን እርሱ እንዴት ከሰማይ ወረድሁ ይላል? ጌታችንም እንዲህ ሲል መለሰላቸው:- እርስ በርሳችሁ አታጕረምርሙ፤ የላከኝ አብ የላከው ካልሆነ በቀር ወደ እኔ መምጣት የሚችል ማንም የለም። ወደ እኔ የሚመጣውንም በመጨረሻው ቀን ከሞት አስነሣዋለሁ።

እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ በእኔ የሚያምን ሰው የዘለዓለም ሕይወት አለው። እኔ የሕይወት እንጀራ ነኝ። አባቶቻችሁ በበረሓ መና በሉ፤ ነገር ግን ሞቱ፤ ከሰማይ የወረደው እንጀራ ይህ ነው፤ ይህን እንጀራ የሚበላ ከቶ አይሞትም። ከሰማይ የወረደው ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ። ከዚህ እንጀራ የሚበላ ሁሉ ለዘለዓለም ይኖራል። ለዓለም ሕይወት እንዲሆን እኔ የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው።

በዚህ ጊዜ አይሁድ ይህ ሰው ሥጋውን እንድንበላ እንዴት ሊሰጠን ይችላል? በማለት እርስ በርሳቸው ተከራከሩ።

በዚህ ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ አላቸው:- እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ፥ ደሙንም ካልጠጣችሁ ሕይወት የላችሁም። ሥጋዬን የሚበላና ደሜን የሚጠጣ ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት አለው፤ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ። ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነው። ሥጋዬን የሚበላና ደሜን የሚጠጣ ሁሉ በእኔ ይኖራል፤ እኔም በእርሱ እኖራለሁ። ሕያው አብ እንደላከኝና፥ እኔም በእርሱ ሕያው እንደሆንኩ እንዲሁም ሥጋዬን የሚበላ ሁሉ በእኔ ሕያው ይሆናል። እንግዲህ ከሰማይ የወረደው እንጀራ ይህ ነው፤ እርሱም አባቶቻችሁ እንደ በሉት ዐይነት አይደለም። ያን እንጀራ የበሉት ሞተዋል፤ ይህን እንጀራ የሚበሉ ግን ለዘለዓለም ይኖራሉ (ዮሐ:ም:6ቍ:35–58)።

## ከዚህ ምዕራፍ የምናገኘው ትምህርት

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከኒቆዲሞስ ጋር ባደረገው ንግግር የጥምቀትን አስፈላጊነትና ያለ ጥምቀት ወደ መንግሥተ ሰማይ ለመግባት እንደማይቻል ገልጦአል። በጥምቀትም የእግዚአብሔር ልጅነትና የኃጢአት ስርየት ይገኛል። ጥምቀትም ከሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያው ነው።

www.ethiopianorthodox.org

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘርና ወገን ሳይለይ በዓለም ላሉ ሕዝቦች ሁሉ ቤዛ ለመሆን የመጣ መሆኑን በተለያዩ ሁናቴዎች አመልክቶአል። ይህንንም ሁናቴ ግልጥ ያደረገው ሁሉንም በማስተማሩና ሁሉንም ከሥጋ ደዌ በመፈወሱ ነው። የዚህን አባባል እውነተኛነት ለመረዳት ከሰማርያይቱ ሴት ጋር ያደረገውን ንግግርና ከሰማርያ ሰዎች ጋር ያደረገውን የማስተማር ሥራ ይመለከቷል። ለስግደት ኢየሩሳሌም ወይስ የጌሪዚም ተራራ ነው የሚሻለው ብላ ለጠየቀችው ጥያቄ መልስ ሲሰጣት ቀድመው የተወሰኑት ቦታዎችና ወገኖች ብቻ ሳይሆኑ በእውነት የሚሰግዱ ሰዎች በእውነትና በመንፈስ የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል ብሎአታል። ይህም አባባሉ ቀደም ብሎ እግዚአብሔር በነቢዩ ኤርምያስ አማካይነት የተናገረውን ትንቢት ተፈጻሚነት ያመለክታል። ይህም ትንቢት እግዚአብሔር ቀደም ብሎ ከአባቶቻቸው ጋር የገባውን ዐይነት ቃል ኪዳን ሳይሆን አዲስ ቃል ኪዳን ከእስራኤላውያን ጋር የሚገባ መሆኑ ነው (ኤር:ም:31 ቍ:31–32)።

አምላክ ለሰው ልጆች የፈቃድና የፍላጎት ነጻነት ቢሰጣቸውም ሰው ሁሉ እንዲድን እንጂ እንዲጠፉ ስለማይፈልግ የድኅነትን መንገድ ያስተምራቸዋል። በዚህም መሠረት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአይሁድ አድማጮቹ የእርሱን አዳኝነት ገልጦላቸዋል። ያለእርሱም አዳኝነት ድኅነት እንደማይገኝ ገልጦላቸዋል። ይህም ብቻ ሳይሆን የእርሱንም ማንነት ሊገባቸው በሚችል ቋንቋ ነግሮአቸዋል። እርሱ ከአብርሃም በፊት የነበረ ዘለዓለማዊ አምላክ እንጂ እነርሱ እንደሚያስቡት ኀምሳ ዓመት ያልሞላው ተራ ሰው አለመሆኑን ገልጦላቸዋል። እነርሱ ግን በእግዚአብሔር ላይ ጽርፈት ተናገረ ብለው ሊወግሩት ከመነሣታቸው በቀር የነገሩን ሁናቴ እንኳ ለመመርመር አልሞከሩም። ስለዚህም ነው እኔ መጥቼ ባልነግራቸው ኖሮ ኃጢአት ባልሆነባቸውም ነበር ያለው (ዮሐ:ም:15ቍ:22)።

ይህም ገለጻው መለኮታዊ ክብሩን ለማያምኑና ለሚጠራጠሩ ሰዎች ሁሉ ትምህርት ሊሆናቸው በተገባ ነበር።

ሊወግሩት ድንጋይ ሲያነሡ ተሰውሮባቸው ከመካከላቸው ወጥቶ መሄዱ ደግሞ እርሱ ፈቅዶና ጊዜ ወስኖለት ካልሆነ በቀር ማንኛውም ሰው በእርሱ ላይ ምንም ለማድረግ የማይችል መሆኑን ያመለክታል።

ከተአምራቱ መካከል የሮማዊውን መቶ አለቃ አሽከር መፈወሱ ያለምንም ዘር መለየት ለሁሉ እኩል መሆኑን ያመለክታል።



እንዲሁም አጋንንት ያደሩባቸውን ሁለት ሰዎች በፈወሰበት ተአምሩ አጋንንቱ ከሰዎቹ ወጥተው ወደ ዐሣማ መንጋዎች እንዲገቡ መፍቀዱ የአጋንንቱን ልመና ለመቀበል ብሎ አይደለም። እንደሚታወቀው ዐሣማን ዐርዶ መብላት በእስራኤል ሕዝብ ዘንድ የተከለከለ ነበር። ይህንኑም እግዚአብሔር በሙሴ አማካይነት በኦሪት ዘሌዋውያን ም:11ቍ.7 ላይ የከለከለው መሆኑን ይመለከቷል። በዚህ ዐይነት በማርባት የዐሣማዎቹ ባለቤቶች ራሳቸው ዐርደው እንዳይበሉና ለሌሎችም በማብላት እንዳያሳስቱ አጋንንቱ ዐሣማዎቹን እንዲያጠፉአቸው ጌታችን ፈቅዶላቸዋል። ይህም ድርጊት ለዐሣማዎቹ ባለቤቶች ደኅንነት ሲባል እንጂ ለጥፋት አልነበረም።

የተሸሸገ ሀብትና የዕንቍ ምሳሌዎች ሁለት ትርጓሜዎች አሉአቸው።

የመጀመሪያው ትርጓሜ የተሸሸገውን ሀብት ወይም የከበረውን ዕንቍ አገኘ የተባለው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱም ኃጢአተኞችን ለመዋጀት ሕማማትን ተቀበለ። በሕማማትና በሞቱም ከዘለዓለማዊ ሞትና ከኃጢአት ባርነት ዋጀን። ለመንግሥተ ሰማያትም ዐደለን።

ሁለተኛው ትርጓሜ ደግሞ መንግሥተ ሰማያት ምን ያኽል የሚያጓጓ ትልቅ ሀብት መሆኑን የሚያመለክት ነው። በዚህም የመንግሥተ ሰማያትን ጥቅም ያወቀ ኃጢአተኛ ምን ያኽል ዓለማዊ ጥቅሙን ሁሉ ሠውቶ ያቺን ሰማያዊ ሀብት ለማግኘት የሚሠራ መሆኑን የሚያመልክት ነው። ይህም የሚሆነው መንግሥተ ሰማይ ከማንኛውም ዓለማዊ ሀብት የሚበልጥ በመሆኑ ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ብሎ በእርሱ ያመነ የዘለዓለም ሕይወት እንደሚኖረው ገለጠላቸው። በእኔ የሚያምን የዘለዓለም ሕይወት አለው እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ ማለቱ ስለሙታን ትንሣኤ መናገሩ ነው። ይህም ማለት ከሙታን ትንሣኤ በኋላ ማለትም ከፍርድ ቀን በኋላ የዘለዓለም ሕይወትን እሰጠዋለሁ ማለቱ ነው።እርሱም ለእስራኤል ልጆች ከሰማይ ከወረደው መና ጋር ራሱን አነጻጸረ። መናውን የበሉት ሞተዋል። የእርሱን ሥጋ የሚበሉት ግን በመንግሥተ ሰማይ ዘለዓለማዊ ሕይወትን ያገኛሉ።

ሥጋዬን የሚበላና ደሜን የሚጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው ሲል ስለምሥጢረ ቍርባን መናገሩ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ በመጀመሪያ



www.ethiopianorthodox.org

መልእክቱ ምዕራፍ 1 ቍጥር 7 ላይ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአታችን ሁሉ ያነጻናል ብሎአል። ከኃጢአታችን ከነጻን ደግሞ ለሰማያዊ ርስት እንበቃለን ማለት ነው፤ እርሱም ዘለዓለማዊ ሕይወት ማለት ነው።

## ጥያቄዎች

1. ጌታችንን ማነጋገር ለኒቆዲሞስ ቀላል ያልነበረው በምን ምክንያት ነው?
2. ኒቆዲሞስ ምን ዐይነት ሰው ነበር?
3. ኒቆዲሞስ ጌታችንን ሲገናኝ ምን አለው?
4. ጌታችንስ ምን መልስ ሰጠው?
5. ከጌታችን መልስ በኋላ ኒቆዲሞስ ምን አለ?
6. ጌታችንስ እንደገና የሰጠው መልስ ምን ብሎ ነው?
7. ጌታችን የሰጠውን መልስ ኒቆዲሞስ መረዳት ባቃተው ጊዜ ጌታችን ምን ዐይነት የመገረም ጥያቄ ጠየቀ?
8. ጌታችን የሚሰቀለው በምን ምክንያት ነው አለ?
9. ክፉ የሚያደርግ ሰው ለምን ብርሃንን ይጠላል?
10. ጌታችን የሰማርያይቱን ሴት ያነጋገረበት ቦታ ምን ይባላል?
11. ጌታችን ምን ስላላት ነው የሰማርያይቱ ሴት የተገረመችው?
12. የሰማርያይቱ ሴት ጌታችንን አንተ ነቢይ መሆንህን አያለሁ ያለችው ምን ስላላት ነው?
13. ከዚያ በኋላ ሴትየዋ ለሀገርዋ ሕዝብ ምን ብላ ተናገረች?
14. ሴትየዋ ስለ ኢየሩሳሌምና ስለጌሪዚም ተራራ ምን ብላ ጠየቀች?
15. የዚያ አገር ሰዎች ጌታችንን ምን ብለው ለመኑት?
16. አይሁድ ጌታችንን ጋኔን አለብህ ባሉት ጊዜ ምን መልስ ሰጣቸው?
17. ቃሌን የሚጠብቅ ከቶ አይሞትም ቢላቸው ምን አሉት?
18. አብርሃም የእኔን ቀን አይቶ ተደሰተ ባላቸው ጊዜ አይሁድ ምን አሉ?
19. አይሁድ ጌታችንን ሊወግሩት ድንጋይ ያነሡት ምን ስላላቸው ነው?



20. አይሁድ ሊወግሩት ድንጋይ ሲያነሡ ጌታችን ምን አደረገ?
21. ነቢዩ ኢሳይያስ ጌታ ሆይ ምስክርነታችንን ማን አመነ? የግዚአብሔርስ ክንድ ለማን ተገለጠ? ብሎ የተናገረው ትንቢት ምንን ያመለክታል?
22. አይሁድ በጌታችን አለማመናቸውን በተመለከተው በነቢዩ ምን ተብሎ ተነግሮ ነበር?
23. ነቢዩ ኢሳይያስ እነዚህን ትንቢቶች የተናገረው ምንን አይቶ ነው?
24. በጌታችን አምነው በግልጥ ያልመሰከሩ እነማን ናቸው?
25. ያልመሰከሩትስ ለምንድነው?
26. በዚህስ አድራጎታቸው ምንን ያሳያሉ?
27. የጌታችንን ቃል ሰምቶ በሥራ ላይ የማያውለውን ሰው የሚፈርድበት ማነው?
28. ጌታችን በዓለም ላይ የማይፈርደው ለምንድነው?
29. ሮማዊው የመቶ አለቃ ከጌታችን ምንን ለመነ?
30. የመቶ አለቃው ጌታችን ወደቤቱ እንዲገባ ለምን አልፈለገም?
31. ወደቤቱ እንዲገባ ሳይፈልግስ ምን ዐይነት አማራጭ ሰጠ?
32. ጌታችን ለመቶ አለቃው ምን አደረገለት?
33. ጌታችን በስምዖን ጴጥሮስ ቤት ምን አደረገ?
34. አጋንንት በጌታችን ፊት የሚጮኹት ምን ብለው ነበር?
35. ጌታችንስ ምን ብሎ ይገሥጻቸው ነበር?
36. በጌርጌሴኖን ጌታችንን የተገናኙት በሽተኞች ምን ብለው ጮኹ
37. ምን እንዲፈቅድላቸው ለመኑት?
38. እርሱስ ፈቀደላቸውን?
39. የዐሣማ መንጋዎች ምን ሆኑ?
40. የዐሣማዎቹስ እረኞች ምን አደረጉ?
41. የከተማው ሰዎች ጌታችንን ምን ለመኑት?
42. ስለተሸሸገው ሀብት ምሳሌ ተናገር?
43. ስለ ዕንቍ ምሳሌ ተናገር።

www.ethiopianorthodox.org

44. ይህ የዮሴፍ ልጅ አይደለምን? ብለው አይሁድ በጌታችን ላይ ያጉረመረሙት ምን ስላላቸው ነው?

45. ጌታችን የዘለዓለም ሕይወት አለው ያለው ማንን ነው?

46. ጌታችን ለዓለም ሕይወት እንዲሆን የሚሰጠው እንጀራ ምንድነው?

47. አይሁድ እርስ በርሳቸው የተከራከሩት በምን ምክንያት ነው?

48. በጌታችን ኢየሱስ ለመኖር ምን ማድረግ ያስፈልጋል?

49. ጌታችን ኢየሱስ ሥጋውን ከመና ጋር ያነጻጸረው እንደምን አድርጎ ነው?

50. በትንቢተ ኤርምያስ ምዕራፍ 31 ቁ: 31–32 ላይ የተነገረው ትንቢት ምን የሚል ነው?

51. ጌታችን ለአጋንንቱ ወደ ዐማግያቱ እንዲገቡ ለምን ፈቀደላቸው?

52. የተሸሸገው ሀብትና የዕንቍ ምሳሌዎችን ሁለት ትርጓሜዎች ግለጥ።

53. ሥጋዬን የበላና ደሜን የጠጣ በሚልበት ጊዜ ስለምን ጉዳይ መናገሩ ነው?

# ምዕራፍ 4

## ቤተ ክርስቲያን

### ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን

በአንደኛው ክፍል መጽሐፍ ምዕራፍ 4 ላይ እንደተገለጠው ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል አራት ትርጉሞች አሉት። ከእነዚህም ከአራቱ የቤተ ክርስቲያን ትርጉሞች አንዱ ቤተ ክርስቲያን ማለት ሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑ ነው የሚለው ነው።

በዚህም መሠረት ክርስቲያኑ ሕዝብ ተሰብስቦ የኅብረት ጸሎት እንዲያካሄድበት የተሠራው ቤት ማለት የታነጸው ሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ወይም ቤተ እግዚአብሔር ይባላል። ከክርስትና በፊት የነበረው ቤተ መቅደስ ይባል ነበር። የአይሁድ ጸሎት ቤት ቤተ መቅደስ ሲባል የክርስቲያኑ ግን ቤተ ክርስቲያን ይባላል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ ሻጮችንና ገርዎችን ባስወጣበት ጊዜ ቤቴ የጸሎት ቤት ይባላል፤ እናንተ ግን የሌቦች ዋሻ አደረጋችሁት በማለት የእግዚአብሔር ቤትነቱንና የጸሎት ቤትነቱን ገልጾአል (ማቴ:ም:21ቁ:13)።



ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ለጢሞቴዎስ በጻፈው የመጀመሪያ መልእክቱ ም:3ቁ:15 ላይ «ብዘገይ ግን በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት መኖር እንዴት እንደሚገባ ታውቅ ዘንድ እጽፍልሃለሁ፤ ቤቱም የእውነት ዐምድና መሠረት የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ነው» ብሎታል።

<u>የሕንጻው አሠራር</u>:- የክርስቶስ ቤተሰብ የሆኑ ምእመናን ተሰባስበው እንዲጸልዩበት የሚሠራው ወይም የሚታነጸው ቤት ማለት ቤተ ክርስቲያን እንዴት መሠራት እንዳለበት በመጽሐፈ ዲድስቅልያ አንቀጽ ዐሥርና ሠላሳ አምስት ውስጥ ተዘርዝሮ ይገኛል። ቅርጹ እንደ ትልቅ መርከብ ሆኖ ሦስት በሮች ይኖሩበታል። የበሮቹም አቀማመጥ በደቡብ፣ በምዕራብና በሰሜን በኩል ይሆናል።

የበሮቹ ሦስት መሆን ለሥላሴ ሦስትነት ምሳሌ ነው።

ይህንንም በኢትዮጵያ ኦ.ተ.ቤ.ክ.መቅደስ አሠራር ይመለከቷል።

የቤተ ክርስቲያኑ አቀማመጥ በርዝመቱ ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ ይሆናል። ከወደ ምሥራቅና ከወደሰሜን በኩል እንደበረንዳ መሳይ ይኖረዋል። በዚህ ዐይነት ቅርጹ መርከብን ይመስላል። ያገልግሎቱ ቤት ከደቡብ በር በስተቀኝ በኩል ይሁን። ይህም የሚሆነው ምእመናኑ የሚመጣላቸውን ቍርባን እንዳያዩ ነው። በስተምዕራብ በኩል የሚጋርዱ ሁለት ዐምዶች ይኑሩ። የዐምዶቹም ቁመት በነቢያት ጉባኤና እንዲሁም በኻያ አራቱ ካህናት ምሳሌነት ኻያ አራት ክንድ ይሁን። ስፋቱ ደግሞ ወንጌልን ባበሠሩ ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ምሳሌነት ዐሥራ ሁለት ክንድ ይሁን። የመጠመቂያው ቦታ በሰሜን ምዕራብ በኩል ይሁን። እርሱም ከቤተ ክርስቲያኑ ጋር ያልተያያዘ መሆን አለበት። ከቤተ ክርስቲያኑ መካከል ከሌሎቹ ወንበሮች ሦስት ደረጃ ከፍ ያለ የሊቀ ካህናቱ መቀመጫ ይሁን። መሠዊያው ማለት መቅደሱ በመኻል ሆኖ የሚጋርደው መጋረጃ ይኑረው። ከመቅደሱ በስተምሥራቅ ከሊቀ ካህናቱ ወንበር ከፍ ያለ የኤጲስ ቆጶሱ ወንበር ይኑር። ቤተ ክርስቲያኑም በብርሃን የደመቀ ይሁን። በተለየ ቅዱሳት መጻሕፍት በሚነበቡበት ጊዜ በቂ ብርሃን ይብራ።



www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

## የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት

ቀደም ተብሎ እንደተገለጠው የቤተ ክርስቲያን አስተዳደራዊ መዋቅር የተዘረጋው በኤጲስ ቆጶሳት፥ በቀሳውስትና በዲያቆናት ነበር።

በዚህም መሠረት በመጽሐፈ ዲድስቅልያ አንቀጽ 10 ላይ:- ኤጲስ ቆጶሱ በመኻል ሲቀመጥ ቀሳውስቱ በዙሪያው ይቀመጡ። ዲያቆናቱ ግን ተዘጋ ጅተው ይቁሙ ተብሏል።

ቤተ ክርስቲያን በትልቅ መርከብ ትመሰላለች፤ በውስጥዋም ለጸሎት የተሰበሰቡ ምእመናን በመርከቡ ተሳፋሪዎች ይመሰላሉ፤ ዲያቆናቱ ደግሞ በመርከበኛው ወይም በመርከቡ ረዳት ይመሰላሉ። በመርከቡ ውስጥ ያሉት ተሳፋሪዎች በሰላም ወደሚሄዱበት ቦታ እንዲደርሱ የመርከቡ ረዳት ጥረት ያደርጋል። በዚሁም ዐይነት ዲያቆናቱ እያንዳንዱን ምእመን በተገቢው ቦታ በማስቀመጥ፡ ሰዎች እንዳያንቀላፉቸው፥ወይም እንዳይተኙ፥ ወይም እንዳ ይስቁ፥ ወይም በአጠገባቸው ካለ ሰው ጋር ማንኛውንም ዐይነት ወሬ እንዳያ ወሩ፥ ቃለ እግዚአብሔር በጥሞና እንዳይሰማ እንቅፋት እንዳይሆኑ ይጠ ብቃሉ። የሕዝበ ክርስቲያኑ ዓላማ ከግቡ ሊደርስ የሚችለው ሁሉም በበኩሉ አምልኮውን በሥርዓትና በመንፈሳዊነት ስሜት ሲያከናውን ነው እንጂ በአ ጠገብ ካለ ሰው ጋር ዓለማዊ ውይይት ሲያደርግ አይደለም። እንደዚያ ከሆነ ግን ወደ ቤተ ክርስቲያንም መሄድ አስፈላጊ ባልሆነም ነበር።

በመጽሐፈ ዲድስቅልያ መቅድም ላይ እንደተገለጠው ሀሥራ ሁለቱ ሐዋርያት፥ የእግዚአብሔር ምርጥ ዕቃ የተባለው የአሕዛብ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስና የኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ የነበረው የጌታችን ወንድም የተባለው ያዕቆብ በተሰበሰቡበት ጉባኤ ካሳለፉአቸው ውሳኔዎች መካከል እንዲህ የሚል ይገኝበታል።

ቤተ ክርስቲያን በሰማያዊ ሥርዓት መካሄድ ያለባት ስለሆነ ሁሉም አመስግኖ ጌታ በወሰነለት በየሥራ ደረጃው ይጸና ዘንድ የሚከተለውን ወስነናል። ይኸውም ኤጲስ ቆጶሱ እንደጠባቂ፥ ቀሳውስቱ እንደ አስተ ማሪዎች፥ ዲያቆናቱ እንደ አገልጋዮች፥ ንፍቅ ዲያቆናቱ እንደ ረዳቶች፥ አናጉስጢሳውያኑ እንደ አንባቢዎች፥ መዘምራኑ በመረዳት እንደዘማሪዎች፥ አገልጋዮቹ እንደ ጠባቂዎች ሆነው ሌላው ሕዝብ ደግሞ የወንጌልን ቃል በአክብሮትና በጸጥታ የሚያዳምጡ ናቸው።



አንድ ኤጲስ ቆጶስ የሚሾመው ቢያንስ በሦስት ኤጲስ ቆጶሳት ነው። ቀሳውስትና ዲያቆናት ግን በአንድ ኤጲስ ቆጶስ እጅ ይሾማሉ። ዲያቆናት ኤጴስ ቆጶሳትንና ቀሳውስትን ከማገልገል በቀር የኤጲስ ቆጶሱን ወይም የቄሱን ሥራ ሊሠሩ አልተፈቀደላቸውም።

## ንዋየ ቅድሳት

ንዋየ ቅድሳት ማለት የተቀደሱ የክርስቶስ ሥጋና ደም መያዣ፥ ማክበሪያ፥ የቤተ ክርስቲያን ጻሕል፥ ዐውድ፥ ጽዋዕ፥ ዕርፈ መስቀል፥ መሶበ ወርቅ፥ አልባሳትና ጽና(ጥና) ናቸው።

ጻሕል ለቅዱስ ቊርባን ማስቀመጫ እንዲሆን ከወርቅ፥ ወይም ከብር፥ ወይም ከመዳብ፥ ወይም ከነሐስ የተሠራ ዝርግ ሳሕን ነው። ካህኑም ሥርዓተ ቅዳሴውን ከመጀመሩ በፊት በጻሕሉ ላይ የሚከተለውን ጸሎት ይጸልያል።

ቸር ማሕየዊ አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ በዕፀ መስቀል ላይ ቅዱሳት የሚሆኑ እጆችህን የዘረጋህ፤ በጎ ነገርን በተመላች በዚች ጻሕል ላይ ክቡር እጅህን ዘርጋ። ቅዱስ ስምህን የሚወድዱ ሰዎች የሺህ ዘመን ምግብን በላይዋ የሚያዘጋጅባት ናት።

አሁንም አምላካችን እግዚአብሔር ፍሕምን የተመላች ይህችን ጻሕል ባርካት፤ አክብራት፤ አንጻት፤ ይኸውም የሐዋርያት በምትሆን በዚች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በሚገኝ ክቡር በሚሆን በመሠዊያው ላይ ያቀረብነው ያንተ ቅዱስ ሥጋ ነው። ቸር ሰማያዊ ከሚሆን አባትህ ጋር፥ ማሕየዊ ከሚሆን ከቅዱስ መንፈስህም ጋራ፥ ክብር ምስጋና ይገባሃልና፤ ዛሬ፥ ዘወትርም፥ ለዘለዓለሙ አሜን።

ጽዋዕ (ጥዋ) ከወርቅ፥ ወይም ከብር፥ ወይም ከሌላ ማዕድን በዋንጫ የተ ሠራ ባለ እግር የቊርባን ዕቃ ነው። ካህኑም የሚከተለውን ጸሎት ይጸል ይበታል።

አምላካችን እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ፥ አላትዮን፥ በእውነት ሰው የሆነ አምላካችን ነው፤ መለኮቱም በፍጥረቱ ላይ ደሙን በፈቃዱ ካፈሰሰ ከሰውነቱ አልተለየም። በዚህ ጽዋ ላይ ቅዱስ እጅህን አድርግ።

አሁንም ባርከው አክብረው እንዳጸናሃት ክቡር ደምህን ያደርግበት ዘንድ ይህ «እማሬ» አምኖ ከሱ ለሚጠጣ ሁሉ ለሕይወትና ለኃጢአት ማስተሥረያ



www.ethiopianorthodox.org

ይሆን ዘንድ ቸር ሰማያዊ ለሚሆን አባትህ ምስጋና ይግባው፤ ማሕየዊ ለሚሆን ለመንፈስ ቅዱስም፤ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ አሜን።

<u>ዕርፈ መስቀል</u> በመጨበጫው ጫፍ መስቀል ያለበት ማንኪያ፥ የሥጋ ወደሙ ማቀበያ ነው። በዕርፈ መስቀሉ ላይ ካህኑ የሚከተለውን ጸሎት ይጸልይበታል።

አምላካችን እግዚአብሔር፥ ባርያህን ነቢዩን ኢሳይያስን የበቃ ያደረግኸው ጕጠት በእጁ የተያዘ ሱራፌን ያየው ዘንድ በርሱም ፍሕም ወስዶ ባፉ ጨመረ ለት።

አሁንም ሁሉን የምትይዝ አምላካችን እግዚአብሔር አብ በዚህ ዕርፈ መስቀል ላይ እጅህን አድርግ። ያንድ ልጅህን የጌታችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ሥጋውን፥ ክቡር ደሙን እንዲሠሩበት።

አሁንም ባርከው፤ አክብረው፤ አንጻውም። ለዚህም ዕርፈ መስቀል ኃይልንና ክብርን ስጠው፤ ለሱራፌ ጕጠት (ኃይልን) እንደሰጠሃት፤ ምስጋና ኃይልንና ክብርን ስጠው፤ ለሱራፌ ጕጠት (ኃይልን) እንደሰጠሃት፤ ምስጋና ጽንዕ ላንተ ይገባልና፥ ካንድ ልጅህ ከጌታችንና ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር፤ ማሕየዊ ከሚሆን ከመንፈስ ቅዱስም ጋር፤ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ። አሜን።

<u>መሶበ ወርቅ</u>:- በወርቅ ክር የተሰፋ፥ የተለጠፈ ወርቅ ያለበት፥ የወርቅ መሶብ፥ ባለዐለላ፥ በቤተ መንግሥትና በቤተ ክርስቲያን የሚገኝ ነው። የካህኑ ጸሎት እንደሚከተለው ነው።

ምርጥ ዕቃን ለኔ ሥርተህ በደብተራ ኦሪት አኑረው ብሎ በደብረ ሲና ለባሪያው ለነቢዩ ለሙሴ የነገረው አምላካችን እግዚአብሔር።

አሁንም ሁሉን የምትይዝ አቤቱ አምላካችን በዚች መሶበ ወርቅ ላይ ቅድስት የምትሆን ቀኝህን ዘርጋ። ከኃይልና ከጽንዕ ከመንፈስ ቅዱስ ሀብት ከክብርህም ምላት፤ የሐዋርያት ጉባኤ በምትሆን በከበረች በዚች ቤተ ክርስ ቲያን ያንድ ልጅህን ክቡር ሥጋውን ይሠሩባት ዘንድ። ካንድ ልጅህ ጋራ ከመ ንፈስ ቅዱስም ጋር ምስጋና ይገባሃልና ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ። አሜን።

ከዚህም በኋላ ታቦቱን በማልበስ ይጀምር። መንበሩንና ጽዋውን በንጹሕ ልብስ ያልብስ።፡



<u>ማኅፈድ</u>:- በማኅፈድ ላይ የካህኑ ጸሎት እንደሚከተለው ነው።

ጌታችን አምላካችንና መድኃኒታችን እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ይቅ ርታንና ቸርነትን የተመላ መዝገብ ያለው ለሚያምኑበትም ሁሉ በጎ ነገርን የሚሰጥ በጥበቡ ሰማያትን የዘረጋ፥ ለምጽንዓትና ለደመናት የተለወጠ ሥር ዓትን የሰጠ፥ የሰማያትም መልካቸው አልተለወጠም። አሁንም ሰውን የምት ወድድ አምላካችን ክቡር ሥጋህን በሚሸፍኑ በነዚህ ልብሶች ላይ እጅህና የመለኮ ትህ ኃይል ትውረድ። በመቃብር ውስጥ ያለ ቅዱስ ሥጋህ በተገነዘባቸው አልባስ ላይ ኃይልህን ያሳደርህ እኒህም በሰማይ ባሉት አምሳል ይሁኑ። ክብር ምስጋና ከሃሊነት ጽንዕ ይገባሃልና ከቸር አባትህ ከአብ፥ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለሙ አሚን።

<u>አልባሳት</u>:- ልብሰ ተክህኖ ማለት ለጸሎትና ለቅዳሴ ካህናት በቤተ መቅደስ የሚለብሱት ነው።

<u>ጥና (ጽና)</u> ማለት የዕጣን ማጠኛ ነው።

## የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን ጸሎቶች

ቤተ ክርስቲያን ልዩ ልዩ ልብን የሚሰብሩ ጸሎቶች አልዋት። ከነዚህም መካከል የሚቀጥሉት ከማታ ጸሎት የተወሰዱ ናቸው።

<u>በግዕዝ</u>

<u>ጸሎተ ምህላ</u>– (ይኸውም የያሬድ ጸሎት)።

መሐረነ፥ አብ፤ ሃሌ ሉያ፤ ተሣሃለነ ወልድ፤ ሃሌ ሉያ፤ መንፈስ ቅዱስ መሐሪ ተዘከረነ በሣህልከ። (3ጊዜ በል።)

ለከ ንፌኑ ስብሐተ ወለከ ናዐርግ አኰቴተ። – መሐረነ መሐሪ ኃጢአተነ አስተሥሪ፤ ወአድኅነነ ወተማኅፀን ነፍሰነ ወሥጋነ፤ ክርስቶስ ወልደ እግዚአ ብሔር አምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ተሣሃለነ: – በብዝኃ ምሕረትከ ደምስስ አባሳነ ወፈኑ ሣህለከ ላዕሌነ:- አስመ እምኀቤከ - ውእቱ ሣህል፥ ሃሌ ሉያ መሐረነ አብ መሐሪ። – ወተሣሃለነ ሀብ ሣህለከ መሐሪ ኢታጥፍአነ፥ ተዘኪረከ ዘትካት።– በምሕረትከ አስመ መሐሪ አንተ ወበዙኀ ሣህልከ ለዙሎሙ እለ ይጼውዑከ። –ይጼውዑከ በጽድቅ ሰማዒ ወትረ ከሃሊ ዘውስተ



www.ethiopianorthodox.org

አድኅኖ።— ከሃሊ ዘውስተ አድኅኖ ለአምላክነ አስመ ጽድቅ ቃሉ። — ንስአሎ ለአብ ይፈኑ ለነ ሣህሎ እስመ አብ የአክል ለዘሰአሎ።— ሃሌ ሉያ ስብሐት ሎቱ ይደሉ። ሃሌ ሉያ አኰቴት ሎቱ ይደሉ። ሃሌ ሉያ ለክርስቶስ ለእግዚአ ኵሉ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሃሌ ሉያ። — ወይእዜኒ መኑ ተስፋየ አኮኑ እግዚአብሔር ውስተ እዴከ እግዚኦ አመኅፅን ነፍስየ።— ኀበ አምላክ ምሕረት አመኅፅን ነፍስየ።— ኀበ ንጉሠ ስብሐት አመኅፅን ነፍስየ በእግዚእየ ወአምላኪየ አመኅፅን ነፍስየ፤ እምኵሉ ምግባረ እኩይ አድኅና ለነፍስየ።— ሀቡ ንስአሎ ንስአሎ ናስተምሕሮ ለአምላክነ ጻድቅ እስመ ጽድቅ ያቃሉ።—

ዘይክል ኵሎ ወአልቦ ዘይሰአኖ አምላክ ነዳያን ወተስፋ ትቡፃን ንሕነ ኀቤከ ተማኅፀነ። (3ጊዜ በል።)

ወበከመ ዐቀብከነ፥ እምንግህ እስከ ሠርክ ዕቀበነ እግዚኦ እምሠርክ እስከ ነግህ፥ (3ጊዜ በል።)

ትእ ከኪዳን በኋላ ሕዝቡ እንደቆሙ የምህላውን ጸሎት በግራና በቀኝ ይበሉት። (ያስተዛዝሉ)

<u>የምህላ ጸሎት</u>

<u>በአማርኛ</u>

አብ ሆይ ማረን ሃሌ ሉያ፤ ወልድ ሆይ ይቅር በለን ሃሌ ሉያ፤ ይቅር ባይ መንፈስ ቅዱስ ሆይ በይቅርታህ አስበን። ( 3ጊዜ በል።)

ለአንተ ፍጹም ምስጋን እናቀርባለን።— ቸር ይቅር ባይ ሆይ ማረን፤ ኃጢአታችንንም አስተሥርይልን፤ — የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ አድነን፤ በነፍስ በሥጋም ጠብቀን።— አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ይቅር በለን። — በቸርነትህ ብዛት በደላችንን ደምስስ፤ ይቅር ታህንም ላክልን።— ይቅርታ ካንተ ዘንድ ነውና፤ ሃሌ ሉያ ይቅር ባይ አብ ሆይ ማረን።— ይቅር በለን።— መሐሪ የሆንህ አቤቱ ይቅርታህን ስጠን፤ የቀድሞ ኃጢአታችንንም አስበህ አታጥፋን።— በቸርነትህ አንተ ይቅር ባይ ነህ፤ ለሚጠሩህ ለሚለምኑህ ሁሉ ይቅርታህ ብዙ ነው።— በእውነት ይጠሩሃል፤ አንተም ዘወትር ትሰማለህ፤ ሁሉን ለማድረግ የምትችል ነህ።— ሁሉን ለማድረግ የሚችል የአምላካችን ቃሉ እውነት ነውና።— ይቅርታውን ይልከልን ዘንድ አብን እንለምነው፤ አብ ለለመነው ሁሉ ይበቃልና።— ሃሌ ሉያ፥ ለርሱ



ምስጋና ይገባል፤ ሃሌ ሉያ ለርሱ ክብር ምስጋና ይገባል። — ሃሌ ሉያ ለሁሉ ጌታ ለክርስቶስ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሃሌ ሉያ።— ዛሬስ ተስፋዬ ማነው እግዚአብሔር አይደለምን?፤ አቤቱ ነፍሴን ለአንተ ዐደራ አስጠብቃለሁ። — ከምሕረት አምላክ ዘንድ ነፍሴን ዐደራ አስጠብቃለሁ፤ ከምስጋና አምላክ ዘንድ ነፍሴን ዐደራ አስጠብቃለሁ።— በጌታዬና በአምላኬ ነፍሴን ዐደራ አስጠብቃለሁ፤ ከክፉ ሥራ ሁሉ ነፍሴን (ሰውነቴን) አድናት። — ኑ እንለ ምነው፤ እንለምነው እንማልደው፤ የአምላካችን ቃሉ እውነት ነውና።

ሁሉን የሚችል የሚሳነውም የሌለ እርሱ ነው፤ የድኾች አምላክ ተስፋ ላጡ ተስፋቸው የምትሆን አቤቱ እኛ ወዳንተ ተማጥነናል። (3 ጊዜ በል።)

ከጧት እስከ ማታ እንደ ጠበቅኸን አቤቱ እንዲሁ ከማታ እስከ ጧት ጠብቀን። — (3ጊዜ በል)

<u>ጸሎት ዘእምያሬድ።</u>

<u>በግዕዝ</u>

አድኅነነ ሕዝበከ ወባርከነ ርስተከ፥ ሀበነ ኀይለ ወመዊዐ ለአግበርቲከ፥ ለእለ ንጼውዕ ስመከ፤ ዕቀበነ ውሉደ ሕዝብከ፤ ወሕፅረነ በኃይለ መላእክቲከ ወትረ በኵሉ ጊዜ ወበኵሉ ሰዓት። በኀይለ መስቀልከ፥ ርድአነ በዕፀ መስቀ ልከ ቤዝወነ።

በአንተ አብርሃም ፍቁርከ፤ ወበእንተ ይስሐቅ ቍልዔከ ወበእንተ እስ ራኤል ቅዱስከ ተዘከር እግዚኦ ኪዳነከ። ፍጡነ ፈኑ ሣህለከ መሐር ኪያነ ዘፈጠርከ። ሥረይ ኃጢአተ ሕዝብከ ወመሐር ተግባረከ እግዚኦ ታጥፍአነ ሐሰ ለከ።

በእንተ ማርያም ወላዲትከ ወበእንተ ዮሐንስ መጥምቅከ። ወበአንተ ኵሎሙ ቅዱሳኒከ ርድአነ ወትረ በኀይለ መስቀልከ ኢታስተኃፍረነ እግዚኦ በቅድሜከ።

እግዝእትነ ነጽሪ ኀቤነ ጸልዪ ለነ ለደቂቅኪ. ወአድኅንነ እምኵሉ ምንዳቤ ወሐዘን።

መዐልተ ምስሌነ ወሌሊተ ማዕከሌነ አንተ እግዚኦ ኢትርኃቅ አምኔነ ሀሉ ምስሌነ ረዳኤ ኵነነ ኢትግድፈነ ወኢትመንነነ አምላከ ሰላም ተራድአነ።



www.ethiopianorthodox.org

ኢትግድፈነ ኢትግድፈነ ወኢትመንነነ አምላክ ሰላም ተራድአነ። (3ጊዜ በል።)

እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ።

እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ።

እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ።

ትእ. ከዚህም በኋላ የሚከተለውን የያሬድን መስጋና በአንድነት ባንድ ድምፅ ይበሉት።

ከያሬድ የዜማ መጽሐፍ የተቀዳ ጸሎት። (በዋዜማ ምዕራፍ ተመልከት።)

እኛን ወገኖችህን አድነን፤ የጥንት ተገዥዎችህንም ባርከን፤ ስምህን ለመንጠራ ለኛ ለአገልጋዮችህ ድል መንሣትንና ኃይልን ስጠን፤ የወገኖችህን ልጆች በየጊዜውና በየሰዓቱ በመላእክት ታዳጊነት በውስጥ በአፍአ ጠብቀን። በመስቀልህ ታዳጊነት ርዳን። በመስቀልህ ተቤዠን። ስለ ባለሟልህ ስለ አብርሃም፥ ስለ ወዳጅህ ስለ ይስሐቅ፥ ስለ መረጥከው ስለ እስራኤልም ብለህ አቤቱ ቃል ኪዳንህን አስብ። ይቅርታህን ፈጥነህ ላክ፤ የፈጠርኸን እኛን ማረን። አቤቱ አታጥፋን፥ ይህ በአንተ ዘንድ አይደረግ።

በእናትህ በማርያም አማላጅነት፥ በአጥማቂህ በዮሐንስና በቅዱሳንህም ሁሉ አማላጅነት ሁል ጊዜ በመስቀልህ ታዳጊነት ርዳን አቤቱ በፊትህ አታሳፍረን።

እመቤታችን ሆይ ወደኛ ተመልከቺ፤ ለኛ ለልጆችሽ ለምኚልን፤ ከችግርና ከሐዘን ሁሉ አድኚን።

ቀን ከኛ ጋር ሌትም በመካከላችን ሁን። አቤቱ አንተ ከኛ አትለይ። ከኛ ጋራ ኑር፤ ረዳትም ሁነን፤ አትተወን፤ አትናቀንም፤ የሰላም አምላክ ሆይ ተራዳን፥ (3ጊዜ በል።)

እመቤታችን ሆይ እመቤታችን ሆይ ወደኛ ተመልከቺ፤ የልጅሽም ሰላም በኛ ላይ አድሮ ይኑር። (3ጊዜ በል።)

አቤቱ ክርስቶስ ማረን።

አቤቱ ክርስቶስ ማረን።

አቤቱ ክርስቶስ ማረን።

## የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን

ሐዋርያው ቅዱስ በርተሎሜዎስ፡- መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ ከወረደ በኋላ የሐዋርያው ቅዱስ በርተሎሜዎስ ዕጣ በትንቢዋ እስያ አልዋሐት የምትባለዋ ክፍል ነበረች። እዚያም በትምህርቱና በተአምራቱ አስደነቃቸው።

ወደዚያች ከተማም የገባው ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ እንደባሪያ ሸጦት ነበር።

በአንዱ ባለጸጋ የአትክልት ቦታ ውስጥ ይሠራ በነበረ ጊዜ የወይን ግንዶቹን ቅርንጫፎች ባስተካከለ ቍጥር ወዲያው ያፈሩ ነበር። ከዚያ አገር ሰዎች የአንዱ የሽማግሌ ልጅ ሞተና ሐዋርያው በርተሎሜዎስ ከሞት ለሰነሣው። በዚያን ጊዜ ሁሉም አመኑ። አስተምሮም በአምላካችን እንዲጸኑ አደረጋቸው።

ከዚያም በኋላ ጌታ ወደ በርበር አገር እንዲሄድ አዘዘው። ደቀ መዝሙሩም እንዲረዳው ከእርሱ ጋር አብሮት ሄደ። የዚያች የሄደባት ከተማ ሰዎች ክፉዎች ነበሩ። አስደናቂ ተአምራቱን ቢያዩም እንኳ የማይቀበሉአቸው ሆኑ። እነርሱ ግን ተስፋ ሳይቈርጡ ተግተው በማስተማራቸው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያምኑ አድርገዋቸዋል። ከዚያ ካህናትን ሾመላቸውና ቤተ ክርስቲያን ከሠራላቸው በኋላ ወደ ሌላ አገር ሄደ። የሄደውም በባሕር ጠረፍ ወደሚኖሩትና እግዚአብሔርን ወደማያውቁት ወገኖች ነው። እነርሱንም አስተምሮ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያምኑ አደረጋቸው። ለክርስትና ተገዢ የሆነውን ተግባር አስተማራቸው፤ ከኃጢአትም እንዲነጹ አዘዛቸው።

ይህን ድርጊት ንጉሥ አግሪጳ ሰምቶ ተቈጣ። ሐዋርያውንም በጠጕራማ ጆንያ ውስጥ ከትተው በዚያም አሸዋ ሞልተውበት ወደ ባሕር እንዲጥሉት አዘዘ።

የንጉሡም ትእዛዝ ተግባራዊ ስለተደረገበት በዚሁ ትግሉን ፈጸመ። (የመስከረም 1ቀን ስንክሳር)



www.ethiopianorthodox.org

<u>ሐዋርያው ቅዱስ ፊልጶስ:</u>- መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ ከወረደ በኋላ ለሐዋርያው ፊልጶስ የማስተማር ዕጣ የወጣለት አፍሪቃ ውስጥ ነበር። እዚያም ሄዶ በክርስቶስ ስም ሰበከ፤ ሕዝቡንም በእግዚአብሔር እንዲያምኑ አደረ ጋቸው። በተአምራቱም በጣም አስደነቃቸው። በእምነታቸውም ካጸናቸው በኋላ ወደ ኢራጶሊስ ሄደ። እዚያም እንደዚሁ ሕዘቡን አሳምኖ ወደ ክርስቶስ አመጣቸው። አላማንያኑ ግን እንግዳ ሰው ወደዚያ አገር እንዳይገባ ተብሎ የተወሰነውን የንጉሡን ውሳኔ ተላልፎአል ብለው ምክንያት በመስጠት ሊገ ድሉት ተመካከሩ።

ይዘውም ባሰሩት ጊዜ ለምን ዘለዓለማዊ ሕይወትን ከእናንተ ታባርራላችሁ ብሎ በፊታቸው ፈገግ አለ። ለምን ነፍሳችሁን ለማዳን አታስቡም አላቸው።

እነርሱ ግን እርሱ ስለተናገረው ንግግር ግድ አልነበራቸውም። በእርሱም ላይ ተነሥተውበት በብዙ ካሠቃዩት በኃላ እግሩን ወደላይ ራሱን ወደታች አድርገው ሰቀሉት። በሚሰቅሉት ጊዜም ምድር ተንቀጠቀጠች። በዚህ ምክንያት ሁሉም ደነገጡና ሸሹ።

ምእመናን መጥተው ከተሰቀለበት ሊያወርዱት ቢፈልጉ እንዲተውትና ትግሉን እንዲፈጽም ነገራቸው።

በዚህ ዐይነት ነፍሱን ለክርስቶስ አስረከቦ የሰማዕትነቱን አክሊል ተቀዳጀ። ይህም የሆነው በ80 ዓ.ም ነው።

ከክርስቶስ ልደት በስድስተኛው መቶ ዓመት የሐዋርያው ፊልጶስ ዐፅም ወደ ሮም ተወሰዷል።

በቅዱስ ፊልጶስም አስከሬን አማካይነት እግዚአብሔር ብዙ አስደናቂ ተአምራትን አሳይቶአል።

(የኅዳር 18 ቀን ስንክሳር)

<u>ቅዱስኤጺፋንዮስ</u> :- ይህ ቅዱስ የተወለደው አይሁድ ከነበሩ ቤተሰብ ነው። አባቱ ከሞተ በኋላ እናቱ በመልካም አስተዳደግ አሳደገችው።

አባቱ አንዲት ልዩ ዐይነት ድብ ትቶለት ነበር። እናቱ ያችን ድብ እንዲሸጥ ነገረችው። እንስሳዋን የሚገዛ ፊላታዎስ የሚባል አንድ ክርስቲያን የሆነ ሰው ተገናኘው። እንስሳይቱ ግን ኤጺፋንዮስን ጭኑ ላይ ስለረገጠችው ተዝለፍልፎ



www.ethiopianorthodox.org

ወደቀ። ፊላታዎስ የኤጺፋንዮስን ጭን በመስቀለኛ ስለባረከው ከሕመሙ ዳነ። ከዚያም በኋላ እርሱ እንስሳይቱ እንድትሞት ጮኸባት። እግዚአብሔር ጸሎቱን ሰምቶት እንስሳይቱ ወዲያው ሞተች። ኤጺፋንዮስም የአማሙዋትዋን ምሥ ጢር በጠየቀው ጊዜ መስቀል መሆኑን ገለጠለት። ከዚያም ዓለምን ለማዳን ብሎ በገዛ ፈቃዱ በአይሁድ እጅ በኢየሩሳሌም ስለ ተሰቀለው ስለ እግዚአብ ሔር ልጅ ስለ ጌታችን ኢየሱስ አስተማረው። ይህም ጉዳይ በኤጺፋንዮስ ኅሊና ውስጥ ተቀረጸ። በዚያን ጊዜ አንድ ሀብታም አይሁዳዊ ዘር ሳይተካ ሲሞት ሀብቱን ኤጺፋንዮስ እንዲወርሰው ተናዘዘ። በዚህም በውርስ ያገኘውን ገንዘብ የሕግ አስተማሪ ሊቀጥርበት አሰበ።

አንድ ጊዜ በአንድ መንገድ ላይ ሲሄድ ሳለ አንድ ድኻ አንዱን መነኵሴ ምጽዋት ሲለምነውና መነኵሴው ግን ገንዘብ ስላልነበረው የለበሰውን ልብስ አውልቆ ሲሰጠው አየ። ድኻው ልብሱን እንደወሰደ ነጭ ልብስ ከሰማይ ወርዶ መነኵሴውን ሲያለብሰው አየ። በዚህ ጊዜ ኤጺፋንዮስ ተገርሞ ወደ መነኵሴው በመቅረብ ማንነቱንና ሃይማኖቱስ ምን እንደሆነ ጠየቀው። መነኵሴውም ክርስቲያን መሆኑን ገለጠለት። ኤጺፋንዮስ መነኵሴውን ስለክርስቲያን ሃይማ ኖት ያስተምረው ዘንድ ለመነው። ጥያቄውንም በመቀበል ወደ ኤጺስ ቆጶሱ ወስዶ የክርስትናን ሕግጋት ካስተማረው በኋላ አጠመቀው።

ኤጺፋንዮስም ለመመንኰስ ፈልጎ ኤጺስ ቆጶሱ ወደ ቅዱስ ሉቅያኖስ ገዳም ላከው። እዚያም የቅዱስ ኢላርዮን ደቀ መዝሙር ሆነ። የእግዚአብሔር ጸጋ በእርሱ ላይ ነበረ። የቤተ ክርስቲያን ትምህርት፥ የምንኵስና ሕግጋትንና ትሩፋቱን አጠናቅቆ ዐወቀ።

ቅዱስ ኢላርዮን ኤጺፋንዮስ ጳጳስ እንደሚሆን ትንቢት ተናገረለት። ወደ ቆጵሮስም እንዲሄድና የጵጵስና ሹመት ቢቀርብለት እንዲቀበል አዘዘው። የቆጵሮሱ ጳጳስ ባረፈ ጊዜ ኤጺፋንዮስ ከሁለት መነኰሳት ጋር ሆኖ ዕቃ ለመግዛት ወደ ከተማ ገብቶ ነበር። አንድ ቅዱስ የሆነ ጳጳስ ወደ ገበያ ሄዶ ኤጺፋንዮስ የሚባል መነኵሴ ሁለት የወይን ዘለላዎችን ይዞ ስለሚያገኘው የቆጵሮሰ ጳጳስ አድርጎ እንዲሾመው መንፈስ ቅዱስ ገለጠለት።

ጳጳሱም ወደ ሱቅ ገብቶ ኤጺፋንዮስን ሁለት ዘለላ ወይን ይዞ ከሁለት መነኰሳት ጋር ባገኘው ጊዜ ስሙን ጠየቀው። ከእግዚአብሔር የተመረጠው እርሱ መሆኑን ባየ ጊዜ ወደ ቤተ ክርስቲያን ወስዶ በዲቁና፥ ከዚያ በቅስናና

በመጨረሻም በኤጲስ ቆጶስነት ማዕረግ ሾመው። ኤጲስ ቆጶሱ ያየውን ራእይ ለሕዝቡ ገለጠ። በዚህም የቅዱስ ኢሳርዮን ትንቢት ተፈጸመ።

ቅዱስ ኤጲፋንዮስ የጵጵስናውን ተግባር እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ መንገድ አከናውኖአል ብዙ መጻሕፍትም ጽፎአል። ዘወትር የሚሰብከው ስለ ምሕረት ነበር።

በ402 ዓ.ም. ንግሥት አፍዶክሲያ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ይሽርላት ዘንድ አስጠርታው ንግሥቲቱንና ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅን ለማስታረቅ ብዙ ሙከራ አድርጎ ስላልተሳካለት ወደ ሀገሩ ተመልሶአል። በዚያው ዓመት ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቶአል። (የግንቦት 27 ቀን ስንክሳር)

## የቤት ክርስቲያን ዜማ

በግዕዝ

በቅዳሴ ውስጥ የኅብረት ዜማ

ይዲ: (በ1) ሃሌ ሉያ።

አመ ብእሲ እምእመናን ዘቦአ

ቤተክርስቲያን በጊዜ ቅዳሴ።

ወዒሰምአ መጻሕፍተ ቅዱሳተ

ወኢተዐገሠ እስከ ይፌጽሙ

ጸሎተ ቅዳሴ።

ወኢተመጠወ እምቍርባን፤

ይሰደድ እመቤተ ክርስቲያን

አስመ አማሰነ ሕገ እግዚአብሔር

ወአስተሐቀረ ቁመተ ቅድመ ንጉሥ ሰማያዊ ንጉሠ ሥጋ ወመንፈስ ከመ መሀሩን ሐዋርያት በአብጥሊሶሙ።

ይሕ:- አንቲ ውእቱ መሶበ ወርቅ ንጹሕ

እንተ ውስቴታ መና ኅቡዕ

ኅብስት ዘወረደ እምሰማያት



ወሀቤ ሕይወት ለኵሉ ዓለም

ይካ:- አሐዱ አብ ቅዱስ

አሐዱ ወልድ ቅዱስ

አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ

ይሕ:- በአማን አብ ቅዱስ

በአማን ወልድ ቅዱስ

በአማን ወእቱ መንፈስ ቅዱስ

ይ፥ካ አስመ ጸንዐት ምሕረቱ ላዕሌነ

ይ፥ሕ፥ ጽድቀሰ ለእግዚአብሔር ይሄሉ ለዓለም።

ይ፥ካ ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ።

ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን ሃሌ ሉያ

ይ፥ሕ:- ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን ሃሌ ሉያ፤

ይ፥ዲ ተንሥኡ ለጸሎት፤

ይ፥ሕ:- እግዚኦ ተሣሃለነ

ይ፥ካ ሰላም ለኵልክሙ።

ይ፥ሕ፥ምስለ መንፈስከ።

ሃሌ ሉያ።

በአማርኛ

ከምእመናን በቅዳሴ ጊዜ

ወደ ቤተ ክርስቲያን የገባ፥

ከቡራት የሚሆኑ ቅዱሳት መጻሕፍትን የማይሰማ፥

የቅዳሴውን ጸሎት እስኪፈጽሙ የማይታገሥ፥

ሥጋውን ደሙን የማይቀበል ሰው ቢኖር፥ ከቤተ ክስቲያን ይውጣ። የእግዚአብሔርን ሕግ አፍርሷልና፥

ነፍስን ሥጋን በሚገዛ በሰማያዊ ንጉሥ ፊት መቆምን አቃሏልና፥



www.ethiopianorthodox.org

ሐዋርያት በቀኖናቸው እንዲህ አስተማሩን።

ከሰማያት የወረደ ኅብስት፥ ለዓለም ሁሉ ሕይወትን የሚሰጥ።

የንጹሕ ወርቅ መሶብ አንች ነሽ።

በውስጥዋ መና ያለባት።

ይ : ካ:- ቅዱስ አብ አንድ ነው።

ቅዱስ ወልድ አንድ ነው።

መንፈስ ቅዱስ አንድ ነው።

ይ: ሕ፥ ቅዱስ አብ በእውነት አንድ ነው።
ቅዱስ ወልድ በእውነት አንድ ነው።

መንፈስ ቅዱስ በእውነት አንድ ነው።

ይ : ካ:- ምሕረቱ በኛ ላይ ጸንታለችና።

ይ:ሕ:- የእግዚአብሔር ቸርነቱ ለዘለአለም ይኖራል።

ይካ:- ምስጋና ለአብ፥ ለወልድ፥ ለመንፈስ ቅዱስ ይሁን፤

ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለም፤ አሜን ሃሌ ሉያ።
ይ:ዲ ለጸሎት ተነሡ።
ይ:ሕ አቤቱ ይቅር በለን።

ይ:ካ:- ሰላም ለሁላችሁ ይሁን።

ይ:ሕ:- እንደ ቃልህ ይሁንልን።

## ከዚህ ምዕራፍ የምናገኘው ትምህርት

ከዚህ ምዕራፍ በተለየም ከሐርያቱ ታሪክ ጠቃሚ የሆኑ ትምህርቶችን እናገኛለን።

ምንም እንኳ ጌታችን በጌቴሴማኒ የአትክልት ቦታ በአይሁድ እጅ በተያዘ ጊዜ ሐዋርያት ሁሉ ጥለውት ቢሸሹ አሁን የመንፈስ ቅዱስን ኀይል ከተቀበሉ በኋላ የተለዩ ሆነዋል። አሁን እንደያኔው መሸሽ ሳይሆን ችግርን ችሎ በደስታ መቀበል ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት በእነርሱ ያደረው የእግዚአብሔር መንፈስ የዚህ ዓለም ክብርና ምቾት ከዘለዓለማዊው ሕይወት ጋር ሲነጻጸር



www.ethiopianorthodox.org

ዋጋቢስ መሆኑን እንዲገነዘቡና የዚህን ዓለም ፈተና ድል ለመንሣት መንፈሳዊ ጥንካሬውን ስለሰጣቸው ነው።

መንፈስ ቅዱስ ማንኛውን ዓለማዊ ችግር ለመቋቋም ድፍረቱን ስለሰጣቸው የእግዚአብሔር ቃል የሰዎችን ሕይወት እንዲለውጥ ለማድረግ ከማስተማር አልተቈጠቡም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ቃል ባላስተምር ወዮልኝ ያለው መንፈሳዊ ስሜት በሁላቸውም ዘንድ የነበረ መሆኑን ያመለክታል (1ኛ:ቆሮ:ም:9ቊ:16)።

በሐዋርያቱ ዘንድ መሰልቸት ወይም ተስፋ መቊረጥ ያልነበረ መሆኑን ከአሠራራቸው እንረዳለን። ምንም ያኽል ኢ:አማንያኑ ከፉዎችና እምቢተኞች ቢሆኑ ሐዋርያቱ ግን እነዚያን ሰዎች እውነትን እንዲያውቁ ማድረግ ግዴታቸው እንደሆነ አድርገው ስለሚገነዘቡ ብዙዎችን ወደ ቀናው መንገድ ለመመለስ በቅተዋል። ለምሳሌ ሐዋርያው ቅዱስ ፊልጶስ ሊገድሉት ዐቅደው አስረው በሚያሠቃዩት ጊዜ ያሳስበው የነበረው የእነርሱ አለመዳን እንጂ የእርሱ ሥቃይ አልነበረም። ስለዚህም ነው ዘለዓለማዊውን ሕይወት ለምን ከእናንተ ታባርራላችሁ? ለምን ነፍሳችሁን ለማዳን አትሞክሩም? እያለ በፈገግታ ያስተማራቸው።

ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ ሲሉ እንደ ባሪያ የመሸጥን ዘዴ እንኳ ተጠቅመዋል።

በዚህ ዓለምም የሚኖሩት የማስተማር ግዴታቸውን ለመወጣት ካልሆነ በቀር ወደዘለዓለማዊው መኖሪያቸው ለመሄወር ይችሉ ነበር። ይህንንም የምንረዳው ምእመናን ቅዱስ ፊልጶስን ከተሰቀለበት ሊያወርዱት ቢሞክሩ አይሆንም ብሎ መከላከሉን በመመልከት ነው።

ታዲያ እኛም ራሳችንን በፍጹም ለእግዚአብሔር አስረክበን የእግዚአብሔር መንፈስ ማደሪያ ከሆንን ያንን መሰል ኀይል እንደሚሰጠን እርግጠኞች መሆን አለብን።

ለእግዚአብሔር ቃል መስፋፋትና ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት በሚኖረን መንፈሳዊ ቅናት መሰልቸትንና ምንቸገረኝ ባይነትን ከእኛ ዘንድ እንድናስወግድ የሁለቱ ሐዋርያት ታሪክ ያስተምረናል። በአለን ዐቅም ሁሉ ጥረት ባናደደርግ እኛም ወዮልን።

1. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ የጸሎት ቤት ይባላል ባለው ንግግሩ ምንን አመለከተ?

2. ስለቤተ ክርስቲያን ሕንጻ አሠራር የሚናገረው የሃይማኖት መጽሐፍ ምን ይባላል?

3. ቤተ ክርስቲያን ስንት በሮች እንዲኖሩት ታዝዞአል?

4. የበሮቹስ አቅጣጫ ወዴት ወዴት መሆን አለበት ተባለ?

5. የቤተ ክርስቲያን ቅርጽ ምንን መምሰል አለበት?

6. የአገልግሎቱ ቤት ከወዴት መሆን አለበት?

7. የመጠመቂያው ቦታ በየት አቅጣጫ ነው?

8. በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ያሉ ረጃጅም ወንበሮች የእነማን ናቸው?

9. መርከቡ፥ በመርከቡ ውስጥ ያሉት ተጓገኞችና መርከበኛው ከቤተ ክርስቲያን ጋር በምን ይመሳሰላሉ?

10. ሐዋርያት የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓትና መዋቅር ለመወሰን በኢየሩሳሌም በተሰበሰቡ ጊዜ ከነርሱው ጋር እነ ማን ነበሩ?

11. ቤተ ክርስቲያን መካሄድ ያለባት በምን ዐይነት ሥርዓት ነው?

12. የኤጲስ ቆጶሱ ተግባር ምንድነው?

13. የቀሳውስቱ ተግባር ምንድነው?

14. የዲያቆናቱስ ተግባር ምንድነው?

15. አንድን ኤጲስ ቆጶስ ለመሾም ስንት ኤጲስ ቆጶሳት ያስፈልጋሉ?

16. ቀሳውስትንና ዲያቆናትን ለመሾም ስንት ኤጲስ ቆጶሳት ያስፈልጋሉ?

17. ንዋየ ቅድሳት ማለት ምን ማለት ነው?

18. ንዋየ ቅድሳት የሚባሉት ምን ምን ናቸው?

19. ጻሕል ማለት ምንድነው?



20. ጽዋ (ጥዋ) ማለትስ ምንድነው?

21. ዕርፈ መስቀል ማለት ምንድነው?

22. መሶበ ወርቅ ማለት ምንድነው?

23. ማኅፈድ ማለት ምንድነው?

24. ልብሰ ተክህኖ ማለት ምንድነው?

25. ጥና (ጽና) ማለት ምንድነው?

26. ሥርዓተ ቅዳሴውን ከመጀመሩ በፊት ካህኑ በንዋየ ቅድሳቱ ላይ ምን ያደርጋል?

27. የሐዋርያው ቅዱስ በርተሎሜዎስ የአገልግሎት ዕጣ ወዴት ነበር?

28. ወደዚያ አገርስ የገባው እንደምን ነው?

29. በዚያስ አገር እንደምን አድርጎ ሥራ ጀመረ?

30. በሥራው ላይ ምን ተአምር ታየ?

31. ሕዝቡ ሁሉ ያመኑት እንዴት ነው?

32. ጌታችንስ ምንን አዘዘው?

33. የዚያ የሄደበት አገር ሰዎች ምን ዐይነት ሰዎች ነበሩ?

34. በመጨረሻስ እንዴት ሆኑ?

35. ከዚያስ በኋላ ወዴት ሄደ?

36. የዚህን ሐዋርያ ድርጊት ሰምቶ የተቈጣው ማነው?

37. እርሱስ በሐዋርያው ላይ ምን አደረገበት?

38. የሐዋርያው ፊልጶስ አገልግሎት ዕጣ የት ነበር?

39. እዚያስ ሄዶ ምን አደረገ?

40. ከዚያ ቀጥሎስ ወዴት ሄደ?

41. በዚያ አገር ያሉ አላማንያን ምን አደረጉት?

42. እርሱ ግን ምን አላቸው?

43. ምድር የተንቀጠቀጠችው መቼ ነው?

44? በዚህ ጊዜ አላማንያኑ ምን አደረጉ?



www.ethiopianorthodox.org

45. ምእመናንስ ምን ሊያደርጉ ፈለጉ?

46. ሐዋርያው ምእመናን

47. ሐዋርያቱ በጌቴሴማኒ ያትክልት ቦታ ካሳዩት ፈሪነት አሁን የተለዩበት ምክንያት ምንድነው?

48. ሐዋርያው ፊልጶስ አስረው ሊገድሉት በሚያሠቃዩት ጊዜ ከሥቃዩ ይልቅ ያሳሰበው ምን ነበር?

49. ይህን ስሜቱንስ ምን በማለት ገለጠው?

50. ከዚህኛው ዓለም ይልቅ ለወዲያኛው ዓለም የሚጓጓ መሆኑን ፊልጶስ በምን ዐይነት ገለጠው?

51. የሁለቱ ሐዋርያት ታሪክ ለእኛ ምን ትምህርትን ይሰጠናል?

52. በእኛ ላይ ወዮታ የሚደርሰው ምን ባናደርግ ነው?

# ምዕራፍ 5

## መንፈሳዊነትና ግብረገብነት

## ስሕተትን አምኖ ይቅርታ መጠየቅ

እግዚአብሔር ከሰው ልጆች የሚጠብቃቸው ቋሚ ተግባሮች አሉ። ሰውም ከፍጡር ጓደኛው የሚጠብቃቸው ተግባሮች አሉ።

እንደሚታወቀው፥ እግዚአብሔር በነቢያቱ፥ በሐዋርያቱና በተለያዩ ቅዱሳን አማካይነት የሰጣቸውን ትእዛዞች በትክክል በሥራ ላይ መዋላቸውን የሚቈጣጠርበት የራሱ የሆነ መለኮታዊ መንገድ ስላለው ጥፋትን አጥፍቶ ከእግዚአብሔር መሸሽ ወይም መደበቅ አይቻልም። ማንኛውም የሰው ልጅ ድርጊት ግልጥ ሆኖ በእግዚአብሔር ዘንድ ይታወቃል እንጂ ከእርሱ የሚሰወር ምንም ነገር የለም። ስለዚህም ነው የዕብራውያኑ መልእክት ጸሐፊ:- «እኛን በሚቈጣጠር በእርሱ ዐይኖች ፊት ሁሉ ነገር የተራቈተና የተጋለጠ ነው እንጂ ከእርሱ ፊት የተሰወረ ፍጥረት የለም» ያለው (ዕብ:4፥13)። ባለመዝሙሩም ይህን አባባል ሲያረጋግጥ እንዲህ ብሎአል:-

«ከአንተ ለማምለጥ ወዴት መሄድ እችላለሁ? ከፊትህስ ርቄ ወዴት እሸሻለሁ? ወደ ሰማይ ብወጣ እዚያ ትገኛለህ፤ ወደ ሙታን ዓለም ብወርድ በዚያም አንተ አለህ። ከፀሐይ መውጪያ ባሻገር በርሬ ብሄድ ወይም በፀሐይ መግቢያ በኩል ርቄ ብኖር እዚያ ተገኝተህ በእጅህ ትምራኛለህ፤ በቀኝ እጅህም ትደግፈኛለህ። ጨለማን «ሰውረኝ» ወይም ብርሃንን «ወደ ሌሊት ተለወጥልኝ» ብል ጨለማ እንኳ በአንተ ዘንድ አይጨልምም፤ ሌሊቱም የቀን ያኽል ያበራል፤ ስለዚህ በአንተ ዘንድ ጨለማና ብርሃን ልዩነት የላቸውም» (መዝ:139 ቍ:7–12)።

በማስረጃዎቹም መሠረት ከእግዚአብሔር መሸሽ ወይም መደበቅ የማንችል መሆናችንን ዐውቀን ጥፋተኞች በምንሆንበት ጊዜ ጥፋታችንን አምነን ይቅርታ መለመን እንደሚገባን እግዚአብሔር በተለያዩ ሁናቴዎች ገልጾልናል።:

ለምሳሌ አዳምና ሔዋን እንዳይበሉ የተከለከሉትን የዛፍ ፍሬ በልተው ጸጋቸው በተገፈፈ ጊዜ ከእግዚአብሔር ለመደበቅ ሞከሩ። እግዚአብሔርም ፍሬውን በልተው መደበቃቸውን ቢያውቅም እንኳ ጥፋታቸውን አምነው ይቅርታ እንዲጠይቁ ስለፈቀደ አዳምን ሲጠይቀው «አትብላ ያልኩህን ፍሬ ከዛፉ ወስደህ በላህን?» ብሎታል (ዘፍ:ም:3ቍ:11)። አዳም ግን አዎን በልቼአለሁና ይቅርታ አድርግልኝ በማለት ፈንታ ይህች ከእኔ ጋር እንድትኖር የሰጠኸኝ ሴት ሰጥታኝ ነው የበላሁት ብሎ ኃጢአተኛዋ ሔዋን እንጂ እርሱ እንዳልሆነ ተናግሮአል።

ሌላው ምሳሌ ደግሞ ቃየል ነው። ቃየል ወንድሙን አቤልን በገደለው ጊዜ እግዚአብሔር ቃየልን:- «ወንድምህ አቤል የት አለ»? ብሎ የጠየቀው መግደሉን አምኖ ይቅርታ እንዲጠይቅ ነበር። ቃየል ግን እኔ የወንድሜ ጠባቂ ነኝን? ብሎ ነው መልስ የሰጠው። እግዚአብሔርም ወዲያው በቃየል ላይ ፍርዱን በማስተላለፉ ቃየል ቅጣቱ እንደ ጠነከረበት በመግለጥ የማስተዛዘኛ መልስ በሰጠ ጊዜ ይህ አነጋገሩ ይቅርታ እንደመጠየቅ ተቈጥሮለት ማንም ሰው እንዳይገድለው እግዚአብሔር ምልክት አደረገለት (ዘፍ:ም:4ቍ:15)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐሳባችንን ሁሉ የሚያውቅ ሲሆን የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ትወድደኛለህን ብሎ ሦስት ጊዜ መላልሶ ቅዱስ ጴጥሮስን መጠየቁ የሚወድደው ወይም የማይወድደው መሆኑን የማያውቅ ሆኖ አይ

 www.ethiopianorthodox.org 

ደለም። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በሊቀ ካህናቱ ግቢ ጌታችንን አላውቀውም ብሎ ሦስት ጊዜ ስለካደ ያንን አስታውሶና ጥፋቱን አምኖ የእግዚአብሔርን ይቅርታ እንዲለምን ስለፈቀደ ሦስት ጊዜ መላልሶ ትወድደኛለህን ሲል ጠይቆታል (ዮሐ:ም:18 ቍ:15–17)።

እግዚአብሔር ሰው ሁሉ እንዲድን እንጂ እንዲጠፋ ስለማይፈቅድ ለእኛ ደኅንነት ብሎ የጥፋት መንገዳችንን አይፈቅደውም። ይሁን እንጂ ከሰው ልጆች የሥጋ ደካማነት የተነሣ ወድደንም ሆነ ሳንወድድ የጥፋትን መንገድ እንከትላለን። ለዚህ መድኀኒቱ ግን ኃጢአታችንን አምነን የእግዚአብሔርን ይቅርታ መለመን ነው።

ኃጢአታችንን አምነን የእግዚአብሔርን ይቅርታ ብንለምን እርሱ ይቅር እንደሚለን ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ሲያረጋግጥልን እንዲህ ብሎአል:-

«ኃጢአታችንን ለእግዚአብሔር ብንናዘዝ እርሱ ታማኝና ጻድቅ ስለሆነ ኃጢአታችንን ሁሉ ይቅር ይልልናል፤ ከበደላችንም ሁሉ ያነጻናል» (1ኛ: ዮሐ:ም:1ቍ:9)።

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርርስቶስ በደልን ተናዝዞ ይቅርታ መጠየቅ የእግዚአብሔርን ይቅርታ እንደሚያስገኝ፥ ጠፍቶ በተገኘው ልጅ ምሳሌ ግልጽ አድርጎታል። በዚሁ በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 15 ቍ:11–32 ላይ በተሰጠው ምሳሌ ያ የአባቱን ገንዘብ ተገቢ ባልሆነ መንገድ አባክኖ ወደ አባቱ የተመለሰው ልጅ በአባቱ ዘንድ ምን ያኽል ቀባይነትን እንዳገኘ እንመለከታለን። ያ ልጅ በክፉ ተግባሩ ተጸጽቶ ጥፋቱን በመናዘዝ ወደ አባቱ ስለተመለሰ ይቅርታን አግኝቷል። አባቱም በጣም ተደስቶአል። በዚህም ዐይነት ሁላችንም ብንሆን ኃጢአታችንን ለእግዚአብሔር ተናዝዘን ወደ እግዚአብሔር ብንመለስ እግዚአብሔር ይቀበለናል።

በሰዎች በኩል ደግሞ ሰውን ከሰው ወይም ከኅብረተሰቡ ጋር የሚያገናኙ ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ኅብረተሰቡ ትክክል ናቸው ብሎ በሚያምንባቸው መንገድ መከናወን አለባቸው። እንደዚያ ካልሆነ የግለሰብን ወይም የኅብረተሰቡን መብትና ጥቅም ሊጐዳ ይችላል። ይህ የኅብረተሰብን ወይም የግለሰብን መብት የተጋፋ ሰው በደሉን አምኖ ይቅርታ ቢጠይቅ በእርሱ ላይ ያለው ቅሬታ ይወገዳል፤ እርሱም ይመሰገናል፤ ይከበራልም።



ስለዚህ ማናችንም ብንሆን እግዚአብሔርን ቅር ከሚያሰኝ ተግባር በንሣዜ ብንመለስና ኅብረተሰቡን ወይም ግለሰቡን በመበደላችን ጥፋታችንን አምነን ይቅርታ ብንጠይቅ ሰላም፥ የኅሊና ዕረፍት፥ ጽድቅ፥ መከበርና መመስገን እናገኛለን።

## እግዚአብሔርን ማመስገን

ክፍል 1 ምዕራፍ 5 ላይ እንደተገለጠው ከተለያዩ የጸሎት ዐይነቶች አንዱ ምስጋና ነው።

እግዚአብሔርን የምናመሰግነው መለኮታዊ ልዕልናውን ለማክበርና ተገዢነታችንን ለመግለጽ ነው። እንዲሁም ስለመለኮታዊ ጥበቃው፥ ስለ አዳኝነቱ፥ ስለደግነቱ፥ ስለቸርነቱ፥ ስለ መሐሪነቱና ስለፍቅሩ እናመሰግነዋለን። በቃል ኪዳኑም ታማኝ ስለሆነ እናመሰግነዋልን።

እግዚአብሔር መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ዘለዓለማዊ አምላክ ነው። እርሱም ምንም የማይሳነው ሁሉን ቻይ አምላክ ነው። ፍጥረቶች ሁሉ የተገኙት በእርሱ አስገኚነት ነው። በዚህም ምክንያት ለአምላካችን ምስጋና ማቅረብ የሚገባን መሆኑን ለማመልከት የሚከተለውን ጥቅስ እንመልከት:-

«ኻያ አራቱ ሽማግሌዎች ለዘለዓለም እስከ ዘለዓለም በሚኖረው፥

በዙፋኑ ላይ በተቀመጠው ፊት በግንባራቸው ተደፍተው ይሰገዳሉ፤ አክሊሎቻቸውንም በዙፋኑ ፊት አኑረው:- ‹ጌታችንና አምላካችን ሆይ፥ ሁሉን ነገር ስለፈጠርህ፥ ሁሉም ነገር የተፈጠረውና የሚኖረው በአንተ ፈቃድ ስለሆነ ክብርና ውዳሴ ኀይልም ለአንተ ይገባል» ይሉ ነበር።» (ራ:ዮ:ም:4ቍ10–11)

በዚህም ምክንያት ለአምላካችን ተገዢነታችንን ለመግለጥ እናመሰግነዋለን፤ እናከብረዋለንም።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአበሔር ለሰው ልጆች ምን ያኽል ጥበቃ የሚያደርግላቸው መሆኑን ሲያመለክት:- «የእናንተስ የራስ ጠጕራችሁ እንኳ የተቈጠረ ነው» ብሏል (ማቴ:ም 10ቍ:30)። አምላካችንም እንደዚህ አድርጎ የሚጠብቀንና የሚጠነቀቅልን ስለሆነ ማመስገን ይገባናል።



www.ethiopianorthodox.org

በመጀመሪያው ሥጋዊ አባታችን በአዳም ኃጢአት ምክንያት ከተፈረደብን የሞት ፍርድ ለማዳን እግዚአብሔር አንድያ ልጁን በመላክ የእኛን ሥጋ ለብሶ ተቤዥቶናል። ይህም ማለት በእኛ ቦታ ሆኖ ሕማም ተቀብሎ ሞቶልን፥ ከዚያም ከሞት በመነሣቱ የሞትን ኀይል ደምስሶልናል። ይህም እግዚአብሔር በእኛ ላ ያለውን ከፍተኛ ፍቅር ያሳያል። ከዚህ የበለጠ ፍቅርና ከዚህም የበለጠ ውለታ ስለማይኖር እግዚአብሔርን በዚህ ምክንያት እናመሰግነዋለን። የእግዚ አብሔርን ውለታ ለመክፈል ስለማንችልና ሁሉም ነገር የእርሱ ነው እንጂ እኛ ምንም የእርሱ ያልሆነ ነገር ስለማይኖረን በዚህ ምክንያት እርሱን አለማመስገን ውለታቢስ መሆን ይሆናል።

እግዚአብሔር አምላካችን ደግ ስለሆነ ሰው ሁሉ እንዲድን እንጂ እንዲጠፉ አይፈልግም። ይህንንም በሚከተሉት ማስረጃዎች እንመልከት።

«እኔ በክፉ ሰው ሞት የምደሰት ይመስላችኋልን? አይደለም፤ እኔ ደስ የሚለኝ ስለ ኃጢአቱ ንስሓ ገብቶ በሕይወት በሚኖር ሰው ነው» (ሕዝ 18:23)።

«የእግዚአብሔር ፈቃድ ሰዎች ሁሉ እንዲድኑና እውነትን እንዲ ያውቁ ነው።› (1ኛ:ጢ.ሞ:ም:2ቍ:4)።

እነዚህ ከላይ የተመለከቱት ሁለት ጥቅሶች በግልጽ የሚያሳዩት የእግ ዚአብሔርን ደግነት ነው። ለዚህም ለደግነቱ ልናደርግ የምንችለው ነገር ቢኖር ማመስገን ብቻ ነው። እንዲሁም እግዚአቤሔር ቸር፥ ርኅሩኅና መሐሪ መሆኑን የሚገልጡ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች ያሉ ቢሆንም ለጊዜው ጥቂቶቹ ብቻ ከዚህ ቀጥለው ቀርበዋል።

«አባት ለልጆቹ እንደሚራራላቸው እንዲሁም እግዚአብሔር ለሚፈሩት ይራራላቸዋል» (መዝ:103ቍ:13)።

«እግዚአብሔር የፍርድ አምላክ ነውና ስለዚህ እግዚአብሔር ይራራላችሁ ዘንድ ይታገሣል፤ ይምራችሁም ዘንድ ከፍ ከፍ ይላል፤ እርሱን በመተማመን የሚጠባበቁ ሁሉ ብፁዓን ናቸው» (ኢሳ: ም:30ቍ:18)።

«እግዚአብሔር መልካም ነው፤ በመከራ ቀንም መሸሸጊያ ነው» (ናሆ ም:1ቍ:7)።



እንደ አባት ለሚራራልን፥ ምሕረት ለሚያደርግልንና ፍላጎታችንን ሁሉ ለሚያሙአላልን አምላክ ልናደርግ የምንችለው ምስጋና ማቅረብ ነው።

እግዚአብሔርንም ማመስገን እንደሚገባን ቅዱሳት መጻሕፍት ጥሪ አድር ገዋል።

«እናንተ እግዚአብሔርን የምትፈሩት አመስግኑት» (መዝ:22 ቍ:23)።

«አምላክ ሆይ፥ ሕዝቦች ያመስግኑህ፤ ሕዝቦች ያወድሱህ» (መዝ: 67፥3፥5፥መዝ፥117)።

«ግዚአብሔር ሆይ፥ ስለምታደርጋቸው ታምራትና ስለ እውነተኛነትህ ሰማያት በቅዱሳን ጉባኤ ይዘምራሉ።» (መዝ:89ቍ:5–7)።

በእናንተ መካ ከል ያለው የእስራኤል ቅዱስ ታላቅ ስለሆነ በጽዮን የምትኖሩ ሁሉ «እልል» በሉ (ኢ.ሳ:ም:12ቍ:6)።

«እነርሱ እግዚአብሔርን ዐውቀውት ሳለ ለእርሱ የሚገባውን ክብርና ምስጋና አልሰጡትም፤ በሐሳባቸው ከንቱ ሆኑ፤ የማያስተውል ልቦናቸውም ጨለመ» (ሮሜ:1:21)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተለያዩ ጊዜያት እግዚአብሔርን ማመስገን እንደሚገባ ገልጾአል። ከነዚህም ሁለቱ ለማስረጃነት ይቀርባሉ።

አንድ ጊዜ ጌታችን ዐሥር ለምጻሞችን ፈውሶ ነበር። ከእነዚህ ከዐሥር ለምጻሞች መፈወሱን ባየ ጊዜ ወደ ጌታችን ተመልሶ ምስጋና ያቀረበ አንድ ሰው ብቻ በመሆኑ ጌታችን እንዲህ ብሎ ተናግሮአል:- «ከለምጽ የነጹት ሰዎች ዐሥር አልነበሩምን? ታዲያ ዘጠኙ የት አሉ? እግዚአብሔርን ለማመስገን ተመልሶ የመጣ ከዚህ ከባዕድ ሰው በቀር ሌላ የለምን?» (ሉቃ: ም: 17ቍ:17–18)።

ጌታችን ወደ ኢየሩሳሌም በክብር በገባ ጊዜ ብዙ ሰዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እግዚአብሔርን በማመስገናቸው ፈሪሳውያን ጌታችንን ደቀ መዛሙርትህን ዝም አሰኛቸው አሉት። ጌታችን ግን እነርሱ እንኳ ዝም ቢሉ ድንጋዮች ይጮኻሉ እላችኋለሁ ብሎ መልስ ሰጣቸው (ሉቃ: 19 –40)።

www.ethiopianorthodox.org



www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር ቢመሰገን ምንም የሚጨመርለት ነገር የለም፤ ባይመሰ ገንም ምንም የሚጐድልበት ክብር አይኖርም። ማመስገኑ ግን ለእኛ ኀሊናዊና መንፈሳዊ ጠቀሜታ አለው። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ውለታዎች የምን ከፍልበት ምንም መንገድ ስለሌለን በምስጋና ኅሊናችንንና መንፈሳዊ ስሜታ ችንን እናረካለን።

## በተቻለ መጠን የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸም

ተደጋግሞ እንደተገለጠው የእግዚአብሔር ፈቃድ ሰው ሁሉ የአምላኩን መመሪያዎች ተግባራዊ በማድረግ ዘለዓለማዊውን ሕይወት እንዲወርስ ነው።

ሁለቱ አጠቃላይ ዋና ዋና መመሪያዎች በኦሪት ዘጸአት ምዕራፍ 20 ላይ የቀረቡት ዐሥሩ ትእዛዛትና በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 5 ላይ የቀረቡት ስድስቱ ቃላተ ወንጌል ናቸው።

ከእነዚህም ከዋነኞቹ መመሪያዎች ሌላ በትምህርት፥ በምክርና እንዲሁም በትእዛዝ መልክ በየጊዜው የቀረቡ መመሪያዎች ብዙዎች ናቸው። ከነዚህም ጥቂቶቹን እነሆ:-

«ወደ ኃጢአት በሚመራ ምኞት የተበላሸውን አስቀድሞ ትኖሩበት የነበረውን አሮጌውን ሰውነት አስወግዱ ... ውሸትን አትናገሩ:- ... ምንም ያኽል ብትቈጡ ኃጢአት አትሥሩ፤ ቍጣችሁ ሳይወገድ ፀሐይ አይጥ ለቅባችሁ፤ ለዲያብሎስም ዕድል አትስጡት፤ ይሰርቅ የነበረ ከእንግዲህ ወዲያ አይሰረቅ... ከቶ ከአፋችሁ ክፉ ቃል አይውጣ፤ ነገር ግን ለሚሰሙት ጸጋን የሚሰጥና ለማነጽ የሚጠቅም ለሰዎች አስፈላጊ የሆነውን ቃል ተናገሩ፤ ለምትዋጁበት ቀን መያዣ እንዲሆናችሁ የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግ ዚአብሔር መንፈስ አታሳዝኑ። መራራነት፥ ንዴት፥ ቍጣ ጩኸት፥ ስድብና ማናቸውም ዐይነት ክፋት ሁሉ ከእናንተ ይራቅ» (ኤፌ:4፥22፥31)።

«በእናንተ የሚገኙትን የምድራዊ ሕይወት ምኞት ሁሉ ግደሉ፤ እነር ሱም:- ዝሙት፥ ርኵሰት፥ ፍትወት፥ ክፉ ምኞት እንደ ጣዖት ማምለክ የሆ ስግብግብነት ናቸው» (ቆላ:ም:3ቍ:5)።

«የገንዘብ ፍቅር የክፋት ሁሉ ምንጭ ነው» (2ኛ: ጢ.ሞ:ም:6:ቍ:10)።



«ወንድሞች ሆይ፥ እርስ በርሳችሁ አትተማሙ፤ ሰውን የሚያማ ወይም በሰው ላይ የሚፈርድ ሕግን ያማል፤ በሕግም ላይ ይፈርዳል፤ በሕግም ላይ ብትፈርድ ፈራጅ መሆንህ ነው እንጂ ሕግን ፈጻሚ አደለህም። ሕግን የሚሰጥና የሚፈርድ አንድ እግዚአብሔር ብቻ ነው፤ ሊያድንም፥ ሊያጠፋም የሚችል እርሱ ብቻ ነው፤ ታዲያ በሰው ላይ የምትፈርድ አንተ ማነህ?» (ያዕ: ም: 4ቍ:12)።

ስለ እግዚአብሔር ፈቃድስ ቅዱሳት መጻሕፍት ምን ይላሉ?

«እናንተ ዛሬ ወይም ነገ ወደ ሌላ አገር ሄደን እዚያ አንድ ዓመት እንቀመጣለን፤ ነግደንም እናተርፋለን» የምትሉ ተጠንቀቁ። ነገ የሚሆነውን ስለማታውቁ ሕይወታችሁ ምንድነው? ለአንድ አፍታ ታይቶ በኋላ እንደ ሚጠፋ እንፋሎት ናችሁ። ይልቁንስ እናንተ ማለት የሚገባችሁ ጌታ ቢፈቅድና ብንኖር ይህን ወይም ያን እናደርጋለን› ነው» (ያዕ:ም:4ቍ13–15)።

«ክርስቶስ በሥጋው መከራ የተቀበለ ስለሆነ እናንተንም ይህ ሐሳብ እንደጦር መሣሪያ ያበርታችሁ፤ በሥጋው መከራ የተቀበለ ኃጢአት መሥ ራትን ትቶአልና። ከእንግዲህ ወዲህም በምድራዊ ኑሮው የሚኖረው የሥጋን ክፉ ምኞት በማድረግ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈጸም ነው» (1ኛ:ጴጥ:ም:4ቍ:1–2)።

«ዓለምና ምኞቱ ያልፉሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፈጽም ግን ለዘለዓለም ይኖራል» (1ኛ:ዮሐ:ም:2ቍ:17)።

ስለዚህ የዘለዓለምን ሕይወት ለመኖር ዕድል እናገኝ ዘንድ የእግዚ አብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም እንትጋ።

## ሌላውን ሰው እንጂ ራስን አለማመስገን

ብዙዎቻችን ሰው ሁሉ እንዲያመሰግን እንፈልጋለን። በመንፈሳዊ ትሕትና ራስን በመግታት ካልሆነ በቀር ይህ ዝንባሌ የብዙዎቻችን የተፈጥሮ ጠባይ ነው። ይህም በመሆኑ ሰዎች እንዲያመሰግኑን ለማመቻቸት በተለያየ ሁናቴ ራሳችንን ማመስገን እንጀምራለን።

ራሳችንን በምናመሰግንበት ጊዜ አንድም እኛ በእውነትም መመስገን የሚገባን ሰዎች መሆናችንን ለራሳችን አምነንበት ነው፤ ወይም ደግሞ ራሳችንን



www.ethiopianorthodox.org

ከመጠን በላይ ከመወውደዳችን የተነሣ እኛነታችንን ከሌሎች ሰዎች ሁሉ አስበልጠን ለመገኘት በመፈለግ ነው። ይህም ሁናቴ ራስን ከፍ ከፍ የማድረግና ሌላውን ሰው ዝቅ አድርጎ የማየትን ስሜትን ያስከትላል። ይህም ማለት ትዕቢት፥ ኵራትና ትምክሕት ጠፍረው ይዘውናል ማለት ነው።

ስለ እነዚህ አስከፊ ኃጢአቶች ቅዱሳት መጻሕፍት የሚሉትን ቀጥለን እንመልከት:-

«እስቲ በመታበይ አትኳዱ፤ የትምክሕት ንግግራችሁንም አስወግዱ፤ እግዚአብሔር አምላክ ሁሉን ያውቃል፤ ሕዝብ የሚሠራውንም ሁሉ በፍርድ ይመዝናል» (1ሳሙ:2፥3)።

እግዚአብሔር ከሚጠላቸው ነገሮች መካከል አንዱ ትዕቢተኛ ዓይን ነው (ምሳ:6፥16–17)።

«እኔ ዕብሪትንና ኵራትን እጠላለሁ» (ምሳ:8፥13)።

«ትዕቢት ውርደትን ያስከትላል፤ ትሕትና ግን ጥበብን ያስገኛል» (ምሳ:ም:11ቍ:2)።

«እግዚአብሔር ትምክሕተኞችን ሁሉ ይጸየፋል፤ ሳይቀጣም አያልፋቸውም» (ምሳ:ም:16ቍ:5)።

«ትዕቢት ወደ ጥፋት፥ ትምክሕተኛነትም ወደ ውድቀት ያደርሳል» (ምሳ:ም:16ቍ:18)።

«ክፉዎች ሰዎች ትዕቢተኞችና ዕብሪተኞች ናቸው፤ የሚያተርፉትም ኃጢአትን ብቻ ነው» (ምሳ:ም:21ቍ:4)።

«እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- ጠቢብ በጥበቡ ብርቱ ሰውም በኀይሉ አይታበይ፤ ባለጸጋም በሀብቱ አይመካ» (ኤር:ም:9ቍ:23)።

ከላይ በዝርዝር የቀረቡት ጥቅሶች የሚያመለክቱት ኵራት፥ ትዕቢትና ትምክሕት ምን ያኽል በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠሉ መሆናቸውን ነው።

በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የተጻፉት ቅዱሳት መጻሕፍት አጠንክረው የሚመክሩን ከራስ ወዳድነት ተላቅቀን ትሑቶች እንድንሆን ነው። ሰው ትሑት



www.ethiopianorthodox.org

በሚሆንበት ጊዜ ሥጋዊ ፍላጎቱንና ምኞቱን ክዶ ራሱን ከሌሎች ሰዎች ያሳንሳል እንጂ በራስ ወዳድነት፥ ራሱን ከፍ በማድረግና ሌላው ሰው ከእርሱ ያነሰ እንደሆነ በመገመት ወይም በማስመሰል ራሱን አያመሰግንም። እንዲያውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ ያረጋገጠላቸው እኔን መከተል የሚፈልግ ራሱን ይካድ ብሎ ነው (ማቴ:16፥24)።

ይህን የትሕትና ምሳሌነት ቅዱስ ባስልዮስና ቅዱስ ኤፍሬም በተግባር አሳይተውታል። ቅዱስ ኤፍሬም የቅዱስ ባስልዮስን ታላቅነት በራእይ አይቶ ወደ ቂሣርያ ሄደ። እዚያም ባስልዮስ የለበሰውን የክብር ልብስ ባየ ጊዜ በባስልዮስ ቅድስና ተጠራጠረ። እግዚአብሔር ግን የቅዱስ ኤፍሬምን ጥርጣሬ ለማጥፋት ሁለት ምልክቶችን ሰጠው። የመጀመሪያው ምልክት ርግብ ወርዳ በባስልዮስ ራስ ላይ ስታርፍበት አሳየው። ሁለተኛው ምልክት ደግሞ ገና ቅዱስ ባስልዮስና ቅዱስ ኤፍሬም ተገናኝተው ከመተዋወቃቸው በፊት ቅዱስ ኤፍሬም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወደ ጥግ ቆሞ ሳለ ለቅዱስ ባስልዮስ እግዚአብሔር ገልጦለት ቅዱስ ኤፌፍሬምን በስሙ ጠራው። ከዚያ በኋላ ተዋወቁ።

ይህ ከሆነ በኋላ አንዲት ሴት የሠራችውን ኃጢአት ከጥዋት እስከ ማታ በዝርዝር በወረቀት ላይ ስትጽፍ ውላ ወደ ቅዱስ ባስልዮስ በመሄድ ኃጢአትዋ ሁሉ ይቅር ይባልላት ዘንድ ወደ እግዚአብሔር እንዲጸልይላት ለመነችው። እርሱም ከጸለየላት በኋላ በዝርዝር ከቀረበው ኃጢአት ከአንዱ በቀር ሌላው በመላ ተደምስሶ አገኘችው። እንደገና እያለቀሰች ወደ ቅዱስ ባስልዮስ ሄዳ ቀሪው ኃጢአትም ይደመሰስላት ዘንድ ወደ እግዚአብሔር እንዲጸልይላት ለመነችው። እርሱ ግን ስለ ቀረው ኃጢአት እንዲጸልይሽ በበረሓ ወደሚገኘው ወደ ቅዱስ ኤፍሬም ሂጂ ብሎ ላካት። ወደ ቅዱስ ኤፍሬመ ደርሳ ጉዳዩን በነገረችው ጊዜ ይህን ማድረግ የሚችል ሊቀ ጳጳሱ ባስልዮስ ነው እንጂ እኔማ ተራ ሰው ነኝ አላት። ወደ ቅዱስ ባስልዮስ በተመለሰች ጊዜ ሞቶ ሊቀብሩት አስከሬኑን ተሸክመውት ሲሄዱ ደረሰችባቸው። እርስዋም አልቅሳ ወረቀቱን በአስከሬኑ ሳጥን ላይ ጣለችው። ወረቀቱን እንደገና አንሥታ ብታየው የቀረውም ኃጢአት ተደምስሶላት አገኘችው።

በዚህ ታሪክ ውስጥ እንደምናነብበው እነዚያ ሁለቱ ቅዱሳን ክብርን ለራሳቸው ሳያስቀሩ አንዳቸው ለሌላው በማስተላለፍ ምሳሌነታቸውን አበርክተዋል። (ይህን ታሪክ በዐሥረኛውና በዐሥራ ሁለተኛው ክፍል መጻሕፍት፥ በሁለቱም በምዕራፍ አራት ላይ ይመለከቷል።)

ራስን ከፍ አድርጎ ማሰብ ወይም ራስን አመስግኖ መናገር በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ መሆኑን ለመረዳት የሚከተሉትን የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረ ጃዎች እንመልከት:-

«በምታደርገው ሁሉ የእግዚአብሔርን መሪነት አትርሳ፤ እርሱም በትክ ክለኛው መንገድ ይመራሃል፤ እኔ ዐዋቂ ነኝ አትበል፤ ይልቅስ እግዚአብሔርን ፍራ፤ ከክፉትም ራቅ› (ምሳ:3፥6–7)።

«በጣም በዙ ማር መብላት መልካም አይደለም፤ ምስጋናንም ከሰው መፈለግ አያስከብርም።» (ምሳ:25፥27)።

«ሌሎች ሰዎች ያመስግኑህ እንጂ ራስህን አታመስግን፤ ሰዎች ስለ አንተ ይመስክሩ እንጂ አንተ ስለራስህ አትናገር» (ምሳ:27፥2)።

«ራሳቸውን ጥበበኞችና ብልኆች አድርገው ለሚገምቱ ወዮላቸው» (ኢሳ 5፥21)።

በዚህ ዓለምም አስተሳሰብ ቢሆን ራሱን የሚያመሰግን ሰው እንደ ግብዝ ይቈጠራል። በመንፈሳዊ አስተሳሰብ ደግሞ ሰማያዊ ዋጋ ለመቀበል አንድ ሰው የሚፈጽማቸውን በጎ ተግባሮች ሰው ሳያየው በድብቅ እንዲያደርግ እንጂ ያደረጋቸውን በጎ ድርጊቶች እየዘረዘረ በሰው ፊት ራሱን እንዲያመሰግንባቸው አልተፈቀደለትም። በዚህ ጉዳይ ጌታችን ያዘዛቸውን ሁለት ትእዛዞች መመ ልከት ይቻላል።

«ሰዎች ይዩልን ብላችሁ መልካም ሥራችሁን በሰው ፊት ከማድረግ ተጠንቀቁ፤ አለበለዚያ ግን በሰማይ ካለው አባታችሁ ምንም ዋጋ አታገኙም» (ማቴ:ም:6ቍ:1)።

«እናንተም እንዲሁ የታዘዛችሁትን ሁሉ ከፈጸማችሁ በኋላ ‹የማንጠቅም አገልጋዮች ነን፤ የፈጸምነውም ግዳጃችንን ብቻ ነው› በሉ» (ሉቃ:17፥10)።

በእነዚህ ሁሉ የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች መሠረት ራሳችንን በማመስገን መናገር፥ ወይም ሰዎች እንዲያመሰግኑን መፈለግ አስፈላጊ ያልሆነ ግብዝነት መሆኑን ተገንዝበን ከግብዝነት እንጠንቀቅ።



## ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር ከሰው ልጆች ምን ይጠብቃል?
2. ትእዛዞቹ ተግባራዊ መሆናችውን እግዚአብሔር የሚቈጣጠረው እንዴት ነው?
3. ከእግዚአብሔር መሸሽ ይቻላልን?
4. ከፍርድ የምንድነው እንዴት ነው?
5. ትእዛዝ አፍራሾች ብንሆን ምን ይደርስብናል?
6. የማይለወጠው የእግዚአብሔር ሕግና ሥርዓት የትኛው ነው?
7. እግዚአብሔር የጥፋት መንገዳችንን የማይፈቅደው ለምንድነው?
8. ከጥፋት መንገዳችን ለመመለስ የምንችለው እንዴት ነው?
9. ከኃጢአት የመመለሻውን መንገድ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ያረጋ ገጠው ምን ብሎ ነው?
10. በንስሓ ወደ እግዚአብሔር የሚመለስ ሰው ይቅርታ እንደሚያገኝ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያረጋገጠው በየትኛው ምሳሌ ነው?
11. ሰውን የበደለ ሰው ይቅርታ ቢጠይቅ ምንን ያገኛል?
12. እግዚአብሔርን ወይም ግለሰቡን በድለን በኑዛዜ ብንመለስና ይቅርታ ብንጠይቅ ምን እናገኛለን?

113. እግዚአብሔርን የምናመሰግነው ለምንድነው?

14. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ለሁላችንም በቂ ጥበቃ የሚያደርግልን መሆኑን ለማመልከት ምን አለ?
15. ጌታችን የሞትን ኀይል የደመሰሰልን እንዴት ነው?
16. ውለታቢስ የሚያሰኘን ምክንያት ምንድነው?
17. የእግዚአብሔር ፈቃድ ምንድነው?
18. የቅዱስ ባስልዮስንና የቅዱስ ኤፍሬምን የትሕትና ምሳሌነት አስረዳ።



www.ethiopianorthodox.org

# ሦስተኛ ክፍል

## ምዕራፍ 1

## ትምህርተ ሃይማኖት

### የእግዚአብሔር ፍቅር

ፍቅር ማለት አንድ ሰው በተፈጥሮው፥ ወይም በዝምድና ምክንያት ወይም በሌሎች የተለያዩ ምክንያቶች በሌላ ሰው ወይም በሌሎች ሰዎች ላይ ሊኖረው የሚችል ጠንካራ የሆነ መልካም ስሜት ነው።

በሰዎች ዘንድ ሊኖር የሚችለው ፍቅር አብዛኛውን ጊዜ ከግል ጥቅም ጋር የተያያዘ ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው ውለታ የዋለለትን ሰው ይወድዳል። ሌላው በሰዎች ዘንድ ሊኖር የሚችለው የፍቅር ምክንያት ደግሞ ዝምድና ነው። ለምሳሌ አባትና እናት ልጆቻቸውን የሚወድዱት በተፈጥሮ ስሜታቸው ነው እንጂ ከምንም ጥቅም ጋር አያይዘውት አይደለም።

እግዚአብሔር በሰው ልጆች ላይ ያለው ፍቅር አባታዊ ፍቅር ነው የሚባለው እርሱ በባሕርዩ አፍቃሪ ስለሆነ ነው። አንዳንድ ጊዜ የወላጆች ፍቅር በተለያዩ ምክንያቶች ሊቀዘቅዝ ይችላል። የእግዚአብሔር ፍቅር ግን መቼም ቢሆን የማይቀዘቅዝ ዘለዓለማዊ ነው። እግዚአብሔር ፍቅር ነው የሚባለውም በዚሁ ምክንያት ነው። ለዚህም የሚከተለውን የእግዚአብሔርን ማረጋገጫ እንመልከት:- «ኢየሩሳሌም ግን ‹እግዚአብሔር ትቶኛል ጌታዬም ረስቶኛል› አለች። እግዚአብሔርም እንዲህ ሲል ይመልሳል:- እናት የምታጠባውን ልጅ ልትረሳ ትችላለችን? ወይስ ለወለደችው ልጅ አትራራምን? እርስዋ እንኳ ብትረሳ እኔ ግን እርሷን አልረሳም» (ኢሳ:ም:49ቍ:14–15)።

እግዚአብሔር ሰውን በፈጠረው ጊዜ በምድር ላይ ከተፈጠሩት ፍጥረቶች ሁሉ ይበልጥ ስላከበረውና ስለወደደው በእነዚያ ፍጥረቶች ሁሉ ላይ የበላይ አለቃ አድርጎ ሾመው። ሰው ደግሞ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የማፍረስ ኃጢአት በፈጸመ ጊዜ እግዚአብሔር እንደ ትክክለኛ ዳኝነቱ ቀጣው። ይሁን እንጂ የሰው ልጅ ኃጢአት መሥራቱና በኃጢአቱ መቀጣቱ የእግዚአብሔርን ፍቅር አላቀዘቀዘውም። ይህን አባባል የሚያረጋግጠው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሏል:- «እኛ ገና ኃጢአተኞች ሆነን ሳለ ክርስቶስ ስለ እኛ



ሞቶአል፤ ይህም እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ፍቅር ምን ያኽል ታላቅ መሆኑን ያስረዳል» (ሮሜ:ም:5ቍ:8)።

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም በተለያዩ ጥቅሶች ይህንኑ አባባል ደጋግሞ ገልጾታል።

«እግዚአብሔር አንድ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለምን እንዲህ አድርጎ ወድዶታል። ይህንንም ያደረገው በልጁ የሚያምን ሁሉ እንዲድን እንጂ እንዳይጠፋ ነው» (ዮሐ:ም:3ቍ:16) ።

«ፍቅር ምን እንደሆነ የምናውቀው ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወቱን ለእኛ አሳልፎ ስለሰጠን ነው» (1ኛ:ዮሐ:3፥16)።

«በልጁ አማካይነት ሕይወት እንድናገኝ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታል፤ በዚህም የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ መካከል ተገልጦአል። ፍቅር ማለት እንዲህ ነው:- እኛ እግዚአብሔርን ስለወደድነው ሳይሆን እርሱ ስለ ወደደንና ኃጢአታችንን እንዲደመስስ ልጁን ስለላከልን ነው» (1ኛ: ዮሐ:ም:4ቍ:9–10)።

በዚህ ዓለም ላይ ምንም የእግዚአብሔር ያልሆነ ነገር ስለሌለ እርሱ ከማንም ላይ ምንም አይጠብቅም። በዚህም መሠረት የእግዚአብሔር ፍቅር ከምንም ጋር የተያያዘ አይደለም። በእርግጥ እግዚአብሔር ፈቃዱን ፈጽመን በሕይወት እንድንኖር ይፈቅዳል። ሆኖም ስናጠፋ እንደ አባትነቱ ይቀጣናል። ተጸጽተን ወደ እርሱ ከተመለስን ደግሞ ምሕረት ያደርግልናል። ስለዚህ ጉዳይ ቅዱሳት መጻሕፍት ምን ይላሉ?

«እግዚአብሔር መሐሪ ስለሆነ ለዘለዓለሙ አይተወንም። ለጊዜው ሐዘን ቢያመጣብንም በመጨረሻ ይምረናል፤ ለእኛም ያለው ፍቅር እውነተኛና ብርቱ ነው» (ሰቆ:ም:3ቍ:31–32)።

«እግዚአብሔር መሓሪና ይቅር ባይ ነው፤ በቶሎ የማይቈጣና ፍቅሩ የበዛ ነው» (መዝ:103ቍ:8)።



www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካይነት እስራኤል ብሎ በሚናገርበት ጊዜ በተለየ አይሁዶችን ብቻ ማለቱ አይደለም። በእርግጥ የእግዚአብሔር ሕግ የተጀመረው በእስራኤል ሕዝብ አማካይነት መሆኑ የታወቀ ነው። ይህን ከተረዳን በኋላ የእግዚአብሔርን ዘለዓለማዊ ፍቅር የሚያስረዱትን የሚከተ ሉትን ጥቅሶች እንመልከት።

«የእስራኤል ሕዘብ ሆይ፥ እነሆ፥ እናንተን ለዘለዓለም እወድዳችኋለሁ፤ ዘለዓለማዊ ቸርነቴም የጸና ይሆናል» (ኤር:ም:31ቍ:3)።

«እስራኤል ሆይ፥ እናንተ የተወደዳችሁ ልጆቼ ናችሁ፤ ከሁሉ አስበልጬ የምወድዳችሁ አይደለምን? ምሕረት፥ አደርግላችሁ ዘንድ ወደ እኔ ላቀር ባችሁ እፈቅዳለሁ፤ እኔ እግዚአብሔር ይህን ተናግሬአለሁ» (ኤር:31፥20)።

የእግዚአብሔርም ደግነትና ርኅራኄ ለፍጥረቱ ሁሉ እንጂ ለተወሰነ ወገን ብቻ አይደለም። «እግዚአብሔር ለሰው ሁሉ ቸር ነው፥ ለፍጥረቱም ሁሉ ይራራል» (መዝ:145ቍ:9)።

«ጴጥሮስ እንዲህ ሲል መናገር ጀመረ፤ በእውነት እግዚአብሔር ሰውን ከሰው እንደማያበላልጥና እንደማያዳላ አስተዋልሁ፤ የማንኛውም አገር ሰው ቢሆን እግዚአብሔርን የሚፈራና እውነት የሆነውን ነገር የሚያደርግ ከሆነ እግዘአብሔር ይቀበለዋል» (የሐ:ሥ:ም10ቍ:34–35)።

## ምሥጢረ ሥጋዌ

### ከሦስቱ አካላት የአንዱ መለኮታዊ አካል ሥጋ መልበስ

የምሥጢረ ሥጋዌ ዕውቀታችን የሚወሰነው ቅዱሳት መጻሕፍት በሚገ ልጹልን መጠን ብቻ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ «ቃል ሥጋ ሆነ» በሚልበት ጊዜ ሥጋ የሆነው ከሦስቱ አካሎች አንዱ ብቻ መሆኑን እንገነዘባለን (ዮሐ:ም:1ቍ:14)።

ሥጋ የለበሰው ቃል ብቻ መሆኑ ከቀድሞ ጀምሮ በእግዚአብሔር ልጅነት የታወቀ በመሆኑ ነው። የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ እንዲህ ብሏል፦

«እግዚአብሔር በቀድሞ ዘመናት በተለያየ መንገድ በነቢያት አማካይነት ለአባቶቻችን ብዙ ጊዜ ተናግሮ ነበር፤ አሁን ግን ሁሉን ነገር ወራሽ ባደረገውና ዓለምንም በፈጠረበት በልጁ አማካይነት በእነዚህ በመጨረሻ ቀኖች ለእኛ ተናገረን» (ዕብ:ም:1ቍ:1–2)።



## የሥጋ መልበስና የመስቀል ምክንያት (በሰው በኩል)

አንደኛ/ <u>የሰውን ዘር ከተወረሰውና ከሌላው ኃጢአት ለማንጻት</u>፦ በቅዱሳት መጻሕፍት እንደተገለጠው እግዚአብሔር አዳምን ከፈጠረው በኋላ በገነት አስቀመጠው። ከፉና ደግን ከምታስታውቀዋ ዛፍ በቀር ከሌሎች ዛፎች ሁሉ እንዲበላ ፈቀደለት። ምንም እንኳ ክፉንና ደግን ከምታስታውቀዋ ዛፍ ቢበላ እንደሚሞት ማስጠንቀቂያ ቢሰጠው እርሱ ግን በሰይጣን ምክር ትእዛዝ አፍርሶ ከዚያች ከተከለከለች ዛፍ በላ። ከዚያ በኋላ የሞትና የእርግማን ፍርድ በእርሱና በዘሩ ሁሉ ላይ የጸና ሆነ።



በአትክልቱ ቦታ ውስጥ የአንተን ድምፅ ሰማሁ፤ እራቍቴንም ስለሆንሁ አንተን በመፍራት ተደበቅሁ (ዘፍ:ም:3ቍ:10)።

እግዚአብሔር ግን ሰማያዊ አባት በመሆኑ የሰውን ዘር ከኃጢአት ባርነትና ከእርግማን ፍርድ ነጻ ሊያወጣው ፈቀደ።

ታዲያ፥ ነጻ የሚያወጣው እንስሳትን በመሠዋት ነውን? የእንስሳቱ መሥዋ ዕትማ ለክርስቶስ ቤዛነት ምሳሌ (ጥላ) ናቸው እንጂ እነርሱ ራሳቸው ኃጢአትን የሚያስተሠርዩ አይደሉም። እንዲያውም የዕብራውያኑ መልእክት ዓለማውያን ሥርዓቶች ናቸው ይላቸዋል (ዕብ:ም:9ቍ:10)። ከዚያም በላይ በኦሪቱ ሥር ዓት መሥዋዕት ይቀርብ የነበረው ግለሰቦች ስለሚፈጽሙት በደል እንጂ ስለ ጥንተ አብሶ አልነበረም። ሌላው የእንስሳቱ መሥዋትነት ጠባይ ደግሞ በአንድ



www.ethiopianorthodox.org

በኩል ኃጢአቱን የሠሩት እነርሱ አለመሆናቸውና በሌላ በኩል ደግሞ ለመሥዋዕትነት የቀረቡት እነርሱ ፈልገው ሳይሆን ያለፍላጎታቸው መሆኑ ነው። ስለዚህ ጌታችን ኃጢአት የሠራውን የሰውን ሥጋ ለብሶ መቤዥት ነበረበት እንጂ ሌላ ምርጫ አልነበረም።

በኦሪቱ ሥርዓት ወደ ጽድቅና ወደ ቅድስና ደረጃ የደረሱ ሰዎች ነበሩ። ወደዚያ ደረጃ የደረሱት ግን በዚያ በነበረው ሥርዓት ሳይሆን ወደፊት ሊመጣ ባለው በክርስቶስ ስላመኑ ነው። ይህን አባባል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያብራራው:- «የአባታችሁ የአብርሃም ምኞት የእኔን ቀን አይቶ ለመደሰት ነበር፤ አይቶም ተደሰተ ብሏል» (ዮሐ:ም:8ቍ:56)።

ሁለተኛ/ በኦሪት ዘፍጥረት:ም:2ቍ:17 ላይ ከዚያች ዛፍ ብትበላ ትሞታለህ የተባለው አምላካዊ ፍርድ የግድ ተግባራዊ መሆን ነበረበት። ይህን ፍርድ በራሱ ተግባራዊ ለማድረግ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ሥጋ ለበሰ። ቤዛነቱም ኃጢአቱን በሠራው ጠባይ እንጂ በሌላ ጠባይ መሆን እንደማይገባው ከተገለጠበት የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች አንዱን እንመልከት:-

«ልጆች ሥጋና ደም ያላቸው ሰዎች እንደ መሆናቸው ኢየሱስ እንደ እነርሱ ሰው ሆነ፤ ይህን ያደረገውም በሞቱ አማካይነት በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን ዲያብሎስን ለማጥፋት ነው፤ እንዲሁም ሞትን በመፍራት ምክንያት ዕድሜ ልካቸውን በባርነት ይገዙ የነበሩትን ለመዋጀት ነው። የኢየሱስ ፍላጎት መላእክትን ለመርዳት ሳይሆን የአብርሃምን ዘር ለመርዳት መሆኑ ግልጽ ነው። ስለዚህ በሁሉም ነገር ወንድሞቹን መምሰል ተገቢው» (ዕብ:ም:ቍ:14–17)።

ይህም ማለት ክርስቶስ የመላእክትን ተፈጥሮ ሳይሆን የሰውን ተፈጥሮ ለበሰ። ይህም የሆነበት ምክንያት ኃጢአቱን የሠራው ሰው ስለሆነ ነው።

ሦስተኛ/ የእግዚአብሔርን በረከትና ጸጋ ጌታችን ሥጋ ባይለብስ ኖሮ ሰዎች ሊያገኙት ባልቻሉም ነበር። የምሥጢረ ቍርባን፥ የዳግም መወለደና የልጅነት ጸጋ ጌታችን ሥጋ ባይለብስ ኖሮ ባልተገኙም ነበር። በተለየም ጌታችን ሥጋ በመልበሱ ምክንያት ሰው በኃጢአት ከመውደቁ በፊት ከነበረበት ደረጃ ከፍ ብሏል። ከፍ ያለውም ከመለኮት ጋር ባደረገው ተዋሕዶ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ይህን አባባል ሲያረጋግጥ እንዲህ ብሏል:-

«በእነዚህ በተሰጡት ነገሮች አማካይነት በክፉ ምኞች ምክንያት በዚህ ዓለም ካለው ጥፋት ድናችሁ የመለኮታዊ ባሕርይ ተካፋዮች ሆናችኋል፤ የእርሱንም ክቡርና እጅግ ታላቅ የሆነውን ተስፋ አግኝታችኋል» (2ኛ: ጴጥ: 1፥4)።

አራተኛ/ የእግዚአብሔርን ፍርድ ቀጥተኛነትና ለኃጢአትም ቀደም ተብሎ የተላለፈው ዘለዓለማዊ ውሳኔ ምን ያኽል ከባድ እንደሆነ ለማሳየት:- ይህን ኃጢአት ለመደምሰስ የግድ የአምላክ ሥጋ መልበስ አስፈለገ።

አምስተኛ/ሥጋ የለበሰው የእግዚአብሔር ልጅ እርግማናችንን ተሸክሞ ሕማማትን መቀበሉ የቀድሞው ኃጢአት ምን ያኽል ከባድ እንደነበረ ያመለክተናል። «በእንጨት ላይ ተሰቅሎ የሚሞት ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ስለተጻፈ ክርስቶስ ስለ እኛ እንደ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን» (ገላ:3:13)።

ስድስተኛ/ ድኅነታችን የእግዚአብሔር ልጅ ደሙን እስኪያፈስስለት ድረስ የቱን ያኽል ውድ መሆኑን ያስተምረናል።

«አንተ ታርደህ በደምህም ከየነገዱ፥ ከየቋንቋው፥ ከየወገኑና ከየሕዝቡ ሁሉ ሰዎችን ለእግዚአብሔር ዋጅተሃልና መጽሐፉን ለመውሰድና ማኅተሞቹን ለመክፈት የተገባህ ሆነሃል» (ራ:ዮ:ም:5 ቍ:9)።

## ሥጋ የመልበስና የመሰቀል ምክንያት (በእግዚአብሔር በኩል)

አንደኛ/ የእግዚአብሔርን ጻኝነትና መሐሪነት ለማስማማት:-

አምላክ ከክብሩ ጋር የማይመጣጠነውን ሥጋ ለብሶ ሕማማትን መቀበል ሳያስፈልገው ከሁለት አንዱን ነገር ለማድረግ ይችል የነበረ መሆኑ መታወቅ አለበት። አንድም ሰውን በኃጢአቱ ምክንያት በመቅጣት ሊያጠፋው ወይም በሰው ዘር የተፈጥሮ ደካማነት ምክንያት አዝኖለት ይቅርታ ሊያደርግለት ባላቃተውም ነበር። ነገር ግን አዳምን ዝም ብሎ መቅጣት ዳኝነትን ብቻ በሥራ ላይ ማዋል ሲሆን፥ ዝም ብሎ ይቅርታ ማድረግ ደግሞ የሕግ ፍርድን ማዛባት ወይም በዳኝነት ላይ ተጽዕኖ ማድረግ ይሆናል። የዚህ ዐይነቱ አሠራር ሕጸጽን (ጉድለትን) የሚያመለክት እንደመሆኑ ለእግዚአብሔር ባሕርይ የማይስማማ ነው። የአም ላክ ሥጋ መልበስ የተሻለ ሆኖ የተመረጠው ዳኝነቱንና መሐሪነቱን አጣምሮ የያዘ በመሆኑ ነው። እግዚአብሔርም በመካከላቸው ቆሞ ለሁለቱም ማለት ለዳኝቱና ለመሐሪነቱ ተገቢ መብታቸውን ሰጣቸው። መሐሪነት የገባበት እንደሆነ ፍትሕ ሊኖር አይችልም። ፍትሕ መብቱን ጠብቆ በሚራመድበት ጊዜ በደለኛ መቀጣት ስለሚኖርበት ለርኅራኄና ለምሕረት ቦታ ሊኖራቸው አይችልም። ዳኝነት፥ መሐሪነት፥ ቅድስና፥ ደግነትና እውነት የእግዚአብሔር ባሕርያትና ጠባዮቹ ናቸው። የእግዚአብሔር ባሕርያትና ጠባዮቹ ደግሞ እርስ በርሳቸው የሚስማሙ እንጂ የሚቃረኑ አይደሉም።


www.ethiopianorthodox.org

አሁን እንግዲህ የሰውን ዘር ለመቤዠት ሌላ ጻድቅ የሆነ ሰው ይሙት እን በልን? ይህ ሊሆን የማይችልበት ምክንያት የሰው ዘር ሁሉ የአዳምን ኃጢአት ስለወረሰና ሁሉም ባለዕዳ በመሆኑ ማንም ለማንም ሊሞት አይችልም። መልአክ ሞቶ ይቤዠው እንበልን? ይህም የማይሆን ነገር ነው። በአንድ በኩል መላእክት መናፍስት ስለሆኑ አይሞቱም፤ በሌላ በኩል ኃጢአትን የሠራ ሰው ነው እንጂ መልአክ አይደለም። ቅጣቱንም መቀበል ያለበት ሰው እንጂ በደልን ያልበደለው መልአክ ሊሆን አይችልም። ይህ ከሆነ ታዲያ፥ አምላክ በመለኮቱ ይቤዠውን? እንደዚህ ያለው አስተሳሰብ ደግሞ በፍጹም ሊኖር የሚገባው አይደለም። እግዚአብሔር ከሁሉም በላይ ስለሆነ ሞት ሊያሸንፈው አይችልም። በደለኛው ደግሞ ሰው ነው እንጂ እግዚአብሔር አይደለም። አሁን እንግዲህ አምላክ የበደለኛውን የሰው ሥጋ ለብሶ በለበሰው ሥጋ ለሰው ቤዛ ለመሆን የእግዚአብሔር ጥበበኛ ውሳኔ ተላለፈ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህን አባባል ሲያብራራ እንዲህ ብሏል:-

«ከሰው ባሕርይ ደካማነት የተነሣ ሕግ ሊያደርገው ያልቻለውን እግዚአብሔር አድርጎታል፤ እግዚአብሔር የገዛ ልጁን በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌነት ላከ፤ የኃጢአት መሥዋዕት ባደረገውም በዚሁ በልጁ ሥጋ ኃጢአትን በፍርድ አስወገደ» (ሮሜ:ም:8ቍ:3)።

<u>ሁለተኛ/ ደግነቱን ለፍጥረቱ ለመግለጥ</u>:- እግዚአብሔር በባሕርዩ ደግ፥ በጎ አድራጊ፥ ቸርና መሐሪ መሆኑን ፍጥረቱ ሁሉ እንዲያውቅ ይፈቅዳል። እንደዚህ ያሉ የደግነት ጠባዮች መኖራቸውን መገንዘብ ደግሞ በፍጥረቱ ዘንድ ታላቅ ተስፋና መተማመንን ያስገኛሉ። ስለዚህም ባለመዝሙሩ:- «እግዚአብሔር ቸር እንደሆነ ቅመሱ፤ እዩም፤ በእርሱ የሚተማመን ሰው ምስጉን ነው» ብሏል (መዝ:34ቍ:8)።

እነዚህን ደጋግ የእግዚአብሔር ባሕርያት ለማስመስከር የሚቻልበት የሰውን ሥጋ ለብሶ ሕማማትን ከመቀበሉ የበለጠ ሌላ መግለጫ የለም።

የእግዚአብሔርንም ደግነት ጌታችን ከኒቆዲሞስ ጋር ባደረገው ንግግሩ አረጋግጦታል:- «እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እንኳ እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲህ አድርጎ ወድዶታል» ብሎአል (ዮሐ:ም:3ቍ:16)።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ይህን መሠረት በማድረግ እንዲህ ብሏል:-

«ነገር ግን የአዳኛችን የእግዚአብሔር ደግነትና ፍቅር በተገለጠ ጊዜ፥ እኛ በሠራነው የጽድቅ ሥራ ሳይሆን በምሕረቱ አዳነን» (ቲቶ:ም:3ቍ:4–5)።



www.ethiopianorthodox.org

<u>ሦስተኛ/ የክብሩንና የገናናነቱን ልዕልና መጠን ለመሳየት</u>:- የአምላክ ሥጋ መልበስ ለዳኝነትና ለመሐሪነት ተገቢ መብታቸውን መስጠቱንና በዚህም የእግዚአብሔር ደግነት እውነተኛ ጠባዩ እንደሆነ ማሳየቱን የሚክድ የለም። በዚህም አማካይነት የክብሩን መጠንና ህሳቤውን ገለጠልን። የእርሱ ክብርና ልዕልና በጣም ከፍተኛ ቢሆንም እንኳ እግዚአብሔር ቤዛነቱን በሰው ወይም በመልአክ በኩል ሳይሆን ራሱ ሰው ሆኖ አድርጎታል።

<u>በምሥጢረ ሥጋዊ ትምህርት ላይ ከተነሡ መናፍቃን ሁለቱ</u>

አዳም በኃጢአት በወደቀ ጊዜ በእርሱ ላይ የተላለፈው የሞትና የእርግማን ፍርድ በልጆቹ ሁሉ ማለት በሰው ዘር ሁሉ ላይ የተላለፈ መሆኑን ቤተ ክርስቲያን የምታምነውና የምታስተምረው ትምህርት ነው። ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ሥጋ ለብሶ ሕማማትንና ሞትን የተቀበለው በቤዛነቱ እኛን ከፍርዱ ነጻ ሊያወጣን መሆኑ ቀደም ተብሎ ተገልጦአል። የሰውን ሥጋ በተዋሐደ ጊዜ ነፍስ ያለውን ሥጋ ነው እንጂ ነፍስ የሌለውን ሥጋ አልተዋሐደም። ነገር ግን በተለያዩ ጊዜዎች የተነሡ አፖሊናርዮስና ፔላግዮስ የተባሉ መናፍቃን እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ሁለት የቤተ ክርስቲያን ትምህርቶች ተቃውመዋል።

<u>አቡሊናርዮስ (አፖሊናርዮስ)</u>:- ይህ ሰው የሎዶቅያ ኤጲስ ቆጶስ ነበር። እርሱም ምሥጢረ ሥጋዌን በተመለከተ የነበረው እምነት እንደሚከተለው ነው:- መለኮት ተዋሕዶ ያደረገው ነፍስ ከሌለው ሥጋ ጋር ነው። በነፍስ ቦታ መለኮት ስላለ በተዋሕዶው ውስጥ የነፍስ መኖር አስፈላጊ አይደለም። ይህንንም ያለው በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 1ቍ: 4 ላይ:- «ቃል ሥጋ ሆነ» የሚለውን ክፍል መሠረት በማድረግ ነው። እንደ እርሱ አስተሳሰብ እዚህ ላይ ሥጋ የተባለው ነፍስ የሌለው ሥጋ ነው። እርሱ ሳያስተውላቸው ቀርቶ ነው እንጂ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ሰው ወይም የሰው ዘር ለማለት ሥጋ የተባለባቸው ብዙ ክፍሎች አሉ። ከእነዚህም ጥቂቶቹን ቀጥለን እንመለከታለን።

«እግዚአብሔርም ኖኅን እንዲህ አለው የሥጋ ሁሉ ፍጻሜ በፊቴ ደርሶአል» (ዘፍ:ም:6ቍ:13)።

«አንተ ጸሎትን ሰሚ ስለሆንክ ሥጋ ሁሉ ወደ አንተ ይመጣል» (መዝ:65ቍ:2)።

«ሥጋ ለባሽ ሁሉ እንደ ሣር ነው፤ ክብሩም ሁሉ እንደ ሜዳ አበባ ነው» (ኢሳ:ም:40ቍ:6)።

«ከዚህ በኋላ እንዲህ ይሆናል፤ መንፈሴን በሥጋ (ለባሽ) ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ» (ኢዩ:ም:2ቍ:28)።

«እነዚያ ቀኖችስ ባያጥሩ ኖሮ አንድም ሰው (ሥጋ ለባሽ) መዳን ፈልቻለም ነበር» (ማቴ:ም:24ቍ:22)።

«የምታከብረውም ለሰጠኸው ሁሉ የዘለዓለም ሕይወትን እንዲሰጥ በሰዎች ሁሉ ላይ (በሥጋ ለባሽ) ሥልጣን ስለሰጠኸው ነው (ዮሐ:ም:17ቍ:2)።

«ማንም ሰው (ሥጋ ለባሽ) በእግዚአብሔር ዘንድ የኦሪትን ሕግ በመፈጸም አይጸድቅም» (ሮሜ:3፥20)።

«ማንም ሰው (ሥጋ ለባሽ) በእግዚአብሔር ፊት እንዳይመካ» (1ኛ ቆር: ም:1ቍ29)።

እነዚህ ከላይ የቀረቡት ጥቅሶች በግልጽ እንደሚያመለክቱት ሥጋ ወይም ሥጋ ለባሽ የሚለው ቃል ሰው ወይም የሰው ዘር ለማለት እንጂ ነፍስ የተለየው ሥጋ ለማለት አይደለም። በዚሁም ዐይነት በዮሐንስ ወንጌል :ም:1ቍ 14 ላይ ሥጋ የሚለው ቃል ሰው ለማለት ነው እንጂ ሥጋ ብቻ ለማለት አይደለም። ትስብእት ወይም ሰውነት ስንል ደግሞ ነፍስ ያልተለየው ሥጋ ማለታችን ነው። ሥጋ ደግሞ ነፍስ ከተለየው ሰውነት መባሉ ቀርቶ በድን ወይም ሬሳ ይባላል። ስለዚህ መለኮት የተዋሐደው ነፍስ ያለውን ሥጋ ነው እንጂ ነፍስ የተለየውን ሥጋ እንዳልሆነ መገንዘብ አለብን።

ይህ የአፖሊናርዮስ ክሕደት በ381 ዓ.ም በቍስጥንጥንያ በተደረገው ዓለም ዐቀፋዊ ጉባኤ ተወግዟል።

<u>ቢላግዮስ (ፒላግዮስ)</u>:- ቤተ ክርስቲያን የቅዱሳት መጻሕፍትን ማስረጃዎች መሠረት በማድረግ የአዳም ኃጢአት በሰው ዘር ሁሉ ላይ ተላልፎ ሰው ሁሉ ያን ኃጢአት የወረሰ መሆኑን አምና ታስተምራለች። ይሁን እንጂ በ405 ዓ.ም የተወለደ ፒላግዮስ የተባለ እንግሊዛዊ መነኵሴ «አዳም የሠራው ኃጢአት የታሰበው በአዳም ላይ ነው እንጂ ወደ ዘሩ አልተላለፈም፤ ሕፃናት የሚወለዱት ከኃጢአት ንጹሕ ሆነው ነው፤ የሰው ዘር በአዳም ኃጢአት አልተቀጣም፤ ወደፊትም አይቀጣም ብሏል። ሰው በትሩፋት ሕይወት እንዲኖር የእግዚአብሔር ጸጋ አያስፈልገውም፤ የእግዚአብሔር እርዳታ አስፈላጊ ቢሆን ኖሮ ነጻ ፈቃድ ባልኖረም ነበር» ብሏል።

ይህ የፒላግዮስ አባባል ግን የቅዱሳት መጻሕፍትን ትምህርት በተለየም የክርስቶስን አዳኝነት ይቃረናል።



ከዚህ ቀጥሎ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ስለመላው የሰው ዘር ኃጢአተኛነትና ስለክርስቶስ አዳኝነት ከቀረቡት መግለጫዎች መካከል የሚከተሉትን ማስረጃዎች እንመልከት።

«በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር ዓለምን እጅግ ስለወደደው አንድያ ልጁን ሰጠ። እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም የላከው ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም ላይ ለመፍረድ አይደለም» (ዮሐ:ም:3ቍ:16–17)።

«ሴትዮዋንም «ከእንግዲህ ወዲህ እርሱን የምናምነው አንቺ በነገርሽን ቃል ብቻ ሳይሆን፥ እኛ ራሳችን ስለሰማንና በእርግጥ የዓለም አዳኝ እንደሆነ ስላወቅን ነው› አሉአት» (ዮሐ:ም:4ቍ:42)።

«ቃሌን ሰምቶ በሥራ ላይ የማያውለውን የምፈርድበት እኔ አይደለሁም፤ እኔ የመጣሁት ዓለምን ለማዳን ነው እንጂ በዓለም ላይ ለመፍረድ አይደለም» (ዮሐ:ም:12ቍ47)።

«ስለዚህ ደኅንነት ከእርሱ በቀር በሌላ በማንም የለም፤ እኛ ልንድንበት የሚገባን እግዚአብሔር ለሰዎች የሰጠው ስም ከእርሱ በቀር በመላው ዓለም ሌላ የለም» (የሐ:ሥ:ም:4ቍ:12)።

«እኛ የእግዚአብሔር ጠላቶች ሆነን ሳለ በልጁ ሞት ከእግዚአብሔር ጋር ታርቀናል፤ አሁን ከእግዚአብሔር ጋር ከታረቅን በኋላ በሕያው ልጁ አማካይነት ይበልጡን እንድናለን» (ሮሜ:ም:5ቍ:10)።

«ክርስቶስ ከዓመፃ ሁሉ ሊያድነንና መልካም ሥራ ለመሥራት ትጉሆችና ለእርሱ የተለየን እንድንሆን ያነጻን ዘንድ ስለእኛ ራሱን አሳልፎ ሰጠ» (ቲቶ:ም:2ቍ:14)።

«ከተፀነስሁበት ጊዜ ጀምሮ ኃጢአተኛ ነኝ፤ ከተወለድሁበትም ጊዜ ጀምሮ በደለኛ ነኝ» (መዝ:51:ቍ:5)።

«አንድ እንኳ ጻድቅ ሰው የለም፤ አስተዋይም የለም፤ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም። ሁሉም ከመንገድ ወጥተዋል፤ በአንድነት ሆነው ተሳስተዋል፤ ደግ ሥራ የሚሠራ አንድ ሰው እንኳ የለም» (ሮሜ: ም: 3 ቍ: 10–12)።

«ሰዎች ሁሉ ኃጢአት ሠርተዋል፤ እግዚአብሔር የሰጣቸውንም ክብር አጥተዋል» (ሮሜ:ም:3ቍ:23)።

www.ethiopianorthodox.org

«በአንድ ሰው ምክንያት ኃጢአት ወደ ዓለም ገባ፤ በኃጢአት ምክንያትም ሞት መጣ፤ ይኸውም ሰው ሁሉ ኃጢአት ስለሠራ ሞት በሰው ሁሉ ላይ መጣ» (ሮሜ:ም:5ቍ:12)።

«ሞት የመጣው በአንዱ ሰው በአዳም ምክንያት እንደሆነ፥ ከሞት መነሣትም የሚመጣው በአንዱ ሰው በክርስቶስ ምክንያት ነው። በአዳም ምክንያት ሰው ሁሉ እንደሚሞት፥ እንዲሁም በክርስቶስ ምክንያት ሰው ሁሉ ሕይወትን ያገኛል» (1ኛ:ቆሮ:ም:15ቍ21–22)።

«የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል። ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናታልላለን። እውነትም በእኛ ውስጥ የለም» (1ኛ: ዮሐ: ም:1ቍ:7–8)።

እንግዲህ ፒላግዮስ ጥንተ አብሶንና ማለት የተወረሰውን ኃጢአትና የጌታችንን አዳኝነት በሚክድበት ጊዜ እነዚህንና ሌሎችንም ማስረጃዎች አልተመለከታቸው ይሆን?

ይህን የፒላግዮስን ክሕደት በ431 ዓ.ም. በኤፌሶን የተሰበሰበው ዓለም ዐቀፋዊው ጉባኤ አውግዞታል።

## ጥያቄዎች

1. ፍቅር ማለት ምን ማለት ነው?

2. ወላጆች ልጆቻቸውን የሚወድዱት በምን ምክንያት ነው?

3. የእግዚአብሔር ፍቅር አባታዊ ፍቅር ነው የሚባለው በምን ምክንያት ነው?

4. የወላጆች ፍቅርና የእግዚአብሔር ፍቅር በምን ይለያል?

5. ለእግዚአብሔር ፍቅር ዋና ማስረጃ የትኛው ነው?

6. እግዚአብሔር የማይለወጥ መሆኑን ለመግለጥ ከሚቀርቡት ማስረጃዎች ዋነኛው ማስረጃ የትኛው ነው?

7. የእግዚአብሔርን የፍቅር መጠን ከሚገልጡት ጥቅሶች መካከል ዘወትር የሚጠቀሰው የትኛው ነው?

8. እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም የላከው በምን ምክንያት ነው?

9. በዚህ ዓለም ላይ የእግዚአብሔር ያልሆነ ነገር ምንድነው?



10. በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እስራኤል ተብሎ በሚነገርበት ጊዜ ሁሉ ስለ እስራኤላውያን ብቻ መነገሩ ነውን?

11. የእግዚአብሔር ደግነትና ርኅራኄ ለተለዩ ወገኖች ብቻ ነውን? ለመልስህ አንድ የማስረጃ ጥቅስ አቅርብ።

12. ምሥጢረ ሥጋዌ ማለት ምን ማለት ነው?

13. የምሥጢረ ሥጋዌ ዕውቀታችን የተሟላ ነውን?

14. ስለዚህ ያለን ዕውቀት በምን ላይ የተመሠረተ ነው?

15. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ከአብ በቀር ወልድን የሚያውቅ የለም፤ ከወልድም በቀር አብን የሚያውቅ የለም» ያለው ለምንድነው?

16. የምሥጢረ ሥጋዌ ዋና ምክንያት ወይም መነሻ ምንድነው?

17. የተወረሰውን ኃጢአትን (ጥንተ አብሶን) ለማስተሥረይ ለምን በእንስሳት መሥዋዕት አልተጠቀመም?

18. በአራቱ ሥርዓት ሰዎች ወደ ጽድቅና ወደ ቅድስና ደረጃ የደረሱት በምን መንገድ ነው? ማስረጃ አቅርብ።

19. እግዚአብሔር ሰውን በኃጢአቱ ምክንያት ከማጥፋት ይልቅ ሊያድነው የፈቀደው በምን ምክንያት ነው?

20. ጌታችን ሥጋ በመልበሱ ምክንያት የሰው ልጆች ከታደሉት ጸጋ አንዳንዶቹን ጥቀስ።

21. ጌታችን ሥጋ በመልበሱ ምክንያት የሰው ዘር ደረጃ ከፍ ያለው እንዴት ነው?

22. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እርግማናችንን ያስወገደልን እንደምን አድርጎ ነው?

23. የድኅነታችንን ውድነት የምንገምተው ከምን ጋር በማነጻጸር ነው?

24. እግዚአብሔር ወልድ የሰውን ሥጋ ለብሶ ሕማማትን ከመቀበል ይልቅ ምን ለማድረግ ይችል ነበር?

25. ታዲያ፥ ለምን ከሁለቱ አንዱን ድርጊት አልመረጠም?

26. ከሁለቱ አንዱን ድርጊት ቢያደርግ ለእግዚአብሔር ባሕርይ የማይስማማ የነበረው ለምንድነው?



www.ethiopianorthodox.org

27. ጌታችን ዳኝነቱንና መሐሪነቱን ያስማማው እንደምን አድርጎ ነው?

28. የሰውን ዘር ለመቤዠት አንድ ጻድቅ የማይችለው በምን ምክንያት ነው?

29. መላእክትስ ለምን አይችሉም?

30. ጌታችን የግድ የሰውን ሥጋ መልበስ የነበረበት ለምንድነው?

31. ስለ እግዚአብሔር ጥበበኛ ውሳኔ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የሰጠው መግለጫ ምን የሚል ነው?

32. በፍጥረቱ ዘንድ ተስፋና መተማመን የሚጐለብተው የትኞቹን የእግዚአብሔር ጠባዮች ሲገነዘብ ነው?

33. እግዚአብሔር እነዚያን ጠባዮች ያስመሰከረው እንደምን ነው?

34. እግዚአብሔር ለፍትሕና ለመሐሪነቱ ተገቢ መብታቸውን የሰጣቸው እንዴት ነው?

35. የአፓሊናርዮስ ክሕደት ምን ነበር?

36. ቤተ ክርስቲያን በእርሱ ላይ ምን ውሳኔ አሳለፈች? መቼ?

37. የፒላግዮስ ክሕደት ምን ነበር?

38. ቤተ ክርስቲያንስ በእርሱ ላይ መቼና ምን ዐይነት ውሳኔ አሳለፈች?

# ምዕራፍ 2

# መጽሐፍ ቅዱስ

## ብሉይ ኪዳን

<u>የዲና ወንድሞች የበቀል እርምጃ</u>:- ያዕቆብ ከመስጴጦምያ በተመለሰ ጊዜ በከነዓን ምድር ወደ አለችው ወደ ሴኬም በሰላም ደርሶ በዚያ ሰፈረ። የሰፈረ በትንም ምድር ከሼኬም አባት ከኤሞር ልጆች ገዛው። እዚያም መሠዊያ ሠራ።

አንድ ቀን የያዕቆብ ሴት ልጅ ዲና የከነዓናውያንን ሴቶች ለማየት ወጥታ ሳለ የኤሞር ልጅ ሼኬም በግድ ያዛትና አስነወራት። ሼኬምም ዲናን በውበትዋ በጣም ወድዷት ስለነበረ አባቱን ኤሞርን ከእርስዋ ጋር እንዲያጋባው ጠየ ቀው። ኤሞርና ሼኬምም የዲናን አባትና ወንድሞች በጣም ለመኑአቸው።



www.ethiopianorthodox.org


የዲና ወንድሞች በጉዳዩ በጣም ተቈጥተው የበቀል ዘዴ እያመቻቹ ነበር። በዚህም መሠረት እኛ ለእናንተ ሴቶች ልጆቻችንን እንድንድርላችሁና እኛም ደግሞ የእናንተን ሴቶች ልጆች እንድናገባ ከፈለጋችሁ ወንዶች የሆናችሁ ሁሉ እንደ እኛ መገረዝ ይኖርባችኋል አልዋቸው። የሴኬም ሰዎችም በጉዳዩ ተስማምተው ወንዶች ሁሉ ተገረዙ። በሦስተኛው ቀን ሰዎቹ ገና ከመገረዝ ቊስል ሳይድኑ የዲና ሁለት ወንድሞች ስምዖንና ሌዊ ሰይፎቻቸውን ይዘው በመውጣት የዚያን አገር ወንዶች ሁሉ ገደሉ። ከተገደሉትም መካከል ሼኬምና አባቱ ኤሞር ይገኙባቸዋል። ሌሎቹም ወንድሞች ተባብረው የተገደሉትን ሰዎች ቤቶች ሁሉ ዘረፉ። ከዚያም እኅታቸውን ዲናን ከሼኬም ቤት አውጥ ተው ይዘው ሄዱ (ዘፍ:ም:34)።

<u>ዮሴፍና ወንድሞቹ</u>:- ያዕቆብ ዐሥራ ሁለት ወንዶች ልጆች ነበሩት። እነርሱም:- የልያ ልጆች ሮቤል፥ ስምዖን፥ ሌዊ፥ ይሁዳ፥ ይሳኮርና ዛብሎን ናቸው። የራሔል ልጆች ዮሴፍና ብንያም ናቸው። የራሔል አገልጋይ የባላ ልጆች ዳንና ንፍታሌም ናቸው። የልያ አገልጋይ የዘለፋ ልጆች ጋድና አሴር ናቸው። ያዕቆብ ዮሴፍን ከሌሎቹ ልጆቹ ሁሉ አስበልጦ ይወድደው ነበር። ዮሴፍም ለአባቱ የወንድሞቹን በደል ይነግረው ነበረ። ወንድሞቹም አባታቸው ዮሴፍን ከእነርሱ አስበልጦ እንደሚወድደው ባዩ ጊዜ ቀኑበትና ጠሉት።

ከዕለታት አንድ ቀን ዮሴፍ ሕልም ስላየ ለወንድሞቹ ነገራቸው። እኛ ሁላችንም በእርሻ ውስጥ ሆነን የስንዴ ነዶ ስናስር ነበር። የእኔ ነዶ ቀጥ ብሎ ሲቆም የእናንተ ነዶዎች ዙሪያውን ተሰብስበው ለእኔ ነዶ ሰገዱ አላቸው። ወንድሞቹም ታዲያ፥ አንተ በእኛ ላይ ንጉሥ ሆነህ ልትገዛን ታስባለህን? ብ ለው መለሱለት።

እንደገና ዮሴፍ በሌላ ጊዜ ሌላ ሕልም አየ። በሕልሜ ፀሐይ፥ ጨረቃና ዐሥራ አንድ ከዋክብት ሲሰግዱልኝ አየሁ ብሎ ለወንድሞቹና ለአባቱ ተና ገረ፤ አባቱም ነገሩን በሆዱ ይያዘው እንጂ ለጊዜው ግን ተቈጣው።

ከዚህ በኋላ የያዕቆብ ልጆች መንጋዎቻቸውን ወደሚያሰማሩበት ቦታ ደኅንነታቸውን አይቶ እንዲመጣ ያዕቆብ ዮሴፍን ላከው። ወንደሞቹም ዮሴፍ ወደ እነርሱ ሲመጣ በሩቁ ባዩት ጊዜ እንግደለውና አውሬ በላው እንበል ተባባሉ። በመጨረሻ ግን እንደባሪያ ሊሸጡት ተስማሙ። ወደ ግብጽ ለሚሄዱ ነጋዴዎችም ሸጡት። ለብሶት የነበረውን ሸሚዝ ወስደው በደም ከለወሱት በኋላ ለአባታቸው ወስደው ሰጡትና አውሬ እንደበላው አስመሰሉ (ዘፍ: ም:37)።



የያቆብ ልጆች ወንድማቸውን ዮሴፍን እንደሸጡት

<u>ዮሴፍና የጲጥፋራ ሚስት</u>:- ዮሴፍን የገዙት እስማኤላውያን ነጋዴዎች ወደ ግብጽ ወሰደውት ከፈርዖን ባለሟሎች አንዱ ለሆነው ለጲጥፋራ ሸጡት። ዮሴፍም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ስለነበረ ሥራው ሁሉ ይቃናለት ነበር። የፈርዖን ዘበኞች አለቃ የነበረው ጲጥፋራም ዮሴፍን ወደደው። በቤቱም ውስጥ የንብረቱ ሁሉ ኀላፊ አድርጎ ሾመው። በዮሴፍም ምክንያት እግዚአብሔር የጲጥፋራን ቤት ባረከ። ዮሴፍ መልከ ቀና ስለነበረ የጲጥፋራ ሚስት በጣም ተመኘችው። ከእርስዋ ጋር ኃጢአት እንዲሠራም መላልሳ ብትጨቀጭቀው እንደዚህ ያለ ኃጢአት አልሠራም ብሎ እምቢ አላት። አንድ ቀን ሰው በሌለበት ብቻውን ብታገኘው ልብሱን አጥብቃ ያዘች። እርሱ ግን የያዘችውን ልብሱን ትቶ አምልጦ ሄደ። በዚህ ጊዜ እርሱ እንዳስቸገራት አስመስላ በማውራት ባልዋ እንዲያሳስረው አስደረገች። በእስር ቤትም ሆኖ እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ነበር። የእስር ቤቱ አዛዥ በእስር ቤቱ ውስጥ ዮሴፍን በእስረኞቹ ላይ ኀላፊ አደረገው (ዘፍ:ም:39)።

<u>የፈርዖን የወይን ጠጅ አሳላፊና የእንጀራ ቤት ኀላፊ</u>:- ዮሴፍ ከታሰረ ከጥቂት ቀኖች በኋላ የፈርዖን የወይን ጠጅ አሳላፊና የእንጀራ ቤት ኀላፊ ታስረው ዮሴፍ ወደ ነበረበት እስር ቤት መጡ። የእስር ቤቱም አዛዥ ለዮሴፍ አስረከባቸው። ሁለቱ እስረኞች በአንድ ሌሊት የተለያዩ ሕልሞችን አዩ።

www.ethiopianorthodox.org



ሁለቱም ያዩትን ሕልም መተርጐም አቅቶአቸው ተክዘው ባገኛቸው ጊዜ ዮሴፍ ለምን እንደተከዙ ጠየቃቸው። ዮሴፍም አይዞአችሁ ብሎ የሁለታቸውንም ሕልም በትክክል ተረጐመላቸው። ልክ ዮሴፍ እንደተረጐመው ጠጅ አሳላፊው ተፈትቶ ወደ ሥራው ተመለሰ፤ የእንጀራ ቤቱ ኀላፊ ግን ሞት ተፈርዶበት ተገደለ። ዮሴፍም ለጠጅ አሳላፊው እኔ ያለበደል የታሰርሁ ስለሆነ ስትፈታ አስታውሰኝና ለፈርዖን ነግረህ አስፈታኝ ብሎት ነበር። የጠጅ አሳላፊው ግን ዮሴፍን ረሳው እንጂ አላስታወሰውም (ዘፍ:ም:40)።

<u>የፈርዖን ሕልም</u>:- ከሁለት ዓመት በኋላ የግብጽ ንጉሥ ፈርዖን በአንድ ሌሊት ሁለት የተለያዩ ሕልሞችን ካለመ በኋላ ትርጉሙ ስላልገባው ተጨነቀ። በግብጽ ምድር የሚገኙ አስማተኞችንና ጥበበኞችን አስጠርቶ ሕልሙን ቢነግራቸው ከእነርሱ አንዳቸው እንኳ ሕልሙን ሊተረጉምለት የቻለ አልነበረም። በዚህ ጊዜ ያ ከእስር የተፈታው የጠጅ አሳላፊ ዮሴፍን አስታውሶ ለፈርዖን ስለ እርሱ ነገረው። ዮሴፍም የፈርዖንን ሕልም በትክክል ተረጐመ።

የሕልሞቹም ትርጉም በመጀመሪያ ሰባት የጥጋብ ዓመታት ቀጥሎ ደግሞ ሰባት የረሀብ ዓመታት ይመጣሉ የሚል ነው። ዮሴፍም በሰባቱ የጥጋብ ዓመታት እህል ተጠራቅሞ ለረሀቡ ዓመታት እንዲያገለግል የሚል ምክር አቀረበ። ፈርዖን በዚህ ጊዜ ከራሱ ቀጥሎ ያለውን ማዕረግ በመስጠት አከበረው። በሰባቱ የጥጋብ ዘመን ብዙ እህል እንዲከማች አደረገ። ሰባቱ የጥጋብ ዘመን ዐልፎ የረሀቡ ዘመን ሲጀምር ሰዎች ከሌሎች አካባቢ አገሮች ሁሉ ወደ ግብጽ እህል ለመሸመት ይመጡ ጀመር (ዘፍ:ም:41)።



በግብጽ ምድር ዮሴፍ ያገኘው ከፍተኛ ሹመት(ዘፍ. ም:45)

__የዮሴፍ ወንድሞች ወደ ግብጽ መሄድ__:- ረሀቡ በግብጽ ብቻ ሳይሆን በከነዓን ምድርም ስለበረታና ያዕቆብ በግብጽ እህል መኖሩን ስለሰማ ከብንያም በቀር ዐሥሩን ልጆቹን እህል እንዲገዙ ወደ ግብጽ ላካቸው። ዮሴፍ ወንድሞቹን ባያቸው ጊዜ ዐወቃቸው፤ እነርሱ ግን አላወቁትም። ብንያምን ይዘው እንዲ መጡ ስምዖንን አሰረባቸውና እህል ሰጥቶ ላካቸው። ያዕቆብ ግን ችግር ሆኖበት ነው እንጂ ብንያም ከእነርሱ ጋር እንዲሄድ አልፈቀደም ነበር። ዮሴፍም የእናቱን ልጅ ብንያምን ባየ ጊዜ ሆዱ አልችልለት ብሎ ከእነርሱ ተለይቶ ወደ ውስጥ ገባና ምርር ብሎ አለቀ። ወንድሞቹም ከእርሱ ጋር በሚነጋገሩበት ጊዜ ሁሉ እያከበሩ ይሰግዱለት ነበር። ለተወሰነ ጊዜ ሲያስመስል ከቈየ በኋላ ዮሴፍ ስሜቱ አላስችለው ብሎት ለወንድሞቹ ማንነቱን ገልጠላቸውና እየሳማቸው አለቀሰ። ገና የአምስት ዓመት የረሀብ ጊዜ ስላለ ሕይወታችሁን ለማትረፍ እንድትችሉ አባቴንና መላ ቤተሰቡን ይዛችሁ ወደ ግብጽ ተመለሱ፤ እዚህም እኔ እመግባችኋለሁ ብሎ አሰናበታቸው። ከዚያ በኋላ የያዕቆብ ልጆች ወደ ከነዓን ተመልሰው አባታቸውንና መላውን ቤተሰብ ይዘው ወደ ግብጽ ሄዱ። እዚያም ጌሤም በሚባል ሰፈር እንዲያርፉ ተደረገ።



ዮሴፍ ለወንድሞቹ ማንነቱን እንደገለጠላቸው (ዘፍ. ም:45)

ያዕቆብ በግብጽ ምድር ዐሥራ ሰባት ዓመት ከኖረ በኋላ በመቶ አርባ ሰባት ዓመት ዕድሜው ሞቶ ወደ ከነዓን ወስደው በማክፌላ ዋሻ ቀበሩት።



ዮሴፍም ከመሞቱ በፊት ለእስራኤላውያን ወንድሞቹ ወደ ፊት እግዚአብሔር ጐብኝቶአቸው ወደ ከነዓን በሚሄዱበት ጊዜ ዐፅሙን ይዘው እንዲሄዱ ቃል አስገባቸው (ዘፍ:ም:42)።

__ሶስና__:- ወደ ባቢሎን ምርኮ ከተወሰዱት አይሁድ መካከል ኢዮአቄም የሚባል ሰው ነበር። እርሱም ሶስና የምትባለውን የሒልቅያን ልጅ አግብቶ ይኖር ነበር። እርስዋም እጅግ ያማረች መልከ መልካም ነበረች። ሶስና ወላጆችዋ እግዚአብሔርን የምትፈራ ሃይማኖተኛ እንድትሆን አስተምረው አሳድገዋት ነበር። ባልዋ ኢዮአቄም ሀብታምና የተከበረ ሰው ስለነበረ ብዙ ሰዎች ወደ እርሱ ቤት መምጣት ያዘወትሩ ነበር። ከእነዚህም የእርሱን ቤት ከሚያዘወትሩት ሰዎች መካከል ለአንድ ዓመት በዳኝነት እንዲያገለግሉ የተመረጡ ሁለት ሽማግሌዎች ነበሩበት። ሶሰና በጣም መልከ መልካም ከመሆንዋ የተነሣ እነዚያ ሁለቱ ሽማግሌዎች ይመኙዋታል። ኢዮአቄም ሀብታም በመሆኑ የፍራፍሬ ተክል ቦታ ነበረው ። ወደ ቤታቸው የሚመጡ እንግዶች ወደየቤታቸው ሲሄዱ ወደ ባልዋ ያትክልት ቦታ እየገባች ነፋስ ትቀበል ነበር። ይህንንም ነገር ዘወትር ስለምታደርገው እነዚያ ሽማግሌዎች ይመለከቷት ነበር።

አንድ ቀን እነዚያ ሁለት ሽማግሌዎች እርስዋ ከመግባትዋ በፊት በአትክልቱ ቦታ ገብተው ተደበቁ። ከዚያም ሶስና እንደ ልማድዋ ለመናፈስ ከሁለት አገልጋዮችዋ ጋር መጣች። በሙቀቱ ምክንያት አልቧት ስለነበረ አከላትዋን ለመታጠብ ፈለገች። ሁለቱን አገልጋዮችዋን ሄዳችሁ ዘይት አምጡና ታጥቡኛላችሁ፤ ስትሄዱ የአትክልቱን በር ዝጉት አለቻቸው። እነርሱም ዘግተው ሲወጡ ሁለቱ ሽማግሌዎች ከተደበቁበት ወጡና አሁን የአትክልቱ በር ተዘግቶአል፤ ማንም አያየንም፤ ከአንቺ ጋር እንገናኝ፤ እምቢ አትበይን፤ አለበለዚያ ግን ከአንድ ጐረምሳ ጋር ተኝተሽ አገኘንሽ ብለን እኛ ሁለታችን እንመሰክርብሻለን አልዋት። እርስዋም አለቀሰች። እናንተ የጠየቃችሁኝን እሺ ብል ለእኔ ሞት ነው፤ እምቢ ብል ከእጃችሁ አላመልጥም፤ ስለዚህ እንደዚህ ያለውን በደል በእግዚአብሔር ፊት ከምበድል ንጹሕ ሆኜ የእናንተን ፍርድ መቀበል ይሻለኛል ብላ ድምፅዋን ከፍ አድርጋ ጮኸች። በዚህ ጊዜ ሁለቱ ሽማግሌዎችም ጮኹ። ከእነርሱ አንዱ ወደ አትክልቱ በር ሮጦ ሄዶ ሰዎች እንዲገቡ በሩን ከፈተ። ከዚያ በኋላ ሁለቱ ሽማግሌዎች ሶስናን ያላደረገችውን ነገር አደረገች ብለው ከሰስዋት። በማግስቱ በባልዋ ቤት ወደ ተደረገው ስብሰባ ሶስናን ወደ ፍርዱ ሸንጎ አመጥዋት። ፊትዋንም በሻሽ ተሸፍና መጣች። ከእርስዋም ጋር አባትና እናትዋ ዘመድና ወዳጆችዋ እያለቀሱላት መጡ። እነዚያ ክፉዎች ዳኞች ጠላቶችዋ የዐይን ክፉ ፍትወታቸውን ለማርካት ብለው ፊትዋ እንዲገለጥ አስደረጉ። በዚህም ጊዜ እጃቸውን በራስዋ ላይ ጫኑባትና እንዲህ ብለው መሰከሩባት:- እኛ በአትክልቱ ቦታ ሆነን ይህች ሴት ከሁለት



www.ethiopianorthodox.org

አገልጋዮችዋ ጋር ወደ አትክልቱ ውስጥ መጣች። ሁለቱን አገልጋዮችዋን አባርራ ከዚያም አንድ ወጣት ከተደበቀበት ወጥቶ ከእርስዋ ጋር ተገናኘ፤ እኛም አብረው ተኝተው ደረስንባቸው፤ ሰውዬው ጠነከረብንና አመለጠን እርስዋን ግን ያዝናት አሉ። በእግዚአብሔር የተማመነችው ሶስና ከእንባ ጋር ዐይኖችዋን ወደሰማይ አቀናች።

እነዚያ መስካሪዎች፥ ሽማግሌዎችና ዳኞች ስለነበሩ ሰው ሁሉ አመናቸውና ሶስና የሞት ፍርድ ተፈረደባት። እርስዋ ግን ድምፅዋን ከፍ አድርጋ «ዘለዓለማዊው አምላክ ሆይ፥ ነገሮች ከመደረጋቸው በፊት አንተ ምሥጢርን ሁሉ ታውቃለህ፤ በእኔም ላይ በሐሰት የመሰከሩብኝ መሆናቸውን አንተ ታውቃለህ፤ እነርሱ በአቀነባበሩት የሐሰት ክስ ምክንያት ያለጥፋቴ እሞታለሁ?» አለች።

እግዚአብሔርም ጸሎትዋን ሰምቶ ዳንኤል የሚባለውን ወጣት የእግዚአብሔር መንፈስ አነሣሣው። ለመገደል እየተወሰደች ሳለች ዳንኤል ድምፁን ከፍ አድርጎ እኔ ከዚህች ሴት ደም ንጹሕ ነኝ አለ። በዚህ ጊዜ ሰዎች ሁሉ ወደ እርሱ መለስ ብለው ምን ማለትህ ነው አሉት። እርሱም በሕዝቡ መካከል ቆሞ እናንተ የእስራኤል ሰዎች ሆይ፥ እስከዚህ ድረስ አላዋቂዎች ናችሁን? ጉዳይዋን ሳትሰሙና እውነትነቱን ሳትረዱ በአንዲት የእስራኤል ልጅ ላይ የሞት ፍርድ ትፈርዳላችሁን? እነዚህ ሰዎች በእርስዋ ላይ በሐሰት የመሰከሩ ስለሆነ ወደ ፍርዱ (ምርመራው) አደባባይ ተመለሱ። የሕዘብ ሽማግሌዎችም ዳንኤልን እግዚአብሔር ለአንተ የሽማግሌነትን ስጦታ ስለሰጠህ ናና እስቲ ምን ማለትህ እንደሆነ ንገረን አሉት። እርሱም እኔ የምጠይቃቸው ጥያቄ ስላለኝ ሁለቱን ሽማግሌዎች አራርቁአቸው አላቸው። ተራርቀው ከቆሙበት አንዱን አስጠራውና ሲመጣ እንዲህ አለው:- ምንም እንኳ ጌታ፥ ያልበደለውን ሰው ነጻ አትግደል ቢል ቅን ባልሆነ ፍርድህ በንጹሐን ላይ መፍረድህ፥ በደለኞችን መልቀቅህ፥ የዚህ ሁሉ የቀድሞ በደልህ ዕዳ ደርሶብሃል። አሁን እንግዲህ አስተካክለህ ያየህ ከሆነ በምን ዛፍ ሥር ተኝተው አየሃቸው ብሎ ጠየቀው። እርሱም በኮክ ዛፍ ሥር አየኋቸው አለ። ዳንኤልም በእውነት ሐሰትን ተናገርህ የእግዚአብሔር መልአክ ከሁለት ሊሰነጥቅህ በደልህም በራስህ ላይ ነው። የፍርዱን ትእዛዝ ተቀብሏል አለው። ይህንን ወደዚያ ወስደው ሌላውን እንዲያመጡለት አደረገ። እርሱንም እንዲህ አለው አንተ የይሁዳ ዘር ሳትሆን የከነዓን ዘር ነህ። ውበት አታለለህ፤ ፍትወትም ከመንገድህ እንድትወጣ አደረገህ፤ አንተን እምቢ ለማለት ድፍረት ባልነበራቸው የይሁዳ ልጆች ሁሉ ላይ ስታደርግ የኖርከው በዚሁ ዐይነት ነው፤ ይህች የይሁዳ ልጅ ግን የአንተ ክፉ ዝንባሌ ያልተዋጠላት ነች። አሁን እስቲ ንገረኝ በእነዚህ ሰዎች ላይ በድንገት የደረሳችሁባቸው በምን ዛፍ ሥር ሆነው ነው? አለው። እርሱም



በድንገት የደረሳችሁባቸው በምን ዛፍ ሥር ሆነው ነው? አለው። እርሱም በሮማን ዛፍ ሥር ነው አለ። ዳንኤልም በእውነት የሐሰተኛነት በደልህ በራስህ ላይ ነው፤ ሁለታችሁንም በሰይፍ ሰንጥቆ ሊያጠፋችሁ የእግዚአብሔር መልአክ እየጠበቀ ነው አለው።



ነቢዩ ዳንኤል ውሸታሞቹን ሽማግሌዎች እንዳጋለጠ፥ (የሶስና ታሪክ)

በዚህ ጊዜ በእርሱ የተማመኑትን ሁሉ የሚያድነውን አምላክ በማመስገን ሕዝቡ ሁሉ በአንድነት ድምፃቸውን አሰሙ። እነዚያንም ሁለት ሽማግሌዎች በሙሴ ሕግ በታዘዘው መሠረት ገደሉአቸው (ዘዳ:ም:19ቍ:16–19)። የሶስና ወላጆች፥ ባልዋና ዘመዶችዋ ሁሉ ምስጋናቸውን ለእግዚአብሔር አቀረቡ።

ከዚያን ቀን ጀምሮ ዳንኤል በሕዝብ ዘንድ ታላቅ አክብሮትን አገኘ። (የሶስናን ታሪክ ይመለከቷል)

<u>ሩት</u>:- በመሳፍንት ዘመን በእስራኤል አገር ራብ ሆነ። በዚህ ጊዜ ኤሊሜሌክ የሚባል አንድ የቤተልሔም ሰው ኑኃሚን ከምትባል ሚስቱ፥ ማሕሎንና ኬሌዎን ከሚባሉ ልጆቹ ጋር ሆኖ የራቡን ዘመን ለማሳለፍ ወደ ሞአብ አገር ሄደ። እዚያም ብዙ ዓመቶች ከኖረ በኋላ ኤሊሜሌክ ሞተ። ልጆቹ ማሕሎንና ኬሌዎን የሞአባውያን ሴቶች ልጆችን አግብተው ሁለቱም ልጅ ሳይወልዱ ሞቱ። ከዚያ በኋላ ኑኃሚን ከሁለቱ ምራቶችዋ ጋር ቀረች። እግዚአብሔርም ለእስራኤል ሕዝብ ምሕረት ማድረጉንና የራብ ዘመን ማለፉን

www.ethiopianorthodox.org

ኑኃሚን ሰምታ ወደ ሀገርዋ ለመመለስ ወሰነች። ለመሄድም በተነሣች ጊዜ ሁለቱ ምራቶችዋ አብረዋት መጡ። ወደ አንድ ቦታ ሲደርሱ ሁለቱን ምራቶችዋን ለሟቾች ባሎቻችሁና ለእኔ ስለዋላችሁት ውለታ እግዚአብሔር ዋጋችሁን ይክፈላችሁ፤ በሉ አሁን ወደ ወገናችሁ፥ ወደ እናቶቻችሁና ወደ አማልክቶቻችሁ ተመለሱ አለቻቸው። እነርሱ ግን ከአንቺ ጋር አብረን እንሄደለን ብለው አለቀሱ። እርስዋም አይሆንም ልጆቼ ከእኔ ጋር መጥታችሁ የምታገቡአቸው ባሎች የሚሆኑ ልጆች የሉኝም። ከእንግዲህ ወዲያም እንዳ ልወልድ አርጅቼአለሁ፤ ለመውለድስ ብችል አሁን ተወልዶ ዕድጎ ለእናንተ ባል ሊሆን የሚችል እስኪደርስ ልትጠብቁ ትችላላችሁን? እኔን እንደሆነ እግዚአብሔር በድሎኛል፤ እናንተ ግን ወደ እናቶቻችሁ ተመለሱ አለቻቸው። በዚህ ጊዜ ስቅስቅ ብለው አለቀሱ። ከዚያ በኋላ የሟች የኬሌዎን ሚስት የነበረችው ዖርፋ ዐማቷን ስማ ተሰናበተቻትና ተመለሰች። ሩት ግን ከዐማትዋ ላለመለየት ወሰነች። ኑኃሚንም ሩትን እንድትመለስ ብትነግራት ሩት እንዲህ አለቻት:- «ተለይቼሽ እንድመለስ አታስገድጅኝ፤ አብሬሽ እንድሄድ ፍቀጂልኝ፤ አንቺ ወደምትሄጂበት ሁሉ እሄዳለሁ፤ አንቺ በምትኖሪበት እኖራለሁ፤ ከአሁን ጀምሮ ሕዝብሽ ሕዝቤ ነው፤ አምላክሽም አምላኬ ነው፤ በምትሞቺበት እሞታለሁ፤ በምትቀበሪበትም እቀበራለሁ፤ ከሞት በቀር ከአንቺ የሚለየኝ የለም፤ ከአንቺ ለመለየት ባስብ እግዚአብሔር ይፍረድብኝ» አለቻት። ኑኃሚን የሩትን ቍርጥ ሐሳብ ባወቀች ጊዜ ከዚያ በኋላ ሌላ ነገር አልተናገረችም። አብረውም ሄደው ወደ ቤተልሔም ሲደርሱ የገብስ መከር የሚሰበሰብበት ጊዜ ነበር።

ከዕለታት አንድ ቀን ሩት ዐማትዋን እንዲህ አለቻት። መከር ወደሚሰበሰብባቸው እርሻዎች ሄጂ ቃርሚያ ልቃርም አለቻት። ዐማትዋም እሺ ሂጂ አለቻት። ሩትም ወደ አንድ እርሻ ሄዳ ስትቃርም እንደ አጋጣሚ የዚያ እርሻ ባለቤት ቦዔዝ የሚባል ሰው ነበር። ቦዔዘ የኑኃሚን ባል የኤሊሜሌክ የቅርብ ዘመድ ነበር። ቦዔዝ ሠራተኞቹን ለማበረታታትና ሥራውን ለማየት በመጣ ጊዜ ሩትን ስትቃርም አያትና ያቺ ወጣት ሴት ማናት? ብሎ የአጫጆቹን ኀላፊ ጠየቀ። እርሱም ለመቃረም እንድፈቅድላት ጠይቃኝ ከጧት ጀምራ ስትቃርም ነው የዋለችው፤ እርስዋም ኑኃሚንን ተከትላ ከሞአብ አገር የመጣች እንግዳ ነች አለው። ቦዔዝም አይዞሽ ልጄ ሴቶች ሠራተኞችን እየተከተልሽ እዚሁ ቃርሚ እንጂ ወደሌላ እርሻ አትሂጂ ብሎ መከራት። ወንዶች እንዳያስቸግሩሽ አስጠንቅቄአቸዋለሁ። ውሃም ሲጠማሽ ከእንስራዎቹ እየቀዳሽ ጠጪ አላት። ሩትም እጅ ነሥታ አመሰገነችው። ለዐማትዋ ያደረገችውንም መልካም ነገር በማንሣት አመሰገናት ። በምሳም ሰዓት ከአጫጆቹ ጋር እንድትበላ አደረጋት። ቀኑን ሙሉ የቃረመችውን እህልና የተረፋትን ምግብ ይዛ ወደ ዐማትዋ



መጣች። ስትቃርም የዋለችበት እርሻ የቦዔዝ መሆኑንና እርሱም ለእርስዋ ምን ያኽል ደግ እንደነበረ ነገረቻት። ኑኃሚንም ቦዔዝ የቅርብ ዘመድ ስለሆነ መውረስ ያለበት እርሱ መሆኑን ነገረቻት።



ሩትና ኑኃሚን (መጽሐፈ. ሩት)

ከዚያም በኋላ በዔዝ ሩትን በማግባት ለቅርብ ዘመዱ ለኤሊሜሌክ ዘር ለማስቀረት ተስማምቶ አገባትና ከእርስዋ ኢዮቤድን ወለደ፤ ኢዮቤድም የንጉሥ ዳዊት አያት ነው። መጽሐፉ የተጻፈው በነቢዩ ሳሙኤል እንደሆነ ይታመናል። (መጽሐፈ. ሩትን ይመለከቷል)

## ሐዲስ ኪዳን

ስለ ሰባት ዲያቆናት መመረጥ:- በሐዋርያት ዘመን ምእመናን የማኅበራዊ ኑሮ ይኖሩ ነበር። ብዙዎቹ የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ከአይሁዳዊነት ወደ ክርስትና የተዛወሩ ነበሩ። ከእነርሱም ከፊሎቹ የአይሁድ ቋንቋ ይናገሩ የነበረ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ የግሪክን ቋንቋ የሚናገሩ ነበሩ። ግሪክ ተናጋሪዎቹ በይሁዳ አገር ተወላጆች ላይ ስሞታ አሰሙ። ያሰሙትም ስሞታ እነዚያ በይሁዳ የተወለዱት አይሁድ በየቀኑ ይታደል በነበረው እርዳታ ግሪክኛ ቋንቋ ተናጋሪ የነበሩትን መበለቶች ችላ በማለት ይበድሉአቸው እንደነበረ ነው። በዚህ ጊዜ ሐዋ



www.ethiopianorthodox.org

ርያት ለችግሩ መፍትሔ እንዲሆን አንድ ሐሳብ አቀረቡ። ይኸውም ሐሳብ ከምእመናኑ መካከል በመንፈሳዊነታቸውና በመልካም ጠባያቸው የተመ ሰከረላቸው ሰባት ሰዎች ተመርጠው የማኅበራዊ አገልግሎቱን ኀላፊነት እንዲረከቡ ነው። በዚህም መሠረት ሰባት ዲያቆናት ተመረጡ። እነዚህ ሰባት ዲያቆናት እስጢፋኖስ፥ ፊልጶስ፥ ኒቃሮና፥ ጢሞና፥ ርሜ እና ኒቆላዎስ ናቸው። ከእነዚህ ከሰባቱ ዲያቆናት በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ሥራቸው ጉላ ብሎ የሚገኘው እስጢፋኖስና ፊልጶስ ናቸው (የሐ:ሥ:ም:6)።

እስጢፋኖስ:- እስጢፋኖስ ታዋቂ የሆነው በእርዳታ አከፋፋይነቱ ሳይሆን ክርስቲያኖች ካልሆኑ ሰዎች ጋር በመከራከሩ ነው። በተአምራት አድራጊነቱና በዚህም በተከራካሪነቱ ምክንያት በአይሁድ ሸንጎ ፊት ተከስሶ ቀረበ። መስካ ሪዎች መሰከሩበት የተባለው በሙሴ ሕግና በቤተ መቅደስ ላይ የስድብ ቃል ይናገራል ብለው ነው። እስጢፋኖስም በተከሰሰበት ጉዳይ መልስ ሲሰጥ አድማጮቹን የኦሪትን ሕግ እንደማይፈጽሙ አድርጎ ወቅሶአቸዋል። ለቤተ መቅደሱ ግን በቂ ግምት አልሰጠውም (ሐዋ:ሥ:ም:7ቍ47–50) ። ከቤተ መቅደሱ ይልቅ በምድረ በዳ ተንቀሳቃሺ የነበረውን የመገናኛ ድንኳን የበለጠ ያከበረ ይመስላል (ም:7ቍ:44–45)። በዚህም መሠረት ምናልባት የተከ ሰሰባቸው ጉዳዮች ተጋንነው የቀረቡት ሁሉም ሳይሆኑ አንዳንዶቹ ናቸው። በንግግሩም ዋነኛው ነጥብ እግዚአብሔር ለእስራኤል ሕዝብ በየጊዜው የፈጸ ማቸው የማዳን ሥራና የሕዝቡ ውለታቢስነት ነው። በዚህም ንግግሩ በድንጋይ ሊወገር በቅቶአል። እርሱ የመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን ሰማዕት ነው። ከእስጢፋኖስ መወገር በኋላ በቤተክርስቲያን ማለት በክርስቲያኖች ላይ ታላቅ ስደት ሆነ። ከስደቱም የተነሣ ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም ብቻ ሳይሆን በተለያዩ የዓለም ክፍሎች መስፋፋት ጀመረች። አይሁድ ብቻ ሳይሆኑ አረማውያንም ወደ ክርስትና እምነት ገቡ (የሐ:ሥ:ም:7)።





አይሁድ እስጢፋኖስን ወግረው ሲገድሉት (የሐ:ሥ:ም:7)

ፊልጶስ:- ፊልጶስ ወደሰማርያ ከተማ ሄዶ ስለክርስቶስ አስተማረ። የሚያስተምረውን ትምህርት በሰሙና የሚያደርጋቸውንም ተአምራት ባዩ ጊዜ ብዙ የሰማርያ ሰዎች እያመኑ ተጠመቁ። በዚያች አገር አንድ ሲሞን የሚባል ጠንቋይ ነበር። እርሱም በጥንቈላው ሕዝቡን ያስደንቃቸው ነበር። ብዙዎች ሰዎች አምነው በተጠመቁ ጊዜ ሲሞንም አምኖ በመጠመቅ ከዲያቆኑ ፊልጶስ ጋር ተባበረ።

የእግዚአብሔር መልአክ ፊልጶስን ተነሥና ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ በሚመስደው መንገድ ወደ ደቡብ ሂድ አለው። እርሱም ተነሥቶ ሄደ። እነሆ፥ የኢትዮጵያ ንግሥት የነበረችው የሕንደኬ የገንዘብ ቤትዋ ኀላፊ የነበረ ጃንደረባ ለመስገድ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ወደ አገሩ በመመለስ ላይ ነበር። እርሱም በሠረገላ ተቀምጦ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ እያነበበ ነበር። በዚህ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ፊልጶስን ወደ ሠረገላው እንዲቀርብ ነገረው። ፊልጶስም ወደ ሠረገላው ሲቀርብ ኢትዮጵያዊው የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ ሲያነብ ሰማው። ወደ ሠረገላውም ተጠግቶ የምታነብበው መጽሐፍ ትርጉም ይገባ ሃልን? ብሎ ጠየቀው። ኢትዮጵያዊውም የሚያስረዳኝ ሰው ሳይኖር እንዴት ሊገባኝ ይችላል አለውና ፊልጶስን በሠረገላው ላይ ወጥቶ እንዲቀመጥ ጋበ ዘው። ጃንደረባው ያነበበው የነበረው መጽሐፍ ክፍል እንዲህ የሚለውን ነበር።

«እርሱ ብዙ ግፍ ሲደርስበት መከራን ታግሦ ተቀበለ እንጂ አንድ ቃል እንኳ አልተናገረም፤ እርሱ ለመታረድ እንደሚወሰድ ጠቦትና እንደሚ

www.ethiopianorthodox.org

ሸለትም በግ ዝም አለ፤ አንድም ቃል አልተናገረም። እርሱ ተይዞ የግፍ ፍርድ ከተፈረደበት በኋላ ተወሰደ፤ ከዚህ ከሕያዋን ዓለም እንደ ተወገደና ስለ ሕዝቤ ኃጢአት እንዴት እንደተገደለ በዘመኑ ከሚኖሩ ሰዎች ማናቸውም ሊያስተውሉ አልቻሉም» (ኢሳ:53፥7-8)።

ጃንደረባውም ፊልጶስን «ነቢዩ ይህን የተናረው ስለራሱ ነውን? ወይስ ስለ ሌላ ሰው ነው? እባክህ ንገረኝ» ብሎ ጠየቀው። ፊልጶስም ከዚህ መጽሐፍ ጀምሮ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘርዝሮ አስረዳው። እየሄዱም ሳሉ ውሃ ወደ አለበት ቦታ ስለደረሱ ጃንደረባው እዚህ ውሃ አለ፤ እንዳልጠመቅ ምን የሚከለክለኝ ነገር አለ? ብሎ ጠየቀ። ፊልጶስም በፍጹም ልብህ ካመንክ ለመጠመቅ ትችላለህ አለው። ጃንደረባውም «ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን አምናለሁ» አለ።

ጃንደረባው ሠረገላው እንዲቆም አዘዘ፤ ሁለቱም ከሠረገላው ወርደው ፊልጶስ ጃንደረባውን አጠመቀው። ከውሃው ከወጡ በኋላ የእግዚአብሔር መንፈስ ፊልጶስን ወሰደው። ጃንደረባውም ዳግመኛ አላየውም። ግን በአዛጦን ተገኘ ወደ ቂሣርያም እስኪመጣ ድረስ ወንጌልን ያስተምር ነበር።



ፊልጶስና የሕንደኬው ጃንደረባ (የሐ:ሥ:ም:8)

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለመጨረሻ ወደ ኢየሩሳሌም በሄደ ጊዜ እግረ መንገዱን በቂሣርያ በኩል ሀልፎ በፊልጶስ ቤት ተቀምጦአል። ፊልጶስም



ትንቢት የመናገር ችሎታ ያላቸው አራት ያላገቡ ሴቶች ልጆች የነበሩት መሆኑ ተገልጦአል (የሐ:ሥ:ም:8)።

ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች የተላከው የመጀመሪያው የሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መልእክት:- ይህ መልእክት በ55 ዓ.ም በኤፌሶን እንደተጻፈ ይታመናል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህን መልእክት ለመጻፍ ከነሣሡት ምክንያቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል።

1. አሳፋሪ የሆነው የዝሙት ሥራ፥
2. በምእመናን ዘንድ አለ የተባለው መለያየትና ክርክር፥
3. የቆሮንቶስ ምእመናን ስለ ጋብቻ የጠየቁት ጥያቄ፥
4. ለጣዖት ስለተሠዋ ሥጋ፥
5. ማኅበራዊ አምልኮና መንፈሳዊ ስጦታዎች
6. ስለ ትንሣኤ ሙታን

ሰላምታ ካቀረበና እግዚአብሔርንም ካመሰገነ በኋላ በክርስቲያኖች መካከል ልዩነት እንዳይኖር ይመክራል። ልዩነቱም የተነሣው እኔ የጳውሎስ ነኝ፤ ወይም እኔ የአጵሎስ ነኝ፤ ወይም እኔ የጴጥሮስ ነኝ፤ ወይም እኔ የክርስቶስ ነኝ በማለት ወገን እየለዩ በመከራከራቸው ነው። ስለ እነርሱ የተሰቀለው ክርስቶስ እንጂ ሌላ አለመሆኑን ገለጠላቸው። በማጠቃለልም መልስ ሲሰጣቸው ሁሉ ነገር የእናንተ ስለሆነ ማንም በሰው አይመካ። ጳውሎስም ቢሆን፥ አጵሎስም ቢሆን፥ ጴጥሮስም ቢሆን፥ ዓለምም ቢሆን፥ ሕይወትም ቢሆን፥ ሞትም ቢሆን፥ አሁን ያለውም ቢሆን፥ በኋላ የሚመጣውም ቢሆን ሁሉም የእናንተ ነው፤ እናንተ ግን የክርስቶስ ናችሁ ብሎአቸዋል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ መልእክቱ ያነሣው ሌላው ጉዳይ ደግሞ በምእመናን ዘንድ ይሰማ የነበረው አሳፋሪ የዝሙት ሥራ ነው። ሐዋርያው በመልእክቱ በግልጽ እንዳመለከተው አንድ ሰው የእንጀራ እናቱን እንደሚስቱ አድርጎ ይዞአታል ብሎአል። እርሱ እንዳለው ይህ እንደዚህ ዐይነቱ የዝሙት ሥራ በአረማውያን ዘንድ እንኳ የማይደረግ ነው። እንደዚህ ዐይነቱን ሰው ሳይፈርዱበት በመዘግየታቸው ይወቅሳቸውና አሁንም ምንም እርሱ በሥጋ ከእነርሱ ጋር ባይሆን በመንፈስ ከእነርሱ ጋር ስለሆነ ያን በደል የሠራውን ሰው ከኅብረቱ ለመለየት በሚሰበሰቡበት ጊዜ በመካከላቸው እንዳለ እንዲቈጥሩት ገልጾላቸዋል።

የቆሮንቶስ ሰዎች ስለ ጋብቻ ለጠየቁት ጥያቄ መልስ ሰጥቶአቸዋል። የሚቻል ቢሆን እንደ እርሱ ሚስት ሳያገቡ ቢኖሩ ይመርጣል። የማይቻል ከሆነ



www.ethiopianorthodox.org

ግን ማግባት የሚሻል መሆኑን የሚገልጠው በሥጋ ፍትወት ከመቃጠል ይልቅ ማግባት የተሻለ ነው በማለት ነው። አለማግባት የተሻለ ነው ብሎ የሚመ ርጥበትን ምክንያት ሲያብራራ ሁለት የተለያዩ ሐሳቦችን ያቀርባል:-

የመጀመሪያው ሐሳብ ያለንበት የችግር ጊዜ ስለሆነ ሳያገቡ በብቸኝነት መኖር ይመረጣል። ማግባት ኃጢአት ነው ማለት ሳይሆን የሚያገቡ ሰዎች በዚህ ዓለም ብዙ የኑሮ ችግር ስለሚገጥማቸው የእኔ ምኞት ከዚህ ችግር እንድትድኑ ነው ብሏል።

ሁለተኛው ሐሳቡ ደግሞ ያገቡ ሰዎች ሚስታቸውን ወይም ባላቸውን ማስደሰት ስለሚፈልጉ በዚህ ዓለም ጉዳይ ላይ ብቻ ይጨነቃሉ። ሚስት ያላገባ ወንድና ባል ያላገባች ሴት የሚያስቡት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የሚያ ስደስቱበትን መንገድ ነው ብሏል።

ለጣዖት የታረደውን ሥጋ ስለመብላት ጉዳይ ሐዋርያው ሲያብራራ ጣዖት በዚህ ዓለም ከምንም እንደማይቈጠር ይገልጻል። አማልክት ሳይሆኑ አማልክት ተብለው የሚጠሩ በምድርም በሰማይም አሉ። እነርሱም እንደ ፀሐይ፥ ጨረቃ፥ ድንጋይና ዛፍን የመሳሰሉ ግዑዛን ነገሮች እንደመሆናቸው ሲሠዉላቸው፥ ሲመሰገኑ፥ ወይም ሲለመኑ የሚሰሙና የሚያዩ ወይም ስሜት ያላቸው ባለመሆናቸው ለእነርሱ በታረደው ሥጋ ላይ ሊያመጡ የሚችሉት ምንም ለውጥ አይኖርም። ስለዚህ እንደዚህ ያለውን ለጣዖት የተሠዋውን ሥጋ መብላትም ሆነ አለመብላት ምንም የሚያመጣው ጥቅምም ሆነ ጉዳት አይኖርም። እኛ የምናምነው የሁሉ ነገር ምንጭ በሆነው በእግዚአብሔር አብና ሁሉን ነገር ባስገኘው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ይህን የሚያውቁ ግን ሁሉም አይደሉም። ይሁን እንጂ ዕውቀት ያስታብያል ፍቅር ግን ያንጻል ብሏል። እኛ ለጣዖት የታረደው ሥጋ ምንም ልዩነት እንደሌለው ብናውቅም ይህን ዕውቀታችንን ግን በእምነቱ ደካማ የሆነውን ሰው የሚጐዳ ከሆነ ባንበላ ይሻላል ብሏል። በዕውቀቱ ጠንካራ ያልሆነው ሰው ለጣዖት የታረደው ሥጋ እንደማይጐዳ ኅሊናው ገና አጠናክሮ ስላላሳመነው ይጠራጠራል። እኛም በእንደዚህ ያለው ሰው ፊት ለጣዖት የታረደውን ሥጋ ብንበላ የኅሊና መሰናክል ስለምንሆንበት ለእርሱ ስንል ባንበላ ይሻላል ብሏል። ብንበላ ምንም የሚጨመ ርልን ነገር አይኖርም። ባንበላም ምንም የሚጐድልብን ነገር አይኖርም። ወንድማችንን ላለማሰናከል ግን ባንበላ ይሻላል።

ቀጥሎም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለማኅበራዊ አምልኮና ስለተለያዩ መንፈሳዊ ስጦታዎች ዘርዝሮ ይገልጻል። በአንድ ሰውነት ውስጥ የተለያዩ የአካል ክፍሎች ያሉ ቢሆንም ሰውነት ግን አንድ ነው በማለት የተለያዩ የመ ንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች ቢኖሩም መንፈስ ቅዱስ ግን አንድ ነው ብሎ በምሳሌ ያስረዳል። እንዲሁም የተለያየን ሰዎችም ብንሆን አንድ አካል ለመሆን በመ ንፈስ ቅዱስ ተጠምቀናል ብሏል። የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታዎች ሲዘረዝር በጥበብ የመናገር ችሎታ፥ በዕውቀት የመናገር ችሎታ፥ የመፈወስ ስጦታ፥ ተአምራት የማድረግ ስጦታ፥ ትንቢት የመናገር ችሎታ፥ ስጦታዎቹ ከመን ፈስ ቅዱስ ወይም ከርኩስ መንፈስ መሆናቸውን ለይቶ የማወቅ ችሎታ፥ ባልተለመደ ቋንቋ የመናገር ችሎታ፥ ባልተለመደ ቋንቋ የተነገረውን የመተ ርጐም ችሎታ ብሏል። ይህን ሁሉ የሚያደርገው አንዱ መንፈስ ቅዱስ ለያንዳንዱ የተለየ ስጦታ እንደሚሰጠው ተናግሮአል።

በአዲስ ቋንቋ መናገርን በተመለከተ ያ አዲስ ቋንቋ ተርጓሚ የሌለው ከሆነ ምንም ጥቅም እንደሌለው ገልጾአል። አዲስ ቋንቋ መናገርን ከትንቢት መናገር ጋር ሲያነጻጽረው ተንቢት ሰሚውን ያንጻል፤ አዲስ ቋንቋ ግን የሚያንጸው ተናጋሪውን ብቻ ነው ብሏል።

ማኅበራዊ የአምልኮ ሥርዓትን በተመለከተ መናገር ሲጀምር በወንድ ሁሉ ላይ ሥልጣን ያለው ክርስቶስ መሆኑንና በሚስት ላይ ሥልጣን ያለው ደግሞ ባል መሆኑን ይገልጣል። ስለዚህ ራስዋን ሳትከናነብ የምትጸልይ ወይም የትንቢት ቃል የምትናገር ሴት፥ በሴት ላይ ሥልጣን ያለውን ወንድን ታዋር ዳለች። ሴትም መከናነብ ያለባት በወንድ ሥልጣን ሥር መሆንዋን ለማሳየት ነው፤ ወንድ ግን የእግዚአብሔር መልክና የእግዚአብሔር ክብር የሚገለጥበት ስለሆነ መከናነብ አይገባውም ብሏል። ይህንንም በዘመኑ ከነበረው ባህል ጋር እያነጻጸረ ገለጻ አድርጓል። እንዲሁም ሴቶች በጸሎት ስብሰባ ጊዜ ዝም ይበሉ ብሏል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በዚህ መልእክቱ በጣም ያተኰረበት ጉዳይ የሙታንን ትንሣኤ በተመለከተ ነው። ገለጻውንም መነሻ ያደረገው የክርስቶስን ከሞት መነሣት ነው። የሙታን ትንሣኤ የለም ለሚሉ ሰዎች መልስ መስጠቱን ሲጀምር ክርስቶስ ከሞት እንደተነሣ የምናምን ከሆነ እንዴት የሙታን ትንሣኤ የለም ይባላል? ብሎ በመጠየቅ ሙታን የማይነሡ ከሆነ ክርስቶስም ከሞት አልተነሣም ማለት ነው ይላል። ሞት በአዳም እንደመጣ ከሞት መነሣትም በክርስቶስ ይመጣል ብሎአል። እነዚያ የሙታን ትንሣኤ የለም እንደሚሉት እኛ በክርስቶስ የምናምነው ለዚህ ዓለም ሕይወታችን ብቻ ከሆነ በጣም ሊታዘልን የምንገባ ሰዎች ነን ብሏል። ሕይወትም ዋጋቢስ ስለሚሆን በሉ ነገ የምንሞት ስለሆነ ዛሬ እንብላ እንጠጣ እንደተባለው ከከብቶች ያልተሻለ ኑሮ ይሆናል።


www.ethiopianorthodox.org

ታዲያ፥ ሰዎች ከሞት ሲነሡ እንዴት ሆነው ነው? ተብሎ ቢጠየቅ ልክ እንደሚዘራ የእህል ዘር ምሳሌ ነው። አንዱ ዘር ሲዘራ የሚበቅለው የተለየ አካል ይዞ ነው። ይህንንም ለማድረግ እህሉ መሞት አለበት።

በዚሁም ዐይነት ከሞት የሚነሡትን ሰዎች ሁኔታ ለማመሳሰል ይቻላል። የሚጠፋ ሟች አካል ሆኖ የተዘራው የማይጠፋ ሕያው አካል ሆኖ ይነሣል፤ በውርደት የተዘራው በክብር ይነሣል፤ ደካማ ሆኖ የተዘራው ኀይለኛ ሆኖ ይነሣል፤ ሥጋዊ አካል ሆኖ የተዘራው መንፈሳዊ አካል ሆኖ ይነሣል።

ሁላችንም አንሞትም፤ ነገር ግን ሁላችንም እንለወጣለን ። የምንለወጠውም የመጨረሻው መለከት በሚነፋበት ጊዜ እንደ ዐይን ቅጽበት በአንድ ጊዜ ነው። መለከቱ ይነፋል፤ የሞቱት ሰዎች የማይጠፉ ሕያዋን ሆነው ይነሣሉ፤ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን መልበስ አለበት ብሎአል።

ከነዚህም ሌላ ዐልፎ ዐልፎ ማወቅ የሚገቡንን ጉዳዮች አነሣሥቶአል።

ለምሳሌ ቅዱስ ቍርባንን በተመለከተ እንዲህ ይላል:- እግዚአብሔርን አመስግነን የምንካፈለው የበረከት ጽዋ ከክርስቶስ ደም ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን? አብረን የምንቈርሰውስ ኅብስት ከክርስቶስ ሥጋ ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን? ኅብስቱ አንድ በመሆኑ እኛም ከዚህ ከአንዱ ኅብስት የምንካፈል ስለሆንን ምንም እንኳ ብዙዎች ብንሆን አንድ አካል ነን» (1ኛ: ቆሮ:10፥16–17)።

ቍርባንም ምን ያኽል ክብር እንዳለው ሲገልጥ እንዲህ ብሏል:- «ማንም ሰው ያልተገባው ሆኖ ሳለ የጌታን ኅብስት ቢበላና የጌታንም ጽዋ ቢጠጣ የጌታን ሥጋና ደም በማቃለሉ ይጠየቅበታል፤ ስለዚህ ማንም ሰው ይህን ኅብስት ከመብላቱና ይህንንም ጽዋ ከመጠጣቱ በፊት ራሱን መመርመር አለበት» (1ኛ:ቆሮ:ም:11ቍ:27–28)።

በሐዋርያት ዘመን የነበረውንም የአገልግሎት ሥርዓት ሲያመለክት እንዲህ ብሏል:- «ስለዚህ እግዚአብሔር እያንዳንዱ ሰው በቤተ ክርስቲያን የተለያየ አገልግሎት እንዲኖረው አድርጎአል፤ በዚህም መሠረት፥ በመጀመሪያ ሐዋርያትን፥ ሁለተኛ ነቢያትን፥ ሦስተኛ መምህራንን ሾሞአል። ቀጥሎም ተአምራት የሚያደርጉትን፥ቀጥሎም የመፈወስ ስጦታ ያላቸውን፥ ቀጥሎም የማስተዳደር ችሎታ ያላቸውን፥ ቀጥሎም በተለያዩ ቋንቋዎች የመናገር ችሎታ ያላቸውን ሰዎች መድቦአል»(1ኛ:ቆሮ ም:12ቍ:28)።

ከማንኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በለፍቅር ተዘርዝሮ የተገለጠበት ቦታ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት እንዳለው ያለ አይገኝም፡



www.ethiopianorthodox.org

<u>የይሁዳ መልእክት</u> :- ይህ ይሁዳ የጌታ ወንድሞች ተብለው ከተጠቀሱት አንዱ ነው። መልእክቱን የጻፈው በ64 እና በ55 ዓ.ም. መካከል እንደሆነ ይታመናል። መልእክቱን የጻፈው ለማን እንደሆነ አልገለጸውም። አንዳንድ ምሁራን መልእክቱን የጻፈው ለአይሁድ ክርስቲያኖች ነው ሲሉ ሌሎች ደግሞ ለአረማውያን ክርስቲያኖች ነው ብለዋል።

መልእክቱን ለምን እንደጻፈው ሲገልጽ በመጀመሪያ ስለጋራ ደኅንነት ለመጻፍ አስቦ የነበረ መሆኑን ያመለክታል። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ጸጋ ወደ ስድነታቸው የሚለውጡና የጌታችንንም መሲሕነት የሚክዱ ወገኖች ሾልከው ስለገቡ ከእነርሱ ጥንቃቄ እንዲያደርጉና እንዲታገሉ ለመምከር መጻፍ ግድ እንደሆነበት ይገልጣል።

ኋላም መለስ ብሎ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዴት ከግብጽ አውጥቶ እንዳዳነና ያላመኑትንም እንዴት እንደ አጠፋቸው ይዘረዝራል። ማዕርጋቸውንና ቦታቸውን ያልጠበቁት መላእክት እንዴት እግዚአብሔር እስከ መጨረሻው ፍርድ ቀን ድረስ በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ጠብቆ ማቈየቱን ይናገራል። እንዲሁም የሰዶምና የገሞራ ሰዎች ኃጢአት የዘለዓለም ቅጣት ለሚቀጡ ሰዎች ምሳሌ ያደረጋቸው መሆኑን ይገልጣል።

በዚሁም ዓይነት እነዚያ ሾልከው ገቡ ያላቸው ሰዎች ሥጋቸውን እንደሚያረክሱ፥ የእግዚአብሔርን ሥልጣን እንደሚንቁና በሰማይ ክብር ያላቸውን እንደሚነቅፉ ያጋልጣቸዋል። ይህንንም ኃጢአታቸውን ከዐቅማቸው በላይ እንደሚሠሩት ምሳሌ ሲሰጥ የመላእክት አለቃ ሚካኤል እንኳ ከዲያብሎስ ጋር ስለሙሴ ሥጋ በሚከራከርበት ጊዜ እግዚአብሔር ይገሥጽህ አለው እንጂ የስድብ ቃል አልተናገረም ብሏል። እነዚህ ሰዎች ግን ለማስተዋል ያቃታቸውን ነገር ሁሉ ይሳደባሉ በማለት ማንነታቸውን አጋልጦአል።

በዚህም ምክንያት ሔኖክ ስለእነዚህ ሰዎች:- «እነሆ ጌታ ከብዙ ሺህ ቅዱሳን ጋር ይመጣል። የሚመጣውም በሰው ሁሉ ላይ ሊፈርድ፥ ዐመፀኞችንና ኃጢአተኞችን ሁሉ ከዐምፅ ሥራቸው ሁሉና በእግዚአብሔር ላይ በተናገሩት የስድብ ቃል ሁሉ ሊወቅስ ነው ብሎ ትንቢት መናገሩን ይገልጣል (ሔኖክ:1፥9)። በዚህም መሠረት እነርሱ እንዲጠነቀቁና ደካሞችን እንዲያበረቱ ምክር በመስጠት መልእክቱን ይፈጽማል።

## ከዚህ ምዕራፍ የምናገኘው ትምህርት

ምንም እንኳ የመንፈሳዊ ሕይወት መመሪያዎች በጽሑፍ የሰፈሩት በሙሴ ጊዜ ቢሆን ከሙሴ በፊትም በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ጠንካሮች ሰዎች የነበሩ መሆናቸውን በዮሴፍ ምሳሌነት ልንረዳ እንችላለን። ይህም የሚያመለክተው ከሙሴ በፊት በነበሩት ዘመናት የመንፈሳዊ ሕይወት መመሪያ የሚገኘው ከትውልድ ወደ ትው ከትውፊት መሆኑን ነው። ይህም ማለት መመሪያዎች ከትውልድ ወደ ትው ልድ በቃል ይተላለፉ ነበር ማለት ነው። በዚያ በወጣትነት ዕድሜው ዮሴፍ የሥጋ ፍትወትን ፈተና ለመቋቋም መቻሉ ምን ያኽል የመንፈሳዊ ስሜት ጥን ካሬ የነበረው መሆኑን እንገምት።

ቀድሞም ሆነ በኋላ ዘመን እንደእነዮሴፍ ያሉትን መንፈሰ ጠንካሮች ሰዎች እግዚአብሔር ይጠቀምባቸዋል። የግብጽን ሕዝብና የያዕቆብን ቤተሰብ ከረሀብ አደጋ ለማዳን እግዚአብሔር በዮሴፍ ተጠቀመ። ዮሴፍም ከልጅነቱ ጀምሮ የእግዚአብሔር ምርጥ ዕቃ ስለነበረ ወደፊት የሚሆኑትን ነገሮች ሁሉ በሕልም ይገልጥለት ነበር። ሁለት ጊዜ በታዩት ሕልሞቹ መሠረት ወንድሞቹ ሁሉ ወደ ግብጽ መጥተው ሰገዱለት፤ ጌታችን ብለውም አከበሩት። እውነተኛን ሰው እግዚአብሔር በጥበቡ ይጠብቀዋል። ለምሳሌ የጲጥፋራ ሚስት የከሰሰችው በቻለ የሐሰት ክስ እርሱ በባሪያነት የተገዛ እንደመሆኑ በሞት ሊያስቀጣው በቻለ ነበር። ነገር ግን የእግዚአብሔር ጥበቃ ከእርሱ ጋር ስለነበረ ወደ እስር ቤት ተላከ እንጂ አልተገደለም። ያም እስር ቤት የእርሱ ማንነት ታውቆ ለከፍተኛ ማዕረግ የሚበቃበት ቦታ ሆነ።

የሰው ልጅ ምንም ያኽል በጎ ተግባርና መንፈሳዊነት ቢኖረው ፍጹም መሆን ግን አይችልም። ፍጹምነት ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው። በዚህም መሠረት ዮሴፍ አንድ ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነት አጓድሎ የሰውን እርዳታ ፈለገ። ይህንንም ያደረገው የፈርዖንን የጠጅ አሳላፊ ሕልም በተረጐመ ጊዜ ነው። የጠጅ አሳላፊውን ለፈርዖን ነግሮለት ከእስራቱ እንዲ ያስፈታው ዐደራ አለው። ወላጅ አባት የሚወድደውን ልጁን በአርጩሜ እንደሚቀጣው ሁሉ እግዚአብሔርም ወዳጆቹን በአንዳንድ ጥቃቅን ነገሮች ሲያጠፉ በአንዳንድ ምድራዊ ቅጣት ይቀጣቸዋል። በዚህም መሠረት የፈርዖን ጠጅ አሳላፊ ከተፈታ በኋላ ዮሴፍን የሚያስታውሰው አጥቶ ለሁለት ዓመት በእስር ቤት ቈየ። ያችም የአባት አርጩሜ የሆነችው ሁለት ዓመት ካለፈች ... በኋላ እግዚአብሔር ዮሴፍን አስታወሰውና ችግሩን አስወገደለት። ያለ... ችግሩን ሁሉ የሚያስረሳ ክብር ሰጠው። ይህም የሚያመለክተው እግዚአብሔር ወዳጆቹን በሰማያዊ ብቻ ሳይሆን በምድራዊ ክብርም የሚያበለጽግበት ሁ... መኖሩን ነው።



የሶስናን ታሪክ ስንመለከት ብዙ ቁምነገሮችን እንማራለን። ትልቁና ዋነኛው ትምህርት የእግዚአብሔር ጸሎት ተቀባይነት ነው። እግዚአብሔር የሶስናን ጸሎት ሰምቶ ወደምትገደልበት ቦታ ስትወሰድ በዳንኤል ውስጥ መንፈሱን አሳረፈበት። ይህም ሁናቴ በጌታችን በቀኝ በኩል ተሰቅሎ ከነበረውና በመጨረሻው ደቂቃ እግዚአብሔር ኃጢአቱን ይቅር ካለለት ሰው ሁናቴ ጋር ተመሳሳይነት አለው።

ሌላው ትምህርት ደግሞ እውነት በሐሰት ላይ የሚኖረውን ድል አድራጊነት ያመለክታል። ሐሰተኛም ሰው ይዋል ይደር እንጂ አንድ ጊዜ ሳይጋለጥ አይቀርም። የእግዚአብሔርም ዕውቀት በጊዜና በቦታ የማይወሰን ስለሆነ አምላክ የሽማግሌዎቹን ተንኰል ተመልክቶ በዳንኤል ላይ መንፈሱን አሳረፈበት።

በዚህም ዐይነት በእግዚአብሔር ፈቃድ ጸንተን ለሕግጋቱ ታማኞች ከሆንን እግዚአብሔር ራሱ በሚወስነው ጊዜ ተገቢ ዋጋችንን እናገኛለን። ሐሰተኛም ሆነ ሌላ ኃጢአት የሚሠራ ሰው ቅጣቱን እግዚአብሔር በሚወስነው ጊዜ ይቀበላል።

ሞአባዊትዋ ሩት የፍቅርና የታማኝነት ምሳሌ ነች። የሩት ታሪክ ከዕዝራና ከነህምያ አስተሳሰብ ወጥቶ ከሌሎች ዘሮች ጋር የመገናኘትን በር የሚከፍት ነው። እነዕዝራ የሌሎች አገሮች ሴቶችን ያገቡ፥ ልጅ እንኳ የወለዱ ቢሆኑ እንዲፋቱ ነው ያስገደዱአቸው። ሌላ ምንም ምርጫ አልሰጡአቸውም። እንደ ሩት ላሉ አገርሽ አገሬ፥ ሕዝብሽ ሕዝቤ፥ አምላክሽ አምላኪ ነው ለሚሉ አዲስ አማንያን ዕዝራና ነህምያ ዕድል አልሰጡአቸውም። ሩት ግን ቦዔዝን አግብታ የንጉሥ ዳዊትን አያት ኢዮቤድን ወልዳለች። ክርስቶስም በሥጋ የተወለደው ከእርስዋ በመጣ የዘር ሐረግ ነው። ይህም የሚያመለክተው እግዚአብሔር ለሁሉም እኩል እንጂ ዘር የማይለይ መሆኑን ነው።

ሌላው ከሩት ታሪክ የምንማረው ትምህርት ደግሞ ለወዳጁ ከልብ በመነጨ ፍቅር እስከመጨረሻው ታማኝ የሚሆን ሰው እግዚአብሔር ዋጋውን የሚከፍለው መሆኑን ነው። ሩት የዕለት ምግብዋን እንኳ ለማግኘት ከእህል አጫጆች እግር፥ አግር እየተከተለች ቃርሚያ የምትቃርም እንጂ ምንም ነገር የሌላት ድኻ ነበረች። እግዚአብሔር ግን የቅንነት ዋጋዋን ሲከፍላት በጥቂት ጊዜ ውስጥ የሀብታሙ የቦዔዝ ሚስት ለመሆን አበቃት።

በሐዋርያት ዘመን የዲያቆናት መመረጥ የሚያመለክተው ቤተ ክርስቲያን ከመነሻዋ ጀምራ በሥነ ሥርዓት የምትመራ መሆንዋን ነው። ሐዋርያት የማስተማሪያ ጊዜአቸውን እንዳይሻማ የእርዳታ አስጣጡን ተግባር የሚያ

www.ethiopianorthodox.org

ከናውኑ ዲያቆናትን መምረጥ ነበረባቸው። ለተመራጭነት የሚያበቃውም ቅድመ ግዴታ መንፈሳዊነትና መልካም ጠባይ ስለነበረ እነዚህ ተመራጮች በተለየም እስጢፋኖስና ፊልጶስ ከእርዳታ ማከፋፈሉ ሥራ ዐልፈው ታላላቅ ተግባሮችን አከናውነዋል። ሁለቱም በተአምራት ሥራቸው የተደነቁ ነበሩ። እስጢፋኖስ የመጀመሪያው ሰማዕት በመሆን ለቤተ ክርስቲያን ሕይወቱን ሰጥቶላታል። ፊልጶስም ብዙ የማስተማር ሥራ በመሥራት ብዙዎችን ወደ ክርስትናው ቤተሰብነት መልሶአል። በእስጢፋኖስ መገደል ምክንያት ምእመናን ወደ ተለያዩ የዓለም ክፍሎች ስለተበታተኑ ክርስትና በዚያው መጠን እየተስፋፋ ሄዷል። ፊልጶስ ብዙ ሰማርያውያንን ያስተማረና ያሳመነ ከመሆኑም በላይ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ለማጥመቅ በቅቶአል። ይህም የሚያመለክተው መንፈሳዊ አመራረጥ አብዛኛውን ጊዜ መንፈሳዊ ውጤት የሚያመጣ መሆኑን ነው።

ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች በላከው መልእክቱ ብዙ ያልተብራሩ ነገሮችን ያብራራል። በጣም አሳፋሪ የሆኑ ሥራዎች ሲሠሩ ምእመናን ምን ማድረግ እንደሚገባቸው ገልጾላቸዋል። ራሳቸውን ከእግዚአብሔር ጋር ሳይሆን ከእግዚአብሔር አገልጋዮች ጋር በማጣመር መለያየታቸው ትክክል አለመሆኑን ያስረዳቸዋል። የቆሮንቶስ ሰዎች የጠየቋቸውን የተለያዩ ጥያቄዎች በማብራራት ያስረዳል። ለጣዖት ስለተሠዋ ሥጋ ምን መደረግ እንዳለበት ዘርዝሮ አስረድቶአል። በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ ስለ አዲስ ቋንቋ መናገር ያለውን የተሳሳተ ግንዛቤ ያብራራል። እንዲሁም ትንሣኤ ሙታን አይኖርም ብለው ለሚያምኑና ለሚያስተምሩ ሰዎች የተሟላ መልስ ሰጥቶአቸዋል።

## ጥያቄዎች

1. የያዕቆብ ልጅ ዲናን ያስነወራት ማን ይባላል?
2. ካስነወራትስ በኋላ ምን ፈለገ?
3. ያዕቆብ በሴኬም የሰፈረበትን ቦታ ከማን ገዛው?
4. የበቀል እርምጃ የወሰዱት ማንና ማን ናቸው?
5. የወሰዱትስ ምን ዐይነት የበቀል እርምጃ ነበር?
6. ሌሎቹ ወንድሞችስ ምን አደረጉ?
7. ዐሥራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች እነማን ናቸው?
8. እናቶቻቸውስ እነማን ነበሩ?
9. ወንድሞቹ ዮሴፍን ለምን ጠሉት?



10. ዮሴፍ ያያቸው ሁለት ሕልሞች ምንና ምን ናቸው?
11. ወንድሞቹ ሕልሙን በነገራቸው ጊዜ ምን አሉት?
12. ያዕቆብ ዮሴፍን ወዴት ላከው?
13. የዮሴፍ ወንድሞች በሩቅ ሲያዩት ምን ተባባሉ?
14. ወንድሞቹ ዮሴፍን ምን አደረጉት?
15. ለድርጊታቸውስ ምን ምክንያት ሰጡ?
16. ዮሴፍ ወዴት ተወሰደ?
17. የጲጥፋራ ሚስትስ ዮሴፍን ለምን ወደደችው?
18. በዮሴፍ ምክንያት የጲጥፋራ ቤት ምን ሆነ?
19. የጲጥፋራ ሚስት ዮሴፍን ምን እንዲያደርግ ጠየቀችው?
20. ዮሴፍስ በሐሳብዋ ተስማማን?
21. በመጨረሻስ ምን አደረገችው?
22. የፈርዖን የጠጅ አሳላፊና የእንጀራ ቤት ኀላፊ ምን ሆኑ?
23. ዮሴፍስ እነርሱን በምን ሁናቴ ረዳቸው?
24. የጠጅ አሳላፊው ምን ሆነ?
25. የእንጀራ ቤቱ ኀላፊውስ ምን ሆነ?
26. የጠጅ አሳላፊው ዮሴፍን እንዴት ረዳው?
27. ዮሴፍ የጠጅ አሳላፊውን በምን ጉዳይ ዐደራ ብሎት ነበር?
28. ፈርዖን ያያቸው ሁለት ሕልሞች ምንና ምን ናቸው?
29. የግብጽ አስማተኞችና ጠቢባን ሕልሙን ለመተርጐም ቻሉን?
30. ዮሴፍ ሕልሙን በመተርጐሙ ምን አገኘ?
31. የሕልሙስ ትርጉም ምን ነበር?
32. ሁናቴው ዮሴፍ እንደተረጐመው ሆነን?
33. ሁናቴውን በተመለከተ ጊዜ ዮሴፍ ያደረገው ድርጊት ምንድነው?
34. የዮሴፍ ወንድሞች ለምን ወደ ግብጽ መጡ?



www.ethiopianorthodox.org

35. ወደ ግብጽ የመጡት ዐሥሩ አንዱም ወንድሞቹ ናቸውን? ካልሆነ ለምን?

36. ወንድሞቹ ከዮሴፍ ጋር የተገናኙት እንደምን ነበር?

37. ዮሴፍ ወንድሞቹን ዐወቃቸውን?

38. እነርሱስ ዐወቁትን?

39. ዮሴፍ ወንድሞቹን ምን አላቸው?

40. እነርሱስ ምን መልስ ሰጡ?

41. ከመልሳቸው ተነሥቶ ምን ወሰነ? ምንስ አደረገ?

42. ወንድሞቹ ብንያምን ይዘው በተመለሱ ጊዜ ዮሴፍ ምን አደረገ?

43. ለወንድሞቹ ምን ሰጣቸው? ለአባቱስ ምን ላከ?

44. ለአባቱና ለቤተሰቡ መምጫ ምን ላከ?

45. ያዕቆብና ልጆቹ በግብጽ ምን በሚባል ስፍራ ኖሩ?

46. ያዕቆብ በግብጽ ስንት ዓመት ኖረ?

47. ያዕቆብ በሞተ ጊዜ ዕድሜው ስንት ነበር?

48. ያዕቆብ የት ተቀበረ?

49. ያዕቆብ በግብጽ ምድር ያልተቀበረው ለምንድነው?

50. ዮሴፍ ከመሞቱ በፊት ለእስራኤላውያን ወንድሞቹ ቃል ያስገባቸው ምን ብሎ ነው?

51. የሶስና ባል ስሙ ማን ይባል ነበር? አባትዋስ?

52. የሶስና ወላጆች እንደምን አድርገው አሳድገዋት ነበር?

53. ሁለቱ ዳኞች ሶስናን ይመኙዋት የነበረው ለምንድነው?

54. ሶስና ሁለቱን አገልጋዮችዋን ምን ብላ ላከቻቸው?

55. ሁለቱ ዳኞች ጥያቄአቸው ሳይሳካ በመቅረቱ ምን ብለው ከሰሱአት? በዚህስ ምን ተፈረደባት?

56. እርስዋስ ምን መልስ ሰጠቻቸው?

57. ሕዝቡ ሁሉ እየሰማ ምን ብላ ጸለየች?

58. ሕዝቡ እነዚያን ከሳሾች ለምን አመናቸው?

59. ዳንኤል በከፍተኛ ድምፅ ምን ብሎ ተናገረ?

60. በዚህ ጊዜ ሰዎች ምን ብለው ጠየቁት?

61. እርሱስ ምን መልስ ሰጠ? ምንስ ሐሳብ አቀረበ?

62. ዳንኤል በሶስና ከሳሾች ላይ ምን ዐይነት ጥያቄ ጠይቆ ሐሰተኞች መሆናቸውን አጋለጠ?

63. በዚህ ጊዜ የሕዝቡ ስሜት እንዴት ነበር?

64. ሕዝቡስ በሁለቱ ዳኞች ላይ ምን እርምጃ ወሰደ?

65. ከዚያን ቀን ጀምሮ በዳንኤል ላይ የሕዝቡ ስሜት እንዴት ሆነ?

66. የኤሊሜሌክ ቤተሰብ ለምን ወደ ሞአብ አገር ሄደ?

67. የኤሊሜሌክ ሁለት ልጆች ማንና ማን ይባሉ ነበር?

68. የሁለቱ ልጆቹ ሚስቶችስ ማንና ማን ይባሉ ነበር?

69. ኑኃሚን ወደ አገርዋ ለመመለስ የወሰነችው መቼ ነው?

70. ኑኃሚን ወደ አገርዋ ለመመለስ በወሰነች ጊዜ ምራቶችዋ ምን አልዋት?

71. እርስዋስ ምን መልስ ሰጠቻቸው?

72. ተሰናብታት ወደ ዘመዶችዋ የተመለሰችው ማን ናት?

73. ከናዖሚ ጋር ለመሄድ የወሰነችው ማን ናት?

74. ናዖሚ ወደ አገርዋ ስትደርስ የምን ጊዜ ነበር?

75. ሩት በማን እርሻ ውስጥ ነው የእህል ቃርሚያ ስትሰበስብ የዋለችው።

76. ዐማትዋስ ምን መከረቻት?

77. የምክሩ ውጤት ምን ሆነ?

78. መጽሐፈ ሩትን የጻፈ ማነው?

79. በሐዋርያት ዘመን ዲያቆናት የተመረጡት በምን ምክንያት ነው? እነርሱስ እነማን ናቸው?

80. ከዲያቆናቱ መከከል በአይሁድ ሸንጎ ፊት የተከሰሰው ማነው? ለምንስ ተከሰሰ?


www.ethiopianorthodox.org

81. በመጨረሻስ ምን ሆነ?

82. ፊልጶስ ወዴት ሄዶ አስተማረ?

83. በዚያስ አገር ማን የሚባል ጠንቋይ ነበር?

84. ፊልጶስ የሠራው ሌላ ሥራ ምንድነው?

85. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በመጀመሪያ መልእክት የጻፈው የት ሆኖ ነው?

86. ሐዋርያው አሳፋሪ የዝሙት ሥራ ያለው ምኑን ነው?

87. የቆሮንቶስ ሰዎች ስለ ጋብቻ ምን ብለው ጠየቁት?

88. በምእመናን ዘንድ አለ የተባለው መለያየትና ክርክር ምን ዐይነት ነበር?

89. ቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ስጦታዎች ያላቸውን ዘርዝር

90. ለጣዖት ስለተሠዋ ሥጋ ምን መመሪያ ሰጠ?

91. በአዲስ ቋንቋ ስለመናገርስ ምን መመሪያ ሰጠ?

92. ስለ ሙታን መነሣት የሰጠው ምሳሌ ምንድነው?

93. የቅዱስ ቍርባንን ክብር የገለጠው እንዴት ነው?

94. የይሁዳን መልእክት የጻፈው የትኛው ይሁዳ ነው?

95. መልአኩን ሚካኤልን የጠቀሰው በምን ምክንያት ነው?

96. ሔኖክንስ በምን ምክንያት ጠቀሰው?

# ምዕራፍ 3

## ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ

በዚህ መዕራፍ ውስጥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማራቸው ትምህርቶች፥ የሰጣቸው ምሳሌዎችና ያደረጋቸው ተአምራት ይገኙበታል።

### በጌታችን የቀረቡ የተለያዩ ትምህርቶች

የተራራው ላይ ትምህርት:- ይህ አንድ ወጥ ረጅም ትምህርት የተራራ ላይ ትምህርት የተባለው ከገሊላ በአንድዋ ተራራማ ቦታ ላይ ሆኖ ስላስ



www.ethiopianorthodox.org

ተማረው ነው። ይህም ትምህርት ለክርስቲያናዊ ሕይወት እንደ ሕገ መንግሥት ነው።

ጌታችንም ትምህርቱን የጀመረው በአንቀጸ ብፁዓን ነው። የአንቀጸ ብፁዓኑም መመዘኛ ከንቱ የሆነው ምድራዊ መመዘኛ ሳይሆን ከፍተኛው መመዘኛ ነው።

ደስታ የሰው ልጅ ሁሉ ምኞት ሲሆን የደስታን ምንጭ ለማወቅ ግን ብዙዎች ይሳሳታሉ። ሀብት፥ ብልጽግና፥ ሹመት በሚገኝበት ቦታ ደስታ ያለ ይመስላቸዋል። የጌታችን አባባል ግን ከዚህ የተለየ ነው።

በመንፈስ ድኾች:– በዚህ ዓለም ሀብት ድኻ የመሆን ጉዳይ ሳይሆን፥ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው የሚያስቡ፥ ችግርን በትዕግሥት የሚያሳልፉ፥ እነርሱ የክርስቶስ ቤተሰብ ናቸው።

የሚያዝኑ:- ሐዘናቸው ስለዓለማዊ ጉዳይ ሳይሆን ነገር ግን ስለ ኃጢአታቸው በመጸጸት፥ ስለሌሎች በማዘን፥ እነዚህ የሚጽናኑት በዚህች ምድር ሳይሆን በሰማይ ነው።

ትሑቶች:– ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ዝቅ አድርገው የሚያስገዙ፥ ምንም ዐይነት ችግርና መከራ ቢያመጡባቸው ለሰዎች ሁሉ ትሑት መሆን፥ እንደዚህ ያሉት በሰማይ ብቻ ሳይሆን በምድር እንኳ ዋጋቸውን ያገኛሉ።

ስለ ጽድቅ የሚራቡና የሚጠሙ: – ማለት መንፈሳዊ በረከትን የሚናፍቁ ለእነርሱ እግዚአብሔር ፍላጎታቸውን ያረካላቸዋል።

ከመንፈሳዊነትና ከፍቅር የተነሣ ለሚበድሉአቸውና ለሚያታልሉአቸው ይቅታ የሚያደርጉ :– እነዚህ ከእግዚአብሔርም ከሰውም ምሕረትን ያገኛሉ።

ልበ ንጹሖች: – በምንም ሁናቴ ሐሳባቸው ርኩሰት የሌለበት ወይም ምንም ዐይነት ክፉ ዝንባሌ የሌላቸው:- እነዚህ ንጹሖች በመሆናቸው እግዚአብሔርን ፊት ለፊት ያዩታል።

ሰላምን የሚያደርጉ:– ማለት በእነርሱና በእግዚአብሔር መካከል፥ በእነርሱና በሰዎች መካከል፥ በራሳቸውና በነፍሳቸው መካከል ሰላም እንዲሰፍን የሚያደርጉ እነርሱ ሰላምን በማድረግ እግዚአብሔርን ስለሚመስሉት የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉ።

ስለ እውነት የሚሳደዱ :– ማለት በእግዚአብሔርና በትእዛዛቱ ምክንያት፥ ስለክርስቶስ መሰደብና በሐሰት መከሰስ የሚደርስባቸው እነርሱ በመንግሥተ ሰማይ ዋጋቸው ትልቅ ነው።

ጌታም ደቀ መዛሙርቱን የሚደርስባቸውን ነገር ሁሉ በትዕግሥት እንዲቀበሉት አበረታታቸው።

ለኦሪት ሕግና ለነቢያት ትንቢት ቀናተኛ ለሆኑ ሰዎች ሲያረጋግጥላቸው እርሱ ሕግጋቱን ለመፈጸም እንደመጣ ገለጠላቸው።

ጸሐፍትና ፈሪሳውያን የኦሪትን ሕግ ፊደሉን እንጂ መንፈሱን የማይከተሉት ስለነበረ ስድስቱን ያኽል ሕጎች ተንትኖ አስረዳቸው። ለምሳሌ መግደልን በተመለከተ ወደ ግድያ የሚያደርሱትን ክፉ ተግባሮች ሁሉ ከለከለ። ስለዝሙትም ማየትንና መመኘትን በመከልከል ትእዛዙን ፍጹም አደረገው። ፈሪሳውያን ያለምክንያት ፍቺን ይፈቅዱ ነበር፤ ጌታችን ግን ያለዝሙት ምክንያት ፍቺን ከለከለ። በሐሰት አትማል የሚለውን በፍጹም አትማል በማለት ፍጹም አደረገው። ክፉን በተማሳሳይ ማለት ጥርስን በጥርስ፥ ዐይንን በዐይን የሚጠለሚለው በፍጹም አትበቀሉ ብሎ አዘዘ። የሚወድዱአችሁን ውደዱ፤ የሚጠሉአሉአችሁን ጥሉ ለተባለው ክፉ ላደረገ ደግ እንዲደረግለት አዘዘ፤ የሚጠሉአችሁን ውደዱ አለ።


ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ከፈሪሳውያንና ከኦሪት ሕግ መምህራን ትምህርት አስጠነቀቃቸው። በተለየም ከእነዚያ ግብዝነትና ዓለማዊ ምኞት አስጠነቀቃቸው። የሚሠሩት ሥራ ሁሉ ከልብ የመነጨ እንዲሆን አዘዛቸው። ይህም ትእዛዝ በተለይ ምጽዋትን፥ ጾምንና ጸሎትን በተመለከተ ነበር። በምጽዋት፥ ሰዎች በገንዘባቸው እግዚአብሔርን ያመልካሉ እንጂ ለታይታና ለትምክሕት መደረግ የለበትም፤ እርሱም መሰጠት ያለበት በምሥጢር ነው። አለበለዚያ ሰማያዊ ዋጋ አይገኝበትም። በጸሎት፥ እግዚአብሔርን የሚያመልኩት በስሜታቸው ማለት በመንፈሳቸው ነው። እርሱም በእነርሱና በእግዚአብሔር መካከል እንጂ ሰዎችን ማታለያ መሆን የለበትም። አለበለዚያ ግን ሰማያዊ ዋጋ አያገኙበትም። በጾም ደግሞ እግዚአብሔርን በሥጋቸው ማለት በሰውነታቸው ያመልኩታል።

እንዴት መጸለይ እንደሚገባም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አባታችን ሆይ በሚለው ጸሎት የጸሎትን ናሙና አመልክቶአል።

ጾምም በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ሆኖ ሰዎች የሚመለከቱት መሆን የለበትም። ለሰው ለማሳየት ከሆነ ሰማያዊ ዋጋ የለውም።



እንዲሁም ጌታችን በሰዎች መመስገንን ከመፈለግ ግብዝነት እንዲጠነቀቁ ደቀ መዛሙርቱን አስጠንቅቆአቸዋል። በዚህ ዓለም ሀብትን ማከማቸት ጥቅም የሌለው መሆኑንና ለሰማያዊ ሀብት እንዲሠሩ አስተምሮአቸዋል። በእግዚአብሔር መተማመን እንጂ ስለኑሮ መጨነቅም እንደማይገባ አስተምሮአቸዋል።



የተራራው ላይ ትምህርቱ (ማቴ 5–7)

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰው ላይ መፍረድ እንደማይገባ ለደቀ መዛሙርቱ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶአቸዋል።

እንዲሁም ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ የነገራቸው ጸሎት መንፈሳዊ ፍላጎትን እንደሚያሙአላ ነው። ይህንኑም አባባል ለምኑ ይሰጣችኋል፤ ፈልጉ ታገኛላችሁ፤ በር አንኳኩ ይከፈትላችኋል በማለት ገልጾታል።

ሌላው፥ ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ የገለጠላቸው ወደጥፋት የሚወስደው በር ሰፊ በመሆኑ በጠባቡ በር እንዲገቡ ነው።

ዛፍ በፍሬው ስለሚታወቅ ከሐሰተኞች መምህራን እንዲጠነቀቁ ነገራቸው።

www.ethiopianorthodox.org

ማንም ሰው ሕግጋቱን ካላከበረ በቀር በአፍአዊ ሁናቴው ማለት አስመሳይ ሃይማኖታዊነቱ ወደ መንግሥተ ሰማይ ሊያስገባው አይችልም። ቃሉን ሰም ተው የሚፈጽሙትንና የማይፈጽሙትን ሰዎች በአለት ወይም በአሸዋ ላይ በተመሠረቱ ቤቶች ምሳሌነት ገልጾአቸዋል። (ማቴ፥ም:5–7)

ማቴዎስን መጥራቱ:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ጊዜ በቀረጥ መቀበያ በኩል ሲያልፍ ሌዊ ይባል የነበረውንና በኋላ ማቴዎስ የተባለውን ቀራጭ ተከተለኝ አለው። እርሱም ሁሉን ነገር ትቶ ተከተለው። ማቴዎስም ለጌታችን ክብር በቤቱ የምሳ ግብዣ አደረገ። በግብዣውም ብዙ ቀራጮችና ኃጢአተኞች ተገኝተው ነበር። ፈሪሳውያን ለጌታችን ደቀ መዛሙርት መምህ ራችሁ ለምን ከኃጢአተኞች ጋር አብሮ ይበላል አሉአቸው። ቀራጮች የሮማ መንግሥት ሠራተኞች ስለነበሩ እንደ ኃጢአተኞች ይቈጥሩአቸው ነበር። ጌታችንም የፈሪሳውያንን ጥያቄ ሰምቶ በሽተኞች እንጂ ጤነኞች ሐኪም አያስፈልጋቸውም ብሎ መልስ ሰጣቸው። ራሱን በሐኪም ኃጢአተኞችን በበሽተኞች ቦታ አድርጎ በሚናገርበት ጊዜ እኔ የመጣሁት ኃጢአተኛነታ ቸውን አምነው ይቅርታ ለሚጠይቁ እንጂ ጻድቃን ነን ብለው ለሚመጻደቁ አይደለም ማለቱ ነው። በመጨረሻም «እኔ የምፈልገው ምሕረትን ነው እንጂ መሥዋዕትን አይደለም» የሚለውን ጥቅስ በመጥቀስ እኔ የመጣሁት ኃጢአ ተኞችን ወደ ንስሓ ለመጥራት እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አይደለም ብሎአቸዋል (ሆሴ: 6፥6) ፥(ማቴ:ም:9ቍ:9–13)።

ጌታችን በናዝሬት ተቃውሞ ደረሰበት:- ጌታችን ያደገው ናዝሬት በም ትባል ከተማ ነበር። በዚህም መሠረት በናዝሬት ያሉ ሰዎች የጌታችንን መለኮታዊ ክብር አይወቁ እንጂ ስለእርሱ ሥጋዊ አስተዳደግ ደኅና አድርገው ያውቁ ነበር። እንደ አባቱ ይቈጥሩት የነበረው ዮሴፍ በአናጢነት ሥራ የሚተዳደር ነበር። ቤተዘመዶቹ ሁሉ በምን ዐይነት የኑሮ ደረጃ ላይ የነበሩ መሆናቸውን ለመገመት ይቻላል።

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የማስተማር ሥራውን በጀመ ረበት ሰሞን በሰንበት ቀን በናዝሬት ከተማ በምትገኝ በአንዲት ምኵራብ ውስጥ ገብቶ የነቢዩ የኢሳይያስ መጽሐፍ ተሰጥቶት ሊያነብ ተነሣ። መጽሐፉንም ሲገልጥ ስለእርሱ ትንቢት የተነገረበትን ቦታ አገኘ። ያን ትንቢት ካነበበ በኋላ ማብራራት ሲጀምር ያገሬው ሰዎች በአነጋገር ጥበቡ ተገርመው ይህ የእንጨት ጠራቢው የዮሴፍ ልጅ አይደለምን? እናቱስ ማርያም አይደለችምን? ወንድ ሞችና እኅቶቹንስ እኛ የምናውቃቸው አይደለንምን? ይህን ሁሉ ጥበብ ከወዴት አመጣው ብለው ያናንቁት ጀመር። እርሱም ነቢይ በሀገሩ አይከበርም በማለት ጀምሮ ኤልያስ በስራጵታ ወደምትገኘው መበለት ብቻ እንደተላከና



በኤልሳዕ ጊዜ ደግሞ ከሶርያዊው ንዕማን በቀር ሌሎች ለምጻሞች አለመፈ ወሳቸውን በምሳሌ ባስረዳቸው ጊዜ ሊወግሩት ሲፈልጉ በመካከላቸው ዐልፎ ሄደ (ማቴ:ም:13ቍ:53–58)።

ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት :- ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ጠርቶ አጋንንትን እንዲያስወጡ፥ በሽታንና ደዌን እንዲፈውሱ ሥልጣን ሰጣቸው። የዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ስም ዝርዝር ጴጥሮስ፥ እንድርያስ፥ የዘብዴዎስ ልጅ ያዕቆብ፥ ዮሐንስ፥ ፊልጶስ፥ በርተ ሎሜዎስ፥ ቶማስ፥ ማቴዎስ፥ የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ፥ ታዴዎስ፥ ስምዖንና ይሁዳ ነው።

ጌታችንም እነዚህን ዐሥራ ሁለት ሐዋርያት ለማስተማር በላካቸው ጊዜ ወደ አረማውያን አትሂዱ፤ ወደ ሳምራውያንም ከተማ አትግቡ፤ ግን እንደ በጎች ወደጠፉት ወደ እስራኤልውያን ሂዱ ብሎ አዘዛቸው። እንዲሁም መንግሥተ ሰማይ ቀርባለች እያላችሁ ስበኩ፤ በሽተኞችን ፈውሱ፤ ሙታንን አስነሡ፤ ለምጻሞችን አድኑ፤ አጋንንትን አስወጡ፤ በነጻ የተቀበላችሁትን በነጻ ስጡ፤ ወርቅ፥ ወይም ብር፥ ወይም ናስ በኪሳችሁ አትያዙ፤ ከረጢትም፥ ትርፍ እጅ ጠባብም፥ ትርፍ ጫማም፥ በትርም ለመንገዳችሁ አትያዙ አላቸው። መመሪያውንም በመቀጠል በምትገቡበት ከተማ ወይም መንደር እናንተን ለመቀበል ፈቃደኛ የሆነ ሰው ቢኖር መርምሩ፤ ያንንም ስፍራ ለቅቃችሁ እስክትወጡ ድረስ ከዚያ ሰው ጋር ቈዩ፤ ወደ ሰው ቤት ስትገቡ ሰላምታ ስጡ፤ የቤቱ ጌታ ሰላምታችሁን ቢቀበል ሰላምታችሁ ይድረሰው፤ ባይቀበል ግን ሰላምታችሁ ይመለስላችሁ፤ የማይቀበላችሁና ቃላችሁንም የማይሰማ ቢኖር ያን ቤት ወይም ከተማ ለቅቃችሁ ስትወጡ የእግራችሁን ትቢያ አራግፉችሁ ሂዱ፤ በእውነት እላችኋለሁ፥ በፍርድ ቀን ከዚያች ከተማ ይልቅ ለሰዶምና ለገሞራ ቅጣቱ ይቀልላቸዋል አላቸው (ማቴ:10፥5–15)።

## የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ተአምራት

የጌታችንን ልብስ የነካች ሴት:- ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኢያኢሮስ ወደተባለ ወደ አንድ የአይሁድ አለቃ ቤት በመሄድ ላይ እያለ ተከትለውት የነበሩ ብዙ ሰዎች በመጋፊት ያጨናንቁት ነበር። ዐሥራ ሁለት ዓመት ሙሉ ደም እየመታት የምትሠቃይ አንዲት ሴት ነበረች። ያላትን ገንዘብ ሁሉ ለሐኪሞች በመስጠት ጨርሳ ማንም ሊያድናት አልቻለም። እርስዋም ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መጥታ በስተኋላው ቀረበችና የልብሱን ጫፍ ነካች፤ ደምዋም ወዲያውኑ መፍሰሱን አቆመ። ጌታም ማን ነው የነካኝ? ሲል ጠየቀ። ሁሉም እኛ አልነካንህም አሉ። ጴጥሮስ ግን መምህር ሆይ፥ ሕዝቡ

www.ethiopianorthodox.org

እየተጋፊ ሲከተልህ እያየህ ማን ነው የነካኝ ትላለህን? አለው። ጌታችን ግን
ኀይል ከእኔ መውጣቱን ዐውቄአለሁና በእርግጥ አንድ ሰው ነክቶኛል አለ።
ሴትዮዋም እንዳልተሰወረች ባወቀች ጊዜ እየተንቀጠቀጠች ወደ ጌታችን
መጥታ በእግሩ ሥር ወደቀች። ከዚያም በኋላ ለምን እንደነካችውና እንዴት
ወዲያውኑ እንደተፈወሰችም በሕዝቡ ሁሉ ፊት ገለጠች። ጌታችንም ልጄ
ሆይ፥ እምነትሽ አድኖሻልና በሰላም ሂጂ አላት (ማቴ:ም:9ቍ:20–22)።



<u>የኢያኢሮስ ልጅ ከሞት መነሣት</u>:- አንድ የምኵራብ አለቃ ኢያኢሮስ
የተባለ ሰው በጌታ እግር ሥር ወድቆ እባክህ ወደ ቤቴ ናልኝ ብሎ ለመነው፡
የለመነውም ዕድሜዋ ዐሥራ ሁለተ ዓመት የሆናት አንዲት ልጁ ታማ በሞት
አፋፍ ላይ ስለነበረች ነው።

ጌታችንም ከእርሱ ጋር ለመሄድ ተነሥቶ በመንገድ ላይ ሳለ አንድ ሰው
ከምኵራብ አለቃው ከኢያኢሮስ ቤት መጥቶ ኢያኢሮስን ልጅህ ሞታለች
እንግዲህ መምህሩን በከንቱ አታድክመው አለው። ጌታችን ግን ይህን ሰምቶ
ኢያኢሮስን አይዞህ አትፍራ፤ እመን ብቻ፤ ልጅህ ትድናለች አለው። ጌታችን
ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ኢያኢሮስ ቤት በደረሰ ጊዜ ከጴጥሮስ፥ ከዮሐንስ፥
ከያዕቆብ፥ ከልጅትዋ አባትና እናት በቀር ሌላ ማንንም ከእርሱ ጋር ወደ ውስጥ
እንዲገባ አልፈቀደም። በዚያ የነበሩ ሰዎች ሁሉ ስለ ልጅትዋ በማዘን ያለቅሱ
ነበር። ጌታ ግን አታልቅሱ ልጅትዋ ተኝታለች እንጂ አልሞተችም አላቸው።
እነርሱ ግን ልጅትዋ መሞትዋን ስላወቁ ሁሉም በማፌዝ ሳቁበት። ጌታችን
የልጅትዋን እጅ ይዞ አንቺ ልጅ ተነሽ አላት። እርስዋም ነፍስዋ ስለተ
መለሰችላት ወዲያውኑ ተነሣች። ጌታችንም የምትበላውን ስጡአት ሲል
አዘዘ። የልጅትዋም ወላጆች ተገረሙ፤ እርሱ ግን ይህን ነገር ለማንም አትናገሩ
ሲል አዘዛቸው (ማቴ:9፥18–26)።



የኢያኢሮስን ልጅ ከሞት የማስነሣት ተአምር (ማር:5፥35–43)።

## <u>የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌዎች</u>

<u>የደጉና የክፉው አገልጋይ ምሳሌ</u>:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ አለ:-
ቤተሰቦቹን በደንብ እንዲያስተዳድርለትና ለአገልጋዮቹም ምግባቸውን በወ
ቅቱ እንዲሰጣቸው ጌታው የሚሾመው ታማኝና ብልኅ መጋቢ ማን ነው?
ጌታው ከሄደበት ሲመለስ ልክ እንደታዘዘው ሲፈጽም የሚያገኘው አገልጋይ
እንዴት የተመሰገነ ነው? በእውነት እላችኋለሁ፤ ጌታው ያን አገልጋይ የን

www.ethiopianorthodox.org

ብረቱ ሁሉ ኀላፊ አድርጎ ይሾመዋል። ነገር ግን ያ አገልጋይ ጌታዬ ቶሎ አይመጣም፤ ይዘገያል ብሎ በማሰብ እየበላ፥ እየጠጣና እየሰከረ ወንዶችና ሴቶች አገልጋዮችን መምታት ይጀምራል። ይሁን እንጂ ጌታው ባልታሰበበት ቀንና ባልጠበቀበት ሰዓት በድንገት ይመጣል፤ አገልጋዩንም በብርቱ ይቀጣ ዋል፤ ዕድሉም ከወስላቶች ጋር እንዲሆን ያደርጋል።

የጌታውን ፈቃድ እያወቀ ያልተዘጋጀ፥ ወይም የጌታውን ፈቃድ ያልፈ ጸመ አገልጋይ በብርቱ ይቀጣል። ነገር ግን የጌታውን ፈቃድ ባለማወቅ ቅጣት የሚያመጣበትን ነገር አድርጎ ቢገኝ ቅጣቱ ይቀልለታል፤ ይህም የሚሆንበት ምክንያት ብዙ ከተሰጠው ሰው ብዙ የሚፈለግበት ስለሆነ ነው፤ ብዙ ዐደራም ከተሰጠው ሰው ብዙ ይጠበቅበታል (ማቴ:24፥45–51)።

<u>ክፉ አገልጋይ</u>:- መንግሥተ ሰማይ ከአገልጋዮቹ ጋር ሊተሳሰብ የፈለገውን ንጉሥ ትመስላለች። ንጉሡ መተሳሰብ በጀመረ ጊዜ በብዙ ሺህ የሚቈጠር ብር ዕዳ ያለበት አንድ አገልጋይ ተይዞ መጣ። ይህ አገልጋይ ዕዳውን መክፈል ስላልቻለ እርሱ፥ ሚስቱና ልጆቹ፥ እንዲሁም ያለው ንብረት ሁሉ ተሽጦ ዕዳው እንዲከፈል ጌታው አዘዘ። አገልጋዩ ግን በጌታው እግር ሥር ተንበ ርክኮ፥ ጌታ ሆይ፥ እባክህ ታገሠኝ ሁሉንም እከፍልሃለሁ ብሎ ለመነው። ጌታውም ራራለትና ለቀቀው፤ ዕዳውንም ተወለት።

ነገር ግን ያ አገልጋይ ከዚያ ወጥቶ ሲሄድ ሳለ መቶ ብር ያበደረውን የሥራ ጓደኛውን አገኘና ዐንገቱን ዐንቆ ይዞ ያበደርኩህን ገንዘብ ክፈለኝ አለው። ጓደኛውም በእግሩ ሥር ወድቆ እባክህን ታገሠኝ እከፍልሃለሁ ብሎ ለመነው። አበዳሪው ግን እምቢ አለው። እንዲያውም ይዞት ሄደና ዕዳውን እስኪከፍል ድረስ በወህኒ ቤት አሳሰረው። ሌሎች የሥራ ጓደኞቹ ይህን ባዩ ጊዜ እጅግ አዘኑ፤ ሄደውም የሆነውን ሁሉ ለጌታቸው ነገሩት። ጌትዮውም ያን አገልጋይ አስጠርቶ እንዲህ አለው:- አንተ ክፉ አገልጋይ፥ ስለለመንከኝ ያን ሁሉ ዕዳ ተውኩልህ። ታዲያ እኔ ዕዳህን እንደተውኩልህ አንተስ ባልንጀራህ ለሆነው አገልጋይ ዕዳውን ልትተውለት አይገባህም ነበርን? ስለዚህ ጌታው ተቈጥቶ ዕዳውን ሁሉ እስኪከፍል ድረስ ለሚያሠቃዩት ሰዎች አሳልፎ ሰጠው።

እንግዲህ እናንተም እያንዳንዳችሁ ወንድማችሁን ከልብ ይቅር ባትሉ በሰማይ ያለው አባቴም እንዲሁ ያደርግባችኋል (ማቴ:ም:18ቍ23–34)።

## ከዚህ ምዕራፍ የምናገኘው ትምህርት

የተራራው ላይ ስብከት ስለተሰኘው ረጅምና አንድ ወጥ ትምህርት ሁለት ዐይነት አስተያየቶች አሉ። አንዱ አስተያየት ይህ በማቴዎስ ወንጌል ከምዕራፍ



5 እስከ ምዕራፍ 7 ድረስ የቀጠለው ትምህርት በዚያው በተራራው ላይ ሆኖ ሳለ ሳያቋርጥ የሰጠው ትምህርት መሆኑን የሚገልጠው ነው። ሁለተኛው አስተያየት ግን ጌታችን በተለያዩ ጊዜዎች ያስተማራቸውን የተለያዩ ትምህር ቶች ወንጌላዊ ማቴዎስ በአንድ ላይ አሰባስቦአቸው ነው የሚለው ነው።

በዚህ በተራራ ላይ ስብከት በተለያዩ አርእስት የተገለጠው ሁናቴ የመንግሥተ ሰማይን ልጆች መንፈሳዊ ጠባይ የሚመለከት ነው። የመንግሥተ ሰማይ መምጣትም ከጌታችን የማስተማር ሥራ መጀመር ጋር የተያያዘ ነው።

በተራራው ስብከት ይዘት ላይ ያሉ አንዳንድ አስተያየቶች ደግሞ በትም ህርቱ ውስጥ የተካተቱት ጉዳዮች ለካህናትና ለገዳም መነኰሳት የቀረቡ መንፈሳውያን መመሪያዎች እንጂ ለተራ ምእመን የቀረቡ አይደሉም የሚል ነው። ሌላው አስተያየት ግን ይህ ትምህርት የቀረበው ለመላው ክርስቲያን መንፈሳዊ መመሪያነት እንጂ ለተወሰኑ ወገኖች ብቻ አይደለም የሚል ነው።

የተራራው ትምህርት ወይም ስብከት ዋና ዓላማ የእግዚአብሔርን መንግ ሥት ለሁሉም ማወጅ ነው። ከዚያም በመነሣት ለመንግሥተ ሰማይ የሚያበ ቁትን መመሪያዎች ለማቅረብ ነው። በዚህም መሠረት ስብከቱ የሚያተኵረው ጌታችን ስለመንግሥተ ሰማይ የሰጠውን ትምህርት ተቀብለው ተግባራዊ ስላደረጉ ሰዎች መንፈሳዊና ግብረገባዊ ጠባይ ላይ ነው። ከአንቀጸ ብፁዓን የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ የሚያመለክቱት እነዚያ ብፅዕናን አግኝተው ለመንግ ሥተ ሰማያት የበቁት ሰዎች በጥረታቸው ሳይሆን ነገር ግን ከደካማነታቸውና ለዚሁም ለእግዚአብሔር ሥራ ግልጥ በመሆናቸው ነው። እነዚህም ሰዎች ትዕ ቢተኞች አይደሉም፤ በቀላሉም የሚጠግቡ አይደሉም፤ ድል አድራጊዎች አይደሉም፤ እነርሱ ግን ትሑቶች፥ ጭቍኖችና ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም የሚፈልጉ ናቸው።

ምንም እንኳ የመንግሥተ ሰማያት ልጆች ትሑቶች ናቸው ቢባል የእርነርሱ ጽድቅ ግን የኦሪትን ሕግ በመፈጸም በአይሁድ ዘንድ ይደነቁ ከነበ ሩት ከጸሐፍትና ከፈሪሳውያን ጽድቅ ብልጫ ነበረው (ማቴ: 5፥20)። የመን ግሥቱ ልጆች የበለጠ ጽድቅ አላቸው የተባለው አፍአዊውን የሕጉን ፊደል በመፈጸማቸው ሳይሆን ጠለቅ ብለው የሕጉን መንፈስ ስለሚከተሉ ነው። በዚህም መሠረት በመካከላቸው የእግዚአብሔር ሥራ ያለ መሆኑን ለሚያ ያቸው ሁሉ ያስመሰክራሉ።

ጌታችንም ግልጥ እንዳደረገው የኦረትን ሕግ ሊፈጽም እንጂ ሊሽረው አልመጣም። በእርሱና በአይሁድ ባለሥልጣኖች መካከል ያለው ልዩነት ግን ያተረጓጐም ልዩነት ነው። አይሁድ ሕጉን ቃል በቃል መመሪያ ማድረግ

www.ethiopianorthodox.org

የሚፈልጉ ሲሆን ጌታችን እኔ ግን እላችኋለሁ በማለት እራሱን እንደባለ ሥልጣን ያቀርባል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ የሆነውን ማቴዎስን ከሥራው ላይ ጠርቶና ተከተለኝ ባለው ጊዜ ምንም ምክንያት ሳያቀርብና ጊዜ ሳይሰጥ ተነሥቶ መከተሉ አስቀድሞም ቢሆን ልቡ ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ የነበረ መሆኑን ያመለክታል። ጌታችንም ባልተወሰነው መለኮታዊ ዕውቀቱ የማቴዎስን ማንነት ያውቅ ስለነበረ ጠራው።

ከዚያም በኋላ ማቴዎስ ስለ ጌታችን ክብር በቤቱ ባደረገው ግብዣ ብዙ ኃጢአተኞች ተገኝተው ነበር። ፈሪሳውያንና የኦሪት ሕግ መምህራን ለምን ጌታችን ከኃጢአተኞች ጋር በአንድ ማእድ ላይ ተቀምጦ ይበላል ብለው አጕረመረሙ። ይህንንም ያደረጉት ጌታችን ወደዚህ ዓለም የመጣበትን ዋነኛውን ዓላማ ስላልተገነዘቡ ነው። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ዝቅ አድርጎ የፈጠረውን የሰውን ሥጋ የለበሰው በለበሰው ሥጋ እኛን ኃጢአተኞን ለመቤዠት መሆኑን እነርሱ አልተገነዘቡትም። ዓለምን ከኃጢአት ባርነት ነጻ ለማውጣት የመጣው የፍጥረቱ ሁሉ ጌታ በመካከላቸው መሆኑን አልተገ ነዘቡም። በዚሁም ምክንያት ለሕማማቱና ለሞቱ ትንቢት ተፈጻሚነት እነርሱ ምክንያት ሆኑ። በዚሁም ምክንያት ጌታችን በተሰቀለበት ጊዜ የሚያደርጉትን አያውቁምና አባት ሆይ ይቅር በላቸው ብሎ ጸለየ (ሉቃ: 23 ፥ 24)።

በናዝሬት ከተማ ምኵራብ ውስጥ ገብቶ ባስተማረበት ጊዜ የደረሰው ሁናቴ ይኸው ነው። በናዝሬት ከተማ ያሉ ሰዎች ጌታችንን የሚያውቁት ከልጅነት ጀምሮ በዚያ አገር ያደገ መሆኑን ነው። በእነርሱ አስተሳሰብ ዮሴፍ ወላጅ አባቱ ነው፤ የዮሴፍም ልጆች ወንድሞችና እኅቶቹ ናቸው። በዚህም ምክንያት የተሰናከሉበት ስለሆነ ጌታችን በናዝሬት ብዙ ተአምራት አላደረገም። በእነርሱ ዓለማዊ አስተሳሰብ ያ በምኵራብ ውስጥ ሆኖ ያሳየውን ጥበብ የሞላበት አነጋገር ለመናገር በታወቁ አስተማሪዎች እግር ሥር ሆኖ ማደግ አለበት። እነርሱ ሊያውቁና ሊገነዘቡ ያልቻሉት ነገር እርሱ የጥበብ ሁሉ ምንጭ መሆኑን ነው። በዚህም ምክንያት ነው አንድ ጊዜ የእርሱ ትምህርት ወይም ዕውቀት ከዚህ ዓለም አለመሆኑን የገለጠው (ዮሐ:7፥16)።

ጌታችንም በኤልያስ ዘመን በረሀቡ ጊዜ ለአንዲት መበለት ምሕረት የተደረገላት መሆኑና በኤልሳዕ ዘመን ብዙ ለምጻሞች ሲኖሩ እንዲፈወስ የተደረገው ሶርያዊው ንዕማን ብቻ መሆኑን በገለጠላቸው ጊዜ አንድም ከእነዚያ ጋር በማመሳሰሉ ወይም እንዲያውም ከእነዚያ በማሳነሱ አስቈጣቸው።



ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮቹን ሐዋርያትን በመረጠ ጊዜ በዕውቀታቸው፥ በጥበባቸውና በኀይላቸው ዝነኞች የነበሩትን ሰዎች ፈልጎ አልመረጠም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ጉዳይ ሲያብራራ እንዲህ ብሏል:-

«ወንድሞቼ ሆይ እግዚአብሔር ሲጠራችሁ ጊዜ ምን ዐይነት ሰዎች እንደነበራችሁ አስታውሱ፤ እንደ ሰው አስተሳሰብ ከእናንተ መካከል ብዙዎች ጥበበኞች፥ ወይም ብርቱዎች፥ ወይም ታላላቅ ሰዎች አልነበሩም። እግዚአብሔር ጥበበኞችን ለማሳፈር በዓለም እንደ ሞኞች የሚቈጠሩትን ሰዎች መረጠ፤ ብርቱዎችንም ለማሳፈር በዓለም እንደ ደካሞች የሚቈጠሩትን መረጠ፤ እግዚአብሔር በዓለም ሰዎች ዘንድ ክቡር ሆኖ የሚታየውን ነገር ለማጥፋት፥ በዓለም የተዋረደና የተናቀ ከንቱም መስሎ የሚታየውን ነገር መረጠ። ይህንንም ያደረገው ማንም ሰው በእግዚአብሔር ፊት እንዳይመካ ነው» (1ኛ:ቆሮ:ም:1ቍ:26–29)።

ጌታችንም ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ለማስተማር በላካቸው ጊዜ ምንም ስንቅ እንዳይዙ ማዘዙ የተላኩት እነርሱን ወደሚያውቁአቸው ወደ ወገኖቻቸው ስለነበረና እነርሱም እንደሚቀበልዋቸው ይጠበቅ ስለነበረ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን በላካቸው ጊዜ ወደ አረማውያን አትሂዱ፤ ወደ ሳምራውያንም ከተማ አትግቡ፤ ነገር ግን እንደ በጎች ወደጠፉት ወደ እስራኤላውያን ሂዱ ብሎ አዝዞአቸዋል። ይህንንም ያዘዛቸው የደኅንነቱ ትምህርት ወደ ኢ–አማንያን ከመቅረቡ በፊት በእግዚአብሔር አምነው ወደነበሩት ሰዎች እንዲቀርብ ስለተፈለገ ነው።

የጌታችንን ልብስ ስለነካችው ሴት ታሪክና ተአምር ስናነብ የእግዚአብሔር ዕውቀት በጊዜና በቦታ ያልተወሰነ መሆኑን እንረዳለን። በሕዝብ ብዛት እየተጨናነቁ በሚሄዱበት ጊዜ ከጌታችን በስተኋላ መጥታ የልብሱን ጫፍ መንካትዋንና በዚያውም መፈወስዋን ያወቀው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማነው የነካኝ ብሎ ጠየቀ። የነካው ሰው መኖሩን እያወቀ ማን እንደነካው መጠየቁ ሳያውቅ ቀርቶ አይደለም። ነገር ግን አዳምን ወዴት ነው ያለኸው? አትብላ ካልኩህ ዛፍ በልተህ ይሆንን? እንዲሁም ቃየልን ወንድምህ ወዴት አለ? ብሎ እንደጠየቀው ጥያቄ ነው። በአንድ በኩል ከእርሱ ምንም ሊሰወር የሚችል ነገር አለመኖሩን ለማመልከት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ስለተፈጸመው የድብብቆሽ ሥራ ሴትዮዋ እንድትናዘዝ ስለተፈለገ ነው። የአዳምና የቃየልም ጉዳይ ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ ነው። የጌታችንን ልብስ ብትነካ እንደምትድን አምና ስለነበረ ጌታችንም አይዞሽ እምነትሽ አድኖሻል ብሎአታል።

www.ethiopianorthodox.org

የኢያኢሮስን ልጅ ከሞት የማስነሣት ተአምር የጌታችን የኢየሱስ ክርስ ቶስን መለኮታዊ ክብር በማያወላውል ሁናቴ ያስረዳል። አንድ ፍጡር ተመሳ ሳይ ወይም ከዚያም ያነሰ ተአምር ለማድረግ ብዙ ጸሎት መጸለይ ይኖርበታል። ጌታችን ግን ለእኛ አርአያ ለመሆን አንዳንድ ጊዜ ብቻ የሚጸልይ ከመሆኑ በቀር ብዙዎቹን ተአምራቱን የሚያደርጋቸው በትእዛዝ ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ፍጡር ተአምራት በሚያደርግበት ጊዜ ከማድረጉ በፊት የእግዚአ ብሔር ፈቃድ ከሆነ ብሎና በእግዚአብሔር ተማምኖ ይነሣል እንጂ በራሱ እር ግጠኛ ሆኖ አይነሣም። ጌታችን ግን በሥልጣኑ እንደሚያስነሣት እርግጠኛ ስለነበረ ልጅትዋ ተኝታለች እንጂ አልሞተችም ብሎአቸዋል።

ደጉና ክፉው አገልጋይ በተሰኘው ምሳሌ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ዳግም ምጽአቱ ወይም ስለሰዎች ዕለተ ሞት ሁናቴ ይገልጣል። ይኸውም የዓለም ሕዝብ በንስሓና በበጎ ተግባር ተዘጋጅቶ በመጠበቅ ፈንታ ጊዜው ገና እየመሰለው ዕለተ ሞቱ ወይም የፍርድ ቀን በድንገት ሳያስበው የሚደርስበት ከመሆኑ ጋር በማመሳሰል ነው። በዚያን ጊዜ የሚሰጠውም ፍርድ ዐውቀው በሚያጠፉ ሰዎች ላይ እንደሚበረታ ይገልጣል። ይህንንም የገለጠው ብዙ ከተሰጠው ብዙ ይጠበቅበታል በማለት ነው።

የክፉው አገልጋይ ምሳሌ የሚያስተምረን ደግሞ እግዚአብሔር ይቅር የሚልልን ከፍተኛ ኃጢአት፥ ሌሎች ሰዎች በእኛ ላይ እንዳደረሱብን ከምን ገምተው በደል ጋር ሲነጻጸር በእኛ ላይ የሚደርሰው በደል በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ነው። ስለዚህም እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር ይልልን ዘንድ እኛም ለበደሉን ሰዎች ይቅርታ እንድናደርግ፥ ይህን ባናደርግ ግን የእግዚ አብሔርን ይቅርታ እንደማናገኝ ያስተምረናል፤ ያስጠነቅቀናልም።

## ጥያቄዎች

1. የተራራው ላይ ስብከት (ትምህርት) የተባለው ለምንድነው?
2. ይህ ትምህርት ለክርስቲያናዊ ሕይወት እንደምን ተደርጎ ይቈጠራል!
3. ጌታችን የተራራ ላይ ትምህርቱን የጀመረው ከምን ተነሥቶ ነው?
4. የአንቀጸ ብፁዓን መመዘኛ የተለመደው የሰው አኗኗር ነውን?
5. እኛ የምናስበው የደስታ መሠረትና ጌታችን ያቀረባቸው የደስታ መሠረቶች ተመሳሳይ ናቸውን?
6. በመንፈስ ድኾች ማለት ምን ማለት ነው?
7. የሚያዝኑ የተባሉት ምን ዐይነት ሐዘን ነው?
8. ትሑቶች የተባሉትስ እነማን ናቸው?
9. ስለጽድቅ የሚራቡና የሚጠሙ እነማን ናቸው?
10. ምሕረት የሚያደርጉ እነማን ናቸው?
11. ልበ ንጹሖች እንደምን ያሉ ናቸው?
12. ሰላምን የሚያደርጉ እንደምን ያሉ ናቸው?
13. ስለ እውነት የሚሳደዱ እንዴት ያሉ ናቸው?
14. ጌታችን ደቀ መዛሙርቱን ያበረታታቸው ምን ብሎ ነው?
15. ለኦሪት ሕግ ቀናተኞች ለሆኑ ሰዎች ጌታችን ኢየሱስ ክርቶስ ያረጋገጠላቸው ምንን ነው?
16. ጌታችን ስድስቱን ቃላተ ወንጌል ያቀረበው በምን ምክንያት ነው?
17. ሰውን መግደልን በተመለከተ ምን አለ?
18. ስለዝሙት ምን አለ?
19. ስለ ፍቺ ምን አለ?
20. ስለ መሐላ ምን አለ?
21. በቀልን በተመለከተ ምን አለ?
22. ማንንና ማንን መውደድ እንደሚገባ ተናገረ?
23. ምጽዋት፥ ጾምና ጸሎትን በተመለከተ ምን አለ?
24. ጌታችን ያስተማረው የጸሎት ናሙና ምን የሚለው ነው?
25. ስለ ሀብት ማከማቸት ምን አለ?
26. ስለ ኑሮ መጨነቅ ምን ብሎ አስተማረ?
27. በሰው ላይ ስለመፍረድ ምን አለ?
28. ጌታችን የጸሎትን ተሰሚነት ያስተማረው ምን ብሎ ነው?
29. በጠባቡ በር ግቡ ያለው በምን ምክንያት ነው?
30. ዛፍ በፍሬው ይታወቃል ያለው ከምን ጋር በማነጻጸር ነው?
31. ቃሉን ሰምተው የሚፈጽሙትና የማይፈጽሙት ሰዎች በምን ይመሰላሉ?


www.ethiopianorthodox.org

32. ከቀራጭነት ሥራ ለደቀ መዝሙርነት ጌታችን የጠራው ማንን ነው?

33. ከጌታችን ጋር ምሳ ተጋብዘው የነበሩ ኃጢአተኞችን በማየት ፈሪሳውያን ምን አሉ?

34. ጌታችንስ ምን መልስ ሰጣቸው?

35. ጌታችን ተቃውሞ የደረሰበት የት ነው?

36. ጌታ ያደገበት ከተማ ማን ይባላል?

37. በምኵራብ ውስጥ ጌታችን እንዲያነብ የተሰጠው የትኛውን መጽሐፍ ነው?

38. ጌታችን ተቃውሞ የደረሰበት ለምድነው?

39. ሰዎቹ በጌታችን ላይ ምን ዐይነት የማናናቅ ጥያቄ ጠየቁ?

40. ጌታችንስ ምን መልስ ሰጠ?

41. በዚያን ጊዜ ጌታችን ያቀረባቸው ሁለት ምሳሌዎች ማንና ማን ናቸው?

42. ጌታችን ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ጠርቶ ምን ሰጣቸው?

43. የዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ስም በዝርዝር ተናገር።

44. ዐሥራ ሁለቱን ለማስተማር በላካቸው ጊዜ ምን አዘዛቸው?

45. ከሚያስተምሩበት ሰፈር እስኪወጡ ድረስ ወዴት እንዲቈዩ ነገራቸው?

46. እነርሱን ለማይቀበል ከተማ ምን እንዲያደርጉ ነገራቸው?

47. ያቺስ እነርሱን የማትቀበል ከተማ ምን ትሆናለች?

48. ዐሥራ ሁለት ዓመት ሙሉ ደም ይመታት የነበረችው ሴት ምን አደረገች?

49. ጌታችን በዚያን ጊዜ ወዴት እየሄደ ነበር?

50. በዚያን ጊዜ ጌታችን ምን ብሎ ጠየቀ?

51. ቅዱስ ጴጥሮስ ምን አለው?

52. ጌታችንስ ምን መለሰ?

53. ከዚያስ በኋላ ምን መልስ አገኘ?

54. ጌታችንስ ምን መልስ ሰጠ?

55. ኢያኢሮስ ጌታችንን ምን ለመነው?

56. ከጌታችን ጋር እየሄደ ሳለ ለኢያኢሮስ ምን መልእክት መጣለት?

57. በዚህ ጊዜ ጌታችን ምን አለው?

58. ወደ ኢያኢሮስ ቤት ሲደርስ ጌታችን ሰዎቹን ምን አላቸው?

59. ሰዎቹስ የጌታችንን አባባል ሲሰሙ ምን አሉ?

60. ጌታችን ወደቤት የገባው ከነማን ጋር ነው?

61. ወደ ቤት ገብቶስ ምን አደረገ?

62. የደጉንና የክፉውን አገልጋይ ምሳሌ ተናገር።

63. የክፉውን አገልጋይ ምሳሌ ተናገር።

64. በተራራው ስብከት ይዘት ላይ ሁለት አስተያየቶች ምንና ምን ናቸው?

65. የተራራውን ስብከት ዋና ዓላማ ተናገር።

66. ጸሐፍትና ፈሪሳውያን የሙሴን ሕግ የሚጠብቁ ሲሆኑ ከመንግሥቱ ልጆች በምን ይለያሉ?

67. ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ጌታችን ከኃጢአተኞች ጋር መገናኘቱን የነቀፉት በምን ምክንያት ነው?

68. ጌታችን ሐዋርያቱን ለማስተማር በላካቸው ጊዜ ምንም ስንቅ እንዳይዙ ያዘዛቸው በምን ምክንያት ነው?

69. ወደ አረማውያንና ወደ ሳምራውያን እንዳይሄዱ ያዘዛቸው ለምንድ ነው?

70. ማነው የነካኝ ባለው ዐይነት ቀደም ብሎ እግዚአብሔር የጠየቃቸው ጥያቄዎች የትኞች ናቸው?

71. የኢያኢሮስን ልጅ ከሞት በማስነሣት ጌታችን መለኮታዊ ክብሩን ያረጋገጠው እንዴት ነው?


www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ 4

## ቤተ ክርስቲያን

### የቤተ ክርስቲያን መሥራች

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እርሱ ማንነት ሐዋርያቱን በጠየቃቸው ጊዜ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በሰጠው መልስ «አንተ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ነህ» በማለቱ ጌታችን ጴጥሮስን ካመሰገነው በኋላ «አንተ አለት ነህ፤ በዚህ አለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እመሠርታለሁ» ብሎታል።

ይህንንም በማለቱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያን መሥራች እርሱ ራሱ መሆኑን አረጋግጦአል። አለትም የተባለው እምነቱ ነው። ይህም ማለት ቤተ ክርስቲያን የምትመሠረተው ማለት ክርስቲያኖች የክርስቶስ ተከታዮች ወይም ቤተሰብ መሆናቸው የሚታወቀው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ወይም ዓለምን ለማዳን ወደዚህ ዓለም መምጣት የነበረበት መሲሕ እርሱ መሆኑን አምነው የእግዚአብሔር ልጅነት በተቀበሉ ምእመናን ላይ ነው ማለት ነው። ይህን አባባል ሐዋርያው ዮሐንስ ሲያረ ጋግጠው እንዲህ ብሏል:-

«እንግዲህ ኢየሱስ መሲሕ መሆኑን ከሚክድ በቀር ሐሰተኛ ማን ነው! አብንና ወልድን የሚክድ ሁሉ የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው፤ ወልድን የሚክድ አብ የለውም። በወልድ የሚያምን አብ አለው» (1ኛ: ዮሐ:ም:2ቁ: 22-23)።

«ኢየሱስ መሲሕ መሆኑን የሚያምን ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ ነው» (1ኛ: ዮሐ:ም:5ቁ:1)።

ምንም እንኳ የቤተ ክርስቲያን ደንቦችና ሥርዓቶች የተዘጋጁት የሐዋርያት ትምህርት በሆነው በዲድስቅልያና በዓለም ዐቀፋዊዎቹ የቤተ ክርስቲያ ሲኖዶሶች ቢሆን በመጀመሪያ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በጌታች በመድኀኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑ ግልጥ ነው። ይህንኑም በሚከተሉ መግለጫዎች ይመለከቷል።

ቀደም ተብሎ በአንደኛው ክፍል ትምህርት እንደተመለከተው ቤ ክርስቲያን ማለት እንደ ጉዳዩ አመጣጥ:- ምእመናን፥ ወይም የቤተ ክርስቲ መሪዎች፥ ወይም የቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና፥ ወይም ሕንጻ ቤተ ክር ያን መሆኑ ተገልጦአል።



ከእነዚህ ከአራቱ ትርጉሞች አንዱ የሆነውን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በተመለከተ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምን እንዳለ እንመ ልከት:-

«ወንድምህ ቢበድልህ አንተና እርሱ ብቻችሁን ሆናችሁ በደሉን ንገረው፤ ቢሰማህ እንደገና ወንድምህ እንዲሆን ታደርገዋለህ፤ ባይሰማህ ግን የሁለት ወይም የሦስት ሰዎች ምስክርነት ስለሚጸና ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች ይዘህ ወደ እርሱ ሂድ፤ እነርሱንም አልሰማም ቢል ለቤተ ክርስቲያን ንገር፤ ቤተ ክርስቲያንንም የማይሰማ ከሆነ እንደ አረመኔና ተጸጽቶ እንደማይመለስ ኃጢ አተኛ ቊጠረው» (ማቴ:ም:18ቁ: 15–17)።

ይህም ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ራሱ በጌታችን አነጋገር ውስጥ መግባቱና ያን ቃል ስሞታ ሊነገረው የሚችል በምእመናን መካከል መንፈሳዊ ዳኝነት ለመስጠት የተደራጀ አንድ ተቋም የነበረ መሆኑን ያመለክታል። ያም ባይሆን ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ ወደፊት ሊቋቋም ስላለው ስለቤተ ክርስ ቲያን መመሪያ እንደሰጣቸው ያሳያል። በዚህም ሆነ በዚያ ያ አባባል የሚያመለ ክተው ቤተ ክርስቲያንን የመሠረተው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን የመሠረታት አስቀድሞ በደሙ ዋጅቶአት መሆኑን ሲያመለክት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ብሏል:-

«መንፈስ ቅዱስ እናንተን ኤጲስ ቆጶሳት አድርጎ ሾሞአችኋል፤ እንግዲህ ለራሳችሁና ለመንጋው ተጠንቀቁ፤ እግዚአብሔር በገዛ ደሙ የዋጃትን ቤተ ክርስቲያን ጠብቁ» (የሐ:ሥ:ም:20ቁ:28)።

ቤተ ክርስቲያንን ለመዋጀት ጌታችን ደሙን ማፍሰስ ነበረበት። በደሙ የዋጃቸውን በቤተ ክርስቲያን አሰባሰባቸው። ይህም ማሰባሰቡ ቤተ ክርስ ቲያንን መመሥረቱ ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ስለዚሁ ጉዳይ ሲያብራራ እንዲህ ብሏል:-

«ስለዚህ እናንተ ከቅዱሳን ጋር የአንድ አገር ዜጎችና የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ናችሁ እንጂ ከእንግዲህ ወዲህ እንግዶችና መጻተኞች አይደላ ችሁም። በሐዋርያትና በነቢያትም መሠረት ላይ ታንጻችኋል፤ የማእዘኑም ራስ የሆነው ድንጋይ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሕንጻው በሙሉ በእርሱ ተገጣጥሞ የጌታ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ለመሆን ያድጋል። እናንተም እግዚአአብሔር በመንፈሱ የሚያድርበት ሕንጻ ለመሆን በክርስቶስ ትታነጻላችሁ» (ኤፌ: ም:2ቁ:19–22)።



www.ethiopianorthodox.org

«እርሱ ከሁሉ ነገር በፊት ነበረ፤ ሁሉም ነገር ተያይዞ የቆመው በእርሱ ነው፤ እርሱ አካሉ የሆነችው የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው» (ቆላ: ም: 1ቍ:17–18)።

«ሁሉንም ነገር በሥልጣኑ ሥር አድርጎ አስገዛለት፤ በቤተ ክርስቲያንም ከሁሉ በላይ እንዲሆን ራስ አደረገው፤ ቤተ ክርስቲያን የእርሱ አካል ናት፤ ክርስቶስም በቤተ ክርስቲያንና በሌላ ሁሉ የሞላ ነው» (ኤፌ: ም: 1ቍ: 22–23)።

ስለዚህ ከላይ በቀረቡት ልዩ ልዩ ማስረጃዎች መሠረት ጌታችን መድኃ ኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን በደሙ ዋጅቶአታል፤ አካሉ ነች፤ የቤተ ክርስቲያን ራስ ነው፤ እንዲሁም መሥራችዋ እርሱ ነው። ጌታችንም በደሙ ባይዋጃትና በእርሱ ላመኑት ልጅነትን ባይሰጥ ኖሮ ቤተ ክርስቲያ ባልተመሠረተችም ነበርና መሥራችዋ እርሱ ነው የሚባለው ስለዚህ ነው።

## ስዕሎችና አይቆኖች

ስዕል ሲባል በቀለም ቅብ፥ በመሳል ወይም ፎቶግራፍ በማንሣት አንድን ነገር ለምሳሌ ሰውን አስመስሎ የተሠራ ነገር ማለት ነው። ይህ አጠቃላይ የቃሉ ትርጉም ነው።

ስዕሎችና አይቆኖች ተብሎ በሚቀርብበት ጊዜ ግን በተለይ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙትን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን፥ የቅድስት እመቤታችን የድንግል ማርያምን፥ የነቢያትንና የሐዋርያትን፥ የሰማዕታትን እና የቅዱሳንን ስዕሎች ለማለት ነው። አይቆንም ማለት ስዕል ማለት ነው። ይሁ እንጂ አይቆን የሚባለው ልዩ ጸሎት ተጸልዮበት ከሌሎቹ ስዕሎች የተለየ ክብር የተሰጠውና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኝ ስዕል ነው።

እንደሚታወቀው የውጭ ሕዋሳታችን ካላሳወቁን በቀር ምንም ነገ ልናውቅ አንችልም። እነዚህም የውጭ ሕዋሳት ዕውቀትን ወደእኛ ለማድረ እንደ መግቢያ በር ናቸው። ሕዋሳቱ ወደ እኛ የሚያደርሱትን ዕውቀት ሐሳ ይስለዋል፤ ማስታወስ ደግሞ በአንጐል ክርታስ ላይ ይቀርጸዋል። ለምሳ ጆሮዎች ያልሰሙትንና ዐይኖች ያላዩትን ነገር እኛ ልናውቅ አንችልም በጆሮና በዐይን አማካይነት ካልሆነ በቀር ምን ሌላ ማወቂያ መንገድ ይኖረናል

ትምህርት ቤቶች ብዙዎቹን ትምህርቶች ለተማሪዎች ለማስረዳት የሚጠ ሙበት ዘዴ ስዕል በመሳል ነው። ለምሳሌ የጂኦግራፊን ትምህርት ለማስተማ የቦታዎችን የአቀማመጥ ካርታ መንደፍ (መሳል) ያስፈልጋል። የኬሚስት አስተማሪውም የተለያዩ ኬሚካሎችን በማቀላቀል ውጤቱን ለተማሪዎ



ያሳያል፤ የኤከኖሚክሱ አስተማሪ የተለያዩ ግራፎችን በመሳል፥ የጂኦሜ ትሪው አስተማሪ የተለያዩ አንግሎችን በመሥራት ለተማሪዎቻቸው ገለጻ ያደርጋሉ።

በዚህ ጉዳይ ሌሎችም ብዙ ምሳሌዎችን ማቅረብ ይቻላል።

ጆሮዎችና ዐይኖች ዕውቀትን ወደ እኛ የሚያደርሱ ታላላቅና የተሻሉ በሮች ስለሆኑ ቤተ ክርስቲያን ወደ ልጆችዋ እውነተኛውን ትምህርት ለማድረስ እንደ ትምህርት ቤት ትጠቀምባቸዋለች።

በጆሮ አመካይነት ሕይወት የሚሰጠውን የእግዚአብሔርን ቃል እንዲሰሙ ታደርግበታለች። ትምህርት በጆሮ በኩል አድርጎ ወደ ኅሊና ይደርሳል፤ በዐይን አማካይነት ደግሞ የቅዱሳን ሰማዕታትን የትግል ስዕል አሳይታ፥ ይህም በኅሊናቸው እንዲቀረጽ ታደርጋለች።

የትኛው ጨካኝ ልብ ነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደወንጀለኛ በሁለት ወንበዴዎች መካከል ተሰቅሎ ሲያይ የማይራራ? በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራስ ላይ በተደረገው የሾኽ አክሊል አማካይነት ከራሱ የሚፈስሰውን ደም ሲመለከት ልቡ የማይራራ የትኛው ጨካኝ ሰው ነው?

እንደዚህ ያሉት ትርኢቶች በእውነትም ልብን ይነካሉ። በዚህም ምክንያት ትርኢቱ በምእመናን ልብ ውስጥ ተቀርጾ ስሜትን እንዲሰጥ ቤተ ክርስቲያን በስዕሎች ትጠቀማለች።

አንዳንድ ወገኖች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ስዕሎችን መሳለም፥ ማጠንና በእነርሱ ፊት መስገድ፥ እንዲሁም ለእነርሱ ሻማ ማብራት ጣዖትን እንደ ማምለክ ነው ይላሉ። ለዚህም ምክንያታቸው የሚከተለው ጥቅስ ነው።

«በሰማይ ሆነ በምድር፥ ወይም ከምድር በታች ባለው ውሃ ውስጥ ከሚኖሩት ነገሮች የማንኛውንም ዐይነት ምስል ጣዖት አድርገህ አትሥራ፤ እኔ አምላክህ እግዚአብሔር እጅግ ቀናተኛ ስለሆንኩ ተቀርጾ የተሠራውን ማንኛውንም ዐይነት ጣዖት አታምልክ፤ አትስገድለት (ዘጸ:ም:20ቍ:4–5)።

ይህን በሚሉበት ጊዜ ግን በኦሪት ዘጸአት ም 25ቍ 18–22 ላይ ሙሴ የኪሩቤልን ምስሎች ሠርቶ በታቦቱ ላይ እንዲያስቀምጥ ከእግዚአብሔር የታዘዘ መሆኑን የረሱት ይመስላል። እነርሱ እንደሚሉት ትእዛዙ በፍጹም ስዕል እንዳይሠራ ከልክሎ ቢሆን ኖሮ የእግዚአብሔር ቃል የማለወጥ ስለሆነ ሙሴን ባላዘዘውም ነበር።



www.ethiopianorthodox.org

«እግዚአብሔር እንደ ሰው አይዋሽም፤ ሐሳቡንም እንደ ሰው አይለውጥም» (ዘኁ:23፥19)።

በዚህም ሠረት ትእዛዙ የሚያመለክተው ያ የሚሠራው ስዕል የተከለከለው እንዲመለክ የተሠራ እንደ ሆነ ብቻ ነው። ትእዛዙም የሚለው አታምልካቸው ነው።

ንጉሥ ሰሎሞን ቤተ መቅደስን ሠርቶ በጨረሰ ጊዜ የቤተ መቅደሱን ውስጠኛ ክፍል ያስጌጠው በተቀረጹ የኪሩቤል ምስሎች መሆኑን በመጀመርያው መጽሐፈ ነገሥት :ም:6ቍ:23–28 ይመለከቷል። ሰሎሞን ያንን በማድረጉ አልተወቀሰበትም፤ ሕዝቡም የኪሩቤልን ምስል አላመለከም። እንዲያውም የቤተ መቅደሱን ሥራ አጠናቅቆ ባስመረቀበት ቀን ለእግዚአብሔር ላቀረበው ጸሎት መልስ እግዚአብሔር ያን ቤተ መቅደስ እንደሚቀድሰውና ስሙንም በዚያ ለዘለዓለም እንደሚያኖር ቃል ገብቶለታል (1ኛ:ነገ:ም:9ቍ:1–3)።

እኛ ግን ለስዕሎቹ በምንሰግድበት ጊዜ የአክብሮት ስግደት እንጂ የአምልኮ ስግደት አለመሆኑ መታወቅ ይኖርበታል። የምንሰግደውም በስዕሉ አማካይነት ለባለስዕሉ ነው። ስዕሉንም የምንሳለመው፥ ካህኑ የሚያጥነውና እኛም ሻማ የምናበራለት ለባለ ሰዕሉ ክብር ነው። በስዕሉ አማካይነት የባለ ስዕሉ ታሪክ በኅሊናችን ተቀርጾ መንፈሳዊ ስሜትን ያሳድርብናል።

የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ:- «የእግዚአብሔርን ቃል በመጀመሪያ የነገሩአችሁን መሪዎቻችሁን አትርሱ፤ አኗኗራቸውንና የሥራቸውን ውጤት በማስታወስ እምነታቸውን ተከተሉ» ይላል (ዕብ:ም:13፥7)።

የምናስታውስበትም ዋነኛው መንገድ ስዕል ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካነበብነው ይበልጥ በስዕል ላይ ያየነውን እናስታውሳለን።

ስዕልም ክርስትና ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ የነበረ እንጂ አዲስ ነገር አለመሆኑን ለመረዳት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች ምን እንዳላቸው እንመልከት:-

«እናንተ ሞኞች የገላትያ ሰዎች ማን በጥንቈላ አፈዘዛችሁ? ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ ላይ ተሰቅሎ በፊት ለፊታችሁ በግልጥ ይታይ አልነበረምን? (ገላ:ም :3ቍ :1)።



ብዙዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ምሁራን ይህን ጥቅስ ሲተረጕሙ የጌታችን ስቅለት በስዕል ተስሎ በገላትያ ሰዎች ዘንድ ይታይ የነበረ መሆኑን ይስማሙበታል።

በቤተ ክርስቲያን ትውፊት መሠረት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የስቅለት ስዕል በመጀመሪያ የሳለው ወንጌላዊው ዮሐንስ ነው። የእመቤታችን የድንግል ማርያምን ስዕል ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ የሳለው ወንጌላዊው ሉቃስ ነው።

## <u>የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን</u>

<u>ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ</u>:- ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ ያስተማረው በፍልስጥኤም በጢሮስና በሲዶና እንዲሁም በኢትዮጵያ ነው።

ወደ ኢትዮጵያም መጥቶ ወደ ካህናቱ ከተማ ለመግባት በተነሣ ጊዜ አንድ ወጣት ተገናኝቶት ጠጕርህንና ጢምህን ተላጭተህ፥ በእጅህ ዘንባባ ካልያዝህ በቀር ወደ ከተማው ልትገባ አትችልም አለው። እርሱም ወጣቱ እንደነገረው አደረገ። ይህን ጉዳይ እያሰበ ሳለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚያ ቀድሞ በተገናኘው ወጣት መልክ ተገለጠለትና አይዞህ በርታ ብሎ ትሰወረበት። በዚህ ጊዜ ያ ቀድሞ የተገናኘው ወጣት ራሱ የክብሩ ጌታ እንደነበረ ዐወቀ።

ከካህናቱ አንዱን መስሎ ወደ ከተማው ገባና አብሎን ወደተሰኘው መስገጃቸው ሄዶ የካህናቱን አለቃ አገኘው። የእነርሱ አማልክት የማይሰሙና የማይንቀሳቀሱ መሆናቸውንና እውነተኛው አምላክ ግን ሰማይንና ምድርን የፈጠረ መሆኑን ገለጠለት። በዚህ ጊዜ ከሰማይ ጠረጴዛ በማውረድ የእግዚአብሔር ተአምር ታየ። በአካባቢውም ኀይለኛ ብርሃን አንጸባረቀ።

አርምዮስ የተባለው ካህን ይህን ተአምር ባየ ጊዜ የአምላክህ ስም ማን ይባላል? ብሎ ጠየቀው። ሐዋርያውም አምላኪ ክርስቶስ ነው ብሎ መለሰለት። ከዚያ በኋላ ካህኑ አርምዮስ በክርስቶስ አመነ፤ ብዙ ሰዎችም የእርሱን ፈለግ ተከተሉ።

የዚያ አገር ገዥ፥ የሆነውን ነገር በሰማ ጊዜ ያመኑት ሁሉ በእሳት እንዲቃጠሉ አዝዞ ነበር። ይሁን እንጂ በዚያን ጊዜ የአገረ ገዥው ልጅ ሞቶ ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ ከጸለየለት በኋላ ነፍሱ ተመልሳለት ከሞት ስለተነሣ ገዥውና የቀሩትም የከተማው ሰዎች ሁሉ አመኑ።

ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ ከዚያ ወጥቶ ወደሌሎችም አገሮች በመሄድ ወንጌልን ካስተማረ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ። በኢየሩሳሌም ወንጌልን አስተምሮአቸው ትምህርቱን ተቀብለውት የነበሩት የአይሁድ ወገኖች



www.ethiopianorthodox.org

ትምህርቱን በጽሑፍ እንዲያሰፍርላቸው ስለጠየቁት ወንጌሉን በዕብራይስጥ ቋንቋ ጻፈላቸው። የወንጌሉን ጽሑፍ ያጠናቀቀው በሕንድ አገር ያስተምር በነበረ ጊዜ ነው ይባላል። ይህም የሆነው ጌታችን ባረገ በዘጠነኛው ዓመት ነው።

በአገረ ገዥው በፊስጦስ ዘመን በድንጋይ ተወግሮ ሰማዕትነትን ተቀብሎአል።

ሥርዓተ ቀብሩም የቂሣርያ ክፍል በሆነችው በካርቴጅ በምእመናን አማካይነት ተፈጽሞአል። (የጥቅምት 12ቀን ስንክሳር)

<u>ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ</u>:- ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ የያዕቆብ ወንድምና የዘብዴዎስ ልጅ ነው። ወንድማማቾቹን ቅዱስ ጴጥሮስንና ቅዱስ እንድርያስን ከጠራ በኋላ ጌታችን ወዲያው እንዲከተሉት የጠራቸው ወንድማማቾቹን የዘብዴዎስን ልጆች ቅዱስ ያዕቆብንና ቅዱስ ዮሐንስን ነው። ከዐሥራ ሁለቱ የጌታችን ደቀ መዛሙርት መካከል ጌታችን የበለጠ ያስጠጋቸው የነበሩት ቅዱስ ጴጥሮስ፥ ቅዱስ ያዕቆብና ቅዱስ ዮሐንስ ናቸው። በተለየ ቅዱስ ዮሐንስ ደግሞ ጌታችን ይወድደው የነበረ ደቀ መዝሙር በመባል ይታወቃል። ስለዚህም ጌታችን በመስቀል ላይ በነበረ ጊዜ እናቱን ድንግል ማርያምን ለቅዱስ ዮሐንስ ዐደራ ሰጥቶአታል።

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ለማስተማር ዕጣ የወጣለት በእስያ አገሮች ነበር። በዚያ አካባቢ የነበሩ ሰዎች በጣም ክፉዎች ስለነበሩ የእግዚአብሔር ጥበቃ እንዳይለየው ጸለየ።

ደቀ መዝሙሩን አብሮኮሮስን በማስከተል ወደ ኤፌሶን ሄደ።

ለጉዞውም የተሳፈረበት መርከብ በመንገድ ላይ ተሰብሮ እያንዳንዱ ተሳፋሪ በመርከቡ ግድግዳ ላይ ተለጠፈ። ማዕበሉም አብሮኮሮስን ወደ አንድ ደሴት ወስዶ ጣለው።

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ግን በማዕበሉ እየተነሣና እየወደቀ በመጨረሻ በእግዚአብሔር ጥበቃና ዝግጅት ደቀ መዝሙሩ ወደ አለበት ደሴት በጥንቃቄ እስኪወሰድ ድረስ በባሕሩ ውስጥ ለብዙ ቀኖች ቈየ። በተገናኙም ጊዜ ስላደረገላቸው ጥበቃ እግዚአብሔርን አመሰገኑት።

ከዚያ በኋላ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ወደ ኤፌሶን ከተማ ሄዶ ስለ ድኅነት ያስተምር ጀመር። ሕዝቡ ግን ትምህርቱን አልተቀበለውም ነበር።



አንድ ቀን ለእናቱ አንድ ብቻ የነበረ ልጅ ለመታጠቢያ ውሃ ማሞቂያ በሚሆን የእሳት ማንደጃ ውስጥ ወደቀ። ሰዎች ሊያወጡት ቢሞክሩም እርሱ ግን ሞቶ ነበር። የእናቱ ሰቆቃው ምን ያኽል እንደነበር ለመገመት አያዳግትም። በዚህ ጊዜ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ወደ ልጁ በመቅረብ አጥብቆ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ። ከዚያም በመስቀለኛ ባረከውና በፊቱ ላይ እፍ ሲልበት ወዲያው ነፍሱ ተመለሰች። የልጁ እናት በጣም ተደስታ የደስታ እንባ ከዐይንዋ እየረገፈ የሐዋርያውን እግር ሳመች።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የከተማው ሕዝብ የሐዋርያውን ትምህርት ለመስማት በብዛት መምጣት ጀመረ። ብዙዎችም አምነው ተጠመቁ።

ይህ ሁናቴ ግን የጣዖት ካህናትን በጣም አበሳጨ። ይዘው ሊቦጫጭቁትም ብዙ ጊዜ ሞከሩ። የእግዚአብሔር ጥበቃ ስላልተለየው ግን አልቻሉም። እነርሱንም ከብዙ ትግል፥ ከብዙ ችግርና ከብዙ ጭቅጭቅ በኋላ እግዚአብሔርን እንዲያውቁ አደረጋቸው። ኤጲስ ቆጶሳትንና ካህናትን ከሾመላቸው በኋላ ከዚያ ተነሥቶ ወደ እስያ አካባቢ ሄደ። እዚያም አስተምሮ ብዙዎችን አሳመነ።

ሐዋርውያ ቅዱስ ዮሐንስ ወደ ዘጠና ዓመት ዕድሜ ኖሮአል። በጣም ከመሸምገሉም የተነሣ ወደ ምእመናን ስብሰባ ቦታ እየተሸከሙ ይወስዱት ነበር። በዕድሜውም መግፋት ምክንያት ልጆቼ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ በማለት ብቻ ንግግሩን ያሳጥር ነበር።

በስሙ ያለውን ወንጌል፥ በፍጥሞ ደሴት ሳለ ያየውን ራእይና ሦስት መልእክቶቹን ጽፎአል።

ከዚህ ዓለም በሞት የሚለይበት ጊዜ መቃረቡ ሲሰማው ሕዝቡን ጠርቶ ሥጋ ወደሙ አቀበላቸው። በእምነታቸው እንዲጸኑም አስተማራቸው።

በመጨረሻም ከኤፌሶን ከተማ ወጣ ባለ ቦታ ደቀ መዝሙሩንና ከእርሱ ጋር የነበሩትን ሰዎች ጒድጓድ እንዲቈፍሩለት አዘዛቸው።

ከዚያም በኋላ ከጌታችን ትእዛዝ ሳላስተምራችሁ የቀረሁት አንድም ስለሌለ እኔ ከደማችሁ ንጹሕ ነኝ፤ ከእንግዲህ ወዲያ ፊቴን እንደማታዩ ዕወቁ፤ እግዚአብሔር ለሁሉም እንደየሥራው ዋጋውን ይከፍለዋል አላቸው። ይህን ባለ ጊዜ እጁንና እግሩን ስመውት ትተውት ሄዱ።

ሕዝቡም ይህን ጉዳይ ሰምተው ሐዋርያው ወደ ሄደበት ቦታ ቢሄዱ ዐርፎ አገኙትና ጥልቅ በሆነ ሐዘን አለቀሱለት።

www.ethiopianorthodox.org



www.ethiopianorthodox.org

ምንም እንኳ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ እንደ ሌሎቹ ሐዋርያት በሰይፍ የሞተ ባይሆን በድንግልናውና በቅድስናው ምክንያት በሰማያዊው ክብር ከእነርሱ ጋር ይተካከላል እንጂ አያንስም። (የጥር:4 ቀን ስንክሳር)

## የቤተ ክርስቲያን ዜማ

## የቅዳሴ ተሰጥዎ

### በግዕዝ

ይ:ዲንፍቅ:- ጸልዩ በእንተ እለ ያበውኡ መባአ።

ይ:ሕ:-ተወከፍ መባአሙ ለአኃው ወተወከፍ መባአን ለአኃት ለነኒ ተወከፍ መባአነ ወቍርባነነ።

ይ:ዲ :- ትእዛዘ አበዊነ ሐዋርያት፥ ኢያንብር ብእሲ ውስተ ልቡ ቂመ ወበቀለ፥ ወቅንዓተ፥ ወጽልአ ላዕለ ቢጹ ወኢላዕለ መኑሂ።

ይ:ዲ :- ስግዱ ለእግዚአብሔር በፍርሃት።

ይ:ሕ:- ቅድሜከ እግዚኦ ንሰግድ ወንሴብሐከ።

ይዲ :- ተንሥኡ ለጸሎት።

ይ:ሕ:- እግዚኦ ተሣሀለነ

ይ: ካ:- ሰላም ለኵልክሙ።

ይ:ሕ:- ምስለ መንፈስከ ።

ይ: ካ:- ንስግድ።

ይ:ሕ:- ለአብ፥ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እንዘ ሠለስቱ አሐዱ።

ይ:ካ ሰላም ለኪ።

ይ: ሕ:-ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ማኅደረ መለኮት

ይ:ካ:- ሰዓሊ ለነ።

ይ:ሕ:- ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ።

ይ:ካ :- አንቲ ውእቱ።



ይ:ሕ:- ማዕጠንት ዘወርቅ እንተ ፆርኪ ፍሕመ እሳት ቡሩክ ዘነሥአ እመቅደስ ዘይሠሪ ኃጢአተ ወይደመስስ ጌጋየ። ዝ: ውእቱ ዘ እግዚአብሔር ቃል ዘተሰብአ እምኔኪ ዘአዕረገ ለአቡሁ ርእሶ ዕጣነ ወመሥዋዕተ ሥሙረ። ንሰግድ ለከ ክርስቶስ ምስለ አቡከ ኄር ሰማያዊ ፥ወመንፈስከ ቅዱስ ማሕየዊ እስከ መጻእከ ወአድኀንከነ።

ይ:ዲ:- ተንሥኡ ለጸሎት።

ይ:ሕ:- እግዚኦ ተሣሀለነ።

### በአማርኛ

ይ:ዲ: ( ንፍቅ) :- መባ ስለሚያገቡ ሰዎች ጸልዩ።

ይ: ሕ:- የወንድሞችን መባ ተቀበል፤ የእኅቶችንም መባ ተቀበል፤ የእኛንም መባችንንና ቍርባናችንን ተቀበል።

ይ:ዲ:- የአባቶቻችን የሐዋርያት ትእዛዝ ነው። ሰው በባልንጀራው ላይ፥ በማንም ላይ ቢሆን ቂምና በቀልን፥ ቅናዓትንና ጥላቻን በልቡ አያኑር።

ይ:ዲ:- በፍርሃት ለእግዚአብሔር ስገዱ።

ይ: ሕ :- አቤቱ በፊትህ እንሰግዳለን እናመስገንሃለንም።

ይ:ዲ:- ለጸሎት ተነሡ።

ይ:ሕ:- አቤቱ ይቅር በለን።

ይ: ካ :- ሰላም ለሁላችሁ ይሁን

ይ: ሕ :-ከመንፈስ ጋራ

ይ: ካ :- እንስገድ፥

ይ: ሕ :-ለአብ ለወልድ፥ ለመንፈስ ቅዱስ ሦስት ሲሆን አንድ ነው።

ይ: ካ :- ሰላም ለአንቺ ይሁን።

ይ: ሕ :- የአምላክ ማደሪያ ቅድስት ቤተ ክርቲያን ሆይ ፥

ይ: ካ :- ለምኝልን።

ይ:ሕ:አምላክን የወልድሽ ድንግል ማርያም ሆይ፥



www.ethiopianorthodox.org

ይ: ካ :- አንቺ ነሽ።

ይ: ሕ:- የእሳቱን ፍም የተሸከምሽ፥ ቡሩክ በቤተ መቅደስ የያዛት የወርቅ ጥና አንቺ ነሽ፤ ኃጢአትን የሚያስተሠርይ፥ በደልንም የሚያጠፋ ካንቺ ሰው የሆነና ራሱን ለአባቱ ያማረ መሥዋዕትና ዕጣን አድርጎ ያቀረበ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ክርስቶስ ሆይ ቸር ከሚሆን ከሰማያዊ አባትህ ጋራ፥ ሕይወት ከሚሆን ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ መጥተህ አድነሽናልና እንሰግድልሃለን።

ይ:ዲ ለጸሎት ተነሡ።

ይ:ሕ አቤቱ ይቅር በለን።

## ጥያቄዎች

1. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያውን ጴጥሮስን ለምን አመሰገነው?

2. አለት የሚለው ምን ተብሎ ተተረጐመ?

3. ጌታችን የቤተ ክርስቲያን መሥራች እርሱ ራሱ መሆኑን በምን ዐይነት ገለጠ?

4. ቤተ ክርስቲያን በምን ዐይነት እምነት ላይ ትመሠረታለች?

5. የቤተ ክርስቲያን ደንቦችና ሥርዓቶች የተዘጋጁት በማን ወይም እንዴት ነው?

6. እንደየጉዳዩ አመጣጥ ቤተ ክርስቲያን የሚያሰኙ ምን ምን ናቸው?

7. አልሰማም ቢልህ ለቤተ ክርስቲያን ንገር በሚልበት ጊዜ የትኛውን ትርጉም ያመለክታል?

8. ለቤተ ክርስቲያን ተቋም ደንቦችና ሥርዓቶች የተዘጋጁት በኋላ ዘመን ሲሆን እንዴት ጌታችን ለቤተ ክርስቲያን ንገር አለ?

9. በገዛ ደሙ የዋጃት ሲል የትኛውን ትርጓሜ ያመለክታል?

10. ስዕል ማለት ምን ማለት ነው?

11. አይቆን ማለትስ ምን ማለት ነው?

12. አይቆንና ስዕል ተብሎ በሚቀርብበት ጊዜ ምንን ያመለክታል?

14. የዕውቀት በር ናቸው የተባሉት ሁለቱ ሕዋሳት ምንና ምን ናቸው?



15. ትምህርት ቤቶች በምን ዐይነት ስዕሎች ይጠቀማሉ?

16. ቤተ ክርስቲያንስ በእነዚህ ሕዋሳት የምትጠቀመው እንደምን አድርጋ ነው?

17. ልብን ያራራሉ ተብለው የተጠቀሱት ስዕሎች የትኞቹ ናቸው?

18. አንዳንድ ወገኖች ስዕልን የሚቃወሙት ምን ብለው ነው?

19. ማስረጃ አድርገው የሚያቀርቡት ጥቅስስ የትኛውን ነው?

20. ያን ጥቅስ በሚያቀርቡበት ጊዜ ምንን የረሱ ይመስላል?

21. ጥቅሱ እነርሱ እንደሚሉት አለመሆኑን የምናስረዳው በምንድነው?

22. ታዲያ፥ ትእዛዙ የሚያመለክተው ምንን ነው?

23. በመጀመሪያው መጽሐፈ ነገሥት ምዕራፍ 6 ቍ:23–28 ምን ማስረጃ እናገኛለን?

24. እኛ ለስዕሎቹ የምንሰጠው ክብር ለእነዚያ ለስዕሎች ብቻ ብለን ነውን?

25. በዕብራውያን መልእክት ምዕራፍ 13 ቍ:7 ላይ ምን ማስረጃ እናገኛለን?

26. በስዕል ከምናየውና በመጽሐፍ ከምናነበው የትኛውን ይበልጥ እናስታውሳለን?

27. በገላትያ መልእክት ምዕራፍ 3 ቍ:1 ላይ: ምን ማስረጃ እናገኛለን?

28. በቤተ ክርስቲያን ትውፊት መሠረት በመጀመሪያ የጌታችንን ስቅለት ስዕል የሠራ ማን ነው?

29. የእመቤታችንን የድንግል ማርያምንስ ስዕል በመጀመሪያ የሠራ ማን ነው?

30. ወንጌላዊው ማቴዎስ ያስተማረው በየትኞቹ አገሮች ነው?

31. ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ወደ ካህናቱ ከተማ ለመግባት ሲነሣ አንድ ወጣት ምን ምክር ሰጠው?

32. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያው ማቴዎስ በማን መልክ ተገለጠለት?



www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

33. ሐዋርያው ማቴዎስ ለካህናቱ አለቃ ምን አለው?

34. በዚያን ጊዜ ምን ዐይነት ተአምር ታየ?

35. አርምዮስ የተባለው ካህን ሐዋርያውን ምን ጠየቀው?

36. ሐዋርያውስ ምን መልስ ሰጠው?

37. ከዚያስ በኋላ አርምዮስ ምን አደረገ?

38. የአገሩ ገዥ ምን ወስኖ ነበር?

39. ሐሳቡን ያስለወጠው ምንድነው?

40. ወንጌሉን በምን ቋንቋ ጻፈው?

41. ጽሑፉን ያጠናቀቀው በየት አገር ሆኖ ነው?

42. ሰማዕትነቱን የተቀበለው በማን ዘመን ነው?

43. ሥርዓተ ቀብሩስ የት ተፈጸመ?

44. ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ የማን ልጅና የማን ወንድም ነው?

45. ቅዱስ ዮሐንስ ምን በመባል ይታወቅ ነበር።

46. ለጌታችን ቅርብ መሆናቸው የሚነገርላቸው ሦስት ደቀ መዛሙርት እነማን ነበሩ?

47. ጌታችን ከመስቀሉ ግርጌ የነበረውን ቅዱስ ዮሐንስን ምን አለው?

48. ለሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ የማስተማር ዕጣ የወጣለት ወዴት ነበር?

49. በዚያ አካባቢ የነበሩ ምን ዐይነት ሰዎች ናቸው?

50. ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ስለምን ጉዳይ ጸለየ?

51. ወደ ኤፌሶን የሄደው ማንን አስከትሎ ነው?

52. በጉዞው ላይ ምን ደረሰበት?

53. በመጨረሻ ወደ የት ደረሰ?

54. ከዚያ በኋላ ወዴት ሄዶ ምን ያስተምር ጀመረ?

55. ሰዎቹ ትምህርቱን ማዳመጥና መቀበል የጀመሩት መቼ ነው?

56. የጣዖት ካህናት ምን ሊያደርጉ ፈለጉ?

57. ፍላጎታቸው ያልተሳካላቸው በምን ምክንያት ነው?



58. በመጨረሻስ እንዴት ሆኑ?

59. ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ በጣም በመሸምገሉ ሰዎች ምን ያደርጉለት ነበር?

60. እርሱስ ምን ብሎ ያስተምር ነበር?

61. እርሱ የጻፋቸው መጻሕፍት የትኞቹ ናቸው?

62. ደቀ መዝሙሩንና ከእርሱ ጋር የነበሩትን ሰዎች ከኤፌሶን ወጣ ብሎ ምን እንዲያደርጉ አዘዛቸው?

63. ይህን ያዘዛቸው መቼ ነው?

64. እዚያ ቦታ ሆኖስ ምን አላቸው?

65. እነርሱስ ትተውት የሄዱት ምን ካደረጉ በኋላ ነው?

66. ሕዝቡስ ይህን ሲሰማ ምን አደረገ?

## ምዕራፍ 5

## መንፈሳዊነትና ግብረገብነት

### ይቅርታ ማድረግ እንጂ ቂም አለመያዝ

ቂም መያዝ የክርስቲያን ሃይማኖት የሚቃወመው ከመሆኑም በላይ ቂም የሚይዘውንና ቂም የተያዘበትን ይጐዳል እንጂ ለማንም የሚጠቅም አይደለም።

አንድ ሰው ሌላውን ሰው በአንድ ነገር ቢበድለው የተበደለው ሰው ቂም ይይዛል። ይህም ማለት የተበደለው ሰው በበደለው ሰው ላይ ቅሬታ ያድርበታል፤ ያዝናል፤ ጥላቻም ያድርበታል፤ ወይም ቂም ለያዘበት ሰው በጎ ነገር አይመኝለትም፤ ወይም ምንም በጎ ነገር አያደርግለትም።

ታዲያ ቂም መያዝ ሁለቱንም ይጐዳል ሲባል እንዴት አድርጎ ሁለቱንም ይጐዳል? ተብሎ ይጠየቅ ይሆናል።

ሰዎች ሲቀያየሙ ስለሚራራቁ የመረዳዳትና የመጠቃቀም ነገር ሁሉ ይቀራል። ለሰው መድኀኒቱ ሰው ሲሆን ተቀያይሞ መለያየት ግን ያን



www.ethiopianorthodox.org

ያስቀራል። ይህም በሁለቱም በኩል ነው እንጂ በአንዱ ወገን ላይ ብቻ የሚመጣ ችግር አይደለም።

አንዳንድ ጊዜ እንደሚደረገው ቂም የያዘ ሰው ቂም በያዘበት ሰው ላይ ክፉ ነገር በማድረግ ይበቀለው ይሆናል። ክፉ ነገር የሚያደርግ ሰው ደግሞ በዚህ ዓለምም ሆነ በሚመጣው ዓለም ከመጐዳት በቀር ምንም አይጠቀምም። በዚህ ዓለም ሳለ ዓለማዊው የሕግ ፍርድ ይበቀለዋል። በወዲያኛው ዓለም ደግሞ ክፉ አድራጊን እግዚአብሔር ይቀጣዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ በቀል የተወሰደበት ሰው ሕይወቱን፥ ጤንነቱን ወይም ንብረቱን በማጣት ይጐዳል። እርሱም በሕይወት ካለ የበቀል በቀል በመውሰድ ተበቃዩን ይበቀል ይሆናል። እርሱም እንደገና የመጀመሪያው ተበቃይ ችግር ይደርስበታል።

እንደሚታወቀው በዚህ ዓለም ብዙ በደለኞች ሰዎች አሉ። የበደሉንን ሰዎች በመቀየምና እርስ በርስ በመለያየት በቀል እስከመውሰድ ድረስ የምንደርስ ከሆነ በግለሰብና በኅብረተሰቡ ላይ ሊመጣ የሚችለውን ችግር ልናጤነው ይገባል።

ለዚህ ችግር ታዲያ መፍትሔው ምንድነው?

ለዚህ ጥያቄ መልስ ለማግኘት እስቲ የቅዱሳት መጻሕፍትን አባባሎች እንመልከት:-

«ወንድምህን በልብህ አትጥላው፤ በእርሱ ምክንያት ኃጢአት እንዳይ ሆንብህ ገሥጸው። መበቀል አትፈልግ በወገንህ በማንም ላይ ቂም አትያዝ፤ አትበቀል፤ ነገር ግን ጐረቤትህን እንደራስህ ውደድ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ» (ዘሌ19ቍ:17–18)።

«ወንድሞች ሆይ፥ ሰው ማናቸውንም ስሕተት አድርጎ ቢገኝ መንፈሳውያን የሆናችሁት እናንተ እንዲህ ዐይነቱን ሰው በገርነት አቅኑት» (ገላ:ም:6 ቍ:1)።

«እርስ በርሳችሁ ደጎችና አዛኞች ሁኑ፤ እግዚአብሔር በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ፥ እናንተም እርስ በርሳችሁ ይቅር ተባባሉ» (ኤፌ:ም:4ቍ:32)።

«እርስ በርሳችሁ ታገሡ፤ ከእናንተ አንዱ በሌላው ላይ ቅር የተሰኘበት ነገር ቢኖር ይቅር ተባባሉ» (ቆላ:ም:3ቍ:13)።

ከላይ የተዘረዘረሩት የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች ያመለከቱት እርስ በርሳችን እንድንፋቀር እንጂ ቂም እንዳንይዝና በቀል እንዳንበቀል መከል ከላችንን ነው። የቅዱሳት መጻሕፍትን መመሪያዎች በጥብቅ የተከተልን እንደሆነ በመካከላችን ቂምና በቀል አይኖሩም። በእነርሱም ምክንያት የሚመ ጣው ችግር ስለማይኖር ሰላማዊ ኅብረተሰብ ይኖረናል ማለት ነው።

እነዚህን ከላይ የተዘረዘሩትን ትእዛዞች ብንፈጽም ዋጋችን ምንድነው?

«የሰዎችን በደል ይቅር ብትሉላቸው እናንተንም የሰማዩ አባታችሁ ይቅር ይልላችኋል» (ማቴ:ም:6ቍ:14)።

«ይቅር በሉ፤ እናንተም ይቅርታ ታገኛላችሁ (ሉቃ:ም:6ቍ:37)።

በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህን ትእዛዛት ባንፈጽም ምን እንደሚደርስብን የሚያመለክቱትን ጥቅሶች ቀጥለን እንመልከት:-

«እንግዲህ እናንተም እያንዳንዳችሁ ወንድማችሁን ከልብ ይቅር ባትሉ በሰማይ ያለው አባቴም እንዲሁ ያደርግባችኋል» (ማቴ:ም:18ቍ:35)።

«በሰማይ ያለው አባታችሁ ኃጢአታችሁን ይቅር እንዲልላችሁ እናንተም ለጸሎት በምትቆሙበት ጊዜ በሰው ላይ የያዛችሁትን ቂም ተዉ» (ማር:ም:11ቍ:25)።

«የእግዚአብሔር ፍርድ ምሕረት ለማያደርግ ሰው ምሕረትን አያደ ርግም» (ያዕ:ም:2ቍ:13)።

ስለዚህ ቂምና በቀልን እንዳንከተል መመሪያ ተሰጥቶናል፤ መመሪያውን ብናከብር ምን ዋጋ እንደምናገኝ ተስፋ ተሰጥቶናል፤ መመሪያውን ባናከብር ደግሞ ምን እንደሚደርስብን ተነግሮናል። በዚህም መሠረት ከሰውና ከእግ ዚአብሔር ጋር በሰላም ለመኖር እንችል ዘንድ ትእዛዛቱን በጥንቃቄ መጠበቅ ይኖርብናል።

## ደግነት

የሰው ደግነት ስንል ምን ማለታችን ነው?

በምድራውያን ፈላስፎች አስተሳሰብ ደግነት ሲባል የማይጨበጥ ሐሳባዊ ነገር ወይም ግብረገባዊ መለኪያ ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት ግን ደግነትን የሚያዩት እንደ እውነተኛ ተግባራዊ ልምምድ አድርገው ነው።

www.ethiopianorthodox.org

በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት ደግነት ሲባል ቸርነት ርኅሩኅነት፥ ለጋስነት፥ ታማኝነት፥ ታጋሽነት፥ ችግረኛን መርዳት፥ ትሕትና፥ አንደበትን ሌላውን ሰው ከሚያስቀይም ንግግር መግታት፥ በቃል መርጋትና ሌሎችም እነዚህን የመሳሰሉ ሆናቴዎች ናቸው።

ቅዱሳት መጻሕፍት ደግነትን በተመለከተ ምን እንደሚሉ እንመልከት።

«ከክፉ ነገር ሽሹ፤ መልካም ነገርንም አድርጉ፤ ሰላምን ፈልጉአት፤ ተከተሉአትም» (መዝ:34ቍ:14)።

«ደግ ማድረግን ተማሩ፥ ፍትሕ እንዳይጓደል አድርጉ፤ የተጨቈኑትን ታደጉ፥ አባትና እናት የሞቱባቸውን ልጆች መብት ጠብቁ፥ ባሎቻቸው ሞቱባቸውንም ሴቶች ስሙ» (ኢሳ:ም:1ቍ:17)።

«ክፉውን ጥሉ፤ ደጉን ውደዱ፤ በአደባባይም ፍትሕን መሥርቱ፤ ምናልባት የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ለዮሴፍ ቅሬታ ይራራ ይሆናል» (አሞ:ም:5:ቍ:15)።

«ሟች ሆይ፥ ደግነት ምን እንደሆነ ነግሮሃል፤ ፍትሕ ታደርግና ርኅራኄን ትወድድ ዘንድ በቀር እግዚአብሔር ከአንተ የሚፈልገውስ ምንድነው? ከአምላክህም ጋር በትሕትና ትራመድ ዘንድ አይደለምን? (ሚክ:ም:6ቍ:8)።

«ከእናንተ ማንም ሰው በክፉ ፈንታ ክፉ እንዳይመልስ ተጠንቀቁ፤ ነገር ግን ሁልጊዜ እርስበርሳችሁና ለሁሉም ደግነትን አድርጉ» (1ኛ: ተሰ: ም: 5ቍ:15)።

«እንግዲህ ዕድል ባጋለጠመን ጊዜ ሁሉ ለሁሉም በተለየም ለሃይማኖት ቤተሰቦች ደግ እናድርግ» (ገላ:ም:6ቍ:10)።

«እንግዲህ እንደ እግዚአብሔር ምርጦች ቅዱሳንና የተወደዳችሁ ሆናችሁ ምሕረትን፥ ርኅራኄን፥ ቸርነትን፥ ትሕትናን፥ የዋህነትን፥ ትዕግሥትን ልበሱ» (ቆላ:ም:3ቍ:12)።

እንግዲህ ደግነት ስንል የእግዚአብሔርን ፈቃድ እየጠበቁ፥ ለሰው ሁሉ መልካም እያደረጉና መልካምም እያሰቡ መኖር ማለታችን ነው። ቃለ እግዚ አብሔርም የሚለው ይህንኑ ነው።

እርዳታ ስንል ደግሞ የተለያዩ የእርዳታ ዐይነቶች አሉ። ለተቸገረ ገንዘብ በመስጠት፥ በምክር፥ ትምህርት በማስተማር፥ የነጻ ማኅበራዊ አገልግሎት በመስጠት ኅብረተሰቡን መርዳት ይቻላል።



www.ethiopianorthodox.org

የአብርሃም እንግዳ ተቀባይነት፥ የሎጥ እንግዳ ተቀባይነት፥ የደጉ ሳምራዊ ምሳሌ ከደግነት ምሳሌዎች መካከል ናቸው (ዘፍ: 18፥19፥ ሉቃ: ም: 10ቍ:25–37)።

## በጎ አድራጊዎችና አገልግሎት ሰጪዎች ሊመሰገኑ ይገባል

በሥራቸው አጋጣሚም ሆነ በበጎ ፈቃድ ተነሣሥተው ለግለሰብ ወይም ለኅብረተሰቡ የተለያዩ እርዳታዎችንና ቅን አገልግሎቶችን የሚያበረክቱ ሰዎች አሉ። እንደእነዚህ ያሉት ሰዎች ሥራቸው ታውቆላቸው ቢመሰገኑ የበለጠ በጎ ሥራ ይሠራሉ፤ ሌሎችም ሰዎች የእነርሱን አርአያነት ይከተላሉ። ለምሳሌ አንድ ሐኪም የሰዎችን ጤንነት ለመጠበቅ በሚያደርገው ጥረት ቢመሰገን የበለጠ ጥረት ያደርጋል፤ ሌሎችም ሐኪሞች የእርሱን አርአያነት ይከተላሉ። አንድ የፖሊስ ሠራዊት አባል አድልዎ ሳያደርግና በጥቅም ሳይደለል በትክክል ሲሠራ በመገኘቱ ተመስክሮለት ምስጋና፥ ሹመት፥ ሽልማት ቢያገኝ የበለጠ ለመሥራት ይበረታታል፤ ሌሎችም የሥራ ጓደኞቹ የእርሱን አርአያነት ይከ ተላሉ። አንዲት ነርስ በተሰለፈችበት የሕክምና ሙያ ሕመምተኞችን በመር ዳት በትጋትና በቅንነት መሥራትዋ ታውቆላት ብትመሰገን እርስዋም የበለጠ ትሠራለች የሥራ ጓደኞችዋም የእርስዋን አርአያነት ይከተላሉ። አንድ የመሥ ሪያ ቤት ሠራተኛ ዕውቀቱን፥ ጊዜውንና ጉልበቱን ሳይቈጥብ በቅንነትና በትሕትና ሥራውን ሲያከናውን በመታየቱ ምስጋና፥ ሽልማትና ሹመት ቢያ ገኝ በሥራው የበለጠ ይበረታታል፤ የሥራ ጓደኞቹም የእርሱን አርአያነት ይከተላሉ። እነዚህ ሁሉ በሥራቸው አጋጣሚ በትክክል ለሚሠሩ ሰዎች የተ ሰጠ ምሳሌ ነው።

ሌሎች ደግሞ በበጎ ፈቃድ ተነሣሥተው የሙት ልጆች ማሳደጊያ፥ የአረጋውያን መጦሪያ፥ የሥራ ፈቶች ማቋቋሚያ፥ የአካለ ስንኩላን ማቋቋ ሚያ ትምህርት ቤት፥ ክሊኒኮችና ሌሎችም እነዚህን የመሳሰሉ ማኅበራዊ አገል ግሎቶችን የሚያቋቁሙ ሰዎች ሥራቸው በሰፊው ታውቆላቸው ምስጋናና ድጋፍ ቢያገኙ የበለጠ ይሠራሉ፤ ሌሎችም የእነርሱን አርአያነት ይከተላሉ። ለምሳሌ በዓለማችን በአሁኑ ጊዜ ያሉ ደራስያንና በጥናት አዳዲስ ክሥተቶችን የሚያገኙ ሰዎች በትጋት የሚሠሩት ምስጋናና የኖቤል ሽልማት የማግኘት ዕድል ስላላቸው ነው።

አንድ የሕፃናት ማሳደጊያና መርጃ ትምህርት ቤት ያቋቋመ ሰው ምስጋናና ድጋፍ ቢያገኝ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ቤትነት ሊያሳድገውና ብዛት ያላቸውን ችግረኞች ለመቀበል ስለሚችል የኅብረተሰቡን ችግሮች ያቃልላል። እንዲሁም አንድ ክሊኒክ የሠራ ሰው ሥራው ታውቆለት ቢመሰገንና የሌሎችንም ድጋፍ

ቢያገኝ ክሊኒኩን ወደ ሆስፒልነት ደረጃ ሊያሸጋግር ይችላል። ይህም ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች የእነዚያን አርአያነት ይከተላሉ።

በዚህም መሠረት ሰው ሁሉ አገልግሎቱና ጥረቱ ታውቆለት ሲመሰገን የበለጠ ለመሥራት ስለሚገፋፋውና የኅብረተሰቡም ደኅንነት እየተሻሻለ ስለሚ ሄድ ቢያንስ ቢያንስ አገልግሎት ሰጪዎችንና በጎ አድራጊዎችን አሰምተን ማመስገን ይኖርብናል።

## ለትክክለኛ ኑሮ ምሳሌ መሆን

ለትክክለኛ ኑሮ ምሳሌ ለመሆን የሚቻለው እግዚአብሔርና የአካባቢያችን ኅብረተሰብ ከእኛ የሚጠብቁትን መንገድ ወደ ቀኝ ወይም ወደግራ ሳንል በቀጥታ እየተከተልን የኖርን እንደሆነ ነው። በእርግጥ ፍጹምነት በእግ ዚአብሔር ዘንድ እንጂ በማንም ሰው ዘንድ የሚገኝ አይደለም። ይሁን እንጂ ማንም ሰው በዘመንና በቦታ ካለበት ጊዜና አካባቢ ካሉ ሰዎች የተሻለ ሆኖ ከተገኘ እንደ ምሳሌ ሆኖ ይወሰዳል። ለምሳሌ ሎጥ የወይን ጠጅ ጠጥቶ በሰከረ ጊዜ ከሁለት ሴቶች ልጆቹ ጋር የዝሙት ሥራ መሥራቱ ይታወሳል (ዘፍ: ም:19ቍ:30–37)። ይሁን እንጂ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ እንዲህ ሲል ያመሰግነዋል:- «በዐመፀኞች አሳፋሪ ድርጊት እየተሠቀቀ ይኖር ነበረውን ጻድቁን ሎጥን አዳነው» (2ኛ:ጴጥ:ም: 2ቍ:7)።

ከዚህ ሌላ ምሳሌ ደግሞ ንጉሥ ዳዊት ነው። ንጉሥ ዳዊት ሚስቱን ለመውረስ ብሎ ኦርዮን በማስገደሉና ያልተፈቀደለትን የሕዝብ ቈጠራ በማድ ረጉ መቀጣቱ ይታወሳል (2ኛ:ሳሙ:11:14–17፥2ኛ:ዜና:ም :21)። ከዚህ ሁሉ ጋር ነው እግዚአብሔር ለዳዊት እንዲህ ሲል የመሰከረለት:- «ከልቤ ምወድደውን፥ ፈቃዴንም የሚፈጽመውን የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ» (የሐ:ሥ:ም:13ቍ:22)።

በዚህም መሠረት የሰው ልጅ ጻድቅነት አንጻራዊ ነው እንጂ ፍጹምነት አይደለም።

በመጀመሪያ ደረጃ ሰው ለሌሎች ሰዎች ምሳሌ ወይም አርአያ ሊሆን የሚችለው በእርሱና በእግዚአበሔር መካከል ባለው ግንኙት ነው። እነዚህም በእግዚአብሔር ላይ ያለው እምነትና ለሕግጋተ እግዚአብሔር ያለው ተገዥነት ናቸው። ዝርዝር ትእዛዛቱን በጥንቃቄ ከመጠበቅ ጋር፥ በሥጋ ወደሙ በመወ ሰን፥ በጾም፥ በጸሎት፥ ምጽዋትን በማዝወተርና በሌሎችም የበጎ ተግባር ሥራዎች፥ በተለየም ከገቢ ሁሉ ዐሥራትን በማውጣት የሚኖር ቢሆን በምሳሌነት የሚጠቀስ ይሆናል። ዐሥራት ደግሞ የእግዚአብሔር ድርሻ የሆነ



www.ethiopianorthodox.org

ግዴታ እንጂ ትሩፋት አለመሆኑ በግልጽ መታወቅ ይኖርበታል (ሚል 3፥8–10)።

ሁለተኛ/አንድ ሰው ለሌሎች ሰዎች ምሳሌ ወይም አርአያ ለመሆን የሚችልባቸው መንገዶች ከሰዎች ጋር በሚኖረው ግንኙነት ነው።

ሰዎችን ሁሉ እንደራስ አድርጎ መውደድ፥ የባልና የሚስት ፍጹም አንድነትና ተግባብቶ በመረዳዳት መኖር፥ አጠቃላይ አባባሎች ናቸው። ከእኩያ ሰው ጋር በወንድምነትና በእኅትነት ፍቅር መኖር፥ በዕድሜም ሆነ በደረጃ ከፍ ከፍ ያለን ሰው እንደ አባትና እንደ እናት ማክበር፥ በዕድሜና በደረጃ ዝቅ ብሎ ለሚገኝ ሰው እንደወለዱት ልጅ አድርጎ ፍቅር ማሳየት፥ እነዚህን ሁሉ ሰዎች ከልብ በሚመነጭ የፍቅር ፈገግታ ማስተናገድ በምሳሌ ነት ወይም በአርአያነት የሚጠቀስ ተግባር ነው።

ቤተሰብን በተመለከተ፥ አንድ ሰው ቤተሰቡን በሥርዓት ለማስተዳደር የሚችለው ባልና ሚስት በፍቅር ተስማምተው ቤታቸውን በጋራ ሲያስተ ዳድሩት፥ ሁለቱም አምነውበት የየራሳቸውን ድርሻ ያለምንም ቅሬታ ሲያከ ናውኑ፥ የወር ገቢአቸውን አብረው በማቀድ በሥራ ላይ ሲያውሉት፥ ስለልጆች አስተዳደግ ሥርዓት በስምምነት ሲያከናውኑ፥ ከዚህም ሁሉ በላይ በልጆቻቸውም ፊት ሆነ በሌሎች ሰዎች ፊት ምንም ዐይነት ያለ መግባባት ምልክት ሳያሳዩ የኖሩ እንደሆነ በምሳሌነት ወይም በአርአያነት የሚጠቀሱ ይሆናሉ። ኑሮአቸውም የተቃና ይሆንላቸዋል።

## ጥያቄዎች

1. ቂም መያዝ የሚጠቅመው ማንን ነው?
2. አንድ ሰው ቂም የሚይዘው በምን ምክንያት ነው?
3. ቂም መያዝ ማለትስ ምን ማለት ነው?
4. አንዳንድ ጊዜ ቂም የያዘ ሰው ምን ዐይነት ፍላጎት ያድርበታል?
5. ቂም መያዝ ቂም የያዘውንና ቂም የተያዘበትን ሰው ሁለቱንም የሚጐዳው እንዴት ነው?
6. በቀልን የሚበቀል ሰው እንዴት ይጐዳል?
7. በቀል የሚወሰድበት ሰው በምን ዐይነት ይጐዳል?
8. በቀል የሚወሰድበት ሰው የተበቃይ ሰው ችግር የሚደርስበት መቼ ነው?

9. ለችግሮቹ መፍትሔ እንዴት ሊገኝ ይችላል?

10. የቅዱሰት መጻፍቱ ጥቅሶች ምንን ያመለክታሉ?

11. የቅዱሳት መጻሕፍቱን መመሪያዎች በጥብቅ ብንጠብቅ ምን ውጤት እናገኛለን?

12. ትእዛዞቹን ብንጠብቅ የምናገኘው ጥቅምና ባንጠብቅ ደግሞ የሚደርስብን ችግር ምንና ምን ናቸው?

13. የደግነትን አጠቃላይ ትርጉም ግለጽ

14. በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት ደግነት ሲባል ምንን የመሳሰሉ ናቸው?

15. የእርዳታ ዐይነቶች ምንና ምንን የመሳሰሉ ናቸው?

16. ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የደግነት ምሳሌዎችን አቅርብ።

17. ለኅብረተሰቡና ለግለሰቦች እርዳታና አገልግሎት የሚያበረክቱ ምን ዐይነት ሰዎች ናቸው?

18. እነዚህ ሰዎች ምን ቢሆኑ ነው የበለጠ ሊሠሩ የሚችሉት?

19. ለምሳሌም አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎችን ጥቀስ።

20. ምን ምን ዐይነት የበጎ ፈቃድ አገልግሎቶች አሉ?

21. እነዚህን አገልግሎቶች የሚያበረክቱ ሰዎች ምን ምን ያስፈልጋቸዋል?

22. ያን ቢያገኙ ምን ውጤት ይኖረዋል?

23. የኑሮ ምሳሌ ለመሆን ምን ምን ሁለት መንገዶች አሉ?

24. ፍጹም መሆን አለመቻሉና ምሳሌነቱ በምን ይታረቃሉ?

25. ሰው ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖረው ግንኙትና ከሰዎች ጋር በሚኖረው ግንኙት ምሳሌ የሚሆንበትን መንገድ ግለጽ።



# አራተኛ ክፍል

## ምዕራፍ 1

## ትምህርተ ሃማኖት

### የእግዚአብሔር አዳኝነት

**ብሉይ ኪዳን**:- በብሉይ ኪዳን ስለ እግዚአብሔር አዳኝነት በሚነገርበት ጊዜ ከሰው ዐቅም በላይ ከሆነ ዓለማዊ ችግር ማዳን ማለት ነው። ለምሳሌ የእስራኤልን ሕዝብ ከግብጽ ባርነት ነጻ ማውጣቱ፥ እስራኤሎች ከእነርሱ የሚበልጡ ጠላቶቻቸውን ድል ለመንሣት እንዲችሉ ማድረጉና ከሌሎችም ተመሳሳይ ዓለማዊ ችግሮች ማዳኑ የእግዚአብሔር አዳኝነት በመባል ይታወቃሉ።

ለዚህ አባባል ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች ያሉ ቢሆንም ለምሳሌነት ያኽል አንድ ብቻ ቀርቦአል።

«እግዚአብሔርም የእስራኤልን ልጆች እንዲህ አላቸው:- ግብጻውያን፥ አሞራውያን፥ የአሞን ልጆች፥ ፍልስጥኤማዊያን፥ ሲዶናውያን፥ አማሌቃውን ማዖናውያን ባስጨነቁአችሁ ጊዜ ወደ እኔ ጮኻችሁ ከእጃቸው አላዳንኋችሁምን?» (መሳ:ም:10ቍ:11–12)።

በብሉይ ኪዳን የሚቀርቡ አብዛኞዎቹ ጸሎቶች እግዚአብሔር ቀደም ብሎ ስላደረጋቸው ድርጊቶች ምስጋናና ለወደፊቱም ከተለያዩ የዚህ ዓለም ችግሮች እንዲያድን ልመና ናቸው (2ኛ:ሳሙ:ም:22 ቍ:2–20፥ 2ኛ:ዜ: መ: ም: 20 ቍ: 9፥ መዝ:7፥54፥59፥ ዕን:ም:1ቍ:2–4)።

አዲስ ችግሮች ባጋጠሙ ቍጥር አዲስ የማዳን ሁናቴ አስፈላጊ ነበር።

**ሐዲስ ኪዳን**:- በሐዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር አዳኝነት ሲባል ፈጥኖ የሚታወሰን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ሥጋ ለብሶ ለሰው ዘር ቤዛ መሆኑ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከጥንቱ ማለት ከተወረሰው የአዳም ኃጢአት ተቤዥቶናል።

www.ethiopianorthodox.org

በቤተ ክርስቲያን እምነት ሰዎች የሚድኑት በጥምቀት አማካይነት ከሚያገኙት የእግዚአብሔር ልጅነት ወይም ከዳግም ልደት ነው። ይህንንም አባባል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያረጋግጠው «ያመነና የተጠመቀ ይድናል፤ ያለመነ ግን ይፈረድበታል» ብሎአል (ማር:16፥16)።

ለድኅነት የግድ ጥምቀትና እንደገናም መወለድ አስፈላጊ መሆኑን በማያወላውል ቋንቋ ጌታችን ለኒቆዲሞስ ሲገልጥለት እንዲህ ብሏል:-

«እውነት፥ እውነት እልሃለሁ፤ ሰው እንደገና ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም» (ዮሐ:ም:3ቍ:3)።

«እውነት፥ እውነት እልሃለሁ፤ ሰው ከውሃና ከመንፈስ ቅዱስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም» (ዮሐ:ም:3ቍ:5)።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም የዳንነው በጥመቀትና በልጅነት መሆኑን ሲያብራራ እንዲህ ብሏል:-

«እኛ በሠራነው የጽድቅ ሥራ ሳይሆን በምሕረቱ አዳነን፤ ያዳነንም በአዲስ ልደት መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት በተገኘው መታደስ ነው» (ቲቶ:ም:3ቍ:5)።

«ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ባላችሁ ኅብረት በእምነት አማካይነት ሁላችሁም የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ። በጥምቀት ከክርስቶስ ጋር አንድ የሆናችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋል» (ገላ:ም:3ቍ:26–27)

በጥምቀት አማካይነት አዲስ ልደት፥ አዲስ ሕይወትና አዲስ ጸጋ እንቀበላለን። እነዚህም ስጦታዎች መንፈሳዊ ሕይወትን ለመኖር ያስችሉናል። ይሁን እንጂ እነዚህ ስጦታዎች ኃጢአትን እንዳንሠራ የሚከለክሉን፥ ከስሕተትና ከነቀፋ ነጻ የሚያደርጉን አይደሉም። እኛ በሥጋዊ ሰውነታችን እስከ አለን ድረስ ኃጢአትን እንዳንሠራ የሚያስገድደን ነገር አይኖርም። በጥምቀት አማካይነት የተቀበልነው የመታደስ ጸጋ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠርንበትን የነጻ ፈቃድ ጸጋ አላስወገደውም። ደግ ወይም ክፉ የማድረጉ ነጻነት አሁንም ከእኛ ጋር አለ። በፍጹም ኃጢአት ለመሥራት የማንችለውና የጽድቅን አክሊል የምንጐናጸፈው በወዲያኛው የዘለዓለማዊ ሕይወት ብቻ ነው።

ከላይ የተገለጠውን አባባል የሚቃወሙ ወገኖች:- «ሰው ከመንፈስ ቅዱስ ከተወለደና በልቡም ካመነ በኋላ ሊጠፋ አይችልም» ይላሉ። ለዚህም አባባላቸው ማስረጃዎች ናቸው ብለው የሚያቀርቡአቸው የሚከተሉት ናቸው።

--------------------



1. ሰው የሚድነው በእግዚአብሔር ጸጋ እንጂ በራሱ ድካምና ሥራ አይደለም (ሮሜ:8:29–30፥9፥16፥ ኤፌ:2፥8)።

2. እግዚአብሔር በሰው ልብ የሚዘራው ዘር የማይጠፋ ነው (1ኛ:ጴጥ:1፥23)።

3. «አማኝ የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ እግዚአብሔር መንግሥቱን ያወርሰዋል» (ፊል:1፥2ኛ:ጢሞ:1:12፥ 1ኛ:ጴጥ:1፥3–5)።

4. ክርስቶስ ለተከታዮቹ የሚሰጠው ሕይወት የዘለዓለም ሕይወት ነውና ማንም ከእጁ ሊነጥቃቸው አይችልም (ዮሐ:10፥27–28)።

ለቀረቡት ማስረጃዎች የተሰጡ መልሶች:-

1. ምንም እንኳ የሰው ልጆች በጎ ተግባር ከእግዚአብሔር ውለታ ጋር ለማነጻጸር ባይቻል፥ ይብዛም ይነስም እግዚአብሔር ከሰው ዘር የሚጠይቃቸው ግዴታዎች አሉ። ሰዎችም እነዚያን ግዴታዎች ካላሟሉ የእግዚአብሔርን ጸጋ ሊያገኙ አይችሉም። በማቴዎስ ወንጌል ም:25ቍ:15–30 ብንመለከት በመክሊቶች አሰጣጥ ምሳሌ በመክሊቱ የሠሩበት እንደተመሰገኑና ያልሠራበት ግን እንደተወቀሰ እንመለከታለን። እንዲሁም በዚሁ ምዕራፍ ከቍጥር 1 እስከ 13 በተነገረው የዐሥር ደናግል ምሳሌ የተዘጋጁት አምስቱ ከሙሽራው ጋር ወደ ሠርጉ አዳራሽ እንደገቡና አምስቱ ያልተዘጋጁት ግን በሩ እንደተዘጋባቸው እናነባለን። ታዲያ የምንድነው በጸጋ ብቻ ከሆነ ያ ገንዘቡን ቀብሮ የጠበቀው አገልጋይና አምስቱ ልጃገረዶች ለምን ከጓደኞቻቸው የተለየ ዕድል ፈንታ አጋጠማቸው? እንዲሁም ጌታ ስለፍርድ ቀን በማቴዎስ ወንጌል ም:25 ቍ:41–43 ላይ በሚገልጽበት ጊዜ በግራው በኩል ያሉትን:- «እናንተ ርጉማን ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘለዓለም እሳት ከእኔ ወዲያ ሂዱ፤ ተርቤ አላበላችሁኝም፤ ተጠምቼ አላጠጣችሁኝም፤ እንግዳ ሆኜ አልተቀበላችሁኝም፤ ታርዤ አላለበሳችሁኝም፤ ታምሜና ታስሬ አልጠየቃችሁኝም ይላቸዋል» ብሎአል። ታዲያ፥ መዳን በጸጋ ብቻ ቢሆን ኖሮ እነዚያ በጎ ተግባር ያልፈጸሙት ሰዎች ባልተወቀሱም ነበር። ለጊዜው ብቻ ለማስረጃነት እነዚህ ይበቃሉ ተብሎ ነው እንጂ በዚህ ጉዳይ ላይ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎችን ለማቅረብ በተቻለ ነበር።

2. እዚህ ላይ ትክክለኛው ጥቅስ «ዳግመኛ የተወለዳችሁት ሕያው በሆነውና ለዘለዓለም ጸንቶ በሚኖረው በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋው ዘር ነው እንጂ ከሚጠፋ ዘር አይደለም» የሚል ነው (1ኛ:ጴ:ም:1ቍ:23)።

--------------------



www.ethiopianorthodox.org

ታዲያ፥ ይህ ጥቅስ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ቃል ዘለዓለማዊነት ነው እንጂ ያ ዳግመኛ የተወለደ ሰው ኃጢአት አይሠራም ለማለት አይደለም። ይህም መሆኑን ለመረዳት በቍጥር 24 እና 25 ላይ በግልጽ ተብራርቶ እና ገኘዋለን።

«መጽሐፍ እንደሚለው:- ሥጋ ለባሽ ሁሉ እንደ ሣር ነው፤ ክብሩም ሁሉ እንደ ዱር አበባ ነው፤ ሣሩም ይደርቃል፤ አበባውም ይረግፋል፤ የእግዚአብሔር ቃል ግን ለዘለዓለም ጸንቶ ይኖራል።»

3. የተሰጡት ሦስት ጥቅሶችና የተሰጡበት ዓላማ አይመሳሰልም።

4. እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሚሰጠው ተስፋ ሁልጊዜ ከግዴታ ጋር የተያያዘ ነው፤ በዚህም መሠረት የጌታችን ተከታዮች እስከመጨረሻ ተገቢ ሆነው ቢገኙ ነው የዘለዓለምን ሕይወት የሚሰጣቸው። ለምሳሌ ይሁዳ ከዐሥራ አንዱ የጌታችን ደቀ መዛሙርት ጋር ዕድል ፈንታ ተሰጥቶት ነበር። ነገር ግን ብቁ ሆኖ ስላልተገኘ ቦታውን ሌላ ሰው ወሰደበት።

ሰው ከመንፈስ ቅዱስ ከተወለደ በኋላ በጸጋ የዳነ ስለሆነ ኃጢአተኛ ሊሆን አይችልም የሚሉት ወገኖች አብዛኛውን ጊዜ የሚያቀርቡት ማስረጃ የቅዱስ ጳሉሎስን አባባሎች ነው። አባባሎቹንም ቃል በቃል ከመውሰድ በቀር ምንም ዐይነት ትርጓሜ ሊሰጡአቸው ፈቃደኞች አይደሉም።

ወደ ሮሜ ሰዎች በላከው መልእክቱ ም:7:ቍ:14–24 እርሱ የሚፈልገውን ሳይሆን እርሱ የማይፈልገውን ነገር እንደሚያደርግ በመግለጥ በሰውነቱ ውስጥ ስላለው ትግል ይናገራል። በወጨረሻም እኔ ምንኛ ጕስቋላ ሰው ነኝ? ከዚህ ሟች ሰውነትስ ማን ያድነኛል በማለት ብስጭቱን ይገልጣል።

ድነናል፤ ወይም ጸድቀናል ብለው ለሚመጻደቁ ሰዎች ትምህርት ይሆናቸው ዘንድ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የሚከተለውን ምክር ሰጥቶአል።

«በትሕትና ተሞልታችሁ ሌሎች ሰዎች ከእናንተ እንደሚሻሉ አድርጋችሁ ቍጠሩ እንጂ ወገን በመለየትና በራስ ወዳድነት ወይም ያለ እኔ ማን አለ በሚል ትምክሕት ምንም ነገር አታድርጉ» (ፊል:ም:2ቍ:3)።

ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ እርሱ ራሱ ድኘአለሁ፤ ወይም ጸድቄአለሁ የሚል ሳይሆን ስለራሱ በሚናገርበት ጊዜ በምን ዐይነት ትሕትና እንደሚናገር ቀጥለን እንመልከት:-

«ይህን ሁሉ ገና አላገኘሁም፤ ወይም በዚህ ሁሉ ፍጹም ሆኜአለሁ ለማለት አልችልም፤ ይሁን እንጂ ኢየሱስ ክርስቶስ እኔን የእርሱ አድርጎ ያዘጋጀልኝን ሽልማት ለማግኘት ወደፊት በመሮጥ እተጋለሁ። ወንድሞቼ ሆይ፥ ገና ወደዚያ እንደደረስሁ አልቈጥርም፤ ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤ ይኸውም በስተኋላዬ የነበረውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እተጋለሁ» (ፊል: ም3ቍ:12–13)።

ታዲያ ቅዱስ ጳውሎስን የሚያኽል የክርስቶስ አገልጋይ ራሱን በዚህ ዐይነት ትሕትና ሲያቀርብና ሌሎችንም ሲመክር የመጽሐፉን መንፈስ ሳይሆን ፊደሉን ብቻ መሠረት በማድረግ ድነናል፤ ጸድቀናል፤ ኀጢአት አንሠራም ማለትን ምን አመጣው።

«ፊደል ይገድላል መንፈስ ግን ሕይትን ይሰጣል» (2ኛ:ቆሮ:3፥6)።

የእግዚአብሔር ልጅነትን ከተቀበሉ በኋላ በፍጹም አይጠፉም ብለው ለሚከራከሩ ሰዎች ቅዱሳት መጻሕፍት ቀጥተኛ መልስ ስለሚሰጡአቸው ይህን ማስረጃ አተኩረው ቢመለከቱት መልካም ነው። እንዲያውም ቀድሞውንም ቢሆን ከልብ ያላመኑ ስለነበረ ነው እንጂ ባልጠፉም ነበር ይላሉ።

ቅዱስ መጽሐፍ ግን ምን እንደሚል እንመልከት:-

«ከመንገድ የወጡትን ሰዎች ወደ ንስሓ መመለስ እንዴት ይቻላል? እነዚህ ሰዎች ከዚህ በፊት ብርሃን በርቶላቸው ነበር፤ ሰማያዊውንም ስጦታ ቀምሰው ነበር፤ ከመንፈስ ቅዱስም ጋር ተካፋዮች ሆነው ነበር፤ የእግዚአብሔርን መልካም ቃልና የሚመጣውን ዓለም ኀይል ቀምሰው ነበር፤ ከዚህ ሁሉ በኋላ ከመንገድ ከወጡ፥ እነርሱ የእግዚአብሔርን ልጅ እንደገና ስለሚሰቅሉትና ስለሚያዋርዱት እነርሱን ወደ ንስሓ መመለስ አይቻልም» (ዕብ: ም:6ቍ:4–6)።

ከሐዋርያው ከቅዱስ ጳውሎስ ሌላ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም በሚቀጥሉት አባባሎቹ በማስረጃነት ተጠቅሶአል።

«የእግዚአብሔር ባሕርይ በውስጡ ስለሚኖርና፥ ከእግዚአብሔርም ስለተወለደ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ኃጢአት አይሠራም፤ ሊሠራም አይችልም» (1ኛ:ዮሐ:ም:3ቍ:9)።


www.ethiopianorthodox.org

«የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሚጠብቀው የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ሁሉ ደጋግሞ ኃጢአት እንደማይሠራ እናውቃለን፤ ሰይጣንም አይነካውም» (1ኛ:ዮሐ: ም: 5 ቍ 18)።

ከላይ የተገለጹት ጥቅሶች የሚያመለክቱት አንድ ሰው የልጅነትን ጸጋ ከታደለ በኋላ በፍጹም ኃጢአት አይሠራም ለማለት ሳይሆን ኃጢአት ቢሠራ ያን ኃጢአት የሚሠራው በእግዚአብሔር ልጅነቱ አይደለም ለማለት ነው። ሐዋርያው ቅዱስ  ዮሐንስ ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ መሆኑን ደኅና አድርጎ ያውቃል። ከላይ የቀረቡት ጥቅሶች የራሳቸው ትርጓሜ ስላላቸው ነው እንጂ ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ በዚሁ በአንደኛ መልእክቱ ቃል በቃል ከተወሰደው ከእነዚኛዎቹ አባባሎች ተቃራኒ የሆነ አባባል ባላቀረበም ነበር።

«የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል። ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናታልላለን፤ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም። ኃጢአታችንን ለእግዚአብሔር ብንናዘዝ፥ እርሱ ታማኝና ጻድቅ ስለሆነ ኃጢአታችንን ሁሉ ይቅር ይልልናል፤ ከበደላችንም ሁሉ ያነጻናል» (1ኛ: ዮሐ:ም:1ቍ:7–9)።

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ በዚህ መልኩ ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ መሆኑን አረጋገጠ እንጂ ዳግመኛ የተወለደ በፍጹም ኃጢአት አይሠራም በማለት አልጻፍም።

ድነናል፤ ጸድቀናል፤ በፍጹም ኃጢአት አንሠራም ብለው ከሚያቀርቡ አቸው የቅዱስ ጳውሎስ አባባሎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል:-

«በጥምቀት ከእርሱ ጋር በተቀበርን ጊዜ የእርሱ ሞት ተካፋዮች ሆነናል፤ ስለዚህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሞት እንደተነሣ እኛም በአዲስ ሕወት እንኖራልን» (ሮሜ:ም6:ቍ:4)።

«እናንተ የመሞት ያኽል ከኃጢአት እንደተለያችሁና በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ግን ለእግዚአብሔር በሕይወት እንደምትኖሩ አስቡ» (ሮሜ: ም:6:ቍ:11)።

«አሁን እናንተ የምትኖሩት ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች ስላልሆነ ኃጢአት ሊገዛችሁ አይችልም» (ሮሜ:ም:6ቍ:14)።

ከላይ በቀረቡት ሦስት ጥቅሶች ውስጥ ግሦቹ የሚያመለክቱት ታሪካዊ ማረጋገጫ ሳይሆን ምክርን ወይም ትእዛዝን ነው። በመጀመሪያው ጥቅስ ላይ



በአዲስ ሕይወት እንኖራለን ሲል በአዲስ ሕይወት እንኑር ለማለት ነው። በሁለኛው ጥቅስ በሕይወት እንደ ምትኖሩ አስቡ ያለው ለእግዚአብሔር በሕይወት ኑሩ ለማለት ነው። በሦስተኛው ጥቅስ ደግሞ ኃጢአት ሊገዛችሁ አይችልም ማለት ኃጢአት ሊገዛችሁ አይገባም ለማለት ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ታዲያ፥ በቀጥታ በትእዛዝ ወይም በምክር አነጋገር መናገር ሲችል ለምን እንደተፈጸመ ታሪካዊ ትረካ አድርጎ አቀረበው?

ትምህርቶችን በሰሚዎች ኅሊና ለመቅረጽና ተቀባይነትን ለማረጋገጥ ምክርን ወይም ትእዛዛዊ አነጋገርን እንደተፈጸመና ወይም በእርግጥ እንደ ሚፈጸም ጉዳይ አድርጎ ማቅረብ የብዙ ሰባኪዎች ዘዴ ነው። ለምሳሌ በስብከታቸው መካከል ለእኛ ለአማኞች ሁሉ የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልናል ይላሉ። በሰሚዎቹ ኅሊና እንዲቀረጽ ለማድረግ፥ ልክ አይደለም? ብለው ይጠይቃሉ።

እያንዳንዳችን በእግዚአብሔር መንገድ ለመራመድ ተዘጋጅተናል ካሉ በኋላ ልክ አይደለም? ብለው ይጠይቃሉ።

ሌሎችም ተመሳሳይ መግለጫዎችን ይሰጣሉ፤ ሲያስፈልግም ይጠይቃሉ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በሮሜ መልእክቱ ም:6:ላይ ያቀረባቸው መግለጫዎች ተመሳሳይ ናቸው። ይህም አባባል ትክክል መሆኑን የምንረዳው ከእነዚያ ከመግለጫዎቹም ጋር በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ ምክር መስጠቱ ነው።

«ኃጢአት በሚሞተው ሰውነታችሁ ላይ ሥልጣን እንዲኖረውና ለሥጋ ምኞትም ተገዥ እንዲያደርጋችሁ አትፍቀዱለት። እንዲሁም የሰውነታችሁን ክፍሎች የዐመፅ መሣሪያ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታስገዙ፤ ነገር ግን ከሞት እንደተነሣችሁ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ፤ የሰውነታችሁንም  ክፍ ሎች ሁሉ የጽድቅ መሣሪያ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አስገዙ» (ሮሜ: ም:6ቍ:12–13)።

እነዚያ ሦስቱ መግለጫዎች ቃል በቃል መወሰድ የሚገባቸው ቢሆኑ ኖሮ እነርሱ ለደኅንነትና ለጽድቅ ማረጋገጫ ስለሆኑ በዚያው ምዕራፍ ውስጥ ሌላ ምክር መስጠት ባላስፈለገም ነበር።

ስለዚህ ከመጽሐፉ መንፈስ ሳይሆን ከመጽሐፉ ፊደል ተነሥተን የተሳሳተ ሐሳብ ከማቅረብ እንጠንቀቅ።



www.ethiopianorthodox.org

## አማላጅነት

<u>የአማላጅነት ትርጉም</u>:- ማማለድ ማስታረቅን ይመስላል። ማስታረቅ ሲባል ሁለት የተጣሉ ሰዎችን አንተም ተው፣ አንተም ተው ብሎ ማስማማት ሲሆን አማላጅነት ግን ትንሽ ከዚህ ለየት ይላል። አንድ ሌላውን ሰው ያስቀየመ በደለኛ አንድም ጥፋቱን በመገንዘቡ፥ ወይም ካስቀየመው ሰው በኩል የነበረውንና ሊኖረው የሚችለውን ጥቅም ስለሚቀርበት፥ ወይም ደግሞ ከዚያ ካስቀየመው ሰው ጋር በሰላም ካልኖረ ችግር ሊደርስበት ስለሚችል አስታርቁኝ ብሎ አማላጅ ይልካል። አማላጅ በመላክ ፈንታ ራሱ ሄዶ ይቅርታ የማይጠይቀው አንድም ያስቀየመውን ሰው ከማክበሩ የተነሣ በቀጥታ መሄድን እንደድፍረት በመቍጠሩ፥ ወይም ያን ሰው በጣም በማስቀየሙ እንዴት አድርጌ ዐይኑን ለማየት እችላለሁ ብሎ በመፍራት፥ ወይም ደግሞ ያ አማላጅ የሚላክበት ሰው በደረጃው ከፍ ያለ ከመሆኑ የተነሣ በቀላሉ ሊያገኘው የማይችል በመሆኑ ነው።

አማላጅ ሆኖ የሚላከውም ሰው አግባብቶ እሺ ለማሰኘት ተሰሚነት ያለው ሰው መሆን ይኖርበታል።

አማላጅነት የሚለውን ቃል ትርጉም በተመለከተ የተደረገው ገለጻ እስከዚህ ድረስ ይብቃና ልንወያይበት ወደተነሣነው ወደ ቅዱሳን አማላጅነት እንመለስ።

<u>ስለቅዱሳን አማላጅነት</u>:- ኃጢአተኛው የቅዱሳንን አማላጅነት የሚፈልገው ከፍተኛ ኃጢአት በመሥራቱ በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር ሄዶ ይቅርታ መለመን እግዚአብሔርን እንደመዳፈር ስለሚቆጠረው ነው። ይህም ድርጊት እግዚአብሔርን በጣም የማክበር ትሕትና ነው እንጂ የአምላክን ክብር ለፍጡር አሳልፎ መስጠት አይደለም።

<u>የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አስታራቂነትና የቅዱሳን አማላጅነት ልዩነት:</u> አንዳንድ ወገኖች ክርስቶስ አማላጃችን ስለሆነ ሌላ አማላጅ አያስፈልገንም ይላሉ። ይህን በሚሉበት ጊዜ ማስረጃ ብለው ከሚያቀርቡአቸው ጥቅሶች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል።

«እንዴት መጸለይ እንደሚገባን ስለማናውቅ መንፈስ ቅዱስ በድካማችን ይረዳናል፤ በቃል ሊገለጥ በማይችል መቃተት ያማልደናል» (ሮሜ:8፥26)።



«እግዚአብሔር አንድ ነው፤ በመካከል ሆኖ እግዚአብሔርንና ሰውን የሚያስታርቀውም አንድ ነው፤ እርሱም ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» (1ኛ:ጢሞ:ም:2ቍ:5)።

«ስለዚህ እነርሱን ለማማለድ ለዘለዓለም ሕያው ሆኖ ስለሚኖር በእርሱ አማካይነት ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ሁሉ በፍጹም ሊያድናቸው ይችላል» (ዕብ:7፥25)።

«ልጆቼ ሆይ፥ ይህ የምጽፍላችሁ ኃጢአት እንዳትሠሩ ብዬ ነው፤ ነገር ግን ማንም ሰው ኃጢአት ቢሠራ በአብ ዘንድ ጠበቃ አለን፤ እርሱም ጻድቁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው» (1ኛ:ዮሐ:ም:2ቍ:1)።

መንፈስ ቅዱስ በድካማችን እንደሚረዳንና ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በለበሰው ሥጋ ቤዛ ሆኖ መለኮትንና ትስብእትን ማስታረቁ የታወቀ ነው። በዕብራውያን መልእክት የተገለጠው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የአሮን ልጆች የሆኑትን ካህናት ከጌታችን ዘለዓለማዊ ክህነት ጋር ያነጻጸረበት ነው እንጂ ለአማላጅነት የቀረበ ጥቅስ አይደለም። ሐዋርያው ዮሐንስ ክርስቶስ በአብ ዘንድ ጠበቃችን መሆኑን የገለጠው በደሙ ያዳነን መሆኑን ለማመልከት ነው። ይህንኑም ግልጽ ሲያደርገው:- «የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአታችን ሁሉ ያነጻናል» ብሎአል (1ኛ:ዮሐ:ም:1 ቍ:7)።

ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረው አማላጅነት ስለ እኛ በደል ዋጋ የከፈለበት ቤዛነት ነው እንጂ ከቅዱሳን አማላጅነት ጋር ተመሳሳይ አይደለም። ይኸውም ከዘመናት በፊት ነቢዩ ኢሳይያስ እንዲህ ብሎ ትንቢት የተናገረለት ነው:-

«እኛ እያንዳንዳችን ከመንገድ በመባዘን እንደ ጠፉ በጎች ሆነን ነበር፤ እያንዳንዳችን በየራሳችን መንገድ ሄደን ነበር፤ ነገር ግን እኛ ልንቀበለው የሚገባንን ቅጣት ሁሉ በእርሱ ላይ አኖረ» (ኢ.ሳ:ም:53ቍ:6)።

በዚህም መሠረት አምላክ የሰውን ሥጋ ለብሶ ያደረገውን ቤዛ ሆኖ ማስታረቅ ማንኛውም ፍጡር ሊያከናውነው የማይችል በመሆኑ አስታራቂአችን ወይም አማላጃችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው አስኝቶታል። የክርስቶስን አማላጅነት አስታራቂነት ብንለው የተሻለ ይሆናል።

የቅዱሳን አማላጅነት ግን አምላክ በደላችንን ይቅር ይልልን ዘንድ እንዲጸልዩልን እግዚአብሔር ላከበራቸው ቅዱሳን የምናቀርበው ምልጃ ነው። ታዲያ እነርሱን በመለመን ፈንታ ለምን በቀጥታ እግዚአብሔርን አትለምኑም

www.ethiopianorthodox.org

ብለው የሚጠይቁን ጠያቂዎች አሉ። ለእነርሱ የምንሰጠው መልስ ከእኛ ጸሎት ይልቅ የቅዱሳን ጸሎት በእግዚአብሔር ዘንድ የበለጠ ተቀባይነት ስላለው ነው ብለን ነው። ይህንንም የምንለው ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት በማድረግ ነው እንጂ ከራሳችን ያፈለቅነው ሐሳብ አይደለም። እግዚአብሔርም የቅዱሳኑን ጸሎት የሚቀበል መሆኑን በመግለጥ ሰዎችን ወደ አማላጆች እንዴት አድርጎ እንደላከ በሚከተሉት ማስረጃዎች እንመልከት:-

«አሁን ግን ሴቲቱን ለባልዋ መልሰህ ስጥ፤ እርሱ ነቢይ ስለሆነ እንዳትሞት ይጸልይልሃል፤ እርስዋን መልሰህ ባትሰጥ ግን እንደምትሞት ዕወቅ፤ አንተ ብቻ ሳትሆን፥ ሕዝብህም በሙሉ ታልቃላችሁ» (ዘፍ:ም:20ቍ:7)።

«ስለዚህ አሁን ሰባት ወይፈኖችና ሰባት አውራ በጎችን ይዛችሁ ወደ ባሪያዬ ወደ ኢዮብ ሂዱ፤ እዚያም ስለራሳችሁ ኃጢአት የሚቃጠል መሥዋዕት አቅርቡ፤ ባሪያዬ ኢዮብ ይጸልይላችኋል፤ እኔ ጸሎቱን ስለምቀበል በበደላችሁ መጠን አልቀጣችሁም» (ኢዮ:ም:42ቍ:8)።

አማላጃችን አንድ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው እንጂ የፍጡር አማላጅነት አስፈላጊም ጠቃሚም አይደለም የሚሉት ወገኖች ይህን የእግዚአብሔርን ምስክርነት ምን ትርጉም ይሰጡት ይሆን? እኔ የኢዮብን ጸሎት ስለምቀበል ሂዱ እርሱ ይጸልይላችሁና ይቅርታ አደርግላችኋለሁ አለ እንጂ ሌላ ሰው ሳይሆን ራሳችሁ ብቻ ጸልዩ አላለም። እንዲሁም አቢሜሌክን አብርሃም ነቢይ ስለሆነ እንዳትሞት ይጸልይልሃል ብሎታል። እኛ እኮ ቅዱሳንን ወደ እግዚ አብሔር እንዲያማልዱን እንለምናቸዋለን እንጂ የእግዚአብሔርን ክብር ሰጥተን አናመልካቸውም። አክብሮት ደግሞ አምልኮ አይደለም። እኔ ወደ እግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ ብቃት ስለሌለኝ የቅዱሳን አማላጅነት ያስፈ ልገኛል ማለት በትሕትና እግዚአብሔርን ማክበር ነው እንጂ የእግዚአብሔርን ክብር ለፍጡር አሳልፎ መስጠት አይደለም።

<u>የቅዱሳን ክብርና ዕውቀት</u>:- ቅዱሳን የእኛን ፍላጎት እንዴት ዐውቀው ሊረዱን ይችላሉ? የሚሉ ጥያቄዎች በየጊዜው ይነሣሉ። እግዚአብሔር ለቅዱሳኑ ዕውቀትንና ክብርን ሰጥቶአቸዋል።

ለምሳሌ ነቢዩ ኤልሳዕ በዚህ ዓለም በነበረ ጊዜ ደቀ መዝሙሩ ግያዝ በመሥጢር ከሶርያዊው ንዕማን ስጦታ መቀበሉን እንዴት እንዳወቀ በሁ ለተኛው መጽሐፈ ነገሥት:ም:5ቍ:25–27 ይመለከቷል።



ከሶርያ ንጉሥ ባለሟሎች አንዱ ለንጉሡ ስለኤልሳዕ እንዲህ ሲል ነገረው:- «ጌታ ሆይ፥ እንዲህ አይደለም፤ ነገር ግን በእልፍኝህ ውስጥ ሆነህ የምት ናገረውን በእስራኤል ዘንድ ያለ ነቢይ ኤልሳዕ ለእስራኤል ንጉሥ ይነግረዋል» (2ኛ:ነገ:ም:6ቍ:12)።

በረሀቡ ጊዜ የእስራኤል ንጉሥ ሊያስገድለው መልእክተኛ መላኩን ኤልሳዕ ዐወቀ። (2ኛ:ነገ:ም:6ቍ:13)።

በዚሁም ዓዓይነት ሐዋርያው ጴጥሮስ የሐናንያንና የሰጲራን ምሥጢራዊ ስምምነት ዐውቆ ቀጣቸው (የሐ:ሥ:ም:5ቍ:3እና:9)።

ቅዱሳን በዚህ ዓለም በሥጋቸው እንዳሉ ይህን ያኽል ምሥጢር የማወቅ ችሎታ ካላቸው ከሥጋቸው ተላቅቀው በሰማይ በሚሆኑበት ጊዜማ ምንኛ የበለጠ ዕውቀት ሊኖራቸው እንደሚችል መገመት ይቻላል።

ቅዱሳን ከዚህ ዓለም ከተለዩ በኋላ የዚህን ዓለም ሁኔታና የእኛን ፍላጎት እንዴት ሊያውቁ ይችላሉ? የቅዱሳን ነፍስ ከሥጋቸው መለየት የበለጠ የሚያውቁ እንጂ የማያውቁ አያደርጋቸውም። እነርሱም ሕያዋን እንጂ ሙታን አይሆኑም። ስለዚህ ነው ጌታ ከሰዱቃውያን ጋር ይነጋገር በነበረ ጊዜ እግዚአብሔር የአብርሃም፥ የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ ነው ሲባል እነዚህ የቀድሞ አባቶች ሕያዋን ስለሆኑ ነው እንጂ እርሱ የሙታን አምላክ ስለሆነ አይደለም ያለው (ማቴ:ም:22ቍ:31 – 32)።

ስለዚህ መላእክትም ሆኑ ቅዱሳን በዚህ ዓለም ስለላለው ሁናቴ የሚያውቁ መሆናቸውን ከሚገልጹት የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች መካከል የሚከተ ሉት ይገኙባቸዋል።

«ጸጋውና ምሕረቱ ከቅዱሳኑ ጋር እንደሆነና የተመረጡትንም እንደሚ ያከብራቸው ይህን ሰዎቹ አይተው አልተረዱትም፤ በአእምሮ አቸውም አላኖሩትም። ስለዚህ የሞተው ጻድቅ ባልሞቱት ኃጢአተኞች ላይ ይፈርዳል» (ጥበብ :ም:4ቍ:15–16)።

«እግዚአብሔርም እንዲህ አለኝ:- ‹ሙሴና ሳሙኤል እንኳ በፊቴ ቆመው ቢማልዱ ለዚህ ሕዝብ ምሕረት አላደረግም፤ ስለዚህ ከፊቴ ወዲያ እንዲሄዱ አድርግ» (ኤር:ም:15ቍ:1)።

ይህ አባባል የሚያመለክተው ከኤርምያስ ዘመን ከብዙ ጊዜ በፊት የሞቱት ሙሴና ሳሙኤል ስለ እስራኤል ሕዝብ እግዚአብሔርን ይማጸኑ የነበሩ



www.ethiopianorthodox.org

መሆናቸውን ነው። ስለዚህ ሙሴና ሳሙኤል ከሞቱ በኋላ በዚህ ዓለም የነበረው ሁናቴ ዐውቀው ለአማላጅነት በእግዚአብሔር ፊት የቆሙ መሆናቸውንና ከዚህ ዓለም የተለያዩትም ቅዱሳን የእኛን ችግር ዐውቀው የሚያማልዱን ለመሆ ናቸው በሙሴና በሳሙኤል ሁናቴ ልንረዳ እንችላለን።

በሁለተኛው ዜና መዋዕል ምዕራፍ 21 ላይ የይሁዳ ንጉሥ ኢዮራም ብዙ ኃጢአት በመሥራቱ ከዓመታት በፊት በእሳት ሠረገላ ወደሰማይ ተወስዶ የነበረው ነቢዩ ኤልያስ የተግሣጽና የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ላከለት (2ኛ:ዜ ም:21ቍ:12–14)።

ኤልያስ በእሳት ሠረገላ ወደ ሰማይ ከመወሰዱ በፊት በነቢይነት የእርሱ ተተኪ እንዲሆን የተወሰነለትን ኤልሳዕን እንዲቀባው በእግዚአብሔር ታዘዘ። የታዘዘውም የእርሱ ተተኪ እንዲሆን እንጂ ከእርሱ ጋር ወይንም እርሱ ማለት ኤልያስ እያለ እንዲሠራ አይደለም (1ኛ ነገ. 19:16)። ኤልያስ ከመወሰዱ በፊት ኤልሳዕ አንዳችም የትንቢት ሥራ እንደሠራ አልተገለጠም።

የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሣፍጥ በነገሠ በአሥራ ስምንተኛው ዓመት የእስራ ኤልን ንጉሥ ኢዮራምን ለመርዳት በወጣ ጊዜ እንዲህ ሲል ጠየቀ:- «በእርሱ አማካይነት እግዚአብሔርን መጠየቅ እንድንችል በዚህ አንድ ነቢይ የለምን?»

ከንጉሥ ኢዮራም ሠራዊት አዛዦዎች አንዱ:- «ቀድሞ የኤልያስ ረዳት የነበረው የሣፋጥ ልጅ ኤልሳዕ አለ» ሲል መልስ ሰጠ (2ኛ ነገ 3: 11)። እንዚህ ከላይ የቀረቡት ጥቅሶች የሚያመለክቱት ኤልያስ ወደ ሰማይ የተወሰደው ከኢዮሣፍጥ ንግሥ ከዐሥራ ስምንተኛው ዘመን በፊት መሆኑን ነው (2ኛ ነ 3 : 11)።

ኢዮሣፍጥ የነገሠበት ዘመን ኻያ አምስት ዓመት ነው (1ኛ ነገ. 22፥ 41–41)። ኤልያስም ደብዳቤ የጻፈው ኢዮሣፍጥ ከሞተ በኋላ የእርሱን ዙፋን ለወረሰው ለልጁ ለኢዮራም ነው (1ኛ ዜ. መ. 21:12–15)።

ከላይ በቀረቡት የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች መሠረት ነቢዩ ኤልያስ ለንጉሥ ኢዮራም ደብዳቤ የጻፈለት ወደ ሰማይ ከተወሰደ ቢያንስ ከሰባት ዓመት በኋላ ነው።

በትንቢት ዘካርያስ ም:1ቍ:12እና 16 ላይ የእግዚብሔር መልአክ ስለ ኢየሩሳሌም ከተማ ይቅርታ ለምኖ እግዚአብሔር ልመናውን የተቀበለው መሆኑ ተገልጦአል።

«መልአኮቻቸው ዘወትር በሰማይ ያለውን የአባቴን ፊት ስለሚያዩ ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱንም እንዳትንቁ ተጠንቀቁ» (ማቴ:ም:18ቍ:10)።



«ንስሓ በሚገባ አንድ ኃጢአተኛ ምክንያት በእግዚአብሔር መላእክት ዘንድ ደስታ ይሆናል እላችኋለሁ» (ሉ.ቃ:ም:15ቍ:10)።

በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 16 ላይ አብርሃምና ባለጸጋው ሲነጋገሩ ባለጸጋው በዚህ ዓለም በነበረበት ጊዜ በተድላና በደስታ እንደኖረና አልዓዛር ግን በችግር እንደኖረ አብርሃም ገልጦአል። ታዲያ አብርሃም ስለእነአልዓዛር የዚህ ዓለም ኑሮ እንዴት ሊያውቅ ቻለ። እንዲሁም ባለጸጋው በዓለም ላይ ስላሉት ወንድሞቹ አስቦ አብርሃምን በለመነው ጊዜ ሙሴና ነቢያት አሉላቸው ብሎታል። ታዲያ፥ ሙሴና ነቢያት የተነሡት አብርሃም ከሞተ ከብዙ ዘመን በኋላ ሲሆን የእነርሱ መጻሕፈት መኖራቸውን እንዴት ሊያውቅ ቻለ?

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከሞት በኋላ ስለሚኖረን ዕውቀት ሲያብራራ እንዲህ ብሏአ:-

«አሁን በመስታወት እንደምናየው ዐይነት በድንግዝግዝ እናያለን፤ በዚያን ጊዜ ግን በግልጥ እናያለን፤ አሁን የማውቀው በከፊል ነው፤ በዚያን ጊዜ ግን እኔ የምታውቀውን ያኽል ዕውቀት ይኖረኛል» (1ኛ:ቆሮ:ም:13ቍ:12)።

<u>ሌሎች የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች:-</u>

1. እግዚአብሔር የሰዶምን ከተማና ሕዝብዋን በኃጢአታቸው ምክንያት ሊደመስሳቸው መወሰኑን ለአብርሃም ነገረው። በዚህ ጊዜ አብርሃም በከተማው ውስጥ 50 ደጋግ ሰዎች ቢኖሩ ከተማይቱን በሙሉ በመደምሰስ ደጎችን ከክፉዎች ጋር አብረህ ታጠፋለህን? በማለት ምልጃውን ጀመረ። እግዚ አብሔርም ኀምሳ ደጋግ ሰዎች ቢገኙ ለኀምሳዎቹ ስል ከተማይቱን አላጠ ፋትም አለው። አብርሃምም ከእግዚአብሔር ጋር ንግግሩን በመቀጠል ደጋጎቹ ሰዎች አርባ አምስት፥ አርባ ፥ ሠላሳ፥ ዐሥር ቢሆኑስ እያለ በከተቱ ውስጥ ዐሥር እንኳ ደጋጎች ሰዎች ቢኖሩ ከተማይቱን እንደማያጠፋ እግዚአብሔር ቃል ገባለት። ይሁን እንጂ ዐሥር እንኳ ደጋጎች ሰዎች በከተማይቱ ውስጥ ስላልተገኙ ከተማይቱ ተደመሰሰች። ይህም ታሪክ የሚያመለክተው እግዚአ ብሔር ምን ያህል የወዳጆቹን ምልጃ የሚቀበል መሆኑን ነው (ዘፍ: ም:18 ቍ:26–32)። «እግዚአብሔር አብርሃምን አሰበ፤ ሎጥንም ከጥፋት አዳነው» (ዘፍ:19፥29) ።

2. የእስራኤል ሕዝብ ጣዖት ሠርቶ በማምለክ ከአምለኩ ከእግዚአብሔር ሕግ ባፈነገጠ ጊዜ እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ከእርሱ ጋር ለነበረው ለሙሴ ምን እንዳለውና ሙሴም በአማልጅነቱ እንደምን አድርጎ ለእስራኤል ሕዝብ ምሕረትን እንዳስገኘ የሚገልጸውን ታሪክ እንመልከት:-

«እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው:-ከግብጽ ምድር መርተህ ያወ ጣኸው ሕዝብህ ራሱን ስላረከሰ ፈጥነህ ውረድ፤ እነርሱ እንዲከተሉት ካዘዝኋቸው መንገድ ወዲያውኑ ወጥተዋል፤ ከቀለጠ ወርቅ ጥጃ ሠርተውም ሰግደውለታል፤ መሥዋዕት አቅርበውለት ከግብጽ ምድር ያወጣን አምላካችን



www.ethiopianorthodox.org

ይህ ነው ብለዋል። እነርሱ ምን ያኽል አንገተ ደንዳኖች እንደሆኑ አኔ ዐውቃለሁ፤ አሁንም እነሆ በእነርሱ ላይ እጅግ ተቈጥቼ ላጠፋቸው ስለተ ዘጋጀሁ ቍጣዬን ለመግታት አታስብ፤ አንተንና ዘርህን ግን ታላቅ ሕዝብ አደርጋለሁ። ሙሴ ግን እግዚአብሔር አምላኩን በመማለድ እንዲህ አለ:- እግዚአብሔር ሆይ፥ በብርቱ ክንድህና በታላቅ ኀይልህ ከግብጽ ምድር ያወጣኸውን ሕዝብህን እስከዚህ የምትቈጣው ስለምንድነው? ግብጻውያን ከግብጽ ምድር መቶቶ ያወጣቸው ለክፉ ነገር ማለት በተራራ ላይ ሊገድ ላቸውና ፈጽሞ ሊያጠፋቸው ነው እያሉ መዘባበቻ እንዲያደርጉን ለምን ትፈቅዳለህ? አሁንም ከቍጣህ ወደ ምሕረት ተመለስ፤ ይህንንም ሁሉ ጥፋት በሕዝብህ ላይ አታምጣ። አገልጋዮችህን አብርሃምን፥ ይስሐቅንና ያዕቆብን አስብ፤ ዘራቸውን እንደሰማይ ከዋክብት ልታበዛውና የተስፋይቱንም ምድር ለዘለዓለም ርስት አድርገህ ልትሰጣቸው በመሐላ የገባህላቸውንም ቃል ኪዳን አስብ። ስለዚህ እግዚአብሔር ከቍጣ ወደ ምሕረት ተመልሶ ሊያመጣባቸው የነበረውን ቅሰፍት እንዲገታ አደረገ» (ዘደ:ም:32ቍ:7–14)።

«ምንም እንኳ የእስራኤል አምላክ እግዚብሔር ሁለት ጊዜ ተገልጦለት ባዕዳን አማልክትን እንዳያመልክ ያዘዘው ቢሆን ሰሎሞን ለእግዚአብሔር አልታዘዘም፤ ይልቁንም ከእግዚአብሔር እየራቀ ሄደ፤ ስለዚህም እግዚአ ብሔር በሰሎሞን ላይ ተቈጣ፤ እንዲህም አለው:- ‹ከእኔ ጋር የገባኸውን ቃል ኪዳን ሆን ብለህ ስላፈረስክና ትእዛዜንም ስላልፈጸምክ መንግሥትህን ከአንተ ወስጄ ከአገልጋዮችህ ለአንዱ ልሰጠው ወስኜአለሁ፤ ይሁን እንጂ ለአባትህ ለዳዊት ስል ይህን የማደርገው ባለህበተ ዘመን ሳይሆን በልጅህ መንግሥት ጊዜ ይሆናል፤ ከልጅህም ቢሆን መንግሥቱን በሙሉ አልወስድበትም። ለአገልጋዬ ለዳዊትና ለራሴ ርስት እንድትሆን ለመረጥኋት ለኢየሩሳሌም ከተማ ስል አንድ ነገድ እተውለታለሁ» (1ኛ:ነገ:ም:11ቍ:9–13)።

ይህ የእግዚአብሔር መግለጫ የሚያመለክተው ሰሎሞን እንኳ ቢበድል የአግዚአብሔር ቅን ታዛዥ ስለነበረው ስለአባቱ ስለዳዊት ሲል ቅጣቱን የሚያቃልለት መሆኑን ነው።

4. በሁለተኛው መጽሐት ነገሥት :ም:13ቍ:21 ላይ እንደተገለጠው አንድ ትኩስ ሬሳ በነቢዩ በኤልሳዕ መቃብር ላይ ሲጥሉት ከሞት ተነሥቶአል። ይህ ነቢይ የተቀበረ አጥንቱ እንኳ ሙት የሚያስሣ ከሆነ ነፍሱማ ምንኛ ታላቅ ተአምር ታደርግ።

5. «እግዚአብሔር በጣም አስደናቂ የሆኑ ተአምራትን በጳውሎስ እጅ ያደርግ ነበር። በዚህም ምክያት የጳውሎስን አካል የነካውን ልብስና መሐረብ እየወሰዱ በሽተኞችን ሲያስነኩአቸው ከበሽታቸው ይፈወሱ ነበር፤ ርኩሳን መናፍስትም ይወጡላቸው ነበር» (የሐ:ሥ:ም19ቍ:11–12)።

6. ነቢዩ ሳሙኤል ከሞተ በኋላ ነው በሳአል ላይ የሚደርሰውን ችግር ዘርዝሮ ያስረዳው (1ኛ:ሳሙ: ም:28ቍ:15–19)።



ሐዋርያው ጳውሎስ በሥጋው ሆኖ ይህን ያኽል ተአምራት ያደርግ ከነበረ ነፍሱ የቱን ያኽል የከበረች እንደሆነች እናስተውል።

ነቢዩ ሳሙኤል ከሞተ በኋላ የሳአልን የወደፊት ዕድል ፈንታ መናገሩ የቅዱሳንን ነፍሳት ክብርና ዐዋቂነት ያመለክታል።

<u>ማጠቃለያ</u>:- የቅዱሳን አማላጅነት ማለት አንድ ኃጢአተኛ የኃጢአቱን ከባድነት በመገንዘብ በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር ፊት መቅረብ እግዚአብሔርን እንደመዳፈር አድርጎ ስለሚቈጥረውና የቅዱሳን ጸሎት ደግሞ ከእርሱ ከራሱ ጸሎት ይበልጥ ተሰሚነት ስላለው ቅዳሳን እንዲያማልዱት መለመንና ቅዱሳኑ ደግሞ በበኩላቸው ስለዚያ ሰው የሚያቀርቡት ምልጃ ማለት ነው።

አንዳንድ ሰዎች ክርስቶስ አማላጃችን ስለሆነ ሌላ አማላጅ አያስፈልገንም ይላሉ። ክርስቶስ አማላጃችን ወይም አስታራቂአችን ነው የተባለው ምሥጢረ ሥጋዌን በሚመለከት ነው እንጂ ከቅዱሳን አማላጅነት ጋር ግንኙት ያለው ሆኖ አይደለም። የሰው ዘር ሁሉ በአዳምና በሔዋን ላይ የተላለፈውን የእርግማንና የሞት ፍርድ ወርሶ ስለነበረ ማንኛውም ፍጡር ሊረዳው ባልቻለ ጊዜ ዘለዓለማዊው የእግዚአብሔር ልጅ የሰውን ሥጋ ለብሶ ያንን የሞት ዕዳ በለበሰው ሥጋ በመሞት ከፈለልን። በዚህም ቤዛነቱ አምላክንና የሰውን ዘር አስታረቀ። የክርስቶስ አማላጅነት የተባለውም ይህ ነው እንጂ በተራ አማላ ጅነት ደረጃ ልናስበው አይገባም። እርሱ አምላክ ነው፤ እርሱ ተለማኝ ነው። ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመለኮታዊ አንድነቱ ምልጃ የሚቀርብለት መሆኑን አንርሳ።

ቅዱሳን ግን እግዚአብሔር ያከበራቸው ፍጥረቶች ናቸው። እነርሱ እንዲያማልዱን የምንተጋበት ዋናው ምክንያት የእነርሱ ጸሎት ከእኛ ጸሎት የበለጠ ተቀባይነት ያለው በመሆኑ ነው። ይህንንም አባባል ጌታ ራሱ አረጋ ግጦታል።

ሦስቱ የኢዮብ ወዳጆች እግዚአብሔርን ቅር ባሰኙ ጊዜ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው ትእዛዝ እኔ የእርሱን ጸሎት ስለምቀበል ወደባሪያዬ ወደ ኢዮብ ሂዱና ይጸልይላችሁ ተብሎ ነው። እንዲሁም እግዚአብሔር ለአቢሜሌክ የነገረው አብርሃም ነቢይ ስለሆነ እንዳትሞት ይጸልይልሃል ብሎ ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የቅዱሳንን ክብርና ተቀባይነት ለደቀ መዛሙርቱ ሲያረጋግጥላቸው:- «እናንተን የሚሰማ እኔን ይሰማል፤ እናንተን የማይቀበል እኔን አይቀበልም» ብሎአቸዋል (ሉቃ:10:16)።

በሕይወት ያሉም ሆኑ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ ቅዱሳን አማላ ጅነታቸውን ስንጠይቅ የሚያውቁት በተፈጥሮ ዕውቀታቸው ሳይሆን በእግዚ አብሔር ፈቃድና በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ ነው።

ለምሳሌ ነቢዩ ኤልሳዕ የአገልጋዩን የግያዝን ምሥጢራዊ ድርጊት ማወቁ፥ ሐዋርያው ጴጥሮስ ደግሞ የሐናንያንና የሰጺራን ምሥጢራዊ ስምምነት ማወቁ



www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር ምን ያኽል ለቅዱሳኑ ዕውቀትን የሰጣቸው መሆኑን ያመለ ክታል።

እግዚአብሔር የቅዱሳንን ምልጃ ምን ያኽል የሚቀበለ መሆኑን ከሚያ መለክቱት ምሳሌችወች መካከል ደግሞ የአብርሃምንና የሙሴን አማላ ጅነት ይመለከቷል።

አብርሃም ከእግ? ዝአብሔር ጋር በመደራደር ከ50 ሰዎች እስከ 10 ሰዎች ድረስ እንኳ በሰዶም ከተማ ውስጥ ቢገኙ ከተማይቱን እንደማያጠፋ እግዚአ ብሔር ቃል ገብቶለታል።

እስራኤላውያን በበደሉ ጊዜ እግዚአብሔር ሊያጠፋቸው ከወሰነ በኋላ በሙሴ ጸሎት ይቅርታ አድርጎላቸዋል።

ከሞቱም በኋላ ሙሴና ሳሙኤል ለእስራኤል ሕዝብ ለማማለድ በእግዘ አብሔር ፊት መቆማቸው ተገልጾአል።

በእነዚህና በሌሎችም የተለያዩ ማስረጃዎች መሠረት የቅዱሳን አማላጅነት በቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች የተደገፈና ቤተ ክርስቲያንም የምታስተ ምረው ትምህርት ነው።

## ጥያቄዎች

1. በብሉይ ኪዳን አዳኝነት ሲባል ምን ማለት ነው?

2. በብሉይ ኪዳን ከሚቀርቡት አብዛኞዎቹ ጸሎቶች ስለምን ጉዳይ ናቸው?

3. በሐዲስ ኪዳን ውሰጥ የእግዚአብሔር አዳኝነት ሲባል ፈጥኖ የሚታ ወሰን ምንድነው?

4. በቤተ ክርስቲያን ትምህርት መሠረት ሰዎች የሚድኑት እንዴት ነው?

5. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የድኅነትን ማረጋገጫ መንገድ የተናገረው እንዴት ብሎ ነው?

6. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለኒቆዲሞስ ስለድኅነት ምን ብሎ ገለጠለት?

7. መንፈሳዊ ሕይወትን ለመኖር ሚያስችሉን ምን ምን ናቸው?



8. እነዚህስ ስጦታዎች ኃጢአት እንዳንሠራ የማይከለክሉን፥ ከስሕተትና ከነቀፋ ነጻ የማያወጡን እንዴት ነው?

9. በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠርንበት ጸጋ የትኛው ነው?

10. ኃጢአትን ለመሥራት የማንችለው የት ስንሆን ነው?

11. ኃጢአትን ልንሠራ አንችልም የሚሉ ወገኖች የሚያቀርቡአቸው 5 ሐሳቦች ምን ምን ናቸው?

12. ሰው የሚድነው በእግዚአብሔር ጸጋ እንጂ በራሱ ሥራ አይደለም ለሚለው ሐሳብ መልስ ስጥ።

13. እግዚአብሔር በሰው ልብ የሚዘራው ዘር የማይጠፋ ነው ለሚለው ሐሳብ መልስ ስጥ።

14. ክርስቶስ ለተከታዮቹ የሚሰጠው ሕይወት የዘለዓለም ሕይወት ነውና ማንም ከእጁ ሊነጥቃቸው አይችልም ለሚለው ሐሳብ መልስ ስጥ።

15. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሰውነቱ ውስጥ ትግል የሚካሄድ መሆኑን የገለጠው ምን ብሎ ነው?

16. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ምን ብሎ ትሕትናን አስተማረ?

17. ስለራሱስ በትሕትና የተናገረው ምን ብሎ ነው?

18. ልጅነትን ከተቀበሉ በኋላ ከድኅነት መንገድ ስለወጡ ሰዎች ምን ተባለ?

19. በ1ኛ ዮሐንስ ም:3ቍ:9 እና:ም5ቍ:18 ላይ ለተጠቀሱት ጥቅሶች ምን ትርጉም ተሰጠ?

20. ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ምን ብሎ ለእነዚህ ጥቅሶች ተቃራኒ ሐሳብ አቀረበ?

21. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ ምዕራፍ 6ቍ: 4፥11እና 14 ላቀረባቸው ጥቅሶች ምን ትርጓሜ ተሰጣቸው?

22. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በትእዛዝ ወይም በምክር አነጋገር በማቅረብ ፈንታ ለምን እንደ ሆነና እንደሚሆን ነገር አድርጎ አቀረበው?

23. ለዚህስ ማስረጃው ምንድነው?

24. የአማላጅነት ትርጉም ምንድነው?

www.ethiopianorthodox.org



www.ethiopianorthodox.org

25. አንድ ሰው አማላጅ በመላክ ፊንታ ለምን ራሱ ይቅርታ አይጠይቅም?

26. አማላጅ የሚሆን ሰው ምን ዐይነት ሰው መሆን አለበት?

27. የቅዱሳን አማላጅነት ማለት ምን ማለት ነው?

28. የጌታችንና የቅዱሳን አማላጅነት በምን ይለያል?

29. እግዚአብሔር ያዘዛቸውን ሁለት የአማላጅነት ምሳሌዎች አስረዳ።

30. ነቢዩ ኤልሳዕ ምን ምሥጢር ዐወቀ?

31. ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ምን ምሥጢር ዐወቀ?

32. ቅዱሳን ከሞቱ በኋላ የሚያማልዱ ለመሆናቸው ሁለት የማስረጃ ጥቅሶችን አቅርብ።

33. በዚህ ዓለም ያልነበረና ለንጉሥ ኢዮራም የማስጠንቀቂያና ተግሣጽ ደብዳቤ የጻፈለት ነቢይ ማነው?

34. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከሞት በኋላ ስለሚኖረው ዕውቀት ምን አለ?

35. አብርሃም ለማን አማላጅ ሆኖ ምን ስምምነትን አገኘ?

36. ሙሴ ለማን አማላጅ ሆኖ ምን አገኘ?

37. ሰሎሞን ስለአባቱ ስለ ዳዊት ሲባል ምን ተደረገለት?

## ምዕራፍ 2

## መጽሐፍ ቅዱስ

### ብሉይ ኪዳን

የሙሴ መወለድ:- እግዚአብሔር ለቀድሞዎቹ የእስራኤል አባቶች ለአብርሃም፥ ለይስሐቅና ለያዕቆብ በገባው የተስፋ ቃል መሠረት የእስራኤል ሕዝብ በግብጽ በኖረበት በሁለት መቶ ዓመቶች ውስጥ ብዙ ሕዝብ ሆነ። በዚያን ጊዜ በግብጽ አዲስ ንጉሥ ተነሥቶ ለግብጽ ሕዝብ እንዲህ ብሎ ተናገረ:- «እነሆ፥ የእስራኤል ሕዝብ ከእኛ በርትቶአል። እነርሱ ከጠላቶቻችን ጋር እንዳይ ተባበሩብንና ከአገር እንዳይወጡ ኑ እንጨቍናቸው።» ግብጻውያንም



ወንዶች ልጆች ሁሉ ወደ ወንዝ እንዲጣሉ ትእዛዝ አስተላለፈ። በዚህም ተስፋ ያደረገው አንድም ዕብራይውያንን ለማጥፋት፥ ያም ባይሆን ዕድገታቸውን ለመግታት ነበር።

በዚህ ጊዜ አንዲት ዕብራዊት ሴት አንድ ወንድ ልጅ ወለደች። በጣም መልከ መልካም መሆኑንም አይታ ለሦስት ወር ደበቀችው። ከዚያ ይበልጥ ልታቈየው አለመቻልዋን በተረዳች ጊዜ አንድ ቅርጫት ሠርታ በዚያ ውስጥ በማስተኛት ወስዳ በወንዝ ዳር አስቀመጠችው። የሕፃኑ እኅት ራቅ ብላ በመቆም የሚደርስበትን ነገር ለማየት ትጠባበቀው ነበር። እነሆ፥ በዚያን ጊዜ የፈርዖን ሴት ልጅ ለመታጠብ ወደ አባይ ወንዝ ወረደች። ልዕልቲቱም በቄጤማዎች መካከል ቅርጫት ስላየች አገልጋዮችዋን ልካ አስመጣችው። ቅርጫቱንም ሲከፍቱት አንድ መልከ መልካም ሕፃን ሲያለቅስ አገኙት። እርስዋም ራርታለት ይህ ከዕብራውያን ሴቶች አንድዋ የወለደችው መሆን አለበት አለች። የሕፃኑም እኅት ቀርባ ይህን ሕፃን የምታጠባልሽ አንዲት ዕብራዊት ሴት ልጥራልሽን አለቻት። ልዕልቲቱም እሺ አለቻት። ልጅቱም ሄደ እናትዋን ጠራች። ልዕልቲቱ ለሕፃኑ እናት ይህን ልጅ ወስደሽ አጥቢልኝና ደመወዝሽን እከፍልሻለሁ አለቻት። ባደገም ጊዜ ወደ ንጉሡ ቤት ተወስዶ ልዕልቲቱ እንደ እናት ሆነችው (ዘጸ:ም:2ቍ:1–10)።



www.ethiopianorthodox.org



የሙሴ ልደትና ዕድገት (ዘጸ: ም: 2 ቁ:1–10)

<u>የሙሴ ሽሽት</u>:- ሙሴ በፈርዖን ቤተ መንግሥት የግብጾችን ጥበብ ሁሉ እየተማረ ዐደገ። ይሁን እንጂ የወንድሞቹን የዕብራውያንን ችግር ባየ ጊዜ እነርሱን ለመርዳት ወሰነ። እርሱም በክፉው ንጉሥ ቤተ መንግሥት ከመኖር ይልቅ ከወንድሞቹ ጋር መቸገርን መረጠ። የቤተ መንግሥቱን የተንደላቀቀ ኑሮ ትቶ ለእስራኤላውያን ወዳጅ መሆኑን በግልጥ አሳወቀ። ንጉሡ ይህን በሰማ ጊዜ ሊገድለው ፈለገ፤ እርሱ ግን ወደ ምድያም አገር ሸሽቶ ሄደ። ወደዚያም ሄዶ የዮቶር ሰባት ሴቶች ልጆች ለበጎቻቸው ውሃ ለመቅዳት በመጡበት ጉድጓድ አጠገብ ዐርፎ ነበር። ሴቶቹ በጎቻቸውን ይዘው ሲመጡ ሌሎች እረኞች መጥተው አስቸገሩአቸው። በዚህ ጊዜ ሙሴ ተከላከለላቸውና በጎቻቸውን አጠጣላቸው። ከዚያም ወደቤታቸው ተመልሰው ሲሄዱ አባታቸው እንዴት ዛሬስ በቶሎ መጣችሁ አላቸው። እነርሱም አንድ ግብጻዊ ከሚያስቸግሩን እረኞች ተከላክሎልን በጎቻችንንም ውሃ አጠጣልን አሉት። ዮትሮም ታዲያ፥ ያ ሰው የት አለ? ጥሩትና እንጀራ ይብላ አላቸው። ሙሴም ወደ ቤት ገባና ከዮትሮ ጋር ለመኖር ተስማማ። አርባ ዓመትም በዚያ ኖረ። ዮቶርም ሲፓራ የተባለች ልጁን ዳረለት (ዘጸ: ም:2ቁ:11–25)።



<u>በቍጥቋጦ መካከል የእሳት ነበልባል</u>:- ሙሴ የሀማቱን የዩትሮን በጎች ያስማራ ነበር። አንድ ቀን በጎቹን ይዞ እስከ ኮሬብ ተራራ ድረስ ሄደ። እዚያም ከቍጥቋጦ መካከል በነበረ የእሳት ነበልባል ውስጥ ጌታ ተገለጠለት። ሙሴ እሳት እየነደደ ቍጥቋጦው የማይቃጠል መሆኑን ያያል። እርሱም ይህ ቍጥቋጦ ለምን እንደማይቃጠል ሄጄ አያለሁ አለ። ሙሴ ወደ ቍጥቋጦው እየሄደ ሳለ «ሙሴ፥ ሙሴ»፥ የሚለውን የጌታን ድምፅ ከሚነድደው ቍጥቋጦ ሰማ። እርሱም አቤት አለ። እግዚአብሔርም ወደ እዚህ አትቅረብ አለው። የቆምህበት ምድር የተቀደሰ ስለሆነ ጫማህን አውልቅ፤ እኔ የአባቶችህ፥ የአብርሃም፥ የይስሐቅና የያቆብ አምላክ ነኝ አለው።

ሙሴም የእግዚአብሔርን ፊት ላለማየት በፍርሃት ፊቱን ሸፈነ። «በግብጽ ምድር የሕዝቤን ጭንቀት ስላየሁ ከግብጻውያን እጅ አውጥቼ ማርና ወተት ወደምታፈስሰው ምድር ላስገባቸው ወስኜአለሁና ወደ ግብጽ ንጉሥ ሄደህ ሕዝቡን ነጻ እንዲለቀቅ ንገረው» ብሎ አዘዘው።

ሙሴ ግን እኔ ማን ነኝ ወደ ግብጽ ንጉሥ ሄጄ እስራኤልን ነጻ የማወጣ ሲል መለሰለት። እግዚአብሔርም እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ አለው። ሙሴ እስራኤላውያን እንደማያምኑትና ማን እንደላከው እንደሚጠይቁት ገለጸ። እግዚአብሔርም «እኔነኝ» ልኮኛል በላቸው አለው። ሙሴም አያምኑኝም እንዲያውም ጌታ አልላከህም፤ እርሱም አልተገለጠልህም ብለው ቃሌን አይሰሙኝም ሲል መለሰ። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር በእጅህ የያዝከው ምንድነው? ብሎ ጠየቀው። ሙሴም በትር ነው ብሎ መለሰ። ጌታም ወደ መሬት እንዲጥለው ነገረው። ሙሴ በትሩን በጣለው ጊዜ ወደ እባብነት ስለተለወጠ ፈርቶ ሸሸ። ጌታ ግን ጠርቶት ጅራቱን ያዘው አለው። ሙሴም ጅራቱን በያዘው ጊዜ እንደገና ወደ በትርነቱ ተመለሰ። እግዚአብሔርም ይህንና ሌሎችንም ምልክቶችን በእስራኤል ልጆች ፊት ብታደርግ ያምኑሃል ሲል ለሙሴ ነገረው። ሙሴ ግን አሁንም የንግግር ችሎታ የሌለውና አፉም ኰልታፋ መሆኑን በመግለጥ ተቃውሞውን ቀጠለ። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር የሰውን አፍ የፈጠረ ማን ነው? ዱዳና ደንቆሮንስ የፈጠረ ማነው? ዐይን ያለውንና ዕውርንስ የፈጠረ ማን ነው? እኔ አይደለሁምን? ስለዚህ ሂድና ምን እንደምትናገር እኔ አስተምርሃለሁ አለው። ሙሴም ጌታ ሆይ እባክህ ሌላ ሰው ላክ ብሎ ለመነ። ጌታ በሙሴ ላይ ተቈጥቶ ወንድምህ አሮን ንግግር ዐዋቂ ነው፤ ቃሌን ለእርሱ ንገረውና እርሱ ስለ አንተ ሆኖ ይናገራል አለው። ስለዚህ ሙሴ ወደ ግብጽ ተመለሰ፤ አሮንም ስለ ሙሴ መምጣት እግዚአብሔር ገልጦለት ሙሴን ሊቀበል ለው ወጣ።



www.ethiopianorthodox.org

ሙሴ የእግዚአብሔርን ቃል ሁሉ ለአሮን ነገረው። ሁለቱም ሄደው የእስራኤልን ልጆች በማሰባሰብ የደረሰባቸውን ችግር እግዚአብሔር እንደተመለከተላቸው አሮን ነገራቸው። ሙሴም የብትሩንና ሌሎችን ምልክቶች አሳያቸው። ሰዎቹም አምነው ለእግዚአብሔር ሰገዱ።

<u>ጦቢት</u> :- ከንፍታሌም ነገድ የሆነ በአሦር ንጉሥ በሰልምናሶር ዘመን የተማረከ አንድ ጦቢት የተባለ አይሁዳዊ ነበረ። እርሱም ተማራኪ ወገኖቹን የሚያጽናና እና የሚረዳ ደግ ሰው ነበር። ንጉሡ ሰልምናሶር ከሞተ በኋላ ልጁ ሰናክሬም ነግሦ ተማራኪ የአይሁድ ወገኖችን እያስገደለ ሬሳቸውን በአደባባይ ያስጥል ጀመር። ጦቢት ግን የሚያገኛቸውን የተጣሉ ሬሳዎች ወስዶ በቤቱ እየደበቀ ሰው ሳያየው በሌሊት ይቀብራቸው የነበረ መሆኑን ንጉሡ በሰማ ጊዜ በጦቢት ላይ የሞት ፍርድ ፈረደበት። ጦቢት ግን ስለተሸሸገ ሊያገኘው አልቻለም። ይህ ከሆነ ከአርባ ቀን በኋላ የራሱ ልጆች ሰናክሬምን ገደሉት። በዚህ ጊዜ ጦቢት ከተደበቀበት ወጣ። በአይሁድ ስደተኞች ላይ ይደረግ የነበረው በደል ግን አላቋረጠም። ጦቢትም ለወገኖቹ ያደርግ የነበረውን እርዳታና ተገድለው የሚጣሉትን አስከሬኖች መቅበሩን ቀጠለ።

ተስፋ የቈረጡትን ሲያበረታታ፥ የተቸገሩትን ሲረዳ፥ ተገድለው የተጣሉትን ሲቀብር በመቈቱ አንድ ቀን በጣም ደክሞት መጥቶ በአጥር ግቢው በግድግዳው አጠገብ ተኛ። ከተኛበት ግድግዳ በላይ ወፎች መኖራቸውን ሳያውቅ ዐይኑን ከፍቶ ተኝቶ ነበር። የወፎቹ ትኩስ ኵስ በዐይኑ ላይ ወድቆ አሳወረው። ይህ ከሆነ በኋላ ምንም ለማድረግ ስላልቻለ ሚስቱ ሐና የድካም ሥራ እየሠራች ቤቱን ታስተዳድር ጀመር።

ይህ የመጐሳቈል ሁናቴ በአስተሳሰቡ ላይ ተስፋ የመቍረጥ ዝንባሌ አሳደረበት። ስለዚህም በቅርቡ እንደሚሞት ገምቶ ልጁን ጦብያን በመጥራት እንዲህ አለው:- እኔ በምሞትበት ጊዜ በክብር ቅበረኝ። እናትህን አክብረህ ተንከባከባት። እርስዋም ስትሞት በእኔ አጠገብ ቅበራት። የእግዚአብሔርን ትእዛዞች ሁሉ ፈጽም። የሜዶን ክፍል በምትሆን የራጊስ አገር ሰው በሆነው በግብርያል ልጅ በገባኤል ዘንድ ዐደራ ያስቀመጥሁት ዐሥር የብር መክሊት አለ። ያን ገንዘብ ሄደህ አምጣ ብሎ አዘዘው። ልጁም አባቴ ሆይ፥ ትእዛዝህን ሁሉ አከብራለሁ አለ። ጦብያ ያባቱን ትእዛዝ ለመፈጸም ወደ ራጊስ የሚወስደውን ሰው ለመፈለግ ወዲያው ከቤቱ በወጣ ጊዜ መልአኩ ሩፋኤል በአንድ ወጣት ተመስሎ ተገናኘውና እርሱ እንደሚመራው ቃል ገባለት። ጦቢትና ጦብያም ሊቀ መላእክት ሩፋኤል መሆኑን ሳያውቁ የአገልግሎቱን ዋጋ እንደሚከፍሉት ቃል ገቡለት። እግዚአብሔር መንገዳቸውን እንዲያቃናላቸው ጦቢት ከመረቃቸው በኋላ መልአኩና ጦብያ ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ወደ



ማታ ጊዜ ወደ ጤግሮስ ወንዝ ደረሱ። ጦብያ እግሩን ሊታጠብ ወደ ወንዙ ዳር ሲወርድ አንድ ትልቅ ዓሣ አደጋ ሊጥልበት ቃጣው። መልአኩ ግን ያን ዓሣ ያዘው ብሎ ጦብያን አዘዘው። ጦብያም ዓሣውን ይዞ ወደ ውጭ አወጣው። እንደገናም መልአኩ የዓሣውን ጉበት፥ ሐሞቱንና ልቡን አውጥተህ ለመድኀኒትነት ያዘው ብሎ ጦብያን አዘዘው። ጦብያም እንደታዘዘው አደረገ። ከዚያም ጦብያ እሳት በማንደድ ከዓሣው ጠብሶ ከተመገቡ በኋላ የቀረውን ጨው አድርጎበት ለስንቅ እንዲሆን ያዘው።

ጉዞአቸውን በመቀጠል ወደ አንድ ከተማ በደረሱ ጊዜ ጦብያ ወዴት እንደር ብሎ መሪውን ጠየቀው። መልአኩም እዚህ ሣራ የተባለች ልጅ ያለችው ራጉኤል የተባለ አንድ የአንተ ዘመድ አለ። ሣራም ለአንተ ሚስት እንድትሆንህ እግዚአብሔር የወሰነው ጉዳይ ነው አለው። ጦብያ ግን እርስዋ እኮ ሰባት ባሎች አግብታ ሰባቱም እንደባልና ሚስት ከእርስዋ ጋረ ሳይገናኙ ስለሞቱ ያ ዕድል ፈንታ እኔም ይደርስብኝና ወላጆቼን በሐዘን ወደ መቃብር አወርዳቸዋለሁ ብሎ ስጋቱን ለመልአኩ ገለጠለት። መልአኩ ግን አይዞህ በማለት ያ ችግር በእርሱ ላይ እንደማይደርስ አረጋገጠለት። የሣራን ሰባት የቀድሞ ባሎች የገደለውን አስማንድዮስ የተባለውን ሰይጣን መልአኩ ሩፋኤል ካባረረው በኋላ ጦብያና ሣራ ያለ ችግር ተጋቡ።

ጦብያ ከሣራ ጋራ ተጋብቶ ሁለት ሳምንት ከማሳለፉ በፊት እንዳይሄድ የሣራ አባት አስምሎት ስለነበረ ዐሥሩን የብር መክሊት ከገባኤል ዘንድ እንዲያመጣለት አዛርያ ብሎ የሚጠራውን መልአኩን ሩፋኤልን ላከው። መልአኩም ሄዶ ገንዘቡን ይዞ መጣ። ከሰርጉም ከሁለት ሳምንት በኋላ ወደ ጦብያ ቤተሰብ ተመለሱ። ጦብያ ከዓሣው ሆድ በወጣው ሐሞት በመልአኩ በሩፋኤል ምክር መሠረት የአባቱን የጦቢትን ዐይን ባሸ ጊዜ የጦቢት ዐይን ድኖ ለማየ ቻለ።

ከዚህ በኋላ ከተገኘው ሀብት ሁሉ ግማሹን የጦብያ መሪ ለሆነው ሰው ለመስጠት ጦቢትና ጦብያ በመስማማት ሐሳቡን ቢያቀርቡለት እርሱ ሰው አለመሆኑንና የጦቢትን ቤተሰብ ለመርዳት ከእግዚአብሔር የተላከ ከሰባቱ ሊቃነ መላእክት አንዱ ሩፋኤል መሆኑን ከገለጠላቸውና ከአስደሰታቸው በኋላ ከፊታቸው ተሰወረ።

ከእነዚህም ነገሮች በኋላ ጦቢት 42 ዓመቶች በመኖር በቤተሰቡ የደስታ ኑሮ ተሳትፎ አድርጎአል። ከዚህ ኋለም በሞት የተለየውም የዕድሜ ባለጸጋ ሆኖ በአንድ መቶ ሁለት ዓመቱ ነው።

www.ethiopianorthodox.org

**<u>ነቢዩ ዮናስ</u>**:- እግዚአብሔር ለአረማውያን ምሕረት ለማድረግ ፈቅዶ ነቢዩን ዮናስን ወደ ነነዌ ከተማ ሄዶ ንስሓ እንዲገቡ ያስተምራቸው ዘንድ አዘዘው። የነነዌ ከተማ ሕዝብ ክፋት በጣም ስለበዛና እግዚአብሔርን ስላስቈጣ ስለንስሓ ስበክ አለው።

እግዚአብሔር ይቅር ባይ መሆኑን ዮናስ ስለሚያውቅና እርሱም ሄዶ ለነነዌ ሰዎች ቢሰብክ ንስሓ ይገቡና እግዚአብሔር ይቅርታ ያደርግላቸው ይሆናል ብሎ ሰጋ። የሰጋበትም ምክንያት እነርሱ ይቅርታ ከተደረገላቸው እርሱ እንደ ሐሰተኛ ነቢይ እቈጠራለሁ ብሎ ስለራሱ ክብር በማሰብ ነው። ስለዚህ ዮናስ ከእግዚአብሔር ለመሸሽ ብሎ ወደ ተርሴስ በሚሄድ መርከብ ተሳፈረ። እግዚአብሔር ግን ታላቅ ማዕበል አስነሥቶ መርከቢቱ ልትሰጥም ተቃረበች።

በዚህ ጊዜ መርከበኞቹ የመርከቡን ክብደት ለማቃለል ብለው በመርከቡ ውስጥ የነበረውን ዕቃ ሁሉ እያወጡ ጣሉ። እያንዳንዱም ሰው ለሚያምንበት አምላክ ይጸልይ ጀመረ። ዮናስ ተኝቶ ስለ ነበረ የመርከቡ አዛዥ ወደ እርሱ ሄዶ ስለምን ተኝተሃል? ምናልባት እግዚአብሔር ያድነን እንደሆነ ለአምላክህ ጸልይ አለው። መርከበኞቹ ግን ማዕበሉ እያየለ መሄዱን ባዩ ጊዜ ይህ ችግር የመጣብን በማን ምክንያት መሆኑን ለማወቅ ዕጣ እንጣል አሉ። ዕጣውን በጣሉ ጊዜ ዕጣው በዮናስ ላይ ወጣ። ከዚያ በኋላ ዮናስ ኃጢአቱን ተናዘዞ እኔን ወደ ባሕሩ ከጣላችሁኝ ሰላም ታገኛላችሁ አላቸው። መርከበኞቹ ግን እርሱን ወደ ባሕር ከመጣል ይልቅ ወደ አንድ ቦታ አድርሰው ሊያወርዱት ፈልገው ነበር። ይሁን እንጂ ማዕበሉ በጣም ተጠናክሮ ስለነበረ ወደየትም ቀዝፈው ለመሄድ አልቻሉም። በመጨረሻ ዮናስን ወደ ባሕሩ ሲጥሉት ወዲያው ማዕበሉ ቆመ፤ ባሕሩም ጸጥ አለ። በዚያን ጊዜ እግዚአብሔር አንድ ትልቅ ዓሣ ዮናስን እንዲውጠው አደረገ። ዮናስም በዓሣው ሆድ ውስጥ እንዳለ እግዚአብሔር ያድነው ዘንድ ጸለየ። እግዚአብሔርም ጸሎቱን ሰምቶ ዓሣው ከባሕሩ ውጭ በአንድ ደረቅ ቦታ እንዲተፋው አደረገ።

እግዚአብሔርም ለሁለተኛ ጊዜ ዮናስን ወደ ትልቋ ከተማ ወደ ነነዌ ሄዶ ንስሓን እንዲሰብክ ነገረው። ዮናስም ሳያመነታ ነነዌ ከሦስት ቀን በኋላ ትደመሰሳለች በማለት አስተማረ። የነነዌም ሰዎች በኃጢአታቸው ተጸጽተው ከትልቁ ጀምሮ እስከ ትንሹ ድረስ ማቅ ለብሰው፥ ዐመድ ነስንሰው ጾሙ። እግዚአብሔርም ንስሓቸውን በተመለከተ ጊዜ ይቅርታ አድርጎ ሳያጠፋቸው ቀረ። በዚህ ጊዜ ዮናስ ከከተማው ጥቂት ራቅ ብሎ በመሄድ የሚሆነውን ነገር እየተጠባበቀ ነበር። እግዚአብሔር ለነነዌ ሰዎች ይቅርታ ያደረገ መሆኑን በተረዳ ጊዜ እንደ ሐሰተኛ ነቢይ እቈጠራለሁ በሚል ምክንያት በጣም ተበሳጨ። እግዚአብሔር ግን ነቢዩ የሚበሳጭበት ምክንያት ትክክል



አለመሆኑን ሊያስረዳው ፈልጎ እርሱ ባረፈበት ቦታ ለሚያቃጥለው ፀሐይ መጠለያ ይሆነው ዘንድ ቅል አበቀለለት የቅሉም ተክል ፀሐዩን ስለተከላከለለት ደስ አለው። በሚቀጥለው ቀን ግን እግዚአብሔር የቅሉን ተክል ሥር የሚበላ ትል ስለላከበት ተክሉ ደረቀ። ከዚያም ፀሐይ በወጣ ጊዜ ፀሐዩ ስላቃጠለው በጣም ተበሳጭቶ ሞቱን ተመኘ። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ሠርተህ፥ ለፍተህ ላላበቀልኸው ቅል ይህን ያኽል የምታዝን ከሆነ አንድ መቶ ሃያ ሺህ ሕዝብ ለሚኖሩባት፥ ግራና ቀኙንም ለይተው የማያውቁ ሕፃናትና ብዙ እንስሳት ለሚገኙባት ታላቅ ከተማ ለነነዌ ማዘን አይገባኝምን? አለው።

## <u>ሐዲስ ኪዳን</u>

<u>የሳውል በክርስቶስ ማመን</u>:- በኋላ ጳውሎስ ተብሎ የተጠራው ሳውል ከብንያም ነገድ የሆነ አይሁዳዊ ነበር። ያደገው በጠርሴስ ቢሆንም የተማረው ግን በኢየሩሳሌም ነው። እርሱም ሃይማኖት አጥባቂ ፈሪሳዊ ነበር። ለአይሁድ ሃይማኖት በጣም ቀናኢ ከመሆኑ የተነሣ ቤተ ክርስቲያንን በጣም ያሳድድ ነበር። ክርስቲያኖችንም እያስያዘ ያሳስር ነበር። ለዚህ ዓላማውም ይረዳው ዘንድ በኢየሩሳሌም ወደሚገኘው ሊቀ ካህናት ሄዶ የትብብር ደብዳቤ ይጻፍለት ዘንድ ጠየቀ። ይህንንም ያደረገው በደማስቆ የሚያገኛቸውን ክርስቲያኖች ሁሉ ወደ ኢየሩሳሌም አምጥቶ ለማሳሰር እንዲያበቃው ነው። ያን ደብዳቤ ይዞ ወደ ደማስቆ በመሄድ ላይ እያለ በድንገት አንድ አስገራሚ ነገር ተገለጠለት። በድንገትም ታላቅ ብርሃን በዙሪያው አበራ። እርሱም ደንግጦ በምድር ላይ ወደቀ። በዚህ ጊዜ ሳውል፥ ሳውል፥ ለምን ታሳድደኛል የሚል ድምፅ ሰማ። ሳውልም አንተ ማነህ? ብሎ ጠየቀ። ድምፁም እኔ አንተ የምታሳድደኝ ኢየሱስ ነኝ ብሎ መለሰ። ሳውልም በፍርሃት እየተንቀጠቀጠ ጌታ ሆይ ምን እንዳደርግ ትፈልገኛለህ? አለ። ጌታችንም ተነሥና ወደ ከተማው ግባ እዚያም ምን ማድረግ እንደሚገባህ ይነገርሃል አለው።

ሳውልም ከወደቀበት ተነሥቶ ሀይኑን በገለጠ ጊዜ የማያይለት ሆኖ አገኘው። አብረውት የነበሩትም እየመሩ ወደ ከተማው ወሰዱት። እዚያም ሦስት ቀን ሳይበላና ሳይጠጣ ቈየ። በደማስቆም ሐናንያ የተባለ ደቀ መዝሙር ነበር። ጌታ በራእይ ታይቶ ሐናንያ ሆይ፥ አለው፤ ሐናንያም አቤት ጌታዬ አለ፤ ጌታችንም ተነሥና ቀጥተኛ በሚባለው መንገድ ወደ ይሁዳ ቤት ሂድ፤ እዚያም ሳውል የተባለ የጠርሴስ ሰው ታገኛለህ፤ እርሱ አሁን እየጸለየ ነው አለው። ሐናንያ ግን ጌታ ሆይ፥ እኔ ከብዙዎች እንደሰማሁት ይህ ሰው በኢየሩሳሌም በምእመናንህ ላይ ብዙ ክፉ ነገር የሠራ ነው አለው። ጌታችንም ለሐናንያ መልሶ ይህ ሰው ስሜን ለአረማውያን፥ ለነገሥታትና ለእስራ



www.ethiopianorthodox.org

ሌላውያን የሚያሳውቅ ለእኔ ምርጥ ዕቃ ነው፤ ስለ ስሜም ምን ያኽል ብዙ መከራ እንደሚቀበል እገልጥለታለሁ አለው።



የሳውል ወደ ክርስትና መመለስ የሐ:ሥ:ም:9

ሐናንያም ሳውል ወደ አለበት ቤት ሄዶ እጁን ጫነበትና ወንድሜ ሳውል ሆይ፥ ወደዚህ ስትመጣ የተገለጠልህ ጌታችን ኢየሱስ ማየት እንድትችልና መንፈስ ቅዱስን እንድትሞላ ወደ አንተ ልኮኛል ብሎ እጁን ጫነበት። በድንገት ከዐይኑ ላይ እንደ ቅርፊት ነገር ወደቀ። ዐይኑ አየለት፥ ተነሥቶም ተጠመቀ። ከዚያ በኋላ በየምኵራቡ ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአ ብሔር ልጅነት መስበክ ጀመረ።

<u>ሐዋርያው ጴጥሮሰ በልዳና በኢዮጴ</u>:- ሳውል በክርስቶስ አምኖ ማሳደዱን ካቆመ በኋላ ቤተ ክርስቲያን በይሁዳና በሰማርያ ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ሰላም አገኘች። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም ምእመናንን እያአበረታታና እያጸና በየቦታው መዘዋወር ጀመረ። በዚህም ጊዜ ሁለት ታላላቅ ተአምራትን አደረገ። በልዳ ለስምንት ዓመት በአልጋ ላይ የነበረ ኤንያ የተባለ አንድ ሽባ ሰው ነበረ። ቅዱስ ጴጥሮስ ባየው ጊዜ ኤንያ ሆይ፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶሰ ይፈውስሃል፤ ተነሥና አልጋህን አንጥፍ አለው። እርሱም ወዲያውኑ ድኖ ተነሣ። ይህን ተአምር ባዩ ጊዜ በልዳ ያሉ ሰዎች ሁሉ በጌታችን አመኑ። ሐዋርያው ቅዱስ



ጴጥሮስ ገና በልዳ ሳለ አንዳንድ ደቀ መዛሙርት ከኢዮጴ አስቸኳይ መልእክት ላኩበት። ኢዮጴ ለልዳ ቅርብ ነበረች። በኢዮጴ አንዲት ጣቢታ የተባለች በጎ አድራጊ ሴት በሞተች ጊዜ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በልዳ የነበረ መሆኑን ስላወቁ በቶሎ እንዲመጣላቸው አስቸኳይ መልእክት ላኩበት።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ሳይዘገይ በፍጥነት ተነሥቶ ወደ ኢዮጴ ሄደ። እዚያም የጣቢታ አስከሬን ዐርፎበት ወደነበረው ከፍተኛ ሰገነት አመጡት። ብዙ ድኻ መበለቶች እያለቀሱ ጣቢታ በሕወት በነበረች ጊዜ የሠራችላቸውን ቀሚስ አሳዩት። ሐዋርያው ልቡ ተነክቶ ሰው ሁሉ ከክፍሉ እንዲወጣለት አዘዘ። ተምበርክኮም ጸለየ። ከዚያም ፊቱን ወደ አስከሬኑ መለስ አድርጎ ጣቢታ ተነሽ አለ። እርስዋም ዐይንዋን በመክፈት ሐዋርያውን እያየች ተነሥታ ተቀመጠች። የዚህም ተአምር ዝና ብዙዎችን በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲያምኑ አድርጎአል።

<u>ሳውል በደማስቆና በኢየሩሳሌም</u>:- ሳውል በደማስቆ ምኵራቦች እየገባ ስለጌታችን ኢየሱስ መሲሕነት ሳይታክት ይሰብክ ነበር። የሚሰሙት ሁሉ እየተገረሙ ይህ ሰው ይህን አሁን የሚያስተምረውን እምነት የሚከተሉትን ሰዎች ሁሉ ይጠላና ያሳድድ አልነበረምን? እንዲያውም ወደዚህ የመጣው እነርሱን በመያዝ በኢየሩሳሌም ለካህናት አስረክቦአቸው ለማሳሰር አልነበ ረምን? ታዲያ፥ አሁን እንዴት ይህን እምነት ይሰብካል እያሉ ይገረሙ ነበር። ጥቂት ከቈየ በኋላ በደማስቆ የሚገኙ የአይሁድ እምነት ተከታዮች ሊገድሉት ዐቅደው በየመውጫ በሮቹ ሁሉ ሸምቀው ይጠብቁት ጀመር። ዕቅዳቸውም ስለታወቀ የእርሱ ደቀ መዛሙርት በቅርጫት አድርገው በአጥር ላይ አወረ ዱት።



አይሁድ ሊገድሉት ተማክረው በነበረበት ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ቅዱስ ጳውሎስን በቅርጫት አድርገው በቅጥር በኩል አወረዱት (የሐ:ሥ:9፥23–25)



www.ethiopianorthodox.org

ወደ ኢየሩሳሌም ሄዶ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ሊቀላቀል ቢፈልግ የእርሱን ወደ ክርስቶስ መመለስ እውነተኛነት ማመን ስላቃታቸው ፈሩት። በርናባስ ግን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት ሳውልን እንዳነጋገረውና እንዴት አድርጎም በደማስቆ ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በድፍረት ያስተማረ መሆኑን ገለጠላቸው። በኢየሩሳሌምም ከእነርሱ ጋር እየተዘዋወረ ስለጌታችን ኢየሱስ በድፍረት ያስተምር ነበር። የግሪክ ቋንቋ ከሚናገሩ የአይሁድ ወገኖች ጋር ይከራከር ነበር። እነርሱም ሊገድሉት ያቀዱ መሆናቸው ስለታወቀ ወንድሞች ወደ ቂርሣያ ወሰዱት፤ ከዚያም ወደ ጠርሴስ እንዲሄድ አደረጉ።

<u>ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች የላከው ሁለተኛ መልእክት</u>:- ይህ መልእክት በ57 ዓ.ም በመቄዶንያ ተጽፎ በቲቶና በሌሎች ስማቸው ባልተገለጠ ሰዎች እጅ የተላከ ነው (ም:8ቍ:16–24)። የተጻፈው በአንድ ቦታና በአንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ጊዜያትና በተለያዩ ቦታዎች ሊሆን ይችላል የሚል አስተሳሰብ አለ።

ይህን መልእክት ለመጻፍ ካነሣሡት ምክንያቶች መካከል በቆሮንቶስ ስላሉት ሁናቴዎች ቲቶ የነገረውን ዜና መነሻ በማድረግ ለእነዚያ ጉዳዮች መልስ ለመስጠት ፈልጎ ነው።

ከእነዚህም ጉዳዮች መካከል:-

1. ለመጀመሪያ መልእክቱ የነበረ አስተሳሰብ፥ (ም:7ቍ:8)
2. ስለ ሐሰተኞች ሐዋርያት (ም:11)
3. ስለራሱ መከላከያ መልስ (ም:10)
4. ለክርስቲያኖች ስለሚደረግ መዋጮ: (ም:9) ይገኙባቸዋል።

የመጽሐፉም ይዘት እንደሚከተለው ነው።

1. የተለመደው የሰላምታ አሰጣጥ (1፥1–11)
2. ስለ ግል ችግሩ ለቆሮንቶስ ሰዎች መግለጹ (1፥12–17)
3. ሕጋዊ የቤተ ክርስቲያን መሪ ስለመሆኑ (3፥1–18)
4. እውነተኛ ሐዋርያዊ አገልግሎት (4፥1–15)
5. በእምነት መኖር (4፥16–18)
6. ለምን እንደተጠራ ያውቃል (5፥1–9)



www.ethiopianorthodox.org

7. በክርስቶስ አማካይነት የእግዚአብሔር ወዳጅ መሆን (5፥11–21)
8. ልባቸውን ለክርስቶስ እንዲሰጡ ምክር (6፥1–18)
9. ንስሓ የገቡትን ማመስገን (7፥1–16)
10. በይሁዳ ላለች ቤ/ክ አስተዋፅኦ (8፥1–9፥15)
11. በኢየሩሳሌም ላሉ ድኾች አስተዋፅኦ (8፥1–9፥15)
12. አይሁዳዊነትን ለሚሰብኩ መልስ (11፥ 1 –29)
13. መመካት የሚያስፈልግ ቢሆን (11፥30 –12፥8)
14. ማስጠንቀቂያና ቡራኬ (12፥14–13፥13)

ጽሑፉን በሰላምታ ከጀመረ በኋላ እግዚአብሔርን አመስግኖ ወደራሱ ግል ጉዳይ ይገባል። ይኸውም በእስያ በነበሩ ጊዜ እርሱና ጓደኞቹ ስለደረሰባቸው ከባድ ችግር ለቆሮንቶስ ሰዎች ጽፎላቸዋል። እግዚአብሔርም ከዚያ ከባድ አደጋ ስላዳነው ምስጋናውን ያቀርባል።

ከዚያም በኋላ ወደ እነርሱ ያልሄደበትን ምክንያት ሲያስረዳ እነርሱን ላለማሳዘን ብሎ እንደሆነ ይገልጣል። ንግግሩንም በመቀጠል ወደ እነርሱ ቢሄድ ሊያሳዝኑት የማይገባቸው ሰዎች ያሳዝኑኛል ብሎ እንደሆነ መሆኑን ያስረዳል።

ለተቀዋሚዎቹ መልስ ለመስጠትና ለእርሱም ማንነት ለመከላከል ሲጀምር «በክርስቶስ ድል አድራጊዎች አድርጎ ለሚመራንና መልካም መዓዛ እንዳለው ሽቶ ስለ ክርስቶስ ያለንን ዕውቀት በየስፍራው ሁሉ እንድናዳርስ ለሚያደርገን አምላክ ምስጋና ይሁን» ብሏል። እርሱ እንዳለው ለሚጠፉት የሞት ሽታ ሲሆን ለሚድኑት ግን ሕይወትን የሚሰጥ መልካም መዓዛ ነው። የእግዚአብሔርንም ቃል በቅንነት የሚናገር እንጂ እንደ ንግድ ዕቃ እንደሚቸረችሩበት አለመሆናቸውን ገልጦአል። አሁን እንግዲህ ክርስቲያንነትን እያጥላሉ፥ የሐዋርያውንም ኀላፊነት እያናናቁ አይሁዳዊነትን ለማስፋፋት ወይም ክርስቲያኖችን ወደ አይሁዳዊነት ለመመለስ ጥረት ለሚያደርጉት ሰዎች መልስ ሲሰጥ ሐዲስ ኪዳኑ ምን ያኸል ከብሉይ ኪዳኑ ብልጫ እንዳለው ያስረዳል።

በመጀመሪያ ያደራ ደብዳቤ እንደሚያስፈልገውና ያደራው መልእክት ወይም የምስጋናው መልእክት እርሱ ያስተማራቸው እነርሱ ራሳቸው ማለት የቆሮንቶስ ሰዎች መሆናቸውን ይገልጣል። እነርሱም በአገልግሎቱ የመጡ

የክርስቶስ መልእክት መሆናቸውን ከገለጠላቸው በኋላ፥ ይህም በሰው ልብ ጽላት እንጂ በድንጋይ ጽላት ያልተጻፈ መሆኑን ያብራራል።

ቀጥሎም ፊደልን ሳይሆን መንፈስ ያለበትን ሐዲስ ኪዳን እንድናገለግል ያበቃን እግዚአብሔር ነው በማለት ብሉይ ኪዳንን በፊደል ሐዲስ ኪዳንን ደግሞ በመንፈስ ያመሳስላቸዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ ፊደል ሞትን ያመጣል መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል ብሏል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው የተበሠረው ወንጌል የተሰወረ የሚ መስላቸው ለሚጠፉት ወገኖች ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት ሰይጣን ልቡናቸውን ስላሳወረው ነው። ስለ ክርስቶስ ክብር የሚነገረውን የመልካም ዜና ብርሃን እንዳያዩ ያደርጋቸዋል።

ለቆሮንቶስ ሰዎችም ምክር ሲሰጣቸው እንዲህ ብሏል:-

«በማይመች ሁኔታ ከማያምኑ ሰዎች ጋር አትጣመሩ፤ ጽድቅና ኃጢአት እንዴት ሊተባበሩ ይችላሉ? ብርሃንና ጨለማ እንዴት አብረው ሊኖሩ ይችላሉ? ክርስቶስና ዲያብሎስ እንዴት ሊስማሙ ይችላሉ? የሚያምንና የማያምንስ በምን ሊተባበሩ ይችላሉ? የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ከጣዖት ጋር ምን ስምምነት አለው?» (2ኛ:ቆሮ:6ቍ:14–16)።

በመጀመሪያ የጻፈላቸው መልእክት ያሳዘናቸው መሆኑን ቢስማም እንኳ ያን መልእክት በመጻፉ አይጸጸትም። የማይጸጸተውና ደስ የተሰኘው እነርሱን በማሳዘኑ ሳይሆን በሐዘናቸው ምክንያት ንስሓ በመግባታቸው ነው።

ከዚያም በኋላ በይሁዳ ላሉ ክርስቲያኖች ስለሚደረግ መዋጮ ጉዳይ ያሳስባቸዋል። በዚህም ማሳሰቢያው የተለያዩ የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶችን በመጥቀስ የለጋስነትን ጠቀሜታ ያስረዳል።

አንዳንድ ስም አጥፊዎች በሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ላይ ያልሆኑ ነገሮችን እያወሩ መሆናቸውን ሰምቶ መልስ ሰጥቶበታል። እነዚህም ሰዎች የቆሮንቶስ ሰዎች ሳይሆኑ ሐሰተኞች ሐዋርያት እንደነበሩ ይገመታል። የእነርሱም ዓላማ የሌላውን ሰው ስም በማጥፋት ለራሳቸው ተሰሚነትን ለማግኘት ነው። በሐዋርያው ጳውሎስ ላይ ከተናገሩአቸው ሐሜቶች መካከል:- (1) በቅርብ ሲሆን ዐይነ አፋር እንደሆነና በሩቅ ሆኖ መልእክቱን ሲልክ ግን ደፋር



እነደሆነ፥ (2) በሥራውም በመንፈሳዊነት ሳይሆን በሥጋዊ መንገድ የሚ መላለስ ነው የሚሉት ይገኙባቸዋል።

ለመጀመሪያው ሐሜት መልስ ሲሰጥ «እኛ በሩቅ ሆነን በመልእክቶቻችን በምንጽፈውና በቅርብም ከእናንተ ጋር ሆነን በምንሠራው መካከል ምንም ልዩነት አለመኖሩን ይገንዘቡ» ብሏል።

ለሁለተኛው ሐሜት ደግሞ መልስ ሲሰጥ «ምንም እንኳ በዓለም ብንኖር የምንዋጋው እንደ ዓለም ሰዎች አይደለም፤ የጦር መሣሪያዎቻችንም ምሽግ ለማፍረስ የሚያስችል መለኮታዊ ኀይል ያላቸው ናቸው እንጂ እንደ ዓለም የጦር መሣሪዎች አይደሉም» ብሏል።

ራሳቸውን ከሚያመሰግኑ ከአንዳንድ ሰዎች ጋር ራሳችንን ልናነጻጽር አንደፍርም፤ እነርሱ ራሳቸውን ከራሳቸው ጋር ስለሚያወዳድሩ አስተዋዮች አይደሉም፤ እኛ ግን በተሰጠን መጠን እንመካለን እንጂ ከዚያ በላይ አንመካም ብሏል።

ስለሐሰተኞች ሐዋርያት የቆሮንቶስን ሰዎች በጥብቅ አስጠንቅቆአቸዋል። በምሳሌም ሲያስረዳቸው እባብ ሔዋንን በተንኰል እንዳታለላት እናንተም ትታለላላችሁ ብዬ እሰጋለሁ ብሎአቸዋል። ሌላ ሰው መጥቶ እርሱ የሰበከውን ሳይሆን ሌላ ኢየሱስ ቢሰብክላቸው፡ የተቀበሉትን ሳይሆን ሌላ መንፈስ፡ ወይም የተሰበከላቸውን ሳይሆን ሌላ ወንጌል ይዞ ቢመጣ እንዳይቀበሉት አስጠነቀቃቸው።

እንዲሁም እነዚህ ሐሰተኞች ሐዋርያት የክርስቶስ ሐዋርያት ለመምሰል ራሳቸውን የሚለውጡ መሆናቸውን ያስረዳና ይህም የማያስገርመው ሰይጣን እንኳ የብርሃን መልአክ ለመምሰል ራሱን እንደሚለውጥ ያመለክታል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከማንኛውም ሐዋርያ የማያንስ መሆኑ ቀድሞ በአይሁዳዊነቱ ጊዜ የነበረበት ሁናቴና አሁን በሐዋርያነቱ የደረሱበትን ፈተና ዎች፥ እንዲሁም ስለተገለጠለት ታላቅ ራእይ ዘርዝሮ አስረድቶአል።

በመጨረሻም ምክርና ሰላምታውን አቅርቦ ይህን ሁለተኛ መልእክቱን ይፈጽማል።



www.ethiopianorthodox.org

## ከዚህ ምዕራፍ የምናገኘው ትምህርት

የሙሴን አወላለድና አስተዳደግ ስንመለከት የእግዚአብሔርን ጥበባዊ ዝግጅት እናስተውላለን። የእስራኤል ሕዝብ የግብጾች ጭቆና ከብዶት ወደ እግዚአብሔር በጸለየ ጊዜ ጸሎቱ የተሰማለት ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ለቀድሞዎቹ የእስራኤል ሕዝብ አባቶች የገባው የተስፋ ቃል ተግባራዊ መሆን ስለነበረበት እስራኤልን ለማዳን የማዳኛው መንገድ መመቻቸት ነበረበት። በዚህም መሠረት ሕፃኑ ሙሴ በቅርጫት ውስጥ ሆኖ ሲያለቅስ በልዕቲቱ ታይቶ እንዲታዘንለት ማድረጉ ወደቤተ መንግሥት ተወስዶ በልዕልቲቱ አሳዳጊነት እየተማረ እንዲያድግና ለመሪነት እንዲዘጋጅ ለማድረግ ነው። አስተዳደጉም የግብጾችን ጥበብ እየተማረ ብቻ ሳይሆን በወላጅ እናቱ ሞግዚትነት ማንነቱን እንዲያውቅና ለወንድሞቹም ተቈርቋሪ ሆኖ እንዲያድግ ተደርጓል። ይህንንም የምናስተውለው ለእስራኤላዊው አግዞ ግብጻዊውን በመግደሉ ነው።

እግዚአብሔርም ይህን ቀናኢነቱንና ለመሪነት የተዘጋጀ መሆኑን ስለሚያውቅ በቍጥቋጦው እሳት ውስጥ ተገልጦለት የስራኤልን ልጆች መርቶ ከግብጽ ባርነት እንዲያስወጣ አዘዘው። ዓለማዊውን የአስተዳደር ትምህርት በፈርዖን ቤተ መንግሥት ከተማረ በኋላ የመንፈሳዊነቱን ሕይወት ደግሞ ከእግዚአብሔር በኩል ታድሎታል። በዚህም መሠረት የእስራኤልን ሕዝብ ልክ እንደ ወላጅ አባት፥ እንደ ዳኛ፥ እንደ ካህን፥ ከዚያም በላይ በሕዝቡና በእግዚአብሔር መካከል እንደ አማላጅ ሆኖ አርባ ዓመት ሙሉ በበረሓሙ ጉዞ መርቶአቸዋል።

የጦቢትን ታሪክ በምንመለከትበት ጊዜ ለእግዚአብሔር ሕግጋት ታማኝና ለሰው አዛኝ መሆን በወዲያኛው ዓለም ብቻ ሳይሆን በዚህ ዓለምም ዋጋ የሚያስጥ መሆኑን መገንዘብ እንችላለን። ምንም እንኳ ጦቢት ተፈትኖ ማንነቱ እንዲረጋገጥ ለተወሰነ ጊዜ ዐይኑ ቢታወር ከዚያ በኋላ ዐይኑ እንደገና በርቶለት ለ42 ዓመት ከቤተ ሰቡ ጋር በመኖር ዕድሜ ጠግቦ በአንድ መቶ ሁለት ዓመቱ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቶአል።

ሌላው ከመጽሐፈ ጦቢት የምንማረው ትምህርት ደግሞ መላእክት እንደምን እኛን እንደሚጠብቁና። ለእኛ እንደሚያማልዱ ነው። መልአኩ ሩፋኤል የጦቢትን ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ያቀርብ እንደነበረና ተገድለው የተጣሉትን ሰዎች እያነሣ ይቀብር በነበረ ጊዜ እርሱ ይጠብቀው እንደነበረ ገልጦለታል። አሁንም ከእግዚአብሔር ተልኮ የመጣው የጦቢትን ዐይንና ሣራን ለመፈወስ እንደሆነ ነገሮአቸዋል።



በዮናስ ታሪክ ውስጥ የንስሓን ጠቃሚነት እንማራለን። እግዚአብሔር ሁሉም እንዲድን እንጂ ማንም እንዲጠፋ ስለማይፈቅድ ለነነዌ ሰዎች ማስጠንቀቂያ እንዲሰጣቸው አደረገ። እነርሱም ንስሓ በገቡ ጊዜ ይቅርታ አደረገላቸው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ክርስቶስ የተመለሰበትን ሁናቴ ስንመለከት እግዚአብሔር የሚመለከተው የሰውን አፍኣዊ ሁናቴ ሳይሆን ውሳጣዊውን መሆኑን እንገነዘባለን። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቤተ ክርስቲያን በጣም ጠላትዋ እንደነበረ ይታወቃል። ክርስቲያኖችን እየተከታተለ ያሳድዳቸው ነበር፤ ያሳስራቸውም ነበር። እርሱም በጣም ለሃይማኖቱ ቀናተኛ ፈሪሳዊ ነበር። ይህን ሁሉ ያደርግ የነበረው ግን ትክክል የሠራና እግዚአብሔርን ያስደሰተ መስሎት ነበር። በአስተሳሰቡም ክርስትና የትክክለኛው ሃይማኖት ጠላት ይመስለው ነበር እንጂ የክርስትናን ትክክለኛነት አልተገነዘበም ነበር። ይህ ሁሉ አስተሳሰብ ከቅን ልቡና የመነጨ እንጂ በክፋት ወይም በተንኰል አልነበረም። የሰውን ልቡና ጠልቆ የሚያውቀው አምላክም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ መሳሳቱን በገለጠለት ጊዜ ያለምንም ማመንታት የእግዚአብሔርን ቃል ተቀበለ፤ ለቤተ ክርስቲያንም ታላቅ ሐዋርያ ሆነ። ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር አመቻቸለት።

ምንም እንኳ በየጊዜው የግድያ ዛቻና ሽመቃ ቢደረግበት እግዚአብሔር ስለጠበቀው ማንም ለብዙ ጊዜ ምንም ሊያደርገው አልቻለም።

እግዚአብሔር ለሐዋርያቱ የተአምራትና የድንቅ ነገር ኀይል ሰጥቶአቸው ስለነበረ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ በልዳ አንድ ሽባ ሲፈውስ በኢዮጴ ደግሞ አንድ ሰው ከሞት አስነሥቶአል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በላከላቸው መልእክቱ ለክርስትና ሃይማኖት የቱን ያኽል እንደሚሚገት እንገነዘባለን።

### ጥያቄዎች

1. የግብጹ ንጉሥ እስራኤሎች እንዲጨቄኑ የሰጠው ምክንያት ምን ድነው?

2. ግብጻውያን የእስራኤሎችን ሕይወት መራራ ያደረጉት ምን አድርገው ነው?

3. ንጉሡ እሰራኤሎች እንዲጨቄኑ በመወሰን ምን አደረገ?



www.ethiopianorthodox.org

4. የእስራኤል ሕዝብ በቊጥር እንዳይበዛ ለማድረግ ንጉሡ ምን ትእዛዝ አስተላለፈ?

5. የሙሴ እናት ሙሴን ከወለደች በኋላ ምን አደረገች?

6. ከሦስት ወር በኋላ ምን አደረገች? ለምን?

7. የሙሴ እኅት ምን አደረገች?

8. ሙሴን ያገኘችው ልዕለት ምን አደረገች?

9. ልዕልቲቱ ሙሴን ያገኘችው የት ነው?

10. እርስዋስ ምን ልታደርግ ሄዳ አገኘችው?

11. የሙሴ እኅት ልዕልቲቱን ምን አለቻት?

12. ልዕልቲቱ የሕፃኑን እናት ምን አለቻት?

13. ሙሴ የዐማቱን በጎች ሲያሰማራ ጌታ የተገለጠለት ምን በሚባል ቦታ ነው?

14. እዚያስ ምን አስደናቂ ነገር አየ?

15. ከዚያስ ከአስደናቂ ነገር ውስጥ ምን የሚል ድምፅ ሰማ?

16. ሙሴ ስለፈራ ምን ደረገ?

17. እግዚአብሔር ሙሴን መን አዘዘው?

18. ሙሴስ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ወዲያው ተቀበልን?

19. ሙሴ ለሰጠው ምክንያት እግዚአብሔር ምን አለው?

20. ዱዳንና ደንቆሮን የፈጠረ ማነው ብሎ እግዚአብሔር ሙሴን የጠየቀው በምን ምክንያት ነው?

21. በመጨረሻ እግዚአብሔር ምን ብሎት ነው ትእዛዙን የተቀበለው?

22. የእስራኤል ልጆች ሙሴንና አሮንን ያመኑአቸው ምን ስላደረጉ ነው?

23. ጦቢት ከማንኛው የእስራኤል ነገድ ነበር?

24. ጦቢት የተማረከው ማን በሚባለው የአሦር ንጉሥ ዘመን ነበር?

25. ሰናክሬም በአይሁድ ተማራኪዎች ላይ ምን ያደርግ ነበር?

26. ሰናክሬም በጦቢት ላይ የሞት ፍርድ የፈረደበት በምን ምክንያት ነው?



27. የሰናክሬም መጨረሻ ምን ሆነ?

28. ጦቢት ከተደበቀበት የወጣው መቼ ነው?

29. የጦቢትን ዐይን ያሳወረው ምንድነው?

30. ጦቢትን ተስፋ ያስቈረጠው ምንድነው?

31. ልጁን ጦብያን ምን ብሎ አዘዘው?

32. ከዚያስ ወዴት፥ ወደማንና ለምን ላከው?

33. ጦብያ ምን ፍለጋ ከቤቱ ወጣ?

34. በአንድ ወጣት ተመስሎ የተገናኘው ማነው?

35. በጉዞአቸው ወደ ማታ ጊዜ የደረሱበት ወንዝ ማን ይባላል?

36. ጦብያ በወንዙ ዳር ምን አጋጠመው?

37. መሪው ጦብያን ምን እንዲያደርግ አዘዘው?

38. የጦብያ መሪ ዓሣውን ምን እንዲያደርግ አዘዘው?

39. በመሸ ጊዜ የት ዐደሩ?

40. የጦብያ መሪ በዚያ በአደሩበት ቤት እግዚአብሔር ለጦብያ ምን እንዳዘጋጀለት ነገረው?

41. ጦብያ ግን ምን መልስ ሰጠው?

42. አስማንድዮስን ማን አባረረው?

43. የሳራ አባት ጦብያን ምን ብሎ አስማለው?

44. ጦብያ በሳራ አባት ቤት ስንት ጊዜ ቈየ?

45. የጦቢት ዐይን እንዴት ዳነ?

46. መልአኩ ሩፋኤል ማንነቱን የገለጠው መቼ ነው?

47. ጦቢት ከዚያ በኋላ ስንት ዓመት ኖረ?

48. ጦቢት በስንት ዓመት ዕድሜው ሞተ?

49. ማንነቱን ከማወቃቸው በፊት መልአኩን ሩፋኤልን ማን ብለው ይጠሩት ነበር?

50. እግዚአብሔር ነቢዩን ዮናስን ምን አዘዘው?



www.ethiopianorthodox.org

51. የነነዌ ከተማ ሕዝብ ምን ዐይነት ሕዝብ ነበር?

52. ነቢዩ ዮናስ ፈቃደኛ ያልሆነው ለምንድነው?

53. ፈቃደኛ አለመሆኑንስ ያሳየው እንዴት ነው?

54. ነቢዩ ዮናስ የተሳፈረበት መርከብ ምን ሆነ?

55. በመርከቡ ውስጥ የነበሩት ሰዎች ምን አደረጉ?

56. በመጨረሻ መርከበኞቹ ዕጣ በጣሉ ጊዜ በማን ላይ ወጣ?

57. ዮናስንስ ምን አደረጉት?

58. እግዚአብሔር ዮናስን ምን አደረገው?

59. ነቢዩ ዮናስ ሁለተኛ ጊዜ እግዚአብሔር ያዘዘውን ትእዛዝ ለመፈጸም ፈቃደኛ ሆነን?

60. የነነዌ ሰዎች የእግዚአብሔርን ይቅርታ ያገኙት ምን ስላደረጉ ነው።

61. ነቢዩ ዮናስ ግን ለምን ቅር ተሰኘ?

62. የክርስትናን ሃይማኖት ከመቀበሉ በፊት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ምን ዐይነት ሰው ነበር?

63. ሐወርያው ቅዱስ ጳውሎስ ክርስትናን የተቀበለው በምን ሁኔታ ነው?

64. ጌታችን ወደ ቅዱስ ክውሎስ በላከው ጊዜ ሐናንያ ለጌታችን ምን አለው?

65. ጌታችንስ ምን መልስ ሰጠው?

66. ሐናንያ ቅዱስ ጳውሎስን እንዴት ረዳው?

67. ሐዋርያው ጴጥሮስ በልዳና በኢዮጴ ምን ዐይነት ሁለት ተአምራትን አደረገ?

68. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በደማስቆና በኢየሩሳሌም ምን ችግር ደረሰበት?

69. ከችግሮቹስ እንዴት አመለጠ?

70 . ሐወርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች የላከውን ሁለተኛ መልእክቱን የጻፈው በምን መነሻነት ነው?

71. ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ቆሮንቶስ ተመልሶ ላለመሄዱ ምን ምክንያት ሰጠ?



72. የእርሱ ያደራ፡ ወይም የምስጋና ደብዳቤ ምን እንደሆነ ገለጠላቸው?

73. ብሉይ ኪዳንንና ሐዲስ ኪዳንን በምን አመሳስሎ ለያያቸው?

74. የሚገድልና ሕይወትን የሚሰጥ ምንና ምን ናቸው?

75. የተበሠረው ወንጌል የተሰወረ የሚመስላቸው እነማን ናቸው?

76. ለምንስ ተሰወረባቸው?

77. ባሳዘናቸው በመጀመሪያ መልእክቱ የማይጸጸተው ለምንድነው?

78. የሙሴን አወላለድና አስተዳደግ ስንመለከት ምንን እናስተውላለን?

79. ሙሴ በምን በምን ደረጃ ሆኖ የእስራኤልን ሕዝብ መራ?

80. የጦቢትን ታሪክ ስንመለከት ምንን እንገነዘባለን?

81. ከዮናስ ታሪክ ምን እንማራለን?

82. የሐወርያው ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ክርስትና መመለስ ታሪክ ስንመለከት ምን እንገነዘባለን?

## ምዕራፍ 3

## ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ

### የጌታችን ትምህርቶች

በጸሐፍትና በፈሪሳውያን ላይ የቀረበ ወቀሳ:- ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጻሐፍትና በፈሪሳውያን ላይ ካቀረበባቸው ወቀሳዎች መካከል የሚከተሉተ ይገኙባቸዋል:-

«ሰው ወደ መንግሥተ ሰማይ እንዳይገባ በሩን የምትዘጉ፥ እናንተ ግብዞች የሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን፡ ወዮላችሁ፡ እናንተ ራሳችሁ አትገቡበትም፡ መግባት የሚፈልጉትንም እንዳይገቡ ትከለክላላችሁ። ለታይታ በምታቀርቡት ረዥም ጸሎት እያመኻኛችሁ የመበለቶችን ቤት የምትበዘብዙ፡ እናንተ ግብዞች የሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን ወዮላችሁ፡ ስለዚህ እናንተ የባሰ ፍርድ ይደርስባችኋል። እናንተ ግብዞች የሕግ መምህራንና ፈሪሰውያን ወዮላችሁ፡ አንድን ሰው ወደ ሃይማኖታችሁ ለማስገባት በባሕርና በየብስ ትዞራላችሁ፤ ባስገባችሁትም ጊዜ ከእናንተ በሁለት እጥፍ ይብስ ለገሃነም የተዘጋጀ ታርጉታላችሁ። እናንተ የታወራችሁ ወዮላችሁ፥ ሰው በቤተ መቅደስ ቢምል ምንም



www.ethiopianorthodox.org

አይደለም ትላላችሁ፤ በቤተ መቅደሱ ወርቅ ቢምል ግን በመሓላው ይያዛል ትላላችሁ፤ እናንተ ሞኞችና ዕውሮች ከወርቁና ወርቁን ከሚቀድሰው ቤተ መቅደስ የቱ ይበልጣል? እንዲሁም ሰው በመሠዊያው ቢምል ምንም አይደለም? ትላላችሁ፤ በመሠዊያው ላይ ባለው መባ ቢምል ግን በመሐላው ይያዘል» ትላላችሁ። እናንተ ዕውሮች ከመባውና መባውን ከሚቀድሰው መሠዊያ የቱ ይበልጣል?

ስለዚህ በመሠዊያው የሚምል በመሠዊያውና በመሠዊያው ላይ ባለው ነገር ሁሉ ይምላል። በቤተ መቅደስም የሚምል በቤተ መቅደሱና በቤተ መቅደሱ ውስጥ በሚኖረው ሁሉ ይምላል። በሰማይ የሚምልም በእግዚ አብሔር ዙፋንና በዙፋኑ ላይ በሚቀመጠው ይምላል።

እናንተ ግብዞች የሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን ወዮላችሁ፥ ከእዝሙድ፥ ከእንስላል፥ ከከሙን ዐሥራት ትሰጣላችሁ፤ ነገር ግን በሕግ ውስጥ የሚገኙትን ዋና ዋና ነገሮች ትተዋላችሁ፤ እነርሱም ፍርድ፥ ምሕረትና ታማኝነት ናቸው፤ ያንን ሳትተዉ ይህንንም ማድረግ ይገባችሁ ነበር። እናንተ የታወራችሁ መሪዎች፥ ከምትጠጡት ሁሉ እንደ ትንኝ ትንሽ የሆነውን ነገር አውጥታችሁ ትጥላላችሁ+ እንደ ግመል ትልቅ የሆነውን ግን ትውጣላችሁ።

አናንተ ግብዞች የሕግ መምሕራንና ፈሪሳውያን ወዮላችሁ፥ ብርጭቆውንና ሳሕሉን ከውጪ በኩል ታጠራላችሁ፤ ውስጡ ግን ቅሚያና ስስት የሞላበት ነው፤ አንተ ዕውር ፈሪሳዊ፥ አስቀድመህ ብርጭቆውንና ሳሕኑን ከውስጥ በኩል አጥራ፤ በዚያን ጊዜ በውጪም በኩል ንጹሕ ይሆናል።

እናንተ ግብዞች የሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን ወዮላችሁ፥ በውስጣቸው በሞቱ ሰዎች አጥንትና በርኩስ ነገር ሁሉ የተሞሉ በውጪ ግን በኖራ ተለስነው የሚያምሩ የመቃብር ግንቦችን ትመስላላችሁ። እንዲሁም እናንተ በውጪ ለሰው ጻድቃን መስላችሁ ትታያላችሁ፤ በውስጣችሁ ግን ግብዝነትና ክፋት ሞልቶባችኋል።

እናንተ ግብዞች፥ የሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን ወዮላችሁ፥ የነቢያትን መቃብር ትገነባላችሁ፤ ወዮላችሁ፥ የነቢያትን መቃብር ትገነባላችሁ፤ የጻድቃንንም ሐውልት ታስጊጣላችሁ። እናንተ በአባቶችን ዘመን ተገኝተን ብንሆን ኖሮ የነቢያትን ደም በማፍሰስ ከእነርሱ ጋር ባልተባበርንም ነበር» ትለላችሁ። እንግዲህ ነቢያትን ለገደሉ ሰዎች ልጆቻቸው መሆናችሁን ራሳችሁ ትመሰክራላችሁ። እንግዲህ አባቶቻችሁ የጀመሩትን ሥራ እናንተ ፈጽሙት። አናንተ እባቦች፥ የእባብ ልጆች፥ እናንተ ከገሃነም ቅጣት ማምለጥ እንዴት ትችላላችሁ? ስለዚህ እነሆ፥ እኔ ነቢያትን፥ ጥበበኞችን፥ መምህራንን ወደ እናንተ እልካለሁ፡ ከእነርሱ አንዳንዶችን ትገድላላችሁ፤ አንዳንዶቹን ትሰ ቅላላችሁ፤ አንዳንዶቹንም በምኵራባችሁ ትገርፋላችሁ፤ ከከተማ ወደ ከተ ማም ታሳድዱአቸላችሁ፤ በዚህም መክንያት ከጻድቁ ከአቤል ደም ጀምሮ በመቅደሱና በመሠዊያው መካከል እስከገደላችሁት እስከ በራክዩ ልጅ እከ ዘካርያስ ደም በምድር ላይ ስለፈሰሰው የጻድቅ ደም ቅጣቱ በእናንተ ላይ ይደርሳል። በእውነት እላችኋላሁ፥ ይህ ሁሉ ቅጣት በዚህ ዘመን ሰዎች ላይ ይደርሳል» (ማቴ:ም:23ቍ:13–36)።

<u>ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ.ጋብቻ ማስተማሩ</u>:- ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከገሊላ ተነሥቶ ከዮርዳኖስ ማዶ ወደምትገኝ ወደ ይሁዳ ክፍል ሀገር ሄደ። የተከተሉትንም ሰዎች ፈወሳቸው። በዚያን ጊዜ ፈሪሳውያን ሊፈትኑት ፈልገው ሰው በማንኛውም ምክንያት ሚስቱን እንዲፈታ ተፈቅዶለታልን ብለው ጠየቁት። ጌታችንም ለጥያቄአቸው መልስ ሲሰጥ እግዚ አብሔር በመጀመሪያ ሰውን ሲፈጥር ወንድና ሴት አድርጎ እንደፈጠራቸውና ወንድም አባቱንና እናቱን ትቶ ከሚስቱ ጋር የሚተባበር መሆኑን አላነበባችሁምን? ስለዚህ እነርሱን እግዚአብሔር ያጣመራቸው ስለሆነ አንድ ናቸው ሁለት አይደሉም። እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው ሊለየው አይገባም አላቸው። በዚህ ጊዜ ፈሪሳውያን ታዲያ፥ ሙሴ ለምን የፍቺዋን ወረቀት ሰጥቶ ይፍታት አለ? ብለው ጠየቁት። ጌታችንም ሙሴ ሚስቶቻችሁን እንድትፈቱ የፈቀደላችሁ የልባችሁን ደንዳናነትና አስቸጋሪነታችሁን አይቶ ነው። ከቀድሞ ጀምሮ ግን እንደዚያ አልነበረም።

እኔ ግን እላችኋላሁ፤ ማንም ሰው ያለዝሙት ምክንያት ሚስቱን ቢፈታ አመንዝራ ያደርጋታል፤ የተፈታችውንም የሚያገባ እንዳመነዘረ ይቈጠራል። በዚህ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ የባልና የሚስት ጉዳይ እንደዚህ ከሆነ አለማግባት ይሻላል አሉት። ጌታችንም መልሶ ይህ ልዩ ችሎታ ለተሰጣቸው ነው እንጂ ለሁሉም አይሆንም አላቸው (ማቴ:ም:19ቍ:1–12)።

<u>ስታመነዝር የተያዘች ሴት</u>:- አንድ ጊዜ ጌታችን ኢሱስ ክርስቶስ በቤተ መቅደስ ሳለ ጸሓፍትና ፈሪሳውያን አንዲት ስትመነዝር የተያዘች ሴት ይዘው መጡና:- «መምህር ሆይ፥ ይህች ሴት ስታመነዝር ተይዛለች፤ እንድትገደል ሕጋችን ያዝዛል፤ አንተስ ምን ትላለህ» አሉት። ይህንንም ያሉት እርሱን የሚከስሱበት ምክንያት ለማግኘት አስበው ነው። በዚህ ጊዜ ጌታችን ጐንበስ ብሎ በምድር ላይ በጣቱ ይጽፍ ጀመር። ደጋግመው በጠየቁት ጊዜ ቀና ብሎ ከእናንተ መካከል ኀጢአት የሌለበት ሰው በመጀመሪያ ድንጋይ ይወርውርባት አላቸው። ከዚያም በኋላ እንደገና ጐንበስ ብሎ በመሬት ላይ ይጽፍ ጀመር:


www.ethiopianorthodox.org

እነርሱም ይህን በሰሙ ጊዜ አንድ በአንድ ከዚያ ወጥተው ሄዱ። ስለዚህ እዚያ የቀሩት ጌታችንና ተከሳሽዋ ሴት ብቻ ሆኑ።

ከዚህ በኋላ ጌታችን ቀና ብሎ ሴትዮዋን «ከሳሾችሽ የት አሉ? የፈረደብሽ ማንም የለምን? አላት እርስዋም፥ «ጌታ ሆይ፥ ማንም የለም» አለች።

እርሱም እኔም አልፈርድብሽም ሂጂ፤ ዳግመኛ ኃጢአት አትሥሪ አላት» (ዮሐ:ም8ቁ:1–11)።

<u>የሀብታሙ ወጣት ጥያቄ</u>:- አንድ ቀን አንድ ወጣት ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መጥቶ ጌታ ሆይ የዘለዓለምን ሕይወት እንዳገኝ ምን መልካም ነገር ማድረግ ይገባኛል ብሎ ጠየቀው። ጌታችንም ወደ ሕይወት ለመግባት ብትፈልግ ትእዛዞችን ጠብቅ አለው። ጌታችንም አትግደል፤ አታመንዝር፤ አትስረቅ፥ በሐሰት አትመስክር፤ አባትህንና እናትህን አክብር፥ ጐረቤትህን እንደራስህ አድርገህ ውደድ የሚሉት ትእዛዞች ናቸው አለው። ወጣቱም እነዚህንማ ትእዘዞች ፈጽሜአለሁ፤ ሌላስ የሚጐድለኝ ምንድን ነው ብሎ ጠየቀ። ጌታችንም ፍጹም መሆን ብትፈልግ ሂድና ያለህን ሸጠህ ገንዘቡን ለድኻ ስጥ፤ በሰማይ ሀብት ታገኛለህ፤ መጥተህም ተከተለኝ አለው። ወጣቱ ግን ብዙ ሀብት ስለነበረው ይህን በሰማ ጊዜ እየተከዘ ሄደ። በዚህ ጊዜ ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አላቸው:- በእውነት እላችኋለሁ፤ ለሀብታም ሰው ወደ መንግሥተ ሰማይ መግባት በጣም አስቸጋሪ ነው፤ ሀብታም ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ይቀላል። ደቀ መዛሙርቱ ይህን በሰሙ ጊዜ በጣም ተገረሙና ታዲያ፥ ማን ሊድን ይችላል? አሉ። ጌታችንም ወደ እነርሱ ተመልክቶ ይህ ነገር ለሰው የማይቻል ነው፤ ለእዚአብሔር ግን ሁሉ ይቻለዋል አለ (ማቴ:ም:19ቁ:16–25)።

## <u>የጌታችን ተአምራት</u>

<u>የከነዓናዊትዋ ሴት እምነት</u>:- ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደጢሮስና ሲዶና በሄደ ጊዜ አንዲት ከነዓናዊት ሴት ወደ እርሱ መጥታ የዳዊት ልጅ ጌታ ሆይ፥ ልጄ በርኩስ መንፈስ ተይዛ ትሠቃያለችና እባክህ ራራልኝ ብላ ጮኸች። ጌታችንም ምንም መልስ ሳይሰጣት ዝም በማለቱ ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ ቀርበው ይችች ሴት እየተከተለች ስለምትጮህ እባክህ አሰናብታት ብለው ለመኑት። እርሱ ግን እኔ የተላክሁት ከእስራኤል ቤት እንደበጎች ለጠፉት ብቻ ነው ሲል መለሰ። ሴትዮዋ በእግሩ ሥር ወድቃ ጌታ ሆይ፥ እባክህ እርዳኝ አለችው። በዚህ ጊዜ ጌታችን የልጆችን እንጀራ ወስዶ ለውሾች መጣል ተገቢ አይደለም ብሎ መለሰላት። እርስዋም ጌታ ሆይ፥



አሰናብታት ብለው ለመኑት። እርሱ ግን እኔ የተላክሁት ከእስራኤል ቤት እንደበጎች ለጠፉት ብቻ ነው ሲል መለሰ። ሴትዮዋ በእግሩ ሥር ወድቃ ጌታ ሆይ፥ እባክህ እርዳኝ አለችው። በዚህ ጊዜ ጌታችን የልጆችን እንጀራ ወስዶ ለውሾች መጣል ተገቢ አይደለም ብሎ መለሰላት። እርስዋም ጌታ ሆይ፥ እርግጥ ነው፤ ነገር ግን ውሾችም እኮ ከጌታቸው ማእድ የወደቀውን ፍርፋሪ ይበላሉ አለች። ጌታችን በዚህ መልስዋ እንዲህ አላት:- አንቺ ሴት፥ እምነትሽ ትልቅ ነው፤ ስለዚህ እንደ ፍላጎትሽ ይሁንልሽ አላት። የሴትዮዋም ልጅ በዚያኑ ሰዓት ድናለች (ማቴ:ም:15ቁ:21–28)።



የከነዓናዊትዋ ሴት ልጅ መፈወስ (ማር:7፡25–30)

ይህች ሴተ በማቴዎስ ወንጌል ከነዓናዊት ስትባል (ማቴ:ም:15ቁ:2) በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ 7 ቁ:26 ላይ ግሪካዊት ይላታል። እንዲያውም በሌላ ቋንቋ ሶርያዊትና ፊኒቂያዊት ይላል። ይህም ጢሮስና ሲዶና ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ በተለየም በሐዲስ ኪዳን ግሪካዊ ሲባል አብዛኛውን ጊዜ አረማዊ ለማለት ነው። ይህችም ሴት ግሪካዊ ስትባል ሃይማኖትን እንጂ ዜግነትን የሚመለከት አለመሆኑን ልናውቅ ይገባል።



www.ethiopianorthodox.org

__በአጋንንት የተያዙ ሁለት ሰዎች__:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የገሊላን ባሕር ተሻግሮ ወደ ጌራሴኖን አገር በመጣ ጊዜ አጋንንት የያዟቸው ሁለት ሰዎች ከመቃብር ቦታ ወጥተው ተገናኙት። እነርሱ በጣም አደገኞች ስለነበሩ ማንም ሰው በዚያ መንገድ ማለፍ አይችልም ነበር። በአጋንት የተያዙትም ሰዎች በድንገት እንዲህ እያሉ መጮኽ ጀመሩ:- አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ሆይ፥ እኛ ከአንተ ጋር ምን አለን? ጊዜው ሳይደርስ ልታሠቃየን መጣህን? ከእነርሱ ጥቂት ራቅ ባለ ስፍራ የብዙ ዐሣማዎች መንጋ ተሰማርቶ ነበር። አጋንንቱም የምታስወጣን ከሆነ እባክህ ወደዚያ ወደ ዐሣማዎቹ መንጋ ስደደን ሲሉ ለመኑት። ጌታችንም ሂዱ አላቸው። እነርሱም ወደ ዐሣማዎቹ ሄዱና ዐደሩባቸው። ዐሣማዎቹም በሙሉ ከገደሉ አፋፍ ላይ እየተንደረደሩ ወርደው በባሕር ውስጥ ሰጠሙ። የዐሣማዎቹ እረኞች ሸሽተው ወደ ከተማ ገቡና ሁሉን ነገር አወሩ፤ አጋንንት በያዙአቸው ሰዎች የሆነውንም ተናገሩ። ከዚህ በኋላ የከተማው ሰዎች ሁሉ ጌታችንን ለማየት ወጡ፤ ባዩትም ጊዜ ከአገራቸው ወጥቶ እንዲሄድላቸው ለመኑት(ማቴ: ም: 8 ቍ: 28–34)።

__ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በባሕር ላይ መራመዱ__:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኔ ሕዝቡን እስካሰናብት ድረስ በጀልባ ተሳፈሩና ቀድማችሁ ወደ ማዶ ተሻገሩ ብሎ ደቀ መዛሙርቱን አዘዛቸው። ሕዝቡንም ካሰናበተ በኋላ ለመጸለይ ብቻውን ወደ አንድ ተራራ ላይ ወጣ። በመሸም ጊዜ እዚያ ብቻውን ነበር። ደቀ መዛሙርቱ በጀልባ ተሳፍረው ወደ ቅፍርናሆም አመሩ። ጀልባዋ ከወደቡ ብዙ ርቃ በነበረ ጊዜ ብርቱ ነፋስ ከወደፊትዋ ተነሥቶ በማዕበሉ ወዲያና ወዲህ በማለት ትንገላታ ነበር። ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት በኋላ ጌታችን በባሕር ላይ እየተራመደ ወደ ደቀ መዛሙርቱ መጣ። ደቀ መዛሙርቱም በባሕር ላይ እየተራመደ ሲሄድ ባዩት ጊዜ በጣም ፈርተው ደነገጡ። ይህ ምትሐት ነው ብለው በፍርሃት ጮኹ። ጌታችንም ወዲያውኑ አነጋግራቸውና አይዞአችሁ፥ እኔ ነኝና አትፍሩ አላቸው። በዚያን ጊዜ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታ ሆይ፥ አንተስ ከሆንክ በባሕሩ ላይ እየተራመድሁ ወደ አንተ መምጣት እንድችል አድርገኝ አለው። ጌታችንም ና አለው። ስለዚህ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ከጀልባው ወርዶ ወደ ጌታችን ለመሄድ በባሕሩ ላይ ተራመደ። ነገር ግን የነፋሱን ኀይል አይቶ ፈራ፤ ወደ ባሕሩ ውስጥ ለመስጠም በተቃረበ ጊዜ ጌታ ሆይ፥ አድነኝ ብሎ ጮኸ። ጌታችንም ወዲያውኑ እጁን ዘርግቶ ያዘውና አንተ እምነት የጐደለህ፥ ስለምን ተጠራጠርህ አለው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና ሐዋርያው ጴጥሮስ ወደ ጀልባው በገቡ ጊዜ ነፋሱ ጸጥ አለ። በጀልባውም ውስጥ የነበሩት ሁሉ በእርግጥ አንተ የእግዚብሔር ልጅ ነህ ብለው ለጌታችን ሰገዱለት (ማቴ: ም: 14 ቍ:22–26)።



www.ethiopianorthodox.org

## የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መሳሌዎች

__የወይን አትክልት ቦታ ሠራተኞች አቀጣጠር ምሳሌ__:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካቀረባቸው ምሌዎች መካከል አንዱ የሚከተለው ነው:-

መንግሥተ ሰማይ በወይኑ አትክልት የሚሠሩ ሠራተኞችን ለመቅጠር ጠዋት በማለዳ የወጣውን የአትክልት ባለቤት ትመስላለች። እርሱም ለያንዳንዱ ሠራተኛ በቀን አንድ ብር ለመክፈል ተስማምቶ የቀጠራቸውን ሠራተኞች ወደ አትክልቱ ቦታ ላካቸው። በሦስት ሰዓት ገደማ ወደ አደባባይ ሲወጣ ሥራ ፈትተው ያገኛቸውን ሠራተኞች ለእናንተም የሚገባችሁን ዋጋ እከፍላችኋለሁና ወደ ወይኑ አትክልት ቦታ ሄዳችሁ ሥሩ ብሎ ላካቸው። እነርሱም ወደ ወይኑ የአትክልት ቦታ ሄደው ሥራቸውን ቀጠሉ። እንዲሁም በስድስት ሰዓትና በዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ወጥቶ ሌሎችንም ሠራተኞች ጠርቶ እንዲሠሩ ወደ ወይኑ የአትክልት ቦታ ላካቸው። ከዚያም በኋላ በዐሥራ አንድ ሰዓት ገደማ ወጥቶ ያገኛቸውን ሠራተኞች እናንተስ ለምን ቀኑን ሙሉ ሥራ ፈትታችሁ ቆማችኋል ብሎ ጠየቃቸው። እነርሱም የሚቀጥረን ሰው ባለማግኘታችን ነው ብለው መለሱለት። እንግዲያውስ እናንተም ወደ ወይኑ ያትክልት ቦታ ሄዳችሁ ሥሩ ብሎ ላካቸው።

በመሸም ጊዜ የወይኑ አትክልት ባለቤት ሎሌውን ጠርቶ በመጨረሻ ከተቀጠሩት ሠራተኞች ጀምረህ በመጀመሪያ እስከተቀጠሩት ድረስ የሥራ ዋጋቸውን ክፈላቸው ብሎ አዘዘው። ስለዚህ በዐሥራ አንድ ሰዓት የተጠቀሩት መጥተው እያንዳንዳቸው አንድ አንድ ብር ተቀበሉ። በፊት የተጠቀሩት በቀረቡ ጊዜ ይበልጥ የሚቀበሉ መስሎአቸው ነበር። ነገር ግን እነርሱም እያንዳንዳቸው አንዳንድ ብር ተቀበሉ። ገንዘቡን ከተቀበሉ በኋላ በወይኑ አትክልት ባለቤት ላይ እንዲህ ሲሉ አጕረመረሙ:- እነዚህ በመጨረሻ የመጡት ሠራተኞች የሠሩት ለአንድ ሰዓት ብቻ ነው፤ እነርሱን ከእኛ ቀኑን ሙሉ በፀሐይ ሙቀት ስንደክም ከዋልነው ጋር እኩል ከፈልካቸው። የወይን አትክልቱ ባለቤትም ከሠራተኞቹ አንዱን ጠርቶ የተዋዋልነው አንድ ብር ልከፍልህ አልነበረምን? እኔ አንተን ምንም የበደልኩህ ነገር ስለሌለ ገንዘብክን ይዘህ ሂድ። በገዛ ገንዘቤ በኋላ ለመጣውስ ከአንተ እኩል ለመስጠት መብት የለኝምን ? ወይስ እኔ ለጋስ ስለሆንኩ አንተ ትመቀኛለህን?

ከዚህ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ:- እንዲሁም ፊተኞች የሆኑ ኋለኞች ይሆናሉ፤ ኋለኞችም የሆኑ ፊተኞች ይሆናሉ አለ (ማቴ:ም:20ቍ:1–16)።

የሁለቱ ልጆች ምሳሌ:- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚከተለውን ምሳሌ ለአይሁድ ነገራቸው:-

አንድ ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት። ከሁለቱ አንዱን ወደ ወይን የአትክልት ቦታዬ ሄደህ ሥራ አለው። ልጁ ግን እምቢ አልሄድም አለ። ይሁን እንጂ በኋላ ተጸጸተና ሊሠራ ሄደ። አባትየው ሁለተኛውን ልጁን ወደ ወይን አትክልቱ ቦታ ሄዶ እንዲሠራ አዘዘው። እርሱም እሺ እሄዳለሁ አለው። ነገር ግን አልሄደም። ከእነዚህ ከሁለቱ የአባቱን ፈቃድ የፈጸመ የትኛው ነው ብሎ ጠየቃቸው። እነርሱም የመጀመሪያው ነው ብለው መለሱለት።

ጌታችንም በእውነት እላችኋለሁ ኃጢአተኞችና ዘማውያን ወደ መንግሥተ ሰማይ በመግባት ይቀድሙአችኋል። መጥምቁ ዮሐንስ የጽድቅን ሥራ ሊያሳያችሁ ቢመጣ አላመናችሁትም። ኃጢአተኞችና ዘማውያን ግን አመኑት፣ ይህንንም አይታችሁ እንኳ ንስሓ ገብታችሁ አልተመለሳችሁም አላቸው (ማቴ 21፥28–32)።

የአገልጋዮች ትጋት:- ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተናገራቸው ምሳሌዎች መካከል የሚከተለው ይገኝበታል:-

በአጭር ታጥቃችሁ ሁልጊዜ ለሥራ የተዘጋጀችሁ ሁኑ መብራታችሁም የበራ ይሁን። ጌታቸው በድንገት ከሠርግ ቤት ሲመጣ የሚጠባበቁትን አገልጋዮች ምሰሉ። እነርሱ ጌታቸው በድንገት መጥቶ በሚያንኳኳበት ጊዜ ለመክፈት ዝግጁዎች ናቸው። እነዚያ ጌታቸው በድንገት በመጣ ጊዜ ነቅተው ሲጠብቁ የሚያገኛቸው አገልጋዮች የተመሰገኑ ናቸው። በእውነት እላችኋለሁ እርሱ በአጭር ታጥቆ በማእድ ያስቀምጣቸዋል፣ በማስተናበርም ያገለግላቸዋል።

ጌታቸው በእኩለ ሌሊት ወይም ከእኩለ ሌሊት በኋላ በመጣ ጊዜ ነቅተውና ተግተው ሲጠብቁት የሚያገኛቸው አገልጋዮች የተመሰገኑ ናቸው። ደግሞም ይህን ዕወቁ። ሰው ሌባ የሚመጣበትን ሰዓት ለይቶ ቢያውቅ ኖሮ ሌባው ቤቱን ቈፍሮ ሲገባ አይተወውም ነበር። የሰው ልጅ ባላሰባችሁበት ሰዓት በድንገት ይመጣል፣ ስለዚህ እናንተም ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ (ሉቃ: ም: 12 ቊ: 35–48)።



## ከዚህ ምዕራፍ የምናገኘው ትምህርት

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጸሓፍትና በፈሪሳውያን ላይ ወቀሳውን ከመጀመሩ በፊት ለሕዝቡና ለደቀ መዛሙርቱ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶአቸዋል።

በሰጠውም ማስጠንቀቂያ ጸሓፍትና ፈሪሳውያን ለማስተማር በሙሴ ወንበር የተቀመጡ ስለሆነ እነርሱ የሚሉአችሁን ሁሉ ፈጽሙ፣ እነርሱ የሚሉትን ስለማያደርጉት እነርሱ የሚያደርጉትን አታርጉ። ከዚህ አባባል የምንማረው ቁምነገር አንድ ካህን የምሥጢራት ቤት ክርስቲያንን ሥርዓት በሚያከናውንበት ጊዜ በእርሱ ግላዊ ሕይወት ምክንያት የምሥጢራቱ ውጤት ልዩነት የማያመጣ መሆኑን ነው። የክህነትን ጸጋ የተቀበለ እስከሆነ ድረስ ግላዊ ሕይወቱ በውጤቱ ላይ ምንም ዐይነት ተጽዕኖ አያደርግም ማለት ነው።

እነዚህ ጸሓፍትና ፈሪሳውያን የሚያደርጉአቸው ድርጊቶች ሁሉ ለታይታ ስለሚያደርጉአቸው የሚለብሱትን ልብስ እንኳ ከሌላው ሰው የተለዩ ቅዱሳን እንዲያስመስላቸው ይፈልጋሉ። ሰውም በዚሁ በልብሳቸው ማንነታቸውን ለይቶ መምህራን፣ ሊቃውንት እንዲላቸው ይፈልጋሉ። በዚህም ምክንያት ጌታችን ደቀ መዛሙርቱንና ሕዝቡን ማንንም መምህር፣ ማንንም አባት፣ ማንንም ሊቅ ብላችሁ አትጥሩ ብሎ አስጠንቅቆአል። ይህንንም ሲል ደቀ መዛሙርቱ እንደ ጸሓፍትና ፈሪሳውያን የትዕቢትና የኩራት ተግባር እንዳይፈጽሙ ለማስጠንቀቅ ነው። መምህራቸው ክርስቶስ ራሱ እንደመሆኑ መምህራን ለመባል ፍላጎት አይደርባችሁ ብሎአቸዋል። ትምህርቱም የታላቁ መምህር የክርስቶስ እንጂ የእነርሱ ስላልሆነ መምህር አይባሉም። ይህ አባባል ግን የጸሓፍትና የፈሪሳውያንን ዓላማ ለመቃወም የተሰነዘረ ይሁን እንጂ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መምህራን የነበሩ መሆናቸው አይካድም። እነርሱም የክርስቶስን ትምህርት የሚያስተምሩ ናቸው።

ለዚህም የሚከተሉትን ማስረጃዎች እንመልከት:-

«ስለዚህ እግዚአብሔር እያንዳንዱ ሰው በቤተ ክርስቲያን የተለያየ አገልግሎት እንዲኖረው አድርጎአል፣ በዚህም መሠረት በመጀመሪያ ሐዋርያትን፣ ሁለተኛ ነቢያትን፣ ሦስተኛ መምህራንን ሾሞአል» (1ኛ: ቆሮ: ም:12ቊ:28)።



www.ethiopianorthodox.org

«እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ አንዳንዶቹ ነቢያት፥ አንዳንዶቹ የወንጌል ሰባኪዎች፥ አንዳንዶቹ የምእመናን እረኞች፥ አንዳንዶቹ አስተ ማሪዎች እንዲሆኑ ስጦታዎችን ሰጠ» (ኤፌ:ም:4ቍ:11)።

«በአንጾኪያ ባለችው ቤተ ክርስቲያን ነቢያትና መምህራን ነበሩ።» (የሐ:ሥ:ም:13ቍ:1)።

አባታችሁ በሰማይ ያለው ስለሆነ ማንንም በምድር ላይ አባታችን ብላችሁ አትጥሩ ያለው ሐዋርያትንና ተከታዮቻቸውን፥ ፓትርያርኮችንና ጳጳሳትን ነው። ይህም ማለት ምድራውያን የሆኑ ወላጆች አባቶቻቸው በቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አስተዳደርና ትምህርት ጉዳይ ምንም ዐይነት ተጽዕኖ ሊኖራቸው አይገባም ማለት ነው። የመንፈሳዊው አስተደር ኀላፊና አባት ሰማያዊው እንጂ ምድራዊ አባት አይደለም ለማለት ነው። በዚህም ምክንያት ሐዋርያት፥ ተከታዮቻቸው ፓትርያርኮች፥ ጳጳሳት በዚህ ዓለም አባት ብለው የሚጠሩት አይኖርም። ነገር ግን ምእምናን እነርሱን መንፈሳውያን አባቶች ይሉአቸዋል፤ እነርሱም ደግሞ ምእመናንን መንፈሳውያን ልጆቼ ብለው ይጠራሉ። በዚህም መሠረት ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ ምእመናንን ልጆቼ ብሎ ይጠራቸዋል (1ኛ:ዮሐ:ም:2ቍ:1፥18)።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም የቆሮንቶስን ሰዎች ልጆቼ፥ ጢሞቴዎስን ደግሞ ልጄ ብሎ እናገኘዋለን (1ኛ :ቆሮም:4ቍ:14፥17፤2ኛ:ጢሞ: 2 ቍ:1)።

ስለዚህ ጌታ ደቀ መዛሙርቱን ያስጠነቀቃቸው ከፈሪሳውያን ግብዝነት፥ ትዕቢትና ኩራት ተጠንቀቀው በትሕትና እንዲኖሩ ነው።

ጌታችንም ጸሕፍትንና ፈሪሳውያንን በሰባት ጉዳዮች ወቅሶ ወዮታ አቅር ቦባቸዋል።

1. መንግሥተ ሰማያትን እነርሱ ራሳቸው አይገቡበትም፤ ለመግባት የሚፈልጉትንም እንዳይገቡ በሩን ይዘጋሉ። ይህም ማለት እነርሱ ኦሪትንና ነቢያትን የሚያውቁ እንደመሆናቸው የክርስቶስን የመምጣት ምልክት ተገን ዝበው ራሳቸው ማመን ይገባቸው የነበረ ከመሆኑም በላይ የማያውቁትንም አስተምረው በማሳመን ለመንግሥተ ሰማይ ሊያበቁአቸው በተገባ ነበር። ይህን ከማድረግ ይልቅ ማንም እንዳያምን በመከላከል መንገዱን ይዘጉ ነበር።

2. እንዲሁም ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ለታይታ በሚያስረዝሙት ጸሎት አማኝነት ባሎቻቸው በሞቱባቸው ሴቶች ቤት ውስጥ እየገቡ ግፉ የተጋቡትን



ሴቶች የሚረዱ በመምሰል ስለሚበዘብዙአቸው በሃይማኖት ስበብ የማጭ በርበርና የማታለል ሥራ ይሠራሉ ማለት ነው። በፍርድም ቀን የበለጠ ቅጣት ይመጣባቸዋል።

3. ጸሐፍትና ፈሪሳወያን ሕዝቡ ወደ ክርስትና ገብቶ መንግሥተ ሰማይን እንዳይወርስ እየተከላከሉ ወደ እነርሱ የጥፋት መንገድ ለማምጣት የሚ ያደርጉት ጥረት ከፍተኛ ነበር። ሰዎችን ወደ ሃይማኖታቸው ለማስገባት በባሕ ርና በየብስ ይዞራሉ። ይህን የሚያደርጉት ለእግዚአብሔር ክብርና ለነፍሳት ድኅነት ሳይሆን በሰዎች ለመመስገን ብለው ነው። ወደ እነርሱ የሚያስገቡ ትንም የእነርሱን ጠባይና የእነርሱን አሠራር ያስተምሩታል። በክፋቱ፥ በአክራሪነቱና በግብዝነቱ ከእነርሱ የበለጠ ይሆናል። በዚህም ከእነርሱ በእጥፍ ለገሃነም የተገባ ይሆናል።

4. ወርቁን ከቤተ መቅደስ፥ መባውን ከመሠዊያው በማስበለጥ በወርቁና በመባው ነው እንጂ አንድ ሰው በቤተ መቅደሱና በመሠዊያው ቢምል በመሐላው አይያዝም ይላሉ። ይኸውም የግል ጥቅማቸውን ለማዳበር ሕዝቡ መባና ወርቅ እንዲያቀርብ ለመገፋፋት ነው። ይህም አሠራራቸው ሕዘብን ማሳሳትና በእግዚአብሔር ላይ የክሕደት ሥራ መሥራት ነው።

5. ከአዝሙድ፥ ከእንስላልና ከከሙን ዐሥራት መስጠት ሕግን በትክክል የሚፈጽሙ ለማስመሰልና በሰዎች ዘንድ ሃይማኖተኛ መስሎ ለመታየት ሲሆን ያንን መክፈል ደግሞ ምንም ያኽል ወጪ የማያስወጣቸው ነው። ነገር ግን ዋና ዋናዎቹን ነገሮች ማለት ፍርድን፥ ምሕረትንና ታማኝነትን ችላ ማለታቸው ጥቅሞቻቸው እንዳይጓደሉባቸው ነው።

6. ጸሓፍትና ፈሪሳውያን በሰው ፊት ሃይማኖተኛና ደግ መምሰል ይሞክራሉ፤ ውስጣቸው ግን ቅሚያና ስስት የሞላበት ነው። እነርሱም ውጪው ታጥቦ ውስጡ ያልታጠበ ብርጭቆ ወይም ሳሕን ዐይነት ናቸው። እንዲሁም በውስጣቸው በሬሳ ዐፅም የተሞላና በውጭ እንደተለሰነ መቃብር ናቸው።

7. የነቢያትንና የጻድቃንን መቃብር በማስጌጥ እነርሱ በአባቶቻቸው ዘመን ኖረው ቢሆኑ ኖሮ ነቢያትን ለመግደል ከእነርሱ ጋር ይተባበሩ እንዳልነበረ ገልጠዋል። ጌታችን ግን በዚህ አነጋገራቸው አባቶቻቸው ነቢያትን ገዳዮች እንደነበሩ መመስከራቸውን አጋልጦአቸዋል። እናንተም አባቶቻችሁ የጀመ ሩትን ፈጽሙ ያላቸው ነቢያት የገደሉትን እርሱን የሚገድሉ መሆናቸውን ሲነግራቸው ነው።



www.ethiopianorthodox.org

ፈሪሳውያን ለማወቅ ወይም ለመረዳት ብለው ሳይሆን ጌታችንን ለመክሰስ ምክንያት በመፈለግ ሰውሚስቱን በማንኛውም ምክንያት ሊፈታ ተፈቅዶለታልን ብለው ጠየቁት። ለመፍታት ይቻላል ካለ ራሱ የተናገረውን ራሱ አፈረሰው ለማለት፥ ለመፍታት አይቻልም ቢል ነጻነታችሁን ገደበባችሁ ብሎ ለማስጠላት አስበው ነው ጥያቄውን የጠየቁት። ነገር ግን የተጻፈውን አላነበባችሁምን ብሎ መጻሕፍትን በመጥቀስ አፋቸውን አሲዞአቸዋል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተ መቅደስ ሲያስተምር ሳለ የሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን በዝሙት ኃጢአት የተያዘች ሴት ይዘው መጥተው ሊፈትኑት እንዲህ አሉት:- እንደዚች ያለችዋ ሴት እንድትገደል ሕጋችን ያገዛል፤ አንተስ ምን ትላለህ?

በዚያን ጊዜ የነበረው የበላይ ገገር የሮም ንጉሥ ነገሥት ስለነበረ ማንኛውም ሌላ ወገን የሞት ፍርድ ለመወሰን መብት አልነበረውም። እነርሱም ሊያጠምዱት የፈለጉት ትወገር ያለ እንደሆነ በመንግሥት ሥልጣን ውስጥ ገባ ብለው ለመክሰስ፥፤ ምሕረት ይደረግላት ያለ እንደሆነ የሙሴን ሕግ ያፈርሳል ብለው በሕዝብ ዘንድ ሊያሳጡት ነበር። እርሱ ግን ተንኮላቸውን ስለሚያውቅ በራሳቸው ላይ በኅሊናቸው እንዲፈርዱ አደረጋቸው።

በሀብታሙ ወጣት ጥያቄና በጌታችን መልስ ላይ እንደ ተገለጠው፥ ባለጸጋ ወደ መግሥተ ሰማይ ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ይቀላል ተብሏል። ይህም ማለት ባለጸጋ ለመንግሥተ ሰማይ ሲል ሀብቱን በመላ ከሚሰጥ ይልቅ ለማለት ነው እንጂ ባለጸጋ የሆነ ሰው በፍጹም ወደ መንግሥተ ሰማ አይገባም ለማለት አይደለም።

ጌታችን ለከነዓናዊት ሴት የልጆችን እንጀራ ወስዶ ለውሾች መጣል ተገቢ አይደለም ያላት እርስዋን ለመፈተን ብሎ ነው እንጂ ከዘር ዘር ለመለየት ብሎ አይደለም።

በወይን ያትክልት ቦታ ሠራተኞች አቀጣጠር ምሳሌ እንደምንረዳው በመጨረሻ የመጡት በመጀመሪያ ከመጡት ጋር እኩል ክፍያ የተደረገላቸው መሆኑን ያመለክታል። ለዚህ አባባል ሁለት አማራጭ ትርጒሞች ተሰጥተውታል። የመጀመሪያው ትርጒም በመንግሥተ ሰማይ በአንድ የጽድቅ ደረጃ ያሉ ሰዎች ምንም መበላለጥ የሌለባቸው መሆኑ ነው። ሌላው ትርጓሜ ደግሞ በዕድሜአቸው ቀደም ብለው ለመንግሥተ ሰማይ የሚያበቃውን ተግባር በማወቅ የተዘጋጁ ወይም ቃለ እግዚአብሔር ለእነርሱ የደረሰው ዕድሜአቸው ከገፋ በኋላ ቢሆን ቃለ እግዚአብሔርን ከሰሙና ከተቀበሉበት ጊዜ ጀምሮ

ለመንግሥተ ሰማይ የሚያበቃ ተግባር እስከፈጸሙ ድረስ ለምን ከወጣትነት ዕድሜ አልጀመራችሁም አይባሉም ማለት ነው።

በሁለቱ ልጆች ምሳሌ የመጀመሪያው ልጅ ኃጢአተኞችና ዘማውያን፥ ሁለተኛው ልጅ አይሁድ ናቸው። በእግዚአብሔር አምነው የነበሩት አይሁድ የእግዚአብሔር ልጅ ሲመጣ የማይቀበሉት ሆኑ። እምነት ያልነበራቸው አረማውያን ግን የእግዚአብሔርን ልጅ ተቀበሉት።

ስለዚህ ነው ጌታችን በመንግሥተ ሰማይ ኃጢአተኞችና ዘማውያን ይቀድሙአችኋል ያላቸው።

በአገልጋይ ትጋት ምሳሌ ደግሞ የዕድሜአችን ፍጻሜ ወይም የዓለም መጨረሻና የጌታችን ለፍርድ መምጣት መቼ እንደሆነ ስለማናውቅ ሁልጊዜ ተዘጋጅተን እንድንጠብቅ ያስተምረናል።

## ጥያቄዎች

1. ጻሓፍትና ፈሪሳውያን ሰዎችን ወደ መንግሥተ ሰማይ እንዳይገቡ የሚከለክሉትና እነርሱም ራሳቸው የማይገቡት እንዴት ነው?

2. የመበለቶችን ቤት የሚበዘብዙት እንዴት ነው?

3. ሰውን ወደ ሃማኖታቸው አምጥተው ለገሃነም የተዘጋጀ የሚያደርጉት እንዴት ነው?

4. ከመቅደስ ይበልጥ ወርቁን፤ ከመሠዊያው ይልቅ መሥዋዕቱን ያከበሩበት ምክንያት ምንድን ነው?

5. በሰማይ የሚምል በምን ይምላል?

6. በመሠዊያው የሚምል በምን ይምላል?

7. በቤተ መቅደስ የሚምል በምን ይምላል?

8. ከአዝሙድ ከእንስላልና ከከሙን ዐሥራት በመክፈላቸው ለምን ተወቀሱ?

9. በወቀሳው ላይ ብርጭቆና ሳሕን የተጠቀሱት ለምንድን ነው?

10. መቃብርስ የተጠቀሰው በምን ምክንያት ነው?

11. አባቶቻችሁ የጀመሩትን እናንተም ፈጽሙ ማለት ምን ለማለት ነው?

www.ethiopianorthodox.org

12. ፈሪሳውያን ጌታችንን ስለጋብቻ ወይም ስለመፋታት የጠየቁት በምን ዐይነት ፈተና ሊፈትኑት ፈልገው ነው?

13. ጌታስ ምን መልስ ሰጣቸው?

14. ጸሐፍትና ፈሪሳውያን ስታመነዝር የተያዘች ሴት ይዘው ወደ ጌታችን ሲመጡ በምን ዐይነት ፈተና ሊፈትኑት ፈልገው ነበር?

15. እነርሱ ምን ብለው ጠየቁት?

16. እርሱስ ምን መልስ ሰጣቸው?

17. ሀብታሙ ወጣት ጌታችንን ምን ብሎ ጠየቀው?

18. ጌታችንስ ምን ብሎ መለሰለት?

19. ወጣቱ ሀብታም ለጌታችን መልስ ምን ዐይነት አጸፋ መልስ ሰጠ?

20. ሀብታሙ ወጣት ለምን አዘነ?

21. በወጣቱ ማዘን ምክንያት ጌታችን ምን አለ?

22. ደቀ መዛሙርቱ ማን ሊድን ይችላል ባሉት ጊዜ ጌታችን ምን አላቸው?

23. ጌታችን ለከነዓናዊቱ ሴት ጥያቄ ለምን መልሱን አዘገየባት?

24. የከነዓናዊቱ ሴት ጌታችንን ምን ለመነችው?

25. ጌታችንስ ምን መልስ ሰጣት?

26. እርስዋስ በጌታችን መልስ ላይ ምን አለች?

27. ከዚያስ በኋላ ምን አላት?

28. በጌራሴኖን አገር በአጋንንት የተያዙት ሁለት ሰዎች ጌታችንን ባዩ ጊዜ ምን ብለው ጮኹ?

29. እነርሱስ ጌታችንን ምን ለመኑት?

30. ዐሣማዎቹ ምን ሆኑ?

31. የዐሣማዎቹ እረኞች ምን አደረጉ?

32. የከተማው ሰዎች ጌታችንን ምን ለመኑት?

33. የጌታችን ደቀ መዛሙርት በጀልባ ወደ ቅፍርናሆም ሲሄዱ ምን ችግር ደረሰባቸው?



34. ከሌሊቱ በዘጠኝ ሰዓት ጌታችንን ወዴት አዩት?

35. ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታችንን ምን ለመነው?

36. ከዚያስ በኋላ ቅዱስ ጴጥሮስ ምን ደረሰበት?

37. ጌታችንስ እንዴት ረዳው?

38. ጌታችን ወደ ጀልባው ሲገባ ምን ሁናቴ ተከሠተ?

39. በጀልባው ውስጥ የነበሩ ሰዎች ምን አሉ?

40. ከወይን አትክልት ቦታ ሠራተኞች አቀጣጠር ምሳሌ ምን እንማራለን?

41. የወይን አትክልት ባለቤቱ በስንት በስንት ሰዓት ወጥቶ ሠራተኞችን ቀጠረ?

42. ለሠራተኞች የሠሩበትን ዋጋ በሚከፍልበት ጊዜ ተቃውሞ የተነሣበት ለምንድነው?

43. አባታቸው ያዘዛቸው የሁለቱን ልጆች ምሳሌ ተናገር

44. ከሁለቱ ልጆች ምሳሌ ምን እንማራለን?

45. ከአገልጋዮች ትጋት ምሳሌ ምን እንማራለን

46. ጌታችን ለሕዝቡ ጸሐፍትና ፈሪሳውያን በሙሴ ወንበር ተቀምጠዋልና የሚነግሩአችሁን አድርጉ እነርሱ የሚያደርጉትን ግን አታድርጉ የሚለውን ትምህርት ከምን ጋር እናወዳድረዋለን?

47. መምህር አትባሉ ሲል ምን ለማለት ነው?

48. አባታችን ብላችሁ አትጥሩ ሲልስ ምን ማለቱ ነው?

49. በወይን ያትክልት ቦታ ለተቀጠሩት ሠራተኞች ዋጋ አከፋፈል ሁለት አማራጭ ትርጒሞች አቅርብ።

50. ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ከሀብታም ሰው ወደ መንግሥተ ሰማይ መግባት የሚቀልለው እንዴት ነው?

www.ethiopianorthodox.org

# ምዕራፍ 4

# ቤተ ክርስቲያን

## የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት

ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን አዳኝነት በረከትና ለምእምናንዋ የምታ ስጥባቸው፥ ከሐዋርያት ዘመን ጀምራ የተረከበቻቸው ሰባት ምሥጢራት አሉአት። እነርሱም ምሥጢረ ጥምቀት፥ ምሥጢረ ሜሮን፥ ምሥጢ ቊርባን፥ ምሥጢረ ክህነት፥ ምሥጢረ ንስሐ፥ ምሥጢረ ተክሊልና ምሥ ጢረ ቀንዲል ናቸው።

ምሥጢረ ጥምቀት:- ምሥጢረ ጥምቀትን የመሠረተው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለመሆኑ የሚከተሉትን ጥቅሶች ይመለከቷል።

«እንግዲህ ወደ ዓለም ሕዝብ ሁሉ ሂዱና በአብ፥ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው የእኔ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው» (ማቴ: ም: 28ቊ:19)።

«ያመነ፥ የተጠመቀ ይድናል፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል» (ማር: ም:16ቊ:16)።

«እውነት፥ እውነት እልሃለሁ፤ ሰው ከውሃና መንፈስ ቅዱስ ካልተወለ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም (ዮሐ:ም:3ቊ:5)።

ጥምቀት ማለት በውሃ ውስጥ መዘፈቅ ማለት ነው። በጥምቀትም አማ ይነት:-

1. ከጥንቱ የተወረሰ ኃጢአት ነጻ እንሆናለን።
2. ከኃጢአታችን ይቅር እንባላለን።
3. የመንፈስ ቅዱስን ልደት እንወለዳለን።
4. የእግዚአብሔር ልጆች እንሆናለን።



ጥምቀት ወደ ክርስትና ሃይማኖት መግቢያ በርና መታወቂያ ምልክት ነው። በጥምቀት አማካይነት የምንታደላቸው ጸጋዎች በዐይን ሊታዩና በእጅ ሊዳሰሱ ስለማይችሉ ምሥጢር የተባለው ስለዚህ ነው።

ምሥጢረ ሜሮን:- የጥምቀትን ጸጋ ከተቀበልን በኋላ በእምነታችን እንድንጸና የሚረዳን በምሥጢረ ሜሮን አማካይነት የምንቀበለው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ነው። ሰው ከተወለደ በኋላ ለዕድገቱ ሥጋዊ ምግብ እንደሚ ያስፈልገው ሁሉ በምሥጢረ ጥምቀት አማካይነት የተወለድነው የመንፈስ ቅዱስ ልደት መንፈሳዊ ዕድገት ስለሚያስፈልገው በምሥጢረ ሜሮኑ አማካ ይነት ለመንፈሳዊ ዕድገታችን መንፈስ ቅዱስን መቀበል አስፈላጊ ነው።

ቀደም ብሎ በሐዋርያት ዘመን ለመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የሚጸለየው ሜሮን በመቀባት ሳይሆን በእጅ በመጫን ነበር። ይህ ግን በያንዳንዱ ሰው ላይ እጅ በመጫን ሲጸለይ ብዙ ጊዜ የሚወስድ በመሆኑና ወደ ክርስትና የሚገቡ ሰዎች እየበዙ በመሄዳቸው በሜሮን መቀባቱ ተመረጠ።

ከጥምቀት በኋላ መንፈስ ቅዱስን መቀበል አስፈላጊ መሆኑን ለመረዳት የሚከተሉትን ማስረጃዎች እንመልከት:-

«በኢየሩሳሌም የነበሩት ሐዋርያት የሰማርያ ሰዎች የእግዚአብሔር ቃል እንደተቀበሉ ሰምተው ጴጥሮስንና ዮሐንስን ሰደዱላቸው፤ እነርሱም በወረዱ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ ጸለዩላቸው፤ እነርሱ በጌታ ኢየሱስ ስም ተጠምቀው ነበር እንጂ መንፈስ ቅዱስ ገና በአንዳቸውም ላይ አልወረደም ነበር። ስለዚህ ጴጥሮስና ዮሐንስ እጆቻቸውን በጫኑባቸው ጊዜ ሰዎቹ መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ» (የሐ:ሥ:ም:8ቊ:14–17)።

«ይህን በሰሙ ጊዜ በጌታ በኢየሱስ ስም ተጠመቁ ጳውሎስም እጁን በጫነባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በነርሱ ላይ ወረደና በሌላ ቋንቋዎች ተናገሩ» (የሐ:ሥ:ም:19ቊ:5–6)።

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ የሜሮኑን ጥቅም ሲያብራራ እንዲህ ብሏል:-

«ክርስቶስ ግን በመንፈስ ቅዱስ ባርኳችኋል፥ መንፈስ ቅዱስ ከእናንተ ጋር እስካለ ድረስ ሌሎች አስተማሪዎች አያስፈልጉአችሁም፤ መንፈስ ቅዱስም እውነታችሁ ስለሆነ ሁሉንም ነገር ያስተምራችኋል፥ ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እንዳስተማራችሁ በልባችሁ ከክርስቶስ ጋር ኑ» (1ኛ:ዮሐ: ም: 2 ቊ: 27)።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

<u>ምሥጢረ ቍርባን</u>– በቅዳሴው ጸሎት አማካይነት ኅብስቱ ወደ ጌታችን ሥጋነት ወይኑ ደግሞ ወደ ጌታችን ደምነት እንደሚለወጡ በማመን ሥጋውን በልተንና ደሙን ጠጥተን ለኃጢአታችን ስርየት እንድናገኝና ከጌታችንም ጋር ኅብረት እንዲኖረን የሚደረገው ሥርዓት ምሥጢረ ቍርባን ይባላል። ቤተ ክርስቲያን ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስና ከሐዋርያት የተቀበለችው ትምህርት የቅዳሴው ጸሎት ከተጸለየባቸው በኋላ ኅብስቱ ተራ ኅብስት፥ ወይኑ ደግሞ ተራ ወይን አለመሆናቸውንና ነገር ግን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም መሆናቸውን ነው።

እነዚህን ከላይ የተገለጡትን አባባሎች ጌታችን እንዴት አድርጎ እንደነ ለጣቸው ቀጥለን እንመልከት።

«ሲበሉም ኢየሱስ ኅብስት አንሥቶ የምስጋና ጸሎት አደረገ፤ ቆርሶም ለደቀ መዛሙርቱ እንካችሁ ብሎ ይህ ሥጋዬ ነው ብሎ ሰጣቸው። ጽዋውንም አንሥቶ የምስጋና ጸሎት ካደረገ በኋላ እንዲህ ሲል ሰጣቸው፤ ሁላችሁም ከዚህ ጽዋ ጠጡ፤ ይህ ስለብዙዎች የኃጢአት ይቅርታ የሚፈስስ የሐዲስ ኪዳን ደሜ ነው» (ማቴ:ም:26ቍ:26–28)።

«ስለዚህ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው:- እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ፥፤ ደሙንም ካልጠጣችሁ ሕይወት የላችሁም። ሥጋ ዬን የሚበላና ደሜንም የሚጠጣ ሁሉ በእኔ ይኖራል፤ እኔም በእርሱ እኖራ ለሁ» (ዮሐ:ም:6ቍ:53፥56) ።

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስም የጌታችን ሥጋና ደም ከኃጢአታችን እንደ ሚያነጻ ሲያብራራ እንዲህ ብሏል:-

«የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአታችን ሁሉ ያነጻናል» (1ኛ: ዮሐ:ም:1ቍ:7)።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ስለ ምሥጢረ ቍርባን ክብር እንዲህ ብሏል:- «ማንም ሰው ያልተገባው ሆኖ ሳለ የጌታን ኅብስት ቢበላና የጌታንም ጽዋ ቢጠጣ የጌታን ሥጋና ደም በማቃለሉ ይጠየቅበታል» (1ኛ: ቆሮ: ም: 11 ቍ:27)።

<u>ምሥጢረ ክህነት</u>:- የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት ለማከናወን፥ ምእመናን ለማስተማር፥ የንስሓ ኑዛዜን በመስማት ተገቢውን እርማትና ምክር ለመስጠት የሚያስችለውን ጸጋ መቀበል ምሥጢረ ክህነት ይባላል።



ይህን ምሥጢር የመሠረተው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያቱን በመረጠ ጊዜ ነው። ለእነርሱም ለሌሎች ያልተሰጡ ስጦታዎችን ሰጣቸው። በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 28 ላይ እንደተገለጠው የማጥመቅን መብት የሰጣቸው ለእነርሱ ነው። ሥጋውንና ደሙን የሰጣቸው ለእነርሱ ነው። እጅ የመጫንን መብት የሰጣቸው ለእነርሱ ነው። በመጨረሻም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእነርሱ ጋር እንደሚሆን ገልጦላቸውል (ማቴ:28፥20)።

ሐዋርያው ቅዱስ ቅጳውሎስ ስለዚህ ምሥጢር ለጢሞቴዎስ እንዲህ ሲል ጽፎለታል:- «ትንቢት በተነገረልህ ጊዜና የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችም እጃቸውን በጫባኑብህ ጊዜ የተሰጠህን በአንተ ያለውን መንፈሳዊ ስጦታ አትዘንጋ» (1ኛ:ጢ.ሞ:4፡14)።

ይህም ምሥጢር ምን ያኽል ክብር እንዳለው ለጢሞቴዎስ ሲገልጥለት እንዲህ ብሎታል:- «እጅህን በመጫን ማንንም ለመሾም አትቸኩል፤ ከሌሎች ሰዎች ጋር በኃጢአት አትተባበር፤ ራስህን በንጽና ጠብቅ» (1ኛ:ጢ.ሞ:ም:5፥ቍ:22) ።

የክህነት ደረጃዎች ሦስት ናቸው፡ እነርሱም:- ኤጲስ ቆጶስነት፥ ቅስናና ዲቁና ናቸው።

<u>ምሥጢረ ንስሓ</u>:- ንስሓ ምሥጢር ነው የተባለው ለካህናት በተሰጣቸው በዐይን በማይታየው ሥልጣን አማካይነት በንስሓ ተመላሾቹ በዐይን የማይታይ የኃጢአት ስርየት የሚያገኙ በመሆናቸው ነው። በጥምቀት እንደገና ተወልደን የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ከተቀበልን በኋላ በተፈጥሮ ክፉ ዝንባሌአችን ለምናደርሰው በደል መድኀኒቱ ንስሓ ነው።

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ምሥጢር የመሠረተው:- «እውነት እላችኋለሁ፤ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድር የምትፈቱት በሰማይ የተፈታ ይሆናል» በማለት ነው (ማቴ:ም:18ቍ:18)።

ንስሓ መግባት ማለትም አንድ ከኃጢአተኛነቱ ተመልሶ በጽድቅ ሥራ ለመኖር የሚፈልግ ሰው ስለ ሠራው ኃጢአት በመጸጸት እንደዚህ ያለውን ችግር ለመስማት ሥልጣን ለተሰጠው ካህን መናዘዝና ካህኑ የሚሰጠውን ምክርና ትእዛዝ ተቀብሎ በሥራ ላይ ማዋል ነው።



www.ethiopianorthodox.org

ምሥጢረ ተክሊል፡- ጋብቻን የመሠረተው ፈጣሪ አምላክ መሆኑ ግልጽ ነው። ይህን ትምህርት ሲያብራራ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ብሏል፡- «እግዚአብሔር በመጀመሪያ ወንድና ሴት አድርጎ እንደፈ ጠራቸው አላነበባችሁምን? ደግሞም በዚህ ምክንያት ሰው አባቱንና እናቱን ትቶ ከሚስቱ ጋር ይተባበራል፤ ሁለቱም አንድ ይሆናሉ ያለውን አላነበባችሁምን? ስለዚህ እነርሱ ከእንግዲህ ወዲህ አንድ ናቸው እንጂ ሁለት አይሆኑም፤ እግዚአብሔር አንድ ያረገውን ሰው አይለየው» (ማቴ: ም: 19:ቍ:4–6)።

አንድነትን ለማስገኘትና የጋብቻቸውን ግዴታ ለማክበር በቤተ ክርስቲያን አማካይነት ቃል ለሚገቡት ሙሽራና ሙሽሪት ካህኑ የሚያከናውነው የጸሎት ሥነ ሥርዓት ምሥጢረ ተክሊል ይባላል።

መሥጢረ ቀንዲል፡- ለአንድ ሕመምተኛ የተለየ የቀንዲል ጸሎት በሚደ ረግበት ጊዜ ከሥጋው ሕመም ፈውስና ከኃጢአት ስርየት የሚያገኝበት ሥርዓት ምሥጢረ ቀንዲል ይባላል።

የቀንዲል ጸሎት የተጀመረው ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ ለመሆኑ የሚከ ተለውን ማስረጃ እንመልከት።

«ብዙ አጋንንትንም አወጡ፤ ብዙ ድውዮችንም ዘይት እየቀቡ ፈወሱ አቸው።» (ማር:ም:6ቍ:13)

ሐዋርያው ያዕቆብ የምሥጢረ ቀንዲልን አሠራር በዝርዝር ሲያስረዳ እንዲህ ብሏል።

«ከእናንተ መካከል የታመመ ሰው ቢኖር የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችን ወደ እርሱ ይጥራ፤ እነርሱም በሽተኛውን በጌታ ኢየሱስ፥ ክርስቶስ ስም ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት። እንዲህ ዐይነቱ በእምነት የተመሠረተ ጸሎት በሽተ ኛውን ያድነዋል፤ የሠራው ኃጢአትም ቢኖር ይቅር ይባልለታል» (ያዕ: ም:5ቍ:14–15)።

## የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳን

ሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ፡- መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ ከወረደ በኋላ ሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ ወደ ሕንድ አገር ሄደ። እዚያም በአንድ ሉቅዮስ በሚባል የንጉሡ ወዳጅ ቤት እንደ ባሪያ ሆኖ ሠራ። ሉቅዮስም ወደ ንጉሡ



ወሰደው። ሙያው ምን እንደሆነ ንጉሡ በጠየቀው ጊዜ ማንበኝነት፣ አናጢነትና ሐኪምነት መሆኑን ገለጠለት። በቤተ መንግሥቱ ጥቂት ቀናት ከቈየ በኋላ በቤተ መንግሥቱ ላሉ ሰዎች ወንጌል ማስተማሩን ቀጥሎ የሉቅዮስ ሚስትና ከቤተሰቡ ሌሎችም አመኑ። ንጉሡ ምንድን ነው የሠራኸው ብሎ ለጠየቀው ጥያቄ ሐዋርያው መልስ ሲሰጠው የሠራኸው ቤተ መንግሥት የክብር ንጉሥ ቦታ ሆነ አለው። የሠራሁት የአናጢነት ሥራ የኃጢአትን እሾኽ የሚቈርጠው ወንጌል ነው፤ ሕክምናውና መድኀኒቱ የእግዚአብሔር ቅዱሳት ምሥጢራት ናቸው። የደግነት ጠላት ከሆነው መርገዝ ያድናል አለው። ንጉሡ በዚህ ጉዳይ ተቈጥቶ ሐዋርያውን በጣም አሰቃየው። በአራት ካስማዎች አስሮ ቈዳውን ገፈፈው። ሰውነቱንም በኖራና በጨው አሸው። ሐዋርያው ይህን ሁሉ ታገሠ።የሉቅዮስ ሚስት ይህን ባየች ጊዜ ከበትዋ መስኮት ወድቃ ሞተች። ቶማስን ግን እግዚአብሔር ከቍስሉ ፈወሰው። ሉቅዮስ በሚስቱ ሞት አዝኖ ሚስቴን ከሞት ብታስነሣልኝ በአንተ አምላክ አምናለሁ ብሎ ለሐዋርያው ነገረው።

ሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ የሉቅዮስ ሚስት አስከሬን ወደነበረበት ገብቶ አርሳቦና ሆይ፣ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነሺ አላት። ወዲያው ተነሥታ ለሐዋርያው ቶማስ ሰገደችለት። ባልዋም ይህን ባየ ጊዜ እርሱና ከከተማው ብዙዎቹ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው ተጠመቁ።

በባሕሩ ላይ ትልቅ ዛፍ ወድቆ ማንም ሰው ሊያወጣው አልቻለም ነበር። ሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ ዛፉን ለማውጣትና በእርሱም ቤተ ክርቲያን እንዲሠ ሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ ዛፉን በመስራብት ይፈቀድለት ዘንድ ንጉሡን ጠየቀ። ንጉሡም ፈቀደለትና ዛፉን በመስ ራብት

ለምእመናኑም ኤጲስ ቆጶስና ካህናት ከሾመላቸውና በእምነታቸውም እንዲጸኑ ካደረገ በኋላ ቀን ጡራ ወደምትባል ከተማ ሄደ። በዚያች ከተማም ንጉሡ ስድስት ልጆቹን የገደለበት አንድ ሽማግሌ መራራ ለቅሶ ሲያለቅስ አገኘው። ሐዋርያው ቶማስ ከጸለየላቸው በኋላ ግን እግዚአብሔር ከሞት አስነሣቸው። ይህ ሁናቴ የጣዖትን ካህናት ስለአበሳጫቸው በድንጋይ ሊወግ ሩት ፈለጉ። ይህንንም ለማድረግ ከእነርሱ አንዱ እጁን በዘረጋ ጊዜ እንደዚያው እንደተዘረጋ ደርቆ ቀረ። ሐዋርያው ቶማስ በመስቀለኛ ሲባርከው እንደቀ ድሞው ተመልሶ ደኅና ሆነለት። ይህን ተአምር ባዩ ጊዜ ሁላቸውም በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አመኑ። ከዚያም በኋላ በርኪናስ ወደተባለች ከተማና ወደሌሎችም ሄደ ስለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስተማረ። የዚያ አገር ንጉሥ ስለ ሐዋርያው ማስተማር በሰማ ጊዜ ይዞ አሰረው። እንደገናም በእስር ቤት



www.ethiopianorthodox.org

በእስር ቤት ሆኖ ለእስረኞቹ የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚያስተምር ሆኖ ስላገኘው ከእስር ቤት አውጥቶ በተለያየ ዐይነት ሥቃይ ያሠቃየው ጀመር።

በመጨረሻም ራሱን ቈርጦት የሰማዕትነትን አክሊል ተቀዳጀ። በመሊባር ተቀብሮ በኋላም ዐፅሙ ወደ ራሓ ተወስዶአል። (የግንቦት 26 ቀን ስንክሳር)

<u>ሐዋርያው ቅዱስ ማትያስ</u>:- ሐዋርያው ቅዱስ ማትያስ የተወለደው በቤተልሔም ነው። ሐዋርያትን ተከትለው ከሚሄዱት አንዱ ነበር። በከሐዲነቱ ቦታውን በለቀቀው በአስቆሮቱ ይሁዳ ምትክ ከዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ ለመሆን ዕጣ የደረሰው ሐዋርያው ማትያስ ነው። ከተመረጠም በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ወንጌልን ለማስተማር ሄደ። የሄደውም የሰው ሥጋ ወደሚበሉ ሰዎች አገር ነበር። የዚያ አገር ሰዎች አንድ እንግዳ በእጃቸው ሲገባ ወደ እስር ቤት ይወስዱትና ለሠላሳ ቀኖች ሣር እንዲበላ ያደርጉታል። ይህን ካደረጉ በኋላ ነበር ከእስር ቤት አውጥተው ሥጋውን የሚበሉት።

ሐዋርያው ማትያስ ወደዚያ አገር ደርሶ ስለፍቅር ባስተማራቸው ጊዜ ያዙትና ዐይኑን አወጡት። ከዚያም ወደ እስር ቤት አስገቡት። ጊዜው ከመድረሱ በፊት ግን ጌታችን ሐዋርያውን እንድርያስንና ደቀ መዝሙሩን ወደ እርሱ ላከለት። ወደ እስር ቤቱም ሄደው በእስረኞቹ ላይ ምን እንደሚደረግ ተመለከቱ። በዚህ ጊዜ እነዚህን ሐዋርያት ይገድሉአቸው ዘንድ ሰይጣን የከተማውን ሕዝብ አነሣሣ።

ሕዝቡም ሊይዛቸው ባሰበ ጊዜ ሁለቱ ሐዋርያት ወደ እግዚአብሔር ጸለዩ። ከዚያ በኋላ ከእስር ቤቱ ዐምዶች በአንዱ ሥር የውሃ ምንጭ ፈነዳና ከተማውን አጥለቀለቀው። የከተማው ኑዋሪዎች በሁናቴው በተጨነቁና ተስፋ በቈረጡ ጊዜ ወደ ሐዋርያቱ መጥተው ኃጢአታቸውን በመናዘዝ አለቀሱ። ሐዋርያቱም በጌታ ኢየሱስ እመኑና ትድናላችሁ አሉአቸው። ሁሉም አመኑ፤ ሐዋርያው ማትያስንም ከእስር ፈቱት። እንድርያስና ደቀ መዝሙሩም ወደ እግዚአብሔር ጸልየው ጐርፉ ተወገደላቸው። ከዚያም ምሥጢረ ሥጋዌን ካስተማሩአቸው በኋላ በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጠመቁአቸው። የነበረባቸውም የአውሬነት ጠባይ እንዲወገድላቸው ወደ ጌታችን ኢየሱስ ከጸለዩላቸው በኋላ ተወግዶላቸዋል።

ለተወሰነ ጊዜ ከእነርሱ ጋር ከቈዩ በኋላ ኤጲስ ቆጶስና ሌሎችንም ካህናት ሾመውላቸው ሄዱ።

ሐዋርያው ማትያስ ግን ወደ ደማስቆ ሄዶ ወንጌልን በሚያስተምርበት ጊዜ ሕዝቡ ተቈጥቶ በመያዝ በአዲስ አልጋ ላይ አስተኝተው ከበታቹ እሳት



www.ethiopianorthodox.org

ቢለኰሱበት እሳቱ ምንም ሳይጐዳው ቀርቶአል። እንዲያውም ፊቱ እንደ ፀሐይ ሲያንጸባርቅ ታይቶአል። በዚህ ተገርመው ሁሉም በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አመኑ። ሐዋርያውም ካጠመቃቸው በኋላ ካህናትን ሾመላቸው። በእምነታቸው እንዲጠናከሩ እያስተማራቸውም ለብዙ ጊዜ ከእነርሱ ጋር ቈየ። ከዚያም ፋላኦን በምትባል በአንዲት የአይሁድ ከተማ በሰላም ዐርፎ እዚያው ተቀበረ። (የመጋቢት 8 ቀን ስንክሳር)

<u>ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ</u>:- ቅዱስ ጊዮርጊስ ዘሮንቶስ አንስጣስዮስ ከሚባል አባትና ቴኦብስታ ከምትባል እናት በቀጰዶቅያ ተወለደ። ዕድሜው ሃያ ዓመት በሞላው ጊዜ አባቱ ሞተበት። የአባቱን ሥራ ለመውረስ በሄደ ጊዜ ንጉሡ ከሐዲ በመሆን የጣዖት አምልኮን ትእዛዝ የሚያስተላልፍ ሆኖ አገኘው። ቅዱስ ጊዮርጊስም በዚህ ነገር አዝኖ ገንዘቡን ሁሉ ለድኆች ከሰጠ በኋላ ወደ ንጉሡ ቀርቦ እኔ የማመልከው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ነው ብሎ ገለጠለት። ይህንንም ያደረገው በክርስቲያኖች ላይ የተወሰነው ውሳኔ ካየ በኋላ ነው። በክርስቲያኖች ላይ የተላለፈውንም የውሳኔ ወረቀት በቍጣ ቀድዶ ጣለው። በዚህም ምክንያት ወደ ንጉሡ ነገሥቱ ወሰዱት።

እውነተኛ ባለመሆኑ እናንተም እንኳ የምትጠራጠሩትን መንገድ እንዴት ተሉ ፈልጋችሁ ትክክለኛውን ሃይማኖት የሚከተሉትን ንጹሓን ክርስቲያኖችን የምትጠሉአቸውና ቍጣችሁን በእነርሱ ላይ የምታወርዱት እስከመቼ ድረስ ነው? አንድም በዚህ እውነተኛ የክርስቲያን ሃይማኖት ማመን ይኖርባችኋል፤ አለበለዚያም ሃይማኖቱን የያዙትን ሰዎች በድንቁርና አታስቸግሩአቸው ብሎ በመካከላቸው ከፍ ባለ ድምፅ ተናገረ። ንጉሡም ቅዱስ ጊዮርጊስን ዝም ያሰኘው ዘንድ መፍናንዮስ የተባለውን ሚኒስትር ጠቀሰውና ምልክት ሰጠው። ሚኒስትሩም ቅድስ ጊዮርጊስን ይህን ድፍረት ማን አስተማረህ በሎ ጠየቀው። እርሱም እውነት ነው ብሎ መለሰለት። ከዚያም ማብራራት ጀመረ። በዚህ ጊዜ ንጉሡ በንግግሩ ውስጥ ጣልቃ ገብቶ ከአሁን ቀደም ምን ያኽል ደረጃ እንዳሳደገው ያስታውሰው ጀመር። አሁንም ክርስቶሱን ከካደ የበለጠ እንደሚ ጨምርለት ቃል ገባለት። ሰማዕቱ ግን የዚህን ዓለም ኀላፊና ጠፊ የሆነውን ተስፋ ግምት ውስጥ ከማስገባት እምቢ አለ። ንጉሡ በጣም ቢያሰቃየውም ጌታችን ግን ያበረታውና ቍስሉን ይፈውሰው ነበር። ሁናቴው ግራ ባጋባው ጊዜ ንጉሡ አትናቴዎስ የተባለ አንድ ጠንቋይ አስመጣና አንድ ኩባያ ውሃ ሞልቶ በማምጣት አስማቱን ከደገመበት በኋላ እንዲጠጣ ሰጠው። ሰማዕቱም መስቀለኛ ከባረከው በኋላ ጠጣው። ያን ጠጥቶ ምንም ጉዳት ሳይደርስበት ባየው ጊዜ ጠንቋዩ ራሱ በጌታችን ኢየሱስ አምኖ የሰማዕትነትን አክሊል ተቀዳጀ። ንጉሡ በጣም ተበሳጭቶ ሰማዕቱን እስኪሞት ድረስ እንዲጨ ፈልቁት አዘዘ ሥጋውንም ከከተማ ዉጪ ጣሉት። ጌታችን ኢየሱስ ግን ከሞት

አስነሥቶት ወደ ከተማ ተመለሰ። ብዙዎችም አዩትና በቅጽበት ሦስት ሺህ ሰባት መቶ ሰዎች በእርሱ ምክንያት አመኑ። ዲዮቅልጥያኖስ የሁላቸውም ራስ እንዲቈረጥ አዝዞ ሁሉም የሰማዕትነትን አክሊል ተቀዳጅተዋል።

እንደ አጋጣሚ ወደ ዲዮቅልጥያኖስ ዘንድ መጥተው የነበሩ ነገሥታት ቅዱስ ጊዮርጊስን እነዚህን ወንበሮች ቅጠል አውጥተው ፍሬ እንዲያፈሩ አድርገ አሉት። እርሱም ወደ ጌታ ጸልዮ ጸሎት ተቀባይነትን አግኝቶአል። ከዚያም ወደ መቃብር ቦታ መስደውት ሙታንን እንዲያስነሣ ጠየቁት። እንደገናም ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጸልዮ ጌታችንም ሙታኑን ካስነሣለት በኋላ ከእነርሱ ጋር ተነጋግረው ተመልሰው ዐርፈዋል። አንዲት ድኻ ሴትም ደንቆሮ፥ ድዳና ዕውር የነበረውን ልጅዋን አምጥታለት ጌታችን ኢየሱስ ከጸለየ በኋላ በመስቀለኛ ባርኮት ልጁ ከአለበተ ደዌ ሁሉ ተፈውሶአል። ይህ ሁሉ ሲሆን ዲዮቅልጥያኖሰ ሰማዕቱን እያሰቃየው ነበር። ይህ ማሰቃየቱ ግን በቅዱስ ጊዮርጊስ አስተሳሰበ ላይ ምንም ለውጥ ያላመጣ መሆኑን ባየ ጊዜ ለጣዖት ያጠንህ እንደሆነ ልጄን እድርልሃለሁ በማለት ያባብለው ጀመር። ቅዱስ ጊዮርጊስም በንጉሡ ሐሳብ የተስማማ በማስመሰል አታለለው። ዲዮቅልጥያኖስም ደስ ተሰኝቶ ሰማዕቱን ወደቤተ መንግሥቱ አስገባው። እዚያም ሲጸልይና መዝሙራትን ሲደግም ንግሥቲቱ ሰምታ ያንን እንዲያብራራላት ጠየቀችው። እርሱም ከፍጥረተ ዓለም ጀምሮ እስከ ልደተ ክርስቶስ ድረስ የነበረውን ሁናቴ ሁሉ ገለጸ አደረገላት። ቃሉም በልብዋ ገብቶ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አመነች።

ንጉሡም ሰማዕቱ ጊዮርጊስ ለንጉሡ አማልክት ሲያጥን እንዲያይ የከተማው ሕዝብ እዲጠራ ትእዛዝ አስተላልፎ ነበር። ብዙ ሰዎች ወደ ጣዖቱ በተሰበሰቡ ጉዜ ሰማዕቱ ጊዮርጊስ በዓለም መድኀኒት በጌታ ኢየሱስ ስም በጣዖታቱ ላይ ጮኸ። መሬት ተከፍታ ጣዖታቱን ሁሉ ዋጠቻቸው። ንጉሡና ከእርሱ ጋር የነበሩት ሁሉ ደነገጡ። ንጉሡም እያዘነ ወደ ቤተ መንግሥቱ ተመለሰ። ንግሥቲቱም ንጉሡን አምላካቸው ኀያል ስለሆነ ከእነዚህ ከገሊላውያን ጋር እልኽ አትጋባ ብዬህ አልነበረምን አለችው። በዚህ ጊዜ ሰማዕቱ ጊዮርጊስ ንግሥቲቱን ወደ ክርስትና እንደመለሳት ንጉሡ ዐወቀ። ከቍጣውም የተነሣ ሰውነትዋ እንዲቦጫጨቅና ራስዋ እንዲቈረጥ አዝዞ የሰማዕትነትን አክሊል ተቀዳጀች።

በመጨረሻም ዲዮቅልጥያኖስ የሚደርስበትን ውርደት ሁሉ ለማቆምና እንዳይቀጥል ለማድረግ የቅዱስ ጊዮርጊስ ራስ እንዲቈረጥ ውሳኔ አስተላለፈ። በዚህም ቅዱስ ጊዮርጊስ የሰማዕትነትን አክሊል ተቀዳጀ። ከክርስቲያኖች



አንዱ የሰማዕቱን አስከሬን ክብር ባለው ከፈን ከፍኖ ወደ አገሩ ወሰደው። በስሙም ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ታነጸ (የሚያዝያ 23 ቀን ስንክሳር)።

ሌላው የቅዱስ ጊዮርጊስ ታሪክ ምንጭ ደግሞ እንደሚከተለው ነው።

ቅዱስ ጊዮርጊስ ልዳ በምትባል አገር ተወለደ፥ አባቱ ዘሮንቶስ ይባላል። እናቱም ቴዎብስታ ትባላለች። እነርሱም እጅግ ባለጠጎች ነበሩ። እግዚአብሔርን የሚያፈቅሩ፥ ለድኾች የሚራሩ ጥዋትና ማታ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት የሚያዘወትሩ ጠንካሮች ክርስቲያኖች ነበሩ። የቅዱስ ጊዮርጊስ አባት ዘሮንቶስ በፍልስጥዔም ውስጥ የአንድ ክፍል አስተዳዳሪ ነበር።

ቅዱስ ጊዮርጊስ የዐሥር ዓመት ልጅ አባቱ ሞተ። በአባቱም ቦታ ሌላ ሹም ተተካ። አባቱን ቦታ የተረከበውም ሹም ጊዮናርጊስን ከእናቱ ለምኖ ከእርሱ ጋር እንዲኖር ወሰደው። ከእርሱም ጋር ዐሥር ዓመት ተቀመጠ። በዚህም ጊዜ ቅዱሳት መጻሕፍትን፥ ፈረስ ግልቢያን፥ ቀስት መሳብን፥ አራዊት ማዳንንና ሌላውንም ጥበብ ሁሉ ተማረ። በሥራው ሁሉ እጅግ ጠንካራና ኀይለኛ ሆነ በስልፍም ውስጥ የበላይነትን አገኘ። ከጀግኖችም ውስጥ የሚመስለው ማንም አልነበረም። የእግዚአብሔር ጸጋ ያደረበት ነበርና። የሚያየው ሁሉ ከኀይሉና ከጉብዝናው የተነሣ እስኪደነቅ ድረስ በየቀኑ በሞገስ ላይ ሞገስ፥ በኀይል ላይ ኀይል ይጨመርለት ነበር። ወደ ስልፍም በሄደ ጊዜ ሊጋጠሙት የመጡ ሁሉ ገና ሲያዩት ይፈሩት ነበር። በመንገዱ ሁሉ እግዚአብሔር ይረዳው ነበርና።

ቅዱስ ጊዮርጊስ ሃያ ዓመት በሆነው ጊዜ ከእናቱ ለምኖ የወሰደው መኰንን ልጁን ሊድርለት አሰበ። መኰንኑ ይህን ማሰቡ ቅዱስ ጊዮርጊስ ንጹሕ ድንግል ስማያዊ ሙሽራ እንዲሆንክርስቶስ እንደመረጠው ባለማወቁ ነበር። መኰንኑም በዚህ አሳብ ላይ እንዳለ ዐረፈ።

ከዚህ በኋላ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤሩት ወደምትባል ሀገር ሄደ የቤሩት ሰዎችም ፈጣሪያቸው እግዚአብሔርን የማያውቁ አረማውያን ነበሩ። ደራጎን የሚባል ዘንዶንም ያመልኩ ነበር: ደራጎኑ እንደ ንስር ክንፎች አሉት፥ እንደ ውሻም ጆሮች አሉት፤ እንደ ፍየልም ጢም አለው፤ እንደ አንበሳ እግርና ጥፍር አለው፤ ዥራትም አለው። እንደ አዞ ጥርሶች አሉት። አንገቱም እንደ ስጐን አንገት ነው።

ደራጎን የባሕር ዓሣዎችንም ሆነ የሚባሩ ወፎችን እንደዚሁም የምድር አራዊትንና እንስሶችን ባየ ጊዜ ይተነፍስባቸዋል፤ ትንፋሹም ሲደርስባቸው



www.ethiopianorthodox.org

ይሞታሉ። ወዲያውም ይባላቸዋል። ሰውንም ለብቻው ሲያገኝ እንደዚሁ ያደርጋል።

የቤሩት ሰዎች ግን ሴቶች ልጆቻቸውን በየተራ ይሰጡት ነበር። በዚህም ሁኔታ ብዙ ጊዜ ከኖሩ በኋላ አንድ ቀን ተሰብስበው ወደ አገረ ገዥው በመሄድ ሴቶች ልጆቻችን ሁሉ ስላላቁ ደራጎን እኛን ወደማያገኝበት አገር እንሄዳለን አሉት። አገረ ገዥውም ብቻዬን ትተውኛላችሁን? አገሬንስ ምድረ ባዳ ልታደርጓት ነውን? እንደዚህ አታድርጉ አላቸው። ሰዎችም መልሰው:- እንግዲህ ለአምላካችን ለደራጎን ምን እንሰጠዋለን? ሴቶች ልጆቻችን አልቀዋልና። ሚስቶቻችንንም እንዳንሰጠው ያለ እነርሱ መኖር አንችልም አሉት።

መኰንኑም:- አትፍሩ፥ ወደ ሌላ አገርም አትሂዱ፥ እኔም በተራዬ ሴት ልጄን ለደራጎን እሰጣለሁ አላቸው። እነርሱም መልካም ነው አሉት። ጊዜውም በደረሰ ጊዜ የመኰንኑን ልጅ ወስደው ለደራጎን ሰጡአት። ነገር ግን እነርሱ ልጅቱን ይዘው በሄዱ ጊዜ ደራጎን በቦታው አልነበረም። የሚበላውን አውሬ ለመፈለግ ወደ ጫካ ሄዶ ነበርና። ስለዚህም የመኰንኑን ሴት ልጅ በተለመደው ቦታ አስቀምጠዋት ወደ ቤታቸው ተመለሱ።

ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤሩት በደረሰ ጊዜ እየተዘዋወረ አካባቢዋን ሲጐበኝ የመኰንኑን ልጅ ለብቻዋ ተቀምጣ አገኛትና ከዚህ ምን ትጠብቂያለሽ? አላት። ልጅቱም:- አምላካችን ደራጎን እንዲበላኝ ሰዎች ለእርሱ ሰጥተውኝ ነው ስትል መለሰችለት። ቅዱስ ጉዮርጊስም የአምላክሽ የደራጎን ግብሩ ምንድን ነው? አላት። ልጅቱም የሆነውን ሁሉ ነገረችው። ቅዱስ ጊዮርጊስም አሁን ደራጎን ወዴት አለ? ብሎ ጠየቃት። እርስዋም ለምግቡ አራዊትን ሊፈልግ ወደ ጫካ ሄዶአል፤ እኔንም ለመብላት አሁን ይመለሳል፤ አንተንም እንዳይበላህ ከዚህ ሂድ አለችው።

ቅዱስ ጊዮርጊስም ይህን የሰይጣን ማደሪያ ደራጎንን እኔ አልፈራውም አላት። ልጅቱም አንተ ገና ጢም ያላበቀልህ ጐልማሳ ነህ፤ ከቤሩት ሰዎች ሁሉ አንተ ትበልጣለህን? እነርሱ እንኳ ሴቶች ልጆቻቸውን ከደራጎን ሊያድኑ አልቻሉም አለችው።

ቅዱስ ጊዮርጊስም ከሁሉ የሚበረታ ሰማይንና ምድርን የፈጠረ አምላኬ አለ። እርሱ ከዚያ ከተረገመ አውሬ ያድነኛል አላት። ከልጅቱም ጋር ይህን ሲነጋገር ደራጎን መጣ። ቅዱስ ጊዮርጊስንም ባየው ጊዜ ምላሱን አውለበለበ፤ አንገቱንም አስገገ። ትንፋሹን ሊተነፍስበትና በራሱ ላይ ሊከመርበት ተቍነጠነጠ። መንፈስ ቅዱስ ያደረበትና በእግዚአብሔር ፈቃድ ወደ ቤሩት የመጣው ቅዱስ ጊዮርጊስ ግን ከደራጎን ቁጣ የተነሣ ምንም አልፈራም። በሥላሴ ስም በመስቀል ምልክት በላዩ ላይ አማተበበት። ወዲያውም የደራጎን ኃይሉ ደከመ፥ መርዙም ጠፋ።

ከዚህ በኋላ ቅዱስ ጊዮርጊስ ከነጭ ፈረሱ ላይ ወረደና መታጠቂያውን ከወገቡ ፈትቶ ደራጎንን አንገቱን አስረውና እንድትጐትተው ለልጅቱ ሰጣት። ቅዱስ ጊዮርጊስ በፈረሱ ላይ ሆኖ ልጅቱም ደራጎንን እየጐተተች ወደቤሩት ከተማ ገቡ።

የከተማው ሰዎችም ደራጎንን ባዩት ጊዜ ፈሩ እጅግም ደንግጠው:- ወደ ግንብ ላይ የወጡ አሉ። በሰገነትም ላይም የወጡ አሉ። ቅዱስ ጊዮርጊስንም እንዲህ አሉት፤ ደራጎንን ያመጣህብን ምን አደረግንህ? አምላካችን ስለሆነ ሴቶች ልጆቻችንን ጨርሶአል።

ቅዱስ ጊዮርጊስም ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር አምላክ የለም። አሁንም በእርሱ እመኑ። ራሱን

ማዳን የማይችል ይህን ሰይጣናዊ ደራጎን ተውት አላቸው።

እነርሱም በአምላክህ እናምን ዘንድ ደራጎንን መግደል ትችላለህን? አሉት። እርሱም አዎ በጌታዬ በኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል ልገድለው እችላለሁ አላቸው። የህንም ብሎ ከከተማው ወደ ውጭ አንድ ምዕራፍ ያህል ወጣ። ሕዝቡም ቅዱስ ጊዮርጊስ የሚያደርገውን ያዩ ዘንድ ተከተሉት። ቅዱስ ጊዮርጊስም ከፈረሱ ወረደና ከደራጎን አንገት ላይ መታጠቂያውን ፈትቶ ወገቡን ታጠቀ። በፈረሱም ላይ ተቀመጠና ደራጎንን አንገቱን በጦር ወጋው። ወዲያውም ሞተ። ሕዝብም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአገልጋዩ በቅዱስ ጊዮርጊስ እጅ ያደረገውን ተአምር ባዩ ጊዜ አመኑ። ቤሩታዊትንም ከደራጎን አፍ ስላዳናት እግዚአብሔርን አመሰገኑ።

ቅዱስ ጊዮርጊስም አንድ ከሆነ አምላክ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አስጠመቃቸውና ወደ ሀገሩ ተመለሰ። ከዚያም በኋላ የቤሩት ሰዎች ሁለት አብያተ ክርስቲያናት አንዱን በቤሩት መካል ሁለተኛውን ደራጎን በተገደለበት ቦታ ሠርተው እግዚአብሔርን እያመለኩ ኖሩ።

ገድለ ጊዮርጊስን ይመለከቷል



www.ethiopianorthodox.org



ቅዱስ ጊዮርጊስ

## የቤተ ክርስቲያን ዜማ

እንደሚታወቀው በቅዳሴው ጸሎት ውስጥ ካሉት የምስጋናና የጸሎት ዜማዎች መካከል የካህኑ፥ የዲያቆኑ እንዲሁም የሕዝቡ ድርሻዎች አሉ። ካህናቱና ዲያቆናቱ ተራቸውን ጠብቀው የየራሳቸውን ድርሻ የሚያዜሙ ቢሆኑም በሕዝቡ በኩል ግን ድርሻቸውን ጠብቀው የሚያዜሙት ሰዎች ጥቂቶች ናቸው። ጸሎትና ምስጋናውም የሁሉም የጋራ እንጂ የተወሰኑ ሰዎች ድርሻ ብቻ ስላልሆነ ሁሉም አጥንቶት ተሰጥዎውን እንዲቀበል በማሰብ የሕዝቡ ድርሻ በዚህ በተከታታይ ክፍሎች ዝግጅት ውስጥ ተከፋፍሎ ቀርቦአል።

## የቅዳሴ ተሰጥዎ

### በግዕዝ

ይ:ካ:- ሰላም ለኵልክሙ፤

ይ:ሕ:- ምሰለ መንፈስከ፤



ይ:ሕ:- ቅዱስ ሐዋርያ ጳውሎስ ሠናየ መልእክት ፈዋሲ ዱያን ዘነሣእከ አክሊለ፤ ሰአል ወጸሊ በእንቲአነ ያድኅን ነፍሳቲነ በብዝኀ ሣህሉ ወምሕረቱ በእንተ ስሙ ቅዱስ።

ይ:ዲ:- ተንሥኡ ለጸሎት

ይ:ሕ:- እግዚኦ ተሣሃለነ

ይ:ካ :- ሰላም ለኵልክሙ

ይ:ሕ:- ምስለ መንፈስከ

ይ:ሕ:- ቅዱስ ሥሉስ ዘኅቡር ህላዌከ ዕቀብ ማኅበረነ፤ በእንተ ቅዱሳን ኀሩያን አርዳኢከ ናዝዘነ በሣህልከ በእንተ ቅዱስ ስምከ።

ይ:ዲ:- ተንሥኡ ለጸሎት፡

ይ:ሕ:- እግዚኦ ተሣለነ

ይ:ካ፥ ሰላም ለኵልክሙ፡

ይ:ሕ፥ምስለ መንፈስከ፡

ይ:ሕ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ አንተ አምላክ፥ አብ አኀዜ ኵሉ፤ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ አንተ ወልድ ዋሕድ ዘአንተ ቃለ አብ ሕያው፤ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ አንተ መንፈስ ቅዱስ ዘተአምር ኵሎ

### በአማርኛ

ይ:ሕ:- ለጸሎት ተነሡ።

ይ:ሕ:- አቤቱ ይቅር በለን።

ይ:ሕ:- አክሊልን የተቀበልህ ዱያንን የፈወስክ፥ መልካም አገልግሎት ያለህ ቅዱስ ሐዋርያ ጳውሎስ ሆይ፥ ስለኛ ማልድ፤ በይቅርታውና በቸርነቱ ብዛት ስለ ቅዱስ ስሙ ብሎ ሰውነታችንን ያድን ዘንድ።

ይ:ሕ:- ለጸሎት ተነሡ።



www.ethiopianorthodox.org

ይ:ሕ:- አቤቱ ይቅር በለን።

ይ:ካ:- ሰላችም ይሁን።

ይ:ሕ:- ከመንፈስህ ጋራ

ይ:ሕ:- በባሕርይህ አንድ የምትሆን ሥሉስ ቅዱስ ሆይ፥ አንድነታችንን ጠብቅ፤ ስለ ተመረጡ ክቡራን ስለሚሆን ደቀ መዛሙርትህ በይቅርታህ አድናን፤ ክብር ስለሚሆን ስለ ስምህ ብለህ።

ይ:ሕ:- ለጸሎት ተነሡ።

ይ:ሕ:- አቤቱ ይቅር በለን።

ይ:ሕ:- ሰላም ለሁላችሁ ይሁን

ይ:ሕ:- ከመንፈስ ጋራ።

ይ:ሕ:- ቅዱስ፤ ቅዱስ፤ ቅዱስ አንተ አምላክ አብ ሁሉን የፈጠርህ ነህ። ቅዱስ፡ ቅዱስ፡ ቅዱስ አንተ ወልድ ወሕድ የሕያው አብ ቃል ነህ። መንፈስ ቅድስ ሁሉን የምታውቅ ነህ። ቅዱስ፤ ቅዱስ፤ ቅዱስ አንተ መንፈስ ቅዱስ ሁሉን የምታውቅ ነህ።

## ከዚህ ምዕራፍ የምናገኘው ትምህርት

ሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት የተባሉበት ምክንያት በዐይን በሚታይ አገልግሎት አማካይነት በዐይን የማይታይና በእጅ የማዳሰስ ጸጋ የሚገኝበት በመሆኑ ነው።

ለምሳሌ የጥምቀት ሥርዓት የሚከናወነው በካህናት አማካይነት በዐይን በሚታይና በእጅ በሚዳሰስ ውሃ፡ እንዲሁም በጆሮ በሚሰማ ጸሎት ሲሆን እንዴት ከጥንተ አብሶ እንደምንነጻ፥ እንዴት ኃጢአታችን ይቅር እንደ ሚባልልን፥ እንዴት የመንፈስ ልደት እንደምንወለድና እንዴት የእግዚ አብሔር ልጆች እንደምንሆን በዐይናችን የማናየው፥ በጆሮአችን የማንሰማውና በእጃችን የማንዳስሰው የእግዚአብሔር ምሥጢራዊ ስጦታ ነው።

የቀሩትም የስድስቱ ምሥጢራት ሁናቴ ይህንኑ የመሰለ ነው።



ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ለማስተማር በላካቸው ጊዜ የተአምራትን ሥልጣን የሰጣቸው መሆኑ፡ ስለስሜ ወደ ነገሥታትና ወደ ገዢዎች ሲወስዱአችሁ ስለ እኔ ለመመስከር መልካም አጋጣሚ ይሆንላችኋል ያለው አባባል በሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ አሠራር ላይ ተፈጽሞአል። በንጉሡ ፊት በድፍረት መናገሩና አስደናቂ ተአምራትን ማድረጉ ይህንኑ የጌታችንን አባባል የሚያመለክት ነው።

በሦስቱ ቅዱሳን ታሪክ ውስጥ ተፈጽመው ያገኘናቸው ሁናቴዎች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰጠው ተስፋ ጋር ተመሳሳይ ናቸው፡-

«በእኔ የሚያምኑ ሁሉ እነዚህን ተአምራት የማድረግ ሥልጣን ይኖራ ቸዋል፤ በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፤ እባቦችን ቢይዙ፥ ወይም የሚገድል መርዝ እንኳ ቢጠጡ አይጐዳቸውም፤ እጃቸውን በበሽተኞች ላይ ሲጭኑ በሽተኞቹ ይድናሉ» (ማር:ም:16ቍ:17:18) ።

በታሪኮቹ እንደተመለከትነው ሐዋርያቱና ሰማዕታቱ ከማያምኑ ባለሥ ልጣኖች ጋር በአነጋገር እየተጋፈጡ መንፈሳዊ ተግባራቸውን በሚያከናው ኑበት ጊዜ ለሕይወታቸው ምንም የማይሳሱ መሆናቸው ይታያል። በዚህም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጣቸውን መመሪያ ተግባራዊ ማድረጋቸው መሆኑን እንገነዘባለን።

«ሊከተለኝ የሚወድድ ቢኖር ራሱን ይካድ፤ በየቀኑም መስቀሉን ተሸክሞ ይከተለኝ፤ ከእኔ ይልቅ ለሕይወቱ የሚሳሳ ሁሉ ያጠፋታል፤ ስለእኔ ሕይወቱን አሳልፎ የሚሰጥ ግን ያድናታል» (ሉቃ:ም:9ቍ:23–24)።

ጌታችንም:- «እነሆ፥ እኔ እስከ ዓለም መጨረሻ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ» ብሎ ቃል በገባላቸው መሠረት አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው ጊዜ ሁሉ ታላላቅ ተአምራትን አድርጎላቸዋል።

ሌላው በጣም ሚያስገርመው ነገር እነዚያ የማያምኑ ወገኖች ምንም ያኽል ታላላቅ ተአምራትን ቢያዩ ከስሕተት መንገዳቸው አለመመለሳቸውና በክርስቲ ያኖች ላይ ያላቸውን ጥላቻ አለማርገባቸው ነው። ይህ የሚሆን ሰዎች በእግዚአብሔር መተማመናቸውን ትተው በሰይጣን ማመንን በሚጀምሩበት ጊዜ ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለዚህ ጉዳይ ምን እንደሚል እንመልከት:-



www.ethiopianorthodox.org

«የዐመፅ ሰው የሚመጣው በሰይጣን ኀይል አሳሳች ተአምራትንና ምልክቶችን አስደናቂ ነገሮችንም በማድረግ ነው፤ እንዲሁም በሚጠፉት ሰዎች ላይ ልዩ ልዩ ክፉ ማታለል በማድረግ ነው፤ እነዚህ ሰዎች የሚጠፉትም ለመዳን የሚያበቃቸውን እውነት ስላልወደዱ ነው፤ በዚህም ምክንያት በሐሰት እንዲያምኑ እግዚአብሔር የስሕተትን ኀይል ይልክባቸዋል። ይህም የሚሆነው እውነትን አናምንም ብለው በኃጢአት የሚደሰቱ ሁሉ እንዲፈረድባቸው ነው» (2ኛ:ተሰ:ም:2ቍ:9–12)።

ይህ ጥቅስ የፈርዖንን ሁናቴ ያስታውሰናል። ሙሴና አሮን አንድ ተአምር ባደረጉ ቍጥር ሰይጣንም በአስማተኞች አማካይነት ተመሳሳይ ተአምር እያደረገ እስከ ተወሰነ እርምጃ አብሮአቸው ስለተጓዘ ፈርዖን በእነርሱ ምክንያት ልቡን አደነደነ። የእግዚአብሔርን ክብር ንቆ ሰይጣንን የሚከተል ሁሉ ሰይጣን ያን በእርሱ ያመነውን ሰው እውነትን እንዳያስተውል ያደር ገዋል። ለሰው ደግሞ ነጻ ፈቃድ የተሰጠው ስለሆነ ሰይጣንን ለማምለክ የሚፈልገውን ሰው እግዚአብሔር አይከለክለውም። በአንድ በኩል እውነትና ጽድቅ ከሚገኝበት ከእግዚአብሔር በመራቃቸው፥ በሌላ በኩል ደግሞ እውነ ትንና ጽድቅን ከሚጠላው ከሰይጣን ጋር በማበራቸው እነ ፈርዖንና እነ ዲዮቅልጥያኖስ እንዲሁም መሰሎቻቸው እነዚያን የሚያደርጓቸውን ክፉ ድርጊቶች የሚያደርጉትና አስደናቂዎች የሆኑት የእግዚአብሔር ተአምራትም ሊያሳምኑአቸው አለመቻላቸው የሚያስገርም አይደለም። ይህም የሚሆነው መላ ሕይወታቸውን ለሰይጣን ስላስረከቡና የእግዚአብሔርን እርዳታ ጠቃ ሚነት ሊገነዘቡ ባለመቻላቸው ነው።

ሰይጣንም ሐሰተኛና የሐሰት አባት መሆኑን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተናግሮአል (ዮሐ:ም:8ቍ:44)።ይህም በመሆኑ ለእርሱ ለሚገዙለት ሰዎች ሁሉ የሐሰትንና የጥፋትን መንገድ ብቻ ስለሚያስተምራቸውና እነርሱም አምነው ስለሚቀበሉት እነዲዮቅልጥያኖስ የሆኑትን ሆነዋል።

## ጥያቄዎች

1. የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት ስንት ናቸው? እነርሱስ ምን ምን ናቸው?
2. ጥምቀት ማለት ምን ማለት ነው?
3. በጥምቀት የምናገኛቸው ጸጋዎች ምን ምን ናቸው?
4. በምሥጢረ ሜሮን አማካይነት ምንን እናገኛለን?



5. መንፈሳዊ ዕድገት የምናገኘው በምንድነው?
6. የምሥጢረ ሜሮን ሥርዓት ቀደም ሲል በምን ዐይነት ይፈጸም ነበር?
7. ለምን ወደ ሜሮን መቀባት ተለወጠ?
8. የምሥጢረ ቍርባን ሥርዓት እንዴት ይፈጸማል?
9. የምሥጢረ ቍርባን ጥቅም ምንና ምን ነው?
10. ምሥጢረ ክህነት የሚባለው ምን ነው?
11. ጌታ ምሥጢረ ክህነትን የመሠረተው መቼ ነው?
12. ምሥጢረ ንስሐስ ምን ማለት ነው?
13. ጌታችን ምሥጢረ ንስሓን የመሠረተው ምን ብሎ ነው?
14. ንስሓ ማለትስ ምን ማለት ነው?
15. ምሥጢረ ተክሊል ማለት ምን ማለት ነው?
16. ጋብቻን የመሠረተው ማነው? እንዴት አድርጎ?
17. ምሥጢረ ቀንዲል ማለት ምን ማለት ነው?
18. ምሥጢረ ቀንዲል ከሌሎቹ ምሥጢራት በምን ይለያል?
19. ሐዋርያው ቅዱስ ቶማስ በመጀመሪያ የሄደው ወዴት ነው?
20. እዚያስ በምን ዘዴ ሥራውን ጀመረ?
21. ማን በሚባል ሰው ቤት ሥራውን ጀመረ?
22. ቀጥሎስ የሠራው የት ነው?
23. ንጉሡ ሲጠይቀው ምን ሙያ አለኝ አለው?
24. ንጉሡ ምንድነው የሠራኸው ብሎ ቢጠይቀው ምን መልስ ሰጠው?
25. ከዚያ በኋላ ንጉሡ ሐዋርያውን ምን አደረገው?
26. የሉቅዮስ ሚስት ድርጊቱን ስታይ ምን ሆነች?
27. ሉቅዮስ ሐዋርያውን ምን እንዲያደርግለት ጠየቀው?
28. ሐዋርያው ለሉቅዮስ ምን አደረገለት?
29. ከዚያ በኋላ ሉቅዮስ ምን አደረገ?
30. ሐዋርያው ንጉሡን ምን ጠይቆት ፈቀደለት?



www.ethiopianorthodox.org

31. ሐዋርያው ዛፉን ከባሕር ውስጥ እንዴት አወጣው? አውጥቶስ ምን አደረገበት?

32. ለምእመናኑ ኤጲስ ቆጶስና ካህናት ከሾመላቸው በኋላ ምን ወደም ትባል ከተማ ሄደ?

33. ወደዚያች ከተማ ሲገባ ምን የሆነ ሰው አጋጠመው?

34. ሐዋርያው ለሰውዬው ምን አደረገለት?

35. ያን ድርጊት በማድረጉ ያልተደሰቱት እነማን ነበሩ?

36. ምን ሊያደርጉት ዐቀዱ?

37. በዚህ ጊዜ ምን ተአምር ተደረገ?

38. ከዚያስ በኋላ ምን ሆነ?

39. የበርኪናስ ንጉሥ ሐዋርያውን ባሰረው ጊዜ ሐዋርያው ምን አደረገ?

40. ከዚያስ በኋላ ንጉሡ ምን አደረገ?

41. በመጨረሻስ ምን አደረገው?

42. ሐዋርያው ማትያስ ለሐዋርያነት የተመረጠው እንዴት ነው?

43. ለማስተማር የሄደበት እንዴት ያለ አገር ነበር?

44. የዚያ አገር ሰዎች እንግዳ ሰው ሲመጣ ምን የማድረግ ልማድ ነበራቸው?

45. ሐዋርያው ማትያስ ምን ማስተማር ጀመረ?

46. ከዚያስ ያገሬው ሰዎች ምን አደረጉት?

47. ጌታችን ማንን ላከለት?

48. ሊረዱት የመጡት ምን ደረሰባቸው?

49. የጸሎታቸው ውጤት ምን ነበረ?

50. ከዚያስ ሕዝቡ ምን አደረገ?

51. የሕዝቡስ ሁናቴ እንዴት ተለወጠ?

52. የነበረባቸውስ የአውሬ ጠባይ እንዴት ተወገደላቸው?

53. ሐዋርያው ማትያስ በደማስቆ ምን ደረሰበት?

54. ምን ተአምር ተደረገ?

55. ሕዝቡ ከተአምሩ በኋላ ምን አደረገ?

56. የሐዋርያው ማትያስ አሟሟት እንዴት ነበር?

57. የሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስ አባትና እናት ማንና ማን ይባሉ ነበር?

58. የሰማዕቱ ዕድሜ ስንት በነበረ ጊዜ ነው አባቱ የሞተበት?

59. ሰማዕቱ የአባቱን ሥራ ወርሶ በዚያ ለመቀጠል ፈቃደኛ ያልሆነው ለምንድነው?

60. ቅዱስ ጊዮርጊስ ለንጉሡ ምን ብሎ ገለጠለት?

61. ቅዱስ ጊዮርጊስን ወደ ንጉሡ የወሰዱት በምን ምክንያት ነው።

62. ቅዱስ ጊዮርጊስ በመኳንንቶቹ ምን ብሎ ነው ከፍ ባለ ድምፅ የተናገረው?

63. ንጉሡ ቅዱስ ጊዮርጊስን ገዶ እንዲያሰቃየው የነገረው ማን ለሚባል ሰው ነው?

64. ሚኒስትሩ ቅዱስ ጊዮርጊስን ምን ብሎ ጠየቀው?

65. ቅዱስ ጊዮርጊስ ምን መልስ ሰጠ?

66. በዚህ ጊዜ በንግግር ውስጥ ባልታ ገብቶ ምን ዐይነት ተስፋ ሰጠው?

67. ንጉሡ ቢያስቃየውም ጌታ ምን ያደርግለት ነበር?

68. ንጉሡ ግራ በተጋባ ጊዜ ምን አደረገ?

69. ያስማቱ ውሃ ሰማዕቱን ባልጐዳው ጊዜ አስማተኛው ምን አደረገ?

70. ንጉሡ በጣም በተበሳጨ ጊዜ በሰማዕቱ ላይ ምን ምን እንዲዲ ደረግበት አዘዘ?

71. በቅጽበት ሦስት ሺህ ሰባት መቶ ሰዎች ያመኑት በምን ምክንያት ነው?

72. እነዚህ ያመኑት ሰዎች ምን ሆኑ?

73. በዲዮቅልጥያኖስ ዘንድ የነበሩ ነገሥታት ሰማዕቱን ምን ምን ተአምር እንዲያደርግላቸው ጠየቁት?


www.ethiopianorthodox.org

74. የዲዮቅልጥያኖስ ማሠቃየት በሰማዕቱ ስሜት ላይ ምንም ለውጥ አለማምጣቱን ባየ ጊዜ ምን ዐይነት ተስፋ ሰጠው?

75. ሰማዕቱ ንግሥቲቱን ያሳመናት እንዴት ነው?

76. ሰማዕቱ ምን ባደረገ ጊዜ ነው ጣዖታቱን መሬት ተከፍታ የዋጠቻቸው?

77. ንግሥቲቱ ምን ስላለችው ነው ዲዮቅልጥያኖስ እንድትገደል ያደረገው?

78. በመጨረሻም ንጉሡ እየደረሰበት የነበረውን ውርደት ሁሉ ለማቆም ምን አደረገ?

79. የቤተ ክርስቲያን ምሥጢራት ለምን ምሥጢራት ተባሉ?

80. እነዲዮቅልጥያኖስ ብዙ ተአምራትን እያዩ ልባቸው የደነደነበት ምክንያት ምንድነው?

# ምዕራፍ 5

## መንፈሳዊነትና ግብረገብነት

### ንስሓ መግባት

ንስሓ መግባት ማለት ስለፈጸሙት በደል ተጸጽቶ ዳግመኛ ያን በደል ላለመፈጸም በመወሰን ስላለፈው ኃጢአት የእግዚአብሔርን ይቅርታ ለማግኘት እንዲቻል ኃጢአትን ለካህን መናዘዝ ነው።

ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ንስሓና ስለ ኑዛዜ ብዙ ብለዋል። ከእነዚህም ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

«ኃጢአቱን የሚሰውር አይለማም የሚናዘዝባትና የሚተዋት ግን ምሕረትን ያገኛል» (ምሳ:ም:28ቍ:13)።

«የእስራኤል ቤት ሆይ፥ እንደ መንገዱ በየሰው ሁሉ ላይ እፈርድባችኋለሁ ይላል ጌታ እግዚአብሔር፤ ንስሓ ግቡ፤ ኃጢአትም ዕንቅፋት እንዳይሆንባችሁ ከኃጢአታችሁ ሁሉ ተመለሱ» (ሕዝ:ም:18ቍ:30)።



«ንስሓ ግቡ፤ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ» (የሐ:ሥ: መ:2 ቍ:38)።

«ሰዎች ባለማወቅ ያደረጉትን እግዚአብሔር ችላ ብሎ አልፎታል፤ አሁን ግን በየአገሩ ያሉ ሰዎች ንስሓ እንዲገቡ አዝዞአል» (የሐ:ሥ:ም:17ቍ:30)።

«አስቀድሜ በደማስቆ ያሉትን ሰዎች ቀጥሎም በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ክፍለ ሀገረ ያሉትን ንስሓ ገብተው ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ አስተማርኋቸው፤ ንስሓ መግባታቸውን የሚያመለክት ነገር እንዲያደርጉም ነገርኋቸው» (የሐ:ሥ:ም:26ቍ:20)።

«እንደ እግዚብሔር ፈቃድ የሚሆን ሐዘን ወደ ድኅነት የሚያመጣ በንስሓ የሚገኘውን ለውጥ ስለሚያስገኝ ጸጸት የለበትም» (2ኛ:ቆሮ:ም:7ቍ:10)።

«አንዳንድ ሰዎች እንደሚመስላቸው ጌታ ኢየሱስ የተናገረውን የተስፋ ቃል ለመፈጸም አይዘገይም፤ ነገር ግን ሰው ሁሉ ለንስሓ እንዲበቃ ማንም ሰው እንዳይጠፋ ፈልጎ ስለ እናንተ ይታገሣል» (2ኛ:ጴጥ:ም:3ቍ:9)።

በእርግጥ ንስሓ ሲባል ከልብ ተጸጽቶ ያለፈውን የኃጢአት ሥራ ዳግመኛ ላለመሥራት መወሰንና ያንንም በተግባር ማሳየት ነው። ሆኖም የንስሓ ማጠናቀቂያው ለካህን በመናዘዝና ስርየትን በማግኘት ነው። ካህናትም ይህን ሊያደርጉ የሚችሉት ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ በተሰጣቸው ሥልጣን ነው።

«እናንተ የሰዎችን ኃጢአት ይቅር ብትሉ ይቅር ይባልላቸዋል፤ እናንተ የሰዎችን ኃጢአት ይቅር ባትሉ ግን ቅር አይባልላቸውም» (ዮሐ: ም: 20ቍ:23)።

«እውነት እላችኋለሁ፤ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድር የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል» (ማቴ: ም:18ቍ:18)።

ስርየቱም የሚገኘው ንስሓ የሚገባው ሰው ከመንፈሳዊ ማለት ከንስሓ አባቱ የሚሰጠውን መመሪያ በመከተል ነው።



www.ethiopianorthodox.org

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ «የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአታችን ሁሉ ያነጻናል» ባለው መሠረት ድኅነት በክርስስቶስ ደም መሆኑን አንክድም (1ኛ:ዮሐ:ም:1ቍ7) ። ነገር ግን ያለ ንስሓ ድኅነት የለም።

«ንስሓ ባትገቡ ሁላችሁም እንዲሁ ትጠፋላችሁ» (ሉቃ:ም: 13ቍ:3)።

ማንም ኃጢአት የሌለበት ሰው ስለሌለ ለድኅነት ንስሓ የግድ አስፈላጊ ነው። ኃጢአት እስካለ ድረስ ስለኃጢአቱ መቀጣት አለ፤ የኃጢአት ዋጋው ሞት ነው። ከሞት ለመዳንም የግድ ንስሓ ያስፈልጋል። ንስሓም ለክርስቶስ ደም የተገባን ያደርገናል።

ቤተ ክርስቲያን የሰው መንፈሳዊ ሕይወት ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ኅብረት ማድረግ መሆኑን ታምናለች። እርዳታውን ከለሙኑት መንፈስ ቅዱስ ይረዳል፤ ሰው ግን ጥረት ማድረግ አለበት።

መንፈሳዊ ሕይወትም የእግዚአብሔር ጦር መሣሪያ የሚያስፈልገው ትግል መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጸዋል።

«ትግላችን ከአለቆች፥ ከባለሥልጣኖች፡ ከዚህ ከጨለማ ዘመን የዓለም ገገርዎች፥ ከሰማያዊ የክፉ መንፈስ ሠራዊት ጋር ነው እንጂ ከደምና ከሥጋ ጋር ስላልሆነ የዲያብሎስን ተንኰል ለመቋቋም የእግዚአብሔርን ሙሉ የጦር መከላከያ ልብስ ልበሱ» (ኤፌ:ም:6ቍ:11–12)።

ጸጋ ሁሉን ነገር አያደርግም፤ ያለበለዚያማ እግዚአብሔር:- «ወደ እኔ ተመለሱ... እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ» ባላለም ነበር (ዘካ:ም:1ቍ:3)።

የንስሓ መግባት አስፈላጊነትም በተለያዩ ሁኔታዎች የተገለጠ ሲሆን ከእነርሱም ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣው ኃጢአተኞችን ወደ ንስጣ ለመጥራት መሆኑን ገልጦአል። (ማቴ: ም: 9 ቍ:13፥ ማር: ም:2 ቍ: 17፥ ሉቃ:ም:5ቍ:32)።

በዚህም ጌታችን ለንስሓ ምን ያህል ግምት እንደሰጠው ልንረዳ እንችላለን።

ሐዋርያው ጳውሎስም በሮሜ መልእክቱ ም:2ቍ:4ላይ የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሓ እንደሚመራ ይገልጣል።



ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም እግዚአብሔር እኛ ንስሓ ገብተን እንድንድን በመፍቀድ ብዙ ጊዜ እንደሚታገሠን ይገልጣል (2ኛ:ጴጥ:ም:3ቍ:9)።

ጌታችን የተለያዩ ምሳሌዎችን ከተናገረ በኋላ ንስሓ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ ምክንያት በሰማይ በእግዚአብሔር መላእክት ዘንድ ደስታ እንደሚ ሆን ገልጦአል (ሉቃ:ም:15ቍ 7 እና 10)።

በእነዚህና በሌሎችም ሊቀርቡ በሚችሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች መሠረት እግዚአብሔር የንስሓ መግባትን አስፈላጊነት ያደረጋገጠ መሆኑን ለመገንዘብ እንችላለን።

## በእውነት መጽናት

እውነት ማለት ምን ማለት ነው? እውነት ማለት እርግጥ፡ ትክክል፡ ሐሰት የሌለበት፡ ሐሰት ያልሆነ ማለት ነው። እርሱም የውሸት ተቃራኒ ነው። እውነት ይጠቅማል፡ ውሸት ግን ይጐዳል። የእግዚአብሔር መንገዶች ሁሉ እውነቶች ናቸው። እግዚአብሔርም ሁልጊዜ እውነተኛ ነው። እኛም ሁላችን ሁልጊዜ እውነተኞች እንድንሆን ያዝዘናል። ሰው ያየውንና የሰማውን ምንም ሳይደ ጨምር፥ ወይም ምንም ሳይቀንስ ቢናገር እውነት ተናገረ ይባላል። እርሱም እውነተኛ ይባላል። ያየውንና የሰማውን እንዳላየና እንዳልሰማ፡ ያላየውንና ያልሰማውን እንዳየና እንደሰማ፡ የተደረገውን ነገር እንዳልተደረገ፡ ያልተደ ረገውን እንደተደረገ አድርጎ ማውራት ውሸት መናገር ነው። ውሸት ደግሞ የሰይጣን ተግባር በመሆኑ እግዚአብሔር ውሸትን አይፈቅድም።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ውሸታሞች ሰዎችን በወቀሰበት ንግግሩ እንዲህ ብሎአል:-

«እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ፤ የአባታችሁንም ምኞት ልታደ ርጉ ትወድዳላችሁ፤ እርሱ ከመጀመሪያ ጀምሮ ነፍስ ገዳይ ነበረ፤ እውነትም በእርሱ ዘንድ ስለሌለ በእውነት አልቆመም፡ ሐሰተኛ፡ የሐሰት አባት ስለሆነ፥ ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል» (ዮሐ:ም:8ቍ:44)።

ይህን፥ ጌታችን የተናገረውን ወቀሳ ለመረዳት ወደ ኦሪት ዘፍጥረት ም:3:መለስ ብለን መመልከት እንችላለን። በመጀመሪያ እግዚአብሔር አዳም ንና ሔዋንን ወደ ገነት ባስገባቸው ጊዜ በገነት ውስጥ ከምትገኘዋ መልካሙንና ክፉን ለይታ ከምታስታውቀዋ ዛፍ አትብሉ፤ ከእርስዋ በበላችሁ ቀን ሞትን ትሞታላችሁ ብሎ አስጠንቅቆአቸው ነበር። በእባብ ሀድሮ ወደ ሔዋን



www.ethiopianorthodox.org

የቀረበው ሰይጣን ግን ከፉንና ደግን ለይታችሁ ታውቃላችሁ እንጂ አትሞቱም ብሎ ዋሸና አሳሳታት (ዘፍ:ም:3ቍ:4–5)። የሞቱ ፍርድ ግን ለአዳምና ለሔዋን ብቻ ሳይሆን ለሰው ዘር ሁሉ የተላለፈ መሆኑ ግልጽ ነው (ሮሜ:ም 5ቍ:12)።

የእውነትን መንገድ በመከተላቸው እግዚአብሔር በዚህ ዓለም እንኳ ዋጋቸውን የከፈላቸው ሰዎች መኖራቸውን የሚያስረዱ ብዙ የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጃዎች አሉ። ከእነዚህም መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል።

ዮሴፍ በሁሉም ነገር የእውነትን መንገድ ይከተል ስለነበረ በመጀመሪያ በወንድሞቹ አማካይነት እንደ ባሪያ የመሸጥ ችግር ደርሶበታል፤ ቀጥሎም በጲጥፋራ ሚስት የሐሰት ክስ ተከስሶ የመታሰር ችግር ደርሶበታል። በመጨረሻ ግን እግዚአብሔር ዋጋውን ከፍሎት የግብጽ ገዢ ለመሆን አብቅቶታል (ዘፍ:ም:39፥40፥41)።

ሦስት የነቢዩ ዳንኤል ጓደኞች ሲድራቅ ሚሳቅና አብደናጎ (ሠለስቱ ደቂቅ) እውነት የሆነውን የአምልኮ ሥርዓት ስለተከተሉ ተከስሰው በሚነድድ እሳት ውስጥ ቢጣሉም የሚያመልኩት አምላክ ከእነርሱ ጋር ስለነበረ ምንም ሳይጎዱ ከእሳት ውስጥ ወጥተዋል፤ አምላካቸውንም አስከብረዋል (ዳን:ም: 3 ቍ: 26–30)።

ነቢዩ ዳንኤል የእግዚአብሔርን እውነተኛ መንገድ ስለተከተለ በሐሰተኛ አማልክት አምላኪዎች ተከስሶ ወደ አንበሳ ጉድጓድ ቢጣልም አምላኩ ከእርሱ ጋር ስለነበረ ምንም ሳይደርስበት ከመውጣቱም በላይ ጠላቶቹን ተበቅሎለታል (ዳን:ም:6)።

የእግዚአብሔርን እውነተኛ መንገድ ትከተል የነበረችው ሶስና በሐሰት በተከሰሰች ጊዜ እግዚአብሔር ጸሎትዋን ሰምቶ ከክሱ ነጻ ስትወጣ በሐሰት የከሰሱአት ዳኞች ግን ተገቢ ፍርዳቸውን ተቀብለዋል። (የሶስና ታሪክ)

እንዲሁም የእግዚአብሔርን እውነት በማጥፋት በመንፈስ ቅዱስና በቤተ ክርስቲያን ላይ የሐሰትና የማታለል ተግባር የፈጸሙ ሐናንያና ሰጲራ የተባሉት ባልና ሚስት በመዋሸታቸው የሞት ፍርድ ተፈርዶባቸው ፍርዱም ተግባራዊ ሆኗል (የሐ:ሥ:ም:5ቍ:1–11)።

ሌላው ልንገነዘበው የሚገባ ጉዳይ ደግሞ በእውነት ላይ መጽናት ሁልጊዜ ቁሳዊ ወይም ዓለማዊ ጥቅምን የሚያስገኝ አለመሆኑን ነው። የእውነትን መንገድ ብቻ በመከተል መሥዋዕትነትን የከፈሉ ሐዋርያት ሰማዕታትና



ሌሎችም ቅዱሳን ብዙዎች ናቸው። ቤተ ክርስቲያንም እየተጠናከረች የሄደችው በእነርሱ መሥዋዕትነት ነው። እነርሱ ግን ዋጋቸውን የሚጠብቁት በዚህ ዓለም ሳይሆን በወዲያኛው ዓለም ነው።

ስለዚህ የሚያስከትለውን ማንኛውንም ዓለማዊ መሰናክል ችለንና ታግሠን በእውነት ከጸናን አምላክ እርሱ በሚወስነው መንገድ ዋጋችንን እንደሚከፍለን እርግጠኞች እንሁን።

## አክብሮትና ትሕትና

በዚህ ትምህርት ውስጥ አክብሮት የተባለው ቃል የሚያመለክተው በአነጋገር ወይም ትሕትና በማሳየት ሌላውን ሰው ከራስ አስበልጦ ከፍ ማድረግን ነው።

ትሕትና ማለት ደግሞ በግል ፈቃድ ራስን ዝቅ ማድረግ ወይም ማዋረድ ነው።

ሰዎችን በማክበር ለራስም አክብሮትን ማግኘት የሚቻል በመሆኑ ሁልጊዜ ሰውን ማክበር ይገባል። ሰውን ማክበርና ትሑት መሆን እግዚአብሔር የሚፈቅዳቸው ተግባሮች በመሆናቸው ሰዎችን ብናከብርና ትሑቶች ብንሆን ከእግዚአብጠር ዘንድ ዋጋ እናገኝባቸዋለን። ሕይወታችንም ከስድነትና ከትዕቢተኛነት ይልቅ ትሑትነትንና ሰው አክባሪነትን ብናለማምደው በእግዚአብሔርም በሰውም ዘንድ ዋጋ እናገኝበታለን። በዚህም መሠረት በእግዚአብሔር ዘንድ ዘለዓለማዊ ሕይወት የሚጠብቀን ሲሆን በዚህ ዓለም ሕይወታችን በሰላም ለመኖር እንችላለን።

በኦሪት ዘልቍ ም:12ቍ:6–8 እግዚአብሔር አሮንንና ማርያምን በገሠጸበት ንግግሩ ስለሙሴ እንዲህ ብሏል:-

«በመካከላችሁ ነቢይ ቢኖር እኔ እግዚአብሔር በራእይ እገለጥለታለሁ፤ ወይም በሕልም እናገረዋልሁ። ባሪያዬ ሙሴ ግን እንዲህ አይደለም፤ እርሱ በቤቴ ሁሉ የታመነ ነው። እኔ አፍ ለአፍ በግልጥ እናገረዋለሁ፤ በምሳሌ አይደለም፤ የእግዚአብሔርንም መልክ ያያል።»

እንደዚህ አድርጎ እግዚአብሔር የመሰከረለት ታላቁ ነቢይ ሙሴ በዚሁ ምዕራፍ ቁጥር 3 ላይ:- «ሙሴም በምድር ላይ ካሉት ሰዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ ትሑት ሰው ነበረ» ተብሎ ተነግሮለታል። ይህም የሚያመለክተው የሙሴ



www.ethiopianorthodox.org

ለእግዚአብሔር ቅርብነት ከትሑትነት ጋር የተያያዘ መሆኑን ነው። በዚህም መሠረት ትሕትና ምን ያኽል ከእኛ የሚጠበቅ መሆኑንና በእግዚአብሔርም ዘንድ ታላቅ ዋጋ የሚያስጥ መሆኑን እንገነዘባለን።

ወደ ሐዲስ ኪዳን መለስ ያልን እንደሆነ ደግሞ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ከሞት ፍርድ ለመዋጀት ዝቅ ብሎ የፍጡሩን የሰውን ሥጋ በለበሰ ጊዜ በትሕትናው ለእኛ አርአያ ሆኖልናል። በዚህ ጉዳይ የሚከተሉትን የቅዱሳት መጻሕፍት ማስረጀዎች እንመልከት።

‹እኔ የዋህ፥ በልቤም ትሑት ስለሆንሁ ከእኔ ተማሩ።» (ማቴ:1፥29)

«ኢየሱስ ክርስቶስ ያሳየው የትሕትና ጠባይ በእናንተም ሕይወት ሊኖር ይገባል። እርሱ የመለኮት ባሕርይ አለው፤ ይሁን እንጂ፥ ከእግዚአብሔር ጋር እኩል የሚያደርገውን የመለኮት ባሕርይ እንደያዘ መቅረት አልፈለገም፤ የአገልጋይ መልክ በመውሰድ በሰው ምሳሌ ተገለጠ። እንደ ሰው ሆኖ በትሕና ራሱን ዝቅ አደረገ፤ እስከ ሞት ድረስ፥ ያውም በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እስከ መሞት ድረስ ታዛዥ ሆነ» (ፊል:ም:2ቍ:5–8)።

<u>ከዚህ ቀጥለን ስለ አክብሮትና ትሕትና ቅዱሳት መጻሕፍት ከአቀረቡአቸው ማስረጃዎች መካከል ጥቂቶቹን እንመልከት</u>:-

«ከክብር በፊት ትሕትና ነው» (ምሳ:ም:15ቍ:33)።

«ሀብት፥ ክብርና ሕይወት የትሕትናና እግዚአብሔርን የመፍራት ዋጋ ናቸው» (ምሳ:ም:22ቍ:4)።

«ራሱን ከፍ የሚያደርግ ዋረዳል፤ ራሱንም ዝቅ የሚያደርግ ከፍ ይላል» (ማቴ:ም:23ቍ:12)።

«እርስ በርሳችሁ ለመከባበር ተሽቀዳደሙ» (ሮሜ:ም12ቍ:10)።

«በትሕትና ተሞልታችሁ ሌሎች ሰዎች ከእናንተ እንደሚሻሉ አድርጋችሁ ቍጥሩ እንጂ ወገን በመለየትና በራስ ወዳድነት:- ወይም ያለ እኔ ማን አለ በሚል ትምክሕት ምንም ነገር አታድርጉ» (ፊል:ም:2ቍ:3)።

«እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፤ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል።» (ያዕ:ም:4ቍ:6)

«ሰውን ሁሉ አክብሩ።› (1ኛ:ጴጥ:ም:2ቍ:17)



«እንዲሁም እናንተ ጐልማሶች፥ ለሽማግሌዎች ታዘዙ፤ ሁላችሁም ትሕትናን እንደ ልብስ ለብሳችሁ አንዱ ሌላውን ያገልግል፤ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፤ ለትሑቶች ግን ጸጋን ይሰጣል። እንግዲህ እግዚአብሔር በወሰነው ጊዜ ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከእግዚአብሔር ብርቱ እጅ ሥር ራሳችሁን ዝቅ አድርጉ» (1ኛ:ጴጥ:ም5:ቍ:5–6)።

## ጥያቄዎች

1. ንስሓ መግባት ማለት ምን ማለት ነው?
2. የንስሓ ማጠናቀቂያው ምንድነው?
3. ካህናት ለማናዛዝና ለማስተስረይ የሚችሉት እንዴት ነው?
4. ስርየት የሚገኘው እንዴት ነው?
5. ንስሓ የግድ አስፈላጊ የሆነው በምን ምክንያት ነው?
6. መንፈስ ቅዱስ እንዲረዳ ሰው ምን ማድረግ አለበት?
7. መንፈሳዊ ሕይወት ምን ያስፈልገዋል?
8. ወደ እኔ ተመለሱ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ የሚለው ጥቅስ ለምን ማስረጃነት ተጠቀሰ?
9. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአይሁድ ተቃውሞ መልስ ሲሰጥ እርሱ የመጣው ምን ለማድረግ ነው አለ?
10. በሰማይ መላእክት ዘንድ ደስታ የሚሆነው መቼ ነው?
11. እውነት ማለት ምን ማለት ነው?
12. ሁልጊዜ እውነቶች ምንች ናቸው?
13. ሁልጊዜ እውነተኛ ማነው?
14. እውነተኛ የሚባል እንዴት ያለ ሰው ነው?
15. ውሸት መናገር ማለት ምን ማለት ነው?
16. ውሸት የማን ሥራ ነው?
17. ውሸትን የማይፈቅድ ማነው?
18. የሐሰት አባት ስለተባለው ማስረጃ አቅርብ።
19. ዮሴፍ የእውነትን መንገድ በመከተሉ ምን ደረሰበት?



www.ethiopianorthodox.org

20. እግዚአብሔርስ ዋጋውን እንደምን ከፈለው?

21. ሦስቱ ወጣቶች የእውነትን መንገድ ስለተከተሉ ምን ደረሰባቸው?

22: ችግራቸውስ ምን ዐይነት መፍትሔ ተገኘለት?

23. ነቢዩ ዳንኤል የእግዚአብሔርን እውነተኛ መንገድ ስለተከተለ ምን ችግር ደረሰበት?

24. እግዚአብሔርስ ምን አደረገለት?

25. የእግዚአብሔርን እውነተኛ መንገድ ትከተል የነበረችው ሶስና ምን ዐይነት ችግር ደርሶባት እግዚአብሔር እንዴት አዳናት?

26. ሐናንያና ሰጺን ለምን በሞት ተቀጡ?

27. የእውነትን መንገድ መከተል ሁልጊዜ ቁሳዊ ወይም ዓለማዊ ዋጋ ያስገኛልን? አብራራ።

28. የአክብሮትንና የትሕትናን ትርጉም ግለጥ።

29. አክብሮትና ትሕትና ምን ጥቅም አላቸው?

30. የጌታችን የኢየሱስስ ክርስቶስን የትሕቷና ምሳሌነት ግለጽ።

www.ethiopianorthodox.org